# እስልምናን ለምን ተውኩት?

# (Why I Reject Islam?)



ጥንታዊ የሆኑ ኢስላማዊ ጽሑፎችን ብቻ መሠረት ተደርጎ የተዘጋጀ
Based upon the earliest & original source of Islamic manuscripts

የቀድሞዋ አሚና መሐመድ (የአሁኗ ወለተ ማርያም)
Former muslim Amina Muhammad (presenetly Welete Mariam)

2013 G.C
LONDON, ENGLAND

ይህ ጽሑፍ የተዘጋጀው ለከፍተኛ ሃይማኖዊ ዓላማ ስለሆነ በመጽሑፉ ውስጥ የተካተቱትን ነጥቦች ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ወስዶ የሌሎችን እምነት ለመንቀፍና ለመተቸት መጠቀም ፈጽሞ የተከለከለ ነው፡፡ ይህ ዓይነቱ አካሄድ ትክክለኛውንና እውነተኛውን ክርስትና አለመረዳት ከመሆኑም በላይ የአስተሳሰብም ችግር መሆኑን የጽሑፉ አዘጋጅ በፅኑ ታምናለች፡፡ ድርጊቱንም በእጅጉ ታወግዛለች፤ ይህም እንዳይሆን የአደራና የተማፅኖ መልእክቷን ታስተላልፋለች፡፡

መጽሐፉ ለምድራዊና ለሥጋዊ ዓላማ መጠቀሚያነት አልተዘጋጀም፡፡ በፍጹም ምድራዊ ዓላማ የለውም፡፡ ይልቁንም ፍጹም ለሆነችው ሰማያዊት መንግስት የተዘጋጀ ስለሆነ መጽሐፉን ማንም ይሁን ማን ለፖለቲካዊ ዓላማ አሊያም ለሌላ ጥሩ ላልሆነ ዓላማ እጠቀማለሁ ቢል እርሱ በቅዱስ ጴጥሮስና በቅዱስ ጳውሎስ ሥልጣን የተወገዘ ይሁን! መድኃኔዓለም ክርስቶስ ዳግም በሚመጣ ጊዜ ይፈር!

## ይህ መጽሐፍ ሊታተም የቻለበት ዋነኛ ምክንያት

ይህ መጽሐፍ የአንድ ሰው ዝግጅት ብቻ አይደለም፡፡ ቀድሞ ሙስሊም የነበሩ የብዙ ሰዎችም እጅ አለበት፡፡ ዋና ዋናዎቹን ሁለቱን ብቻ ልጥቀስላሁ፡፡ ለደኅንነት ሲባል ስም መጥቀስ የሚያስፈልግ አይመስለኝም፡፡ አንደኛው ሶሪያዊ ሲሆን ሌላኛው ግብፃዊ ነው፡፡ ሁለቱም እስልምናውን ማለትም (ቁርአንን፣ ሐዲስን፣ ሙአዚንን፣ ሂድሰን ተፍሲርን…) በዓለም ኢስላም ሀገራት ላይ እየዞሩ ሲያስተምሩ ኖረዋል፡፡ ሶሪያዊው ለ42 ዓመታት፣ ግብፃዊው ደግሞ ለ28 ዓመታት እስልምናውን ሲያስተምሩ ኖረው በመጨረሻ ግብፅ ውስጥ ቅድስት ድንግል ማርያም ባደረገችላቸው እጅግ ድንቅ ተአምር ምክንያት ነው ወደ ክርስትናው የመጡት፡፡ እንዲያውም ሶሪያዊው ሼህ እንደሚናገረው ከሆነ እመቤታችን በሕልሙ እንዳናገረችውና ለተልዕኮም እንደተጠራ መመረጡን ያስረዳል፡፡ በአሁኑ ሰዓት ሁለቱም ትውልድ ሀገራቸውን ትተው አንደኛው በአውስትራሊያ ሌላኛው ደግሞ በአውሮፓ በስደት ይኖራሉ፡፡ ይህ መጽሐፍ የእነዚህና የሌሎችም ሰዎች እጅ አለበት፡፡ ከእስልምናው ጋር በተገናኘ እነዚህ ሁለት ሰዎች በግል የሚልኩልኝን እጅግ አስገራሚና አስደንጋጭ ጽሑፎችን ከአማርኛው ቁርአን ጋር በማመሳከር ለሁለት ዓመታት ያህል መረጃዎችን ስሰበስብ ቆይቻለሁ፡፡ መረጃውን እስካሁን ድረስ ለግል አገልግሎት ካልሆነ በቀር ማለትም በግል ከማገኛቸው ሌሎች ሙስሊሞች ጋር ለመማማሪያነት ከመጠቀም በቀር ወደ ውጭ ለማውጣት ፍቃደኛ አልነበርኩም፡፡ በግል የማገኛቸውና ወደ ክርስትናው የተቀየሩ ብዙ ሙስሊሞች ግን መረጃው መታተምና ለሌላውም ሰው መዳረስ እንዳለበት በተደጋጋሚ አጥብቀው ቢነግሩኝም ይህን አስተያየታቸውን ለመቀበል ዝግጁ አልነበርኩም፡፡ ነገር ግን በቅርቡ ኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ ሙስሊም ወገኖቼ «27 ዓመት መነኩሴ የነበረን ክርስቲያን አሰለምን፣ በዚህም ክርስትና ሐሰት ሆኖ እስልምና እውነት መሆኑ ተረጋገጠ…» በማለት በውጭ በዐረቡ ዓለምና በሀገር ውስጥ ባሉ በተለያዩ ሚዲያዎቻቸው አማካኝነት ያቀረቡትን የተቀናበረ ፕሮግራም ስመለከት ይህን መረጃ የምለቅበት ጊዜው አሁን መሆኑን ተረዳሁ፡፡ «እጅህ ላይ ያለው መረጃ ለብዙ ሰዎች መዳኛ ምክንያት ስለሚሆን በመጽሐፍ መልክ ይታተም» በማለት ለሚጠይቁ ወገኖችም መልስ መስጠት እንዳለብኝ ተሰማኝ፡፡ እውነት ተቀብራ ሐሰት ስትነግስ ስመለከት ውስጤም በእጅጉ ታወከ፡፡ የቤቱ ቅናት አቃጠለኝ፡፡ እግዚአብሔር ሥራውን የሚሠራበት የራሱ የሆነ ቦታና ጊዜ አለው፡፡ ሥራውንም ለመሥራት ምክንያት ይፈልጋል፡፡ ይህ መረጃ እኔ እጅ ላይ ለበርካታ ዓመታት ተቀምጧል፡፡ ዛሬ ግን ሙስሊም ወገኖቼ እያደረጉት ያለውን ነገር ስመለከት መረጃውን ከእጄ ላይ ለማውጣትና ይፋ ለማድረግ ተገደድኩ፡፡ ነገሩ አባቶቻችን «ሳይገባው የመነኮሰ ሰልሞ ይሞታል» እንደሚሉት ተረት ቢሆንም የመነኩሴው ጉዳይ በዝምታና በንቀት የሚታለፍ ጉዳይ አይደለም፡፡ ስለዚህም እኔ ይህን መረጃ ለሕዝብ እንዲደርስ ያደረኩበት ዋነኛ ምክንያት አንድም ይህ «መነኩሴ ነበርኩ» ላለው ወንድሜና ከኋላው ሆነው ድራማውን ሲያቀናብሩት ለነበሩ ሙስሊም ወገኖቼ ሁሉ እንዲሁም ለዓለም ሁሉ እስልምና እምነት ከላይ ከላይ እንደሚወራው ሳይሆን በትክክል ምን እንደሚመስል ቁልጭ አድርጌ ማሳየት ስለፈለኩ ነው፡፡

© አሚና መሐመድ (የአሁኗ ወለተ ማርያም)

ውክልና ካልሰጠች በቀር በየትኛውም ሁኔታ ቢሆን የጸሐፊዋ መብት በሕግ የተጠበቀ ነው፡፡ ነገር ግን ለአገልግሎቱ መስፋትና መፋጠን ሲባል ፍቃድ በመጠየቅና ሕጋዊ ውክልና በመውሰድ ብቻ መጽሐፉን በድጋሚ ወይም ወደ ሌላ ቋንቋ በመተርጎም ማሳተም ይቻላል፡፡

All Rights Reserved

የመጀመሪያ ኅትመት መስከረም 2006 ዓ.ም

የአዘጋጇ አድራሻ፡-

Tel: +447423549663

E-mail: elishaday27@gmail.com

Facebook:

## ምስጋና

1. በድካሜ ውስጥ ኃይሉን ለገለጠ፣ አነሳስቶ ስላስጀመረኝ አስጀምሮም ስላስጨረሰኝ ምስጋና የባሕርይ ገንዘቡ ለሆነ አምላክ ለመድኃኔዓለም ክብርና ምስጋና ይግባው ለዘላለሙ አሜን!

2. በነገሮች ሁሉ ፈተና በገጠመኝ ሰዓት ‹‹እናቴ›› እያልኩ ስጠራት ሁልጊዜ በአማላጅነቷ ፈጥና ለምትደርስልኝ ለአምላኬ እናት ለቅድስት ድንግል ማርያምና ለቅዱሳን ጻድቃን ሰማዕታቱ ሁሉ ምስጋና ይሁን!

3. እግዚአብሔርና እናንተ በምታውቁት መንገድ በመጽሐፉ ዝግጅት ላይ ከፍተኛ እገዛ ላደረጋችሁልኝ ነገር ግን ለደኅንነታችሁ ሲባል ስማችሁን ያልጠቀስኳችሁ ክርስቲያን ወገኖቼ እንዲሁም ቀድሞ በእስልምናው እምነት ውስጥ ለነበራችሁና መረጃዎችን ለሰጣችሁኝ ሁሉ እግዚአብሔር አምላክ የውለታችሁን ዋጋ ይክፈልልኝ፡፡

4. ሁሉ መዳንን ይወርሱ ዘንድ ይህንን መጽሐፍ ቅንና ንጹሕ ልቦና ላላቸው ወገኖች ብቻ በማዳረስ ሐዋርያዊ ተልእኮን ለምትወጡ ሁሉ ምስጋናዬ በቅድሚያ ይድረሳችሁ፡፡

‹‹ለቅኖች ምስጋና ይገባል!›› እንዲል መጽሐፍ፡፡ መዝ 32፡1፡፡

## መታሰቢያነቱ

የዚህ መጽሐፍ መታሰቢያነቱም ሆነ ማስታወሻነቱ ዓለሙንና በዓለሙ ያለውን የሚገዙ ሥጋውያንና ደማውያን ያልሆኑ እርኩሳን ረቂቅ መናፍስት በሰው ልጆች ሁሉ አእምሮ ውስጥ የሚፈጥሩትን እጅግ ከፍተኛ የሆነ የሀሳብ ውጊያ ተቋቁመው በቅንና በንጹሕ ልቦና ሆነው ነገሮችን ከሁሉም አቅጣጫ በመመርመር እውነተኛውን አምላክ የድንግልን ፍሬ መድኃኔዓለም ኢየሱስ ክርስቶስን በአብርሃማዊ ፍለጋ ላገኙትና በእርሱም ታምነው ለኖሩ፣ እየኖሩ ላሉና ወደፊትም ለሚኖሩ ሙስሊም ወገኖቼ ሁሉ ይሁንልኝ!

ይህን መጽሐፍ ሲያነቡት ሙስሊም ከሆኑ ቢቻል ቁርአኑን በእጅዎ ይዘው በመጽሐፉ ውስጥ የምጠቅስልዎትን ምዕራፍና ቁጥር እያረጋገጡ ቢያነቡት በእጅጉ ይመረጣል፡፡ ይህም ባይሆን እንኳ በሁሉም ኢስላማዊ መካነ ድሮች (web sites) ላይ ገብተው የተጠቀሱትን የቁርአንና የሐዲስ ጥቅሶች ከዚያ ላይ ማረጋገጥ እንደሚቻል ሳልጠቁም አላልፍም፡፡

ነገር ግን መጽሐፉን የሚያነቡት ክርስቲያን ከሆኑ አንብበው ይጨርሱትና ቅንና ንጹሕ ልቦና ላላቸው ሌሎች ወገኖች ብቻ እደግመዋለሁ «ቅንና ንጹሕ ልቦና ላላቸው ወገኖች ብቻ» መጽሐፉን በማዳረስ ሐዋርያዊ ተልእኮን በመወጣት የበኩልዎን አስተዋፅኦ በማድረግ ሰማያዊ ክብር የሚያሰጠውን አገልግሎት ይፈጽሙ!

«...ነፍሴንም ስለ በጎች አኖራለሁ፡፡ ከዚህም በረት ያልሆኑ ሌሎች በጎች አሉኝ፤ እነርሱን ደግሞ ላመጣ ይገባኛል፣ ድምፄንም ይሰማሉ፣ አንድም መንጋ ይሆናሉ፣ እረኛውም አንድ፡፡» (ዮሐ 10፡16) «መቶ በጎች ያሉት ከእነርሱም አንዱ ቢጠፋ ዘጠና ዘጠኙን በበረሃ ትቶ የጠፋውን እስኪያገኘው ድረስ ሊፈልገው የማይሄድ ከእናንተ ማን ነው? ባገኘውም ጊዜ ደስ ብሎት በጫንቃው ይሸከመዋል፤ ወደ ቤትም በመጣ ጊዜ ወዳጆቹንና ጐረቤቶቹን በአንድነት ጠርቶ ‹የጠፋውን በጌን አግኝቼዋለሁና ከእኔ ጋር ደስ ይበላችሁ› ይላቸዋል፡፡ እላችኋለሁ፥ እንዲሁ ንስሐ ከማያስፈልጋቸው ከዘጠና ዘጠኝ ጻድቃን ይልቅ ንስሐ በሚገባ በአንድ ኃጢአተኛ በሰማይ ደስታ ይሆናል፡፡» ሉቃ 15፡4-7፡፡

## ማውጫ


1.መግቢያና መግባቢያ......19

2.እስልምናን ለምን ተውኩት? (Why I Reject Islam?)......23

3.የክርስትያኖች መንግስተ ሰማያትና የሙስሊሞች ጀነት......69

4.ዝሙት ከ72 ደናግላን ጋር-በሙስሊሞች ጀነት ውስጥ (72 virgins in Islamic paradise)75

5.የሙስሊሞቹ ነቢይ የመሐመድ ልዩ ችሎታቸው (Muhammad's Sexual Prowess).79

6.የሙስሊሞቹ ነቢይ መሐመድ ኃጢአተኛ መሆናቸውን ቁርአኑ ይናገራል (sins of Muhammad)......83

7.ሰይጣናዊ መገለጦች (Satanic Verses)......99

8.የሙስሊሞቹ ነቢይ መሐመድ መተት ተደርጎባቸው ነበር......115

9.ጂሃድ (jihad-the Way of Islam)

‹‹ባገኛችሁባቸውም ስፍራ ሁሉ ግደሉዋቸው›› (ቁርአን አል-በቀራህ 2፡191)....117

10.የሙስሊሞቹ ነቢይ ‹‹መሐመድ ማለት... እንዲህ...ዓይነት ሰው ነበሩ!››......160

11.በቀጥታ በመሐመድ ትእዛዝና ሙሉ ድጋፍ የተፈጸሙ በርካታ ግድያዎች......170

12.የሙስሊሞቹ ነቢይ መሐመድ ያገቧቸው የ32 ሚስቶቻቸው ዝርዝር ታሪክ......190

13.ባርነት በእስልምና (slavery in Islam)......198

14.ሴቶች በእስልምና (woman in Islam) የሙስሊሞቹ ነቢይ መሐመድ እንዳስተማሩት.236

15.ወሲብና ወሲባዊነት በእስልምና (Sex and sexuality in Islam/......261

ጎረምሳ ወንዶችን ጡት ማጥባት (Adult Suckling/......280

16.ሴቶች በእስልምና-ክፍል ሁለት (woman in Islam part-2 )......293

17.የሙስሊሞቹ ነቢይ መሐመድ ያስተማሯቸው ትምህርቶችና የሕይወት ተሞክሯቸው.....310

18.የዐረቢያ ምድር-ከሙስሊሞቹ ነቢይ ከመሐመድ መወለድ በፊት......328

19.አብደላህ ኢብን ሳድ ኢብን አቢ ሳርህ (ቁርአንን የጻፈው የመሐመድ የግል ጸሐፊ)......345

20.በቁርአን ላይ የደረሱ ብክለቶችና እንዳይታመን ያደረጉት ነገሮች (Corruption of the Qur'an)......355

21.በድንጋይ ወግሮ መግደልና የክብር ግድያ (honor killing & Stoning)......399

22.እናወዳድር እንዴ!?......413

23.በእስልምናውም አላህ ወደፊት የሰውን ሥጋ ለብሶ ይገለጣል (ሐዲሱ በሰፊው ዘግቦታል).423

## የንዑስ ርዕሶች ማውጫ


የሙስሊሞቹ ነቢይ መሐመድ የሠሯቸው ኃጢአቶች.............................................83

ቁርአን 40፡55 ላይ "ለስሕተትህም ምሕረትን ለምን" ተብሎ ተነግሯቸዋል..........83

የሙስሊሞቹ ነቢይ መሐመድ የሠሯቸውን ኃጢአቶች አላህ ይቅር አላቸው........83

የሙስሊሞቹ ነቢይ መሐመድ የሠሯቸው ኃጢአቶች ምን ነበሩ?...........................83

ያሳደጉትን ልጅ የዛይድን ሚስት ማግባታቸው..................................................83

የጦር ወረራ አድርገው ሳፊያ የተባለቸውን ሴት ባሏን፣ አባቷንና ወንድሟን በሰይፍ እንዲሰየፉ ካደረጉ በኋላ የዚያኑ ዕለት ከእርሷ ጋር ተኝተው ማደራቸው..............85

በ53 ዓመታቸው ከ9 ዓመት ሕጻን ልጅ ጋር ወሲብ መፈፀማቸው (A'isha)...87

ትምህርታቸውን አንቀበልም እያሉ ይቃወሟቸው የነበሩትን ግለሰቦች በጨለማ ተከታዮቻቸውን እየላኩ በሰይፍ አስገድለዋል............................................89

900 በሚሆኑ የባኑ ቁራይዛ ጎሳዎች ላይ ጅምላ ጭፍጨፋ አካሂደዋል...........93

ጂሃድ (jihad- the Way of Islam)

"ባገኛችሁባቸው ስፍራ ሁሉ ግደሉዋቸው"(ቁርአን 2፡191)................................117

የጂሃድ የመጨረሻ ዓላማና ተግባሩ ምንድን ነው? /the ultimate goal & purpose of jihad/ ..........................................................................................129

የዘመኑ ሙስሊም መምህራኖቻቸውስ ስለ ጂሃድ ምን ይላሉ? (What did the modern Muslim scholars say about jihad?)....................................................................132

በቁርአን ውስጥ የሚገኙ 164 የጂሃድ ጥቅሶች (The Koran's 164 Jihad Verses)...142

የሙስሊሞቹ ነቢይ መሐመድ እንዚህን ቀጥሎ የተጠቀሱትን ነገሮች ያደርጉ ነበር.160

ባደረባቸው መንፈስ ምክንያት ራሳቸውን ሊያጠፉ ይሞክሩ ነበር...160

በሴት ቀሚስ ውስጥ እያሉ መገለጦች ይመጡላቸው ነበር................161

መጠጥ ይጠጡ ነበር /Drinker/.............................................................162

ይዋሹ ነበር /Liar/.......................................................................................163

ሰዎች ስብከታቸውን "ቀድሞ የምናውቃቸው የዱሮ ተረቶች ናቸው" ይሏቸው ነበር.163

ጉቦ (ሙስና) ይሰጡ ነበር /Briber/........................................................164

ያታልሉ ነበር /Deceiver/...........................................................................164

የሰዎችን አካል በመቆራረጥ ያሰቃዩ ነበር /Torturer/.........................165

ጅምላ ጭፍጨፋ ያካሄዱ ነበር /Mass Murderer/.............................168

በጦርነት ይቀሙና ይዘርፍ ነበር /Plunderer/......................................169
ጦርነት ባይኖርባቸውም እንኳ በግል ጉዳያቸው ሰዎችን ይገድሉ ነበር /Suicidal/...170
የሙስሊሞቹ ነቢይ መሐመድ ያስገደሏቸው የ64 ሰዎች ስም ዝርዝርና ታሪካቸው...172
የሙስሊሞቹ ነቢይ መሐመድ አሸባሪ ነበሩ /Terrorist/..................................178
የሙስሊሞቹ ነቢይ መሐመድ የፈጸሟቸው 94 የሽብር ጥቃቶች ዝርዝር ታሪክ.......179
የሙስሊሞቹ ነቢይ መሐመድ የሞቱት በመርዝ ነበር /Death/........................184
የሙስሊሞቹ ነቢይ መሐመድ በጣም ብዙ ሚስቶች ነበሯቸው /Polygamist/.187
መሐመድ ያገቧቸው የ32 ሚስቶቻቸው ታሪክ..................................................190

የሙስሊሞቹ ነቢይ መሐመድ በመልካቸው ነጭ ነበሩ /White Man/...................198
የሙስሊሞቹ ነቢይ መሐመድ ዘረኛ ነበሩ /Racist/....................................................199
ዐረቦች ከሁሉም የሰው ዘር የበላይ መሆናቸውን አስተምረዋል.......................199
በጥቁሮች ላይ ከፍተኛ ጥላቻ ነበራቸው..............................................................199
የባሪያ ንግድ ያካሂዱ ነበር /Slaver/....................................................................200
ሸጠው የለወጧቸው ባሪያዎች /Slaves Traded by Muhammad/.............201
እስልምና ባርነትን ይፈቅዳል..................................................................................202
የሙስሊሞቹ ነቢይ መሐመድ በግል ለራሳቸው ይገዟቸው የነበሩ ባሪያዎች/Slaves Owned by Muhammad/....................................................................204
የመሐመድ ሚስቶቻቸውም የሚገዟቸው ባሪያዎች ነበሯቸው..................205
መሐመድ ባሎቻቸውን በመግደል ሴቶችን በጦር እየማረኩ ለባርነት ይዳርጓቸው ነበር.206
የሙስሊሞቹ ነቢይ መሐመድ ከባሪያዎችና ከጦር ምርኮኛ ሴቶች ጋር ግብረ ሥጋ ግንኙነት መፈጸምን ፈቅደዋል /sex with slaves and captives/......207
እስልምና የጦር ምርኮኞችንና ባሪያዎችን አስገድዶ መድፈርን ይፈቅዳል /Islam Permits Raping Captives and Slaves/.............................................209
እስልምናና ባርነት ከትናንት እስከ ዛሬ.................................................................209
እስልምናና ባርነት አሐዛዊ መረጃዎች.................................................................210
የሸሪዓው ሕግ ስለ ባርነት ምን ይላል? ...........................................................212
ሙስሊም ምሁራኖችስ ስለ ባርነት ምን ይላሉ?................................................212

የሙስሊሞቹ ነቢይ መሐመድ በጦርነት ዘርፈው በሚያገኙት ንብረት በጣም ሀብታም ሆነው ነበር /Wealthy/.....215
የሙስሊሞቹ ነቢይ መሐመድ ሴቶችን አስገድደው ይደፍሩ ነበር /Rapist/.......216
የሙስሊሞቹ ነቢይ መሐመድ ግብዝና ተመጻዳቂ ሰው ነበሩ /Hypocrite/........217
ልዩ ጥቅም ያላቸውና ሁሉም ነገር የተሟላላቸው ሰው ነበሩ /Privileged/.........218
የሙስሊሞቹ ነቢይ መሐመድ የዝሙት ሱሰኛ ነበሩ /Sex Addicted/..................220
የሙስሊሞቹ ነቢይ መሐመድ ከሕጻናት ጋር ወሲብ መፈጸምን ይወዱ ነበር (Pedophile-sexually attracted to children/.....221
በሕጻናት ልጆች ላይ ተገቢ ያልሆነ ቅጣት እንዲፈጸምባቸው ትእዛዝ ይሰጡ ነበር/Child Abuser/..225
የሙስሊሞቹ ነቢይ ሕጻናት ልጆችን ይገድሉ ነበር /Child Killer/................226
የሙስሊሞቹ ነቢይ መሐመድ ራሳቸውን ያስመልኩ ነበር /Megalomaniac/...227
የግል ንጽሕናና ጽዳት የላቸውም ነበር /unclean/.....229
በመሐመድ የራስ ፀጉራቸው ውስጥ ያለውን ቅማል ሚስታቸው ትቀምልላቸው ነበር/ Lice on Mohammed's head/.....229
መሐመድም ሆኑ ተከታዮቻቸው መጥፎ የሰውነት ጠረን ነበራቸው /Bad bodily odor/.229
መሐመድ እጅግ አስገራሚ የምግብ ጤና አጠባበቅ አስተምህሮ ነበሯቸው...............230
የሙስሊሞቹ ነቢይ መሐመድ ደርቆ የተጣበቀ የዘር ፈሳሽ በልብሳቸው ላይ ይታይ ነበር /Semen on Mohammed's closes/.....231
ውኃ ከጠፋ በአሸዋ ታጥባችሁ ስገዱ /Ablution with Dirt/......................232
የሙስሊሞቹ ነቢይ መሐመድ ራስ ወዳድና ስስታም ሰው ነበሩ...................232
ከሰላም ይልቅ ጦርነትን የሚወዱና ጥላቻን የሚሰብኩ ሰው ነበሩ /Warmonger & hate preacher/.....233

ሴቶች በእስልምና- (የሙስሊሞቹ ነቢይ መሐመድ እንዳስተማሩት)......236
ሴቶች ከወንዶች ያነሱ ናቸው /Inferior to Men/.....236
ሴቶች ከወንዶች በግማሽ ያነሱ ናቸው /Worth Half a Man/..............236
በአእምሮ ጎዶሎዎች ናቸው /Deficient in Intelligence/.......................238
ብዙዎቹ የሲኦል ነዋሪዎች ሴቶች ናቸው /the majority of hell is occupied by women/.....239
ሴቶች የዝሙት ባሪያዎች ናቸው /Sex Slaves/.....242

ዕድሜያቸው ገፋ ያሉ ሴቶች ከትዳራቸው እየተፈናቀሉ በኮረዳዎች መተካት አለባቸው.243
ውሻ፣ አህያና ሴቶች ጸሎትን አስተጓጓዮች ናቸው........................................243
ሴቶች ሰይጣንን ይመስላሉ /like Devils/......................................................244
ሴቶች በባሕርያቸው ደካሞች ናቸው /weak/...............................................245
ሴቶች ለወንዶች የሚታረሱ እሻዎች ናቸው /Tilth for Men to Cultivate/...245
ሴቶች አሻንጉሊቶች ናቸው /Toys/................................................................246
ሴቶች በወርሃዊ ልማዳቸው ወቅት በካዮችና ጎጂዎች ናቸው...................246
ሴቶች ለወንዶች ጠላቶች ናቸው......................................................................247
ሴቶች መሸፋፈን አለባቸው..............................................................................247
የሚስቶች ቁጥር ...............................................................................................247
ቅምጥ የሆኑ ሴቶች...........................................................................................248
ሴቶች እንደ ጎድን አጥንት የጎበጡ (የተጣመሙ) ናቸው /Crooked Like Ribs/...249
የሰይጣናዊ ወይም የክፉ ነገር ወይም የመቅሰፍት ወይም የኃጢአት ምልክት ናት/ Evil Omen/.................................................................................................249
ሴቶች ከዳተኞች ናቸው /Betrayers/...............................................................249
ሴቶች ለወንዶች ጎጂዎች ናቸው /Detrimental to Men/............................249
ሴቶች ለወንዶች ታዛዦች ካልሆኑ መደብደብ አለባቸው..............................250
ወንዱ ሙስሊም ሚስቱን ለምን እንደሚመታት መጠየቅ የለበትም............250
የባሎቻቸውን ፍላጎቶች በቅፅበት ማሟላት አለባቸው /The Husband's Desires Must be immediately Met/...................................................................252
ሙስሊም ወንዶች ሴቶች ባሪያዎቻቸውን አስገድደው መድፈር ይችላሉ /Men have a Right to Rape their Female Slaves, even in front of their Husbands/....253
ሙስሊም ሴቶች ሂጃብ (veil) እንዲለብሱ የተደረገበት እውነተኛ ምክንያት /The Real Reason Why Women Have to Wear the Hijab/............256

## ወሲብና ወሲባዊነት በእስልምና /Sex and sexuality in Islam/

በገንዘብ ክፍያ የሚፈጸም ወሲብ..........................................................................261
ለአንድ ቀን ብቻ በስምምነት የሚፈጸም ወሲብ /one-night stand/...............262
በፍቅር ጨዋታ ለመደሰት ድንግል የሆነች ልጃገረድ ተመራጭ ናት /virgin girl is preferable for fun and frolic/..........................................................................263
ጤናማ ያልሆነ የወሲብ ፍላጎት/Sexual perversion/........................................265

ሙሉ ያልሆነ የወሲብ እርካታ /incomplete sexual pleasure/......................267
የሴቷን ሰውነት ለመደሰቻነት መጠቀም /Enjoyment of a female's body/..268
ፈቃደኛ ባትሆንም እንኳ ባልየው ሚስቱን አስገድዶ ወሲብ ሊፈጽምባት ይችላል /One can enjoy a wife by force/.....................................................................................270
ካረገዙች ሴት ጋር ወሲብ መፈጸም /Sex with pregnant women/...................270
በውርሃዊ ልማድ ወቅት ወሲብ መፈጸም /sex with menstruating women/..271
በጾም ወቅት መሳሳምና መጥባት /Kissing and sucking during fasting/.........272
የዘር ፈሳሽን ወደ ውጭ እንዲፈስ ማድረግ /Coitus interruption (or spilling ones seed!)/...274
ከሴቷ ሰውነት የሚወጣው የዘር ፈሳሽ መልኩ ቢጫ ነው! /Women's semen is yellow?/..277
ባልተገባ ቦታ ወሲብ መፈጸም /Backside or anal sex/.....................................277
ጎረምሳ ወንዶችን ጡት ማጥባት /Adult Suckling/...........................................280
ሚስት ባሏ ሌላ ሴት ጋር ሄዶ እንዳይወሰልትና እንዳይማግጥ ከፈለገች የእርሱን ውሽማ (ቅምጥ) ጡቷን ማጥባት አለባት............................282
ከጦር ምርኮኞችና በባርነት ከተያዙ ሴቶች ጋር ወሲብ መፈጸም /Sex with war captives & slave girls/...................................................283
አንድ ወንድ ሙስሊም በባርነት በያዛቸው ሁለት እኅትማማቶች ላይ በየተራ ወሲብ መፈጸም ይችላል........................................................285
ሙስሊም ወንዶች በባርነት የያዙዋቸውን ሴቶች ሀፍረተ ሥጋ በዓይናቸው መመልከት ይችላሉ...285
በባርነት የተያዙ ባሪያ ሴቶችን ለወሲብ ተግባር መዋዋስ ይቻላል..........................285
ብልትን በመነካካት በራስ ላይ ዝሙት መፈጸም Masturbation-Adultery with one's own hands!.....................................................287
በአፍ በኩል የሚደረግ ወሲብ /oral sex/................289

## ሴቶች በእስልምና-ክፍል ሁለት

የሙስሊሞቹ ነቢይ መሐመድ ሚስታቸውን ይደበድቡ ነበር /Wife Beater/...293
በቁርአኑም ሆነ በሐዲሱ ሕግ መሠረት ሙስሊም ወንዶች ሴቶችን መደብደብ ይችላሉ /Qur'an allows Wife Beating/............................................................293
መሐመድ ለተከታዮቻቸው ሚስቶቻቸውን እንዲመቷቸው ፈቅደውላቸዋል..294
ባሎቻችን ደበደቡን ብለው ቅሬታ ያቀረቡትን ሴቶች «ጥሩ ሴቶች አይደሉም» ብለዋቸዋል.295
የሙስሊሞቹ ነቢይ መሐመድ ለእነ አቡ በከርና ኡማር ሴቶችን እንዲመቱ ስላዘዟቸው እነርሱም ለሌሎች ወንዶች ይህንኑ ትእዛዝ አስተላልፈዋል...........................297

የዘመኑ ሙስሊም ምሁራኖችም ወንዱ ሚስቱን መምታት እንዳለበት ይስማማሉ/ modern Muslim Scholars Agree with Wife beating/........................297
አሃዛዊ መረጃዎች /Statistics on Domestic Violence in the Muslim world/...300
መጥፎ ሥራ ሠርታለች ተብላ የተወነጀለችን ሴት በረሀብ መግደል /Kill Woman Guilty of Lewdness by Starvation/............................................................304
የሙስሊሞቹ ነቢይ መሐመድ የጦር ወረራ ሲያደርጉ ሴቶችና ሕጻናትም አብረው እንዲገደሉ ትእዛዝ ሰጥተዋል............................................................................304
ሴቶች ተገደው እንደደፈሩ እስልምና ይፈቅዳል /Raping of Women is allowed in Islam/...305
የሴት ልጅ ግርዛት በእስልምና የተፈቀደ ነው፣ ነቢያቸው መሐመድም አዘዋል /Female Circumcision is allowed & Prescribed/....................................................306
የዘመኑ ሙስሊም ምሁራኖችም ሴት ልጅ መገረዝ እንዳለባት ይስማማሉ /modern Muslim Scholars Agree with Circumcision/......................................................307

የሙስሊሞቹ ነቢይ መሐመድ ያስተማሯቸው ትምህርቶችና የሕይወት ተሞክሯቸው
የስነ ባሕርይ /Genetics/ ትምህርታቸው.......................................................310
መልአኩ ጂብሪል ለመሐመድ “ሚስትህን ሰላም በልልኝ” አላቸው...........310
በግብረ ሥጋ ግንኙነት ወቅት ባልና ሚስት የሚጸልዩት ጸሎት .................311
በጨረፍታ ሰረቅ አድርጎ ወይም በማጮለቅ የሚያይዎትን ሰው በእንጨት ዓይኑን ቢያወጡት ተጠያቂ አይደሉም.....................................311
ዘካ ያልተከፈለበት ገንዘብ በዕለተ ምፅአት ቀን ገንዘቡ ራሱ ወደ መርዛማ እባብነት ይለወጥና ባለቤቱን ይውጠዋል.....................................312
በአላህ መንገድ ተዋግቶ በጂሃድ ለተሳተፈ ጦረኛ አላህ ለፈረሱ ያወጣውን ወጪ በዕለተ ምፅዓት ይከፍለዋል........................................................312
መላኢኮች (መላእክት) አርብ አርብ መስጊድ ያልመጣውን ሰው በቀሪ ይመዘግባሉ..313
እስራኤላውያን ወደ አይጥነት ተለውጠዋል .....................................................................313
ኃጢአት ያደረጉ ሰዎች ወደ ዝንጀሮነትና አሳማነት ይለወጣሉ........................................313
የአይሁድና የክርስቲያኖች ተቃራኒ ለመሆን ከፈለጋችሁ ፂማችሁን ቀለም ተቀቡ...314
የአየር ንብረትን በተመለከተ የመሐመድ አስተምህሮ.....................................................315
የግመል ሽንት መድኃኒት ነው.............................................................................................315
ዝንብን እንደ መድኃኒት መጠቀም......................................................................................315
የሰይጣን መኝታ ቤት............................................................................................................316
ሰይጣን በሚያፋሽጉ ሰዎች ላይ ይስቅባቸዋል.................................................................316

ሰይጣን በሰው ጆሮ ውስጥ ሽንቱን ሸንቶ አደረ....317
ሰይጣን የሙስሊሞችን ጸሎት ለማስታጎል ሲል ፈሱን ይፈሳባቸዋል....317
ማንኛውም ሕጻን ገና ሲወለድ ሰይጣን ይዋሐደዋል....317
ሰይጣን የሚመገባቸው ምግቦች....318
ሰይጣን በሦስት የተለያዩ ምሽቶች በሰው አምሳል እየተገለጠ የሰዎችን ምግብ ሰርቋል....319
ሰይጣን መሐመድን ከጸሎት ሊያቋርጣቸው መከረ....319
የእምነትን ሕግ በጣሱ ሰዎች ላይ በዕለተ ምፅዓት ቀን በጀርባቸው በኩል ባንዲራ ይታሰርባቸዋል....319
ሰይጣን ማታ ማታ በእያንዳንዱ ሰው ጀርባ ላይ ሦስት የድግምት ቋጠሮዎችን አስሮ ያድራል....319
ሙሴ ከሰይጣን (ከመልአከ ሞት) ጋር ቦክስ ገጠመ....319
መሐመድና ሰይጣን ተደባድበው እሳቸው አሸነፉ....320
ሰይጣኖች በማታ ቁርአንን እንደሰሙ ዛፏ ነገረቻቸው....320
ሰይጣን በሕልም የሙስሊሞቹን ነቢይ መሐመድን ተመስሎ ሊታይ አይችልም....320
መሐመድ ሕጋዊ ያልሆነ ወሲብ የፈጸመችን ዝንጀሮ በድንጋይ ወግረው ገደሉ....320
ሴት፣ ፈረስና ቤት መጥፎ ገዶች (ምልክቶች) ናቸው....320
ዝንጀሮ፣ ጥቁር ውሻ፣ አህያና ሴት ጸሎትን ዋጋ ቢስ ያደርጋሉ....321
የሙስሊሞቹ ነቢይ መሐመድ በአይሁዳዊ ሰው መተት ተደርጎባቸው ነበር....321
ግርፋትና በድንጋይ ወግሮ መግደል....321
ሰይጣን መሬትን ተሸክሟታል....321
ጨረቃ ለሁለት ተሰንጥቃለች....321
የሙስሊሞቹ ነቢይ መሐመድና መጠጥ....321
የሙስሊሞቹ ነቢይ መሐመድ ስለ ራሳቸው የሰጡት ግምት....322
መንገድ ላይ ያገኛችሁትን ሰው ገፍትራችሁ እለፉ....322
በረመዳን ወር ሰይጣን ጡረታ ይወጣል....322
ከሞተ ውሻ ጋር የተቀለቀለ ውኃ ንጹሕ ነው....322
የበሽታዎች ሁሉ መነሻ ....322
ሙስሊሞች መስመራቸውን ጠብቀው ካልሰገዱ አላህ ፊታቸውን ያጣምማቸዋል....323
ሙስሊሞች ወደፊት አላህን ባዶ እግሩን ሆኖ፣ እርቃኑን በእግሮቹ እየሄደ ያዩታል....323
ከብር በተሠራ ዕቃ መጠጣት ለገሀነም እሳት ይዳርጋል....323
የሙሴን ልብስ ይዛ የሮጠችው ድንጋይ....324

የመሐመድ ምግብ አላህን አመሰገነች..........324
በመካ ያሉ ድንጋዮች ለመሐመድ ሰላምታ ይሰጡ ነበር..........324
ውዱ፣ ጸሎትና ፈስ..........324
በጀነት ውስጥ መቶ ዓመት ጋልበው የማያቋርጡት የዛፍ ጥላ አለ..........324
ጠቢቡ ሰሎሞን በአላህ መንገድ የሚዋጋ ወታደር ለመውለድ ሲል በአንድ ሌሊት ከመቶ ሴቶች ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት አደረገ..........325
የአውራ ዶሮና የአህያ ጩኸት..........325
ላምና ተኩላ እረኛን በአንበታቸው አናገሩት..........325
ሰዎች ልክ እንደ ግመሎች ናቸው..........325
ውኃ ቆሞ መጠጣት ፈጽሞ የተከለከለ ነው..........325
ሙስሊሞች በሚሰግዱና በሚጸልዩ ጊዜ ዓይኖቻቸውን ወደ ሰማይ የሚያነሱ ከሆነ ከባድ ቅጣት አለባቸው..........326
መሐመድ እጅግ አድርገው የሚያፈቅሯቸው 3 ነገሮች ..........326
መሐመድን አሸናፊና ድል አድራጊ አይደሉም ብለው ካሰቡ ራስዎን ይስቀሉ........327
መልአኩ ጂብሪል ለመሐመድ “አላህን ያመነነና አንተን የተከተለ ዝሙተኛም ይሁን ቀማኛ ሌባ እርሱ ጀነት ይገባል” ብሎ ነገራቸው..........327

የዐረቢያ ምድር-ከሙስሊሞቹ ነቢይ ከመሐመድ መወለድ በፊት.........243
የመሐመድ የልጅነት ሕይወታቸው እጅግ አሰቃቂ ነበር..........244
የሙስሊሞቹ ነቢይ መሐመድ ያደጉት የፓጋን ዐረቦችን ሃይማኖታዊና ባህላዊ ሥርዓታቸውን እየፈጸሙ ነበር..........250
የሙስሊሞቹ ነቢይ መሐመድ አምላካቸውን ፈጠሩ..........251
አላህ-የሚለው የቃሉ ትርጉም..........255
በቁርአን ላይ የደረሱ ብክለቶችና እንዳይታመን ያደረጉት ነገሮች (Corruption of the Qur'an)...267
ቁርአን በመሐመድ በግል ጸሐፊያው በኩል የተጻፈ ስለሆነና ጸሐፊያውም የራሱን ሀሳብ ስለጨመረበት ሊታመን አይችልም.......... 268
ቁርአኑ በየጊዜው ተለዋዋጭ እንደሆነ ራሱ ቁርአኑ ይናገራል..........268
የቁርአኑ የተለያዩ አንቀጾች ተሰብስበው በአንድ የተጠቃለሉበት መንገድ አስቸጋሪነት ነበር (Difficulty in Collecting the Qur'anic Verses)..270
ቁርአኑ በብዙ የቋንቋ ሰዋሰዋዊ ስሕተቶች /grammatical errors/ የተሞላ ስለሆነ ሊታመን አይችልም..........271

ቁርአኑ ሊታመን ያልቻለበት ሌላው ምክንያት በውስጡ ያሉት ታሪኮች ከሌሎች እምነቶች የተኮረጁ በመሆናቸው ነው.......................................................274
ቁርአኑ ታማኝ ካልሆነባቸው ምክንያቶች ውስጥ አንዱ መጽሐፍ ቅዱስን አረጋግጣለሁ ማለቱ ነው..........................................................................280
ቁርአኑ ለመሐመድ ሰይጣናዊ በሆነ መንገድ የተገለጠ በመሆኑ ታማኝ አይደለም..284
ቁርአኑ አጠቃላይ ይዘቱ እጅግ አሰልቺ በመሆኑ ታማኝ አይደለም.................284
ቁርአን የጀመረውን ሀሳብም ሆነ ታሪክ የማይጨርስ ስለሆነ ሊታመን አይችልም...284
ቁርአኑ ከሰማይ የወረደ ሳይሆን የራሱ የሆኑ የተለያዩ ምንጮችና ጸሐፊዎች ስላሉት ሊታመን አይችልም..........................................................286

በቁርአን ዝግጅትና ጽሕፈት ላይ ቀጥተኛ አስተዋፅኦ የነበራቸው ግለሰቦች
1.ኢምሩል ቃይስ.......................................................................................287
2.ዛይድ ቢን አምር ቢን ነውፋል...........................................................288
3.ላቢድ....................................................................................................289
4.ሀሰን ቢን ጣቢት....................................................................................290
5.ፐርሺያዊው ሰልማን............................................................................291
6.መነኩሴው ባሂራ..................................................................................292
7.ኢብን ቁምታ.........................................................................................293
8.ጃብር......................................................................................................294
9.ሳቢያኖች...............................................................................................294
10.ከድጃ፣ ዋራቃና ኡቤይዱላህ.............................................................295
11.አብዱላህ ቢን ሰላምና ሙካያሪቅ......................................................296
12.አን-ናድር ቢን አል-ሀሪዝ..................................................................296
13.ኡቤይ ቢን ካብ.....................................................................................297
14.አይሻ......................................................................................................297
15.ዓይነ ስውሩ ኢብን ኡም ማክቱም.....................................................299
16.ራሳቸው መሐመድ በፈጠራ ያዘጋጁዋቸው ጥቅሶች....................299
ቁርአን ከዐረብኛ ውጭ የሆኑና ከሌሎች ቋንቋዎች የወረሳቸው ባዕድ ቃላትን ስለሚጠቀም ታማኝ ሊሆን አይችልም..............................................394
የመሐመድ አስተምህሮታቸውና የሕይወት ተሞክሮአቸው በጣም ብዙ አስከፊ ገጽታዎች ያሉት በመሆኑ ቁርአኑ ሊታመን አይችልም......................302

ከቁርአኑ ውስጥ የተሰረዙና እንዲጠፉ የተደረጉ ብዙ ጥቅሶች /Cancelled Verses & Lost Verses/ መኖራቸው ቁርአኑን እንዳይታመን አድርጎታል......303
ፍየል በልታው የጠፋው ቁርአን......399
በድንጋይ ወግሮ መግደልና የክብር ግድያ /honor killing & Stoning/...305
ቁርአን ወደፊት ስለሚሆነው የዓለም ክስተት ምንም ነገር አለማወቁ እንዳይታመን አድርጎታል......314

*በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን!*

## *መግቢያና መግባቢያ*

በአጠቃላይ በእስልምና እምነት ታሪክ ውስጥ ሱኒና ሺዓ የተባሉ ሁለት ዋና ዋና ክፍሎች ይገኛሉ፡፡ ሱኒዎች በዓለም ላይ ካለው የእስልምና እምነት ውስጥ እስከ 90% የሚሆነውን ድርሻ ይይዛሉ፡፡ የተቀሩት ደግሞ ሺዓዎች ናቸው፡፡ በጋራ ሁለቱም ክፍሎች የሚስማሙበትና የሚያምኑበት ነገር አላቸው፡፡ ይህም ሁሉም ሙስሊሞች የሚመሩባቸው የአላህን ‹‹ፍጹም መለኮታዊ ቃል›› የያዙ ሁለት መጽሐፎች አሏቸው- ቁርአንና ሐዲስ፡፡ ቁርአንና ሐዲስ የእምነቶቹ ምንጮችና ዋነኛ መመሪያዎች ናቸው፡፡ የሸሪዓውም ሕግ ከሁለቱ ተውጣቶ ነው የተዘጋጀው፡፡ ቁርአኑና ሐዲሱ በአተገባበርና በአፈፃፀም ደረጃ አንድ ናቸው፡፡ ልዩነታቸው የአመጣጣቸው ጉዳይ ብቻ ነው፡፡ እንደ እስልምናው እምነት ቁርአኑ ለሰው ልጆች ሁሉ መመሪያ ይሆን ዘንድ በቀጥታ ከአላህ በመልአኩ በጂብሪል (በገብርኤል) በኩል ለነቢያቸው ለመሐመድ የተሰጠ መገለጥ ሲሆን ሐዲሱ ደግሞ አላህ በሙስሊሞቹ ነቢይ በመሐመድ የዕለት ተዕለት ሕይወት ውስጥ በመገለጥ ለአማኞቹ መልእክቱን ያስተላለፈበት መንገድ ነው፡፡ ቀርአኑ የሙስሊሞቹን ነቢይ የመሐመድን ቀጥተኛ የሆኑ መለኮታዊ መገለጦችን (revelations) የያዘ ሲሆን ሐዲሱ ደግሞ ነቢያቸው መሐመድ የተናገሯቸውን ንግግሮች፣ ያደረጓቸውን ድርጊቶች፣ ያዘዟቸውን ትእዛዞች፣ የመከሯቸውን ምክሮች…በአጠቃላይ ከነቢያቸው ከመሐመድ ሕይወት ጋር የጠቆራኙ ባሕሎችን (traditions) እና አባባሎችን (sayings) ያካትታል፡፡ አላህ ቁርአኑን ለሙስሊሞቹ ነቢይ ለመሐመድ በማውረድ ለአማኞቹ መመሪያ አድርጎ ሲሰጥ ሐዲሱን በተመለከተ ግን መመሪያዎቹን በነቢያቸው በመሐመድ ሕይወት ውስጥ እንዲገለጡ አድርጓል ተብሎ በአማኞቹ ዘንድ በጽኑ ይታመናል፡፡ "I have left you two things and you will not stray as long as you hold them fast. The one is the Book of Allah and the other the Law (Sunnah) of his Prophet." (Mishkat 1:120, Volume 1, page 173).

የሙስሊሞቹ ነቢይ መሐመድ ያደረጓት ወይም የተናገሯት እያንዳንዷ ነገር አላህ በነቢያቸው በመሐመድ የዕለት ተዕለት ሕይወት ውስጥ ለሙስሊሞች ያስተላለፋት መለኮታዊ ሕግ እንደሆነች በጽኑ ይታመናል፡፡ ይህቺ አንዷ ድርጊት ወይም ንግግር ሱና ትባላለች፡፡ የሱናዎቹ ስብስብ ሐዲሱን ፈጥሯል፡፡ የነቢያቸው የመሐመድ ሕይወቱ በአጠቃላይ አላህ የተናገራቸውን ነገሮች በሙሉ በተግባር ያሳየ ተብሎ ይታመናል፡፡

ሐዲስ ማለት በአጭሩ አላህ ቁርአኑን በተግባር ያሳየበትና ያረጋገጠበት መንገድ ማለት ነው፡፡ ሙስሊም ምሁራኖቻቸውም (Muslim scholars) ይህንን የሚገልጹበት መንገድ ተመሳሳይ ነው፣ (The hadith is the Qur'an in action. Muhammad's life is a visible expression of Allah's utterances in the Qur'an) በማለት ይገልጹታል፡፡ በመሆኑም ቁርአኑም ሆነ ሐዲሱ በመመሪያና በአተገባበር ደረጃ የሚሰጣቸው ቦታ እኩል ነው፡፡ እንዳውም በተሻለ ቋንቋ እንግለጸው ከተባለ ቁርአኑን ያለ ሐዲሱ መረዳት ፈጽሞ አይቻልም፡፡

"Indeed the Quran without the Hadis remains unintelligible in many cases in the work-a-day life of a man. It is the very injunction of the Quran to follow the Prophet in all his deeds and sayings. Therefore if the Quran is believed, there is no other alternative but to believe in the Hadis of the Prophet.

በአማኞቹ ዘንድ ሐዲሱን እንደ ቁርአኑ አድርጎ የማይቀበል ሰው ልክ እንደማያምን ከሐዲ ነው የሚቆጠረው፡፡ በአረብኛው "ካፊር" *(kafeer)* ይሉታል፡፡ ስለዚህ ማንኛውም ሙስሊም በየትኛውም ቦታ ቢሆን ነቢያቸው መሐመድ ያደረጓትንና የተናገሯትን ሁሉ የማድረግና የመጠበቅ ግዴታ አለበት፡፡ መስጊድ ውስጥም ይሁን ሥራ ቦታ፣ ጦር ሜዳም ይሁን ሽንት ቤት...ብቻ የትም ይሁን የት ነቢያቸው መሐመድ ያደረጉትን ነገር የማድረግና ያዘዙትን ትእዛዝ የመጠበቅ ግዴታ አለበት፡፡

ቁርአኑም ይህንኑ ሲያረጋግጥ *"መልእክተኛው የሰጣችሁን ማንኛውንም ነገር ያዙት፡፡ እርሱም የከለከላችሁን ነገር ተከልከሉ፡፡ አላህንም ፍሩ፤ አላህ ቅጣተ ብርቱ ነውና"* ነው ያለው፡፡ ሱረቱ አል-ሐሽር 59፡7፡፡ በሌላም ቦታ እንዲሁ በተመሳሳይ ሁኔታ ተገልጧል፡፡ *"አላህና መልእክተኛውም ነገርን በፈረዱ ጊዜ ለምእመናንና ለምእመናት ከነገራቸው ለእነርሱ ምርጫ ሊኖራቸው አይገባም"* ሱረቱ አል-አሕዛብ 33፡36፡፡

ነቢያቸው መሐመድም ራሳቸው ሲናገሩ "እኔን የሚታዘዝ ጀነት ይገባል..." ነው ያሉት፡፡ "Whoever obeys me shall enter Paradise and whoever disobeys me, has indeed rejected truth." (Mishkat 1:97, page 159). በእነዚህ ምክንያት ነው አንድ ሙስሊም ነቢያቸው መሐመድ ያደረጉትን ማንኛውንም ነገር የማድረግና ያዘዙውን ትእዛዝ የመፈጸም ግዴታ ያለበት፡፡ ለዚህ ታማኝ የሆኑ አማኞችን ታዲያ ለየት ያለ ድርጊት ሲያደርጉ አይታችሁ "ምነው?" ብትሏቸው "ሱና" ነው ይሏችኋል፡፡ ሱና ማለት የነቢያቸው አንዱ ድርጊታቸው ወይም ንግግራቸው ናት፡፡ ለምሳሌ፡-

ሙስሊም ወንዶች ፂማቸውን ቀለም ይቀባሉ፡፡ ይህ አንድ ሱና ነው፡፡ ፂማቸውንም ቀለም የሚቀቡት ነቢያቸው መሐመድ አይሁዶችና ክርስቲያኖች ስለማይቀቡ እናንተ በተቃራኒው መቀባት አለባችሁ ብሎ ስላዘዟቸው ነው፡፡ ይህንንም ሐዲሱ እንዲህ በማለት ይገልጸዋል፡- "The Prophet said, 'Jews and Christians do not dye their hair so you should do the opposite of what they do.'" Sahih Bukhari 7:72:786 (ዝርዝር ሁኔታውን በኋላ በደንብ እናየዋለን) ግን አሁን በአጭሩ መጥቀስ የፈለኩት ነገር በዚህ ዘመን በዓለም ላይ በሙስሊሙ ማኅበረሰብ ዘንድ እየተደረገ ያለው ማንኛውም ነገር የነቢያቸው የመሐመድ ነፀብራቅ መሆኑን አስምሬበት ማለፍ እፈልጋለሁ፡፡

ስለ ሐዲሱ ይህችን ታህል ለማንሳት የፈለኩት ከዚህ በኋላ የሚቀርበው ሙሉው ጽሑፍ ከቁርአኑና ከሐዲሱ የተወሰደ ስለሆነ ሐዲስ ሲባል ምን እንደሆነ መነሻ የሚሆን ሀሳብ ለመስጠት ነው፡፡ የሐዲሱ ስብስቦች ምን ምን እንደሆኑ እንይና ወደ ዋናው ነጥብ እገባለሁ፡፡ ስድስት ዋና ዋና የሐዲስ ስብስቦች ናቸው ያሉት፡፡ እነርሱም፡- ሳሂህ ቡኻሪ (Sahih Bukhari)፣ ሳሂህ ሙስሊም (Sahih Muslim)፣ አቡ ዳውድ (Abu Dawud)፣ ማሊክ ሙዋታ (Maliks Muwatta)፣ ሻማ ኢል-ቲርሚድ (Shama-il Tirmidhi) እና ሐዲስ ቁድሲ (Hadith Qudsi) ናቸው፡፡ የመጀመሪያዎቹ ሁለቱ ስብስቦች ከሁሉም በተሻለ እጅግ ታማኞችና እውነተኛ ተደርገው ነው የሚወሰዱት፡፡ Sahih የሚለውን ቃል "genuine or authentic" ወይም በአማርኛው "እውነተኛ" የሚለውን ቃል ተክቶ የሚገባ ቃል ነው፡፡ በዝርዝር እንያቸው፡-

Sahih Bukhari፡ ከ7000 በላይ ስብስቦች ያሉት ሲሆን በእውነተኛነቱና በታማኝነቱ ከሁሉም የበላይ ተደርጎ ይታያል፡፡ አሰባስቦ ያዘጋጀው ኢማም Bukhari በ256 A.H ነው የሞተው፡፡ M. Muhsin Khan ወደ እንግሊዝኛ ተርጉሞታል፡፡ (A.H after hijra ማለትም ነቢያቸው መሐመድ በ622 ዓ.ም ከመካ ወደ መዲና የተሰደዱበትን ዘመን ይዘው ሙስሊሞች ዘመናቸውን የሚቆጥሩበት ነው)

Sahih Muslim: በእውነተኛነቱና በታማኝነቱ በ2ኛ ደረጃ ተቀምጧል፡፡ ከ4,000 በላይ ስብስቦችን የያዘውን ይህንን ሐዲስ በ261 A.H. ከመሞቱ በፊት Muslim ibn al-Hajjaj የተባለው ሰው ሰብስቦ ያዘጋጀው ሲሆን Abdul Hamid Siddiqui ወደ እንግሊዝኛ ተርጉሞታል፡፡

Abu Dawud: 4,800 ስብስቦችን የያዘው ይህ ሐዲስ ከ6ቱ ዋና ዋና የሐዲስ ስብስቦች ውስጥ በ3ኛ ደረጃ የሚቀመጥ ነው፡፡ ሐዲሶቹን ያሰባሰባቸው Abu Dawud ሲሆን prof.Ahmad Hasan ወደ እንግሊዝኛ ተርጉሞታል፡፡

Maliks Muwatta፡ ይኸኛው ሐዲስ በቀደምትነቱ ከሁሉም ይበልጣል፡፡ ያሰባሰበውና

ያዘጋጀው ኢማም Malik ibn Anas ሲሆን A'isha `Abdarahman ወደ እንግሊዝኛ ተርጉሞታል፡፡

የተቀሩት ሁለቱ (Shama-il Tirmidhi እና Hadith Qudsi) እንደ ሌሎቹ ሐዲሶች ብዙም ተዘውትረው አይጠቀሱም፡፡ የመጀመሪያዎቹ ሦስቱ ግን ከቁርአኑ እኩል እጅግ ትልቅ ቦታ የሚሰጣቸው ናቸው፡፡ እኔም በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ለማጣቀሻነት የተጠቀምኩት በዋናነት እነዚህን የሐዲስ ስብስቦች በተለይም የመጀመሪያዎቹን ሦስቱን ነው፡፡ ቁርአኑ በዋናነት እንዳለ ሆኖ ማለት ነው፡፡ ከእነዚህ ስድስት ዋና ዋና የሐዲስ ስብስቦች በተጨማሪ ከሁሉም እውነተኛና ታማኝ ሐዲሶች ውስጥ የተውጣጡ በርካታ የነቢያቸውን የመሐመድን ንግግሮችና ድርቶች የያዘ al-Baghawi በተባለ ሰው የተዘጋጀ "Mishkat-al-Masabih" የተባለ ጥንታዊ መጽሐፍ አለ፡፡ James Robson ወደ እንግሊዝኛ የተረጎመውን ይህን መጽሐፍም ለማጣቀሻነት ተጠቅሜበታለሁ፡፡

ሌላው በማጣቀሻነት የተጠቀምኩበት መጽሐፍ ከሁሉም ኢስላማዊ ጽሑፎች ውስጥ እጅግ ጥንታዊ የሆነውና በ750 ዓ.ም የተጻፈው የኢብን ኢሻቅ "Sirat Rasul Allah" መጽሐፍ ነው፡፡ ይህ መጽሐፍ በጥንታዊነቱ የመጀመሪያ ነው፡፡ ቁርአኑንንም ሆነ ሁሉንም ሐዲሶች ይቀድማል፡፡ ቁርአኑ በሙስሊሞቹ ነቢይ በመሐመድ ተከታይ ከሊፋዎች አማካኝነት ተሰብስቦ በአንድ ጥራዝ መልክ የተዘጋጀው ነቢያቸው መሐመድ በ632 ዓ.ም ከሞቱ በኋላ ቢያንስ 200 ዓመትና ከዚያ በላይ ቆይቶ ነው፡፡ ይህን እጅግ ጥንታዊ የሆነና የነቢያቸውን የመሐመድን የሕይወት ታሪክ (biography) የያዘ መጽሐፍ ግን የተጻፈው በ750 ዓ.ም ነው፡፡ በዚህ ዘመን መጽሐፉን በጣም ጥልቀትና ስፋት ባለው መልኩ የጻፈው ኢብን ኢሻቅ (Ibn Ishaq) ሲሆን እርሱ "Sirat Rasul Allah" በሚል ርዕስ የጻፈውን Alfred Guillaume የተባለው ጸሐፊ "The Life of Muhammad" ማለትም «የመሐመድ ሕይወት» በሚል ርዕስ ለመጀመሪያ ጊዜ በ1955 ዓ.ም ወደ እንግሊዝኛ ተርጉሞታል፡፡ ይህንን መጽሐፍ እኔም ባዘጋጀሁት ጽሑፍ ላይ በምንጭነት ተጠቅሜበታለሁ፡፡ ሌሎችም እንዲሁ በቀደምትነት የተጻፉ ኢስላማዊ መጽሐፎችን ለማየት በጣም ከፍተኛ ጥረት ተደርጓል፡፡ ስለዚህ ይህ መጽሐፍ ቁርአኑን፣ ሐዲሱንና ጥንታዊ የሆኑ ኢስላማዊ መጽሐፎችን ብቻ መሠረት ተደርጎ የተጻፈ ስለሆነ መጽሐፉ "based upon the earliest & original source of Islamic manuscripts" "የመጀመሪያና ጥንታዊና የሆኑ ኢስላማዊ ጽሑፎችን መሠረት ተደርጎ የተዘጋጀ" ነው መባሉ ትክክልና አሳማኝ ነው፤ ተገቢም ነው፡፡

## 2. እስልምናን ለምን ተውኩት? “Why I Reject Islam?”

ሁሉንም ነገር በቅንነትና በንጹሕ ልቦና ሆኜ ከማየት ነው የምጀምረው፡፡ የምጨርሰውም እንዲሁ እንደ አጀማመሬ ነው፡፡ ነገር ግን የማነሳቸው ሀሳቦች ወደፊት እየጠነከሩ ስለሚመጡ ለመንደርደሪያነት ያመች ዘንድ አበውም «ነገርን ከሥሩ ውኃን ከጥሩ» እንዲሉ ነገረ ሃይማኖትን አንስቼ ከመጻፌ በፊት የሃይማኖትን ምንነት ከመናገር እጀምራለሁ፡፡

የሰው ልጅ በባሕርይው ከሃይማኖት ውጭ ሆኖ መኖር አይችልም፡፡ ዓለማዊ የሆኑ አሊያም ከነጭራሹ ለይቶላቸው ‹ሃይማኖት የለኝም› ብለው የሚናገሩ ሰዎች እንኳ ሳይቀሩ ሃይማኖታዊ እሳቤዎችን ሲያራምዱ ይታያሉ፡፡ ዓሣ ከባሕር ወጥቶ መኖር እንደማይችል ሁሉ የሰው ልጅም ከፈጠረው አምላኩ ተለይቶ መኖር አይችልም፡፡ ከሃይማኖት ውጭ ሆኜ እኖራለሁ ካለም ለዓለምና ለገዥዋ ለዲያብሎስ ተገዥ ሆኖ ነው የሚኖረው፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ ላይ እንዲህ ተብሎ እንደተጻፈ፡- «ኃጢአትን የሚያደርግ ከዲያብሎስ ነው፣ ዲያብሎስ ከመጀመሪያ ኃጢአትን ያደርጋልና» (1ኛ የሐ 5፡8)፤ «ዓለምን መውደድ ለእግዚአብሔር ጥል እንዲሆን አታውቁምን? እንግዲህ የዓለም ወዳጅ ሊሆን የሚፈቅድ ሁሉ የእግዚአብሔር ጠላት ሆኖአል» እንዲል መጽሐፍ፡፡ ያዕ 4፡4፡፡ ይህ እጅግ አስፈሪ የሆነ ግን ደግሞ እውነቱን ብቻ ቁልጭ አድርጎ የሚናገር የእግዚአብሔር ቃል ነው፡፡ «የእግዚአብሔር ወዳጅ» አለመሆን በነፍስም በሥጋም እጅግ ትልቅ ጉዳት ሆኖ ሳለ «የእግዚአብሔር ጠላት» መሆን ግን ምንኛ አስፈሪና አስጨናቂ ነገር ነው በእውነት!

ሰው በሃይማኖት ኖሮ ለአምላኩ ታማኝ ሆኖ እርሱንም እያገለገለ መኖር ካልቻለ የዓለምና የዲያብሎስ ተገዥ መሆኑ እርግጥ ነው፡፡ ማንኛውም ሰው በባሕርይው ድከመት ስላለበት በየጊዜውና በየአጋጣሚዎቹ ወይም በሕይወቱ ፍጻሜ በሞት አፋፍ ላይ ሲገኝ ያን ጊዜ የመለኮታዊ ኃይል እርዳታን መፈለጉ አይቀርም፡፡ ስለዚህ ያ ከመሆኑ በፊት በሃይማኖት መኖር ለሰው ልጆች ሁሉ አማራጭ የሌለው መፍትሄ ነው፡፡

ሃይማኖት ማለት አምላክ የአዳም ዘር በሙሉ መንግሥቱን ይወርሱለት ዘንድ ለሰው ልጆች ሁሉ የሰጣት እጅግ ውድና የከበረች ስጦታ ናት፡፡ ሃይማኖት አምላክ እርሱን ያመልኩባት ዘንድ ለሰው ልጆች ሁሉ የሰጣት ብቸኛ የነፍስ መዳኛ መንገድ ናት፡፡ መንግስተ ሰማያት ወይም በሙስሊሞቹ አጠራር «ጀነት» የምትወረሰው በሃይማኖት ብቻ ነው፡፡ ስለዚህ አምላክ ሰማያዊት ርስት መንግሥተ ሰማያትን ወይም ጀነትን ይወርሱ ዘንድ ለልጆቹ የሰጣትን እውነተኛዋን ሃይማኖት ጠንቅቆ ማወቅ

እርሷንም በንጽሕናና በቅድስና አጽንቶ ይዞ መጠበቅ አለበት፡፡ ይህ ምርጫ ሳይሆን ግዴታ ነው፡፡ የሰው ልጅ «እውነተኛይቱና ትክክለኛዋ ሃይማኖት የትኛዋ ናት?» የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ የተሰጠውን ነፃነትና ሰፊ ዕድል ተጠቅሞ የፈለገውን እምነት የመምረጥ ሙሉ መብት አለው፡፡ ምርጫውን ከወሰነ በኋላ ግን የአምላኩን መንግስት የሚወርስባትንና ከአምላኩ የተቀበላትን አንዷቷን ሃይማኖት ግን እስከመጨረሻው በንጽሕናና በቅድስና አጽንቶ መያዝና መታመን አለበት፡፡ ይህ ግዴታ ነው፡፡ እምነቱን ጠንቅቆ አውቆ ለዚያች በደንብ ተረድሮ ላወቃት እምነቱ እስከ ሞት ድረስ በቆራጥነት መታመንም የግድ ያስፈልጋል፡፡ በእውነተኛው ክርስትና ውስጥ ሆነው ያለፉት ጻድቃን ሰማዕታቱ ሁሉ ይህን በተግባር አሳይተውናል፡፡ በዚህ ዘመንም እስከ ሞት ድረስ የታመኑና እግዚአብሔርንም ቀን ከሌሊት የሚያገለግሉ እውነተኛ ክርስቲያኖች ቢኖሩም ብዙኃኑ ግን ክርስትናቸውን በስም ብቻ ነው የያዙት፡፡

በአሁኑ ጊዜ ለአምላካቸው ለአላህ በቆራጥነት በመታመንና በማገልገል ረገድ ሙስሊሞች በጣም ጠንካሮች ናቸው፡፡ ሌሊት 11፡00 ተነስተው አፍረተ ሥጋቸውን ታጥበው (ውዱ አድርገው) ለአምላካቸው ይሰግዳሉ፡፡ ይህ ዓመቱን ሙሉ የማይቋረጥ ተግባራቸው ነው፡፡ አሁን ለጊዜው እዚህ ጋር ሌላ ሌላውን ነገር ማሰብ አልፈለኩም ነገር ግን እነርሱ ግንባራቸው ተልጦ ጥቁር ምልክት እስኪታይባቸው ድረስ ሁልጊዜ ምንም ሳያቋርጡ የሚሰግዱት ለአምላካቸው ለአላህ ያላቸውን ፍቅርና ታማኝነት ለመግለጽ ሲሉ ነው፡፡ በተቃራኒው በዘመናችን ያሉት ብዙዎቹ ክርስቲያኖች ግን ለአምላካቸው ያላቸውን ፍቅርና ታማኝነት የሚገልጹት የተወሰኑ በዓላትን ብቻ ጠብቀው ነው፡፡ ሁሉንም አይደለም እያልኩ ያለሁት፡፡ አብዛኛው ሕዝበ ክርስቲያን ግን መንፈሳዊ ሕይወቱ ቋሚና ወጥ ካለመሆኑም በላይ በአጠቃላይ ጥሩ የሚባል አይደለም፡፡ ብዙዎቹ ክርስትናውን ከዓለማዊነት ጋር በመቀላቀል የሆነ የማስመሰል ኑሮ ነው የሚኖሩት፡፡ ይህንን ደግሞ እግዚአብሔርም፣ እነርሱም፣ ሰይጣንም ጠንቅቀው ያውቁታል፡፡

ሙስሊም ሴቶች ፊታቸውንና መላ ሰውነታቸውን እንደዚያ በሂጃብ ጀቡነውና ሸፍነው የሚሄዱትኮ የነቢያቸውን የመሐመድን ትእዛዝ ለመጠበቅ ሲሉ ነው፡፡ ይህም ለእርሱ ያላቸውን ታማኝነት ነው የሚያሳየው፡፡ በተቃራኒው ግን እስቲ ብዙዎቹን ክርስቲያኖን ሴቶች በየቦታው ተመልከቱ፡፡ ጡታቸውን፣ ጭናቸውን፣ እንብርትና ዳሌያቸውን በግልጽ በገሃድ በአደባባይ ካላሳዩ የሰለጠኑ ስለማይመስላቸው በጣም አሳፋሪ በሆነ መልኩ ነው የሚለብሱት፡፡ አለባበሳቸውም ሆነ ድርጊታቸው እውነተኛው ክርስትና ፍጹም የማይፈቅደውን ነው፡፡ እውነቱን እንነጋገርና እንደነዚህ ዓይነቶቹ

እንኳን ሊታመኑለትና ሊያገለግሉት ይቅርና አምላካቸውን እግዚአብሔርን የሚያሰድቡ ናቸው፡፡

አንድ ሌላ ምሳሌ ልጨምር፡፡ ወንዶቹ ሙስሊሞች ሃይማኖታቸው የሚያዘውን ነገር ለመፈጸም ሲሉ ነው የሰውን አንገት በሰይፍ የሚቆርጡት፡፡ ድርጊቱን እኔ በእጅጉ የማወግዘው ተግባር ነው፣ የከፉው መንፈስም ሥራ መሆኑን አምናለሁ፡፡ ግን እኔ አሁን ማየት የፈለኩት ነገር ሙስሊሞቹ ያንን የሚያደርጉት አምላካቸውን አላህን ለማገልገል በቆራጥነት ስለተነሱ መሆኑን ነው፡፡ ምንም እንኳን ድርጊታቸው ከኅሊና በታች የሆነ ነገር ቢሆንም እነርሱ ግን ቁርአኑ ለሚያዛቸው ነገር ለመፈጸም ታማኞችና ምንጊዜም ዝግጁዎች ናቸው፡፡ አምላካቸውን አላህን ለማገልገል ቆራጦች ናቸው፡፡ ግን ምን ዋጋ አለው! ያን ሁሉ ነገር የሚያደርጉት በእውቀት፣ በንጹሕ ኅሊናና በማስተዋል ላይ ተመሥርተው አይደለም፡፡

ማንኛውም ሰው «እውነተኛይቱና ትክክለኛዋ ሃይማኖት የትኛዋ ናት?» የሚለውን ጥያቄ በንጹሕ ኅሊና ሆኖ በትክክል መመለስ መቻል አለበት፡፡ ይህችንም እውነተኛዋን ሃይማኖት ያውቅ ዘንድ አምላክ ፍጹም ነፃ ፈቀድና ሙሉ ሙብት ሰጥቶታል፡፡ የተሰጠውን ፍጹም ነፃ ፈቀድና ሙሉ ሙብት ተጠቅሞ የፈለገውን እምነት የመምረጥ ሙብቱ የተጠበቀ ነው፡፡ ምርጫውን ከወሰነ በኋላ ግን ላመነው እምነት የመታመን ግዴታ አለበት፡፡ የሰው ልጅ ደግሞ በዚህ መንገድ ሄዶ ግዴታውን ከተወጣ በኋላ ስለሚወርሳት የአምላኩ መንግስት እርግጠኛነት ሊሰማው ይገባል፡፡ አምላኩንም ማገልገል ያለበት በትክክል አውቆት ነው፡፡ ስለዚህ አጠቃላይ ስለ እምነቱም ሆነ ወደፊት ከሞት በኋላ እወርሳታለሁ ብሎ ተስፋ ስለሚያደርጋት ስለ አምላኩ መንግሥት ቀድሞ በቂ ግንዛቤ ሊኖረው ይገባል፡፡ ይህንንም የሚያውቀው አምላኩ መመሪያ ይሆነው ዘንድ ከሰጠው መጽሐፍ ነው፡፡ እናም ክርስትያኖችም ሆኑ ሙስሊሞች በመጽሐፍ ቅዱስና በቁርአን ላይ የተጻፈውን መሠረት በማድረግ ከጽርፈኛ አስተሳሰብ ነፃ ሆነው ስለ እምነታቸው በደንብ ጠንቅቀው የማወቅ ግዴታ አለባቸው፡፡ ሁለቱም ወገኖች ተስፋ ስለሚያደርጓት ስለ ሰማያታቸውና ስለ ጀነታቸው በቂ ግንዛቤ ሊኖራቸው ግድ ነው፡፡ ሰው የት እንደሚሄድ ሳያውቅ አይጓዝም፡፡ ከተጓዘም ጉዞው ከንቱ ነው የሚሆነው፡፡

እነዚህን ነገሮች ታሳቢ በማድረግ ወደ ግል ታሪኬ ልምጣና አንዳንድ ነጥቦችን ላንሳ፡፡ ሃይማኖት የነፍስ ጉዳይ ብቻ ነው እንጂ የሥጋ ጉዳይ አይደለም፡፡ ለሥጋ ጉዳይማ ሰርቆና ቀማኛ ሆኖም መኖር ይቻላል፡፡ ሃይማኖት የሥጋ ወይም የምድራዊ ኑሮ ጉዳይ አይደለም፡፡ ስለዚህ በእስልምናው እምነት ውስጥ እያለሁ ብዙ የነፍስ

ጥያቄዎች ነበሩብኝ፡፡ ኢትዮጵያ ውስጥ እያለሁ በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ለ4 ዓመታት ስቆይ በዩኒቨርሲቲው ውስጥ የሚካሄደው የጠነከረ የእምነት እንቅስቃሴና ነፃነት ከቀለሙ ትምህርቴ ጎን ለጎን መንፈሳዊውን ነገር እንድመረምር በእጅጉ እረድቶኛል፡፡

ከመጀመሪያው ጀምሮ ለእስልምና እምነቴ ቀናተኛና ታማኝ ስለነበርኩ መስጊድ እየሄድኩ እሰግዳለሁ፤ ሶላት ለመስገድ ከመስጊድ ቀርቼ አላውቅም፡፡ የአላህንም ትእዛዝ ለመፈጸም እስልምናው የሚያዘኝንም ነገር ሁሉ ለመፈጸም በጣም እጥራለሁ፡፡ ነገር ግን ስለ እምነቴ እውቀቱ አልነበረኝም፡፡ እኔም ብቻ ሳልሆን አብዛኛው ሙስሊም ምእመን ማድረግ ስላለበትና ስለታዘዘ ብቻ የእስልምናውን ሃይማኖታዊ ሥርዓቶች ይፈጽማል እንጂ እምነቱን በደንብ ጠንቅቆ አውቆ አይደለም የሚኖረው፡፡ እኔ ግን አሁንም ሆነ ወደፊት እስልምና እምነቴን ጠንቅቄ አውቄው ከበፊቱ በበለጠ በመስገድ እየተጋሁ የአላህን ትእዛዞች ሁሉ ለመጠበቅ በእጅጉ እመኝና እፈልግ ነበር፡፡ ግን ስለ እምነቴ ጠንቅቄ ማወቅ እንዳለብኝ ራሴን አሳምኜዋለሁ፡፡ በደንብ ጠለቅ ብዬ በጣም ብዙ ነገሮችን እያነበብኩ ስመጣ በውስጤ በጣም ብዙ ጥያቄዎች ተፈጠሩብኝ፡፡ እናም ከበፊትም ጀምሮ የነበሩብኝን ጥያቄዎች ለሙስሊም መምህራኖችና ወንድሞች ስጠይቅ የሚሰጠኝ ምላሽ ነገሩን የበለጠ እንድገፋበት አደረገኝ፡፡ እኔ እስልምናው ውስጥ ስላሉ በግልጽ የማይነገሩ ድብቅ ነገሮችን ስጠይቃቸው ለጥያቄዬ መልስ ሳይሆን የሚሰጡኝ «ይህን የነገረሽ ማነው?» በማለት ለጥፋት ራሳቸውን ያዘጋጁ ነበር እንጂ የእኔን የነፍስ ጥያቄዎችን አይመልሱልኝም ነበር፡፡ ወደ ቤተሰቦቼም ለእረፍት ስመለስ በዚያ ያሉትን መምህራኖች በስልክና በአካል ቀስ እያልኩ ስጠይቃቸው ምላሹ ተመሳሳይ ነው፡፡ «ይህን የነገረሽ ማነው?፡፡»

ዩኒቨርሲቲው ውስጥ አብራኝ አንድ ክፍል ውስጥ የምትኖርና የምትማር ጥሩና ጠንካራ ክርስቲያን ጓደኛ ነበረችኝ፡፡ መኝታ ክፍላችን ውስጥ ከሌሎች ክርስቲያን ጓደኞቿ ጋር ስለ እምነታቸው ስታወራ «ጊቢ ጉባዔው ባዘጋጀው ልዩ ጉባኤ ላይ ዛሬ መምህር እከሌ ፕሮቴስታንቶች ለሚጠይቋቸው ጥያቄዎች መልስ ይሰጣሉ ስለተባለ ጉባኤው ላይ መገኘት አለብን» እያለች ስታወራ ሰማኋት፡፡ በሌላ ጊዜ ብቻችን ስንሆን ጥያቄዎች ጠየኳት፡፡ «እናንተ ጋር ሁላችሁም ለምትጠይቁት ጥያቄ በቂ መልስና ማብራሪያ ይሰጣችኋል?» ብዬ ጠየኳት፡፡ እሷም «አዎ በቂ መልስ ይሰጠናል፡፡ ሊቃውንት መምህራኖቻችንንም በፈለግነው ሰዓት የፈለግነውን ነገር እንጠይቃለን፡፡ በተለይም የነፍስ አባቶቻችንን በግል እየሄድን ጾታዊ ጉዳዮችን ሁሉ እንጠይቃለን፤ ከበቂ በላይ የሆነ መልስም ይሰጠናል» አለችኝ፡፡ እኔ ጋር ካለውና ካጋጠመኝ ጋር ሳነፃፅረው ፍጹም የተለየ ስለሆነብኝ መንፈሳዊ ቅናት አደረብኝ፡፡ በሥጋ ዘመዶቼ

ወደሆኑት ሼሆች ጋር ስልክ እየደወልኩ «እውነት በእስልምና እምነታችን ውስጥ እንደዚህ ዓይነት ነገር አለ እንዴ?» እያልኩ የነፍሴን ጥያቄዎች ስጠይቃቸው «ልጄ ይህን ደግሞ ከየት ነው የሰማሽው?» እያሉ መልሰው ይጠይቁኛል እንጂ እኔ ለጠየኳቸው ጥያቄ መልስ አይሰጡኝም ነበር፡፡ ይህም ነገር ይበልጥ ሲደጋገምብኝ ስለ እስልምና እምነቴ በደንብ ለማወቅ ከፍተኛ ጉጉት አደረብኝና ቀንም ሌሊትም ማንበብ ጀመርኩ፡፡ አማርኛውን ቁርአንን ገዛሁና ሙሉውን ሳነበው የቀድሞ የነፍስ ጥያቄዎቼን ይበልጥ አጠናከረልኝ፡፡ በዚህ ምድር ላይ ያለው የዝሙት ኃጢአት በጀነትም እንዳለ ቁርአኑ በደንብ ይናገራል፡፡ ሐዲሱንም ከተለያዩ ኢስላማዊ ድረ ገጾች (web sites) ላይ ሳነብ ጭራሽ ቁጥራቸው 72 የሚሆኑ ሴቶች በጀነት ለአንድ ወንዱ ሙስሊም ለወሲብ ተግባር ሽልማት ተደርገው እንደሚሰጡት ይናገራል፡፡ (ነገሩን ወደፊት በዝርዝር እናየዋለን፡፡) እናም ቁርአኑ ደጋግሜ በደንብ አነበብኩት፡፡ እንኳን ለነፍስ ጥያቄዎቼ መልስ ሊሰጠኝ ይቅርና መለኮታዊ ይዘትም አጣሁበት፡፡ ሌላው ቢቀር የአማርኛ ሰዋሰዋዊ ስሕተቶች ሁሉ አሉበት፡፡ ምንም ትርጉም የማይሰጡ አገላለጾች አሉበት፤ ዛቻና ማስፈራሪያዎች ይበዙበታል፡፡ የጀመራቸውን አንዳንድ ታሪኮች አይጨርሳቸውም፡፡ ስለ እነዚህና ስለ ሌሎቹንም ነገሮች አሁንም ሆነ ወደፊት ሙስሊም ሼሆችንና መምህራኖችን እጠይቃለሁ ብዬ አሰብኩ፡፡ ግን ቁርአኑ ውስጥ ሌላም ብዙ ነገሮችን አገኘሁ፡፡ ቁርአኑ ስለ ክርስትና ምስክርነት ይሰጣል፡፡ ቁርአን ለሙስሊሞች የመጣው መጽሐፍ ቅዱስን ለማረጋገጥ እንደሆነ ራሱ ቁርአኑ ይናገራል፡፡ (ወደፊት በደንብ እናየዋለን፡፡) ይሄ ደግሞ ጎሊናዬን ይበልጥ አስጨነቀው፡፡ ሁለቱ እምነቶች (እስልምናና ክርስትና) የማይገናኙ ተቃራኒ እምነቶች ሆነው ሳሉ እንዴት ቁርአን ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ሊመሰክር ይችላል? ለምንስ መመስከር አስፈለገው?

አንድ ቀን ያችን ክርስቲያን የክፍሌን ጓደኛ ብቻችንን ስንሆን ጥያቄ ጠየኳት፡፡ መጽሐፍ ቅዱሳችሁ ስለ እስልምና ምን ይናገራል? ብዬ ስጠይቃት «ኸረ እኛ ጋር ስለሌላ እምነት አይወራም፤ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥም ወደፊት በክርስቶስ ስም የሚመጡ አስመሳዮች እንደሚመጡ ትንቢት ተነግሯል እንጂ ስለ እስልምና እምነት እኛ ክርስቲያኖች ጋር ምንም አይወራም የተጻፈም ነገር የለም፡፡ ካለም ደግሞ ቆይ ሊቃውንት መምህራንን ጠይቄ እነግርሻለሁ» አለችኝ፡፡

እኔም 114ቱንም የቁርአን ምዕራፎች በደንብ ማንበቤን እንደቀጠልኩ ነው፡፡ በጣም አስገራሚ በሆነ ሁኔታ ቁርአኑ በሱረቱ አል-መርየም ሙሉ ምዕራፍ ላይ፣ በሱረቱ አል-ዒምራን 3፡42-49 እና በሱረቱ አል-ማኢዳህ 5፡110 ላይ ክርስቶስ ከሴቶች ተለይታ ከተመረጠች ከድንግል ማርያም በደንግልና መወለዱንና በኋላም ያደረጋቸውን

አስደናቂ ተአምራቶች ማለትም ኢየሱስ ክርስቶስ ዕውራንን ማብራቱን፣ ሙታንን ማስነሣቱን፣ ለምፃሞችን ማንፃቱን፣ ድውያንን መፈወሱን፣ መና ከሰማይ ማውረዱን፣ የሕይወት ፈጣሪ መሆኑን፣ ሁሉን ዐዋቂ መሆኑን ቁርአኑ በትክክል ይመሰክራል፡፡ ይህ ነገር እንዴት ነው? በማለት ሙስሊም ምሁራኖችን ስለጉዳዩ ለመጠየቅ ብዙ ደከምኩ፡፡ እኛ ሀገር ኢትዮጵያ ውስጥ ያሉት በጥያቄዎች ደስተኞች ካለመሆናቸውም በላይ ምንም ሳልጠይቅና ሳላውቅ በቃ ዝም ብዬ እንድኖር ብቻ ነው ጫና የሚያደርጉብኝ፡፡

ለጥያቄዎች ሁሉ መልስ የሚሰጡ በውጭ ሀገር ያሉ የተለያዩ ኢስላማዊ ድረ ገጾች (web sites) ስላሉ ለእነርሱ ጥያቄዎቼን ላኩኝ፡፡ የሰጡኝም መልስ ‹‹ዒሳ (ኢየሱስ) በነቢይነቱ አላህ እረድቶት ነው እነዚያን ተአምራት ያደረገው›› የሚል ነው፡፡ በሌላ ጊዜም የነፍስ ጥያቄዎቼን ጨምሬ ብዙ ጥያቄዎችን ላኩላቸው፡፡ ልክ ለዓሳ እንዲህ ተብሎ በቁርአኑ ውስጥ እንደተጻፈው ሁሉ ታዲያ ለምን ለነቢያችን ለመሐመድም እንዲህ ተብሎ አልተጻፈም? ነቢያችን መሐመድ ከነቢያት ሁሉ ይበልጣሉ ከተባለ ልክ እንደዒሳ ስለእሳቸውም በቁርአኑ ውስጥ ሙት ስለማስነሣታቸው፣ ሕይወትን የፈጠሩ ስለመሆናቸው ለምን አልተጻፈም? ዒሳ (ኢየሱስ) በእስትንፋሱ እፍ ብሎ ሕይወት እንደፈጠረ በቁርአኑ ላይ ተጽፏል፤ ታዲያ ይሄ በራስ ሥልጣን የሚደረግ ነገር አይደለም ወይ? በሌላም ቦታ ቁርአኑ አምላክነቱንም ጭምር መመስከሩስ እንዴት ነው? በቁርአኑና በሐዲሱ ላይ በጀነት ውስጥ ዝሙት ስለመኖሩ የተጻፈውን ነገር ልታብራሩልኝ ትችላላችሁ? የነቢያችን የመሐመድ የግል የሕይወት ታሪካቸውን በጥልቀት ልትነግሩኝ ፈቃደኞች ናችሁ? ከ30 በላይ ሚስቶች እንደነበሯቸው የሚነገረውስ እውነት ነው? በ53 ዓመታቸው ከ9 ዓመት ሕጻን ልጅ ጋር ወሲብ እንደፈጸሙ በሐዲሱ የተነገረው ምን ያህል እውነት ነው? ስለነቢያችን መሐመድ እውነተኛ ሕይወት በደንብ ማወቅ እፈልጋለሁ?...... እያልኩ እጅግ በርካታ ጥያቄዎችን ጠየኳቸው፡፡ እነርሱም እንደሚመች አድርገው መልሳቸውን ነገሩኝ፡፡

እኔም በውጭ ያሉት ሙስሊም መምህራኖች በድረ ገጾቻቸው የሰጡኝን መልሶች እንደመነሻ ይዤ በጣም ብዙ ነገሮችን ከኢስላማዊ ድረ ገጾች ላይ ስፈልግ ባጋጣሚ በፊት ሙስሊም የነበሩ አንድ ግብፃዊ ሼህ (ለደኅንነት ሲባል ስም አልጠቅስም) እሳቸው የጻፉትን ጽሑፍ አገኘሁ፡፡ ለእሳቸውም አንዳንድ ጥያቄዎችን ጠየኳቸው፡፡ በቁርአኑና በሐዲሱ ውስጥ የተጻፉ እጅግ ብዙ ነገሮቸን ስለነገሩኝ ማመን ነው ያቃተኝ፡፡ የነቢያችን የመሐመድ የግል የሕይወት ታሪክ፣ የቁርአንን ምንነት፣ የእስልምናውን አጀማመር... ማስረጃዎችን እየጠቀሱ ሁሉንም ዘርዝረው ነገሩኝ፡፡ እኔም ለነገሩ እጅግ ከፍተኛ ትኩረት ሰጥቼ ያገኘኋቸውን መረጃዎች ሁሉ ከአማርኛው

ቁርአንና ከሐዲሱ ጋር እያመሳከርኩ ቀን ከሌሊት ለብዙ ጊዜ ያህል አነበብኩ፡፡ ከዩነቨርሲቲ ተመርቄ እስከወጣ ድረስ ይህን ሁኔታ ቀጠልኩበት ግን ለሌላ ሰው ለምንም አልተናገርኩም ነበር፡፡ ከሙስሊም መምህራኖች ጋር ጉዳዩን ለመወያየት ብሞክርም ‹‹ከየት አመጣሽው? ማነው ይህን ያለሽ?›› እያሉ ለጥፋት ከመነሳት በቀር ያገኘሁት ጥቅም ስለሌለ አሁን ማንንም ለማናገር አልፈለኩም፡፡ ለ3 ዓመታት ያህል የዚያን ግብፃዊ ሼህ መረጃዎች ከአማርኛው ቁርአንና ከሐዲሱ ጋር በማመሳከር ስመረምር ከቆየሁ በኋላ ተመርቄ ወደ ሥራ ተሰማራሁ፡፡ ብቻዬን ቤት ተከራይቼ ስኖር ሁሉንም ነገር በነፃነት ለማወቅ ነገሮች የበለጠ ተመቻቹልኝ፡፡

ሌላም ምቹ አጋጣሚው ተፈጠረልኝ፡፡ ያች በዩኒቨርሲቲ ቆይታዬ አንድ ክፍል ውስጥ አብራኝ ትኖርና ትማር የነበረችው ክርስቲያን ጓደኛዬ ሀገሯ ሌላ ቦታ ቢሆንም መሥሪያ ቤቷ አዘዋውሯት እኔ ከምሠራበት ሀገር መጣች፡፡ እየተገናኘን እንጫወታለን፤ አብረንም እያደርን ብዙ ነገር እናወራ ስለነበር አንድ ቀን ስለ እስልምናው ያወኩትን ነገር ሁሉ ነገርኳት፡፡ ለመጀመሪያ ጊዜ ከእኔ አንደበት ስትሰማ በጣም ደነገጠች፡፡ ‹‹የምትናገሪው ነገር በጣም ከባድ ነው፤ እንዲህ ብለሽ ለማንም እንዳትናገሪ ይገሉሻል›› አለችኝ፡፡ ‹‹እንዲህ ዓይነቱንስ ነገር ከየት አመጣሽው?›› በማለት ደግማ ጠየቀችኝ፡፡ እውነቱን ማወቅ እፈልጋለሁ እስቲ ስለ እናንተ እምነት ነገሪኝ ስላት ብዙ ቀን አብረን እያደርን ስለ ክርስትናው ነገረችኝ፡፡ መጽሐፎቿን እየገለጠች ስለ ክርስቶስ የተነገሩ ትንቢቶችን፣ አምላክነቱን፣ ወደዚህች ምድር የመጣበትን ዓላማ፣ መጥቶም ያን ሁሉ መከራ ለምን እንደተቀበለ... ብቻ ክርስትናውን በአጠቃላይ በደንብ አስረዳችኝ፡፡ መጽሐፎቿንም ተረጋግቼ እንዳነባቸው ሰጠችኝ፡፡ በቁርአን ላይ ስለ ክርስቶስ ኢየሱስ የተጻፉ እነዚያን ነገሮችን እንደመነሻ ይዤ ከክርስትናው አስተምህሮ ጋር ሳስተያየው ነገሩ ሁሉ በጣም ቀላል ሆኖ አገኘሁት፡፡ ቁርአኑም ለምን መጽሐፍ ቅዱስን አረጋግጣለሁ እንደሚል አሁን ገባኝ፡፡

እንደተለመደው አንድ ቀን ማታ ጓደኛዬ ጋር አዳሬን ሄድኩና ‹‹መጠመቅ እፈልጋለሁ›› አልኳት፡፡ እሷም ‹‹ማወቅ ከፈለግሽማ ይኸውልሽ በደንብ እወቂ›› በማለት ስለ ክርስትናው የምታውቀውን ነገረችኝ መጽሐፎቿንም ሰጠችኝ እንጂ ካሁን በፊት ክርስቲያን ሁኚ ብላ አንድም ቀን ተናግራኝ አታውቅም ነበርና አሁን ‹‹መጠመቅ እፈልጋለሁ›› ስላት ገረማት፡፡ ‹‹ግን አንቺ እስካሁን ድረስ እንዴት አላነሳሽብኝ?›› ብዬ ጠየኳት፡፡ ‹‹እውነትን ስታውቂያት እውነት ራሷ ነፃ ታወጣሻለች ብዬ ነው›› ስትለኝ ምን ማለቷ እንደሆነ ጠየኳት፡፡ እሷም ‹‹ሁሉን ነገር በደንብ ስታውቂው ምንም ዓይነት ተፅዕኖ ሳይኖርብሽ ራስሽ በፈቃድሽ ብቻ መወሰን እንድትችይ ብዬ ነው›› አለችኝ፡፡

በጣም ልክ ነበረች፡፡

ሁሉንም ነገር ጠንቅቄ ከተረዳሁ በኋላ አምኜ ተጠመቅሁ፡፡ እኔ አምኜ ተጠምቄ ብቻ አላቆምኩም፡፡ የዋህና ቅን ልቡና ያላቸውን ሌሎች ሙስሊም እኅቶቼንና ወንድሞቼን መረጃዎችን በማቀበል «እስልምናው ውስጥ እንዲህ እንዲህ... ዓይነት ነገር አለኮ! እስቲ እውነት መሆኑን አረጋግጡና ነገሩን በደንብ መርምሩት» እያልኩ መረጃዎቼን እሰጣቸዋለሁ፡፡ ሄደውም ሲጠይቁ ለጥያቄዎቹ መልስ ሳይሆን የሚሰጣቸው «እንዲህ ዓይነቱን ነገር ከየት አመጣችሁት?» ይባላሉ፡፡ ከዚያም ሳይፈልጉም ባይሆን በግድ ስለ ክርስትናው እንዲያውቁ ይገደዳሉ፡፡ እውቀውም ይጠመቃሉ፡፡ በዚህ ዓይነት መንገድ ከእኔ በኋላ አምነው የተጠመቁ ብዙዎች ናቸው፡፡ እኔም የማስተርስ ዲግሪ የትምህርት ዕድል አግኝቼ ወደ አውሮፓ ሄድኩ፡፡ ትምህርቴንም ጨርሼ እዛው ሀገር መኖር ከጀመርኩ በኋላ ጉዳዩን እጅግ በጥልቀት መመርመሬን ቀጠልኩበት፡፡

እስልምናውን ለምን እንደተውኩትና የነፍስ ጥያቄዎቼ ምን እንደነበሩ ከዚህ ቀጥሎ በዝርዝር አቀርባቸዋለሁ፡፡ አሁንም ቢሆን ቀጥሎ የማነሳቸውን የነፍሴን ጥያቄዎች ሊመልስልኝ የሚችል ማንኛውም ኢማም (ኢስላማዊ መምህር) ካለ ደስ ይለኛል፤ እውነቱንም ለመቀበል ፍቃደኛ ነኝ ግን ማንም ሊመልስልኝ የሚችል የለም፡፡ ጥያቄዎቼን ከመመለስ ይልቅ በእኔ ላይ አካላዊ ጉዳት ለማድረስ መሯሯጡ ነው የሚቀላቸው፡፡ እስልምናውን ከተውኩባቸው ምክንያቶች ውስጥ ለማሳያ ያህል ቀጥሎ የምጠቅሳቸው ዋና ዋና ነጥቦች በቀጥታ ከቁርአኑና ከሐዲሱ የተወሰዱ ናቸው፡፡

በመጀመሪያ የሙስሊሞቹን ነቢይ የመሐመድን የግል ሕይወታቸውን ቀጥሎ ደግሞ ያስተማሯቸውን ትምህርታቶቻቸውን ለሁለት ከፍሎ ማየቱ የተሻለ ነው፡፡ በዚህ መጽሐፉ ውስጥ ሁሉንም ነጥቦች በዝርዝር ስለምናይ ለአሁኑ ነጥብ ነጥቦቹን ብቻ በአጭሩ ላስቀምጥ፡፡ እኔ አንድም እስልምናውን የተውኩበት ምክንያት የመሐመድ የግል ሕይወታቸው ብዙ ሙስሊሞች በማያውቁት መልኩ እጅግ አስደንጋጪ በሆኑ ድርጊቶች የተሞላ በመሆኑ ነው፡፡ ከእነዚህም ውስጥ፡-

1ኛ. በመጀመሪያ ደረጃ ነቢያቸው መሐመድ ኃጢአተኛ እንደነበሩ ራሱ ቁርአኑ የሚመሰክርባቸው መሆኑን ማየቱ በጣም ተገቢ ነው፡፡ ቁርአኑ ብዙ ቦታ ላይ “መሐመድ ሆይ! ስለ ኃጢአትህ ምሕረትን ለምን” “ask forgiveness for your sin” በማለት በግልጽ ይናገራል፡፡ ሱረቱ መሐመድ 47፡19፣ ሱረቱ አል-ፈትሕ 48፡2፣ ሱረቱ አል-ሙእሚን 40፡55፡፡

ቁርአኑ በዚህ መልኩ ኃጢአተኛ መሆናቸውን ከመሰከረባቸው ነቢያቸው መሐመድ የሠሯቸው ኃጢአቶች ምን ምን ናቸው? ከተባለ ወደፊት በጣም በሰፊው እናየዋለን ለአሁኑ ግን ለማሳየት ያህል ብቻ በአጭሩ የተወሰኑ ምሳሌዎችን ከቁርአኑና ከሐዲሱ ላይ መጥቀስ እንችላለን፡፡

ነቢያቸው መሐመድ በ53 ዓመታቸው ከ9 ዓመት ህጻን ልጅ ጋር ወሲብ ፈጽመዋል፡፡ አይሻን ያገቧት በ6 ዓመቷ ሲሆን በሚስትነት ከእናቷ ለይተው ወደቤታቸው የወሰዷት ግን በ9 ዓመቷ ነው፤ በዚህ ጊዜ የእሳቸው ዕድሜ 53 ነበር፡፡ ይህንንም በመመስከር ራሷ አይሻ የተናገረችው በሐዲሱ ላይ ተመዝግቦ ይገኛል፡፡ A'isha reported: Allah's Messenger married me when I was six years old, and I was admitted to his house at the age of nine. Sahih Muslim 8:3309, & Sahih Muslim 8:3310. “the Prophet married her when she was six years old and he consummated his marriage when she was nine years old, and then she remained with him for nine years (i.e., till his death”) Sahih Bukhari 7:62:64, Abu Dawud 2:2116.

የሙስሊሞቹ ነቢይ መሐመድ የአሳደጉትን ልጅ የዛይድን ሚስት እሱን አስፈትተው እሳቸው አግብተዋታል፡፡ ይህም ቁርአኑ ሱረቱ አል-አሕዛብ 33፡37 ላይ እንዲሁም በሐዲሱ Sahih Bukhari 9:93:516 ላይ በሰፊው ተጠቅሷል፡፡

መሐመድ በወቅቱ ‹‹ነቢይ ነኝ›› ብለው ሲነሱ ትምህርታቸውን ‹‹ትክክለኛ ነገር አታስተምርም፣ ትምህርትህን አንቀበልም›› በማለት ይቃወሟቸው የነበሩትን ግለሰቦች በጨለማ ሰው እየላኩ ያስገድሉ ነበር፡፡ በእሳቸው ቀጭን ትእዛዝ የተገደሉ ብዛታቸው ከ64 በላይ የሆኑ ሰዎች ዝርዝር ታሪካቸውና የአገዳደላቸው ሁኔታ በግልጽ በሐዲሱ ላይ ተመዝግቦ ይገኛል፡፡ ወደፊት በዝርዝር እናየዋለን፡፡

የሙስሊሞቹ ነቢይ መሐመድ ጅምላ ጭፍጨፋ ያካሂዱ ነበር፡፡ በ627 ዓ.ም ቁጥራቸው ከ800 በላይ የሚሆኑ ወንዶች የባኑ ቁራይዛ ጎሳ አባል የሆኑ በመዲና ከተማ ይኖሩ የነበሩ አይሁዶች በነቢያቸው መሐመድ ትእዛዝ በአንድ ቀን በሰይፍ ተጨፍጭፈዋል፡፡ ሚስቶቻቸውና ልጆቻቸው ደግሞ ለመሐመድ ተከታዮች በጦር ምርኮነት እንዲከፋፈሉ ሲደረጉ የተረፉትም ለባርነት ተሸጠዋል፡፡ ይህም በቁርአኑና በሐዲሱ ላይ በግልጽ ተጽፎ ይገኛል፡፡ ሱረቱ አል-አሕዛብ 33፡26 ላይ እንዲህ ተብሎ

ነው የተጻፈው:- *«እነዚያንም ከመጽሐፉ ባለቤቶች የረዱዋቸውን ቁረይዟን ከምሽጎቻቸው አወረዳቸው፤ በልቦቻቸውም ውስጥ መባባትን ጣለባቸው፤ ከፊሉን ትገድላላችሁ፤ ከፊሉንም ትማርካላችሁ:: ምድራቸውንም፣ ቤቶቻቸውንም፣ ገንዘቦቻቸውንም ገና ያልረገጣችኋትንም ምድር አወረሳችሁ፤ አላህም በነገሩ ሁሉ ላይ ቻይ ነው»* ይላል ቁርአኑ:: በሐዲሱና በታሪክ ድርሳናቱ ደግሞ እንዲህ ተብሎ ተጽፏል፡ "The Jews were made to come down, and Allah's Messenger imprisoned them. Then the Prophet went out into the marketplace of Medina (it is still its marketplace today), and he had trenches dug in it. He sent for the Jewish men and had them beheaded in those trenches. They were brought out to him in batches. They numbered 800 to 900 boys and men. Al-Tabari, Vol. 8, p. 35, See Also Ishaq:464. "The Prophet then killed their men and distributed their women, children and property among the Muslims." (Sahih Bukhari 5:59:362), "Then the Apostle divided the property, wives, and children of the Qurayza among the Muslims. Allah's Messenger took his fifth of the booty." Ibn Ishaq:465.

ከዚሁ ጋር በተያያዘ አንድ ነገር አብረን ማየት እንችላለን:: ነቢያቸው መሐመድና ተከታዮቻቸው በጦርነት በሚዘርፉት ንብረት በጣም ሀብታም ሆነው ነበር:: በቁርአኑ ሱረቱ አል-አንፋል 8፡41 ላይ *«ከማንኛውም ነገር በጦር ከከሓዲዎች የዘረፋችሁትም አንድ አምስተኛው ለአላህና ለመልእክተኛው... የተገባ ነው መሆኑን ዕወቁ፤ አላህም በነገሩ ሁሉ ላይ ቻይ ነው»* ተብሎ ነው የተጻፈው:: እየቆየ ሲሄድ ነው የነቢያቸው ድርሻ ወደ አንድ አምስተኛ ተቀይሮ ለተከታዮቻቸውም ማካፈል የጀመሩት እንጂ መጀመሪያ ላይ ለተከታዮቻቸው ሳይሰጡ ሙሉውን ለራሳቸው ብቻ ነበር የሚወስዱት:: ቁርአኑ 8፡1 እንዲህ ይላል:- «ከጦር ዘረፋ ገንዘቦች ይጠይቁሃል፤ የዘረፋ ገንዘቦች የአላህና የመልእክተኛው ናቸው፤ ስለዚህ አላህን ፍሩ» በማለት ቁርአኑ በግልጽ አስቀምጦታል:: ቀጥሎ ያለውን የሐዲሱንም ማስረጃ ይመልከቱ:- "When Allah made the Prophet wealthy through conquests, he said, 'I am more rightful than other believers to be the guardian of the believers." Sahih Bukhari 3:37:495. «አላህ መሐመድን በጦር በተያዘ ንብረት ሀብታም ባደረገው ሰዓት... "When Allah made the Prophet wealthy through conquests" የምትለዋ

አገላለጽ ነቢያቸው መሐመድ በጦርነት በሚዘርፉት ንብረት አላህ ሀብታም እንዳደረጋቸው ነው የምታመለክተው፡፡ ታዲያ እንዲህ ዓይነት ለአእምሮ የሚከብዱ ነገሮችን የፈጸሙትን ነቢያቸው መሐመድን እንዴት ነቢይ ናቸው ብዬ ልመን? ኃጢአተኛና በደለኛ የሆነን ሰውስ እንዴት አርአያ አድርጎ መከተል ይቻላል? ሕመምተኛ ሰው ለራሱ መድኃኒት ያስፈልገዋል እንጂ ሌላውን ያድን ዘንድ ይችላል እንዴ? እኔ በበኩሌ ሁሉም ነገር ከአእምሮ በታች ስለሆነብኝ እስልምናውን በእነዚህና በሌሎችም በርካታ ምክንያቶች ነው የተውኩት፡፡

2ኛ. የሙስሊሞቹ ነቢይ መሐመድ የጦር መሪ (Jihadist) ነበሩ፡- እኔ አይደለሁም ይህን ያልኩት! ነቢያቸው መሐመድ ራሳቸው «እኔ አሸናፊ (ባለድል) የሆንኩት በሽብር ነው» በማለት ተናግረዋል፡፡ “Allah’s Apostle said, ‘I have been made victorious with terror.’” Sahih Bukhari: 4:52:220. አሁንም በዚሁ ሐዲስ ላይ መሐመድ ስለራሳቸው ሲናገሩ “አንደበተ-ርቱእ የመሆንና በሽብር ድል የማድረግ ቁልፍ ተሰጥቶኛል” ነው ያሉት፡፡ “The Prophet of Allah said, ‘I have been given the keys of eloquent speech and given victory with terror.’” Sahih Bukhari: 9:87:127. መሐመድ ሙስሊሞች መንግስተ ሰማያትታቸው ጀነትን ለመውረስ በጂሃድ ተሳትፈው መግደል እንዳለባቸው አስተምረዋል፡፡ “Allah’s Apos-tle said, ‘know that Paradise is under the shade of swords.’” Sahih Bukhari: 4:51:73. ነቢያቸው መሐመድ እስልምና እምነትን ጀምረው ያስፋፉበትም መንገድ ይኸው ነው፡፡ እስልምና የጂሃድ ወረራ ውጤት ነው፡፡ ነቢያቸው መሐመድ እስልምናን ሊመሠርት ከተነሱበት ከ622 ዓ.ም ጀምሮ እስከሞቱበት 632 ዓ.ም ድረስ ብቻ 94 የጂሃድ ወረራና የሽብር ጥቃቶችን ፈጽመዋል፡፡ ከእነዚህ 94 የጂሃድ ወረራና የሽብር ጥቃቶች ውስጥ መሐመድ ራሳቸው በቀጥታ የጦሩ መሪ ሆነው የተሳተፉባቸው 27 ሲሆኑ ቀሪዎቹ 67ቱ ላይ ደግሞ ሌሎች የጦር መሪዎችን ሹመው የተደራጀና የታጠቀ ተዋጊ ሠራዊት አሰማርተው የፈጸሟቸው የጂሃድ ወረራና የሽብር ጥቃቶች ናቸው፡፡ ቆይተን ሁሉንም በዝርዝር እናያቸዋልን፡፡ ለአሁኑ ግን እስቲ ቀጥሎ ያሉትን በቁርአኑ ላይ የተጻፉትን የነቢያቸው የመሐመድን ትእዛዞች ልብ ብላችሁ ተመለከቷቸው፡-

«ባገኛችሁባቸውም ስፍራ ሁሉ ግደሉዋቸው» (ሱረቱ አል-በቀራህ 2:191)፤ «አጋሪዎቹን (ያልሰለሙትን) በአገኛችሁባቸው ስፍራ ግደሉዋቸው፤ ያዙዋቸውም፤ ከበቡዋቸውም፤ ለእነሱም መጠባበቅ በየመንገዱ ተቀመጡ» (ሱረቱ አል-ተውባህ 9:5)፤ «እነዚያ አላህንና መልዕክተኛውን የሚዋጉ ሰዎችን ቅጣት መገደል ወይም መሰቀል

ወይም እጆቻቸውንና እግሮቻቸውን በማፈራረቅ መቆረጥ ወይም ከሀገር መባረር ነው (ሱረቱ አል-ማኢዳህ 5፡33)፤ «አላህ ከምእመናን ነፍሶቻቸውንና ገንዘቦቻቸውን ጀነት ለእነሱ ብቻ ያላቸው በመሆን ገዛቸው፤ በአላህ መንገድ ላይ ይጋደላሉ፤ ይገድላሉም፤ ይገደላሉም፡፡ «እናንተ ያመናችሁ ሆይ እነዚያን በአቅራቢያችሁ ያሉትን ከሓዲዎች (ያልሰለሙትን) ተዋጉ» አል-ተውባህ 9፡111፣ 123፡፡

ለአሁኑ ለማሳያ ያህል እነዚህ 5 የቁርአን አንቀጾች ጠቀስኩ እንጂ በቁርአን ውስጥ በእንደነዚህ ዓይነት ሁኔታ ተጽፈው የሚገኙ 164 የጂሃድ ጥቅሶች አሉ፡፡ በዝርዝር እናያቸዋለን፡፡ በሐዲሱም ውስጥ እንዲሁ እጅግ በሚያሰለችና በሚያሳዝን ለማመንም በሚያስቸግር ሁኔታ ከ35 ሺህ በላይ የጂሃድ ጥቅሶች ተጽፈዋል፡፡

በዚህም መሠረት እስልምና ተስፋፍቶ ዛሬ ያለበት ደረጃ ላይ የደረሰው በጂሃድ ወረራና በሽብር ጥቃቶች ነው፡፡ ጦርነትና የጂሃድ ወረራ ብሎም የሽብር ጥቃቶች የሚጠቅሙት ወታደራዊ መንግሥት ለማቋቋም ብቻ ነው፡፡ ሃይማኖት የሰው ልጆች ሁሉ በሰላም ይኖሩባት ዘንድ ከሰላማዊው አምላክ የምትሰጥ የሰላም ምልክት ናት፡፡ መሪዎቿም ፍጹም ሰላማዊ ካልሆኑ ከእውነተኛውና ከሰላማዊው አምላክ የተላኩ እንዳልሆኑ በዚህ ይታወቃሉ፡፡ ዛፍ በፍሬው ይታወቃልና፡፡ መገኛዋ ፍቅርና ሰላም ሆኖ በእውነትም ላይ ተመስርታ በትምህርት ያልተስፋፋች ሃይማኖት ለነፍስ በፍጹም አትጠቅምም፡፡ እስልምናውን ለምን እንደተውኩት እየተግባባን ይመስላኛል!

እስካሁን እንዳየነው ቁርአኑ፣ ሐዲሱና የታሪክ ድርሳናቱም በግልጽ እንደሚናገሩት መሐመድና ተከታዮቻቸው በባኑ ቁራይዛ ጎሳዎች ላይና በሌሎችም ጎሳዎች ላይ የጦር ወረራ ባደረጉባቸው ቦታዎች ሁሉ ወንዶቹን እየገደሉ ሴቹንና ሕጻናቱን እየማረኩ ለዝሙትና ለባሪያ ንግድ ይጠቀሙባቸው ነበር፡፡ ይህንንም ቀጥሎ በተራ ቁ.3 ላይ እንየው፡-

3ኛ. የሙስሊሞቹ ነቢይ መሐመድና ተከታዮቻቸው በጦርነት የማረኳቸውን ሴቶች በግዳጅ ወሲብ ይፈጽሙባቸው ነበር፡፡ ይህም በቁርአኑና በሐዲሱ ውስጥ በሰፊው ተጠቅሷል፡፡ እነዚህን የቁርአን ጥቅሶች ልብ ብላችሁ ተመልከቱ፡- ‹‹አንተ ነቢዩ ሆይ! እነዚያን እጅህ የጨበጠቻቸውን ምርኮኞች ለአንተ ፈቅደንልሃል›› (ሱረቱ አል-አሕዛብ 33፡50)፣ ‹‹ቀኝ እጆቻችሁ የራስ ያደረጉትን ንብረት ያዙ›› "…and that which your right hand possesses" (አል-ኒሳእ 4፡3)፣ ‹‹እጆቻችሁ በምርኮ የያዟቸውን ሴቶች ተገናኙዋቸው›› (ሱረቱ አል-ኒሳእ 4:24)፤ ‹‹እነሱ ብልቶቻቸውን ጠባቂዎች የሆኑት አገኙ፡፡ በሚስቶቻቸው ወይም እጆቻቸው በያዟቸው ባሪያዎች ላይ ሲቀር እነሱ

በእነዚህ የማይወቀሱ ናቸው›› (ሱረቱ አል-ሙእሚኑን 23:6) እንዲሁም ተመሳሳይ አገላለጽ በሱረቱ አል-መዓሪጅ 70:29 ላይ ተጽፏል፡፡ በእነዚህ የቁርአን መመሪያዎች መሠረት ነቢያቸው መሐመድና ተከታዮቻቸው ሴቶችን በጦርነት ከማረኳቸው በኋላ በግዳጅ ወሲብ ይፈጽሙባቸው ነበር፡፡ ለምሳሌ መሐመድ ራሳቸው የፈጸሙትንና በቡኻሪ ሐዲስ ላይ የተጻፈውን ታሪክ ማየት እንችላለን፡፡

ነቢያቸው መሐመድ በካይባር የሚገኙ ገሳዎችን በድንገት ሌሊት የጦር ወረራ አድርገው ሁሉንም የካይባር ወንዶች ከገደሉ በኋላ ሴቶቹንና ሕጻናቱን በምርኮ ውስደው ለዝሙትና ለባርነት እንዲጠቀሙባቸው ለተከታዮቻቸው ፈቅደውላቸዋል፡፡ ራሳቸው መሐመድም ሳፊያ ቢንት ሁያይ የተባለችውን ምርኮኛ ሴት ቆንጆ ስለነበረች ለራሳቸው ወስደዋታል፡፡ እጅግ አሳዛኝና ዘግናኝ በሆነ መልኩ ነቢያቸው መሐመድ የሳፊያን አባቷን፣ ባሏን፣ ወንድሞቿንም በትእዛዝ ካስገደሉ በኋላ ነው እርሷን የዚያኑ ዕለት በግዳጅ ዝሙት ሲፈጽሙባት ያደሩት፡፡ መሐመድ በዚያው ወስደው ያገቧት ቢሆንም በሕይታቸው መጨረሻ ላይ በምግብ ውስጥ መርዝ ሰጥታ በመግደል ተበቅላቸዋለች፡፡ ይህም በሐዲሱ ላይ በግልጽ ተጽፎ የሚገኝ ታሪክ ነው እንጂ እኔ ፈጥሬ አላወራሁትም፡፡ “Anas said, 'When Allah's Apostle invaded Khaibar, we offered the Fajr prayer there yearly in the morning) when it was still dark. The Prophet rode and Abu Talha rode too and I was riding behind Abu Talha. The Prophet entered the town, he said, 'Allahu Akbar! Khaibar is ruined. Whenever we approach near a (hostile) nation (to fight) then evil will be the morning of those who have been warned.' He repeated this thrice. We conquered Khaibar, took the captives, and the booty was collected.” Sahih Bukhari 1:8:367.

“The Prophet came to Khaibar and when Allah made him victorious and he conquered the town by breaking the enemy's defense, the beauty of Safiya bint Huyai bin Akhtab was mentioned to him and her husband had been killed. Allah's Apostle selected her for himself and he set out in her company till he reached Sadd-ar-Rawha' where her menses were over and he married her.” Sahih Bukhari 3:34:437.

የነቢያቸው መሐመድ ተከታዮቻቸውም እሳቸው እንደፈቀዱላቸው ከጦር ምርኮዎቻቸውና በባርነት ከያዟቸው ሴቶች ጋር ዝሙት ሲፈጽሙ ለባርነት ንግድ እንዲያመቻቸው የዘር ፈሳሻቸውን ወደ ውጭ በማፍሰስ (ejaculate) በማድረግ ወይም (coitus interruptus) በመፈጸም እንዳያረግዙ ያደርጉ ነበር፡፡ "We got female captives in the war booty and we used to do coitus interruptus with them. So we asked Allah's Apostle about it and he said, "Do you really do that?" repeating the question thrice, "There is no soul that is destined to exist but will come into existence, till the Day of Resurrection." Sahih Bukhari 7:62:137.

4ኛ. የሙስሊሞቹ ነቢይ መሐመድ በግልጽ የታወቁ ከ31 በላይ ሚስቶች ነበሯቸው፤ ወደፊት ሁሉንም ሚስቶቻቸውን በዝርዝር እናያቸዋለን፡፡ ነቢያቸው መሐመድ በጣም አስገራሚ የሆነ ወሲባዊ ሕይወትም ነበራቸው፡፡ በሐዲሱ ውስጥ እንደተመዘገው ነቢያቸው መሐመድ ከአስራ አንድ ሚስቶታቸው ጋር በአንድ ቀን ግብረ ሥጋ ግንኙነት ይፈጽሙ ነበር፡፡ ይህንንም ለመፈጸም የሚያስችል ብቃት ነበራቸው፡፡ ማለትም የ30 ወንዶችን ያህል ጥንካሬ አላህ እንደሰጣቸው ነው በሐዲሱ ላይ የተጻፈው፡፡ Anas bin Malik said, "The Prophet used to visit all his wives in a round, during the day and night and they were eleven in number." I asked Anas, "Had the Prophet the strength for it?" Anas replied, "We used to say that the Prophet was given the strength of thirty (men)." (Sahih al-Bukhari, Volume 1, Book 5, Number 268)

ሙስሊም ወንዶች እስከ አራት ሚስቶችን እንዲያገቡ ቁርአን 4፡3 ላይ ተጠቅሷል፡፡ ‹‹ሁለት ሁለት፣ ሦስት ሦስትም፣ አራት አራትም አግቡ›› ይላል ቁርአኑ፡፡ ነገር ግን እዚሁ አንቀጽ መጨረሻ ላይ ‹‹ቀኝ እጆቻቸው የጨበጧቸው የጦር ምርኮኞቻቸውንም›› ያለምንም ገደብ እንዲያገቡ ያዛቸዋል፡፡ እስከ አራት ድረስ የተባለው ሙስሊም ሴቶችን ብቻ ሲያገቡ ነው እንጂ የጦር ምርኮኞቹ ላይ ገደብ የለም፡፡ ይህንን ሕግ ራሳቸው መሐመድም በተለየ ሁኔታ ሲጠቀሙት ነበር፡፡ ነቢያቸው መሐመድ ከ31 በላይ የሆኑትን መደበኛ ሚስቶቻቸውን ጨምሮ በጦርነት ከማረኳቸው

ገደብ አልባ ሚስቶቻቸው በተጨማሪ በሥጋ የቅርብ ዘመድ የሆኑ የአጎታቸውንና የአክስታቸውን ሴቶች ልጆችም ጭምር እንዲያገቡ ቁርአኑ ፈቅዶላቸዋል፡፡

በቁርአኑ ሱረቱ አል-አሕዛብ 33፡50-51 ላይ እንዲህ ተብሎ ነው የተጻፈው፡- ‹‹አንተ ነቢዩ ሆይ! እኛ እነዚያን መህሮቻቸውን (የቅጥር ገንዘቦቻቸውን) የሰጠሃቸውን ሚስቶችህን፣ አላህ በአንተ ላይ ከመለሰልህም እነዚያን እጅህ የጨበጠቻቸውን ምርኮኞች፣ እነዚያንም ከአንተ ጋር የተሰደዱትን የአጎትህን ሴቶች ልጆች፣ የአክስቶችህንም ሴቶች ልጆች፣ የየሹማህንም ሴቶች ልጆች፣ የየሹሜዎችህንም ሴቶች ልጆች ማግባትን ለአንተ ፈቅደንልሃል፡፡ ከእነርሱ የምትሻትን ታቆያለህ፤ የምትሻትንም ወደ አንተ ታስጠጋለህ፤ በመፍታት ከአራቅሃትም የፈለግሃትን በመመለስ ብታስጠጋ በአንተ ላይ ኃጢአት የለብህም፤ አላህም ዐዋቂ፣ ታጋሽ ነው›› ይላል ቁርአኑ፡፡ ‹‹የሹማ›› ማለት የእናት ወንድም ማለት ሲሆን የሹሜ ማለት ደግሞ ‹‹የእናት እህት›› መሆኑን የቁርአኑ የግርጌ ማስታወሻ ይገልጻል፡፡ ሕጻኗ ሚስታቸው አይሻም ይህንን የነቢያቸውን የመሐመድን ልዩ የጋብቻና የዝሙት ሙብት በተመለከተ ስትናገር ‹‹ጌታህ ከፍተኛ የሆነ የወሲብ ፍላጎትህን በመሟላት ምኞትህን እያፋጠነልህ እንደሆነ ይሰማኛል›› ነው ያለችው፡፡ “Narrated Aisha: I used to look down upon those ladies who had given themselves to Allah's Apostle and I used to say, "Can a lady give herself (to a man)?" But when Allah revealed 33.51, I said to the Prophet, "I feel that your Lord hastens in fulfilling your wishes and desires.” Sahih Bukhari 6:60:311.

5ኛ. የሙስሊሞቹ ነቢይ መሐመድ የግል ሕይወታቸውና ማንነታቸው በጥልቀት ሲታይ እጅግ አስገራሚና አሳዛኝ በሆኑ ድርጊቶች የተሞላ በመሆኑ በእሳቸው ነቢይነት ለማመን ለኅሊና በእጅጉ ይከብዳል፡፡ ይህንንም በአጭሩ ከቁርአኑና ከሐዲሱ ላይ ጥቅሶችን በማስረጃነት እያቀረብኩ ማሳየት ይቻላል፡-

ሲጀመር የልጅነት ሕይወታቸው በጣም አስቃቂ ነበር፡፡ ገና በሕጻንነታቸው ሁለት ሰዎች በመልአክ ተመስለው መጥተው ልባቸውን ቀደው ውስጣቸውን በዘምዘም ውኃ እንዳጠቧቸው ተነግሯል፡፡ ወደፊት በደንብ እናየዋለን፡፡ ይኸው ሁኔታ ቀጥሎ ካደጉም ራሳቸው መሐመድ ሲናገሩ ያን ጊዜ በሕጻንነቴ ልቤን ቀደው ውስጤን በዘምዘም ውኃ ካጠቡኝ ሰዎች መካከል አንደኛው ሰው (እንደሳቸው አገላለጽ መልአኩ ጂብሪል) መካ ወደሚገኘው ሂራ ተራራ ላይ አውጥቶ ከመሬት ላይ ጥሎ አረፋ እስኪደፍቁ ድረስ

ያስጨንቃቸው ነበር፡፡ በዚህም ተጨንቀው ራሳቸውን ሊያጠፉ እንደነበር በሐዲሱ ላይ ተመዝግቧል፡፡ “the Prophet (Mohammad) became so sad as we have heard that he intended several times to throw himself from the tops of high mountains and every time he went up the top of a mountain in order to throw himself down, Gabriel would appear before him and say, "O Muhammad! You are indeed Allah's Apostle in truth" whereupon his heart would become quiet and he would calm down and would return home.” Sahih Bukhari 9:87:111.

እውነቱን እውነት ሀሰቱንም ሀሰት ማለት ተገቢ ነው፡፡ የሙስሊሞቹ ነቢይ መሐመድ የተወለዱት በ570 ዓ.ም ነው፡፡ ‹‹ነቢይ ሆኜ በአላህ ተመርጫለሁ›› ያሉት በ40 ዓመታቸው ነው፡፡ በቁርአኑ ላይ ጂብሪል መርየምን ልጅ እንደምትወልድ እንዳበሰራት በደንብ ተጽፏል፡፡ እንግዲህ መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል ቅድስት ድንግል ማርያምን ‹‹ከሦስቱ ቅዱስ አንዱ ቅዱስ ከአንቺ ይወለዳል›› ብሎ ካበሰራትና ክርስቶስም ወደ ምድር መጥቶ የሰው ልጆችን ሞት በሞቱ ሽሮ ፍጹም ድኅነት ሰጥቶ ካረገ ከ600 ዓመት በኋላ ገብርኤል ስሙን ቀይሮ ‹‹ጂብሪል›› ሆኖ ቃሉንም ለውጦ ‹‹አላህ አይወልድም አይወለድም›› በማለት አስተማረ ብሎ ማመን ለእኔ ከአእምሮ በታች ሆኖብኛል፡፡ ሲጀመር መልአክ የነቢይነትን ጸጋ ሊሰጥ ከአምላክ ተልኮ ከመጣ ልብን ቀዶ ውስጥን በውኃ እያጠበ አረፋም እስኪያስደፍቅ ድረስ እያስጨነቀ ሞትን የሚያስመኝ መልአክ የለም፤ ፈጽሞ ሊኖርም አይችልም፡፡ ከዚህ አንጻር ከነቢያቸው መሐመድ ጋር ማን እንደነበር ለማወቅ በጣም ቀላል ነው፡፡

ሌላው በአፅንዖት ልናየው የሚገባው ነገር የዐረቢያ ምድር ማዕከላዊና የንግድ መናኸሪያ የነበረችው መካ ከተማ ከሙስሊሞቹ ነቢይ ከመሐመድ መወለድ በፊት ከ360 በላይ ጣኦታት ይመለከባት የነበረች ሀገር መሆኗ ነው፡፡ ነቢያቸው መሐመድ ያደጉት የፓጋን ዐረቦችን ሃይማኖታዊና ባህላዊ ሥርዓታቸውን እየፈጸሙ ነበር፡፡ በዐረቢያ ምድር ያለውን ሁኔታ ለመለወጥ በነቢይነት የተነሱት ከተወለዱ ከ40 ዓመት በኋላ ነው፡፡ ይህም ለንግድ ወደተለያዩ ሀገራት (ኢየሩሳሌም፣ ሶሪያ፣ ግብፅ፣ የመን…) ሲሄዱ ባዩት የክርስቲያኖች ሃይማኖት ተነሳስተው «የእኔ ሀገር ሕዝቦች ከአስከፊ ሕይወትና ከጣኦት አምልኮ በወጡልኝ» ብለው ተመኝተው ነጋዴነቱን ትተው ወደ ነቢይነት ተለወጡ፡፡ የመካ ጣኦታትንም አጠፉና «አላህ ብቻ ነው አምላክ እኔም

መልእክተኛው ነኝ» ብለው ጂሃድን ዋነኛ መመሪያቸው አደረጉ፡፡ ነቢያቸው መሐመድ ከጂሃድ ወረራና ጦርነት የሚገኘውም የዘረፋ ገንዘብ እጅግ በርካታ ጦረኛ ተዋጊዎችን እንዲያፈሩ አስቻላቸው፡፡ ለጦረኛ ተዋጊዎቻቸው በዝርፊያው ከሚገኘው ንብረት በጨማሪ ለዝሙት የሚሆኑ ምርኮኛ ሴቶችን ይሰጧቸው ስለነበር ሀገሩን ሁሉ መውረር የሚችል ጦር ለመመስረት ጊዜ አልፈጀባቸውም፡፡ ይህንንም ነቢያቸው መሐመድ ራሳቸው «እኔ አሸናፊ (ባለድል) የሆንኩት በሽብር ነው» በማለት አረጋግጠውልናል፡፡ “Allah’s Apostle said, ‘I have been made victorious with terror.’” Sahih Bukhari: 4፡52፡220. ይህም ማለት በሌላ አገላለጽ «አሸባሪ ነበርኩ» እያሉን ነው፡፡ ቀጥሎ ነቢያቸው መሐመድ የግል ሕይወታቸው የቱን ያህል አስከከፊ ገጽታዎች እንደነበሩት እናያለን፡፡ ለምሳሌ፡-

5.1.የሙስሊሞቹ ነቢይ መሐመድ ይቀሙና ይዘርፉ ነበር /Plunderer/፡- ከዚህ በፊት ያየነውን የቁርአን ጥቅስ እናስታውሰው፡፡ ‹‹ከጦር ዘረፋ ገንዘቦች ይጠይቁሃል፤ የዘረፋ ገንዘቦች የአላህና የመልእክተኛው ናቸው›› ይላል ቁርአኑ፡፡ 8፡1፡፡ ከዚህ በተጨማሪ እነዚህን የሐዲስ ጥቅሶች በደንብ ተመልከቷቸው፡- “Allah's Apostle said, ‘Booty has been made legal for me.’” (Sahih Bukhari 4:53:351), “The Prophet conquered Khaybar by force after fighting. Khaybar was something that Allah gave as booty to His Messenger. He took one-fifth of it and divided the remainder among the Muslims.” Tabari VIII:123.

5.2.የሙስሊሞቹ ነቢይ መሐመድ የሰዎችን አካል በመቆራረጥ ያሰቃዩ ነበር/ Torturer/፡- “they should be murdered or crucified or their hands and their feet should be cut off on opposite sides or they should be imprisoned.” (Qur'an 5:33), “The Prophet then ordered to cut their hands and feet and it was done. Then he ordered for nails which were heated and passed over their eyes, and they were left in the Harra.” (Sahih Bukhari 4:52:261 & Sahih Bukhari 1:4:234)

5.3.ነቢያቸው መሐመድ ያታልሉ ነበር /Deceiver/፡- “When the Prophet intended to go on an expedition, he always pretended to be going

somewhere else, and he would say: 'War is deception.'" Abu Dawud 14:2631.

5.4.የሙስሊሞቹ ነቢይ መሐመድ ይዋሹ ነበር /Liar/፡- "So far as I am concerned, by Allah, if He so wills, I would not swear, but if, later on, I would see better than it, I (would break the vow) and expiate it and do that which is better." Sahih Muslim 15:4044.

5.5.ነቢያቸው መሐመድ ጉቦ (ሙስና) ይሰጡ ነበር /Briber/፡- "So the Quraish and the Ansar became angry and said, 'He (the Prophet) gives the chief of Najd and does not give us.' The Prophet said, 'I give them so as to attract their hearts.'" Sahih Bukhari 4:55:558.

5.6.ነቢያቸው መሐመድ መጠጥ ይጠጡ ነበር /Drinker/፡- "Narrated by Gaber bin Abdullah: We were with the messenger of Allah, and he asked for a drink. One of his men said: "Oh Messenger of Allah, Can we offer you wine to drink?" He said "yes." He (Gaber) went out looking for the drink and came back with a cup of wine. The messenger asked: 'Have you fermented it, even with one piece of ferment?" He (Gaber) said "yes" and he (Muhammad) drank.'" (Sahih Muslim-Hadith #3753), "Narrated Abu Huraira: Allah's Apostle was presented a bowl of milk and a bowl of wine on the night he was taken on a journey (Al-Mi'raj). (Sahih Bukhari 7:69:508)

5.7.የሙስሊሞቹ ነቢይ መሐመድ የዝሙት ሱሰኛ ነበሩ /Sex Addicted/፡- ከአስራ አንድ ሚስቶቻቸው ጋር ግብረሥጋ ግንኙነት ለማድረግ ሁሉንም በአንድ ቀን በተራ ይጎበኛቸው እንደነበር በቡኻሪ ሐዲስ ላይ የተመዘገበውን ቀደም ብለን በፊት አይተናል፡፡ Sahih Bukhari 1:5:268. እንዲያውም ከዚህም በላይ ነቢያቸው የ40 ወንዶችን ያህል ብቃት እንደነበራቸው በሌሎች ኪታቦች ላይ ተጽፏል፡፡ He once said of himself that he had been given the power of forty men in sex. (Mohammad Ibn Saad, al-Tabakat al- Kobra, Dar al-Tahrir, Cairo, 1970, Vol 8, p. 139.)

5.8.መሐመድ ከሕጻናት ጋር ወሲብ መፈጸምን ይወዱ ነበር /Pedophile-sexually

attracted to children/፡- ከ9 ዓመት ሕጻን ልጅ ከአይሻ ጋር በ53 ዓመታቸው ወሲብ መፈጸማቸውን ቀደም ብለን አይተናል፡፡ (Sahih Muslim 8:3310)

5.9.የሙስሊሞቹ ነቢይ መሐመድ ዘረኛ ነበሩ /Racist/፡- ሐዲሱ የነቢያቸው መሐመድን የተለያየ የሰውነት ክፍላቸውን እየጠቀሰ መልካቸው ነጭ እንደነበር ብዙ ቦታ ይናገራል (Sahih Muslim 30፡26, Abu Dawud 20:3200, and Sahih Bukhari 8:78:631), መሐመድ ዐረቦች ከሁሉም የሰው ዘር የበላይ መሆናቸውን አስተምረዋል (Al-Tabari, Vol.9, p.69 & Ibn Sa'd, Vol.1, p.12), በጥቁሮች ላይ ከፍተኛ ጥላቻ ነበራቸው (Sahih Muslim 5:2334 & Sahih Bukhari 1:11:662),

5.10.ነቢያቸው መሐመድ የባሪያ ንግድ ያካሂዱ ነበር /Slaver/፡- (Sahih Bukhari 3፡34፡433), ራሳቸው መሐመድ ሸጠው የለወጧቸው ባሪያዎች ታሪካቸው በሐዲሱ ላይ ተጠቅሷል (Sahih Bukhari 8፡78፡455, Sahih Muslim 10:3901, Sahih Bukhari 3:41:598)

እንዲህ…እንዲህ እያልን ለቁጥር በሚያዳግት ሁኔታ በጣም ብዙ ነገር መዘርዘር ይቻላል፡፡ እኔ እነዚህን ነገሮች ሁሉ የጠቀስኩት ለመንቀፍ ወይ ደግሞ ለመተቸት ብዬ አይደለም፡፡ ይልቁንም በቁርአኑና በሐዲሶቹ ላይ የተጻፈውን ነገር ነው መልሼ የጻፍኩት፡፡ ብዙዎቹ ሙስሊሞች ስለማያውቋቸው የሚያውቋቸውም ቢሆን ደፍረው ስለማይናገሩ ነው እንጂ ቁርአኑና ሐዲሶቹ ስለ መሐመድ ከዚህም በላይ እጅግ ብዙ ነገር ይናገራሉ፡፡ ሰው በሃይማኖታዊ ወይም በሰብዓዊ አስተሳሰብ ነገሮችን መመዘን ባይችል እንኳ እንዴት ሰው ሰውኛ አስተሳሰብ ማሰብ ይሳነዋል!

መጀመሪያ ከሕዝብ ዘንድ ተቀባይነት ሲታጣ ሰይፍን የመጨረሻ አማራጭ አድርጎ መጠቀም፣ በከፉ መንፈስ ተይዞ ራስን ለማጥፋት መሞከር፣ መጠጥ መጠጣት፣ መዋሸት፣ ጉቦና ሙስና መስጠት፣ ማታለል፣ የሰዎችን አካል በመቆራረጥ ማሰቃየት፣ የጅምላ ጭፍጨፋ ማካሄድ፣ መቀማትና መዝረፍ፣ በግል ጉዳይ ሰዎችን በጨለማ ማስገደል፣ ሰዎችን በማሸበር የበላይ መሆን፣ ከ31 በላይ ሚስቶችን በገሃድ ማግባት፣ የተወሰኑ ጎሳዎችን የበላይ አድርጎ በማየት የዘረኝነት አቋም መያዝ፣ የባሪያ ንግድ ማካሄድ፣ ባሎቻቸውን እየገደሉ ሴቶችን ለዝሙትና ባርነት መጠቀም… በመጨረሻም በመርዝ መሞት እንዴት ተደርጎ ነው የነቢይነት መስፈርት የሚሆነው? ምን ዓይነት ከፉ ኅሊና ቢኖር ነው እንዲህ ዓይነቱን ሰው ለነፍስ ይጠቅመኛል ብሎ የሚያስበው? እኔ በበኩሌ ግን ነፍሴን ማዳን ስለምፈልግ ብቻ እስልምናውን ለመተው ተገድጃለሁ፡፡

ከምንም በላይ ደግሞ የሙስሊሞቹ ነቢይ አጠቃላይ አስተምህሮታቸው ምን ይመስል እንደነበር ስናይ ነገሩ ሁሉ የበለጠ ራስ ያማል፡፡

ከላይ የጠቀስኳቸው ሁሉም ነጥቦች ወደፊት በመጽሐፉ ገጾች ውስጥ በደንብ ተብራርተው ስለተቀመጡ ለአሁን ለማሳየት ያህል እነዚህን መጥቀሱ ብቻ በቂ ነው ብዬ አምናለሁ፡፡ አንድ ነገር ግን ሳልጠቅስ አላልፍም፡፡ እነ ሂትለር መሐመድን አርአያ / role model/ አድረገውት ይከሏቸው ነበር፡ እ.ኤ.አ ከታህሳስ 23 ቀን 1805 ዓ.ም እስከ ሰኔ 27 ቀን 1844 ዓ.ም ድረስ የኖረው አሜሪካዊው የሞርሞኒዝም ሃይማኖት መሪ የነበረው ጆሴፍ ስሚዝ /joseph smith/ ነቢይ ነኝ ብሎ በተነሳበት ወቅት በሺዎች የሚቆጠሩ በርካታ ተከታዮችን ማፍራት ችሎ ነበር፡፡ ‹‹የኋለኛው /የፍጻሜው ዘመን ቅዱስ እንቅስቃሴ›› /Latter day saint move-ment/ የሚል መርህ ይዞ የነበረው ይህ ግለሰብ በዘመኑ ‹‹የመርሞን መጽሐፍ›› የሚል የእምነቱ መመሪያ መጽሐፍም አሳትሞ ነበር፡፡ ነገር ግን መጽሐፉን እኔ ጻፍኩት አልነበረም ያለው ይልቁንም ‹‹ሞሮኒ የሚባል መልአክ ነው ከሰማይ ያወረደልኝ›› በማለት ሲያስተምር ያለጥርጣሬ የተከተሉት በሺዎች የሚቆጠሩ ነበሩ፡፡ እንደ እርሱ ትምህርት ሞሮኒ የሚባል መልአክ መገለጦችን በየጊዜው ያመጣለት ነበር፡፡ የጆሴፍ ስሚዝ ተከታዮች በመጨረሻው ዘመን የተገኘ የነቢያት ሁሉ መደምደሚያ እንደሆነ ይመሰክሩለት ነበር፡፡ በካርቴጅ ኢሊኖይስ እስር ቤት ከመታሰሩና ከመሞቱ በፊት የአሜሪካ ፕሬዝዳንት የመሆን ትልቅ ሕልም ነበረው፡፡ ታዲያ ይህ ግለሰብ በሚያስገርም ሁኔታ አርአያ /role model/ አድርጎ የተነሳው የሙስሊሞቹን ነቢይ መሐመድን ነበር፡፡ ራሱ ጆሴፍ ስሚዝ በአንድ ወቅት ሲናገር ‹‹እኔ ለዚህ ተውልድ ሁለተኛው መሐመድ እሆንለታለሁ›› ብሎ የተናገረው ሕዝብ በተሰበሰበብ አደባባይ ነበር፡፡ “I will be to this generation a second Mohammed, whose motto in treating for peace was ‘the Alcoran [Koran] or the Sword.’ So shall it eventually be with us—‘Joseph Smith or the Sword!’” (Fawn M. Brodie, No Man Knows My History, second edition, (New York: Alfred A. Knopf, 1971), p. 230–231) See also “History of the [Mormon] Church, Vol. III, p.167” (Joseph Smith made this statement at the conclusion of a speech in the public square at Far West, Missouri on October 14,

1838.) ጆሴፍ ስሚዝ ከሙስሊሞቹ ነቢይ ከመሐመድ የወረሳቸውን መመሪያዎችና ሁለቱም እርስ በእርስ የሚመሳሰሉባቸውን 17 ነጥቦች ‹‹እናወዳድር እንዴ!›› በሚለው ርዕስ በሰፊው እናየዋለን፡፡

መሐመድ በ627 ዓ.ም ቁጥራቸው ከ800 በላይ የሚሆኑ የባኑ ቁራይዛ የአይሁድ ጎሳዎችን በአንድ ቀን የጂምላ ጭፍጨፋ እንዳካሄደባቸው ከዚህ በፊት በዝርዝር አይተናል፡፡ ይህም ታሪክ በሐዲሱና በቁርአኑ ላይ በጣም ብዙ ቦታ ተመዝግቦ ይገኛል፡፡ የጀርመኑ አዶልፍ ሂትለርም ከ6 ሚሊዮን በላይ አይሁዳውያንን በግፍ ሲጨፈጭፍ ሃይማኖትን መሠረታዊ ጉዳይ አድርጎ ነበር የተነሳው፡፡ ሂትለር በዘመኑ (Mein Kampf) የሚል መጽሐፍ ጽፎ ነበር፡፡ በጣም በሚገርም ሁኔታ የዚህ የሂትለር መጽሐፍ ይዘቱ ከቁርአኑ ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡ ሁለቱም ለተከታዮቻቸው ያስተማሯቸው ትምህርቶችና የፈጸሟቸው ድርጊቶች ተመሳሳይ ናቸው፡፡ ለዚህም ማሳያ ይሆን ዘንድ ከሁለቱም መጽሐፎች (ከቁርአኑና ከሂትለር መጽሐፍ) የተወሰዱ ጥቅሶችን ቀጥለን በዝርዝር እናያለን፡-

1ኛ.መሐመድና ሂትለር ሁለቱም በወቅቱ አይሁዶችን ከምድረ ገጽ ማጥፋት እንዳለባቸው ለተከታዮቻቸው ትእዛዝ ሰጥተዋል፡፡ “Jews are vampires who must die sooner or later. They must be destroyed” (Mein Kampf. P.450) “The Prophet then killed their men and distributed their women, children and property among the Muslims.” (Sahih Bukhari 5:59:362), “Just issue orders to kill every Jew in the country.” (Bukhari:1፡1፡6)

2ኛ. ሁለቱም አይሁዶችን የጨፈጨፉት በአምላካቸው ትእዛዝና ፈቃድ እንደሆነ ተናግረዋል፡፡ ቁርአኑ ‹‹አላህ ነው እንጂ እናንተ አልገደላችኋቸውም›› ይላል፡፡ 8፡17፡፡ ሂትለርም የአምላኩን ፈቃድ ለመፈጸም ሲል ድርጊቱን ተግባራዊ እንዳደረገው ነው የተናገረው፡፡ “It is not ye who slew them; it is God; when thou threwest a handful of dust, it was not thy act, but God’s…..” (The killing of surrendered men of Qurayza tribe was done by the wish of

Allah). (Qur'an, 8:17), "I believe today that I am acting in the sense of the Almighty Creator. By warding off the Jews I am fighting for the Lord's work." (Hitler's speech: 1936, Reichstag), "… We have the right to murder 400,000 to 500,000 people in the Nazi Revolution!" (Hitler's speech: January 30, 1937 Berlin, Reichstag)

3ኛ. ሁለቱም ለተከታዮቻቸው ሽብር በመፍጠር ማጥቃት እንዳለባቸው ትእዛዝ መስጠታቸውንና ማስተማራቸውን በየመጽሐፎቻቸው ላይ በሰፊው ጽፈዋል፡፡ እነርሱም ራሳቸው አሸናፊ የሆኑት በሽብር መሆኑን ተናግረዋል፡፡ "Allah shall cast terror into the hearts of the unbelievers. Strike them above the necks, smite their fingertips". (Qur'an 8፡12), "Allah made the Jews leave their homes by terrorizing them so that you killed some and made many captive. And He made you inherit their lands, their homes, and their wealth. He gave you a country you had not traversed before." (Qur'an 33.26), "Therefore, when you meet the unbelievers smite their necks…" (Qur'an, 47፡4), "Allah's Apostle said, 'I have been sent with the shortest expressions bearing the widest meanings, and I have been made victo-rious with terror.'" (Bukhari: 4፡52፡220), "Spiritual terror...men must threaten and dominate men by compulsion. Compulsion is only broken by compulsion and terror by terror." (Mein Kampf:676), "The importance of physical terror against the individual and the masses also became clear to me." (Mein Kampf.P. 58)

አሁን ደግሞ የሙስሊሞቹ ነቢይ መሐመድ ያስተማሯቸውን ትምህርታቶቻቸውን እንመልከት፡፡ ለምሳሌ ያህል፡-

1ኛ. ሴቶች በሙስሊሞቹ መንግስተ ሰማያት ‹‹በጀነት›› ውስጥ ለዝሙት መጠቀሚያነት እንደሚውሉ ቁርአኑና ሐዲሱን በደንብ ስለሚናገሩ እንዲህ ከሆነማ እስልምናው ለነፍሴ አይጠቅመኝም ብዬ እስልምናን ተውኩት፡፡ (ቁርአን 78፡33፣

55:46-56፣ 56:36, Sahih Bukhari 4:54:476, Al-Tirmidhi, Vol.4, Ch.21, No. 2687)

2ኛ. ነቢያቸው መሐመድ ሙስሊሞችን ምግብ ከበሉ በኋላ በውኃ ከመታጠብ ይልቅ ጣታቸውን እንዲልሱ ወይም ለሌላ ሰው እንዲያስልሱ አዘዋል፡፡ “After eating you should not wipe your hand until you have either licked your fingers or given them to someone else to lick.” Sahih Muslim vol.3 book 21 no.5037-5042 p.1119-1120. See also Abu Dawud vol.3 book 20 no.3838 p.1081. Narrated Ibn 'Abbas: The Prophet said, “When you eat, do not wipe your hands till you have licked it, or had it licked by somebody else.” Sahih Bukhari 7:65:366.

3ኛ. በሙስሊሞቹ ነቢይ በመሐመድ ትምህርት መሠረት ዝንብ በአንድ ክንፏ በሽታን የሚያመጡ ተሕዋሲያንን ብትይዝም በሌላኛው ክንፏ ደግሞ መድኃኒቱንም ጭምር ስለያዘች በመጠጥ ውስጥ ብትገባ አውጥቶ መጣል ተገቢ አይደለም፡፡ ይልቁንም ዝንቧ እዛው መጠጡ ውስጥ እንዳለች መጠጡን መጠጣት ነው መፍትሄው፡፡ The Prophet of Allah said "If a house fly falls in the drink of anyone of you, he should dip it (in the drink), for one of its wings has a disease and the other has the cure for the disease." Sahih Bukhari 4:54:537.

4ኛ. የሙስሊሞቹ ነቢይ መሐመድ የግመል ሽንት መድኃኒት ነው በማለት ለታመሙ ተከታዮቻቸው እንዲጠጡ አድርገዋቸዋል፡፡ Sahih Bukhari 7:71:590.

እስቲ አስቡት! ምግብ የበላበትን የሌላን ሰው እጅ መላስ፣ የግመልን ሽንት ለመድኃኒትነት መጠቀም፣ ዝንብ የገባችበትን የብርጭቆ ውኃ ዝንቧን ሳያወጡ እዛው እንዳለች ውኃውን መጠጣት.... እነዚህ ነገሮች ምን ያሳዩናል? እናም ከጤና አጠባበቅ አንፃር እንደነዚህ ዓይነት የነቢያቸውን የመሐመድን ትምህርቶች በውስጡ የያዘውን እስልምናን ለነፍስም ብቻ ሳይሆን ለሥጋዊ ኑሮም ጤናማ አስተሳሰብ ስለሌለው እስልምናውን ለመተው ተገደድኩ፡፡ በዚያ ላይ ራሳቸው ነቢያቸው መሐመድ የግል ንጽሕናቸውን አይጠብቁም ነበር፡፡ ዘይነብ የተባለችው ሚስታቸው የራስ ፀጉራቸውን ቅማል ትቀምልላቸው እንደነበር በአቡ ዳውድ ሐዲስ ላይ ተመዝግቦ ይገኛል፡፡

"Narrated Zaynab: She was picking lice from the head of the Apostle of Allah while the wife of Uthman ibn Affan and the immigrant women were with him." Abu Dawud 19:3074. ከዚሁ ጋር በተያያዘ አሁንም አንድ ነገር ልጨምር፡፡ የሙስሊሞቹ ነቢይ መሐመድና ተከታዮቻቸው መጥፎ የሰውነት ጠረን ነበራቸው፡፡ "Abu Burdah said: My father said to me: 'My son, if you had seen us while we were with the Apostle of Allah and the rain had fallen on us, you would have thought that our smell was the smell of the sheep.'" Abu Dawud 32:4022. እንዲሁም የመሐመድ ልብሳቸው በዘር ፈሳሽ (sperm cell) ተለውሶ መገኘቱ በሐዲሱ ላይ በግልጽ ተጽፎ እናገኛለን፡፡ ለዚያውም ምንም እንኳን ሚስታቸው አይሻ ልብሳቸውን እያጠበችላቸው ወደ መስጊድ ቢሄዱም ከልብሳቸው ላይ የዘር ፈሳሹ ነጠብጣብና ክብ ምልክቱ አልጠፋም ነበር፡፡ "Narrated Sulaiman bin Yasar: I asked 'Aisha about the clothes soiled with semen. She replied, 'I used to wash it off the clothes of Allah's Apostle and he would go for the prayer while water spots were still visible.'" (Sahih Bukha-ri Volume 1, Book 4, Number 231)

6ኛ. በነቢያቸው መሐመድ ትምህርት መሠረት ሰይጣን ማታ ሰዎች ሲተኙ በአፍንጫ ቀዳዳቸው ውስጥ ተኝቶ ያድራል፤ ስለዚህም ጠዋት ተነስተው ከመስገዳቸው በፊት አፍንጫቸውን መታጠብና ሦስት ጊዜ በውኃ መናፈጥ አለባቸው (Sahih Bukhari 4:54:516)፤ ሙስሊሞች በጠዋት ተነስተው ሶላት ካልሰገዱ ሰይጣን ጆሮቸው ውስጥ ሽንቱን ሸንቶባቸው ያድራል (Sahih Bukhari 2:21:245)፤ እንዲሁም ‹‹ሰይጣን በሚያፋሽጉ ሰዎች ላይ ይስቅባቸዋል›› በማለት ነቢያቸው መሐመድ አስተምረዋል (Sahih Bukhari 8:73:242)፤ ማንኛውም ሕጻን ገና ሲወልድ ሰይጣን ተቆራኝቶ ይዋሐደዋል፤ ይህ ደግም ራሳቸው ነቢያቸውን መሐመድንም ይጭምራል፡፡ Sahih Bukhari 4:54:506. ይህ ብቻ አይደለም የሙስሊሞቹ ነቢይ መሐመድ ‹‹ነቢይ ነኝ›› ብለው ከመነሳታቸው በፊት ስለነበረው ማንነታቸው ራሳቸው መሐመድ ሲናገሩ ሰይጣን ወደ ተራራ ላይ አውጥቶ ራሳቸውን እስኪስቱ ድረስ እንዲሁም በአፍ በአፍንጫቸው አረፋ እስኪደፍቁ ድረስ ልባቸውን እየረገጠ ያስጨንቃቸው እንደነበር ተናግረዋል፡፡ Sahih Bukhari Volume 9, Book 87, Number 111. (ዝርዝር ሁኔታውን ወደፊት በደንብ እናየዋለን) በዚህም ምክንያት መሐመድ ራሳቸውን ከገደል

ላይ ወርውረው ሊያጠፉ ሲሉ መልአኩ ጂብሪል መጥቶ ‹‹አንተ ነቢይ ስለምትሆን ራስህን አታጥፋ›› ብሎ እንዳዳናቸው ተናግረዋል፡፡ በወቅቱ ሁኔታቸውን ያዩ የመካ ሰዎችም ግማሹ ‹‹ይህ ሰው አብዷል›› ሲላቸው ግማሹ ደግሞ ‹‹ሰይጣን ይዞታል›› እያሉ ይዘባበቱባቸው ነበር፡፡ በሌላም በኩል ሚስታቸው አይሻ መሐመድ በአንድ አይሁዳዊ ሰው መተት ተደርጎባቸዋል በማለት ተናግራለች፤ ይህም በሐዲሱ ላይ በግልጽ ተመዝግቦ ይገኛል፡፡ (Sahih Al-Bukhari, Number 3175) & (Ibid, Number 5765)

አሁን እስቲ አንድ ነገር በደንብ እናስብ! የሙስሊሞቹ ነቢይ መሐመድ ከላይ የጠቀስኳቸውን ስለ ሰይጣን ያላቸውን አመለካከት በደንብ ተመልከቱና ከእሳቸው ሕይወት ጋር አነፃፅሩት! ታዲያ በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታ ‹‹ነቢይ ሆንኩ›› ያሉትን መሐመድን እንዴት አድርጌ ነቢይነታቸውን ልመን? ሰይጣን መድኃኔዓለም ክርስቶስን የፈተነበትን መንገዶችና ጌታ ኢየሱስ ፈተናዎቹን እንዴት እንደተወጣቸው አስቡት፡፡ እነዚያ ለጌታችን የቀረቡ ፈተናዎች ለሙስሊሞቹ ነቢይ ሲቀርቡለት እንዴት ተስተናግደው ይሆን? ዓለሙን ሁሉ ያሳተው ዲያብሎስ በረቀቀ መንገድ አንድ ትልቅ ሥራ እንደሠራ በእርግጠኝነት መናገር አንችልም? እስልምናውን የተውሉት ለዚህ ነው፡፡ ሁኔታውን ወደፊት በጣም በጥልቀት እናየዋለን፡፡

7ኛ. ነቢያቸው መሐመድ ለሴቶች እጅግ የወረደ አመለካከት ነበራቸው፡- ለምሳሌ በእሳቸው ትምህርት መሠረት ሴቶች ከወንዶች በግማሽ ያነሱ ናቸው (Qur'an 2:282)፣ ሴቶች በአእምሮአቸው ጎደሎዎች ናቸው(Sahih Bukhari 3:48:826)፤ ብዙዎቹ የሲኦል ነዋሮች ሴቶች ናቸው (Sahih Muslim36:6597)፤ ባለትዳሮችም እንኳ ቢሆኑ ዕድሜዓለቸው ገፋ ያሉ ሴቶች በጎረዳዎች መተካት አለባቸው (Sahih Bukhari 7:62:16)፤ ወንዱ ሲሰግድ አህያ፣ ውሻና ሴት በፊቱ ካለፉ ወንዱን ከጸሎት ያስተጓጉሉታል (Sahih Bukhari 1:9:490)፤ ሴቶች ለወንዶች የሚታረሱ እርሻዎች ናቸው (Qur'an 2፡223)፤ ሴቶች አሻንጉሊቶች ናቸው (Al-Musanaf Vol. 1 Part 2, p. 263)፤ ሴቶች ለወንዶች ጠላቶች ናቸው (Qur'an 2:282)፤ የሰይጣናዊ ወይም የከፉ ነገር ምልክቶች ናቸው (Sahih Muslim 8፡3240 Sahih Bukhari 4:52:110)፤ ጎጂዎችና ከዳተኞች ናቸው (Sahih Bukhari 4:55:547 &

7:62:33)፤ ወንዶች ሚስቶቻቸውን መደብደብ ይችላሉ፣ ራሳቸው መሐመደም ሚስታቸው አይሻን ይደበድቡ ነበር (Qur'an 4:34, Sahih Muslim 4:2127)፤ ባሎቻቸው ሲደበድቧቸው ቅሬታ የሚያቀርቡ ሴቶች ‹‹ጥሩ ሴቶች አይደሉም›› (Abu Dawud 11:2141)፤ ሙስሊም ወንዶች ሴቶቹ ለወሲብ ፍቃደኛ ባይሆኑላቸው እንኳ አስገድደው እንዲደፍሯቸው ተፈቅዶላቸዋል (Qur'an 70:29-30 & Abu Dawud11:2155)፤ የሴት ልጅ መገረዝ እንዳለባት በነቢያቸው መሐመድ ታዟል (Abu Dawud 41:5251)

አራት ሙስሊም ወንዶች አንድን ሴት መጥፎ ሥራ ሠርታለች ብለው ከመሰከሩባት ባዶ ቤት ውስጥ በረሀብ መገደል አለባት /Kill Woman Guilty of Lewdness by Starvation/፡- በቁርአኑ ሱረቱ አል-ኒሳእ 4፡15 ላይ እንዲህ ተብሎ ነው የተጻፈው፡- ‹‹እነዚያም ከሴቶቻችሁ መጥፎን ሥራን የሚሠሩ በነርሱ ላይ ከናንተ አራት ወንዶችን አስመስክሩባቸው፡፡ ቢመሰክሩም ሞት እስከሚደርስባቸው ወይም አላህ ለነርሱ መንገድን እስከሚያደርግ ድረስ በቤቶች ውሰጥ ያዙዋቸው፡፡››

ነቢያቸው መሐመድ ባሎቻቸውን በመግደል ሴቶችን በጦር እየማረኩ ለባርነት ይዳርጓቸው ነበር፡፡ መሐመድ ባካሄዳቸው ጦርነቶች ብዙ ሴት የጦር ምርኮዎችን (war captives) ከወሰዱ በኋላ አንድ አምስተኛውን ለራሳቸው ወስደው የተቀረውን ለተከታዮቹ ያከፋፍሉ እንደነበር በቁርአን 8፡41 እና በሐዲሱ ላይ የተጠቀሰውን ቀደም ብለን አይተናል፡፡ በዚህም መሠረት እነ መሐመድ ምርኮዎቻቸውን ለዝሙትና ለባሪያ ንግድ ነበር የሚጠቀሙባቸው፡፡ ለምሳሌ እነ መሐመድ ካይባርን ከተቆጣጠሩ በኋላ ከጦርነቱ ብዙ ንብረት ዘርፈዋል፣ በረካታ ሴቶችን ማርከው ወስደዋል፡፡ ወንዶቹን ከገደሉ በኋላ ሴት የጦር ምርኮዎቹን በባርነት እንዲይዟቸውና ለዝሙት እንዲጠቀሙባቸው ነቢያቸው መሐመድ ለተከታዮቻቸው ፈቅዶላቸዋል፡፡ ራሳቸውም ያንን አድርገዋል፡፡ “We conquered Khaibar, took the captives, and the booty was collected. Dihya came and said, 'O Allah's Prophet! Give me a slave girl from the captives.' The Prophet said, 'Go and take any slave girl.' He took Safiya bint Huyai. (Sahih Bukhari 1:8:367), The Prophet had their warriors killed, their offspring and woman taken as captives. (Sahih Bukhari 5:59:512) See also: Ishaq:511.

ሴት ልጅ በአጠቃላይ በእስልምናው ውስጥ ለወሲባዊ ተግባርና ለወንዱ መጠቀሚያነት ብቻ የተፈጠረች ተራ ፍጡር ናት፡፡ (Sunaan Abu Dawud: Book 11, Number 2044). ለዚያውም ለወንዱ ወሲብ መጠቀሚያነቷ በምድር ላይ ብቻ ሳይሆን በጀነትም ጭምር ነው! ምሳሌዎችን ልጥቀስላችሁ፡-

ወንዱ መንገድ ላይ ሲሄድ ወይም ሥራ ቦታ ሆኖ ሴት አይቶ ቢመኝ በዚያው አይቶ በተመኘበት ቅፅበት ቶሎ ብሎ ወደቤቱ ሄዶ ሚስቱን አግኝቶ ወሲብ መፈጸም አለበት፤ እሷም እሱን ከቤት ሳትወጣ ቁጭ ብላ መጠበቅ አለባት፡፡ ይህን ስታነሱባቸው ሙስሊሞቹ ‹‹ልክ አይደለም፣ ይሄ ውሸት ነው…›› ይሏችኋል፣ መጽሐፋቸው ላይ ግን የተጻፈውና ነቢያቸውም ያዘዙት እንደዚያ ነው-ሴቷ የባሏን የወሲብ ፍላጎት ለማርካት ብቻ ስለተፈጠረች እቤት ውስጥ ቁጭ ብላ መዋል ነው ያለባት፡፡ (Sahih Muslim Book 008, Number 3240) መመልከት ይቻላል፡፡ በአንጻሩ ግን ሙስሊም ወንዶች እቤት መሄድ ባይፈልጉ እንኳ የፈለጓት ሴት ጋር ሄደው ገንዘባቸውን ከፍለው ወሲብ መፈጸም ይችላሉ፡፡ ገንዘቡን ግን የግድ መክፈል አለባቸው፡፡ ይህም በቁርአን 4:24 ላይ በደንብ ተጠቅሷል፡፡ *‹‹ከሴቶችም በባል ጥብቆቹ፣ እጆቻችሁ በምርኮ የያዙዋቸው ሲቀሩ በናንተ ላይ እርም ናቸው፡፡ ይህን አላህ በናንተ ላይ ጻፈ፤ ከዚሃችሁም ከተከለከሉት ወዲያ ጥብቆች ሆናችሁ ዝሙተኞች ሳትሆኑ በገንዘቦቻችሁ ልትፈልጉ ለናንተ ተፈቀደ፤ ከነርሱም በርሱ በመገናኘት የተጠቀማችሁባቸውን ሴቶች መህሮቻቸውን ግዴታ ሲሆን ስጡዋቸው፡፡ ከመወሰንም በኋላ በተዋደዳችሁበት ነገር በናንተ ላይ ኀጢአት የለም›*› ይላል ቁርአኑ፡፡ ሱረቱ አል-ኒሳእ 4:24፡፡ በዚህ ጥቅስ መሠረት ወንዶች ወሲብ መፈጸም የሚችሉት ካገቧቸው ሚስቶቻቸውና በጦርነት ከማረኳቸው ሴቶች ጋር ነው፡፡ ከእነዚህ ውጭ ዝሙተኞች እንዳይሆኑ ከከለከለ በኋላ እንደገና መልሶ ገንዘባቸውን ከፍለው ዝሙት እንዲፈጽሙ መፍቀድ ምን ማለት እንደሆነ የሚያውቁት ነቢያቸው መሐመድና እነርሱ ብቻ ናቸው፡፡ እኔ ግን እስልምናው ውስጥ በግልጽ የማይነገረውና በድብቅ ተይዞ ያለው ሁሉም ነገር በቃል መግለጽ ከምችለው በላይ ስለሆነብኝ እስልምናውን ለመተው ተገድጃለሁ፡፡ እውነቱን ልንገራችሁና መጀመሪያ ላይ ስለ ክርስትናው እውቀቱም ሆነ ፍላጎቱ ኖሮኝ አይደለም ክርስቲያን የሆንኩት፡፡ ከንቱነቱ ግን እውነትን እንድፈልጋት አስገደደኝ፡፡ እስልምናው ውስጥ ያሉት እጅግ በርካታ አስከፊ ነገሮች ናቸው ሳልፈልግ በግድ ስለ ክርስትናው እንዳውቅና እንዳምን በፍላጎቴም እንድጠመቅ ያስገደዱኝ፡፡ ክርስትናውን በደንብ ሳውቀው ደግሞ ምን ያህል ዕድለኛና የተመረጥኩ እንደሆንኩ ተረዳሁ፡፡

አሁን ደግሞ ስለ ቁርአን የተወሰኑ ነጥቦችን በአጭሩ ላስቀምጥ፡፡ በቁርአኑ ውስጥ የተጻፉና እኔም እስልምናውን እንድተው ካደረጉኝ ምክንያቶች ውስጥ የሚከተሉት ዋናዋና ነጥቦች ይገኙበታል፡-

ነቢያቸው መሐመድ አላህ ወደፊት የሰውን ሥጋ ለብሶ እንደሚገለጥ ለተከታዮቻቸው አስተምረዋቸዋል፡፡ ‹‹አላህን ያለ ጫማ ባዶ እግሩን ሆኖ፣ ያለ ምንም ልብስ እርቃኑን ሆኖ፣ በእግሮቹ እየሄደና ያልተገረዘ ሆኖ ታገኙታላችሁ›› ተብሎ ነው በሐዲሱ ላይ የተጻፈው፡፡ The Prophet of Allah said, "You will meet Al-lah barefooted, naked, walking on feet, and uncir-cumcised." Sahih Bukhari 8:76:531, See also Sahih Bukhari 1:4:238. እንዲሁም ይህ አገላለጽ በሐዲሱ ውስጥ ብዙ ቦታ ተጽፎ ይገኛል፡፡ ይህ ዓይነቱ አስተምህሮ ግን በእስልምናው ተደብቆ ስለኖረና የትም ቢሆን በግልጽ ስለማይነገር እኔ አሁን በሐዲሱ ውስጥ መኖሩን ካረጋገጥኩ በኋላ በእስልምናው ገና ወደፊት ‹‹ይገለጣል›› መባሉ በክርስትናው ደግሞ ‹‹ተገልጧል›› መባሉ ነገሩን በተለየ ሁኔታ በአፅንዖት እንድመለከተው አድርጎኛል፡፡ ምክንያቱም በወቅቱ እምነትን ፍለጋ ላይ ሳለሁ ስለ አምላክ መገለጥ ክርስትናውና እስልምናው ጋር ያለው አስተምህሮ ልዩነቱ የጊዜ ቅደም ተከተል ብቻ ስለሆነብኝ ነው፡፡ በሙስሊሞቹ መጽሐፍ ውስጥ አላህ ወደፊት የሰውን ሥጋ ለብሶ እንደሚገለጥ ከተነገረ ለምንድነው ሙስሊሞች የክርስቲያኖቹ አምላክ በሥጋ ተገልጦ መጥቷል ሲባል የሚቃወሙት? ስለዚህ ሁለቱም ጋር ያለውን አስተምህሮ በደንብ ስመረምረው ልዩነቱ እጅግ ሰፊ መሆኑ ለኅሊና ፍርድ አመቺ ሆኖልኛል፡፡ በእስልምናው አላህ እርቃኑን ሁኖ ወደፊት ለሰው ልጆች የሚገለጠው ለተቃውሞ ሲል ነው፡፡ ማለትም ሐዲሱ እንደሚናገረው አላህ ወደፊት የሚገለጠው ‹‹‹ክርስቲያኖቹ አምላካችን ተገለጠ፣ ተወለደ…› ብለው ማመናቸው ውሸት ነው፣ ይኸው የእኔ አካል ይህን ይመስላል›› ብሎ ሊያሳፍራቸውና በገሃነም እሳት ሊቀጣቸው ነው፡፡

በክርስትናው ግን ስለ እግዚአብሔር መገለጥ ያለው አስተምህሮ ከዚህ በእጅጉ የተለየ ነው፡፡ ከአምላኩ ሕግ ወጥቶ በሥጋም በነፍስም ሞት ተፈርዶበት የነበረውን የሰውን ልጅ ከዘላለማዊ ቅጣት ለማዳንና ወደቀደመ ክብሩ ለመመለስ መድኃኔዓለም የበደለውን የአዳምን ሥጋ ለብሶ የእርሱንም ሞት ሞቶለት ፍጹም ድኅነትን ሰጥቶ ወደ ቀደመ ክብሩ መለሰው፡፡ ቀድሞውንም በበደለ ጊዜ ‹‹ከልጅ ልጅህ ተወልጄ

አድንሃለሁ›› ብሎ ቃልኪዳን ሰጥቶት ነበር፡፡ እናም ክርስቶስ ኢየሱስ የሰው ልጅ ሞት ወስዶ የእርሱን ሕይወት ለዓለሙሉ ሁሉ ሰጠ፡፡ የሰው ልጅ መቼም ቢሆን ከኃጢአት ተጠብቆ ስለማይኖር በሕይወቱ ቢበድል እንኳ የመዳኛን መንገድ ንስሐን አዘጋጀለት፡፡ ይህም እንኳ ባይሆን ሰው ዳግመኛ በነፍሱ እንዳይጠፋ ቅዱሳን ጻድቃን ሰማዕታትን ሁሉ የመዳኛን መንገድ አድርጎ ሰጠው፡፡ እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ሁሉ ብዙ የመዳኛ መንገዶችን ሰጥቷል፣ ነገር ግን ይህ ሳይሆን ቀርቶ የሰው ልጅ አላምን ብሎ በነፍሱ ቢጠፋ ለዚያች ነፍስ ዘላለማዊ ፍርድን ሊሰጥና ዓለምንም ለማሳለፍ መድኃኔዓለም ክርስቶስ በታላቅ ክብር ይመጣል፡፡ ስለዚህ እኔ በበኩሌ ወደፊት የክርስቲያኖችን አምላክ መገለጥ ለማስተባበልና እነርሱንም ለመቅጣት የሚገለጠውን አላህን ሳይሆን በሥጋ ተገልጦ የሰውን ልጆች ሁሉ የሥጋና የነፍስ ሞታቸውን በእርሱ ሞት ፍጹም መዳንን የሰጠውን አምላክ ነፍሴ ስለመረጠች እስልምናን ተውኩት፡፡

ሌላው በእስልምናው እንዳላምን ያደረገኝ ነገር የቁርአን አመጣጥ ነው፡፡ በአማኞቹ ዘንድ እንደሚታሰበው ከሆነ ቁርአኑ በቀጥታ ከሰማይ በአላህ ዘንድ ካለው መዝገብ ተቀድቶ በጂብሪል በኩል ለነቢያቸው ለመሐመድ የመጣላቸው መገለጥ ነው፡፡ ይህም በ23 ዓመታት ውስጥ በየጊዜው ለነቢያቸው ሲገለጥ እንደነበር ይታመናል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ራሱ ቁርአኑ እንደሚያረጋግጠው የሙስሊሞቹ ነቢይ መሐመድ ምንም ስላልተማሩ ማንበብና መጻፍ እንኳ አይችሉም ነበር፡፡ (/// **ጥቅሱን አስቀምጥ** ///) ስለሆነም ነቢያቸው መሐመድ አብደላህ ኢብን ሳድ ኢብን አቢ ሳርህ (Abd Allah Ibn Sa'd Ibn Abi Sarh) የተባለ የግል ጸሐፊ ነበራቸው፡፡ ነቢያቸው መሐመድ ጸሐፊያቸውን «እንዲህ ብለህ ጻፍ…» እያሉ ሲያጽፉት ጸሐፊውም በሀሳብ ይረዳቸውና የራሱንም ሐሳብ እየጨመረ ይጽፍ ነበር፡፡ ይህንንም ሲመለከት ነገሩ ሁሉ ስለገባው ነቢያቸው መሐመድን ትቷቸው ጠፋ፣ እሳቸውም እንዲገድሉት ገዳዮችን ልከውበታል፡፡ ቁርአኑ 6፡93 ላይ ይህንኑ በተወሰነ መልኩ ይገልጸዋል፡፡ ሌሎች የእስልምናውን ታሪክ ከትበው የያዙት መዛግት ደግሞ ጉዳዩን በዝርዝር አስቀምጠውታል፡፡ ወደፊት በደንብ እናየዋለን፡፡ በወቅቱ ከ622 ዓ.ም ጀምሮ ነቢያቸው መሐመድ በእምነት ምሥረታ ላይ እንዳሉ ይቃወሟቸው የነበሩት የራሳቸው ሰዎች ቁርአንን ‹የሌላ ሰው ቃል ነው› እያሉ ይቃወሟቸው እንደነበር ቁርአኑ 74፡24 ተጽፏል፡፡ «ይህ (ቁርአን) ከሌላ የሚቀዳ ድግምት እንጂ ሌላ አይደለም፡፡ ይህ የሰው ቃል እንጂ ሌላ አይደለም» አሉ ተብሎ ነው የተጻፈው፡፡ በአጭሩ ቁርአኑ እንደሚታሰበው ከሰማይ የወረደ ሳይሆን በወቅቱ የነበሩ የተለያዩ የመናፍቃንንና የፍልስፍና አስተምህሮዎችን በአንድ ላይ የያዘ ከመሆኑም ባሻገር ከ15 በላይ የሆኑ ሰዎች

በጸሐፊነትና በአዘጋጅነት የተሳተፉበትና በየጊዜው የተለያዩ ማሻሻያዎች የተደረጉበት መጽሐፍ ነው፡፡ ድርሰቱን በማዋቀር፣ የቁም ጽሕፈቱን በመጻፍ፣ አንቀጾቹን በማሻሻል ወይም በማስተካከል፣ ከአንቀጾቹ ውስጥ የተወሰኑትን በማጥፋት አሊያም የሚፈልጉትን ሀሳብ በማስገባት በርካቶች ተሳትፈውበታል፡፡ እንደዚህም እንኳ ተደርጎ ከስሕተት መጽዳት አልቻለም፡፡ ይህንንም ለማረጋገጥ ብዙ ርቆ መሄድና ምርምር ማድረግ አያስፈልግም፡፡ በይዘቱ ይታወቃል፣ የቁርአኑን የተወሰኑ ገጾች ገልጻችሁ ስታነቡት ሌላው ቢቀር በርካታ የቋንቋ ሰዋ ሰዋዊ ስሕተቶች /grammatical errors/ ያሉት መሆኑን በቀላሉ መረዳት ትችላላችሁ፡፡ ወደፊት በጣም በሰፊው የምናየው ቢሆን ለአሁኑ ግን እኔን በቁርአኑ ላይም ሆነ አጠቃላይ በእስልምናው ፈጽሞ እንዳላምን ያደረጉኝን ምክንያቶች በአጭሩ ላስቀምጥ፡-

1ኛ. ቁርአን በየጊዜው ተለዋዋጭ እንደነበር ራሱ ቁርአኑ ስለሚናገር እኔ በበኩሌ ላምንበት አልቻልኩም፡፡ የአምላክ ቃል ሕያውና ዘላለማዊ ስለሆነ ፈጽሞ ሊለወጥ አይችልም፤ መለወጥም የለበትም፡፡ ቁርአን ግን ተለዋዋጭ መሆኑን በጣም ብዙ ቦታ ይናገራል፡፡ ሱረቱ አል-በቀራህ 2፡106 ላይ እንዲህ ተብሎ ነው የተጻፈው፡- ‹‹ከአንቀጽ ብንለውጥ ወይም እርሷን ብናስረሳህ ከእርሷ የሚበልጥን ወይም ብጤዋን እናመጣለን፤ አላህ በነገሩ ሁሉ ላይ ከሃሊ መኾኑን አታውቅምን?›› ተብሎ ነው ለነቢያቸው መሐመድ የተጻፈላቸው፡፡ እንደዚህ ዓይነት ብዙ የቁርአን ጥቅሶችን ከቁርአኑ ውስጥ ማውጣት እንችላለን፡፡
«ብንሻም ያንን ወዳንተ ያወረድነውን በእርግጥ እናስወግዳለን» (አል-ኢስራእ 17፡86)፤ «በአንቀጽም ስፍራ አንቀጽን በለወጥን ጊዜ አላህም የሚያወርደውን ነገር ዐዋቂ ነው፤ አንተ ቀጣፊ እንጂ ሌላ አይደለህም ይላሉ፤ በእውነት አብዛኞቻቸው አያውቁም» ይላል ቁርአኑ፡፡ አል-ነሕል 16፡101፡፡ ስለዚህ እውነተኛ አምላክ ቅዱስ ቃሉን እንደውሸተኛ ተራ ፍጡር በየጊዜው ሊለዋውጥ ስለማይችል እኔ በበኩል ቁርአኑን የአምላክ ቃል ነው ብዬ ለማመን በፍጹም አልቻልኩም፡፡

2ኛ. ቁርአንን ለማመን ካልቻልኩባቸው ምክንያቶች ውስጥ አንዱ ቁርአን መጽሐፍ ቅዱስን አረጋግጣለሁ ማለቱ ነው፡፡ ቁርአን ፈጽሞ መጽሐፍ ቅዱስን ሊያረጋግጠው ባይችልም ቁርአኑ በራሱ መጽሐፍ ቅዱስን አረጋግጣለሁ ብሎ ተቃራኒው ነኝ ለሚለው የክርስቲያኖች እምነት እውቅና መስጠቱ ነገሩን አስገራሚም አስቂኝም ያደርገዋል፡፡ እነዚህን የቁርአን ጥቅሶች በደንብ ተመልከቷቸው፡-

«ወደ አንተም መጽሐፉን ከበፊቱ ያለውን መጽሐፍ አረጋጋጭና በርሱ ላይ ተጠባባቂ ሲሆን (ቁርአንን) በእውነት አወረድን» (ሱረቱ አል-ማኢዳህ 5፡48)፤ «ቁርአን የሚቀጣጠፍ ወሬ አይደለም፤ ግን ያንን በስተፊቱ ያለውን አረጋጋጭ፣ ለነገርም ሁሉ ገላጭ ነው» (12፡111)፤ «አላህ አወረደው በላቸው፡፡ ያንንም በፊቱ የነበረውን መጽሐፍ አረጋጋጭ መጽሐፍ ነው» (6፡92)፤ «እናንተ መጽሐፉ የተሰጣችሁ ሆይ! ከናንተ ጋር ያለውን የሚያረጋግጥ ሆኖ ባወረድነው ቁርአን እመኑ» (4፡47)፤ «ከእነርሱም ጋር ያለውን መጽሐፍ አረጋጋጭ የሆነ መጽሐፍ ከአላህ ዘንድ በመጣላቸው ጊዜ...» (2፡89)፤ «ቁርአን ከእነርሱ ጋር ላለው መጽሐፍ አረጋጋጭ እውነተኛ ሲሆን ይከዳሉ» (2፡91)፤ «ቁርአኑን ከበፊቱ ለነበሩት መጻሕፍት አረጋጋጭ ለምእመናን መሪና ብስራት ሲሆን በአላህ ፈቃድ በልብህ ላይ አውርዶታል» (2፡97)፤ «ያም ከመጽሐፉ ወዳንተ ያወረድንልህ ከበፊቱ ላለው አረጋጋጭ ሲሆን እርሱ እውነት ነው» (35፡31)... እያለ ለቁጥር በሚያዳግት ሁኔታ ቁርአኑ የመጽሐፍ ቅዱስ አረጋጋጭ መሆኑን በግልጽ ይናገራል፡፡ ለመሆኑ ቁርአን ይህን ያህል ለመጽሐፍ ቅዱስ ታኮ መሆን ለምን ፈለገ? እንዴትስ ተቃራኒው የሆነውን እምነት አረጋግጣለሁ ይላል? እነዚህንና ሌሎችም ጥያቄዎችን ለመመለስ በራሱ ብዙ ስለሚያስኬድ ወደፊት በደንብ እናየዋለን፡፡

3ኛ. ቁርአን ሙስሊሞችን በክርስቲያኖቹ መጽሐፍ እንዲያምኑና የማውቁትም ነገር ሲያጋጥማቸውም ክርስቲያኖቹን እንዲጠይቁ ያዘዘ በመሆኑ እኔም ክርስቲያኖቹን ጠይቄ እውነትን በመመርመር እስልምናውን ለመተው ተገደድኩ፡፡ ቁርአኑ ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ ሳይሆን ስለ ክርስትያኖችም የሚሰጠው ምስክርነት አለ፡፡ ‹‹የመጽሐፉ ሰዎች›› (people of the book) አንዳንድ ቦታ ደግሞ ‹‹የመጽሐፉ ባለቤቶች›› እያለ ክርስትያኖችን ብዙጊዜ ይጠቅሳቸዋል፡፡ (3፡110፣ 4፡115፣ 5፡59፣ 5፡65፣ 5፡68፣ 5፡77፣ 17፡4፣ 98፡6) የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍቶቻቸውም ብርሃን እንደሆኑና ቀጥተኛ መምሪያዎች እንደሆኑ ቁርአኑም ይህን ሊያረጋግጥ እንደመጣ ቁርአኑ ተናግሯል፡፡ ቁርአኑ በዚህ ብቻ አያበቃም ነቢያቸው መሐመድም ሆኑ ተከታዮቻቸው ሙስሊሞች በክርስቲያኖቹ መጽሐፍ እንዲያምኑና የማውቁትም ነገር ቢያጋጥማቸው እንኳ ክርስቲያኖቹን እንዲጠይቁና እንዲረዱ አዟቸዋል፡፡ ቀጥሎ ያሉትን ጥቅሶች ይመለከቱ፡- «እኛ ተውራትን (ኦሪትን) በውስጧ መምሪያና ብርሃን ያለባት ስትሆን አወረድን፤ እነዚያ ትእዛዝን የተቀበሉት ነቢያት በነዚያ ይሁዳውያን በሆኑት ላይ በርሷ ይፈርዳሉ፤ ሊቃውንቱና ዐዋቂዎቹም ከአላህ መጽሐፍ እንዲጠብቁ በተደረጉትና በእርሱም ላይ መስካሪዎች በሆኑት ይፈርዳሉ፤...በፈለጎቻቸውም በነቢያቶቹ ፈለግ ላይ የመሪየምን ልጅ

ዒሳን ከተውራት (ከኦሪት) በስተፊቱ ያለውን አረጋጋጭ ሲሆን አስከተልን፤ ኢንጂልንም (ወንጌልንም) በውስጡ ቀጥታና ብርሃን ያለበት በስተፊቱ ያለችውን ተውራትንም የሚያረጋግጥ ለጥንቁቆችም መሪና ገሳጭ ሲሆን ሰጠነው» (5፡44-46)

«ወደ አንተም ካወረድነው (ቁርአንን) በመጠራጠር ውስጥ ብትሆን እነዚያን ከአንተ በፊት መጽሐፉን የሚያነቡትን ጠይቅ» (10፡94)

«ከአንተም በፊት ወደነሱ የምናወርድላቸው የሆኑ ሰዎችን እንጂ ሌላ አልላክንም፤ የማታውቁ ብትሆኑ የመጽሐፉን ባለቤቶች ጠይቁ» (21፡7)

«አላህ በመልክተኛው ላይ ባወረደው መጽሐፍ በዚያም ከበፊቱ ባወረደው መጽሐፍ እመኑ» (4፡136)... እያለ ቁርአኑ በጣም ብዙ ምስክርነቶችን ከመስጠቱም በላይ በተመሳሳይ አነጋገሮች ታጭቆ እናገኘዋለን፡፡

ታዲያ እንደዚህ ዓይነት ምስክርነቶች በቁርአኑ ውስጥ በስፋት ተጽፈው እያለ በክርስቲያኖቹ መጽሐፍ አለማመን እንዴት ይቻላል? «ከበፊቱ ባወረደው መጽሐፍ እመኑ» ያለው ተውራትን (ኦሪትን) እና ኢንጂልን (ወንጌልን) መሆኑ ለሁሉም ሙስሊም ግልጽ ነው፡፡ ታዲያ ቁርአኑ እንዲህ ብሎ ካዘዘ «የመጽሐፉን ባለቤቶች» ማለትም ክርስቲያኖቹን አለመጠየቅና ቀድሞ በወረደው በመጽሐፋቸውም አለማመን እንዲያውም የቁርአንን ትእዛዝ አለማክበር አይሆንም?

4ኛ. በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉ የብሉይ ኪዳን ታሪኮች በሙሉ በቁርአንም ውስጥ አሉ፤ ሁለት ተቃራኒ በሆኑ ሃይማኖቶችና በመጽሐፎቻቸው ውስጥ እንዴት አንድ ዓይነት ታሪክ ሊገኝ ቻለ? እንደ ተቃራኒነታቸውኮ አንድ ዓይነትና ተመሳሳይ ታሪክ ሊገኝባቸው አይገባም ነበር፡፡ ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስንና ቁርአንን ሁለቱንም አንድ ላይ ይዛችሁ ብታስተያዩአቸው በውስጣቸው ያሉ ታሪኮችን አንደኛው ከአንደኛው ገልብጦ የኮረጀ መሆኑን በቀላሉ በደንብ መረዳት ትችላላችሁ፡፡ የትኛው እንደኮረጀ ግልጽ ነው፤ በይዘቱ ይታወቃል፡፡ ብሉይ ኪዳን ላይ ያሉ ታሪኮች በሙሉ በቁርአኑም ውስጥ ቢገኙም ታሪካቸው ግን በቁርአን ውስጥ በተዘበራረቀና አንዳንዶቹም ፍጻሜ በሌለው መልኩ ነው የተቀመጠው፡፡ ለጊዜው የብሉይ ኪዳኑን ዘመን እንተወውና በክርስቶስ የተመሠረተው የሐዲስ ኪዳን ክርስትናና በነቢያቸው መሐመድ የተመሠረተው እስልምና የ600 ዓመት ልዩነት አላቸው፡፡ ክርስቶስ ካረገ በኋላ እ.ኤ.አ በ570 ዓ.ም ተወልዶ ከ622 ዓ.ም በኋላ ነው ነቢያቸው መሐመድ እስልምናን የመሠረቱት፡፡

እስልምናውን ነቢያቸው መሐመድ እንደመሠረቱት በቁርአኑ ላይ በተደጋጋሚ

ተጠቅሷል፡፡ «እኔም የሙስሊሞች መጀመሪያ ነኝ» (ሱረቱ አል-አንዓም 6፡163)፤ «የሙስሊሞችም መጀመሪያ እንድኾን ታዘዝኩ» (ሱረቱ አል-ዙመር 39፡12) ተብሎ ነው ስለ መሐመድ የተጻፈው፡፡ መቼም ካልነበረና ገና ወደፊት ከሚኖር ነገር ላይ ተገልብጦ አይወሰድምና ታሪኮቹን መጽሐፍ ቅዱስ ከቁርአን ገልብጦ ወስዷል ብሎ ማሰብ አይቻልም፡፡ ስለዚህ እርግጠኞች ሆነን መናገር የምንችለው ነገር ታሪኮቹን ቁርአን በትንሹ 600 ዓመት ከሚቀድመው ከመጽሐፍ ቅዱስ ገልብጦ ወስዷል፡፡ በዚያ ላይ ከላይ በቁ.3 እንዳየነው ቁርአኑ ራሱ ‹መጽሐፍ ቅዱስን ለማረጋገጥ ነው የመጣሁት› እያለ ምስክርነት መስጠቱን ልብ ማለት ያስፈልጋል፡፡ እኔ አንድም ቁርአንን ላምነው ያልቻልኩበት ዋነኛው ምክንያት በውስጡ ያሉት ታሪኮች ከመጽሐፍ ቅዱስ ብቻም ሳይሆን ከሌሎች እምነቶችም የተኮረጁ በመሆናቸው ነው፡፡ ቁርአን በወቅቱ ከነበሩት ዞራስትርያን ከሚባሉ መናፍቃንና ከአይሁድ ታልሙድ መጽሐፎች እንዲሁም ከክርስትናው የተውጣጡ ታሪኮችን በውስጡ አጭቆ የያዘ መጽሐፍ ነው፡፡

በጣም የሚገርም ሁኔታ ሌላው ቢቀር በክርስትናው ያሉትን ቅዱሳን ቁርአኑ ታሪካቸውን ገልብጦ ሲወስድ ለየት ያለ የስም ለውጥ እንኳን አላደረገባቸውም፡፡ የመጽሐፍ ቅዱሱን «ሙሴን» ቁርአኑ «ሙሳ» ብሎ ነው የቀየረው፡፡ ሌሎቹንም እንዴት እንደቀየራቸው ተመልከቱ፡- አዳምን አደም፣ ሔዋንን ሐዋ፣ አብርሃምን ኢብራሂም፣ ኖኅን ኑኅ፣ ዳዊትን ዳውድ፣ ሰለሞንን ሱለይማን፣ ሎጥን ሉጥ፣ ዮናስን ዩኑስ፣ ይስሐቅን ኢስሐቅ፣ ኤልያስን ኢልያስ፣ እስማኤልን ኢስማዒል፣ ያዕቆብን ያዕቁብ፣ ዮሴፍን ዩሱፍ፣ አሮንን ሐሩን...... እየተባሉ ነው በቁርአን ውስጥ የተለወጡት፡፡ መጥምቁ ዮሐንስን የሕያ ሲለው አባቱን ዘካርያስን ደግሞ ዘከሪያ፣ ገብርኤልን ጂብሪል፣ ሚካኤልን ሚካል፣ ድንግል ማርያምን መሪየም፣ ኢየሱስን ዒሳ በማለት ቁርአኑ ያን ያህል የተለየ የስም ለውጥ እንኳ አላደረገም፡፡ ታሪካቸው በቁርአኑ ውስጥ የተቀመጠው የታሪክ ፍሰቱን ባልጠበቀ መልኩ ከመሆኑም በላይ ሐሰተኛና ትርጉም አልባ በሆኑ ክስተቶች ነው ታሪኮቹ የተቋጩት፡፡ ይህንንም ለማሳየት በሁለቱም መጽሐፎች ውስጥ አንዳንድ ታሪኮች የተጻፉበትን መንገድ ወድሰን በዝርዝር በኋላ በደንብ የምናየው ቢሆንም ለአሁኑ ግን የችግሩን መነሻ ልጠቁም፡፡

ሕግ ጥሶና የሃይማኖት ሕፀፅ ተገኝቶበት ከሶሪያ ገዳም ተወግዞ የተለየ ባሂራ የተባለ ክርስቲያን መነኩሴ ነበር፡፡ ከገዳሙ ሲባረር በንዴትና በእልህ ወደ ዐረቢያ ምድር መዲና ሄዶ በዚያ መኖር እንደጀመረ ከሙስሎሞቹ ነቢይ ከመሐመድ ጋር ተገናኝቷል፡፡ በወቅቱ ነቢያቸው መሐመድም አዲሱን እምነታቸውን የሚመሠርቱበት ወቅት ስለነበር ይህን አኩራፊ መነኩሴ በደንብ ተቀብሎ አስተናግደውታል፡፡ መነኩሴውም

ክርስትናውን በደንብ ነግረዋቸው መጽሐፎቹንም ለመሐመድ አሳልፎ እንደሰጣቸው በታሪክ መዛግብት ላይ በደንብ ተመዝግቦ ይገኛል፡፡ (በኋላ ላይ በደንብ እናየዋለን) በአጭሩ ግን ቁርአኑ ውስጥ ከክርስትናው ጋር በተገናኘ የተጻፉት ታሪኮች በሙሉ ምንጫቸው ይህ መነኩሴና መጻሕፍቶቹ ናቸው፡፡ ዛሬ ላይ ለሚታየው የእምነት ቅሰጣና የታሪክ ግልበጣ ችግር ዋነኛ ተዋናዩ ይህ አኩራፊ መነኩሴ ነው፡፡ አቀናባሪው ደግሞ ዓለምን ሁሉ የሚያስተው አጅሬ ዲያብሎስ እንደሆነ ግልጽ ነው፡፡

5ኛ. ቁርአን ታማኝ ካልሆነባቸው ምክንያቶች ውስጥ አንዱ ከዐረብኛ ውጭ የሆኑና ከሌሎች ቋንቋዎች የወረሳቸው ባዕድ ቃላት በመኖራቸው ነው፡፡ ቁርአኑ 26፡195 ላይና በሌሎችም ቦታዎች ላይ ቁርአን በዐረብኛ ቋንቋ ብቻ የተጻፈ እንደሆነ ተጠቅሷል፡፡ ነገር ግን ቁርአን በውስጡ ከሌሎች ቋንቋዎች የወረሳቸውን ማለትም ከግብፅ፣ ከአረማይክ፣ ከግእዝ፣ ከሳባውያን...የተውጣጡ በርካታ ባዕድ ቃላትን ሲጠቀም እናገኘዋለን፡፡ ለምሳሌ ለማሳያ ያህል፡- ቁርአኑ በዐረብኛ ‹‹ጀነት›› ማለት ሲችል ‹‹ኤደን›› የሚለውን የዕራይስጥ ቃል ይጠቀማል፡፡ ቁርአኑ በዐረብኛ ‹‹ባስራ›› ማለት ሲችል ‹‹ኢንጂል›› የሚለውን የግሪክ ቃል ይጠቀማል፡፡ ቁርአኑ በዐረብኛ ‹‹የሹዋ›› ማለት ሲችል ‹‹ኢሳ›› የሚለውን የሶሪያ ቃል ይጠቀማል.... እንዲህ እያልን በጣም ብዙ ባዕድ ቃላትን ከቁርአን ውስጥ ማውጣት እንችላለን፡፡ ቁርአን በዐረብኛ ቋንቋ ብቻ የተጻፈ እንደሆነ እየተናገረ እንደገና መልሶ የሌሎችን ባዕድ ቃላት መጠቀሙ ይህ በራሱ በውስጡ ያሉት ታሪኮች ከሌሎች የተኮረጁ ለመሆናቸው ምስክር ነው፤ ሙሉ ይዘቱ ጠለቅ ተብሎ ከታየ ደግሞ ማንነቱ ፍንትው ብሎ ይታያል፡፡

6ኛ. ሌላው ማየት የሚገባን ነገር ቁርአንን በጊዜ ሂደት ያሻሻሉትና ያስተካከሉት ሰዎች ከቁርአኑ ውስጥ ብዙ እየተሰረዙ እንዲጠፉ ያደረጓቸው ጥቅሶች በመኖራቸው እኔ ቁርአንን እንዳላምነው አድርጎኛል፡፡ የተሰረዙትን የቁርአን ጥቅሶችንና /Cancelled Verses/ የጠፉ የቁርአን ጥቅሶችን /Lost Verses/ ወደፊት በዝርዝር እናያቸዋለን፡፡

7ኛ. ቁርአን በነቢያቸው በመሐመድ የግል ጸሐፊ አማካኝነት የተጻፈ ስለሆነ እኔ ቁርአንን መለኮታዊ ነው ብዬ ላምንበት ፈጽሞ አልችልም፡፡ ሲጀመር ቀደም ብለን እንዳየነውና ወደፊትም በደንብ እንደምናየው የሙስሊሞቹ ነቢይ መሐመድ መለኮታዊ መልእክትን ከእውነተኛው አምላክ ከሰማይ ለመቀበል የሚያስችል ማንነትና ስብእና

የላቸውም፡፡ ቀደም ብለን እንዳየነውና ወደፊትም በደንብ እንደምናየው የነቢያቸው የመሐመድ ትምህርታቸውና የሕይወት ተሞክሯቸው በብዙ አስከፊ በሆኑ ገጽታዎች የታጀበ በመሆኑ ነቢይነታቸውን አምኖ ለመቀበል ሙሉ በሙሉ ለጎሊና በጣም ፈታኝ ሆኖ አግኝቼዋለሁ፡፡

8ኛ. በአጠቃላይ ቁርአን ወደፊት ስለሚሆነው የዓለም ክስተት ምንም ነገር አለማወቁና ትንቢቶችንም በውስጡ አለማካተቱ የሰዎች ቅንብር መሆኑ ያስታውቃል፡፡ በዚያ ላይ የጀመረውን ሀሳብም ሆነ ታሪክ አይይጨርስም፤ መጽናኛ ቃላት የሉበትም ይልቁንም በማስፈራሪያና በዛቻ ቃላት የተመላ ነው፤ ‹‹ቁረጠው፣ ፍለጠው›› በሚሉ የጂሃድ አንቀጾች የታጨቀ ነው፡፡ ቁርአን አጠቃላይ ይዘቱ በጣም አሰልቺና አድካሚ ነው፤ የተለያዩ ምንጮችና ጸሐፊዎች አሉት፤ በቋንቋ ሰዋሰዋዊ ስሕተቶች /grammatical errors/ የተሞላ ነው፤ ከምንም በላይ ደግሞ ቁርአኑ ለመሐመድ ሰይጣናዊ በሆነ መንገድ የተገለጠ በመሆኑ እኔ በፍጹም ላምንበት አልቻልኩም፡፡ እነዚህን ነገሮች ሁሉ ወደፊት በዝርዝር ስለምናያቸው ለማረጋገት እንዲያመች ሲባል ወደፊት በደንብ ስናየው ያንጊዜ ቢቻል ካገኙት ቁርአኑን በእጅዎ ቢይዙት ይመረጣል፡፡

9ኛ. ቁርአን ስለ ክርስቶስና ስለ ቅድስት እናቱ ድንግል ማርያም የሚመሰክር በመሆኑ እኔም ስለ እነርሱ በደንብ ካወኩ በኋላ እስልምናን ተውኩት፡፡ በሱረቱ አል-መርየምና ሌሎቹም የቁርአን ምዕራፎች ላይ ስለ ክርስቶስና ስለ ቅድስት እናቱ ድንግል ማርያም ብዙ ነገር ተጽፏል፡፡ በአንጻሩ ግን በክርስቲያኖቹ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስለ እስልምናውም ሆነ ስለ ሙስሊሞቹ ነቢይ ስለ መሐመድ ምንም የተጻፈ ነገር የለም፡፡ አሁን በቅርብ ጊዜ ብቅ ያሉ ሙስሊም መምህራኖቻቸው በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከሦስቱ አካል አንዱ ስለሆነው ስለ መንፈስ ቅዱስ የተነገሩትን ጥቅሶች ለነቢያቸው መሐመድ እንደተነገሩ አደርገው ወደራሳቸው በመለጠፍ የሆነ ራስንም የማታለል ዓይነት ሥራ በቅርቡ እንደሠሩ አስታውሳለሁ፡፡ ወደ እውነታው ስንመጣ ግን መጽሐፍ ቅዱስ ነቢያቸውንም ሆነ እምነታቸውን ፈጽሞ አያውቃቸውም፡፡ ቁርአኑ ግን ስም እየጠቀሰ ስለ ክርስትስና ስለ ቅድስት እናቱ ድንግል ማርያም ይመሰክራል፡፡ ይህ በራሱ ስለ ክርስትናውና ስለ እስልምናው ብዙ እንድጠይቅና እንዳውቅ እረድቶኛል፡፡ በሱረቱ አል-መርየም ሙሉ ምዕራፍ ላይ፣ በሱረቱ አል-ዒምራን 3፡42-49 እና በሱረቱ አል-ማኢዳህ 5፡110 ላይ ክርስቶስ ከሴቶች ተለይታ ከተመረጠች ከድንግል ማርያም በደንግልና መወለዱንና በኋላም ያደረጋቸውን ተአምራቶች ማለትም ዕውራንን

ማብራቱን፣ ሙታንን ማስነሣቱን፣ ለምፃሞችን ማንፃቱን፣ ድውያንን መፈወሱን፣ መና ከሰማይ ማውረዱን፣ የሕይወት ፈጣሪ መሆኑን፣ ሁሉን ዐዋቂ መሆኑን ቁርአኑ በትክክል ይመሰክራል፡፡

ቁርአኑ ስለ ክርስቶስ ከሚሰጣቸው ምስክርነቶች ውስጥ እኔን በእጅጉ የሚያስገርመኝ አንድ የቁርአን ጥቅስ አለ፡፡ ‹‹ሰላምም በኔ ላይ ነው፤ በተወለድሁ ቀን በምሞትበትም ቀን ሕያው ሆኜ በምቀሰቀስበትም ቀን፤ ይህ የመርየም ልጅ ዒሳ ነው፤ ያ በርሱ የሚጠራጠሩበት እውነተኛ ቃል ነው›› ይላል ቁርአኑ፡፡ ሱረቱ መሪየም ምዕራፍ 19፡33-34፡፡ ይህ ምን ማለት ነው? ቁርአኑ እንዴት እንዲህ ብሎ ሊመሰክር ቻለ? ‹‹አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ በአብ ልብነት ያስባሉ፣ በወልድ ቃልነት ይናገራሉ፣ በመንፈስ ቅዱስ እስትንፋስነት ሕያው ይሆናሉ›› የሚለው አእማደ ትምህርት የእውነተኛው ክርስትና ዋነኛና መሠረታዊ አስተምህሮት ነው፡፡ የቁርአኑን አገላለጽ በደንብ ካስተዋልነው ይህ የቁርአን ምስክርነት የክርስትናውን ዋነኛ አስተምሮት ነው እየመሠከረ ያለው፡፡ ‹‹ይህ የመርየም ልጅ ዒሳ ነው፤ ያ በርሱ የሚጠራጠሩበት እውነተኛ ቃል ነው›› ማለትኮ ‹‹አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ በወልድ ቃልነት ይናገራሉ›› ማለት ነው፡፡ ስለዚህ ‹‹ቁርአኑ በእዚህ ዓይነት ሁኔታ ስለ ክርስቶስና ስለ ድንግል ማርያም የሚመሰክር ከሆነ ታዲያ ለምን እስልምናውም ሆነ ክርስትናው በትክክል ስለ እነርሱ የሚያስተምሩትን አውቄ በእነርሱ አላምንም?›› ብዬ አሰብኩ፡፡ ምክንያቱም ቁርአኑ እስከመሰከረላቸው ድረስ ስለ እነርሱም በደንብ አውቄ የማመን ግዴታ ስላለብኝ ነው፡፡ በቃሉ እንዳልጠራጠርበት አይደል ቁርአኑ እየነገረኝ ያለው! ስለዚህ በሁለቱም እምነቶች በእስልምናውና በእውነተኛው ክርስትና በኦርቶዶክስ ተዋሕዶ እምነት ውስጥ ስለ ክርስቶስና ስለ ድንግል ማርያም ያለውን አስተምህሮ በትክክል ከተረዳሁ በኋላ በክርስትናው ለማመን ተገደድኩ፡፡ ሰው ወይም ሌላ ነገር ሳይሆን እውነት ራሷ አስደደችኝ፡፡

10ኛ. ከእኔ በእጅጉ በተሻለ ሁኔታ ቁርአኑንና ሐዲሱን በደንብ ጠንቅቀው የሚያውቁት በውጭ ሀገር ያሉ እስልምናውንም ለ40ና 30 ዓመት ሲያስተምሩ የነበሩት የቀድሞ ሙስሊሞች ስለ እስልምናው ያስተማሩት ትምህርት እውነት መሆኑን በደንብ መርምሬ ካረጋገጥኩ በኋላ እስልምናን ተውኩት፡፡

በመሠረቱ አንድን ሃይማኖት የሰዎች ምስክርነት አያቀናውም፡፡ አንድን እምነት እውነተኛ ነው ለማለት የግለሰቦችን ምስክርነት ማረጋገጫ አድርጎ ማቅረቡ በራሱ

ውድቀት ነው በእውነት! ምክንያቱም የእውነተኛው ሃይማኖት መገኛው እውነተኛው አምላክ እንጂ ተለዋዋጭ የሆነው ተራ ፍጡር አይደለም፡፡ እውነትን ለመፈለግ ሲባል ምስክርነት የሰጡትን ሰዎች ሀሳባቸውንና ያነሷቸውን ነጥቦች እንደ አንድ መነሻ ወይም ግብአት ወስዶ መጠቀም ይቻላል፡፡ ነገር ግን ሰዎች ስለመሰከሩለት ብቻ ያ እምነት እውነተኛው እምነት ነው አያሰኘውም፡፡ በምስክርነቱ ላይ የተነሱትን ሀሳቦች እንደ መነሻ ሀሳብ ወስዶ እነዚያን ሀሳቦች ከሌሎች የበላይ ካሉ መምህራን ጠይቆና ተረድቶ እውነቱን ማረጋገጥ ተገቢ ነው፡፡ መሆንም ያለበት እንደዚያ ነው እንጂ ሰው ስለመሰከረለት ብቻ ያ ምስክርነት የተሰጠለት እምነት እውነተኛ ሃይማኖት ሆኖ ተረጋገጠ ማለት አይደለም፡፡ ነገር ግን በምስክርነቱ ውስጥ የተነሳውን ሀሳብ ይበልጥ በስፋትና በጥልቀት ለመመልከትና ተጨማሪ ጥናትም ለማድረግ እጅግ አመቺ ነው፡፡ በሩንም ይከፍታል፡፡ ከዚህ አንጻር ስለ እስልምናውም ሆነ ስለ ክርስትናው በቀድሞ አማኞቻቸው አማካኝነት የተሰጡትን ምስክርነቶች እንደመነሻ መጠቀሙ ተገቢ ነው፡፡ እስቲ የተወሰኑትን ቀጥሎ እንመልከታቸው፡-

ባለፈው ኢትዮጵያ ውስጥና በዐረቡ ዓለም ያሉ ሙስሊሞች አንድን መነኩሴ አሰለምን በማለት ሌሎችንም ለማስለሚያነት ሊጠቀሙበት ሲሞከሩ መታየታቸው በእጅጉ አስገርሞኛል፡፡ ምክንያቱም ሲጀመር 27 ዓመት መነኩሴ ነበርኩ ያለው ወንድሜ ካሊድ ካሳሁን እንኳን 27 ዓመት ቀርቶ አንድም ዓመት እውነተኛውን ክርስትና ሲማርና ሲያስተምር የኖረ እንዳልሆነ ሁለመናው ያሳብቅበታል፡፡ በዚያ ላይ ከጀርባው ያለውን እውነት ስንመረምረው ነገሩ ሁሉ ድራማ መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ ምክንያቱም ካሊድ ከመጀመሪያው ጀምሮ «በየገዳማቱ እየዞርኩ አስመስክሬአለሁ፤ ክርስትናንም አስተምሬአለሁ» ያላት ነገር ገና ከመነሻው በዕቅድ ተይዛ የተደረገች ነገር ናት፡፡ ማለትም በየጉባኤ ቤቶቹ እየገባ ሲማር የነበረው አሁን ለተነሳበት ዓላማ ሲል ነበር፡፡ መጀመሪያ በገዳም ሳለ ከተመለመለ በኋላ «እንዲህ ነበርኩ» ለማለት ያህል ብቻ እንዲያመቻው በማሰብ ከፍተኛ ገንዘብ ከዐረቡ ዓለም ተመድቦለት የዓላማ ሥራ ነበር ሲሠራ የኖረው፡፡ «ግእዝ ቋንቋንና ሌሎችንም የቤተክርስቲያን ትምህርቶች እዚህ ቦታ ከእከሌ ተምሬ አስመስክሬአለሁ» በማለት ሊቅነትን ለራስ ወስዶ በመለጠፍ ታዋቂነትን በማግኘት ብዙዎችን ለማስለም ከፍተኛ ጥረት ተደርጓል፡፡ (በነገራችን ላይ በዐረቡ ዓለም ያሉ ሙስሊሞች ከፍተኛ ገንዘብ ፈንድ በማድረግ ለወደፊቱም ለ10 እና ለ20 ዓመት ዕቅድ ይዘው በአብነት ተማሪዎችና በመነኮሳት ላይ ከፍተኛ ሥራ እየሠሩ እንደሆነ ተደርሶበታል) ካሊድ ካሳሁንም የዚሁ አንዱ አካል ነበር፡፡ ነገር ግን እርሱም ሆኑ ከጀርባው ሆነው ድራማውን ያቀናብሩ የነበሩ ሙስሊሞች ያልተረዱት አንድ

ትልቅ ነገር አለ፡፡ ይህም አንድን እምነት ምን እንደሚል ማወቅና በእምነቱ ውስጥ በተግባር መኖር ሁለቱ ፍጹም የተለያዩ ነገሮች መሆናቸውንም ለይተው አለማወቃቸው በራሱ አስገምቷቸዋል፡፡ ካሊድ ከመሻው ከገዳም ውስጥ ከተመለመለ በኋላ በተጠና ዕቅድና ዓላማ ተጉዞ ስለ ክርስትና ተምሯል፣ ክርስትናው ምን እንደሚመስል አውቋል ነገር ግን ክርስትና ግን ምን እንደሆነ አላወቀውም፡፡ ካሊድ ሲናገር «አምላክ እንዴት ይራባል? ይጠማል? እግዚአብሔር ራሱ እኔ አንድም ሦስትም ነኝ አላለም፤ ምንኩስና ስለማያስፈልግ አሁን እስላም ሆኜ ሚስት አግብቼ እየኖርኩ ነው….» እያለ ነው ክርስትናውን የተወበትን ምክንያት የተናገረው፡፡ ካሊድ ሆይ! ምንኩስና አያስፈልግም ከማለት ይልቅ «ፈተናውን መቋቋም አልቻልኩም ፍትወትና ዝሙት አማረኝ» ማለት ቀላል አገላለጽ ነበርኮ! ስለ ትምህርቱም ላነሳኸው ሀሳብ አይደለም ሊቃውንተ ቤተክርስቲያንን አንድ የ12 ዓመት የሰንበት ት/ቤት ተማሪን ስለ ምሥጢረ ሥላሴና ስለ ምሥጢረ ሥጋዌ ብትጠይቀው ኖሮ በደንብ ያስረዳህ ነበርኮ! እነ አርዮስም ታላቅ የቤተክርስቲያን ሊቅ ነበሩ ግን በነበሩ ቀሩ፡፡ አንተም ዛሬ ቅድስት ቤተክርስቲያንን በስሟ ልትነግድባት «ነበርኩ» ለማለት በቃህ፤ እንዲያውም ለእነ አርዮስ ጠበቃ ሆነህ «እነርሱም መወገዝ አይገባቸውም ነበር» አልክ፡፡ እስቲ ክርስትናውን ለጊዜው እንተወውና የእውነት ካሊድ እንዲያው ምን አይተህ ወደ እስልምናው መጣህ? በሞቴ ካሊድ ካለህበት ሆነህ በኢሜይል አድራሻዬ ጻፍልኝ!? ለምን ወደ እስልምናው እንደመጣህ ስለ ገንዘብም ብለህ የተታለልክበትን እምነት እውነተኛውን እስልምና ምን እንደሚመስል ላሳይህ ስለፈለኩ ነው እኔ አንድም ይህን መጽሐፍ ያሳተምኩት እንጂ መጀመሪያ ለማሳተም ፍላጎቱ አልነበረኝም፡፡ መጽሐፉ ለአንተ ይድረስህ አይድረስህ ባላውቅም መጽሐፉ ግን ገና ሳይታተም በተወሰኑ ኮፒዎች ብቻ በእስልምናው ውስጥ ያሉ ንጹሕ ልቡና ያላቸው ብዙ ሙስሊሞችን ካሉበት ሕይወት ነቅሎ አውጥቷቸዋል፡፡

ሙስሊም ወገኖቼ ሆይ! እንደነካሊድ ባሉ ሰዎች የተቀናበረ ምስክርነትን ካነሳችሁ አይቀር እስቲ እኔም የተወሰኑ ምስክርነቶችን ልጥቀስላችሁ፡-
ዕድሜውን ሙሉ ቁርአንን፣ ሙዓዚንን፣ ሂድስን ተፍሲርንና ሌሎችንም በተለያዩ የዓለም ኢስላም ሀገራት ማለትም በየመን፣ በፓኪስታን፣ በአፍጋኒስታን፣ በሶማሊያ፣ በጂቡቲ፣ እንዲሁም በአውስትራሊያ፣ በኬንያ፣ በኡጋንዳና በሌሎቹም ሀገራት እስልምናን ዞሮ ከ35 ዓመታት በላይ ያስተማረው ሼህ ረመዳን ሙስጠፋ በመጥምቁ ዮሐንስ እጅግ አስገራሚ ተአምር በክርስትናው አምኖ ሲጠመቅ ምን ተሰማችሁ?

ሼህ ረመዳን ሙስጠፋ ማለት የአዲስ አበባ እስልምና ጉዳዮች ጽ/ቤት ምክትል

ፕሬዝዳንትና የአንዋር መስጊድ አስተባባሪ ኮሚቴ የነበሩት የሐጂ ሙስጠፋ ጣሂር ልጅ ነው፡፡ ሼህ ረመዳን ሙስጠፋ ክርስትና ከኢትዮጵያ ጠፍቶ እስልምና እንዲስፋፋ በቃልቻ ድግምት አሠርቶና በሰውነቱ ላይ አስቀብሮ እስልምና እምነቱን ለማስፋፋት በከፍተኛ ሁኔታ ሲንቀሳቀስ ነበር፡፡ ሼህ ረመዳን ሙስጠፋ በኋላ ላይ አምኖ የተጠመቀው እንደ ካሊድ በከፍተኛ የገንዘብ ኃይል በተቀናበረች ሴራ ሳይሆን መጥምቁ ዮሐንስ በራእይ በተደጋጋሚ ተገልጦለት «አንተም ሆንክ የታመመችው ሚስትህ ሸንኮራ ዮሐንስ ሄዳችሁ ካልተጠመቃችሁ አትድኑም» ብሎት ነው፡፡ ለበርካታ ዓመታት እስልምናን በዓለም ላይ እየዞረ ሲያስተምር የነበረው ሼህ ረመዳን ሙስጠፋም መጀመሪያ ይህ ሲነገረው በእልህ እምቢ ቢልም በኋላ ራእዩ ሲደጋገምበትና ሚስቱም በብዙ ህክምና ስላልተሻላት ሸንኮራ ዮሐንስ ሄደው ሲጠመቁና ጸበሉን ሲጠጡ ከሚስቱ ሆድ ውስጥ እባብ፣ እንቁራሪትና የተለያዩ ነፍሳት ወጣላት፡፡ መጥምቁ ዮሐንስም ለሼህ ረመዳን ሙስጠፋ በተደጋጋሚ በራእይ ተገልጦለት አምኖ የልጅነት ጥምቀትን ካተጠመቀ በቀር ለነፍሱ ድኅነት እንደማያገኝ ነገረው፡፡ ክርስትናን ከአባቶች ሲማር ከቆየ በኋላ ያ ሁሉ የእስከዛሬ ልፋቱና ድካሙ ከንቱ መሆኑን ተረድቶ አምኖ ተጠመቀ፡፡ ሼህ ረመዳን ሙስጠፋ ራሱ በ1995 ዓ.ም የሰጠውን ሙሉ የቪዲዮ ምስክርነት "Ethiopia a Muslim converted to Christian" ብለው youtube ላይ ቢፈልጉት በሰባት የተለያዩ ክፍሎች ተከፋፍሎ ስለተቀመጠ መመልከት ይችላሉ፡፡ ወይም ----- በሚለው የእኔ የፌስቡክ አድራሻ ላይ የቪዲዮውን ምስክርነት ይመልከቱ፡፡

ሼህ ረመዳን ሙስጠፋ አምኖ መጠመቁን ሲያውቁ ወዲያው ሙስሊሞች ዘጠኝ የግድያ ሙከራ ያደረጉበት ቢሆንም የጠራው አምላክ ለገዳዮቹ አሳልፎ አልሰጠውም፡፡ የኢ.እ እስልምና ጉዳዮች ጽ/ቤት ምክትል ፕሬዝዳንትና የአንዋር መስጊድ አስተባባሪ ኮሚቴ የነበሩት ወላጅ አባቱ ሐጂ ሙስጠፋ ጣሂር ልጃቸው ላይ ጂሃድ አሳውጀው ሊያስገድሉት 38 ሺህ ብር መደቡ፡፡ ዘጠነኛው የግድያ ሙከራ ትንሽ ሰውነቱን ጎድቶት ስለነበር በፖሊስ ጥበቃ ተደርጎለት የተጎዳ ሰውነቱን እያሳየ ነበር ምስክርነቱን የሰጠው፡፡ በመጨረሻም ኢትዮጵያን ለቆ ወደ ኢየሩሳሌም ሊሄድ ሲል አባቱ ሐጂ ሙስጠፋ ጣሂር እንዲህ ብለው ነገሩት፡- «ልጅ ላደረኩብህ ነገር ሁሉ ይቅርታ አድርግልኝ፡፡ እዚያች የተቀደሰች ሀገር ስትሄድ ለእኔም ጸልይልኝ፡፡ አንተ የቀበልከውን መከራ እኔ በዚህ ዕድሜዬ መቀበል ስለማልችል ወደ አንዱ ገዳም ሹልክ ብዬ እንድገባ ጸልይልኝ» አሉት፡፡ ከዚያ በኋላ መጨረሻቸው ምን እንደሆነ ግን ማወቅ አልቻልኩም፡፡ አንድ ነገር ግን እርግጠኛ ሆኜ የማውቀውን እናገራለሁ፡፡ ብዙ ትላልቅ ሙስሊሞች እምነታቸውን በደንብ ከመረመሩ በኋላ በዕድሜያቸው መጨረሻ ላይ በድብቅ

እየተጠመቁ ወደ ገዳም የገቡ እንዳሉ በታሪክ አውቃለሁ፤ በገዳም ያሉ አሁንም በአካልም የማውቃቸው ሰዎች አሉ፡፡

ሙስሊም ወገኖቼ ሆይ! በካሊድ ካሳሁን አማካኝነት በዕቅድ በሠራችኋት ቅንብር «ክርስትናው ሀሰት እስልምናው ደግሞ እውነት መሆኑን አስመሰከረን» እያላችሁ ስትናገሩ ነበር፡፡ ኢትዮጵያ ውስጥ ብቻ ያሉትን የእነ ሼህ ዘካርያን፣ የእነ ሐጂ ዑስማን መሐመድንና የእነ ሼህ ረመዳን ሙስጠፋን እውነተኛ ታሪክስ ምነው ደበቃችሁት? በአፍሪካ ውስጥ ብቻ እስከ 6 ሚሊዮን የሚደርሰው ሙስሊሙ ሕዝባችሁ በዓመት ውስጥ ሲነጉድባችሁ ለምን አልተናገራችሁም? (አፍሪካ ውስጥ በአንድ ዓመት ውስጥ 6 ሚሊየን ሙስሊሞች ወደተለያዩ የክርስትና እምነቶች እንደሄዱ አል-ጀዚራ የተባለው የቴሌቭዥን ጣቢያ በአንድ ወቅት ዘግቦ ነበር) አል-ጀዚራም ጉዳዩ የሚመለከታቸውን የሊቢያው የሃማኖት መምህርና የኢስላማዊ ማኅበር ፕሬዝዳንት የሆኑትን ሼህ አህመድ አል-ካታኒን ቃለ መጠይቅ አድርጎላቸው እሳቸውም ይህንኑ አረጋግጠዋል፡፡ ፕሮግራሙንም አዘጋጅቶ ያቀረበው የአል-ጀዚራው ጋዜጠኛ ማህር አብደላህ ነው፡፡ ጣቢያው ያቀረበውን የቪዲዮ ማስረጃና ሼህ አህመድም በጉዳዩ የሰጡትን ማረጋገጫ youtube ላይ “6 Million Muslims convert to Christianity-Al-Jazeerah!” ብለው ይመልከቱ፡፡ ወይም ከእኔ የፌስ ቡክ አድራሻ ላይ መመልከት ይችላሉ፡፡ ሙስሊም ወገኖቼ ሆይ! እንዲሁም በየሀገሩ እስልምናውን ሐዲሱንም ሆነ ቁርአኑን በደንብ ጠንቅቀው የሚያውቁት ብዙ ትላልቅ ሙስሊም ሼሆች፣ መምህራኖች፣ ጸሐፊዎች፣ ኢማሞች፣ የኢስላማዊ ዩኒቨርሲቲ ምሁራኖችና ሌሎችም እስልምናውን እየተው የመሄዳቸውን ምሥጢርስ ለምን ይፋ አላደረጋችሁትም? እነዚህን እስልምናን ትተው የወጡትን የተለያዩ ሼሆችና ኢማሞች አሁንም youtube ላይ “Imams convert to Christ” ብለው ይመልከቱ፡፡ Many Former Muslim Clerics, Imams, sheikhs, Mullahs, Muslim scholars, preachers, Islamic writers, Quranic and hadiths translators, Islamic theology teachers, Dawa’h missionaries embraced Christianity.

በቀደመው ዘመን በሀገራችን ኢትዮጵያ የመናዊው ሼህ ዘካርያ ቁርአኑን በደንብ ሲመረምሩ ኖረው በኋላ ላይ ስለ መንግስተ ሰማያት ወይም ጀነት የተጻፈውን ሲመረምሩ የነፍሳቸውን ጥያቄ ሊመልስላቸው ስላልቻለ እስልምናውን ትተው ወደ ክርስትናው በመምጣት የሰጡት ምስክርነት ጥሩ መነሻ ሆኖ ስላገኘሁት እኔም የእነርሱን

ፈለግ በመከተል «እንዴት በጀነት (በመንግስተ ሰማይ) ዝሙት ይኖራል?» በማለት ለጠየኩት ጥያቄ ማንም አግባብነት ያለው መልስ ሊመልስልኝ ስላልቻለ በእስልምናው ለማመን ለአእምሮዬ ስለከበደኝ ስለነፍሴም ማሰብ ስለነበረብኝ እስልምናውን ተውኩት።

ከላይ የጠቀስኳቸው ሁሉ እንደ ግብፃዊው ሼህ እና እንደነ የመናዊው ሼህ ዘካርያና ሌሎችም ያሉ ሙስሊም መምህራኖች እስልምናው ውስጥ ያለውን ነገር በቅንነት ከመረመሩ በኋላ እውነተኛውን አምላክ መድኃኔዓለም ክርስቶስን እንዳገኙት ሁሉ ዛሬም ሆነ ወደፊት በየዋሕነትና በቅን ልቡና ሆኖ እውነትን የሚፈልግ ሰው ማንም ቢኖር እርሱ በትክክል እውነተኛውን አምላክ ያገኛዋል። በጽርፈኛና በጭፍን አስተሳሰብ የተሞላ አእምሮ ግን የባሰ ለከፋ ጥፋት ይፋጠናል። የእነ ፈርኦን፣ የእነ ሔሮድስ፣ የእነ ቅዱስ ጳውሎስና የእነ ሙሴ ጸሊም ሕይወት ለእኛ ትልቅ ምሳሌ ነው። እንደነ ፈርኦንና ሔሮድስ ያሉቱ ልባቸው እንደ ዓለት ጠጥሮ ቀረና በአመጻቸው ጸኑ፣ ይልቁንም ለራሳቸው ክብርና ስም ሲሉ በክርስቲያኖች ላይ ጭካኔ የተሞላበት ተግባር ግድያ ሲፈጽሙ እንደ ቅዱስ ጳውሎስ ያሉት ደግሞ ለአምላካቸው ቀናዒ በመሆን ክርስቲያኖችን ያሳድዱ ነበር። የሼህ ረመዳን ሙስጠፋ ታሪክም እንዲሁ ተመሳሳይ ነው።

የእነ ቅዱስ ጳውሎስ ድርጊት በቅን ልቡናና በየዋህነት የተሞላ ስለነበር በጥፋታቸው ውስጥ እውነተኛውን አምላካቸውን አገኙት። ቅዱስ ጳውሎስ የጥፋቱ ኃይል ወንጌልን ወደ መሸከም ተለውጦ የሚሊዮኖችንም ሰውነት ሕንፃ ቤተ መቅደስ አድርጎ በመገንባት ለክርስቶስ ማደሪያ እንዲሆን አደረገ። መድኃኔዓለም ክርስቶስ ይሰቀልልኝ የሚለውን የአይሁድን ጩኸት አስፈጻሚ የነበሩትና ክርስቶስን እንዲሰቀል የፈረዱበት እነ ጲላጦስ እንኳ ሳይቀሩ ወደ ኅሊናቸው ሲመለሱ እውነቱን ሲያውቁት ስለ ክርስቶስ መስክረው አስተምረው በሰማዕትነት ዐረፈዋል። እንደነ ሙሴ ጸሊም ያሉት የዓለም ኃያል የነበሩትም በአብርሃማዊ ፍሊጋ እውነተኛውን አምላካቸውን ፈልገው አግኝተውታል። እውነተኛው አምላክም ከፈለጉት ቅርብ ነውና ራሱን ገልጦላቸዋል። እነ አብርሃምና እነ ሙሴ ጸሊም አምላካቸውን ፈልገው ያገኙበት መንገድ እጅግ አስደናቂና ደስ የሚል ነው በእውነት! እነርሱና እነርሱን የመሰሉት ሁሉ በንጹሕ ልቡና በቅን መንፈስ ሆነው እውነተኛውን አምላክ ፈልገው ካገኙትም በኋላ ራሳቸውን ለዓለም ሙት በማድረግ አገልግለውት አልፈዋል። እውነቱን ለመናገር የእኔም ሕይወት ከዚህ የተለየ አይደለም። አሁን ለሞት እንኳ የተዘጋጀሁ ሰው ነኝ። እውነትን በትክክል ስላገኘሁ አሁን ብሞትም አይቆጨኝም። ከእውነተኛው አምላክ

ከመድኃኔዓለም ክርስቶስ በቀር ሌላ እውነት የለም፡፡ የነፍስ አባቷ እርሱ ብቻ ነው፡፡ እውነተኛዋ ሃይማኖትም ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ብቻ ናት፡፡ የዚህም ምስክርነቱ ቃለ እግዚአብሔር ነው፡፡ ቀጥሎ እንመልከተው፡-

## ‹‹ከትውልዱ ማን አስተዋለ?››

‹‹እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፡- በመንገድ ላይ ቁሙ ተመልከቱም፥ የቀደመችውንም መንገድ ጠይቁ፤ መልካሚቱ መንገድ ወዴት እንደ ሆነች እወቁ፥ በእርስዋም ላይ ሂዱ፥ ለነፍሳችሁም ዕረፍት ታገኛላችሁ፤ እነርሱ ግን አንሄድባትም አሉ›› (ኤር 6፡16) ‹‹መንገድ›› የተባለችው ሃይማኖት ናት፡፡ በሌላም ቦታ ‹‹ለሰው ቅን የምትመስል መንገድ አለች ፍጻሜዋ ግን የሞት መንገድ ነው›› ተብሎ ተጽፏል፡፡ ምሳ 14፡12፡፡ መንገድ ከተባለች ከዚህች ከእውነተኛዋ ሃይማኖት ውጭ ያሉት ሌሎቹ በዓለም ላይ ያሉ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ሃይማኖቶች ሁሉ ቀድሞ ትንቢት የተነገረባቸው የገሃነም ደጆች ናቸው፡፡ ትንቢቶቹን እንያቸው፡-

‹‹ኢየሱስም በደብረ ዘይት ተቀምጦ ሳለ፥ ደቀ መዛሙርቱ ለብቻቸው ወደ እርሱ ቀርበው ንገረን፥ የዓለም ፍፃሜ መቼ ይሆናል? የመምጣትህና የዓለም መጨረሻ ምልክቱስ ምንድር ነው? አሉት። ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አላቸው፡- ማንም እንዳያስታችሁ ተጠንቀቁ። በዚያን ጊዜም ብዙዎች ይሰናከላሉ…ብዙ ሐሰተኞች ነቢያትም ይነሣሉ፣ ብዙዎችንም ያስታሉ፤ ከዓመፃም ብዛት የተነሣ የብዙ ሰዎች ፍቅር ትቀዘቅዛለች። እስከ መጨረሻ የሚጸና ግን እርሱ ይድናል፡፡›› ማቴ 24÷6-12፡፡

በቅዱሳን ሐዋርያቱም ላይ አድሮ ወደፊት የሚሆነውን እንዲሁ አስቀድሞ ነግሮናል፡- ‹‹በግልፅ በኋለኞቹ ዘመናት አንዳንዶች የሚያስቱ መናፍስትንና በውሸተኞች ግብዝነት የተሰጠውን የአጋንንትን ትምህርት እያዳመጡ፥ ሃይማኖትን ይክዳሉ›› (1ኛ ጢሞ 4፡1)፤ ‹‹ሐሰተኞች ነቢያት ደግሞ በሕዝቡ መካከል ነበሩ እንዲሁም በመካከላችሁ ደግሞ ሐሰተኞች አስተማሪዎች ይሆናሉ፤ እነርሱም የዋጃቸውን ጌታ እንኳ ክደው የሚፈጥንን ጥፋት በራሳቸው ላይ እየሳቡ የሚያጠፉ ኑፋቄን አሹልከው ያገባሉ›› (2ኛ ጴጥ 2፡1)፤ ‹‹በቅዱሳን ነቢያትም ቀድሞ የተባለውን ቃል በሐዋርያቶቻችሁም ያገኛችኋትን የጌታንና የመድኃኒትን ትእዛዝ እንድታስቡ በሁለቱ እያሳሰብኋችሁ ቅን ልቡናችሁን አነቃቃለሁ። በመጨረሻው ዘመን እንደ ራሳቸው ምኞት የሚመላለሱ ዘባቾች በመዘበት እንዲመጡ ይህን በፊት እወቁ›› (2ኛ ጴጥ 3፡2)፤ ‹‹ኢየሱስ ክርስቶስ

ትናንትና ዛሬ እስከ ለዘላለምም ያው ነው። ልዩ ልዩ ዓይነት በሆነ በእንግዳ ትምህርት አትወሰዱ›› (ዕብ 13:7-8)፤ ‹‹ጢሞቴዎስ ልጄ ሆይ፥ እምነትና በጎ ሕሊና ይኑርህ፥ አንዳንዶች ሕሊናን ጥለው፥ መርከብ አለ መሪ እንደሚጠፋ፥ በእምነት ነገር ጠፍተዋልና›› (1ኛ ጢሞ 1:19)፤ ‹‹ከሄድሁ በኋላ ለመንጋው የማይራሩ ጨካኞች ተኩላዎች እንዲገቡባችሁ፥ ደቀ መዛሙርትንም ወደ ኋላቸው ይስቡ ዘንድ ጠማማ ነገርን የሚናገሩ ሰዎች በመካከላችሁ እንዲነሡ እኔ አውቃለሁ›› (ሐዋ 20÷29)፤ ‹‹ብዙዎች ለክርስቶስ መስቀል ጠላቶቹ ሆነው ይመላለሳሉና፤ ብዙ ጊዜ ስለ እነርሱ አልኋችሁ፥ አሁንም እንኳ እያለቀስሁ እላለሁ። መጨረሻቸው ጥፋት ነው›› (ፊል 3÷18)፤ ‹‹የሚያናውጡአችሁ የክርስቶስንም ወንጌል ሊያጣምሙ የሚወዱ አንዳንዶች አሉ፤ ነገር ግን እኛ ብንሆን ወይም ከሰማይ መልአክ፥ ከሰበክንላችሁ ወንጌል የሚለይ ወንጌልን ቢሰብክላችሁ፥ የተረገመ ይሁን። አስቀድመን እንዳልን እንዲሁ አሁን ሁለተኛ እላለሁ፥ ከተቀበላችሁት የተለየውን ማንም ቢሰብክላችሁ የተረገመ ይሁን›› (ገላ 1÷6)፤ ‹‹ያልተማሩትና የማይጸኑትም ሰዎች ሌሎችን መጻሕፍት እንደሚያጣምሙ እነዚህን ደግሞ ለገዛ ጥፋታቸው ያጣምማሉ። እንግዲህ እናንተ፥ ወዳጆች ሆይ፥ ይህን አስቀድማችሁ ስለምታውቁ፥ በዓመፀኞቹ ስሕተት ተስባችሁ ከራሳችሁ ጽናት እንዳትወድቁ ተጠንቀቁ›› (2ኛ ጴጥ 3÷16)፤ ‹‹እንደ ተማራችሁም በሃይማኖት ጽኑ፥ እንደ ክርስቶስ ትምህርት ሳይሆን እንደ ሰው ወግና እንደ ዓለማዊ እንደ መጀመሪያ ትምህርት ባለ በፍልስፍና በከንቱም መታለል ማንም እንዳይማርካችሁ ተጠበቁ›› (ቆላይ 2÷7)፤ ‹‹ልጆች ሆይ፥ መጨረሻው ሰዓት ነው። የክርስቶስም ተቃዋሚ ይመጣ ዘንድ እንደ ሰማችሁ አሁን እንኳ ብዙዎች የክርስቶስ ተቃዋሚዎች ተነሥተዋል፤ ስለዚህም መጨረሻው ሰዓት እንደ ሆነ እናውቃለን›› (1ኛ ዮሐ 2:18)፤ ‹‹አእምሮአቸው የጠፋባቸው ስለ እምነትም የተጣሉ ሰዎች ሆነው፥ እውነትን ይቃወማሉ። ዳሩ ግን የእነዚያ ሞኝነት ደግሞ ግልጥ እንደ ሆነ፥ ሞኝነታቸው ለሁሉ ይገለጣል... አንተ ግን በተማርህበትና በተረዳህበት ነገር ጸንተህ ኑር፥ ከማን እንደ ተማርኸው ታውቃለህና ከሕፃንነትህም ጀምረህ ክርስቶስ ኢየሱስን በማመን፥ መዳን የሚገኝበትን ጥበብ ሊሰጡህ የሚችሉትን ቅዱሳን መጻሕፍትን አውቀሃል›› (2ኛ ጢሞ 3÷8-15)... እየተባሉ በመጽሐፍ ቅዱስ የተነገሩ ትንቢቶች ሁሉ ተፈጽመዋል፣ በዘመናችንም በትክክል እየተፈጸሙ ነው፣ ወደፊትም ይፈጸማሉ፡፡ እስልምናውም ከ600 ዓመት በኋላ አዲስ መልክ ይዞ የመጣ እምነት ስለሆነ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስና የሐዋርያቶቹ ትንቢቶች በትክክል ይመለከተዋል፡፡

በመጨረሻው ዘመን እንደ ራሳቸው ምኞት የሚመላለሱ ዘባቾች በመዘበት እንደሚመጡ፤ በግልፅ በኋለኞቹ ዘመናት አንዳንዶች የሚያስቱ መናፍስትንና በውሸተኞች ግብዝነት የተሰጠውን የአጋንንትን ትምህርት እያዳመጡ ሃይማኖትን የሚክዱ ሐሰተኞች ነቢያት በሕዝቡ መካከል እንደሚነሡ፣ የሚያጠፉ ኑፋቄንም አሾልከው እንደሚያገቡ የተነገረን እስልምናው ሳይመሠረት ከ600 ዓመት በፊት ነው፡፡ ይህ እንደሚሆን እርግጠኞች ሆነው ነው ጌታችንና ሐዋርያቶቹ አስቀድመው የነገሩን፡፡ እንደተናገሩትም ይኸው ዛሬ እንደ አሸን የፈሉ የገሃነም ደጆች የሆኑ የተለያዩ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ሃይማኖቶች ሊፈበረኩ ችለዋል፡፡ ጥንታዊና ቀደምትነት ያለው ይሁን እንጂ እስልምናውም ከእነዚህ እምነቶች ውስጥ አንዱ ነው፡፡ በትንቢት እንደተነገረው አንድ ሰው የአጋንንትን ትምህርት ሰምተው የመሠረቱትና በሰይፍ ያስፋፉት እምነት መሆኑን በቀላሉ ለመረዳት ራሳቸው ቁርአኑና ሐዲሱ ምስክር ናቸው፡፡ በሂራ ተራራ ላይ ለነቢያቸው መሐመድ በመልአኩ በቅዱስ ገብርኤል ስም ተገልጦ ያስተማራቸው «ጂብሪል» እርሱ እውነተኛ መልአክ አልበረም፡፡ የነቢያቸውን ልብ ቀዶ ውስጣቸውን በውኃ አጥቦ አረፋና ደም አስኪደፍቁ ድረስ በማስጨነቅ የነቢይነትን ማዕረግ የሚሰጥ መልአክ የለም፣ ፈጽሞ ሊኖርም አይችልም፡፡ (ስለ ሁኔታው ሐዲሱ ላይ በዝርዝር የተጻፈውን ገጽ ----ላይ ይመልከቱ፡፡)

ሙስሊም ወገኖቼ ሆይ! ለነፍሳችሁና ለዘላለማዊው ሕይወታችሁ የምታስቡ ከሆነ ልክ እንደነ አብርሃምና እንደነ ሙሴ ጻሊም፣ እንደነ ሼህ ረመዳን ሙስጠፋና እንደነ ሼህ ዘካርያ፣ እንደ እኔም ጭምር ወደ አእምሮአችሁና ወደ ኅሊናችሁ ወደ ልባችሁም ተመለሱና እውነትን በቅን መንፈስ ሆናችሁ መርምሩ፡፡ ሃይማኖት የሥጋ ሳይሆን የነፍስ ጉዳይ ነው፡፡ ስለ ሃይማኖት ስናስብ ዘላለማዊ ሕይወትን ብቻ ነው ማሰብ ያለብን፡፡ ትንቢቶች ተፈጽመውባችሁ ከሚቀሩና ወደፊትም በነፍሳችሁም ከምትጎዱ እውነትን በቅን ልቡና ሆናችሁ ፈልጓት፡፡ በነፍስ መሸወድ እጅግ ትልቅ ኪሳራ ነው! መጽሐፍ «ሰው ዓለሙን ሁሉ ቢያተርፍ ነፍሱንም ቢያጐድል ምን ይጠቅመዋል?» ይላል፡፡ ማቴ 16፡26፡፡ እውነት ነው! ሰው ዓለሙን ሁሉ አትርፎ ነፍሱን ግን ቢያጐድል ምንም አይጠቅመውም፡፡ ይህንን ከትውልዱ ማን አስተውሎ ይሆን? በቁርአኑም ሆነ በሐዲሱ ውስጥ ስለነቢያችሁ መሐመድ ምንም የተነገረ ትንቢት የለም፡፡ ይልቁንም ነቢያችሁ ኃጢአተኛ እንደነበሩ ነው ቁርአኑም ሆነ ሐዲሱ በግልጽ የሚናገሩት፡፡ በአንጻሩ ግን መጽሐፍ ቅዱስ ያለፈውንም ሆነ ወደፊት እስከ ዕለተ ምፅዓት ድረስ የሚሆነውን ሁሉ

በግልጽ ይናገራል፡፡ እውነተኛው አምላክ መድኃኔዓለም ክርስቶስ በዚህች ምድር ላይ በሥጋ ሳለ ያደረጋት እያንዳንዷ ነገር ቀድማ ከ1000 እና ከ700 ዓመታት በፊት በነቢያት የተነገረች ትንቢት ናት፡፡ ለማሳያ ያህል አንዷን ቃል ብቻ ልጥቀስላችሁ፡- ነቢዩ ኢሳይያስ ክርስቶስ ኢየሱስ ሥጋ ተወልዶ በሞቱ ዓለሙን ሁሉ እንደሚያድን ትንቢት የተናገረው ክርስቶስ ከመወለዱ ከ700 ዓመት በፊት ነው፡፡ ይህንን ከክርስቶስ ልደት ከ700 ዓመታት በፊት የተነገረውንም ትንቢት ክርስቶስ በተግባር ፈጽሞታል። ትንቢተ ኢሳያስን ምዕራፍ 53 ሙሉ ቃሉ እንዲህ ይላል፡-

«በእውነት ደዌያችንን ተቀበለ ሕመማችንንም ተሸክሞአል፤ እኛ ግን እንደ ተመታ በእግዚአብሔርም እንደ ተቀሠፈ እንደ ተቸገረም ቈጠርነው። እርሱ ግን ስለ መተላለፋችን ቈሰለ፥ ስለ በደላችንም ደቀቀ፤ የደኅንነታችንም ተግሣጽ በእርሱ ላይ ነበረ፥ በእርሱም ቍስል እኛ ተፈወስን። እኛ ሁላችን እንደ በጎች ተቅበዝብዘን ጠፋን፤ ከእኛ እያንዳንዱ ወደ ገዛ መንገዱ አዘነበለ፤ እግዚአብሔርም የሁላችንን በደል በእርሱ ላይ አኖረ። ተጨነቀ ተሣቀየም አፉንም አልከፈተም፤ ለመታረድ እንደሚነዳ ጠቦት፥ በሸላቶቹም ፊት ዝም እንደሚል በግ፥ እንዲሁ አፉን አልከፈተም። በማስጨነቅና በፍርድ ተወሰደ፤ ስለ ሕዝቤ ኃጢአት ተመትቶ ከሕያዋን ምድር እንደ ተወገደ ከትውልዱ ማን አስተዋለ? ከክፉዎችም ጋር መቃብሩን አደረጉ፥ ከባለጠጎችም ጋር በሞቱ ሆኖም ግፍን አላደረገም ነበር፥ በአፉም ተንኰል አልተገኘበትም ነበር። እግዚአብሔርም በደዌ ያደቅቀው ዘንድ ፈቀደ፤ ነፍሱን ስለ ኃጢአት መሥዋዕት ካደረገ በኋላ ዘሩን ያያል፥ ዕድሜውም ይረዝማል፥ የእግዚአብሔርም ፈቃድ በእጁ ይከናወናል። ከነፍሱ ድካም ብርሃን ያያል ደስም ይለዋል፤ ጻድቅ ባሪያዬም በእውቀቱ ብዙ ሰዎችን ያጸድቃል፥ ኃጢአታቸውን ይሸከማል። ስለዚህም እርሱ ብዙዎችን ይወርሳል፥ ከኃያላንም ጋር ምርኮን ይከፋፈላል፤ ነፍሱን ለሞት አሳልፎ ሰጥቶአልና፥ ከዓመፀኞችም ጋር ተቈጥሮአልና፤ እርሱ ግን የብዙ ሰዎችን ኃጢአት ተሸከመ» ይላል ትንቢተ ኢሳይያስ ምዕራፍ 53፡፡ በነገረው ትንቢት መሠረት መድኃኔዓለም ክርስቶስ «ነፍሱን ለሞት አሳልፎ በመስጠት የብዙዎችንም ኃጢአት ተሸክሟልና ይህን ከትውልዱ ማን አስተውሎታል?» ነቢዩ ኢሳይያስ የክርስቶስን መከራ በትንቢት መነፅር ተመልክቶ መከራውን ከዘረዘረ በኋላ ለጠየቀው ጥያቄ መልስ ያስፈልገዋል፡፡ «ከትውልዱ ማን አስተዋለ?»

ነቢያቱ አስቀድመው «እነሆ የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ...» እያሉ ክርስቶስን የገለጹበትን መንገድ ከትውልዱ ማን አስተዋለው? ዮሐ 1፡29፡፡

«እኔ የዓለም ብርሃን ነኝ፤ የሚከተለኝ የሕይወት ብርሃን ይሆንለታል እንጂ

በጨለማ አይመላለስም» (ዮሐ 8፡12)፤ «በእኔ የሚያምን ሁሉ በጨለማ እንዳይኖር እኔ ብርሃን ሆኜ ወደ ዓለም መጥቻለሁ» (ዮሐ 12፡46)፤ «መልካም እረኛ እኔ ነኝ፤ መልካም እረኛ ነፍሱን ስለ በጎቹ ያኖራል» (ዮሐ 10፡11)፤ «ትንሣኤና ሕይወት እኔ ነኝ፤ የሚያምንብኝ ቢሞት እንኳ ሕያው ይሆናል» (ዮሐ 11፡25) ያለውን የመልካሙን እረኛ ድምፅ ከትውልዱ ማን ይሆን ያስተዋለው?

ማቴዎስ ወንጌል 4፡14-16 ላይ እንዲህ ተብሎ ነው የተጻፈው፡- «በነቢዩም በኢሳይያስ ‹በጨለማ የተቀመጠው ሕዝብ ታላቅ ብርሃን አየ፥ በሞት አገርና ጥላ ለተቀመጡትም ብርሃን ወጣላቸው› የተባለው ይፈጸም ዘንድ ይህ ሆነ» ይላል መጽሐፉ:: መድኃኔዓለም ክርስቶስ በዮሐንስ ወንጌል ላይ በተደጋጋሚ «ብርሃንም ወደ ዓለም ስለ መጣ ሰዎችም ሥራቸው ክፉ ነበርና ከብርሃን ይልቅ ጨለማን ወደዱ» (3፡19)፤ «በቀን የሚመላለስ ቢኖር የዚህን ዓለም ብርሃን ያያልና አይሰናከልም» (11፡9)፤ «ጨለማ እንዳይደርስባችሁ ብርሃን ሳለላችሁ ተመላለሱ፤ በጨለማም የሚመላለስ ወዴት እንዲሄድ አያውቅም። የብርሃን ልጆች እንድትሆኑ ብርሃን ሳለላችሁ በብርሃኑ እመኑ አላቸው» (12፡35) እያለ ያስተማረውን ትምህርት አምኖ ከጨለማ ለውጣትና ወደሚደነቅ ብርሃን ለመምጣት ከትውልዱ ያስተዋለው ማነው?

በቅዱሳን ሐዋርያትስ «ለእነርሱም የእግዚአብሔር ምሳሌ የሆነ የክርስቶስ የክብሩ ወንጌል ብርሃን እንዳያበራላቸው፥ የዚህ ዓለም አምላክ (ዲያብሎስ) የማያምኑትን አሳብ አሳወረ» ተብሎ የተነገረውን ቃል «ከትውልዱ ማን አስተዋለው?» 2ኛ ቆሮ 4፡4::

ሰው ዓለሙን ሁሉ አትርፎ ነፍሱን ግን ቢያጎድል ምንም እንደማይጠቅመው አውቆ (ማቴ 16፡26) ለሥጋው ሳይሆን ለነፍሱ በመትጋት በንጹሕ ልቡና ሆኖ እውነትን ለማወቅ ፈቃደኛ የሆነና ከትውልዱ ያስተዋለ ማነው? የነቢዩ ኢያሳይያስ ጥያቄ በትክክል መልስ ያስፈልገዋል፣ «ከትውልዱ ማን አስተዋለ?›

## የክርስትያኖች መንግስተ ሰማያትና የሙስሊሞች ጀነት

ክርስትያኖችም ሆኑ ሙስሊሞች እንደራሳቸው አረዳድና ግንዛቤ መጠን ከሞት በኋላ ዘላለማዊ ሕይወት አግኝተው ሊኖሩባት የሚናፍቋትና ተስፋ የሚያደርጓት ሰማያዊት ሀገር አለች:: ለመሆኑ ክርስትያኖች ዘላለማዊ ሕይወት አግኝተው ሊኖሩባት የሚናፍቋት መንግስተ ሰማያት ምን ትመስላለች? ሙስሊሞችስ ተስፋ የሚያደርጓት ጀነት ምን ትመስል ይሆን? ክርስቲያኖችም ሆኑ ሙስሊሞች ከሞት በኋላ አምላካችን ያወርሰናል፣ እንገባባታለን ብለው ተስፋ ስለሚያደርጓት መንግስተ ሰማያትና ጀነት

መጽሐፍ ቅዱስና ቁርአን ላይ ብቻ የተጻፈውን መሠረት በማድረግ የተወሰኑ ነጥቦችን ቀጥለን እናያለን፡፡ እይታችንን ከክርስትናው እንጀምር፡-

+++ «ትንሣኤ ሙታን የለም የሚሉ ሰዱቃውያን ወደ ኢየሱስ ቀረቡ፥ እንዲህም ብለው ጠየቁት፡- መምህር ሆይ፥ ሙሴ አንድ ሰው ልጅ ሳይወልድ ሲሞት ወንድሙ ሚስቱን አግብቶ ለወንድሙ ዘር ይተካ አለ። ሰባት ወንድማማቾች በእኛ ዘንድ ነበሩ፤ ፊተኛውም ሚስት አግብቶ ሞተ፥ ዘርም ስለሌለው ሚስቱን ለወንድሙ ተወለት፤ እንዲሁ ደግሞ ሁለተኛው ሦስተኛውም፥ እስከ ሰባተኛው ድረስ። ከሁሉም በኋላ ሴቲቱ ሞተች። ሁሉ አግብተዋታልና በትንሣኤ ቀንስ፥ ከሰባቱ ለማናቸው ሚስት ትሆናለች? ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አላቸው፡- መጻሕፍትንና የእግዚአብሔርን ኃይል አታውቁምና ትስታላችሁ። በትንሣኤስ እንደ እግዚአብሔር መላእክት በሰማይ ይሆናሉ እንጂ አያገቡም አይጋቡምም። ስለ ትንሣኤ ሙታን ግን፡- እኔ የአብርሃም አምላክ፥ የይስሐቅም አምላክ የያዕቆብም አምላክ ነኝ የሚል ከእግዚአብሔር ዘንድ ወደ እናንተ የተባለውን አላነበባችሁምን? የሕያዋን አምላክ ነው እንጂ የሙታን አይደለም። ሕዝቡም ይህን ሰምተው በትምህርቱ ተገረሙ፡፡» +++ ማቴዎስ 22፡23-33፡፡

ከላይ ባየነው በመድኃኔዓለም ክርስቶስ ትምህርት መሠረት ክርስቲያኖች በመንግስተ ሰማያት ልክ እንደመላእክት ሆነው በንጽሕናና በቅድስና 24 ሰዓት አምላካቸውን ያለ እረፍት ያመሰግናሉ፡፡ ማግባት፣ መጋባት፣ መውጣት፣ መውረድ፣ መድከም...በአጠቃላይ ሥጋዊ ባሕርያት ፈጽሞ አይኖርባቸውም፡፡ ክርስቲያኖች በመንግስተ ሰማያት ከመላእክት ጋር አምላካቸውን በማመስገን ብቻ እንደሚኖሩ ቅዱስ ዮሐንስ በራእይ አይቶታል፡፡ ራእይ 7፡9 ላይ እንዲህ ተብሎ ነው የተጻፈው፡-

«ከዚህ በኋላ አየሁ፣ እነሆም አንድ እንኳ ሊቆጥራቸው የማይችል ከሕዝብና ከነገድ፣ ከወገንም፣ ከቋንቋም ሁሉ እጅግ ብዙ ሰዎች ነበሩ፤ ነጭ ልብስም ለብሰው፣ የዘንባባንም ዝንጣፊዎች በእጆቻቸው ይዘው በዙፋኑና በበጉ ፊት ቆሙ፤ በታላቅም ድምፅ እየጮሁ ‹በዙፋኑ ላይ ለተቀመጠው ለአምላካችንና ለበጉ ማዳን ነው› አሉ፡፡ መላእክቱም ሁሉ በዙፋኑ ዙሪያ ቆመው ነበር፤ በዙፋኑም ፊት በግንባራቸው ተደፉ፣ ለእግዚአብሔርም እየሰገዱ ‹አሜን በረከትና ክብር፣ ጥበብም፣ ምስጋናም፣ ውዳሴም፣ ኃይልም፣ ብርታትም ከዘላለም እስከ ዘላለም ድረስ ለአምላካችን ይሁን፤ አሜን› አሉ» በማለት ቅዱስ ዮሐንስ በራእይ ያየውን ጽፎልናል፡፡ ስለዚህ ክርስቲያኖች ከሞት በኋላ ያላቸው ሕይወት ልክ እንደመላእክት ያለ ነው፡፡ ከምስጋና በቀር ሌላ ምንም ነገር የለባቸውም፡፡ ይህ ግልጽ የሆነ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ነው፡፡

ቁርአን ግን ስለ ጀነት ያለው አመለካከት ከዚህ ፍጹም የተለየ ነው፡፡ በሙስሊሞች

ጀነት ውስጥ ሁሉም ሥጋዊ ፍላጎቶች ይሟሉበታል፡፡ መብላት፣ መጠጣት፣ መዝናናት፣ ዝሙት መፈጸም...ሁሉም ሥጋዊ ፍላጎቶች በጀነት ውስጥ ይፈጸማሉ፡፡ እንዲያውም በምድር ላይ ያልነበረ በሥጋዊ ፍላጎቶት የሚገኝ ደስታ ነው በጀነት ያለው፡፡ ለምሳሌ አንድ ሙስሊም ወንድ በምድር ላይ እያለ እስከ 4 ሚስት እንዲያገባ በቁርአኑ የተፈቀደለት ሲሆን በጀነት ግን ለወሲብ ተግባር የሚውሉ 72 ደናግላን ቆነጃጂት ሴቶችን እንደሚያገባ ነው በሐዲሱ ላይ የተጻፈው፡፡ (ማስረጃውን በኋላ በዝርዝር እናየዋለን) እነዚህ 72 ደናግላን ቆነጃጂቶች በተጠበቁ ድንኳኖች ውስጥ ምቾት ባላቸው መቀመጫዎችና አልጋዎች ላይ ሆነው ወንዶችን በዝሙት ለማስደሰት እንደሚጠብቋቸው ነው የተጻፈው፡፡ ሌላው ከሥጋዊ ፍላጎቶች ውስጥ ለምሳሌ ልክ የሌለው የወይን ጠጅ ይሰጣቸዋል፣ አልኮል መጠጥ ይጠጣሉ ነገር ግን አይሰክሩም፤ በውሃ ፏፏቴዎች አጠገብ የሚበሏቸው ፍራፍሬዎች ይሰጧቸዋል፤ በአረንጓዴ የሐርና የወርቅ ልብስ ያጌጣሉ፤...ያላመኑት ደግሞ በሲኦል ያሉትን ሰዎች የእግራቸውን እጣቢ ይጠጣሉ፣ የሚመገቡትም እሾሃማ ዛፍን ነው፡፡ የቁርአኑን የጥቅስ ማስረጃዎች እንመልከት፡-

በጀነት ውስጥ ለዝሙት የተዘጋጁ ሆነው ወንዶቹን የሚጠብቁት ቆነጃጂት ሴቶች የተሸፈነ የሰጎን እንቁላል ይመስላሉ፣ ዓይኖቻቸው ውብና ማራኪዎች ናቸው፡፡ ቁርአኑ 37:48 ላይ ስለ እነዚህ ሴቶች የሚከተለውን ቃል ተጽፎ እናገኛለን፡- "ምርጥ የሆኑት የአላህ ባሪያዎች ቅጣትን አይቀምሱም፣ ለነርሱ የታወቀ ሲሳይ አላቸው፡፡ ፍራፍሬዎች አሏቸው፣ እነርሱም በደሎት ጀነቶች ውስጥ የተከበሩ ናቸው፡፡ ፊት ለፊት የሚተያዩ ሲሆኑ በአልጋዎች ላይ ይንፈላሰሳሉ፡፡ ከሚመነጭ ወይን ጠጅ በያዘ ብርጭቆ በእነርሱ ላይ ይዞርባቸዋል፡፡ ነጭ ለጠጪዎች ጣፋጭ ከሆነች በእርሷ ውስጥም ምታት የሌለባትም እነርሱም ከእርሷ የሚሰከሩ አይደሉም፡፡ እነርሱም ዘንድ ዓይኖቻቸውን በባሎቻቸው ላይ አሳጣሪዎች የሆኑ ሌላ የማይመለከቱ ዓይናማዎች ናቸው፡፡ እነርሱ ልክ የተሸፈነ የሰጎን እንቁላል ይመስላሉ፡፡" ሱረቱ አልሷፍፋት 37፡40-48፡፡

ወንዶቹ በጀነት የሚፈልጉት ምግብ እሸትና ሥጋ ይጨመርላቸዋል፣ መጠጥ የገባበዛሉ፣ የሚሰጧቸው ሴቶች ዓይናማዎችና ነጫጮች ናቸው፡፡ ቁርአኑ በምድር ላይ ሳሉ በአላህ መንገድ የተጋደሉት ሰዎች በጀነት ስለሚሰጣቸው ክብር ሲናገር እንደህ ይላል፡- "ትሠሩት በነበራችሁት ምክንያት ተደሳቾች ኾናችሁ ብሉ፣ ጠጡም ይባላሉ፡፡ በተደረደሩ አልጋዎች ላይ ተደጋፊዎች ኾነው በጀነት ይኖራሉ፡፡ ዐይናማዎች በኾኑ ነጫጭ ሴቶችም እናጠናዳቸዋልን፡፡ እነዚያ ያመኑትና ዝርያቸውም በእምነት የተከተላቸው ዝርያቸውን በእነርሱ እናስጠጋለን፤ ከሥራቸውም ምንንም

አናጎልባቸውም፤ ሰው ሁሉ በሰራው ሥራ ተያዢ ነው፡፡ ከሚሹትም ሁሉ እሸትንና ሥጋን እንጨምርላቸዋልን፡፡ በውስጧ መጠጥን ይሰጣጣሉ፤ በውስጧ ውድቅ ንግግርና መወንጀልም የለም፡፡ ለእነርሱም የሚኾኑ ወጣቶች ልክ የተሸፈነ ሉል መስለው በእነርሱ ላይ ይዘዋወራሉ፡፡" ሱረቱ አል-ጡር 52፡20-24፡፡

ቁርአኑ በጀነት ውስጥ ስላሉት በርካታ ደናግላን ሴቶች ሲናገር እንዲህ ይላል፡- "በጌታውም ፊት መቆምን ለፈራ ሰው ሁለት ጀነቶች አሉት፡፡ በሁለቱ ውስጥ የሚፈሱ ሁለት ምንጮች አሉ፡፡ በሁለቱ ውስጥ ከፍራፍሬዎች ሁሉ ሁለት ዓይነቶች እርጥብና ደረቅ አሉ፡፡ በውስጣቸው ዐይኖቻቸውን በባሎቻቸው ላይ አሳጣሪዎች የኾኑ ሴቶች አሉ፡፡ ከሁለቱ ጀነቶች ሌላ ሁለት ጀነቶች አሉ፡፡ በውስጣቸው ሁለት የሚንፏፉ ምንጮች አሉ፡፡ በውስጣቸው ፍራፍሬ ዘምባባም፣ ሩማንም አለ፡፡ በውስጣቸው ፀባየ መልካሞች፣ መልከ ውቦች ሴቶች አሉ፡፡ በድንኳኖች ውስጥ የተጨጎሉ የዓይኖቻቸው ጥቁረትና ንጣት ደማቅ የኾኑ ናቸው፡፡ በሚያረገርጉ አረንጓዴ ምንጣፎችና በሚያማምሩ ስጋጃዎች ላይ የተደላደሉ ኾነው ይቀመጣሉ" ሱረቱ አል-ረሕማን 55፡46-76፡፡

"በእነርሱ ላይ ሁልጊዜ የማያረጁ ወጣቶች ልጆች ይዘዋወራሉ፡፡ ከጠጅ ምንጭም በብርጭቆዎችና በኩስኩስቶች በፅዋም በእነርሱ ላይ ይዞራሉ፡፡ የራስ ምታት አያገኛቸውም፤አይሰክሩምም፡፡ ከሚመርጡትም ዓይነት በእሸቶች፣ ከሚሹትም በኾነ የበራሪ ሥጋ ይዞርባቸዋል፡፡ ዐይናማዎች የኾኑ ነጫጭ ቆንጆዎችም አሏቸው፡፡ ልክ እንደተሸፈነ ሉል መሰሎች የኾኑ ናቸው፡፡ በዚያ ይሠሩት በነበሩት ምክንያት ዋጋ ይኾን ዘንድ ይህንን አደረግንላቸው፡፡ በውስጧ ውድቅ ንግግርንና መወንጀልን አይሰሙም፣ ግን ሰላም መባባልን ይሰማሉ፡፡ በተቀፈቀፈ እሾህ በሌለው ቁርቁራ ውስጥ ናቸው፡፡ ፍሬው በተነባበረ በሙዝ ዛፍም፣ በተዘረጋ ጥላ ሥርም፣ በሚንቧቧ ውኃ አጠገብም፣ ብዙ ዓይነት በኾኑ ፍራፍሬዎችም ውስጥ ናቸው፡፡ ከፍ በተደረጉ ምንጣፎችም እኛ አዲስ ፍጥረት አድርገን ለእነርሱ ፈጠርናቸው፡፡ ደናግሎችም አደረግናቸው፡፡ ለባሎቻቸው ተሽሞርሟሪዎች እኩያዎች አደረግናቸው፡፡" ሱረቱ አል-ዋቂዓህ 56፡17-37፡፡

ጠቅለል ባለ መልኩ ስናየው በእነዚህና በሌሎቹም የቁርአን ጥቅሶች መሠረት ሙስሊሞች በጀነት ውስጥ፡-

#በጥላዎችና በምንጮች አጠገብ ሆነው ከሚፈልጉት ከሁሉም ዓይነት ፍራፍሬ ብሉ፣ ጠጡ ይባላሉ (77፡43)

#አማኝ ሙስሊሞች በጀነት እሸትና ሥጋ እንዲሁም መጠጥን ብሉ፣ ጠጡም ተብለው

ይሰጣቸዋል፣ በተደረደሩ አልጋዎች የተኙና ዓይናማ የሆኑ ነጫጭ ቆንጆ ሴቶች ይሰጧቸዋል (52፡18-24፣ 44፡54)

#የወርቅ አንባርና ከሐር የተሠራ አረንጓዴ ልብስ ለብሰው ወንዞች በሥሮቻቸው ያልፉባቸዋል (18፡31) ሥጋዊ ፍላጎቶቻቸው ሁሉ ይሟሉላቸዋል (50፡35)

#ከሁሉም ፍራፍሬዎች ውስጥ ሁለት ሁለት ዓይነቶች ያሏቸው ሁለት ጀነቶች ከቆንጆ ሴቶች ጋር ይሰጣቸዋል (55፡46-48፣56፣62)

#ለሚያስፈልጋቸው ነገር ሁሉ እንዲላላኳቸው አገልጋይና አሳላፊ የሆኑ ቆንጆ ወጣት ወንዶች ልጆች ይሰጧቸዋል (52፡24)

#በምድር ላይ እያሉ የሠሩትን እንዳያጡ ከቤተሰቦቻቸውና ልጆቻቸውና ጋር ይገናኛሉ (52፡21)፤ በባለ አጎበር አልጋዎች ላይ ሆነው ጠጅ እየጠጡ ባላመኑ ሰዎች ላይ ይስቁባቸዋል (83፡22-25፣ 34-36)

#ሙስሊም ያልሆኑት ሰዎች ደግሞ በሲኦል ውስጥ ዶሪዕ ከሚባል እሾሃማ ዛፍ በቀር ሌላ ምግብ አይሰጣቸውም፡፡ እርሱም ረሀብን አያስታግስም፣ አያሰባም/አያወፍርምም (88፡6-7) እንደሁም ‹ዘቁም› የምትባል እንቡጥዋ ልክ የሰይጣንን ራስ የመሰለች የዛፍ ፍሬ ይበላሉ (37፡65)

#ሳያምን ቀርቶ ሲኦል የገባ አንድ ኃጢአተኛ አብረውት በእሳት የሚቃጠሉን ሰዎች የእግራቸውን እጣቢ እንዲጠጣ ይደረጋል፤ ከዚህና ከፈላ ውኃ ሌላ መጠጥ አይሰጠውም (69፡36፣ 37፡67፣ 56፡93)

#በጀነት ውሰጥ ትልልቅ የመኖሪያ ቤቶች ይሰጧቸዋል፤ በቤቶቹ ሥርም ወንዞች ይፈሱላቸዋል (61፡11-12፣ 39፡20)

#በጀነት ባሉት የአትክልት ቦታዎች ውስጥ ፍራፍሬዎች፣ የጥላ ቦታዎችና የውኃ ፏፏቴዎች የሚገኙ ሲሆን በደናግላን የሞሉ ናቸው፡፡ ደናግሎቹ «ያቁትና መርጃን» ይመስላሉ (እነዚህ ለጌጥ የሚሆኑ የሚያንፀባርቁ የከበሩ ድንጊያዎች ናቸው 55፡56፣ 58)፤ በሁለተኛው ጀነት ውስጥ ደግሞ ጥቁር ዓይን ያላቸው ይኖራሉ፤ እነሱም በትላልቅ ድንኳኖቻቸው ውስጥ እንዲቀመጡ ይደረጋል፡፡ ሰዎችም ሆኑ ጅኒዎች አልነኳቸውም፡፡ ክብረ ንጽሕናቸውም ጀነት የሚገባ ሰው እስከሚመጣ ድረስ የተጠበቀ ነው፡፡ እነሱም በአረንጓዴ አረግራጊ ምንጣፎችና ስጋጃዎች ላይ የተደላደሉ ሆነው ይጠባበቃሉ (55፡76)፤ የተሰናዱና የተጨጎሉ ሆነው የተቀመጡት ደናግሎች ጡቶቻቸው ጉች ጉች ያሉ ናቸው (78፡33)፤ ልክ እንደ እንቁላል የሆኑ ትላልቅ ውብና ማራኪ የሆኑ ጥቁር ዓይኖች አሏቸው፤ ሙስሊሞች ከተጨጎሉት ከእነዚህ ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት ያደርጋሉ (52፡20፣ 44፡54፣ 2፡25፣ 37፡48-49)

#ከሚመነጭ ወይን ጠጅ ይጠጣሉ፣ ፍራፍሬዎች ይበላሉ፣ የተሸፈነ የሰጎን እንቁላል የመሰለ ዓይን ካላቸው ሴቶች ጋር በአልጋዎች ላይ ይንፈላሰሳሉ (37፡40-49)
#በቁርቁራና ፍሬው በተነባበረ ሙዝ አጠገብ እንዲሁም በሚንቧቧ ውሃ አጠገብ ዓይናማ የሆኑ ነጫጭ ደናግላን ይሰጧቸዋል (56፡17-37)
#በድንኳኖች ውስጥ የተጨነሉ የዓይኖቻቸው ጥቁረትና ንጣት ደማቅ የሆኑ እጅግ ውብ ሴቶች በሚያረገርጉ አረንጓዴ ምንጣፎችና በሚያማምሩ ስጋጃዎች ላይ የተደላደሉ ሆነው ይሰጧቸዋል (55፡70-76)

እንደነዚህ ከላይ እንዳየናቸው ዓይነት ያሉ ጥቅሶች በቁርአኑ ውስጥ በጣም ብዙ ቦታ በተደጋጋሚ ተጽፈው እናገኛለን፡- 4:31፣ 7፡42-44፣ 9፡72፣ 19፡62-63፣ 32፡17፣ 32፡16, 35:33፣ 44:51-55፣ 76፡5፣ 76:12-13፣ 76:17-18፣ 76:19-21፣ 6:70፣ 7:179፣ 78:24፣ 88፡13-17፣ 77፡42፣ 69.23-24፣ 10፡9-10፡፡

ከላይ ከጠቀስኳቸው የቁርአን ጥቅሶች ውስጥ የተወሰኑትን በመምረጥ በቁርአኑ ውስጥ እንዴት እንደተቀመጡ እናያለን፡፡ ቀጥሎ ያሉት ጥቅሶች የቁርአኑ 37ኛው፣ 52ኘውና 56ኛው ምዕራፍ ሲሆኑ ለማረጋገጥ እንዲያመች ተብሎ ከቁርአን ላይ ቀጥታ ስካን (scan) ተደረገው የተወሰዱ ናቸው፡፡ ቀጥሎ ስካን የተደረጉትን የቁርአን ክፍሎች (37፡40-49፣ 52፡18-23፣ 56፡18-29) ይመልከቱ፡፡

## ዝሙት ከ72 ደናግላን ጋር-በሙስሊሞች ጀነት ውስጥ

በሙስሊሞች ጀነት ውስጥ የወንዶቹ ብልት ወሲብ ለመፈጸም እንደቆመና እንደተገተረ የሚቀር ለአፍታ እንኳን የማይሟሸሽ "ever-erect penises" ሲሆን የሴቶቹ ብልት ደግሞ የወሲብ ፍላጎትን በእጅጉ የሚጨምር "appetizing vaginas" ነው፡፡ እንደ ነቢያቸው መሐመድ ትምህርት ከሆነ በጀነት ውስጥ ወንዱ ሙስሊም 72 ደናግላን ሴቶች ለዝሙት ተግባር በሽልማት ይሰጡታል፡፡ ይህም በሐዲሱ ላይ በግልጽ ተቀምጧል፡፡ ታዲያ እነዚህ 72 የጀነት ደናግላን ለማንኛውም ተራ ወንድ ዝም ብለው የሚሰጡ አይደሉም! ወንዱ ሙስሊም በምድር ላይ በሕይወት እያለ በአላህ መንገድ ከተዋጋ ብቻ ነው በሽልማት መልክ የሚሰጡት፡፡ በአላህ መንገድ የተዋጋ ከሆነ ግን እነዚህን 72 ደናግላንን የሚጠቀምበትና እጅግ ብቁ የሆነ ለአፍታ እንኳን የማይሟሸሽ የወንድ ብልት "ever-erect penises" አላህ ይሰጠዋል፡፡ እስቲ ጠቅለል ባለ መልኩ መረጃዎቹን እንመልከት፡-

ከቁርአኑ እንጀምር፡- ቁርአኑ ስለ 72ቱ ደናግላን ሲናገር በሱረቱ አል-ነበእ 78፡33 ላይ *"ለጥንቁቆቹ መዳኛ ስፍራ አላቸው፡፡ አትክልቶችና ወይኖችም፣ እኩያዎች የሆኑ ጡተ ጉቻማዎችም፣ የተሞሉ ብርጭቆዎችም፣ በውስጧ ትርፍ ቃልንም ማስዋሸትንም አይሰሙም"* በማለት ይጠቅሳቸዋል፡፡ እንደ ቁርአኑ አገላለጽ ሴቶቹ ጡተ ጉቻማዎች (ጡቶቻቸው የተወጠሩና ጉች ጉች ያሉ ናቸው)፣ አትክልትና ወይን ባለበት ስፍራ ነው ያሉት፣ በመጠጥ የተሞሉ ብርጭቆዎችን ይዘዋል፣ ውሸት አይሰሙም፡፡ ወደ ሐዲሱ ስንመለስ ደግሞ ስለ እነዚሁ ሴቶች ነቢያቸው መሐመድ የሚከተለውን ትምህርት በዝርዝር አስተምረዋል፡-

*"አላህ ወደ ጀነት የሚያገባው ማንኛውም ሰው ከ72 ሚስቶች ጋር ይጋባል፡፡ ከእነርሱም ውስጥ ሁለቱ ከአማልክት ወገን የሆኑ ውብ ወጣቶች ሲሆኑ ሰባዎቹ ደግሞ በሲዖል ከሚኖሩት ከራሱ ዝርያ ውርስ የሆኑ ናቸው፡፡ ሁሉም ሴቶች ከፍተኛ የሆነ የወሲብ ፍላጎት ያለው (ቅንዝረኛ የሆነ) የወሲብ መፈጸሚያ አካል ይኖራቸዋል፡፡ እርሱ ደግሞ የማይሟሸሽ ነገር ግን እንደቆመና እንደተገተረ የሚቀር ብልት ይኖረዋል"* ነው ያሉት ነቢያቸው በትምህርታቸው፡፡ "The Messenger of Allah said, 'Everyone that God admits into paradise will be married to 72 wives; two of them are houris and seventy of his inheritance of the [female] dwellers of hell. All of them will have libidinous sex organs and he will have an ever-erect penis.' "(Sunan Ibn Majah, Zuhd (Book of Abstinence) 39)

"The Messenger of Allah said, 'The smallest reward for the people of Heaven is an

abode where there are eighty thousand servants and seventy-two houri, over which stands a dome decorated with pearls, aquamarine and ruby, as wide as the distance from al-Jabiyyah to San'a." (Al-Tirmidhi, Vol. 4, Ch. 21, No. 2687), "large, round breasts which are not inclined to hang" (Al-Tirmidhi, Sunan al-Tirmidhi, Vol. 2)

*"This [Qur'an 78:33] means round breasts. They meant by this that the breasts of these girls will be fully rounded and not sagging, because they will be virgins, equal in age." - Ibn Kathir.* Tafsir Ibn Kathir, Abridged, Volume 10 Surat At-Tagabun to the end of the Qur'an, *333-334.*

ነገሩን የበለጠ አስገራሚ የሚያደርገው ነገር የሴቶቹ ድንግልና በየጊዜው እየታደሰ የሚሄድ መሆኑ ነው፡፡ ድንግልናው በአንድ ጊዜ ግንኙነት ብቻ አይጠፋም፤ ይልቁንም በየቀኑ ይታደሳል፡፡ ስለዚህ ወንዱ ወሲብ ለመፈጸም በፈለገ በማንኛውም ጊዜ የሚያገኘው ድንግል የሆነችን ሴት ነው፡፡ የሴቷም ብልት ሁልጊዜ የወሲብ ፍላጎትን የሚጨምር ሆኖ በተለየ ሁኔታ እጅግ ጣፋጭ ይሆናል፡፡ በዚህ ምድር ላይ የእርሱን ጣዕም የሚስተካከል ነገር ፈጽሞ የለም፡፡ "The Messenger of Allah said, Each time we sleep with a Houri we find her virgin. Besides, the penis of the Elected never softens. The erection is eternal; the sensation that you feel each time you make love is utterly delicious and out of this world and were you to experience it in this world you would faint. Each chosen one [i.e. Muslim] will marry seventy [sic] houris, besides the women he married on earth, and all will have appetizing vaginas." (Al-Itqan fi Ulum al-Qur'an, p. 351) & Shaykh Gibril Haddad-How Many Wives Will The Believers Have In Paradise? (SunniPath, Question ID:4828, July 3, 2005)

በቁርአኑ፣ በሐዲሱና በአንዳንድ የቆዩ ኢስላማዊ መጽሐፎች ላይ በግልጽ እንደተጻፈው የ72ቱ ሴቶች የተከለ ሰውነታቸው ሁኔታና ባሕሪያቸው በዝርዝር ተቀምጧል፡፡

ጡቶቻቸው ጉች ጉች ያለና ክብ ትልቅ ሆኖ የተወጠረ ነው (full grown, swelling or pears-shaped breasts) Noble Quran, translated by Hilali-Khan, Qur'an 78:33

ዐይኖቻቸው አንፀባራቂዎች፣ ትልልቅ፣ ሰፋፊ፣ በጣም ውብና ማራኪዎች ናቸው፡፡ "They will recline (with ease) on Thrones (of dignity) arranged in ranks; and We shall join them to Companions, with beautiful big and lustrous eyes." Qur'an 52:20 , "And (there are) fair ones with wide, lovely eyes,-" - Qur'an 56:22 , Sahih Bukhari: Vol:4 Book :54, Number: 476

ከቅንድባቸውና ከራስ ፀጉራቸው በቀር ሌላ ቦታ ፀጉር የለባቸውም፡፡ (Hairless except

the eye brows and the head) Al-Tirmidhi, Sunan al-Tirmidhi, hadith: 5638

ከዚህ በፊት ወንድ የሚባል ያልነካቸው ፍጹም ደናግላን ናቸው፡፡ "In them will be (Maidens), chaste, restraining their glances, whom no man or Jinn before them has touched" Qur'an 55:56, "Then We have made them virgins" Qur'an 56:36, "Companions restrained (as to their glances), in (goodly) pavilions;- Then which of the favours of your Lord will ye deny?- Whom no man or Jinn before them has touched" Qur'an 55:72-74

በቡኻሪ ሐዲስ ላይ እንደተመዘገበው እነዚህ ደናግላን አይፀዳዱም፣ ሕመም የለባቸውም፣ ምራቅ ወይም ማንኛውም ዓይነት ፈሳሽ ከሰውነታቸው አይወጣም፣ የፀጉር ማበጠሪያቸው የወርቅ ነው፣ ከሰውነታቸው የሚወጣው ላብ ጠረኑ ልክ እንደዝባድ ጣፋጭ ነው፣ መልካቸውና ዕድሜያቸው አንድ ዓይነትና ተመሳሳይ ነው፣ እጅግ ውብ ሲሆኑ ከለራቸው የአባታቸውን የአዳምን ይመስላል፣ ቁመታቸው 60 ክንድ ነው፡፡ "They will not urinate, relieve nature, spit, or have any nasal secretions. Their combs will be of gold, and their sweat will smell like musk. The aloes-wood will be used in their centres. Their wives will be houris. All of them will look alike and will resemble their father Adam (in statute), sixty cubits tall." Sahih Bukhari 4:55:544, "And voluptuous women of equal age;" - Qur'an 78:33

"The Messenger of Allah said, "The first batch (of people) who will enter Paradise will be (glittering) like the full moon, and the batch next to them will be (glittering) like the most brilliant star in the sky. Their hearts will be as if the heart of a single man, for they will have neither enmity nor jealousy amongst themselves; everyone will have two wives from the houris, (who will be so beautiful, pure and transparent that) the marrow of the bones of their legs will be seen through the bones and the flesh." Sahih Bukhari 4:54:476

በጀነት ውስጥ መግቢያ ቀዳዳው አንድ ብቻ የሆነና 60 ማይል ስፋት ያለው ያሸበረቀ ዳስ አለ፡፡ በእያንዳንዱ የዳስ ጥግ ላይ እርስ በእርሳቸው የማይተያዩ ብዙ ሚስቶች አሉ፡፡ ወደ ጀነት የሚገቡ ወንዶች እነዚህን ሴቶች ይጎበኙዋቸዋል፣ ይዝናኑባቸዋል፡፡ "Allah’s Apostle said: "In Paradise there is a pavilion made of a single hollow pearl sixty miles wide, in each corner of which there are wives who will not see those in the other corners; and the believers will visit and enjoy them." Sahih Bukhari 6:60:402

በመጨረሻም አንድ ሌላ  አስገራሚ የሆነ በሀዘኔታ ዓይን ከታየ ደግሞ የሚያስለቅስ አንድ ነገር ልጠቁምና አርዕስቱንም በዚሁ ላብቃ፡፡ ነቢያቸው መሐመድ በጀነት ስላለው የዝሙት ሁኔታ እያስተማሩ እያለ ማለትም አላህ ለወንዱ እነዚያን 72 ደናግላንን ለመጠቀም የሚያስችል እጅግ ብቁ የሆነ ለአፍታ እንኳን የማይሟሸሽ እንደቆመ የሚቀር ብልት እንደሚሰጠው ሲያስተምሩ በዚህ መሀል ድንገት ከተሰባኪዎቹ መካከል አንዱ "ኦ የአላህ ነቢይ ሆይ! ያንን በእውነት ማድረግ ይችላልን?" ብሎ ይጠይቃል፡፡ ነቢያቸው መሐመድም መልስ ሲሰጡት እንዲህ አሉት፡- "ያን ጊዜ አላህ የመቶ ሰዎችን ያህል ጉልበት ይሰጠዋል" "The Messenger of Allah said, 'The believer will be given such and such strength in Paradise for sexual intercourse. It was questioned: O prophet of Allah! can he do that? He said: "He will be given the strength of one hundred persons." (Mishkat al-Masabih Book IV, Chapter XLII, Paradise and Hell, Hadith Number 24)

"The Messenger of Allah said, "The servant in Paradise shall be married with seventy two wives." Someone said, "Messenger of Allah, can he bear it?" He said: "He will be given strength for a hundred." From Zayd ibn Arqam, when an incredulous Jew or Christian asked the Prophet, "Are you claiming that a man will eat and drink in Paradise??" He replied: "Yes, by the One in Whose hand is my soul, and each of them will be given the strength of a hundred men in his eating, drinking, coitus, and pleasure."" (Sifat al-Janna, al-`Uqayli in the Du`afa', and Musnad of Abu Bakr al-Bazzar)

ተጨማሪ ምንባቦች፡-

Shaykh Gibril Haddad - How Many Wives Will The Believers Have In Paradise? - SunniPath, Question ID:4828, July 3, 2005.

72 wives await the Martyrs for Allah: Six rewards quoted in Hamas TV sermon - Al-Aqsa TV (Hamas), January 1, 2010.

British martyrs 'promised 72 virgins' - BBC News, January 23, 2003.

Beautiful virgins await Muslim Martyrs in Paradise-Palestinian TV (Fatah), February 7, 2010.

Shaykh Waleed al-Firyaan-The six blessings of the martyrs - Islam Q&A, Fatwa No. 8511.

The number of Hoors (70 or more) in Jannah for a Shaheed or a Jannathi is fixed by which hadeeth, and in which book-Mufti Ebrahim Desai, Ask-

Imam, Question No.7007, October 29, 2002.
Nashid Abdul-Khalliq-Debunking the 'Suicide for 72 Virgins' Myth- TheUg-lyTruth, March 4, 2007.
Imam Tirmidhi (209 - 279 H)-As-Sunnah Foundation of America, accessed February 20, 2012.
Sandro Magister-The Virgins and the Grapes: the Christian Origins of the Koran-Chiesa press, March 17, 2004.
Faisal Bodi-Bombing for God (Special report: Israel and the Middle East)-The Guardian, August 28, 2001.
Sheikh Yusuf Al-Qaradawi-Palestinian Women Carrying Out Martyr Operations - Islam Online, November 6, 2006.
The number of Hoors (70 or more) in Jannah for a Shaheed or a Jannathi is fixed by which hadeeth, and in which book -Mufti Ebrahim Desai, Ask-Imam, Question No. 7007, October 29, 2002.

በመጨረሻም ከዚሁ ከወሲብ ጋር በተገናኘ አንድ ነገር ማንሳት ወደድኩ፡፡ ነቢያቸው መሐመድ በጀነት ስላለው ወሲብ ይህን ያህል ጠልቀው ለተከታዮቻቸው ማስተማር ከቻሉ ለመሆኑ ራሳቸው በሕይወት በነበሩበት ወቅትስ ምን ዓይነት የትዳር ሕይወትና ወሲባዊ ግንኙነት ነበራቸው? እስካሁን ካየነው የእሳቸው አስተምህሮ አንጻር ይህን ጥያቄ ሁሉም አንባቢ መጠየቅ ያለበት ይመስለኛል፡፡ ስለዚህ ጥያቄውን በውስጣችን ይዘን ማንበባችንን እንቀጥልና ቁርአኑንና ሐዲሱን መሠረት በማድረግ የነቢያቸውን የመሐመድን የትዳርና ወሲባዊ ሕይወታቸው ምን ይመስል እንደነበር በተከታዩ ርዕስ ላይ በዝርዝር እናየዋለን፡፡

## የሙስሊሞቹ ነቢይ የመሐመድ ልዩ ችሎታቸው /Muhammad's Sexual Prowess/

ስለ 72ቱ ደናግላን ስንነጋገር በአላህ መንገድ ተዋግተው ጀብድ ለፈጸሙ ሙስሊም ወንዶች ከ72ቱ የጀነት ደናግላን ጋር ወሲብ ለመፈፀም የሚያስችል ልዩ ችሎታ እንደሚሰጣቸው አይተናል፡፡ ማለትም ለአንዱ ወንድ ሙስሊም ከ72ቱም ጋር ወሲብ ለመፈፀም የሚያስችለው የመቶ ወንዶችን ያህል ብቃት እንደሚሰጠው አይተናል፡፡ ይህ ስጦታ ለሙስሊም ወንዶች የሚሰጠው ከሞት በኋላ ባለው ሕይወታቸው በጀነት ሲሆን ለነቢያቸው መሐመድ ግን እዚሁ ምድር ላይ በሕይወት በነበሩበት ወቅት ከብዙ

ሚስቶቻቸው ጋር በአንድ ቀን ከብዙዎቹ ጋር ወሲብ ለመፈጸም የሚያስችል ልዩ ችሎታ እንደነበራቸው ሐዲሱ ይተርካል፡፡

ነቢያቸው መሐመድ ስንት ሚስቶች ነበሯቸው? የሚለውን በኋላ በዝርዝር ስለምናየው ለአሁኑ እናቆየውና በሐዲሱ ውስጥ መሐመድ ከአስራ አንድ ሚስቶቻቸው ጋር ግብረሥጋ ግንኙነት ለማድረግ ሁሉንም በአንድ ቀን በተራ ይጎበኙዋቸው እንደነበር በቡኻሪ ሐዲስ ላይ ተመዝግቦ ይገኛል፡፡ የነቢያቸው መሐመድ ተከታይ የነበረው አናስ ቢን ማሊክ የተባለው ሰው ስለመሐመድ ሲናገር “ነቢዩ ሁሉንም ሚስቶቹን ቀንና ማታ በተራ ይጎበኛቸው ነበር፤ ቁጥራቸውም አስራ አንድ ነበር” ነው ያለው፡፡ አናስ ቢን ማሊክ ይህንን ሲናገር “ታዲያ ነቢዩ ለዚህ ጥንካሬው አለውን?” ተብሎ ለተጠየቀው ጥያቄ መልስ ሲሰጥ ነቢዩ የ30 ሰዎች ያህል ጥንካሬ እንደተሰጠው ነው የተናገረው፡፡ Anas bin Malik said, "The Prophet used to visit all his wives in a round, during the day and night and they were eleven in number." I asked Anas, "Had the Prophet the strength for it?" Anas replied, "We used to say that the Prophet was given the strength of thirty (men)." (*Sahih al-Bukhari*, Volume 1, Book 5, Number 268)

በሐዲሱ ውስጥ በሌሎችም ቦታዎች ላይ ይህ ዓይነት ንግግር በተመሳሳይ አገላለፅ ብዙጊዜ ተጠቅሷል ነገር ግን ቁጥራቸውን ከአስራ አንድ ወደ ዘጠኝ ቀይሮታል፡፡ Narrated Anas bin Malik:The Prophet used to visit all his wives in one night and he had nine wives at that time. (Sahih al-Bukhari, Volume 1, Book 5, Number 282; see also parallel hadiths in Vol. 7, Book 62, Numbers 6 and 142), "The Prophet used to go round (have sexual relations with) all his wives in one night, and he had nine wives." Bukhari (62:6)

ይህ የነቢያቸው መሐመድ በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታ ግብረ ሥጋ ግንኙነት የማድረግ ልዩ ብቃትና ጥንካሬ የመጣው አላህ ለመሐመድ ማሰሮ ሙሉ ሥጋ ሰጥቷቸው ያንን ከተመገቡ በኋላ መሆኑን ራሳቸው መሐመድ ተናግረዋል፡፡ Waqidi said: “The prophet of Allah used to say that I was among those who have little strength for intercourse. Then Allah sent me a pot with cooked meat. After I ate from it, I found strength any time I wanted to do the work.” (Ibn Sa'd's Kitab Tabaqat Al-Kubra, Volume 8, Page 200)

ነቢያቸው መሐመድ በምድር ላይ ሳለ ስለነበራቸው የወሲብ ሕይወታቸው በመጽሐፎቻቸው ላይ በዚህ መልኩ መነገሩ አስገራሚ ነው በእውነት፡፡ ነቢያቸው መሐመድ በነበራቸው ወሲባዊ ፍለጎትና ምኞት የተነሳ የትኛዋንም ሴት ዐይናቸው

አይተው ልባቸው የተመኛት ሴት ካለች ከእርሷ ጋር የግድ ዝሙት ይፈጽሙ ነበር፡፡ (ወደፊት በደንብ በዝርዝር እናየዋለን፡፡) እናም አይተው የተመኙዋት ሴት ካለች ባለትድርም ብትሆን ባሏን መፍታት አለባት፡፡ ይህም ካልሆነ ባልየው ይገደልና ሚስቱን ነቢያቸው መሐመድ ይወርሳሉ፡፡ ወደፊት ከበቂ ማስረጃ ጋር እመለስበታልሁ ብያለሁ፡፡ ለአሁኑ ግን ማየት የፈለኩት ጉዳይ ነቢያቸው መሐመድ በነበራቸው ወሲባዊ ፍለጎትና ምኞት የተነሳ በምድር ላይ ዐይናቸው አይቷት ልባቸው የተመኛት ሴት ካለች ከእርሷ ጋር ዝሙት መፈጸማቸው ሳይበቃቸው በምድር ላይ ሊያገኙዋቸው ያልቻሉትን ሴቶች በጀነት አግኝተዋቸው ከእነርሱ ጋር ዝሙት ሊፈጽሙ እንደሚችሉ ራሳቸው መሐመድ በአንደበታቸው ተናግረዋል፡፡ ቀጥሎ የተጻፈውን ነገር አንብባችሁ ለሚፈጠርባችሁ መጥፎ ስሜት በጣም ይቅርታ የግድ መግለጽ ስላለብኝ ነው፡፡ አሁን ነቢያቸው መሐመድ የተናገሩትን ነገር በግልጽ ላስቀምጠው ነው፡፡ እጅግ በጣም በሚያፀይፍና በሚዘገንን ሁኔታ መሐመድ በጀነት ይኖረኛል ብለው ስላሰቡት የዝሙት ሕይወታቸው እንዲህ ነው ያሉት፡-(ለስም አጠራራቸው ክብርና ምስጋና ይግባቸውና እንደሙስሊሞቹ አጠራር ዒሳ ማለት ኢየሱስ ነው፤ መሪየም-ድንግል ማርያም፤ ኢምራን-አባቷ ኢያቄም መሆኑን ቅድሚያ ያስታውሱ)

*"በጀነት ውስጥ የዒሳ እናት መሪየም ከሚስቶቼ ውስጥ አንዷ ትሆናለች"፤ "የአላህ መልእክተኛ እንዲህ አለ፡- 'አላህ በጀነት ውስጥ ከኢምራን ልጅ ከመሪየም ጋር፣ ከፈርዖን ሚስት ጋርና ከሙሳ እኅት ጋር እንድጋባ ያደርገኛል፡፡'"* Muhammad said, "In heaven, Maryam mother of Isa will be one of my wives." Al-Siyuti (6/395)

"The Messenger of Allah said, 'Allah married me in paradise to Maryam the daughter of 'Imran and to the wife of Pharaoh and the sister of Musa.'" Tabarani (Ibn Kathir, Qisas al-Anbiya [Cairo: Dar al-Kutub, 1968/1388], p. 381- as cited in Aliah Schleifer's Mary The Blessed Virgin of Islam [Fons Vitae; ISBN: 1887752021; July 1, 1998], p. 64)

ይህ ነገር ምን ያህል እውነት መሆኑንና ለመሐመድም ለዚህ እጅግ አፀያፊ ድፍረታቸው ምን ዓይነት የአፀፋ ቅጣት እንደተሰጣቸው ለማወቅ ተአምረ ማርያም ላይ 19ኛውን ምዕራፍ መመልከት እንችላለን፡፡ እመቤታችን በረድኤትና በቸርነት ለግብፆች ተገልፃላቸው ሳለ የሚያምነውም የማያምነውም ሁሉም በገሀድ ያዩዋት ነበር፡፡ ጥያቄያቸውንም ሁሉ ታሟላላቸው ነበር፡፡ ግማሹ ዳዊትን አሳይን ሲሏት ከነበገናው አምጥታ ታሳያቸዋለች፤ ጊዮርጊስን አሳይን ሲሏት ከነፀዓዳ ፈረሱ አምጥታ ታሳያቸዋለች... ሁሉንም እንደየጥያቄዎቻቸው ታስተናግዳቸው ነበር፡፡ ከመካከላቸውም አንዱ ካህን "እመቤቴ ሆይ! እነዚህ ሙስሊሞች መሐመድ ነው ነቢያችን እያሉ

ያስቸግሩናልና እስቲ እርሱን አሳይን" ይሏታል፡፡ ያን ጊዜ የነቢያቸው መሐመድ ብልት ከግምል አንገት ጋር በእሳት ሰንሰለት ታስሮ እሳቸውም ከሰል መስለው ጠቁረው በግመሏ ላይ ተቀምጠው ኢጋንንት ከፊት ከኋላ፣ ከቀኝ ከግራ በእሳት አለንጋ እየገረፏቸውና እያዳፏቸው ከሲኦል አውጥተው የተሰበሰበው ሕዝብ ሁሉ እንዲመለከታቸው አደረጉ፡፡ የተሰበሰበው ሕዝበ ክርስቲያንም እመቤታችን ባሳየቻቸው ተአምር እጅግ ተደንቀው ለክብሯ እየሰገዱ በእንባ አመሰገኗት፡፡ በቦታው የነበሩ ሙስሊሞችም ወዲያው በክርስቶስና በድንግል እናቱ እንዳመኑ ተአምረ ማርያም ላይ በሰፊው ተጽፏል፡፡

የነቢያቸው መሐመድን ይህንን እጅግ አፀያፊና ፅርፈኛ አመለካከታቸውን ስናስብ ስለ ግል ሕይወታቸውና ስለማንነታቸውም አብረን ማሰብ መቻል አለብን፡፡ ምክንያቱም ትምህርቶቻቸውና የተናገሯቸው ነገሮች ስለ የግል ሕይወታቸውና ስለማንነታቸው በጣም በጥልቀት እንድናይ ያስገድዱናል፡፡ በክርስትናው ዓለም በክርስቶስ የተመሠረተውን የሐዲስ ኪዳን ክርስትና ሙሉ በሙሉ ለመረዳት የክርስቶስን ማንነት፣ ትምህርቱንና ሕይወቱን በጥልቀት ማወቅ የግድ እንደሆነ ሁሉ እስልምናውንም በጥልቀት ለመረዳት የነቢያቸውን የመሐመድን ማንነት፣ ትምህርታቸውንና ሕይወታቸውን በጥልቀት ማወቅ ግድ ነው፡፡ ክርስቶስን በትክክል ያላወቀ ሰው እውነተኛውን ክርስትናን በፍጹም አያውቅም፤ ነቢያቸው መሐመድንም በጥልቀት ያላወቀ እንዲሁ እስልምናን ማወቅ አይችልም፡፡ ስለዚህ ከዚህ በኋላ ባለው ርዕስ በሙሉ ስለ ነቢያቸው መሐመድ ሕይወት በጣም በስፋትና በጥልቀት እናያለን፡፡ ከዚህ ብንጀምርስ!

ቁርአኑ ‹‹ስለ ኃጢአትህም፣ ለምእመናንም ምሕረትን ለምን››, "ask forgiveness for your sin" በማለት ነቢያቸው መሐመድ ኃጢአተኛ ሰው እንደነበሩ በደንብ ይመሰክርባቸዋል፡፡ ጥቅሱን በሱረቱ መሐመድ 47፡19 ላይና በሌሎችም ቦታዎች ላይ በግልጽ ተጽፎ እናገኘዋለን፡፡ ለመሆኑ ነቢያቸው መሐመድ የሠሯቸው ስሕተቶች ወይም ኃጢአቶች ምን ምን ናቸው? እንዴትስ ሊፈጽሟቸው ቻሉ? መቼም ኃጢአተኛ መሆናቸው በገሃድ ከተነገረ አይቀር ኃጠተኛ መሆናቸውን ብቻ ጠቅሶ ማለፉ በቂ አይደለም፡፡ ስለዚህ ቁርአኑም ሆነ ሐዲሱ የሠሯቸውንም ስሕተቶች ጭምር በመጥቀስ ምን ምን እንደሆኑ ማሳየት መቻል አለባቸው፤ መሆንም ያለበትና ተገቢም የሚሆነው እንደዚያ ሲሆን ነው፡፡ ይህንንም ቀጥሎ ባለው ርዕስ ላይ ሰፋ ባለ መልኩ እናየዋለን፡-

የመሐመድ ኃጢአቶች፡- በሚገርም ሁኔታ ነቢያቸው መሐመድ ኃጢአተኛ እንደነበሩ ቁርአኑ ብዙ ቦታ ላይ አውጀባቸዋል፡፡ ተከታዮቹን የቁርአን ጥቅሶች በደንብ ተመልከቷቸው፡-

"መሐመድ ሆይ! ታገስም፤ የአላህ ተስፋ እውነት ነውና ለስሕተትህም ምሕረትን ለምን፤ ከቀትር በኋላም በማለዳም ጌታህን በማመስገን አጥራው" ሱረቱ አል-ሙእሚን 40፡55

"ስለ ስሕተትህም፣ ለምእመናንም ምሕረትን ለምን" ሱረቱ መሐመድ 47፡19

"አላህ ከኃጢአትህ ያለፈውንና የሚመጣውን ላንተ ሊምር፣ ጸጋውንም ባንተ ላይ ሊሞላ፣ ቀጥተኛውንም መንገድ ሊመራህ ከፈተልህ" ሱረቱ አል- ፊትሕ 48፡2

በመጀመሪያዎቹ ሁለቱ ጥቅሶች ላይ በአማርኛው ቁርአን ላይ "... ስለ ስሕተትህም ምሕረትን ለምን" ተብሎ ቢጻፍም የእንግሊዝኛው ቁርአን ግን "ask forgiveness for your sin" በማለት ነው የሚገልጸው፡፡ ሦስተኛው ጥቅስ ላይ ግን የአማርኛውም ቁርአን በግልጽ "አላህ ከኃጢአትህ ያለፈውንና የሚመጣውን ላንተ ሊምር..." በማለት አስቀምጦታል፡፡ ስሕተት መስራት ማለት ኃጢአት ማለት ነው፡፡ ስለዚህ "ስሕተትም" ተባለ "ኃጢአት" በየትኛውም መንገድ ቢገለጽ የአገላለጹ ጉዳይ ችግር የለውም፡፡ ከዚህ ይልቅ በአገላለጹ ላይ ችግር ያለበት "ያለፈውንና የሚመጣውን" በምትለዋ አገላለጽ ላይ ነቢያቸው መሐመድ ገና ወደፊት ለሚሠሩት ኃጢአት ሁሉ ሳይቀር ዋስትና ያገኙ መሆኑ ላይ ነው፡፡ መሐመድ በእስልምናው እምነት እንደሚሰጣቸው እጅግ ትልቅ ቦታ ኃጢአት ወይም ስሕተት መሥራታቸው በራሱ እጅግ አሳፋሪ ቢሆንም ያለፈውን ኃጢአታቸውን ይቅር መባላቸው አግባብ ነው፡፡ ግን ገና ለገና ወደፊት ለሚሠሩት ኃጢአት እንዴት የይቅርታ ዋስትና ሊሰጣቸው ቻለ? ለመሆኑ በሕይወት ዘመናቸው የሠሯቸውና ይቅር የተባሉበት ኃጢአቶታቻቸው ምን ምን ናቸው? ቀድሞ ይቅርታ ያገኙባቸውና የወደፊት ኃጢአቶቻቸውስ ምን ሊሆኑ ይችላሉ? ለማሳያ ያህል የተወሰኑትን እንይ፡-

መሐመድ ያሳደጉትን ልጅ የዛይድን ሚስት ማግባታቸው፡- ነቢያቸው መሐመድ ዛይድ የሚባል ያሳደጉት ልጅ ነበራቸው፡፡ ዛይድም ዘይነብ የተባለች ሚስት አግብቶ ይኖር ነበር፡፡ አንድ ቀን መሐመድ ልጃቸው ዛይድ ቤት ሲሄዱ ዛይድ እቤቱ አልነበረም፡፡ በቤት ውስጥ የነበረችው በቅጡ ልብስ እንኳን ያለበሰችው ዘይነብ ብቻ ነበረች፡፡ ነቢያቸው መሐመድም በቅጡ ያልተሸፈነውን ውበቷን አይተው አደነቁ፡፡ ከዚህ በኋላ ያለውን ነገር የሚያውቁት ራሳቸው መሐመድ ብቻ ናቸው፡፡ ልጃቸው ዛይድ ግን ትዳሩ ችግር ውስጥ መግባቱን ካየ በኋላ ነቢያቸው ዘንድ ሄዶ ሊፈታት እንደሚፈልግ ነገራቸው፡፡ መሐመድ ለጊዜው "ለምን ትፈታታለህ?" ቢሉትም ዘይድ ግን ሚስቱ

የእርሱ ብቻ መሆኗን ስለጠረጠረና በሁኔታው ስላላመነበት "ጠቅልለው ይውሰዷት" በሚል ስሜት ሚስቱን ፈታት፡፡ መሐመድም ያን ጊዜ ቶሎ ብለው ነው ጠቅልለው ያገቧት፡፡ ከዚያ በኋላ ነው ነቢያቸው መሐመድ ተከታዩ የቁርአን ጥቅስ ከሰማይ ወረደልኝ ያሉት፡- "ዛይድም ከእርሷ ጉዳይን በፈጸመ ጊዜ በምእምናኖች ላይ ልጅ አድርገው ባስጠጉዋቸው ሰዎች ሚስቶች ከነርሱ ጉዳይን በፈጸሙ ጊዜ በማግባት ችግር እንዳይኖርባቸው እርሷን አጋባንህ፤ የአላህም ትእዛዝ ተፈጻሚ ነው፡፡ በነቢዩ ላይ አላህ ለእርሱ በፈረደው ነገር ምንም ችግር ሊኖርበት አይገባም" ይላል ቁርአኑ፡፡ ሱረቱ አል-አሕዛብ 33፡37፡፡ የዚህን ታሪክ በሐዲሱም ላይ በብዙ ቦታዎች ተጠቅሶ እናገኘዋለን፡፡

Zaid bin Haritha came to the Prophet complaining about his wife. The Prophet kept on saying (to him), "Be afraid of Allah and keep your wife." And Thabit recited, "The Verse:- 'But (O Muhammad) you did hide in your heart that which Allah was about to make manifest, you did fear the people,' (33.37) was revealed in connection with Zainab and Zaid bin Haritha." Sahih Bukhari 9:93:516

Muhammad took his cousin Zainab as his wife after getting his adopted son Zaid to divorce her: Narrated Anas bin Malik: "The Verse: 'But you did hide in your mind that which Allah was about to make manifest.' (33.37) was revealed concerning Zainab bint Jahsh and Zaid bin Haritha." Sahih Bukhari 6:60:310

በጣም የሚገርመው በዚህኛው ጉዳይ ላይ ብቻ ሳይሆን በሌሎቹም ጉዳዮች ላይ መሐመድ ለሚሠሯት ለእያንዳንዷ ኃጢአት "በቁርአን የወረደልኝ ሕግ ነው" የሚል ሽፋንና ከለላ መስጠታቸው ነው፡፡ ይህንን ወደፊትም በሌሎች ጉዳዮች ላይ በደንብ እናየዋለን፡፡ እንደኔ እይታ በዚህ ጉዳይ ላይ 3 ችግሮች ይታዩኛል፡፡ የመጀመሪያው መሐመድ ዛይድ በሌለበት እቤቱ ሄደው ያሳደጉትን ልጅ ሚስቱን መመኘታቸው ይህ ከማንም የሚጠበቅ ባሕርይ አይደለም፡፡ አሳፋሪም ነው በእውነት፡፡ ሁለተኛው ነገር በቀጥታም ባይሆን በተዘዋዋሪ ለዛይድ ትዳር መፍረስ መሐመድ ተጠያቂ ናቸው፡፡ ስለዚህ ቢያንስ የራሳቸውን ፍላጎትና ምኞት ትተው የልጃቸውን ትዳር እንዳይፈርስ ማድረግ ይችሉ ነበር ግን ያን ማድረግ አልፈለጉም፡፡ ሦስተኛው ዛይድ ቢፈታትም እንኳን በፍጹም መሐመድ ሊያገቧት አይገባም ነበር፡፡ ቆይ ሌላው ቢቀር ሞራላዊ አስተሳሰብ የሚባል ነገር የለም እንዴ! እንዴት ነው ሰው ያሳደገውን ልጅ ሚስት የሚያገባው? ነቢያቸው መሐመድ ይህንን ዓይነቱን ድርጊታቸውን ተከታዮቻቸውም እንዲፈጽሙት ፈቅደውላቸዋል፡፡ ቁርአኑ እንዲህ ነው የሚለው፡- "ለአባቶቻቸው በማስጠጋት ጥሩዋቸው፤ እርሱ አላህ ዘንድ ትክክለኛ ነው፤ አባቶቻቸውንም ባታውቁ

በሃይማኖት ወንድሞቻችሁና ዘመዶቻችሁ ናቸው፡፡ በእርሱ በተሳሳታችሁበት ነገርም በእናንተ ላይ ኃጢአት የለባችሁም" ይላል ቁርአኑ፡፡ ሱረቱ አል-አሕዛብ 33፡5፡፡

በነገራችን ላይ በቁርአኑ ላይ ለነቢያቸው መሐመድ በጣም የተለየ የጋብቻ መብት እንዳላቸው ነው የተጻፈው፡፡ ይኸው አል-አሕዛብ የተባለው የቁርአን ማዕራፍ እንደሚያስረዳው መሐመድ የአጎታቸውንና የአክስታቸውን ልጆችም ማግባት ይችላሉ፡፡ ሱረቱ አል-አሕዛብ 33፡50-51 ላይ እንዲህ ተብሎ ነው የተጻፈው፡- "አንተ ነቢዩ ሆይ! እኛ እነዚያን መህሮቻቸውን የሰጠሃቸውን ሚስቶችህን አላህ ባንተ ላይ ከመለሰልህም እነዚያን እጅህ የጨበጠቻቸውን ምርኮኞች፣ እነዚያንም ከአንተ ጋር የተሰደዱትን የአጎትህን ሴቶች ልጆች፣ የአክስቶችህንም ሴቶች ልጆች፣ የየሹማህንም ሴቶች ልጆች፣ የየሹሜዎችህንም ሴቶች ልጆች ማግባትን ለአንተ ፈቅደንልሃል፡፡ ከእነሱ የምትሻትን ታቆያለህ፤ የምትሻትንም ወደ አንተ ታስጠጋለህ፤ ከአራቅሃትም የፈለግሃትን በመመለስ ብታስጠጋ በአንተ ላይ ኃጢአት የለብህም፡፡" በተመሳሳይ ሁኔታ በሐዲሱም ላይ ቢሆን እንዲህ ተብሎ ነው የተጻፈው፡- "አ የአላህ ሐዋርያ ሆይ! አላህ በአንተ ላይ ምንም ዓይነት እገዳ አልጣለብህም፤ እናም ለአንተ የሚሆኑ ከበቂ በላይ ብዙ ሴቶች አሉ" ሳሂህ ቡኻሪ 6፡60፡274

<u>መሐመድ የጦር ወረራ አድርገው ሳፊያ የተባለቸውን ሴት ባሏን፣ አባቷንና ወንድሟን በሰይፍ እንዲሰየፉ ካደረጉ በኋላ የዛኑ ዕለት ከእርሷ ተኝተው ማደራቸው</u>፡- ሙሉ ስሟ ሳፊያ ቢንት ሁያይ ትባላለች፡፡ ከአይሁድ ወገን ስትሆን በካይባር ጦርነት ወቅት መሐመድ በጦር ምርኮ አስገድዶ ያገባት ሚስቱ ናት፡፡ በሐዲሱ ላይ እንደተዘገበው ነቢያቸው መሐመድ ኪናን የተባለውን ወጣት ባሏን አሰቃይተው እንዲሞት ካደረጉት በኋላ ነው እርሷን ወዲያው ወደ መኝታቸው ድንኳን ይዘዋት የሄዱት፡፡ ከዚያ ቀደም ብሎ ደግሞ አባቷን ሁያይንና ወንድሟን ከሌሎች አይሁዶች ጋር በሰይፍ እንዲሰየፉ አድርገዋቸዋል፡፡ (*Bukhari* vol.2 book 14 ch.5 no.68 p.35); (vol.4 book 52 ch.74 no.143 p.92); (vol.4 book 52 ch.168 no.280 p.175 and *al-Tabari* vol.39 p.185.) http://www.muslimunited.org/topics/prophet/wives.html

በዚህም ድርጊታቸው ተከታዮቻቸው ማመን ስላቃታቸው በተኙበት ጉዳት እንዳታደርስበባቸው ሰግተው ቆመው ድንኳኑን ሲጠብቁ ነው ያደሩት፡፡ አቡ አዩብ የተባለው ተከታያቸው ሰይፉን ታጥቆ ድንኳኑን ሲጠብቅ አድሮ ጠዋት ላይ ዙሪያውን ሲንጎራደድ መሐመድ አግኝተውት ምን እየሠራ እንደሆነ ቢጠይቁት "በአይሁዳዊቷ

ሴት ምክንያት ላንተ ስለሰጋሁና ስለፈራሁ ነው” የሚል መልስ ነበር የሰጣቸው፡፡ ከእሳቸው አረመኔያዊ ድርጊት አንፃር ጠባቂው እውነቱን ነው፡፡ መሐመድም ሳፊያን በዛው ሚስታቸው እንዳደረጓት ቀርተዋል፡፡ ከላይ እንዳየነው በቁርአኑ “...እጅህ የጨበጠቻቸውን ምርኮኞች ለአንተ ፈቅደንልሃል” ተብሎ የለ! የሚገርመው መጨረሻ ላይ መሐመድን ምግባቸውን በመርዝ በክላ የገደለቻቸው እርሷ መሆኑ ነው፡፡ ይህን ራሱን የቻለ ርዕስ ስላለው ያንጊዜ በደንብ እናየዋለን፡፡ ሳፊያ ከአይሁድ ወገን የሆነች በጣም ቆንጆ ስለነበረች ሌሎቹ የመሐመድ ሚስቶቻቸው ይቀኑባትና ያንገላቷት ነበር፡፡ ይህን ብሶቷን አምርራ ለእሳቸው ስትነግር ሊያረጋጓት ይሞክሩ ነበር፡፡ በጣም በሚገርም ሁኔታ ነቢያቸው መሐመድ ለሳፊያ “አባትሽንና ባልሽን የገደልኩት በአላህ ትእዛዝና ፈቃድ ነው” ይሏት ነበር፡፡ መሐመድ ሳፊያን በእንዴት ዓይነት ሁኔታ ማርከው ወስደው ሊያገቧት እንደቻሉ ተከታዮቹ የቡኻሪ ሐዲሶች በቂ ምስክር ናቸው፡፡

Anas said, 'When Allah's Apostle invaded Khaibar, we offered the Fajr prayer there yearly in the morning) when it was still dark. The Prophet rode and Abu Talha rode too and I was riding behind Abu Talha. The Prophet passed through the lane of Khaibar quickly and my knee was touching the thigh of the Prophet. He uncovered his thigh and I saw the whiteness of the thigh of the Prophet. When he entered the town, he said, 'Allahu Akbar! Khaibar is ruined. Whenever we approach near a (hostile) nation (to fight) then evil will be the morning of those who have been warned.' He repeated this thrice. The people came out for their jobs and some of them said, 'Muhammad (has come).' (Some of our companions added, "With his army.") We conquered Khaibar, took the captives, and the booty was collected. Dihya came and said, 'O Allah's Prophet! Give me a slave girl from the captives.' The Prophet said, 'Go and take any slave girl.' He took Safiya bint Huyai. A man came to the Prophet and said, 'O Allah's Apostles! You gave Safiya bint Huyai to Dihya and she is the chief mistress of the tribes of Quraiza and An-Nadir and she befits none but you.' So the Prophet said, 'Bring him along with her.' So Dihya came with her and when the Prophet saw her, he said to Dihya, 'Take any slave girl other than her from the captives.' Anas added: The Prophet then manumitted her and married her." Sahih Bukhari 1:8:367

Narrated Anas bin Malik:The Prophet came to Khaibar and when Allah made him victorious and he conquered the town by breaking the enemy's defense, the beauty of Safiya bint Huyai bin Akhtab was mentioned to him and her husband had been

killed while she was a bride. Allah's Apostle selected her for himself and he set out in her company till he reached Sadd-ar-Rawha' where her menses were over and he married her. Sahih Bukhari 3:34:437, See also: Sahih Bukhari 5:59:522

Narrated 'Abdul 'Aziz bin Suhaib: Anas bin Malik said, "The Prophet took Safiya as a captive. He manumitted her and married her." Thabit asked Anas, "What did he give her as Mahr (i.e. marriage gift)?" Anas replied. "Her Mahr was herself, for he manumitted her." Sahih Bukhari 5:59:513, See also: Sahih Bukhari 7:62:23 & Sahih Bukhari 7:62:98

መሐመድ በ53 ዓመታቸው ከ9 ዓመት ሕጻን ልጅ ጋር ወሲብ መፈጸማቸው (A'isha)፡ በሂንዱ እምነትም ሆነ በሌላው ኃላቀር ገጠራማ ሀገራት የሕጻናት ጋብቻ የተለመደ ነገር ነው፡፡ በእኛም ሀገር ኢትዮጵያ በየገጠሩ ይህ የሕጻናት ጋብቻ አሁንም ድረስ ይፈጸማል፡፡ የሕጻና ቤተሰቦች በሚያደርጉት ስምምነትና ውል መሠረት ሕጻና ወደተዳረችበት ቤት ትወሰዳለች፡፡ የግብረ ሥጋ ግንኙነት ለመፈጸም ትንሽ ጎልመስ እስከትል ድረስ ትጠበቃለች፡፡ “በቃ አሁን እንግዲህ ደርሳለች” ተብሎ ሲታሰብ በማደጎነት ያገባት ባሏ ያን ጊዜ ከሕጻኗ ጋር ወሲብ ይፈጽማል፡፡ ይህ ዓይነቱ ሕጻን ልጅን የማግባት ባሕል በእስልምና ሀላል (የተፈቀደ) ነው፡፡ የሸሪዓውም ሕግ ቢሆን ይህንኑ ይፈቅዳል፡፡ ነቢያቸው መሐመድም ይህንን በተግባር አሳይተውናል፡፡ መሐመድ አይሻ የተባለችውን ሕጻን ያገቧት እርሷ የ6 ዓመት ሕጻን እያለች ሲሆን በ9 ዓመቷ ደግሞ ወሲብ ፈጽመውባታል፡፡ እሳቸው ከ9 ዓመቷ ሕጻን ጋር ወሲብ ሲፈጽሙ ዕድሜአቸው 53 ነበር፡፡ አይሻ እሳቸው እስከሞቱበት ጊዜ ድረስ ለ9 ዓመታት ያህልም አብራቸው ኖራለች፡፡ ሐዲሱ ላይ እንደተጻፈው አይሻ የሚከተለውን ታሪክ ስለራሷ ተናግራለች፡-

“ነቢዩ በዋስትና ያገባኝ የ6 ዓመት ልጅ እያለሁ ነበር፡፡ ወደ መዲና ሄደን በባኒ-አል-ሀሪዝ ቢን ካዝራጅ ቤት ቆየን፡፡ ከዚያም አመመኝና የራሴ ፀጉርም ተመለጠ፤ በኋላም አደገልኝ፡፡ ከሴት ጓደኞቼ ጋር ዥዋዥዌ እየተጫወትኩ እያለ እናቴ ኡም ሩማን ወደኔ መጣች፤ ምን ልታደርግልኝ እንደሆነ ሳላውቅ ወደ እርሷ ሄድኩ፡፡ ያዘችኝና በቤቱ በር ላይ እንድቆም አደረገችኝ፤ መተንፈስ አቅቶኝ ነበር፡፡ ተረጋግቼ መተንፈስ ስጀምር ውኃ ወሰደችና ራሴንና ፊቴን አሻሸችኝ፡፡ ከዚያም ወደቤት ወሰደችኝ፡፡ እቤት ውስጥ ‘አላህ ይባርክሽ፣ መልካም ዕድል’ የሚሉ የአናሳሪ ሴቶችን አየሁ፡፡ ለእነርሱም በኃላፊነት አደራ ሰጠችኝ፤ እነርሱም አዘጋጁኝ፡፡ ባልተጠበቀ ሁኔታ ንጋት ላይ ድንገት የአላህ ሐዋርያ ወደኔ መጣ፡፡ እናቴም ይዛኝ ወደእርሱ አቀረበችኝ (ሰጠችኝ) ያን ጊዜ የ9 ዓመት ልጅ

ነበርኩ” በማለት ነው አይሻ በአንደበቷ የተናገረችው፡፡

Narrated Aisha: The Prophet engaged me when I was a girl of six (years). We went to Medina and stayed at the home of Bani-al-Harith bin Khazraj. Then I got ill and my hair fell down. Later on my hair grew (again) and my mother, Um Ruman, came to me while I was playing in a swing with some of my girlfriends. She called me, and I went to her, not knowing what she wanted to do to me. She caught me by the hand and made me stand at the door of the house. I was breathless then, and when my breathing became all right, she took some water and rubbed my face and head with it. Then she took me into the house. There in the house I saw some Ansari women who said, "Best wishes and Allah's Blessing and good luck." Then she entrusted me to them and they prepared me (for the marriage). Unexpectedly Allah's Apostle came to me in the forenoon and my mother handed me over to him, and at that time I was a girl of nine years of age. Sahih Bukhari 5:58:234

“የአላህ መልእክተኛ ያገባኝ እኔ የ6 ዓመት ልጅ እያለሁ ነው፤ ወደ ቤቱ የገባሁት ግን በ9 ዓመቴ ነው፡፡” 'A'isha reported: Allah's Messenger married me when I was six years old, and I was admitted to his house at the age of nine. Sahih Muslim 8:3309, & Sahih Muslim 8:3310 “the Prophet married her when she was six years old and he consummated his marriage when she was nine years old, and then she remained with him for nine years (i.e., till his death”) Sahih Bukhari 7:62:64 , Abu Dawud 2:2116, & Sahih Bukhari 7:62:64

በአጠቃላይ እንደዚህ ዓይነት ጥቅሶችን በሐዲሱ ውስጥ ከ30 በላይ ጥቅሶችን ማግኘት ይቻላል፡፡ እጅግ አስገራሚ የሆኑ ተያያዥ ጉዳዮችም አሉ፡፡ ይህንን ጉዳይ ስለ ነቢያቸው መሐመድ ከ31 በላይ ሚስቶች በዝርዝር መመልከት ስንጀምር ያንጊዜ በጥልቀት እናየዋለን፡፡ አሁን ግን በአጭሩ ለማሳየት የፈለኩት ነገር መሐመድ ማለት በ53 ዓመታቸው ከ9 ዓመት ሕጻን ልጅ ጋር ወሲብ የመፈጸሙ መሆኑን ነው፡፡ በወቅቱ መሐመድ የአይሻን ዕድሜ 6 እጥፍ ይበልጣሉ፡፡ የዕድሜያቸውን ስሌት በተመለከተ ስሌቱን ለማወቅ እንዲረዳን እነዚህን ቁጥሮች እንናስላቸው፡፡ ነቢያቸው መሐመድ በ570 ዓ.ም ተወልደው በ632 ዓ.ም በ62 ዓመታቸው ነው የሞቱት፡፡ አይሻ በ9 ዓመቷ ወሲብ ከፈጸሙባት በኋላ እሳቸው እስከሞቱበት ጊዜ ድረስ ለ9 ዓመታት ያህል አብራው ስለኖረች ስሌቱ በትክክል ይመጣል፡፡ ስለዚህ መሐመድ በ623 ዓ.ም በ53 ዓመታቸው ከእርሷ ጋር ወሲብ ሲፈጽሙ የእርሷ ዕድሜ 9 ነበር፡፡ እሳቸው በ632 ዓ.ም

በ62 ዓመታቸው ሲሞቱ የእርሷ ዕድሜ 18 ዓመት ብቻ ነበር፡፡ ነቢያቸው መሐመድ አንድ ጊዜም እንኳ ቢሆን የነኳቸውን ሴቶች ሌላ ወንድ ፈጽሞ መንካት እንደማይችል በቁርአኑ ስለተደነገገ አይሻ ከዚህ ከአፍላ ዕድሜዋ (ከ18 ዓመቷ) በኋላ ሌላ ባል ሳታገባ እንደቀረች ነው የሞተችው፡፡ ሌላውን ዝርዝር ሁኔታ በሌላ ጊዜ በሌላ ርዕስ እመለስበታለሁ፡፡

<u>መሐመድ ትምህርታቸውን አንቀበልም እያሉ ይቃወሟቸው የነበሩትን ግለሰቦች በጨለማ ተከታዮቻቸውን እየላኩ በሰይፍ አስገድለዋል</u>፡- ነቢያቸው መሐመድ ገና ከመነሻው እምነታቸውን ሲመሠርቱና በኃይል ሲያስፋፉ በጽኑ የተቃወሟቸው በርካቶች ነበሩ፡፡ የራሳቸው አጎቶቻቸውን ጨምሮ የሥጋ ዘመዶቻቸውም የመሐመድን እምነታቸውን ሳይቀበሏቸው ቀርተዋል፡፡ የመካ ሰዎችም ትምህርታቸው ሐሰት መሆኑን የሚገልጹ ግጥሞችን እየጻፉ በመካ ከተማ ውስጥ ለኅብረተሰቡ ያሰራጩባቸው ነበር፡፡ እነዚህን ግለሰቦች ታዲያ መሐመድ ተከታዮቻቸውን በምሽት እየላኩ አንገታቸውን እያስቆረጡ ይጥሉ እንደነበር ሐዲሱ በግልጽ ታሪካቸውን መዝግቦ አስቀምጦታል፡፡

መሐመድ ለተከታዮቻቸው ቀጭን ትእዛዝ እየሰጡ እንዴት አድርገው ተቃዋሚዎቻቸውን ግለሰቦች እንዳስገደሏቸው ሐዲሱ ታሪካቸውን በስፋት መዝግቦ ያስቀመጠው ቁጥራቸው ከ32 በላይ የሆኑ ሰዎችን ነው፡፡ የሁሉም ታሪክ በቁርአኑ ላይ ከታዘዙት የግድያ አንቀፆች ጋር ተያይዞ የሚታይበት ራሱን የቻለ ርዕስ ስላለው ያን ጊዜ በሰፊው እናየዋለን አሁን ግን ለማሳያ ያህል ብቻ ጥሎ የ3 ግለሰቦችን የግድያ ሁኔታ እንመልከት፡፡ በዚህም መሠረት ለአሁኑ የምናየው 1. ካብ ቢን አሽራፍ 2. አቡ አፋቅ 3. አስማ ቢንት ማርዋን የተባሉትን ግለሰቦች የግድያ ሁኔታ ነው፡፡ እነዚህ ሦስት ግለሰቦች የመሐመድን ትምህርታቸውንና የሚሠሯቸውን ወንጀሎች ብቻ ነበር የተቃወሙት እንጂ እነርሱ የሠሩት ምንም ወንጀል አልነበረም፡፡ መሐመድም “እንዴት እምነቴን አትቀበሉም ስለማደርገው ማንኛውም ነገርስ ምን አገባችሁ?” በማለት እንዴት አድርገው እንዳስገደሏቸው በአጭሩ እናያለን፡፡

<u>ካብ ቢን አሽራፍ /Ka’b bin Ashraf/</u>፡- የሙስሊሞቹ ነቢይ መሐመድ ተከታዮቻቸውን መስጊድ ውስጥ ሰብስበው አንድ የትብብር ጥያቄ ይጠይቋቸዋል፡፡ “አላህንና ሐዋርያውን የጎዳውን ካብ ቢን አል-አሽራፍን ለመግደል ፈቃደኛ የሆነ ማነው?” ብለው ሲጠይቁ መሐመድ ቢን ማስላማ የተባለው ተከታያቸው ፈጥኖ ይነሳና “የአላህ ሐዋርያ ሆይ! እንድገለው ትፈልጋለ?” ብሎ መልሶ ሲጠይቃቸው ነቢያቸውም “አዎ” ይሉታል፡፡

ይህን ጊዜ የመግደል ኃላፊነቱን የተረከበው መሐመድ ቢን ማስላማ ካብ ቢን አሽራፍ ቤት እንዴት አድርጎ አታሎ ገብቶ መግደል እንዳለበት ያሰበውን ዘዴ ለነቢያቸው ይነግራቸዋል፡፡ በሀሳቡም ይስማሙና ጉዳዩ ማስላማ ተጨማሪ ሰው ይይዝና ካብ ቢን አሽራፍ ቤት ይሄዳል፡፡ ቀድሞ ያሰበውን የሐሰት ዘዴ ተጠቅሞ ከጓደኛው ጋር ሆኖ የካብ ቢን አሽራፍን አንገት ከቆረጡ በኋላ የአላህንና የነቢያቸውን ተቃዋሚ የመግደላቸውን ዜና ለማብሰርና ይህንን ለማሳየት ጭንቅላቱን ለነቢያቸው መሐመድ ይዘውላቸው ሄደው ከእግራቸው ስር ጥለውላቸዋል፡፡ መሐመድም ይህንን ሲመለከቱ አላህን አመስግነዋል፡፡

Allah's Apostle said, "Who is willing to kill Ka'b bin Al-Ashraf who has hurt Allah and His Apostle?" Thereupon Muhammad bin Maslama got up saying, "O Allah's Apostle! Would you like that I kill him?" The Prophet said, "Yes," Muhammad bin Maslama said, "Then allow me to say a (false) thing (i.e. to deceive Kab). "The Prophet said, "You may say it." Then Muhammad bin Maslama went to Kab and said, "That man (i.e. Muhammad demands Sadaqa (i.e. Zakat) from us, and he has troubled us, and I have come to borrow something from you... When Muhammad bin Maslama got a strong hold of him, he said (to his companions), "Get at him!" So they killed him and went to the Prophet and informed him. (Abu Rafi) was killed after Ka'b bin Al-Ashraf." Sahih Bukhari 5:59:369

"The Prophet said, 'Who will rid me of Ashraf.' Muhammad bin Maslamah, said, 'I will rid you of him, Messenger of Allah. I will kill him.' 'Do it then.' he said, 'if you can.'" Tabari VII:94

"We carried Ka'b's head and brought it to Muhammad during the night. We saluted him as he stood praying and told him that we had slain Allah's enemy. When he came out to us we cast Ashraf's head before his feet. The Prophet praised Allah that the poet had been assassinated and complimented us on the good work we had done in Allah's Cause. Our attack upon Allah's enemy cast terror among the Jews, and there was no Jew in Medina who did not fear for his life." Al-Tabari, Vol. 7, p. 97, See Also Ishaq 368

የካብ ቢን አሽራፍን ግድያ በተመለከተ የቡኻሪ ሐዲስ በብዙ ቦታ በሰፊው ዘግቦታል፡፡

See Also Sahih Bukhari 3:45:687, Sahih Bukhari 4:52:270, Sahih Bukhari 4:52:271, Sahih Muslim 19:4436, Ibn Sa'd, Vol. 1, P. 37.

አቡ አፋቅ /Abu`Afak/፡- አቡ አፋቅ ከባኑ አምር ኢብን አውፍ ጎሳዎች ውስጥ ሲሆን የ120 ዓመት አይሁዳዊ ሽማግሌ ሰው ነበር፡፡ መሐመድ አል-ሀሪዝ ቢ.ሱዋይድ የተባለውን ሰው ስላስገደሉት ይህንን ድርጊታቸውን አቡ አፋቅ በጽኑ ተቃውሟቸዋል፡፡ ተቃውሞውንም በግጥም መልክ እያጻፈ ሰዎች እንዲያነቡት ያስደርግ ነበር፡፡ መሐመድ ይህን ሲሰሙ "የዚህን ተንኮለኛ ሰው ጉዳይ የሚጨርስልኝ ማን ነው?" ብለው ሲናገሩ ሳሊም ኢብን ኡማይር የተባለው ተከታያቸው በማታ ሄዶ አቡ አፋቅን ገድሎታል፡፡ አቡ አፋቅ ማታ በተኛበት ሰይፉ ሰውነቱን አልፎ አልጋውን እስኪወጋው ድረስ ነበር በሰይፍ ወግቶ የገደለው፡፡

The apostle said, "Who will deal with this rascal for me?" Where upon Salim b. Umayr, brother of B. Amr b. Auf, one of the "weepers", went forth and killed him. Ishaq:675

Abu Afak was from Banu Amr Ibn Awf, and was an old man who had attained the age of one hundred and twenty years. He was a Jew, and used to instigate the people against the Apostle of Allah, and composed (satirical) verses [about Muhammad]. Salim Ibn Umayr who was one of the great weepers and who had participated in Badr, said, "I take a vow that I shall either kill Abu Afak or die before him. He waited for an opportunity until a hot night came, and Abu Afak slept in an open place. Salim Ibn Umayr knew it, so he placed the sword on his liver and pressed it till it reached his bed. The enemy of Allah screamed and the people who were his followers, rushed to him, took him to his house and interred him. Ibn Sa'd, Vol. 2, P. 32

አስማ ቢንተ ማርዋን /`Asma' Bint Marwan/፡- በአቡ አፋቅ መገደል አሁንም ተቃውሞዋን ስታሰማ የነበረች አስማ ቢንተ ማርዋን የተባለችው ሴት ጽሑፎችን እየጻፈች በማሰራጨቷ መሐመድ በግል ሰዎችን ማስገደላቸውን በጽኑ ስለተቃወመች የግድያ ትእዛዝ የእርሷም ዕጣ ፋንታ ሆኗል፡፡ መሐመድ እርሷንም ማን ይገላግለኝ በሚል አነጋገር ለተከታዮቻቸው ሲጠይቁ የዚህን ኃላፊነት የወሰደው ኡማይር አል-ካትሚ የተባለው ሰው ነበር፡፡ እርሱም ሌሊት በጨለማ አስማ ቢንተ ማርዋን በተኛችበት ለመሰየፍ እቤቷ ሲሄድ ከ5 ልጆቿ ጋር ተኝታ ነበር ያገኛት፡፡ እንዲያውም አንዱን ሕጻን እያጠባች ነበር፡፡ ሕጻኑን ከጡቷ ላይ መንጭቆ ይጥልና በያዘውን ሰይፍ እርሷን ይገድላታል፡፡ በቀጣዩ ቀን ጠዋት ላይ መሐመድ ዜናውን ቀድመው ሰምተው ነበርና ገዳዩን ሰው ሲያገኙት "አላህንና ሐዋርያውን በትክክል እረድተሃል" ነበር ያሉት፡፡ ገዳዩ ኡማይርም ነቢያቸው መሐመድን "ሴትዮዋኮ 5 ልጆች ነበሯት፣ ጥፋተኝነት ሊሰማኝ ይገባልን?" ብሎ ሲጠይቃቸው ከመሐመድ ያገኘው መልስ "ጥፋተኛ

አይደለህም” የሚል ነበር፡፡ ምክንያቱም አሉ ነቢያቸው “ምክንያቱም እርሷን መግደል የሁለት ፍየሎች ውጊያ ያህል ትርጉም አልባ ነበር”

When Abu `Afak had been killed she displayed disaffection. `Abdullah b. al-Harith b. Al-Fudayl from his father said that she was married to a man of B. Khatma called Yazid b. Zayd. Blaming Islam and its followers she said:

> I despise B. Malik and al-Nabit and `Auf and B. al-Khazraj. You obey a stranger who is none of yours, one not of Murad or Madhhij. Do you expect good from him after the killing of your chiefs like a hungry man waiting for a cook's broth? Is there no man of pride who would attack him by surprise and cut off the hopes of those who expect aught from him?

Asma was the wife of Yazid Ibn Zayd Ibn Hisn al-Khatmi. She used to revile Islam, offend the prophet and instigate the (people) against him. She composed verses. When the apostle heard what she had said he said, "Who will rid me of Marwan's daughter?" `Umayr b. `Adiy al-Khatmi who was with him heard him, and that very night he went to her house and killed her. First, he crept into the writer's home while she lay sleeping surrounded by her young children. There was one at her breast. Umayr removed the suckling babe and then plunged his sword into the poet. The next morning in the mosque, Muhammad, who was aware of the assassination, said, 'You have helped Allah and His Apostle.' Umayr said. 'She had five sons; should I feel guilty?' 'No,' the Prophet answered. 'Killing her was as meaningless as two goats butting heads.'" (Ibn Ishaq: 675-676 & Ibn Sa`d, Vol. 2, p. 31.)

ለማሳያነት ሲባል ከላይ ያየናቸው እነዚህ ሦስት ግድያዎች በግለሰብ ደረጃ የተፈጸሙ ናቸው፡፡ በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታ የተደሉ ሰዎች ብዛት ከ32 በላይ መሆኑን ሐዲሱ በተለያየ ቦታ መዝግቦት ይገኛል፡፡ በወቅቱም የመሐመድን የግል የሕይወት ታሪካቸውን በስፋት የጻፉት የተለያዩ ጸሐፊዎችም በየኪታቦቻቸው ላይ ይህንኑ ያረጋግጡልናል፡፡ ከእነዚህ በከፋ ሁኔታ ደግሞ ነቢያቸው መሐመድ 900 በሚሆኑ ሰዎች ላይ የጅምላ ጭፍጨፋ ማካሄዳቸውን ተከታዩ የቁርአንና የሐዲስ ዘገባ በስፋት ያስረዳናል፡፡

<u>የባኑ ቁራይዛ ጅምላ ጭፍጨፋ</u>፡- በ627 ዓ.ም ቁጥራቸው ከ800-900 የሚደርሱ ወንዶች የባኑ ቁራይዛ ጎሳ አባል የሆኑ በመዲና ከተማ ይኖሩ የነበሩ አይሁዶች በመሐመድ ትእዛዝ በአንድ ቀን በሰይፍ ተጨፍጭፈዋል፡፡ ሚስቶቻቸውና ልጆቻቸው ደግሞ ለነቢያቸው ተከታዮች በጦር ምርኮነት እንዲከፋፈሉ ሲደረጉ የተረፉትም ለባርነት ተሸጠዋል፡፡ እይታችንን ከቁርአኑ እንጀምር፡፡ ሱረቱ አል-አሕዛብ 33፡ 26 ላይ እንዲህ ተብሎ ነው የተጻፈው፡- “እነዚያንም ከመጽሐፉ ባለቤቶች የረዱዋቸውን ቁረይዟን ከምሽጎቻቸው አወረዳቸው፤ በልቦቻቸውም ውስጥ መባባትን ጣለባቸው፤ ከፊሉን ትገድላላችሁ፤ ከፊሉንም ትማርካላችሁ፡፡ ምድራቸውንም፣ ቤቶቻቸውንም፣ ገንዘቦቻቸውንምገና ያልረገጣችኋትንም ምድር አወረሳችሁ፤ አላህም በነገሩ ሁሉ ላይ ቻይ ነው” ይላል ቁርአኑ፡፡

በሐዲሱ ላይ የተመዘገበውን ታሪክ ስናይ ደግሞ እነዚህን በመዲና ከተማ ይኖሩ የነበሩ የአይሁድ ጎሳ አባላትን መሐመድ እንዴት አድርገው እንዲሰየፉ እንዳደረጓቸው በግልጽ ተጽፏል፡፡ ተይዘው እንዲታሰሩ ካደረጉ በኋላ የሙስሊሞቹ ነቢይ ወደ ገበያ ቦታ ሄደው በዚያ በጣም ትልቅና ረጅም የምሽግ ጉድጓድ እንዲቆፈር አደረጉ፡፡ ከታሰሩበት በግሩፕ በግሩፕ እየተከፈሉ መሐመድ ወዳሉበት ይወሰዱ ጀመር፡፡ ከዚያም እነዚያን ቁጥራቸው ከ800-900 የሚደርሱ ወንዶች አይሁዶች በየተራ አንገታቸው እየተሰየፈ ወደተቆፈረው ጥልቅ ጉድጓድ እንዲጣሉ ተደረገ፡፡ ነቢያቸው መሐመድ ይህን ክስተት ቁጭ ብለው ሲከታተሉት ነው የዋሉት፡፡ መሐመድ በመጨረሻ ያደረጉት ነገር ሚስቶቻቸውንና ሕጻናቱን ለተከታዮቻቸው ነው ያከፋፈሏቸው፡፡ የራሳቸውንም 1/5ኛ ድርሻቸውን ወስደዋል፡፡ (በነገራችን ላይ መሐመድ በጦር ከተዘረፈው ንብረት ውስጥ 1/5ኛው ድርሻ የአላህና የመለእክተኛው ነው የሚል ሕግ በቁርአኑ ላይ እንዲካተት አድርገዋል፡፡ ሱረቱ አል-አንፋል 8፡41 ላይ “ከማንኛውም ነገር በጦር ከከሓዲዎች የዘረፋችሁትም አንድ አምስተኛው ለአላህና ለመልእክተኛው፤ ለነቢዩ የዝምድና ባለቤቶችም፤ ለየቲሞችም፤ ለምስኪኖችም፤ ለመንገደኛም የተገባ ነው መሆኑን ዕወቁ፤ አላህም በነገሩ ሁሉ ላይ ቻይ ነው” ተብሎ ነው የተጻፈው፡፡) ስለ ግድያው ሁኔታ ቀጥሎ ያለውን ሐዲስና የታሪክ ጸሐፊዎች የዘገቧቸውን ማስረጃዎች እንመልከት፡-

“The Jews were made to come down, and Allah’s Messenger imprisoned them. Then the Prophet went out into the marketplace of Medina (it is still its market-place today), and he had trenches dug in it. He sent for the Jewish men and had them beheaded in those trenches. They were brought out to him in batches. They numbered 800 to 900 boys and men. As they were being taken in small groups to the Prophet, they said to one another, ‘What do you think will be done to us?’

Someone said, 'Do you not understand. On each occasion do you not see that the summoner never stops? He does not discharge anyone. And that those who are taken away do not come back. By God, it is death!' The affair continued until the Messenger of Allah had finished with them all." Al-Tabari, Vol. 8, p. 35, See Also Ishaq:464

Narrated Abd-Allah ibn Umar: the Prophet then killed their men and distributed their women, children and property among the Muslims. (Sahih Bukhari 5:59:362)

"Then the Apostle divided the property, wives, and children of the Qurayza among the Muslims. Allah's Messenger took his fifth of the booty." Ishaq:465

"The Prophet selected for himself from among the Jewish women of the Qurayza, Rayhanah bt. Amr. She became his concubine. When he predeceased her, she was still in his possession. When the Messenger of Allah took her as a captive, she showed herself averse to Islam and insisted on Judaism." Al-Tabari, Vol. 8, p. 38

"Then the Messenger of Allah sent Sa'd bin Zayd with some of the Qurayza captives to Najd, and in exchange for them he purchased horses and arms." "The Messenger of God commanded that furrows should be dug in the ground for the Qurayza. Then he sat down. Ali and Zubayr began cutting off their heads in his presence." Al-Tabari, Vol. 8, pp. 39-40

ሳድ የተባለው የመሐመድ ተከታይና የጦርኟ ነው የባኑ ቁራይዛ ጎሳዎች በሰይፍ እንዲሰየፉ መጀመሪያ ውሳኔ የሰጠባቸው፡፡ ይህን የሳድን ውሳኔ መሐመድ ለማስፈጸም ሳድን ያስጠሩትና ይመጣል፡፡ ሳድ ሲመጣ መሐመድ "ለመሪያችሁ ተነሱለት እንጂ!" ብሎ በክብር እንዲቀበሉት ካደረጉ በኋላ ከጎናቸው አስቀምጠውት አንድ ነገር ይነግሩታል፡፡ "እነዚህ ሕዝቦችኮ የአንተን ውሳኔ ነው የሚጠባበቁት" ሲሉት ሳድ የሰጣቸው መልስ "ተዋጊ ወንዶቹ መገደል ሲኖርባቸው ልጆቻቸውና ሴቶቻቸው እስረኞች ሆነው በምርኮ መወሰድ አለባቸው የሚል ትእዘዝ እሰጣለሁ" የሚል ነበር፡፡ ይህን ጊዜ ነው መሐመድ የሳድን ውሳኔ ፍጹም ትክክል መሆኑን በኩራት የተናገሩት፡፡ "ኦ ሳድ ሆይ! በእነርሱ መካከል የወሰንከው ውሳኔ ከንጉሡ ከአላህ ውሳኔ ጋር አንድና ተመሳሳይ ነው" በማለት ነው መሐመድ ሳድን ያሞካሹት፡፡ (ይህን ሳድ ያስተላለውን ውሳኔና መሐመድ ያፀደቁትን ውሳኔ መተመለከተ በሐዲሱ ውስጥ ብዙ ቦታ ተጠቅሶ እናገኘዋለን፣ ውሳኔውም ተግባራዊ ሲደረግ መሐመድ በመቀመጫቸው ላይ ተቀምጠው ድርጊቱን ሲከታተሉት እንደነበር ታባሪ መዘገቡን ከላይ አይተናል፡፡) When the tribe

of Banu Qurayza was ready to accept Sad's judgment, Allah's Apostle sent for Sad who was near to him. Sad came, riding a donkey and when he came near, Allah's Apostle said (to the Ansar), "Stand up for your leader." Then Sad came and sat beside Allah's Apostle who said to him. "These people are ready to accept your judgment." Sad said, "I give the judgment that their warriors should be killed and their children and women should be taken as prisoners." The Prophet then remarked, "O Sad! You have judged amongst them with (or similar to) the judgment of the King Allah." Sahih Bukhari 4:52:280, See Also: Sahih Bukhari 5:58:148, Sahih Bukhari 8:74:278, Sahih Muslim 19:4368, Sahih Muslim 19:4369

በአጠቃላይ ይህን የባኑ ቁራይዛ ጎሳዎችን ጭፍጨፋ በተመለከተ ከላይ እንዳየነው በቁርአኑም ላይ የተጠቀሰ ቢሆንም ሐዲሱ ግን ልዩ ትኩረት ሰጥቶ ብዙ ቦታዎች ላይ ደጋግሞ ሲያነሳው እናገኛለን፡፡ ምናልባት እንደ አንድ ጀብድ ታይቶ ይሆን! See Also: Sahih Muslim 26:5557, Sahih Bukhari 5:57:66, Sahih Muslim 31:5940, Sahih Bukhari 5:59:444, Sahih Bukhari 5:59:445, Sahih Muslim 19:4374, Sahih Muslim 19:4364

"The Prophet divided the properties, women, and children of Banu Quraiza among the Muslims after he had separated one-fifth for public purposes. Each man of the cavalry received two shares, one for himself and one for his horse. On that day, the Muslim force included thirty-six cavalrymen. Sa'd ibn Zayd al Ansari sent a number of Banu Qurayza captives to Najd where he exchanged them for horses and armour in order to increase Muslim military power." (Muhammad Husayn Haykal - The Life of Muhammad. (p. 338))

"Then the apostle sent for Sa'd bin Zayd al-Ansari brother of bin Abdul-Ashhal with some of the captive women of Banu Qurayza to Najd and he sold them for horses and weapons. Ibn Ishaq: 693

በሐዲሱ ውስጥ ስለጅምላ ጭፍጨፋው ይህን ያህል በተደጋጋሚ መጠቀሱ ምናልባት እንደጀብድ ታይቶ ይሆን እንዴ! ያለኩትን አነጋገሬን የዘመኑ ሙስሊም መምህራኖቻቸው ያረጋግጡልኛል፡፡ ምክንያቱም ስለ ድርጊቱ በኩራት ነው የሚናገሩት፡፡ በወቅቱ በቦታው ላይ የነበረውና ለዚህ ነገር ምስክር የሆነው አቲያህ የተባለው ሰው ሲናገር *"ከባኑ ቁራይዛ ምርኮኞች ውስጥ ነበርኩ፤ የመሐመድ የቅርብ ሰዎች ከመረመሩንና ከፈተኑን በኋላ በብልታቸው ላይ ፀጉር ማብቀል የጀመሩት ሲገደሉ ያላበቀሉት ደግሞ ሳይገደሉ ቀርተዋል፡፡ እኔም ፀጉር ማብቀል ካልጀመሩት*

*ውስጥ ነበርኩ”* በማለት ተናግሯል፡፡ Narrated Atiyyah al-Qurazi: I was among the captives of Banu Qurayza. They (the Companions) examined us, and those who had begun to grow hair (pubes) were killed, and those who had not were not killed. I was among those who had not grown hair. (Abu Dawud 38:4390)

“Then the Messenger of Allah commanded that ditches should be dug, so they were dug in the earth, and they were brought tied by their shoulders, and were beheaded. There were between seven hundred and eight hundred of them. The children who had not yet reached adolescence and the women were taken prisoner, and their wealth was seized.” (Tafsir Ibn Kathir - The Campaign against Banu Qurayzah)

“The Messenger of Allah had commanded that all of them who had reached puberty should be killed” Al-Tabari: Vol 8. (p. 38)

እንዲሁም አንድ አይሁዳዊ ሴትም እንደተሰየፈች በቦታው ላይ የነበረችው አይሻ መስክራለች፡፡ የአቡ ዳውድ ሐዲስ እንደዘገበው ስለሁኔታው አይሻ ስትምሰክር እንዲህ ነው ያለችው “ከአንዷ ሴት በቀር የተገደሉ የባኑ ቁራይዛ ሴቶች አልነበሩም፡፡ የአላህ ሐዋርያ የእርሷን ሰዎች በሰይፍ ሲገድል እርሷ (የተሰየፈችው) ሴት ከእኔ ጋር እየተነጋገረችና በኃይል እየሳቀች ነበር፡፡ በድንገት አንድ ሰው ስሟን ጠራው፡፡ የጥሪው ድምፅ ከየት እንደሆነ ስትጠይቅ ‘ምነው ምን ሆነሻል’ አልኳት፡፡ ‘አዲስና ያልተለመደ ድርጊት አደረኩ’ አለችኝ፡፡ ሰውየውም ወሰዳትና አንገቷን ሰየፈው፡፡ መገደሏን እንኳ እያወቀች እንደዚያ በጣም በኃይል መሳቋን በፍጹም ልረሳው አልችልም፡፡” Narrated Aisha: No woman of Banu Qurayza was killed except one. She was with me, talking and laughing on her back and belly (extremely), while the Apostle of Allah (peace be upon him) was killing her people with the swords. Suddenly a man called her name: Where is so-and-so? She said: I I asked: What is the matter with you? She said: I did a new act. She said: The man took her and beheaded her. I will not forget that she was laughing extremely although she knew that she would be killed. Abu Dawud 14:2665

ከጅምላ ጭፍጨፋው በኋላ ስለነበረው ሁኔታ አሁንም አይሻ ስትናገር አንድ አሳዛኝም አስቂኝም የሆነ ነገር እናገኛለን፡፡ አይሻ እንደነገረችንና ሐዲሱ እንደዘገበው ከሆነ መሐመድ ያንን የ900 ሰዎች ጅምላ ጭፍጨፋ ያካሄደው በመልአኩ ጂብሪል ትእዛዝና እረዳትነት ነው፡፡ አይሻ እንዲህ ነው ያለችው፡- “የአላህ ሐዋርያ ከአል-ካንዳቁ የትሬንች ጦርነት እንደተመለሰ የጦር መሳሪያውን አስቀምጦ ሻወር ወሰደ፡፡ ከዚያም ጂብሪል

ፀጉሩ በአቧራ እንደተሸፈነ ወደ መሐመደ መጣና 'የጦር መሳሪያህን አስቀመጥክ እንዴ!?' አለው፡፡ የአላህም ሐዋርያ 'በአላህ ስም ለመዋጋት የጦር መሳሪያዬን ገና አላስቀመጥኩም' ሲለው ጂብሪል 'ወዴት ነው ታዲያ የምትሄደው?' ብሎ ጠየቀው፡፡ ነቢዩም የባኑ ቁራይዛ ጎሳዎች ወዳሉበት እያለመከተው 'በዚህ ነው የምሄደው' አለው፡፡ እናም የአላህ ሐዋርያ ወደ እነርሱ ወጥቶ ሄደ፡፡" Narrated 'Aisha: When Allah's Apostle returned on the day (of the battle) of Al-Khandaq (i.e. Trench), he put down his arms and took a bath. Then Gabriel, whose head was covered with dust, came to him saying, "You have put down your arms! By Allah, I have not put down my arms yet." Allah's Apostle said, "Where (to go now)?" Gabriel said, "This way," pointing towards the tribe of Bani Quraiza. So Allah's Apostle went out towards them. Sahih Bukhari 4:52:68, See Also: Sahih Bukhari 1:1:5, Sahih Bukhari 5:59:443, Sahih Muslim 19:4370

በነገራችን ላይ መሐመድ ይህን የቁራይዛ አይሁዶችን ጅምላ ጭፍጨፋ ሲያካሂዱ አላህ በቀጥታ እያገዛቸው እንደሆነና የሙስሊሞቹ መላኢኮች እነ ጂብሪል እረዳቶቹ እንደነበሩ በቁርአኑም በሐዲሱም ተጠቅሷል፡፡ አንዱን የቁርአን ጥቅስ በምሳሌነት ላሳችሁ፡- ሱረቱ አል-አሕዛብ 33፡9 ላይ እንዲህ ተብሎ ነው የተጻፈው፡- "እናንተ ያመናችሁ ሆይ! ብዙ ሰራዊት በመጣባችሁና በእነርሱ ላይ ነፋስንና ያላያችኋትን ሰራዊት በላክን ጊዜ በእናንተ ላይ ያደረገላችሁን የአላህን ጸጋ አስታውሱ" ይላል፡፡ ስለዚህ በጥቅሱ ላይ "... ያላያችኋትን ሰራዊት" የምትለዋ ቃል እነጂብሪልን ለመግለጽ ነው የተነገረችው፡፡ በሐዲሱም ላይ እንደተጻፈው ነቢያቸው ቁራይዛዎችን በግጥም ለሚያንቋሽሹለት ሰዎች እንኳ ሳይቀር "ጂብሪል ከእናንተ ጋር ነው" ይላቸው ነበር፡፡ "On the day of Qurayza's (besiege), Allah's Apostle said to Hassan bin Thabit, 'Abuse them (with your poems), and Gabriel is with you" Sahih Bukhari 5:59:449

ይህን የጂብሪልንና የመሐመድን ግንኙነትና ንግግር በተመለከተ በሌላም ቦታ በታፍሲር ኢብን ካቲር ላይም ተጽፎ እናገኘዋለን፡፡ ቁርአኑ 33፡26 ላይ እንደተጠቀሰው አላህ የመሐመድን ተቃዋሚዎች በልባቸው ፍርሃትና ጭንቀት ለቆባቸው መሐመድም ድል እንዳደረጋቸው ይጠቅሳል፡፡ መሐመድም ከጦርነት እንደተመለሱ በኡም ሳላማ ቤት ሆኖ በውጊያው ወቅት የቦነነባቸውን አቧራ እየታጠቡ እያለ ጂብሪል ወደ እርሳቸው መጣ፡፡ እንደ ታፍሲር ኢብን ካቲር አገላለጽ ጂብሪል ወደ መሐመድ የመጣው ሙስሊም ሼሆችና ቃልቻዎች አሁንም ድረስ ራሳቸው ላይ የሚጠመጥሙትን በጌጥ ያሸበረቀ ጥምጣም ጠምጥሞ በቅሎ እየጋለበ ነው፡፡ መጥቶም መሐመድን እንዲህ አላቸው፡- "ምን ዓይነት ተዋጊ ነህ አንተ! የጦር መሳሪያህን አስቀምጠሃል እንዴ!"

ይላቸዋል፡፡ መሐመድም አዎንታዊ ምላሽ ሲሰጡት ጂብሪል መልሶ እንዲህ አላቸው፡- “እኛ ግን የጦር መሳሪያዎቻችንን ገና አላስቀመጥንም፤ እኔ አሁን ተመልሼ የመጣሁት ሰዎችን ከተከታተልኩ በኋላ ነው፡፡ ተነሳና ወደነዚህ ሰዎች ሂድ፤ አላህ እነዚህን ባኑ ቁራይዛዎችን እንዳንቀጠቅጥ አዞኛል” ሲላቸው መሐመድ ከሶላት በኋላ ወዲያው ነው ወደ ግድያው የሄዱት፡፡ When Allah helped him by suppressing his enemy and driving them back disappointed and lost, having gained nothing, the Messenger of Allah returned to Al-Madinah in triumph and the people put down their weapons. While the Messenger of Allah was washing off the dust of battle in the house of Umm Salamah, Jibril came to him wearing a turban of brocade, riding on a mule on which was a cloth of silk brocade. He said, "What a fighter you are! Have you put down your weapons" He said, "Yes" He said, "But we (the angels) have not put down our weapons yet. I have just now come back from pursuing the people. get up and go to these people." He said: "Where?" He said, "Banu Qurayzah, for Allah has commanded me to shake them." So the Messenger of Allah got up immediately, and commanded the people to march towards Banu Qurayzah, who were a few miles from Al-Madinah. This was after Salat Az-Zuhr... (Tafsir Ibn Kathir, Q. 33:26 -27) Tafsir Ibn Kathir - The Campaign against Banu Qurayzah

የጀርመኑ አዶልፍ ሂትለር ከ6 ሚሊዮን በላይ አይሁዳውያንን በግፍ ሲጨፈጭፍ እርሱም ሃይማኖትን መሠረታዊ ጉዳይ አድርጎ ነበር የተነሳው፡፡ “ይህን የማደርገው ለፈጣሪዬ ክብር ስል ነው” ነበር ያለው፡፡ መሐመድም በአላህ መንገድ ለመዋጋትና ለእርሱ ክብር ሲሉ ነው 900 የሚሆኑ አይሁዳውንን እንዲሰየፉ ያደረጉት፡፡ ለዚህም አላህና መላኢኮቹ እነ ጂብሪል የመሐመድ ግድያ እረዳቶች ነበሩ፡፡ በጣም በሚገርምና በሚያስደንቅ ሁኔታ መሐመድ እያንዳንዱን ድርጊታቸውን ከጂብሪል ጋር እያገናኙ ነው የሚናገሩት፡፡ ለምን ይሆን? ራሳቸው መሐመድ እንደተናገሩት ብቻውን ወደ ሂራ ተራራ ጫፍ ላይ እያወጣቸው በአፍ በአፍንጫቸው አረፋ እስኪደፍቁ ድረስ ያስጨንቃቸውና ያሰቃያቸው የነበረው በእውነት ጂብሪል ነው? ቁርአኑ መሐመድን “ስለ ኃጢአትህም፣ ለምእመናንም ምሕረትን ለምን” (47፡19፣ 40፡55፣ 47፡19፣ 48፡2) ብሎ ኃጢአተኛነታቸውን ይፋ ባደረገበት አንቀፅ መሠረት እስካሁን መሐመድ የሠሯቸውን ከባድ የሆኑ ኃጢአቶቻቸውን በዝርዝር አይተናል፡፡ እነዚህንም ለማሳያ ያህል ነው እንጂ ሙሉውን ክፍል ገና ወደፊት እናየዋለን፡፡ አሁን መሐመድ ያደረጓቸውን ድርጊቶችና የኃጢአቶቻቸውን ብዛት መዘርዘሩን ልተወውና ነቢያቸው መሐመድ ከጂብሪል ጋር ያላቸውን ግንኙነት በጥልቀት ማየት ፈለግኩ፡፡ ለምንድን ነው መሐመድ እያንዳንዷን

ድርጊታቸውን ከጂብሪል ጋር የሚያያይዙት? እንደራሳቸው አነጋገር በሰይፍ ለገደሏቸው 900 ሰዎች እረዳታቸው የነበረው ጂብሪል ነው፤ በ53 ዓመታቸው ከ9 ዓመት ሕጻን ልጅ ከአይሻ ጋር ወሲብ የፈጸሙት ሕጻኗን "ጂብሪል በህልሜ አሳይቶኛል" በሚል መነሻ ነው፡፡ እንዲያውምኮ መሐመድ በየለቱ ወደቤታቸው በገቡ ሰዓት አይሻን "ጂብሪል ሰላም ብሎሻል!" ይሏት ነበር! መሐመድ የጦር ወረራ አድርገው ሳፊያ የተባለቸውን ሴት ባሏን፣ አባቷንና ወንድሟን በሰይፍ እንዲሰየፉ ካደረጉ በኋላ የዚያኑ ዕለት ከእርሷ ጋር ተኝተው ካደሩ በኋላ በሌላ ጊዜ "አባትሽንና ባልሽን የገደልኩት በአላህ ፈቃድና ትእዛዝ ነው" ነበር ያሏት! የአላህም ትእዛዝ መጣልኝ ይሉ የነበረው በጂብሪል በኩል ነበር፤ ራሱ ቁርአኑንም ቢሆን ከሰማይ ወረደልኝ ያሉት በጂብሪል በኩል ነው! መሐመድ ያሳደጉትን ልጅ ሚስቱን ሲያገቡበት "የዛይድን ሚስት ዘይነብን እርሷን አጋባንህ፤ የአላህም ትእዛዝ ተፈጻሚ ነው" (ሱረቱ አል-አሕዛብ 33፡37) የምትለዋን የቁርአን አንቀፅ ከሰማይ ያመጣላቸው ጂብሪል ነበር! ብቻ በአጠቃላይ መሐመድ በሠሯትና ባደረጓት እንዲሁም በተናገሯት በእያንዳንዷ ነገር ውስጥ የፈረደበት ጂብሪል በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ተሳታፊ ነበር፡፡ "ይህ ለምን ሆነ?" የሚለው ጥያቄ በእውነት መጠየቅ ያለበት ጥያቄ ነው፡፡ ራሳቸው መሐመድ እንደተናገሩት ብቻቸውን ወደ ሂራ ተራራ ጫፍ ላይ እያወጣው በአፍ በአፍንጫው አረፋ እስኪደፍቁ ድረስ ያስጨንቃቸውና ያሰቃያቸው የነበረው በእውነት ጂብሪል ነው? ወይስ ሌላ አካል? ቀጥሎ ባለው ርዕስ ላይ ይህን በጣም በጥልቀት እናያለን፡-

## ሰይጣናዊ መገለጦች (Satanic Verses)

ከሁሉም በፊት እስቲ አንድ ነገር እናስብ! ያልሆነና ፍጹምም ሊሆን የማይችል ቢሆንም ግን ግዴለም ለጊዜው እኛ እናስበው እስቲ! ምን እናስብ አትሉኝም? ለስም አጠራሩ ክብር ምስጋና ይግባውና መድኃኔዓለም ኢየሱስ ክርስቶስን ከጥምቀቱ በኋላ ብዙም ሳይቆይ ወዲያው ነው በፈቃዱ ወደ ምድረ በዳ ሄዶ በሰይጣን የተፈተነው፡፡ *"ከዚያ ወዲያ ኢየሱስ ከዲያብሎስ ይፈተን ዘንድ መንፈስ ወደ ምድረ በዳ ወሰደው፥ አርባ ቀንና አርባ ሌሊትም ከጦመ በኋላ ተራበ። ፈታኝም ቀርቦ የእግዚአብሔር ልጅ ከሆንህ፥ እነዚህ ድንጋዮች እንጀራ እንዲሆኑ በል አለው"* እንዲል መጽሐፍ፡፡ ማቴ 4፡1-3፡፡

ምንም እንኳን ለባሕርይው ፍጹም የማይስማማው ቢሆንም እኛ ግን እንዲህ ብናስብስ! ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ፈተናውን ማለፍ ባይችል ኖሮ ምን ይፈጠር ነበር? ብለን እናስብ፡፡ ለምን ይህን እንዳልኩኝ በኋላ ላይ በደንብ ትረዱታላችሁና አሁን ግር አይበላችሁ፡፡ ይልቁንም አሁን አብረን እናስበው!

መድኃኔዓለም ክርስቶስ ሰይጣን ካቀረበለት ከ3ቱ ፈተናዎች በአንዱ እንኳ ተሸንፎለት ቢሆን ኖሮ ውጤቱ ምን ይሆን ነበር? በክርስቶስ ያገኘናቸውን ጸጋዎች ከዚያ በኋላ ማግኘት ይቻለን ነበር? ሰይጣን ለክርስቶስ ባቀረበው ፈተና ድል አግኝቶ ቢሆን ኖሮ አሁን በዓለም ላይ ያለው የክርስትናው ገፅታ ምን ሊመስል እንደሚችል አስባችሁታል? አዳም ለሰይጣን ፈተና ተሸንፎ ዕፀ በለስን ስለበላ አይደል 5500 ዘመን ሙሉ በአጋንንት ሲቀጠቀጥ የኖረው? ይህም ሕገ እግዚአብሔርን የመጣሱና በሰይጣን ፈተና የመሸነፉ ውጤት ነው እንጂ የአንዲት ዕፀ በለስ መበላት ለእግዚአብሔር ጉዳዩ ሆኖ አይደለም። በአጭሩ ለማለት የፈለኩት በሰይጣን ፈተና መሸነፍ ውጤቱ እጅግ የከፋ ነው። ለዚህ ነው ሰይጣን ለጌታችን ባቀረባቸው ፈተናዎች ድል አድርጎ ቢሆን ኖሮ ብለን እንድናስብ የፈለኩት፣ ምንም እንኳ ፈጽሞ ሊሆን የማይችል ቢሆንም ማለት ነው።

ጌታችን የሰይጣንን ሦስት የተለያዩ ፈተናዎች በአሸናፊነት ተወጥቷቸዋል። ለእኛም የምናሸንፍበትን ኃይልና ጥበብ ሰጥቶናል። ለክርስቶስ የቀረቡለት ሦስት ፈተናዎች ስስት፣ ትዕቢትና ፍቅረ ንዋይ (የገንዘብ ፍቅር) ነበሩ። ጌታችን 40 ቀንና 40 ሌሊት ጾሞ መራቡንና መጠማቱን ያየ ሰይጣን እነዚህን ድንጋዮች ዳቦ አድርግ በማለት በስስት ቢፈትነው "ሰው በእግዚአብሔር ቃል እንጂ በእንጀራ ብቻ አይኖርም" በማለት በትዕግስት አሸነፈው። ማቴ 4፡4። በሁለተኛው ፈተና ወደ ቤተመቅደስ ጫፍ አውጥቶ መላእክት ስለሚጠብቁህ እስቲ ራህን ከዚህ ወርውር ብሎ በትዕቢት ቢፈትነው "አምላክህን አትፈታተነው ተብሏል" በማለት በትሕትናና በጥበብ አሸነፈው። በ3ኛው ፈተና ደግሞ የዓለምን ግዛት ከነክብሩ አሳይቶት ወድቀህ ብትሰግድልኝ ይህን ሁሉ እሰጥሃለሁ ብሎ በገንዘብ ፍቅር ቢፈትነው "ለጌታህ ለአምላክህ ስገድ፣ እርሱንም ብቻ አምልክ ተብሏል" በማለት ገንዘብን በመጥላት አሸንፎታል። ሰይጣንም ከዚህ በኋላ መሸነፉን ሲያውቅ እንደ ጢስ ተኖ እንደ አቧራ በኖ ጠፍቷል።

አሁን የሙስሊሞቹን ነቢይ የመሐመድን ጉዳይ ማየት እንችላለን። ሰይጣን ልክ ጌታችንን እንደፈተነው ሁሉ ሌሎች ሰዎችንስ መፈተኑ ይቀራልን? እነዚያስ ሰዎች ፈተናውን በምን መልኩ ተወጡት? አንድ ቀላል ምሳሌ እንውሰድ፡- መሐመድ ኃጢአተኛ መሆናቸውን ቁርአኑ ራሱ በግልጽ እንደመሰከረባቸው አይተናለል። በአንጻሩ ደግሞ ቁርአኑ ክርስቶስ ምንም ኃጢአት ያልተገኘበት ንጹሕ መሆኑን ያረጋግጣል። ስለዚህ እንዲያው ነገሩን እንደ ቁርአኑ አስተሳሰብ እንኳ እንየውና ፍጹም ከኃጢአት ንጹሕ የሆነው ክርስቶስ በሰይጣን ከተፈተነ ኃጢአተኛው መሐመድ የማይፈተኑበት ምንም ምክንያት የለም። በዚህ ምንም ጥርጥር የለንም፣ ሙሉ በሙሉ እርግጠኞች

ኦማርም ነቢያቸው በሚስቶቻቸው የሚመጣባቸውን ፈጽመው እንደማይወዱ ስለሚያውቅ በመጨረሻም ነገሩን የመሐመድ የግል ጉዳይ ለማድረግ ከራሳቸው ከመሐመድ ሕይወት ጋር ለማያያዝና ለማቆራኘት አሰበ፡፡ አስቦም አልቀረ የመሐመድ ሚስቶች ወደ መፀዳጃ ሲሄዱ እየጠበቀ አብሮ መሄድና ነገሩን መሸረብ ጀመረ፡፡ ሆን ብሎ መሐመድ ይህንን እንዲሰሙና እንዲያውቁም አደረገ፡፡ መሐመድም ይህንን ሲሰሙ ቀድሞ ኦማር እንዲወርደላቸው ይፈልግ የነበረውን ሴቶችን ሂጃብ እንዲለብሱ የሚያስገድደውን ሕግ አወረዱለት፡፡ ኦማርም ይህ ትእዛዝ ከየት በእንዴት ዓይነት ሁኔታ እንደመጣ ጠንቅቆ ስለሚያውቅ ከዚያ በኋላ በየጊዜው ለአላህ ሳይሆን ለመሐመድ ምስጋናውን ያቀርብ ነበር፡፡ ቀድሞውንም ቢሆን ለፍላጎቱ መሳካት አላህን ከመለመን ይልቅ የመሐመድን ሚስቶቻቸውን ማስቸገርንና ነገሩን ወደ መሐመድ የግል ሕይወት ወስዶ መለጠፍ ነበርና የፈለገው ያም ተሳካለት፡፡ ለኦማር ምስጋና ይግባውና ይኸ ዛሬ ይህ ፊትን ተጀቡኖና ሸፍኖ መሄድ በሁሉም የዐረቡ ዓለም ያለውን የሴቶችን ሁኔታ አሳዛኝ አድርጎታል፡፡ ዕቃ መሰል ፍጡሮች አድርጓቸዋል፡፡ ቀጥሎ ባለው ፎቶ

ላይ በግራ በኩል ታስሮ ያለውን ሰማያዊ መዳበሪያና በቀኝ በኩል ሰማያዊ ሂጃብ የለበሰችውን ሙስሊም ሴት ተመልከቱ እስቲ! ምንድን ነው ልዩነታቸው?



በሳውዲ አረቢያ'ኮ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ሴቶች ፊታቸውን ሙሉ በሙሉ ሸፍነው እንዲሄዱ ከመደረጉም በላይ በሀገሪቱ ሕግ መሠረት ሴቶቹ የራሳቸው መታወቂያ እንኳን አይሰጣቸውም ነበር፡፡ ሴቶቹ መታወቂያ ይሰጣቸው የነበረው በባሎቻቸው አሊያም በአሳዳጊዎቻቸው ስም ነበር፡፡ ከላይ እንደጠቀስኩት አሁንም ማንኛውንም ሙስሊም ወንድ ጠጋ ብላችሁ «በሃይማኖታችሁ ለምንድነው ሴቶች ሂጃብ (veil) እንዲለብሱ የሚገደዱት?» ብላችሁ ብትጠይቁት እነዚያን ሁለት ምክንያቶች ማለትም "ለአላህ ትእዛዝ ታዛዦች መሆናቸውን ለማሳየትና ትሁትነታቸውን ወይም ዓይን አፋርነታቸውን አሊያም ያልተብለጨለጩ መሆናቸውን ለማሳየት ሲሉ ሴቶች ሂጃብ ይለብሳሉ" ይላችኋል፡፡ አሁን አሁን ራሳቸው ሴቶቹም ይህንን ሲያስተጋቡ መስማት የተለመደ ነገር ሆኗል፡፡ እኔም ለራሴ ይህንን ነበር ስመሰክር የነበረው፡፡ ያንን ማድረጌ ደግሞ ለአላህ ፍጹም ታማኝ የሆንኩ ስለመሰለኝ ውስጤን ለማስደሰት እሞክር ነበር፡፡ ምንም እንኳን እውነታውና ፍጻሜው ያ ባይሆንም ፊቴን ሙሉ በሙሉ ሸፍኜ በመሄድ ለአላህ ታማኝነቴን ለመግለጽ በተቻለኝ አቅም ሁሉ ሞክሬያለሁ፡፡ ሁሉን ነገር መርምሬና አጣርቼ አውቄ እስልምናውን ትቼ እስከወጣሁበት ቀን ድረስ በዚያ ሁኔታ ለአላህ ትእዛዝ ፍጹም ታማኝ ሆኜ ነበር የኖርኩት፡፡

በመሠረቱ እነዚህ "ለአላህ ትእዛዝ ታዛዦች መሆናቸውን ለማሳየትና ትሁትነታቸውን ወይም ያልተብለጨለጩ መሆናቸውን ለማሳየት ሲሉ ሴቶች ሂጃብ ይለብሳሉ" የተባሉት ሁለቱ የሸፋን የሙስሊሞቹ ምክንያቶች እንደ እነርሱ አስተሳሰብና እኛም በሰው ሰውኛው አስተሳሰብ ካሰብነው ትክክል ሊመስል ይችላል፡፡

የመጀመሪያው የአምላካቸውን ትእዛዝ ከመጠበቅ አንጻር ነው መታየት ያለበት፡፡ ሁለተኛውም ምክንታቸው ቢሆን ትክክል ነው ያልኩበት ምክንያት ከእኛ ከክርስቲያኖች አለባበስ አንጻር አይቼው ነው፡፡ እውነቱን እንነጋገርና አሁን ባለንበት በዚህ ዘመን "ጡትን፣ እንብርትንና ታፋን በአደባባይ ገልብጦ መሄድ እንደስልጣኔ በታየበት" በዚህ በዘመነ ግሎባላይዜሽን ሁሉም ባይሆኑም አንዳንድ ሴት ክርስቲያኖች እንደሚያደርጉት ከሆነ በእውነቱ ከእንደዚያ ዓይነቱ እጅግ አሳፋሪ አለባበስ አሕዛብነት ሳይሻል አይቀርም፡፡ እውነቴን ነው የምላችሁ እኔ ራሴ በፊት በእስልምናው እንደነበርኩበት ማንነቴ ሆኜ ነው የምነግራችሁ በማይረባና ባላወቁት ምክንያት ሙስሊሞቹ ሴቶች እንደዛ ተጀቡነውና ተሸፍነው መሄዳቸው ከልቤ ቢያሳዝነኝም ከዚያ በከፋ ሁኔታ አንገቷ ላይ የክርስቶስን መስቀል እንዳደረገች "ጡቴንና እንብርቴን እዩልኝ" ብላ በአደባባይ ተራቁታና ተጋልጣ የምትሄድ ክርስቲያን እኅቴን ስመለከት ልቤ የበለጠ በእጅጉ ያዝናል፡፡ እስቲ ልዩነቱን ተመልከቱ! ምክንያቱም ሙስሊሞቹ ሁኔታው ጠቀማቸውም ጎዳቸውም እነርሱ ግን ለአምላካቸው ታዛዦች መሆናቸውን ለማሳየት ሲሉ እንደዛ ተሸፍነው ይሄዳሉ፡፡ በተቃራኒው ደግሞ በክርስትናው ቤት ያለውን አፀያፊ የሆነውን የአንዳንድ እኅቶችን አለባበስ ተመልከቱ እስቲ! (አንዳንድ ማለቴን ልብ በሉልኝ፡፡ የክርስቶስ ክብር በእነርሱ የሚገለጥ ክርስትናውን በሕይወታቸው የሚሰብኩ ንጹሕ ክርስቲያን እኅቶች ስላሉ ጉዳዩ እነርሱን አይመለከትም)

ነገር ግን "ጡታችንንና እምብርታችንን በገሃድ በአደባባይ ካላሳየን የሰለጠንን አይመስለንም" ብለው ለሚያስቡ እኅቶች ከዚህም በላይ ሊነገር ይገባዋል ባይ ነኝ፡፡ እስቲ በክርስትናው ያሉ እኅቶችን ከታክሲ ሊወርዱ ሲሉ ያለውን ሁኔታ ተመልከቱ! ቲሸርት ወደታች መጎተቱኮ ራሱን የቻለ አንድ ሥራ ሆኖባቸዋል፡፡ ለዛውምኮ ቢዲ ተሸርቷ እንድትሸፍን የተፈለገውን ሰውነት ልትሸፍን ባለመቻሏ በግድ እንድትጎተት ነው የተፈረደባት፡፡ ይሄ እንዳውም የኋላውን ክፍል ለመሸፍን ነው፡፡ ከፊት ያሉት ፊታውራሪዎቹ እነጡትና እምብርማ ተመልካቾቻቸውንና አድናቂዎቻቸውን ይጠብቃሉ እንጂ በምን እዳቸው ይሸፈናሉ!

እግዚአብሔርን ፈጽሞ ከማያውቅ ከአሕዛብ ያልተሻለ ግብር እውነተኛውን አምላክ በሚያመልኩ ሰዎች ዘንድ ሲገኝ ምን ይባላል? እንዴትስ ያለ እጅግ አሳዛኝ ነገር ነው በእውነት! ለዚህ ነው ቅዱስ ጳውሎስ **«የዚህ ዓይነቱ ልማድ በአሕዛብ ዘንድ እንኳን የለም»** እያለ መልእክቱን የጻፈው፡፡ ሰሚ ግን አላገኘም፡፡ አሕዛቦቹ ምንም ለማይጠቅማቸውና ከንቱ ለሆነው እምነታቸው እንደዛ ሲጨነቁና የማያውቁትን አምላካቸውን ክብር ሲጠብቁ እውነተኛውን አምላክ በሚያመልኩ ክርስቲያኖች ዘንድ

ግን እየሆነ ያለውን ነገር እግዚአብሔር ያሳያችሁ በእውነት!

ሔዋን የአምላኳን ትእዛዝ አልጠብቅ ብላ ሕግ ስትጥስ ጸጋዋና የብርሃን ልብሷ ተገፎ ስትራቆት ያን ጊዜ ሀፍረተ ሥጋዋን በቅጠል ነበር የሸፈነችው፡፡ ሞቷን በሞቱ የሻረላት አምላክ ለሔዋን የቀደመ ክብሯን መልሶላታል፡፡ ሴቶች ልጆቿንም በ80 ቀን ጥምቀታቸው የእርሷን ሙሉ ክብርና ጸጋ ሰጥቶ ሰውነታቸውንም የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ አድርጎ ቢቀድሰውም እነርሱ በዘመኑ ያሉ ሔዋናውያን ግን... ሰውነታቸውን የአምላካቸው ስም የሚሰደብበት አደረጉት! ለዚህም ነውኮ ሐዋርያው "በእናንተ ሰበብ የእግዚአብሔር ስም በአሕዛብ መካከል በከንቱ ይሰደባል" ያለው፡፡ ሮሜ 2፡24፡፡ ግና እነርሱ ይሄ መች ገባቸው! እንዲገባቸውም አይፈልጉም፡፡ "ይህ ሰውነትሽን የሚያሳይልሽ አለባበስሽ ነው የሚያምርብሽ፣ ኋላቀር ሴት አትምሰይ፣ ዘመናዊ ሁኚ እንጂ..." እያለ ሹክ የሚላቸውና ከእግዚአብሔር የሚለያቸው የሰይጣን ፈተና መሆኑንም አላወቁትም፤ አልገባቸውም፡፡ አንዳንዶቹ እንዲያውም እንዲያውቁትና እንዲገባቸውም ፈጽሞ አይፈልጉም፡፡ የበለጠ አስከፊ የሚሆነው ደግሞ ይህ ነው-ከስሕተት ለመመለስ አለመፈለግ! «ፍካሬ ኢየሱስን» አንብቡትና ምን እንደሚል እዩት እስቲ!

እጅግ በጣም የሚገርመውና የሚዘገንነው ነገር ክርስቲያን እኅቶች ያንን የተራቆተን ገላ የሚያሳየውን ልብስ እንደለበሱ ምንም ሳይመስላቸው በእግዚአብሔር ፊት ለመቆም ወደ ቤተክርስቲያን ሰተት ብለው ቤተመቅደሱ በር ድረስ መግባት መጀመራቸው ነው፡፡ ከታክሲ ሲወርዱ ከኋላ ያለውን ሀፍረተ ሥጋቸውን ለመሸፈን የሚጎትቷን ቲሸርት እንደለበሱ ያለ ምንም መሳቀቅ ቤተክርስቲያን ውስጥ ድረስ ሰተት ብለው ይገባሉ፡፡ ገብተው ሲሳለሙና ሲሰግዱ ያችን ተጎትታ ከኋላ ያለውን ሀፍረተ ሥጋቸውን የምትሸፍን ብጥሌ ቦዲ ቲሸርት ምን ሊያደርጓት እንግሚችሉ እነርሱና የሚያያቸው አምላክ ያውቁታል፡፡

ሔዋን ጸጋዋና የብርሃን ልብሷ ተገፎ ስትራቆት ያን ጊዜ ሀፍረተ ሥጋዋን በቅጠል ነበር የሸፈነችው፡፡ የዘመኑ ሴቶችና ልጆቿ ደግሞ ከ5700 ዘመን በኋላ በሰለጠነው ዓለም በውድ ዋጋ በገዟቸው ዘመናዊ ብጥሌ ልብሶቻቸው ሀፍረተ ሥጋቸውን አጋለጡት፡፡ እነጡትና እምብርት፣ እነዳሌና ባት.... ተጋልጠውና ተራቁተው ከ5700 ዘመን በኋላ ስልጣኔንና ዘመናዊነትን ፍለጋ አደባባይ ወጡ!!! እንዲህ ነው ስልጣኔ! አደባባይ ወጥቶ በገሀድ እዩኝ ለማለት ቀጣይና ተረኛ የሴት ልጅ የሰውነት ክፍልስ ማን ይሆን? የሔዋንን ቅጠል ሆይ ወዴት አለሽ???

ወደ እስልምናው ጉዳይ ልመለስና ቀጣዩን ርዕስ በደንብ ተመለክቱልኝና አንብባችሁት ስትጨርሱ ፍርዱን ስጡ፡፡

## 7.ወሲብና ወሲባዊነት በእስልምና /Sex and sexuality in Islam/፡-

በእስልምና እምነት ውስጥ ስለ ወሲብ በግልጽ መነጋገር አልተለመደም፡፡ ተከልክሏልም፡፡ ሴቷ ከራስ ፀጉሯ እስከ እግር ጥፍሯ ድረስ በሂጃብ እንደትሸፈን የተደረገው በወንዱ ላይ የወሲብ ስሜትን እንዳትቀሰቅስ ወይም የዝሙት ጠንቅ እንዳትሆን ተብሎ ነው፡፡ ወሲብን በተመለከተ እስልምናው ውስጥ ያለውን አስተሳሰብ በግልጽ አውጥቶ ለመናገር ልክ ሂጃብ ውስጥ እንዳለችው ሴት የተደበቀና የተሸፋፈነ ይሁን እንጂ የውስጡ ገመና ግን እጅግ ብዙ ነው፡፡ ይህንን ገመና ነው በዚህ ርዕስ ስር ገልጠን የምናየው፡፡

(ማሳሰቢያ፡- ወሲብን በተመለከተ በእስልምናው ውስጥ ያለውን ነገር ገልጦ ማውጣቱና ይፋ ማድረጉ በራሱ በጣም ከባድ ነው፡፡ ቀጥሎ የምታነቡትን ጽሑፍ እኔ ስጽፈው መጥፎ ስሜት እየተሰማኝ ቢሆንም የግድ መታወቅ ስላለበት ነው ተሸፋፍኖ ያለውን ነገር በግልጽ ያወጣሁት፡፡ እኔ ከራሴ የምናገረው (የምጽፈው) አንዳች ነገር የለም ይልቁንም በቁርአኑ፣ በሐዲሱና በሸሪዓው ሕግ ላይ የተጻፉትንና መምህራኖቻቸው ያስተማሩትን ነገር ግን ብዙ ሰዎች የማያውቋቸውን ጥቅሶች ነው መልሼ የጻፍኩት፡፡ ስለዚህ ምንም እንኳን ቀጥሎ የሚነሱት ሀሳቦች የሚያሳፍሩና ለሞራላዊ እሳቤም ፍጹም የማይመቹ ቢሆኑም በእስልምና ሃይማኖታዊ መመሪያዎች ላይ የተጻፈውን ነገር መልሼ መጻፌ የሚያሳፍረኝ ነው ብዬ አላምንም፡፡ እኔ ቀጥሎ በምናገረው ነገር መታፈር ያለበት በሃይማኖታዊ መመሪያዎቹ ነው ወይስ በእኔ ነው? የሚለውን ደግሞ ጽሑፉን አንብቦ ሲጨርስ ፍርዱን እንዲሰጥ ለአንባቢው የቤት ሥራ ሰጥቻለሁ)

**7.1.በገንዘብ ክፍያ የሚፈጸም ወሲብ፡-** እስልምናው ሙስሊም ወንዶች ገንዘብ ከፍለው ወሲብ እንዲፈጽሙ ይፈቅድላቸዋል፡፡ ቁርአኑ ነው ይህን ያለው እንጂ እኔ አይለሁም፡፡ ከዚህ በፊት እንዳየነው ወንዶች ወሲብ መፈጸም የሚችሉት ካገቧቸው ሴቶችና በጦር ምርኮ ከያዟቸው ገደብ አልባ ሴቶች ጋር ነው፡፡ ቁርአኑና ሐዲሱም ይህን በግልጽ አስቀምጠውታል፡፡ ከዚህ ባሻገር ግን ሙስሊም ወንዶች የፈለጓት ሴት ጋር ሄደው ገንዘባቸውን ከፍለው ወሲብ መፈጸም ይችላሉ፡፡ ገንዘቡን ግን የግድ መክፈል አለባቸው፡፡ ቁርአኑ 4:24 ላይ እንዲህ ተብሎ ነው የተጻፈው፡- ‹‹ከሴቶችም በባል ጥብቆቹ፣ እጆቻችሁ በምርኮ የያዙዋቸው ሲቀሩ በናንተ ላይ እርም ናቸው፡፡ ይህን አላህ በናንተ ላይ ጻፈ፤ ከዚሃችሁም ከተከለከሉት ወዲያ ጥብቆች ሆናችሁ ዝሙተኞች

ሳትሆኑ በገንዘቦቻችሁ ልትፈልጉ ለናንተ ተፈቀደ፤ ከነርሱም በርሱ በመገናኘት የተጠቀማችሁባቸውን ሴቶች መህሮቻቸውን ግዴታ ሲሆን ስጡዋቸው፡፡ ከመወሰንም በኋላ በተዋደዳችሁበት ነገር በናንተ ላይ ኀጢአት የለም›› ይላል ቁርአኑ፡፡ ወንዶች ካገቧቸውና በጦር ከማረኳቸው ሴቶች ውጭ ከሌላ ሴት ጋር ወሲብ መፈጸም ክልክል ነው ካለ እንደገና መልሶ ገንዘባቸውን ከፍለው ዝሙት እንዲፈጽሙ መፍቀድ ማለት ምን ማለት እንሆነ የሚያውቁት መሐመድና እነርሱ ብቻ ናቸው፡፡

## 7.2.ለአንድ ቀን ብቻ በስምምነት የሚፈጸም ወሲብ /one-night stand/፡-

በእስልምናው "*M'uta* Marriage" እየተባለ ይጠራል፡፡ ወንዱ ሙስሊም ለአንድ ቀን አዳር ብቻ የሚፈጽመው ወሲብ ነው፡፡ ወንዱ ሌሊቱን ብቻ ነው ከሴቷ ጋር ማደር የሚጠበቅበት፤ ሲነጋ ሁለቱም አይተዋወቁም፡፡ ነገሩን የበለጠ አስገራሚ የሚያደርገው ነገር ድርጊቱ ምንም ዓይነት የጊዜ ገደብ የሌለው መሆኑ ነው፡፡ ድርጊቱን በየጊዜው መፈጸም ይቻላል፡፡ ድርጊቱን የሱኒ ሙስሊሞች የሚቃወሙት ቢሆንም የሺዓ ሙስሊሞች ግን በሰፋት ተግባራዊ ያደርጉታል፡፡ (Malcom's Persia vol.II.p.591) የመሐመድ የልጃቸው ልጅ የሆነው ኢማም ሐሰን ከ300 በላይ በትዳርና በምርኮ የያዛቸው ሴቶች እንደነበሩት ይነገርለታል፡፡ ከእነርሱ በተጨማሪ ይህን ጊዜአዊ የአንድ ቀን ጋብቻም ተግባራዊ ያድርግ እንደነበር በታሪክ ተጽፏል፡፡ በሐዲሱ ላይ ስለ ጊዜአዊ የአንድ ቀን ጋብቻ የተጠቀሰ አንድ ምሳሌ እንዶ፡- ራቢ ቢን ሳብራ የተባለው የመሐመድ ተከታያቸው እንደተናገረው መካን በተቆጣጠሩ ሰዓት ከመሐመድ ጋር ሆነው ለ15 ቀን ጉዞ አድርገው ነበር፡፡ በቆይታቸውም ወቅት መሐመድ በዚያ ካሉ ሴቶች ጋር ጊዜአዊ የስምምነት ጋብቻን በማድረግ ወሲብ እንዲፈጽሙ ፈቅደውላቸዋል፡፡ ራቢ ቢን ሳብራም ከጓደኛው ጋር ወደ መካ በወጡ ሰዓት መንገድ ላይ ካገኛት ኮረዳ ኩብል ጋር ጊዜያዊውን የጋብቻ ስምምነት ይነጋገርና ካባውን ለመክፈል ተስማምቶ ከሴቷ ጋር ወሲብ እንደፈጸመ ነው ራሱ የተናገረው፡፡ ድርጊቱንም መሐመድ ክልክል መሆኑን እስካወጁበት ጊዜ ድረስ ተግባራዊ ያደርገው እንደነበር ተናግሯል፡፡ መጀመሪያም ቢሆን ድርጊቱን እንዲፈጽሙ የፈቀዱላቸው ራሳቸው መሐመድ ናቸው በኋላ ላይ ግን ይህን ከልከለዋል፡፡

Sahih Muslim Book 008, Number 3253: "Rabi' b. Sabra reported that his father went on an expedition with Allah's Messenger during the Victory of Mecca, and we stayed there for fifteen days (i. e. for thirteen full days and a day and a night), and Allah's Messenger permitted us to contract temporary marriage with women. So I and another person of my tribe went out, and I was more handsome than he, whereas he was almost ugly. Each one of us had a cloaks, my cloak was worn out,

whereas the cloak of my cousin was quite new. As we reached the lower or the upper side of Mecca, we came across a young woman like a young smart long-necked she-camel. We said: Is it possible that one of us may contract temporary marriage with you? She said: What will you give me as a dower? Each one of us spread his cloak. She began to cast a glance on both the persons. My companion also looked at her when she was casting a glance at her side and he said: This cloak of his is worn out, whereas my cloak is quite new. She, however, said twice or thrice: There is no harm in (accepting) this cloak (the old one). So I contracted temporary marriage with her, and I did not come out (of this) until Allah's Messenger declared it forbidden."

**7.3.በፍቅር ጨዋታ ለመደሰት ድንግል የሆነች ልጃገረድ ተመራጭ ናት /virgin girl is preferable for fun and frolic/**፡- ሴት ልጅ እስከታገባ ድረስ ድንግልናዋን ጠብቃ የመቆየት ከፍተኛ የሆነ ግዴታና ኃላፊነት አለባት፡፡ በእርግጥም ይህ ይበል የሚያሰኝ ነው፡፡ ይህ ሳይሆን ቀርቶ ግን ሴቷ ድንግልናዋን ብታጣ 100 ጊዜ እንድትገረፍና በድንጋይ ተወግራ እንድትገደል ነው ቁርአኑ የደነገገው፡፡ (——-ጥቅሱን አስቀምጥ) (ሕጉ በዘመናችንም በተለያዩ ኢስላማዊ ሀገሮች እየተፈጸመ መሆኑን እውነተኛ ታሪኮችንና ጥናታዊ መረጃዎችን ለመመልከት በገጽ——-ላይ ‹‹በድንጋይ ወግሮ መግደልና የክብር ግድያ›› /honor killing & Stoning/ የሚለውን ርዕስ ይመልከቱ)

ሙስሊም ሴት ከጋብቻ በፊት ምንም ዓይነት ጾታዊ ግንኙነት ፈጽሞ አይፈቀድላትም፡፡ ይህ በራሱ ጥሩ ሆኖ ሳለ ግን ለወንዱ ደግሞ የማይሠራ ሕግ መሆኑ አስገራሚ ነው፡፡ ወንዱ ሙስሊም ከማግባቱም በፊት መወስለት ይፈቀድለታል፡፡ ይበልጥ የሚያስገርመው ነገር ዝሙት እንዲፈጽም የሚፈቀድለት ነጻ ከሆነች ሙስሊም ሴት ጋር ሳይሆን ከእስልምና እምነት ውጭ ካሉ ሴቶች ጋር መሆኑ ነው፡፡ ከጦር ምርኮኞች ወይም ባርነት ከተያዙ ሴቶች ጋር አሊያም ገንዘቡን ከፍሎ ዝሙት መፈጸም ይፈቀድለታል ነገር ግን ነጻም ብትሆን እንኳ ሙስሊሟን ሴት እንዲነካ አይፈቀድለትም፡፡ "The thought of indulging in premarital sex by an adult woman is absolutely unthinkable in Islam (For men it is a different story altogether. As we shall see later, it is possible for an unmarried Muslim man to be engaged in sex with slavegirls/captive/infidel women but not with free Muslim women.")

አሁን ደግሞ ነቢያቸው መሐመድ ድንግል የሆነች ልጃገረድ ተመራጭ መሆኗን ያስተማሩበትን ትምህርት እንይ፡- ከመሐመድ ተከታዮች ውስጥ አንድ ድንግልና

የሌላትን ሴት እንዳገባ ሲነግራቸው ‹‹ድንግል የሆነችውን ሴት ለምን አላገባህም?›› እያሉ ይጠይቁት ነበር፡፡ ይህንንም ከዚህ በፊት በገጽ—-ላይ ‹‹ዕድሜያቸው ገፋ ያሉ ሴቶች ከትዳራቸው እየተፈናቀሉ በኮረዳዎች መተካት አለባቸው›› በሚለው ርዕስ ስር በደንብ አይተነዋል፡፡ የቀሩትን ጥቅሶች ቀጥሎ እናያቸዋለን፡፡

መሐመድ ጀቢር ቢን አብዱላህ የተባለው ተከታያቸው ሚስት እንዳገባ ሲነግራቸው "ያገባኸው ድንግል የሆነችን ሴት ነው ወይስ ድንግል ያልሆነች ሠራተኛ ሴት?" ብለው ይጠይቁታል፡፡ ጀቢርም በሥራ ላይ ያለች ሚስት እንዳገባ ሲነግራቸው መሐመድ "አብራህ የምትጫወትና አንተም የምታጫውታት ወጣትና ድንግል የሆነች ልጃገረድ ለምን አላገባህም?" በማለት ነው የጠየቁት፡፡ ተከታዮቹን ሦስት ሐዲሶች በደንብ ተመልከቷቸው፡፡

Sahih Bukhari Volume 7, Book 62, Number 16: Narrated Jabir bin Abdullah: While we were returning from a Ghazwa (Holy Battle) with the Prophet, I started driving my camel fast, as it was a lazy camel A rider came behind me and pricked my camel with a spear he had with him, and then my camel started running as fast as the best camel you may see. Behold! The rider was the Prophet himself. He said, 'What makes you in such a hurry?" I replied, I am newly married "He said, "Did you marry a virgin or a matron? I replied, "A matron." He said, "Why didn't you marry a young girl so that you may play with her and she with you?" When we were about to enter (Medina), the Prophet said, "Wait so that you may enter (Medina) at night so that the lady of unkempt hair may comb her hair and the one whose husband has been absent may shave her pubic region.

Sahih Bukhari Volume 3, Book 38, Number 504: Narrated Jabir bin 'Abdullah: "I was accompanying the Prophet on a journey and was riding a slow camel that was lagging behind the others. When we approached Medina, I started going (towards my house). The Prophet said, "Where are you going?" I said, "I have married a widow." He said, "Why have you not married a virgin to fondle with each other?"

Sahih Muslim Book 008, Number 3459: Jabir b. 'Abdullah reported: "I married a woman, whereupon Allah's Messenger said to me: Have you married? I said: Yes. He said: Is it a virgin or a previously married one (widow or divorced)? I said: With a previously married one, whereupon he said: Where had you been (away) from the amusements of virgins? Shu'ba said: I made a mention of it to 'Amr b. Dinar and he said: I too heard from Jabir making mention of that (that Allah's Apostle) said: Why didn't you marry a girl, so that you might sport with her and she might

sport with you?"

ከላይ ካየናቸው በመጀመሪያው ሐዲስ መጨረሻ ላይ ሴቷ ለወሲብ በቂ ዝግጅት ማድረግ እንዳለባት ነው መሐመድ የተናገሩት፡፡ ይህም ባሏ ወጥቶ እስኪመለስ ድረስ ሴቷ የብልቷን ጸጉር ላጭታ መጠበቅ አለባት፡፡ በሌላም ቦታ መሐመድ እንዳስተማሩት ወንዱ ለጉዞ ወጥቶ ሲመለስ ሚስቱ የብልት ጸጉሯን ሳትላጭና የራስ ጸጉሯን ሳታበጥር ወደ ቤት መግባት የለበትም፡፡ "the Prophet said, "Wait so that you may enter (Medina) at night so that the lady of unkempt hair may comb her hair and the one whose husband has been absent may shave her pubic region." ሳሂህ ቡኻሪ 7፡62፡16፡፡

Sahih Bukhari Volume 7, Book 62, Number 173: Narrated Jabir bin 'Abdullah: The Prophet said, "If you enter (your town) at night (after coming from a journey), do not enter upon your family till the woman whose husband was absent (from the house) shaves her pubic hair and the woman with unkempt hair, combs her hair"

ለመሆኑ መሐመድ ስለ ወሲብ ይህን ያህል ትኩረት ሰጥተው መናገር ለምን አስፈለጋቸው? እውነት እንነጋገር እስቲ እንዲያው አሁን ስለ ብልት ጸጉር ተላጨ አልተላጨ አሁን ለዚህ ተልካሻ ነገር ሕግ መውጣት ነበረበት? ይህ በትክክል የሚያሳየን ነገር ቢኖር ወሲብ በእስልምና ውስጥ በግልጽ የማይወራ ቢሆንም ነገር ግን ትልቅ ቦታ የሚሰጠው መሆኑን ነው፡፡

<u>7.4.ጤናማ ያልሆነ የወሲብ ፍላጎት /Sexual perversion/:-</u> ሙስሊም ወንዶች መንገድ ላይ እየሄዱ ድንገት የሆነች ቆንጆ ሴት አይተው ምኞት ቢያስቸግራቸው በዚያው ቅፅበት ሮጠው ወደ ቤታቸው ሄደው ከሚስታቸው ጋር ወሲብ መፈጸም አለባቸው፡፡ መሐመድ ይህን ድርጊት ራሳቸው በተግባር ከፈጸሙት በኋላ ነው ተከታዮቻቸውም እንደ እርሳቸው እንዲያደርጉ ያስተማሯቸው፡፡ "Jabir reported that Allah's Messenger saw a woman, and so he came to his wife, Zainab, as she was tanning leather and had sexual intercourse with her. He then went to his Companions and told them: The woman advances and retires in the shape of a devil, so when one of you sees a woman, he should come to his wife, for that will repel what he feels in his heart." (Sahih Muslim Book 008, Number 3240)

ከዚህ የመሐመድ ትምህርትና ድርጊት ብዙ አገራሚ ነገሮችን እናገኛለን፡፡ የመጀመሪያው ወንዱ ካለበት ሁኔታ አንጻር ቦታና ጊዜ ሳይወስነው በማንኛውም ሰዓት ስሜቱን መቆጣጠር የማይችል ተራ ፍጡር መሆኑ ነው፡፡ እስቲ ተመልከቱ ሰውየው

ሥራ ቦታ ነው ብለን እናስብ! ለምሳሌ የሕክምና ባለሙያ፣ ሾፌር፣ የመንግሥት ሠራተኛ፣ በግብርና ሥራ ላይ ያለ ገበሬ... ሊሆን ይችላል፡፡ እንግዲህ በእነዚህና መሰል የሥራ ቦታዎች ላይ ሆኖ ወንዱ እዚያው ሥራ ቦታው ላይ ሴት አይቶ ስሜቱ ቢመጣ በዚያው ቅፅበት ወደ ቤቱ ሄዶ ወሲብ መፈጸም አለበት ማለት ነው፡፡ እንግዲህ ስንት ጊዜ ሴት አይቶ ተመኝቶ ስንት ጊዜ ወደ ቤቱ ሊመላለስ እንደሚችል ለመገመት አስቸጋሪ ነው፡፡ እሺ እርሱስ ሴት በተመለከተና ስሜቱ በመጣ ሰዓት ሥራውንም ትቶ ወደ ቤት ሲመላለስ ይዋል ይህ የእኛ የሴቶቹ ችግር አይደለም፣ ግን በሌላ በኩል ያለውን አንድምታ ልብ ብላችሁታል? እርሱ ስሜቱ ተነስቶበት ወደ ቤት ሲሄድ ሚስቱ እቤት ውስጥ የግድ መገኘት አለባት፡፡ ሴቷ ባሌ በማንኛውም ሰዓት ሊመጣ ይችላል ብላ እቤት ውስጥ ቁጭ ብላ እርሱን ብቻ መጠበቅ አለባት ማለት ነው፡፡ ይህም ሴቷ ወንዱ ስሜቱን የሚያረካባት የወሲብ መጠቀሚያው ብቻ መሆኗን ነው የሚያሳየው፡፡ አዎ ልክ ነው፤ ትርጉሙ እንደዚያ ነው፡፡ ከቤት ወጥታ ሥራ መሥራት ካልቻለች እርሷ ማለት ለወሲብ እርካታ የምታስፈልግ ተራ ዕቃ /fetish objects/ ናት ማለት ነው፡፡ እውነቴን ነው በዚህ እርግጠኛ ይሁኑ፡፡ እንዲያውም በሌላ ቦታ ሐዲሱ ምን ይላል መሰላችሁ!? ሴቷ ምግብ ማብሰያ ቤት ሆና ምግብ እያበሰለች እንኳን ቢሆን ወንዱ በዚያች ቅፅበት ለወሲብ ከፈለጋት እያበሰለች ያለውን ምግብ እሳቱ ላይ ትታ መሄድ አለባት፡፡ ይህ ባይሆን ግን መላእክት ሲገርፏት ያድራሉ ይላል ሐዲሱ፡፡ ሌላው ቢቀር ሴቷ መስጊድ ሄዳ ከምትሰግድ ይልቅ እቤት ውስጥ ብትሰግድ ይመረጣል፡፡ (የሐዲሱን ማስረጃ አስገባ———)

ቀደም ብለን ባየናቸው ሁለት ሐዲሶች ላይ ሌላም የምናስተውለው ነገር አለ፡፡ እሺ ሴቷ እቤት ውስጥ ቀኑን ሙሉ ቁጭ ብላ ትጠብቀው አሊያም የምታበስለውን ምግብ ትታው ሄዳ ምግቡም ይረር እንበል፡፡ ግን ደግሞ ሴቷ ለወሲብ ዝግጁ መሆኗ አለመሆኗ ወይም የፍላጎቷ ጉዳይ ፈጽሞ ግንዛቤ ውስጥ አለመግባቱ እንዴት የሚያሳዝን ነገር ነው! የእርሷ ስሜት መጠበቅም ፈጽሞ ከግንዛቤ ውስጥ አልገባም፡፡ እንዲገባም አልተፈለገም፡፡ ያለ ምንም ማጋነን ሴቷ ወንዱ የወሲብ እርካታውን እንዲወጣባት የምታስፈልግ ዕቃ /fetish objects/ ተደርጋ ነው የተቀመጠችው፡፡ ስለዚህ እኔ «በእስልምናው ውስጥ ሴት ልጅ ለወንዱ የዝሙት መጠቀሚያ ከመሆን ያለፈ ቦታ የላትም» የሚለው አገላለጽ በጣም ትክክለኛና ገላጭ የሆነ ተስማሚ አነጋገር ነው እላለሁ፡፡

ከዚሁ ከመጀመሪያ ሐዲስ ጋር በተያያዘ ሌላው ሊታለፍ የማይገባው ጉዳይ መሐመድ ስለ ሴት ልጅ የተናገሩት አንድ ነገር አለ፡፡ መንገድ ላይ በመታየቷ ብቻ

የወንዱ ስሜት በመቀስቀሱ ምክንያት «ሴቷ ሰይጣን ወይም እርኩስ መንፈስ ናት» ነው መሐመድ ያሉት፡፡ "...The woman advances and retires in the shape of a devil, so when one of you sees a woman, he should come to his wife, for that will repel what he feels in his heart." (ሳሂህ ሙስሊም 8:3240) ይህም በግልጽ የሚያሳየው ነገር ቢኖር መሐመድ ለሴት ልጅ ያላቸው አመለካከት እስከዚህ ድረስ መሆኑን ነው፡፡

7.5.ሙሉ ያልሆነ የወሲብ እርካታ /incomplete sexual pleasure/፡- ከላይ ባለው ርዕስ ላይ ስንነጋገር በእስልምናው ውስጥ የሴቷ ፍላጎት ወይም የስሜቷ ጉዳይ መጠበቅም አለመጠበቅ ፈጽሞ ከግንዛቤ ውስጥ አይገባም ብዬ ነበር፡፡ ይህንን የሚያረጋግጡልኝ ሁለት ምሳሌዎችን ላሳያችሁ፡፡ በመሐመድ ትምህርት መሠረት ወንዱ ወሲብ እየፈጸመ እያለ በመሀል እርሱ ስሜቱን ካወጣና ከበቃው ዘሩን ሳያፈስ ወሲብ ማድረጉን ማቋረጥ ይችላል፡፡ ማድረግ የሚጠበቅበት ብልቱን ማጠብና መስገድ ነው፡፡ የእርሷን ስሜት ከምንም ሊቆጥረው አይገባም፡፡ "Ubayy Ibn Ka'b reported: I asked the Messenger of Allah about a man who has sexual intercourse with his wife, but leaves her before orgasm. Upon this the Prophet said: He should wash the secretion of his wife, and then perform ablution and offer prayer." (Sahih Muslim Book 3, Number 0677)

"Zaid b. Khalid al-Jubani reported that he askad Uthman b.'Affan: What is your opinion about the man who has sexual intercourse with his wife, but does not experience orgasm? Uthman said: He should perform ablution as he does for prayer, and wash his organ. 'Uthmin also said: I have heard it from the Messenger of Allah." (Sahih Muslim Book 3, Number 0680)

ለመሆኑ በእስልምናው ውስጥ ስለ ወሲብ ይህን ያህል ትኩረት ተሰጥቶ መነገር ለምን አስፈለገ? እንደነዚህ ዓይነት ለዘቀጡና ከአእምሮ በታች ለሆኑ ጉዳዮች እንኳን ሕግ ማውጣት ይቅርና ከነጭራሹ መነገርም አልነበረባቸውም፡፡ መሐመድ ግን ወሲብን በመለከተ እያንዳንዷን ጥቃቅን ነገር እንዴት አድርገው በልዩ ትኩረት እንደተመለከቷትና ትልቅ ቦታ እንደሰጧት መታዘብ ትችላላችሁ፡፡

ርዕሳችን «ወሲብና ወሲባዊነት በእስልምና» /Sex and sexuality in Islam/ መሆኑን አንርሳ፡፡ እንዲያው ነገሩ በግልጽ መነገርና መታወቅ ስላለበት ነው እንጂ እኔም እንደዚህ ዓይነት ነገሮችን ስጽፍ በውስጤ ብዙ ደስ የማይሉ ስሜቶች እየተፈጠሩብኝ ነው፡፡ እናንተም ይህን የአሕዛብ እርኩሰት ስታነቡ ከእኔ በበለጠ መጥፎ ስሜት እንደሚሰማችሁ አውቃለሁ፡፡ ነገር ግን ወሲብ በእስልምና እምነት ውስጥ በግልጽ ባይወራም የቱን ያህል ትልቅ ቦታ እንደተሰጠው ለማሳየት ስለፈለኩ ነው ይህን ሁሉ

የረከሰ ነገር የጠቀስኩት፡፡ በዚሁ መሠረት እይታችንን እንቀጥላለን፡፡

## 7.6.የሴቷን ሰውነት ለመደሰቻነት መጠቀም /Enjoyment of a female's body/፡-

"Narrated Abdullah ibn Abbas: A man came to the Prophet, and said: 'My wife does not prevent the hand of a man who touches her. He said: Divorce her. He then said: I am afraid my inner self may covet her. He said: Then enjoy her.'" (Sunaan Abu Dawud: Book 11, Number 2044). በእስልምና ሴት ልጅ ወንዱ ስሜቱን የሚያረካባት የወሲብ መጠቀሚያው ብቻ መሆኗን ቀደም ብለን አይተናል፡፡ ለመሐመድና ለተከታዮቻቸው ሴት ማለት ከቤት ውስጥ ሳትወጣ ለወሲብ እርካታ ብቻ የምታስፈልግ /fetish objects/ ናት፡፡ ወንዱ የራሱን ስሜት ብቻ ከተወጣባት በኋላ ከአጠገቧ ዘወር የሚልባት ከመሆኗም በላይ ምንም ስሜት እንደሌላት ግዑዝ ነገር ነው የተቆጠረችው፡፡ እንደዚያ ባይሆንማ ኖሮ የእርሷ ስሜትና ፍላጎት ከግንዛቤ ውስጥ ይገባ ነበር፡፡ በግንኙነታቸው ወቅት እርሷ ምንም ዓይነት ድርሻ የላትም፡፡ ሰውነቷ ብቻ ነው የወንዱ መደሰቻ የሚሆነው፡፡ ይሄ ብቻ አይደለም፣ በእስልምናው ውስጥ የሴት ልጅ ሰውነቷ ለወንዱ በገንዘቡ የገዛው መደሰቻው እንደሆነ ተደርጎ ነው የሚቆጠረው፡፡ ለማመን ይከብድ ይሆናል እውነቱ ግን ይኸው ነው፡፡ ለዚያውም ለወሲብ ተግባር የሚውለውን እያንዳንዱን የሰውነት ክፍሏን (sex organs) ወንዱ በገንዘቡ የገዛው እንደሆነ አድርጎ ነው የሚያስበው፡፡ ወደፊት ከሐዲሱ ላይ ምሳሌዎችን እያየን ስንሄድ ነገሩ የበለጠ ግልጽ ይሆንላችኋል፡፡ ስለዚህ ዝም ብላችሁ ማንበባችሁን ቀጥሉ፡፡ ማንኛውም ሙስሊም ወንድ ሴቷን ከማግባቱ በፊት አስቀድሞ የሚከፍለው ክፍያ (dower) አለ፡፡ በእነርሱ ቋንቋ ማህር (*mahr*) ይሉታል፡፡ ክፍያው በሀገራችን ኢትዮጵያ እንዳለው የጥሎሽ ዓይነት ክፍያ ይመስላል ግን አይደለም፡፡ ለወሲብ ተግባር የሚውለውን እያንዳንዱን የሴቷን የሰውነት ክፍሏን (sex organs) ወንዱ በገንዘቡ የገዛው እንደሆነ ተደርጎ ነው በእስልምናው የሚታሰበው፡፡ ይህን እኔ ፈጥሬ ያወራሁት ነገር ሳይሆን በሸሪዓው ሕግ "m5.4 (ref: 8, p.526)" እና በሐዲሱ ላይ በትክክል የተጻፈውን ነገር ነው መልሼ እያስተጋባሁ ያለሁት፡፡

"In Islam, sex means the enjoyment of a female body. The notion that sex could be an exceedingly joyful experience for both male and female is sadly lacking in the Islamic concept of it. A woman does not actively take part or act in sexual copulation. She is merely a passive receiver of male action, simply an instrument for providing carnal pleasure to the man. The idea that sex is a supreme physical satisfaction for both male and female is absent in Islam. Sex is viewed only from a man's angle and it is actually considered as a service or a commodity. In all cases

of marriage and sex she is treated merely as a sexual object, much like the provider of a service for which she must be paid some compensation. In Islamic parlance, this compensation for sexual service is known as *mahr* or dower. All Muslim men must agree to pay an amount of money before marrying a woman.This payment can be immediate or it can be deferred to a future date. Now you know what a *mahr* is. No Islamic marriage is valid without the agreement for a dower. In reality, however, this dower is nothing but the payment for the possession of a female body for sexual gratification by the male. To check the veracity of such a direct and outrageous statement, please open any *Sha'ria* book, such as reference 8. Here is an excerpt from this authentic *Sha'ria* (the divine law of Allah) book. Ownership of a woman's body to do as he likes including beating. m5.4 (ref: 8, p.526)

Let us also look into a book of Islamic jurisprudence that was used (during the British Raj in India) as a textbook for *Hanafi* laws at Inns of Law (London). It is the book, (reference 11) which even the *Sha'ria* lawyers consult regularly in the interpretation of Islamic laws. In page 44 of this book, it is written:

*Full dower is the payment for the delivery of woman's person, Booza, meaning (Genitalia arvum Mulieris.)The wife entitled to her whole dower upon the consummation of the marriage or the death of the husband.*-If a person specify a dower of ten or more Dirms, and should afterwards consummate his marriage, or be removed by death, his wife, in either case, has a claim to the whole of the dower specified, because, by consummation, the delivery of the return for the dower, namely the Booza, or woman's person, is established, and therein is confirmed the right to the consideration, namely, the dower; and, on the other hand, by the decease of the husband the marriage is rendered complete by its completion, and consequently is so with respect to all its effects.

The meaning of Genitalia arvum Mulieris is woman's vagina. The above few sentences clearly meant that a woman sells her vagina in return for the *mahr*. It is a commercial transaction. Make no mistake about it! Period. This is the real meaning of sex in Islam; that is, a man buys a woman's sex organ for enjoyment through the payment of *mahr*, which is the Islamic dower. It is rather interesting to note that, in the legal procedure to obtain Sexual gratification by a man, a woman (a wife or a slave-girl or a captive woman) is merely a servant whose job is only to satisfy her husband sexually. In Islam, we can only find the 'golden' treatment of women, you contend. Perish the thought. Here is what is written in the same Islamic law book as the actual legal status of a female sex partner in Islam.

*Woman is servant and the husband is the person served (ibid, p.47)*

Case of marriage on a condition of service from the husband፡ ...it is not lawful that a woman should be in a situation to exact the service of her husband who is a freeman, as this would amount to a reversal of their appointed stations, *for one of the requisites of marriage is, that the woman be as a servant, and the man as the person served.*

ከላይ ያየነውን የሸሪዓ ሕግ ሐዲሱም ሲያረጋግጠው እናገኘዋለን፡፡ ወንዱ ከማግባቱ በፊት ለሴቷ በስጦታ መልክ የሚከፍለው ቅድመ ክፍያ ከእርሷ ጋር ወደፊት ለሚፈጽመው ወሲብ ታሳቢ ተደርጎ ነው፡፡ ይህንንም ተከታዩ የአቡ ዳውድ ሐዲስ ያረጋግጥልናል፡፡ በመሐመድ ትምህርት መሠረት ሴት ልጅ ከጠባቂዋ ፈቃድ ወይም ስምምነት ውጪ የምትፈጽመው ጋብቻ ባዶ ወይም ዋጋ የሌለው፣ የማያገለግል ነው፡፡ ሳታገባውም አብራው ብትኖርና ወሲብ ብትፈጽም ግን ወሲብ መፈጸሚያ ሆና ለሰጠችው ግልጋሎት ክፍያዋን ታገኛለች፡፡ "Narrated Aisha: The Apostle of Allah said: 'The marriage of a woman who marries without the consent of her guardians is void. (He said these words) three times. If there is cohabitation, she gets her dower for the intercourse her husband has had. If there is a dispute, the sultan (man in authority) is the guardian of one who has none.'" (Sunaan Abu Dawud: Book 11, Number 2078)

7.7.ፈቃደኛ ባትሆንም እንኳን ባልየው ሚስቱን አስገድዶ ወሲብ ሊፈጽምባት ይችላል /One can enjoy a wife by force/፡- በሸሪዓው ሕግ መሠረት እርጉዝ ወይም ወርሀዊ ልማድ ላይ ሳትሆን ቀርታ ሚስት ለባሏ ወሲብ ማድረግን ብትከለክለው ባልየው አስገደዶ ወሲብ ሊፈጽምባት ይችላል፡፡ HEDAYA (ref.11, p.141) writes፡ "...It is otherwise where a woman, residing in the house of her husband, refuses to admit him to the conjugal embrace, as she is entitled to maintenance, notwithstanding her opposition, because being then in his power, he may, if he please, enjoys her by force."

7.8.ካረገዘች ሴት ጋር ወሲብ መፈጸም /Sex with pregnant women/፡- "It is not lawful for a man who believes in Allah and the last day to water what another has sown with his water" (meaning intercourse with women who are pregnant) (Sunaan Abu Dawud: Book 11, Number 2153) በእስልምናውም ካረገዘች ሴት ጋር ወሲብ መፈጸም ክልክል ነው፡፡ ነገር ግን ባጋጣሚ ድንገት ካረገዘች ሴት ጋር ወሲብ ከተፈጸመ የሚመጣው ቅጣት ነው ነገሩን አሳዛኝና ዘግናኝ የሚያደርገው፡፡ አንድ ወንድ

እርሱን ከማግባቷ በፊት አርግዛ ከነበረች ሴት ጋር ወሲብ ቢፈጽም እስልምናው ለዚህ ምን ዓይነት መፍትሄ የሚሰጥ ይመስላችኋል? መሐመድ በዘመናቸው ከሠሯቸው ሕጎች ውስጥ በአቡ ዳውድ ሐዲስ 11:2126 ላይ ተጽፎ የምናገኘው እጅግ የሚረብሽ አንድ ሕግ አለ፡፡ አንድ ወንድ ሚስት እንዳገባ አርግዛ ቢያገኛትና ልጁ እርሱን ከማግባቷ በፊት የተጸነሰ ነው ብሎ ካሰበ ሰውየው መሐመድ እንዳዘዘው ሦስት ነገሮችን ማድረግ አለበት፡፡ እርሷን ስትወልድ ጠብቆ 100 ግርፋት ይገርፋታል፤ ልጁን ደግሞ በባርነት ይገዛዋል፡፡ እንደ እንጀራ አባት ሆኖ ያሳድገዋል አይደለም ያልኩት ባሪያው አድርጎ ይገዛዋል፡፡ ወንዱ ለወሲብ ተግባር የሚውለውን እያንዳንዱን የሴቷን የሰውነት ክፍል (sex organs) ቀድሞ በከፈለው ገንዘብ የገዛው እስከሆነ ድረስ እርሷ ሚስቱ እንደሆነች ትቆያለች፡፡ ይህ መሐመድ የሰጡት መመሪያና ሕግ ነው፡፡ ቃል በቃል የተናገሩት "ብልቷን {ማለትም ግብረ ሥጋ ግንኙነት የምትፈጽምበትን ሰውነቷን} ለአንተ ሕጋዊ ያደረከበትን ባል ለሚስቱ የሚሰጠውን የውርስ ክፍያዋን ታገኛለች፡፡ ልጁም ባሪያህ ይሆናል፡፡ እርሷንም ስትወልድ ደብድባት" በማለት ነው፡፡ Narrated Basrah: "A man from the Ansar called Basrah said: I married a virgin woman in her veil. When I entered upon her, I found her pregnant. (I mentioned this to the Prophet). The Prophet said: She will get the dower, for you made her vagina lawful for you. The child will be your slave. When she has begotten (a child), flog her" (according to the version of al-Hasan). (Sunaan Abu Dawud: Book 11, Number 2126)

በዚህ ሐዲስ ውስጥ ግልጽ ባለ አነጋገር መሐመድ ሲናገሩ «ብልቷን ለአንተ ሕጋዊ ያደረከበትን ክፍያዋን ታገኛለች» ነው ያሉት፡፡ "She will get the dower, for you made her vagina lawful for you" ይህም እስካሁን ስንነጋገርበት የነበረውን ነገር በሙሉ ሊያጠቃልለው ይችላል፡፡ ከዚህ ሌላ ማስረጃ ምን ያስፈልጋል?

## 7.9.በውርሃዊ ልማድ ወቅት ወሲብ መፈጸም /sex with menstruating women/፡-

ይህም እንደላይኛው ነው፡፡ በውርሃዊ ልማድ ወቅት ወሲብ መፈጸም ክልክል ነው፡፡ ነገር ግን ባጋጣሚ ድንገት በዚህ ወቅት ወሲብ ከተፈጸመ የሚሰጠው መፍትሄ ነገሩን አሳዛኝ ያደርገዋል፡፡ በአቡ ዳውድ ሐዲስ ላይ እንደተመዘገበው ወንዱ በአጋጣሚ ወርሃዊ ልማድ እየታያት እያለ ከሴቷ ጋር ወሲብ ቢፈጽም ለዚህ መፍትሄ ተደርጎ የተወሰደው ነገር አንድ ዲናር ሰደቃ መስጠት አለበት፡፡ (ሰደቃ ማለት በክርስትናው ዝከር/ምጽዋት የሚባለው ነው) ወሲቡ የተፈጸመው ደግሞ ደሙ ከቆመ በኋላ ከሆነ ግማሽ ዲናር ይከፍላል፡፡ "Narrated Abdullah ibn Abbas: If a man has sexual intercourse (with menstruating woman) during her bleeding, he should give one dinar as sadaqah, and if he does so when bleeding has stopped, he should give half a

dinar as sadaqah." *(Sunaan Abu Dawud: Book 11, Number 2164)*

"Narrated Abdullah ibn Abbas: The Prophet Said፡ about a person who had intercourse with his wife while she was menstruating: He must give one dinar or half a dinar in alms." *(Sunaan Abu Dawud: Book 1, Number 0264)*

«ሚስቴ ወርሃዊ ልማድ ላይ ባለችበት ወቅት ከእርሷ ጋር ለማድረግ የሚፈቀድልኝ ምንድነው?» በማለት አንዱ ተከታያቸው መሐመድን ይጠይቃቸዋል፡፡ መሐመድም ከወገቧ በላይ ለእርሱ የተፈቀደችለት መሆኑን ነው የተናገሩት፡፡ "Abdullah asked the Apostle of Allah: What is lawful for me to do with my wife when she is menstruating? He replied: What is above the waist-wrapper is lawful for you." (Sunaan Abu Dawud: Book 1, Number 0212)

መሐመድ ከ32ቱም ሚስቶቻቸው ውስጥ በበለጠ ሁኔታ በጣም ይወዷት የነበረችውና በ9 ዓመቷ ወሲብ የፈጸሙባት ቢቢ አይሻ በወርሃዊ ልማዷ ወቅት መሐመድ ምን ያደርጓት እንደነበር በግልጽ የተናገረችው ነገር አለ፡፡ በወርሃዊ ልማዷ ወቅት መሐመድ መኝታቸውን የለዩ ቢሆንም ሌሊት በእንቅልፍ ላይ ሳለች መጥተው ጭኖቿን እንድትከፍት ነገሯት፣ እንዳሏትም አደረገች፡፡ ከዚያም ደረታቸውንና ጉንጫቸውን በጭኖቿ መካከል አድርገው እንደተኙ ነው አይሻ የተናገረችው፡፡ "Narrated Aisha, One night he entered (upon me) while I was menstruating. He went to the place of his prayer, that is, to the place of prayer reserved (for this purpose) in his house. He did not return until I felt asleep heavily, and he felt pain from cold. And he said: Come near me. I said: I am menstruating. He said: Uncover your thighs. I, therefore, uncovered both of my thighs. Then he put his cheek and chest on my thighs and I lent upon he until he became warm and slept." (Sunaan Abu Dawud: Book 1, Number 0270)

7.10.በጾም ወቅት መሳሳምና መጥባት /Kissing and sucking during fasting/፡-

መሐመድ በጾም ወቅት ጾመኛ ሆነው ሳለ የአይሻን ከንፈር ይስሙ ምላሷንም ይጠቡ እንደነበር ራሷ አይሻ የተናገረችውን ሐዲሱ መዝግቦት ይገኛል፡፡ "Narrated Aisha, Ummul Mu'minin: The Prophet used to kiss her and suck her tongue when he was fasting." *(Sunaan Abu Dawud: Book 13, Number 2380).* መሐመድ ይህን ያደረጉት በ53 ዓመታቸው የ9 ዓመቷ አይሻ ላይ መሆኑን ማስታወስ ያስፈልጋል፡፡ (በዚሁ ዕድሜዋ ወሲብ የፈጸመባት መሆኑን በገጽ——ላይ በዝርዝር ይመልከቱ፡፡)

መሐመድ የወንዶች ልጆችንም ከንፈር ይስሙ እንደ ነበር ነው የተጻፈው፡፡ ነገር ግን ይሄ ከወሲብ ጋር በተገናኘ ሳይሆን ሌላ ምክንያት ስላለው ነው፡፡ መሐመድ የሳሙትን ከንፈር የሲዖል እሳት እንደማይነካው ስለሚታመን ነው፡፡ የቤዱይን ዐረብ ሰዎች ወደ

መሐመድ ዘንድ መጥተው «እናንተ ወንዶች ልጆችን ትስማላችሁ እኛ አንስምም» ብለው መናገራቸውን አይሻ ተናግራለች፡፡ Narrated 'Aisha: A bedouin came to the Prophet and said, "You (people) kiss the boys! We don't kiss them." The Prophet said, "I cannot put mercy in your heart after Allah has taken it away from it." Sahih Bukhari 8:73:27. Narrated by Hisham Ibn Kasim: I saw the prophet sucking on the tongue or the lips of Al-Hassan son of Ali, may the prayers of Allah be upon him. For no tongue or lips that the prophet sucked on will be tormented (by hell fire). (Musnad Ahmad - Hadith No. 16245, Volume Title: "The Sayings of the Syrians," Chapter Title: "Hadith of Mu'awiya Ibn Abu Sufyan,") For it was narrated by Fatimah Bint Asad, the mother of Ali who related that when she gave birth to her son, it was the prophet who named him Ali and the prophet spat in Ali's mouth then allowed him to suck on his tongue till he fell asleep. (Al-Amin Al-Ma'moun-Biography of Muhammad, Chapter: "The first people to believe in the prophet.")
ይህ የመሐመድ ሱና ዛሬም በአንዳንድ ሙስሊም ምሁራኖቻቸው ዘንድ ተግባራዊ ይደረጋል፡፡ ወንዶችም ይሁኑ ሴቶች ሕጻናትን በዕድሜ ትልቅ የሆኑት ሙስሊሞች በጾማቸው ወቅት ከንፈራቸውን ይስመጧቸዋል፡፡ ይህንን ግን ማድረግ የሚችሉት ዕድሜያቸው ከ50 ዓመት በላይ የሆናቸው ሙላህ /Mullah/ ተብለው የሚጠሩት እስልምናውን የሚያስተምሩት ሙስሊም ምሁራን ብቻ ናቸው፡፡



7.11.በወሲብ ጊዜ የዘር ፈሳሽን ወደ ውጭ እንዲፈስ ማድረግ /Coitus interruption (or spilling ones seed)/፡- ወሲብ ከፈጸሙ በኋላ የወንዱን የዘር ፈሳሽ ወደ ውጭ ማፍሰስን እነርሱ በዓረብኛው አል-አዝል እግሊዝኛው ደግሞ coitus interruptus, ejaculate እያሉ ይጠሩታል፡፡ የመሐመድ ተከታዮቹ በጦርነት ከማረኳቸውና በባርነት ከያዟቸው ሴቶች ጋር ዝሙት ሲፈጽሙ ሴቶቹ ካረገዙባቸው ለሽያጭ ስለማይውሉ አርግዘውባቸው የባርያ ንግዳቸው እንዳይስተጓጎል ሲሉ የዘር ፈሳሻቸውን ወደ ውጭ በማፍሰስ (ejaculate በማድረግ) ነበር ዝሙት ሲፈጽሙባቸው የነበረው፡፡ በመሐመድ ጊዜ ተከታዮቻቸው ድርጊቱን ይፈጽሙት እንደነበር ጃቢር የተባለው ተከታያቸው በግልጽ ተናግሯል፡፡ "Narrated Jabir: We used to practice coitus interruptus during the lifetime of Allah's Apostle." Sahih Bukhari 7:62:135. እንዲያውም ጃቢር ጨምሮ የተናገረው መሐመድ በሕይወት በነበሩበት ዘመን ቁርአኑም እየወረደ እያለ ድርጊቱን ይፈጽሙት እንደነበር ነው፡፡ "Narrated Jabir: We used to practice coitus interruptus during the lifetime of Allah's Apostle while the Quran was being revealed." Sahih Bukhari 7:62:136

መሐመድም ይህንን ድርጊት እንደፈጸሙ መጥተው ሲነግሯቸው ከዚህ እኩይ ድርጊታቸው እንዲታቀቡ ሊከለክሏቸው አልፈለጉም፡፡ «ባታደርጉት ይሻል ነበር ግን ደግሞ አላህ እስከ ዕለተ ምፅዓት ቀን ድረስ እንዳይፈጠር የሚያደርገው ነፍስ የለም» ነው ያሏቸው፡፡ "Narrated Abu Said Al-Khudri: that while he was sitting with Allah's Apostle he said, 'O Allah's Apostle! We get female captives as our share of booty, and we are interested in their prices, what is your opinion about coitus interruptus?' The Prophet said, 'Do you really do that? It is better for you not to do it. No soul that which Allah has destined to exist, but will surely come into existence.'" Sahih Bukhari 3:34:432

"Narrated Abu Said Al-Khudri: We got female captives in the war booty and we used to do coitus interruptus with them. So we asked Allah's Apostle about it and he said, "Do you really do that?" repeating the question thrice, "There is no soul that is destined to exist but will come into existence, till the Day of Resurrection." Sahih Bukhari 7:62:137

«አላህ እንዳይፈጠር የሚያደርገው ነፍስ የለም» በሚለው ንግግራቸው መሐመድ ተከታዮቻቸውን ድርጊቱን እንዲፈጽሙት የሚያበረታታ አስተያየት ነበር የሰጧቸው፡፡ እንዲያውም ድርጊቱን እንዲፈጽመው ለአንዱ ተከታያቸው የተናገሩበት ሁኔታም አለ፡፡ አንዱ ተከታያቸው ወደ እርሳቸው መጥቶ «የምታገለግለን ባሪያ ሴት ልጃገረድ አለችኝ፤

ውኃ ትቀዳልናለች፡፡ ከእርሷ ጋር ዝሙት ፈጽሜያለሁ ነገር ግን እንድታረግዝ አልፈልግም›› ሲላቸው መሐመድ የሰጡት መልስ ‹‹ከፈለግህ ዘርህን ወደ ውጭ ማፍሰስ (coitus interruptus መፈጸም) ትችላለህ ነገር ግን በእርሷ ላይ የታወጀው ነገር መምጣቱ አይቀርም›› የሚል ነበር፡፡ "Jabir reported that a man came to Allah's Messenger and said: 'I have a slave-girl who is our servant and she carries water for us and I have intercourse with her, but I do not want her to conceive.' He said: 'Practise azl, if you so like, but what is decreed for her will come to her.'" Sahih Muslim 8:3383

በሌላም ቦታ እንዲሁ አንዱ ተከታያቸው ድርጊቱን መፈጸሙን ለመሐመድ ይነግራቸዋል፡፡ አይሁዳዊያንም ‹‹ይህን መፈጸም ማለት በተወሰነ ደረጃ ሕጻናትን በሕይወት መቅበር ነው›› እያሉ መናገራቸውን መሐመድ ሲሰማ ‹‹አይሁዳውያኑ ውሸት ተናግረዋል፣ ያንን ነፍስ አላህ እንዲፈጥረው ከፈለገ አንተ ልትከለክል አትችልም›› ነው ያሉት፡፡ "Narrated Abu Sa'id al-Khudri: A man said: 'Apostle of Allah, I have a slave-girl and I withdraw the penis from her (while having intercourse), and I dislike that she becomes pregnant. I intend (by intercourse) what the men intend by it. The Jews say that withdrawing the penis (azl) is burying the living girls on a small scale.' He (the Prophet) said: 'The Jews told a lie. If Allah intends to create it, you cannot turn it away.'" Abu Dawud 11:2166

በሐዲሱ ውስጥ እነዚህን እስካሁን ያየናቸውን ዓይነት መሰል ታሪኮችን ለቁጥር በሚያዳግት ሁኔታ በብዛት ሰፍረው እናገኛለን፡፡ "Abu Sirma said to Abu Sa'id al Khadri: We went out with Allah's Messenger on the expedition to the Bi'l- Mustaliq and took captives; and we desired them, for we were suffering from the absence of our wives, (but at the same time) we also desired ransom for them. So we decided to have sexual intercourse with them but by observing 'azl (Withdrawing the male sexual organ before emission of semen to avoid-conception). But we said: We are doing an act whereas Allah's Messenger is amongst us; why not ask him? So we asked Allah's Messenger, and he said: It does not matter if you do not do it, for every soul that is to be born up to the Day of Resurrection will be born." (Sahih Muslim Book 008, Number 3371)

"Abu Sa'id al-Khudri was asked if he had heard it himself, to which he said: Yes. (I heard) Allah's Apostle as saying: There is no harm if you do not practise it, for it (the birth of the child) is something ordained by Allah." Sahih Muslim 8:3374, See

also: Sahih Muslim 8:3375

ከመሐመድ ሞት ሞት በኋላ እስልምናውን ሲመሩት የነበሩት ከሊፋዎች ግን ለድርጊቱ በይፋ ፈቃድ ሲሰጡ ነበር፡፡ “Al-Hajjaj ibn Amr ibn Ghaziya that he was sitting with Zayd ibn Thabit when Ibn Fahd came to him. He was from the Yemen. He said, "Abu Said! I have slave-girls. None of the wives in my keep are more pleasing to me than them, and not all of them please me so much that I want a child by them, shall I then practise coitus interruptus?" Zayd ibn Thabit said, "Give an opinion, Hajjaj!" "I said, 'May Allah forgives you! We sit with you in order to learn from you!' He said, 'Give an opinion! 'I said, 'She is your field, if you wish, water it, and if you wish, leave it thirsty. I heard that from ayd.' Zayd said, 'He has spoken the truth.'" (Malik's Muwatta: Book 29, Number 29.32.99)

በመጨረሻም አንድ በጣም አሳዛኝ ነገር ልንገራችሁ፡፡ በ7.9 ንዑስ ርዕስ ላይ ስንነጋገር ሕጻኗ የመሐመድ ሚስት ቢቢ አይሻ በወርሃዊ ልማዷ ወቅት መሐመድ ሌሊት በእንቅልፍ ላይ ሳለች መጥተው ጭኖቿን እንድትከፍት ከነገሯት በኋላ ደረታቸውንና ጉንጫቸውን በጭኖቿ መካከል አድርገው ይኙ እንደነበር አይሻ ማናገሯን ይህም በአቡ ዳውድ ሐዲስ (1፡270) ላይ በግልጽ የተጻፈ መሆኑን አይተን ነበር፡፡ ከዚህ ድርጊታቸው ጋር በተያያዘ የተከሰተ ይሁን ወይም መሐመድ የዘር ፈሳሻቸውን ወደ ውጭ እንዲፈስ አድርገው ወሲብ ፈጽመው ይሁን ብቻ ምክንያቱ ግልጽ ባይሆንም የመሐመድ ልብስ በዘር ፈሳሽ ተጨማልቆ መገኘቱን በሐዲሱ ላይ በግልጽ ተጽፎ እናገኛለን፡፡ ለዚያውም ምንም እንኳን አይሻ ልብሳቸውን እያጠበችላቸው ወደ መስጊድ ቢሄዱም ከልብሳቸው ላይ የዘር ፈሳሹ ነጠብጣብና ክብ ምልክቱ አልጠፋም ነበር፡፡ “Narrated Sulaiman bin Yasar: I asked 'Aisha about the clothes soiled with semen. She replied, 'I used to wash it off the clothes of Allah's Apostle and he would go for the prayer while water spots were still visible.'” (Sahih Bukhari Volume 1, Book 4, Number 231)

በሌላኛው ሐዲስ ላይ ደግሞ አይሻ ስትናገር በወርሃዊ ልማዷ ወቅት መሐመድና እርሷ ሌሊት አንድ ልብስ ለብሰው ይተኙ ነበር፡፡ ከእርሷም ሆነ ከእርሳቸው ሰውነት የሚወጣው ፈሳሽ ልብሳቸውን ከነካው የልብሳቸውን የነካውን ክፍል ብቻ ቆንጥረው ያጥቡትና በእሱም ይሰግዱበት እንደነበር አሁንም አይሻ ተናግራለች፡፡ “Narrated Aisha, Ummul Mu'minin: I and the Apostle of Allah used to lie in one cloth at night while I was menstruating. If anything from me smeared him, he washed the same place (that was smeared), and did not wash beyond it. If anything from him smeared his clothe, he washed the same place and did not wash beyond that, and prayed with it.” (Sunaan Abu Dawud: Book 11, Number 2161)

መሐመድ የዘር ፈሳሻቸውን ወደ ውጭ እንዲፈስ አድርገው ወሲብ ፈጽመዋል ብዬ ለመደምደም ባልችልም ግን አንዳንድ ነገሮችን አያይዤ ማንሳት እችላለሁ፡፡ አይሻ ከነጭራሹ አርግዛ አታውቅም፡፡ ይህ ለምን ሆነ? በ7.3 ንዑስ ርዕስ ላይ እንዳየነው መሐመድ ተከታያቸው ዕድሜዋ ገፋ ያለች ሴት እንዳገባ ሲነግራቸው "አብራህ የምትጫወትና አንተም የምታጫውታት፣ የምታሻሻትና የምታሻሽህ ወጣትና ድንግል ልጃገረድ ለምን አላገባህም?" በማለት ነው የጠየቁት፡፡ "the Prophet said, 'Why didn't you marry a young girl so that you may play with her and she with you?'", (Bukhari 7:62:16), "Why have you not married a virgin to fondle with each other?" (Bukhari 3:38:504) ስለዚህ ራሳቸው መሐመድም በ53 ዓመታቸው ከ9 ዓመት ሕጻን ልጅ አይሻ ጋር የተጋቡትና ወሲብ የፈጸሙት ለዚሁ ለመተሻሸቱ አመቺነት ሲባል መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ አይሻ ያደገችው መሐመድ ጋር ቢሆንም ልጅ ግን አልወለደችም ነበር፡፡ ታዲያ አይሻ እንዴት ጭራሽ ሳታረግዝ ቀረች? እኔ ዝም ብዬ ስገምተው ግን አይሻ ከወለደች የልጅነት ሰውነቷ ስለሚጠወልግባቸው ያ ከሆነ ደግሞ መሐመድ ለመተሻሸት ተመራጭ ስለማይሆንላቸው እርሷ እንዳታረግዝ ለማድረግ ሲሉ የዘር ፈሳሻቸውን ወደ ውጭ ያፈሱ ነበር የሚለው ሀሳብ ሚዛን የሚደፋ ሆኖ ታይቶኛል፡፡

7.12.ከሴቷ ሰውነት የሚወጣው የዘር ፈሳሽ መልኩ ቢጫ ነው! /Women's semen is yellow?/፡- መሐመድ እንዳስተማረው ትምህርት ከሆነ ከሴቷ ሰውነት የሚወጣው የዘር ፈሳሽ መልኩ ቢጫ ነው፡፡ "Anas b.Malik reported that Umm Sulaim narrated it that she asked the Apostle of Allah about a woman who sees in a dream what a man sees (sexual dream). The Messenger of Allah said: In case a woman sees that, she must take a bath. Umm Sulaim said: I was bashful on account of that and said: Does it happen? Upon this the Apostle of Allah said: Yes (it does happen), otherwise how can (a child) resemble her? Man's discharge (i.e. sperm) is thick and white and the discharge of woman is thin and yellow; so the resemblance comes from the one whose genes prevail or dominate." *(Sahih Muslim Book 3, Number 0608)* See also *(Sahih Muslim Book 3, Number 0610)*

7.13.ባልተገባ ቦታ ወሲብ መፈጸም /Backside or anal sex/፡- የመሐመድ ተከታዮች እርሳቸው በሕይወት በነበሩበት ዘመን ተከታዮቻቸው በሴቶች ላይ ባልተገባ ቦታ የወሲብ ጥቃት ይፈጽሙ እንደነበር ብዙ የቁርአንና የሐዲስ ማስረጃዎች አሉ፡፡ ከዚህ በፊት በቁርአኑ ሱረቱ አል-በቀራህ 2:223 ላይ "ሴቶቻችሁ ለእናንተ እርሻ

ናቸው፤*እርሻችሁንም በፈለጋችሁት ሁኔታ ድረሱ፤ ለነፍሶቻችሁም መልካም ሥራን* አስቀድሙ” የሚለውን የቁርአን ጥቅስ አይተነዋል፡፡ (“Your wives are as a tilth unto you; so approach your tilth when or how ye will; but do some good act for your souls beforehand; and fear Allah.”) ይህንን የመሐመድ አነጋገር በሌላ ርዕስ እመለስበታለሁ ብዬ ነበር፡፡ ይኸው አሁን ተመልሼበታልሁ፡፡ ስለዚህ በዝርዝር እንየው፡- ቁርአኑ ላይ የተጻፈውን ሙሉውን ቃል በተመሳሳይ ሁኔታ በአቡ ዳውድ ሐዲስ ላይም ተመዝግቦ እናገኘዋለን፡፡ Narrated Mu'awiyah ibn Haydah: I said: Apostle of Allah, how should we approach our wives and how should we leave them? He replied: Approach your tilth when or how you will, give her (your wife) food when you take food, clothe when you clothe yourself. Abu Dawud 11:2138

*“በፈለጋችሁት ሁኔታ ድረሱ”* የሚለዋ አገላለጽ ለምንና እንዴት ልትነገር እንደቻለች ማየቱ የግድ አስፈላጊ ነው፡፡ ጥቅሱን ከመጀመሪያው ከቁ.222 ጀምሮ ብናየው ነገሩን ይበልጥ ግልጽ ያደርግልናል፡፡ “ከወር አበባም ይጠይቁሃል፤ እርሱ የተበከለ ነው፤ ሴቶችንም በወር አበባ ጊዜ ራቋቸው፤ ንጹሕ እስከሚሆኑም ድረስ አትቅረቡዋቸው፤ ንጹሕ በሆኑም ጊዜ አላህ ካዘዛችሁ ስፍራ ተገናኙዋቸው፤ አላህ ተመላሾችን ይወዳ፤ ተጥራሪዎችንም ይወዳል በላቸው፡፡ ሴቶቻችሁ ለእናንተ እርሻ ናቸው፤ እርሻችሁንም በፈለጋችሁት ሁኔታ ድረሱ፤ ለነፍሶቻችሁም አስቀድሙ፤ አላህንም ፍሩ” ይላል ቁርአኑ፡፡ አል-በቀራህ 2፡222-223፡፡

*“...አላህ ካዘዛችሁ ስፍራ ተገናኙዋቸው፤*...እርሻችሁንም በፈለጋችሁት ሁኔታ ድረሱ” የሚሉትን አባባሎች ልብ ብላችሁ ተመልከቱልኝ! እነዚህ የቁርአን አነጋገሮች በውስጣቸው ብዙ መልእክት ስለያዙ ጉዳዩን ወደ ሌላ ርዕስ መውሰዳቸው አልቀረም፡፡ ግልጽ ባለ አነጋገር መሐመድ ወንዶችን *“...አላህ ካዘዛችሁ ስፍራ ተገናኙዋቸው”* ያሏቸው በወቅቱ የነበሩት ተከታዮቻቸው በሴቶች ላይ ባልተገባ ቦታ Anal Sex (ማለትም በዐይነ ምድር መፀዳጃ በኩል) ግንኙነት ይፈጽሙባቸው ስለነበር ነው፡፡ This hadith has been reported on the authority of Jabir and there is an addition of these words: "If he likes he may have intercourse being on the back or in front of her, but it should be through one opening (vagina)." (*Sahih Muslim* Book 008, Number 3365), “Narrated AbuHurayrah: The Prophet said: He who has intercourse with his wife through her anus is accursed.” (Sunaan Abu Dawud: Book 11, Number 2157), “Narrated Jabir: Jews used to say: 'If one has sexual intercourse with his wife from the back, then she will deliver a squint-eyed child.' So this Verse was revealed:- 'Your wives are a tilth unto you; so go to your tilth when or how you will.'” (2.223) (Sahih Bukhar: Volume 6, Book 60, Number 51), “Jabir reported that the Jews used

to say that when one comes to one's wife through the Vagina, but being on her back, and she becomes pregnant, the child has a squint. So the verse came down: 'Your wives are your ti'lth; go then unto your tilth, as you may desire.'" (Sahih Muslim Book 008, Number 3364).

ስለዚህ በወቅቱ የነበሩት ተከታዮቻቸው በሴቶች ላይ ይህን አጸያፊ ግርጊት ባልተገባ ቦታ ላይ በዐይነ ምድር መፀዳጃ በኩል /Anal Sex/ መፈጸማቸውን ተከትሎ መሐመድ "*አላህ ካዘዛችሁ ስፍራ ተገናኙዋቸው...*" ካሉ በኋላ ነው "ሴቶቻችሁ ለእናንተ እርሻ ናቸው፤ እርሻችሁንም በፈለጋችሁት ሁኔታ ድረሱ" ያሏቸው፡፡ ይህም ማለት መሐመድ በወቅቱ የነበረውን ወሲባዊ ግንኙነት የከለከሉት በዐይነ ምድር መፀዳጃ በኩል መሆኑን ብቻ ነው፡፡ ሌለውን እንስሳዊ ድርጊታቸውን ግን ሊከለክሏቸው አልፈለጉም፤ ይልቁንም «እርሻችሁንም በፈለጋችሁት ሁኔታ...» ነው ያሏቸው፡፡ እርሳቸውን ያሳሰባቸው ወሲባዊ ግንኙነቱ በዐይነ ምድር መፀዳጃ በኩል መሆኑ ብቻ ነው እንጂ ከጀርባ በኩል ወሲብ መፈጸማቸውን አልተቃወሟቸውም፡፡ ወንዶቹ ወሲቡ የሚፈጽሙት በሴቷ ብልት (Vagina) በኩል ከሆነ ግን እንደፈለጉ ሆነው ልክ እንደ እንስሳ ሲፈልጉ ከፊት ሲፈልጉ ከኋላ ሆነው ወሲብ መፈጸም ይችላሉ፡፡ እስቲ ድርጊቱን ወንዶቹ እስከ አራት ሚስት ማግባታቸውንና በጦር ምርኮ ከተያዙ ገደብ አልባ ሴቶች ጋር ወሲብ መፈጸማቸውን ተከትሎ የሚከሰተውን ነገር አስቡት! መሐመድ የፈቀዱላቸውና ተከታዮቻቸውም ይፈጽሙት የነበረው ይህ ልቅ የሆነ የወሲብ ተግባር ዛሬ በዚህ ኃጢአት በነገሰበት አስከፊ ዓለም ፖርኖግራፊ /pornography/ የሚል ስያሜ ተሰጥቶት ተግባራዊ እየተደረገ ነው፡፡ የሚገርማችሁ አሁንም ያሉት ሙስሊም ምሁራኖች በዚህ ሀሳብ ይስማማሉ፡፡ «መሐመድ የከለከለው በዐይነ ምድር መፀዳጃ በኩል የሚፈጸመውን ወሲብ ነው እንጂ አላህ ካዘዘን ስፍራ እርሻችዎቻችንን (ሴቶቻችንን) በፈለግነው ሁኔታ ማረስ እንችላለን» የሚል አቋም ነው ያላቸው፡፡

(Fatwa: Islamic Ruling on Anal Sex-IslamOnline, February 22, 2010), (Ibn Abi Shaybah, 3/529, classified authentic by At-Tirmidhi, hadith, 1165), (Musnad Ahmed Vol. 1, Pg. 86) & (al-Tirmidhi, 1/243; Saheeh al-Jaami', 5918)

በሌላም በኩል ማንኛውንም ዓይነት የሙስሊሞች ጾታዊ ጥያቄዎችን እያስተናገደ ኢስላማዊ ምላሾችን የሚሰጠው ZAWAJ.COM የተሰኘው ድረ ገጽ "Straight Talk about sex" በሚል ርዕስ ያወጣውን ጽሑፍ ማየት እንችላለን፡፡ መጋቢት 15 ቀን 2001 ዓ.ም ድረ ገጹ ይዞት የወጣው ጽሑፍ አንድ ሙስሊም በጉዳዩ ዙሪያ ለጠየቀው ጥያቄ የተሰጠውን ማብራሪያ እንይ፡- «እስልምና በመጸዳጃ በኩል ስለሚፈጸም ወሲብ ምን ይላል? እኔስ ከሚስቴ ጋር ብፈጽመው?›› "What does Islam say about anal sex? What

if I had anal sex with my wife?" ይላል ጥያቄው፡፡

በድረ ገጹ ላይ አማካሪና መፍትሄ ሰጪዎች በመሆን ለሚነሱ ማንኛውም ዓይነት ጥያቄዎች ኢስላማዊ ምላሾችን የሚሰጡት የእስልምና ሃይማኖት ሕግጋትን የማስረዳት ሕጋዊ መብት ያላቸው በኮሚቴ የተዋቀሩ መምህራኖቻቸው ናቸው፡፡ እነርሱ በጉዳዩ ላይ ቁርአኑንና ሐዲሱን መሠረት አድርገው በጋራ የሰጡት መልስ እስካሁን ካየነው ሀሳብ ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡ መልሳቸው በአጭሩ ቁርአን 2፡223 ላይ «...*እርሻችሁንም በፈለጋችሁት ሁኔታ ድረሱ*» የሚለውን በመጥቀስ ወሲብ መፈጸም የሚቻለው በሴቷ ብልት ብቻ መሆኑን የሚገልጽ ሲሆን አላህም ሆነ መሐመድ «ከሴቶች ጋር በመጸዳጃ በኩል ወሲብ አትፈጽሙ» ብለው ማዘዛቸውንም እንዲሁ የሐዲስ ምንጮችን እየጠቀሱ ሰፊ ማብራሪያ ሰጥተውበታል፡፡ እነርሱ የሰጡትን መልስ ቀጥሎ ይመልከቱ፡-

Almighty Allah says in the Qur'an: "Your wives are a tilth for you, so go to your tilth, when or how you will..." (Al-Baqarah: 223.) In the foregoing verse the word *Harth* (tilth) indicates that only vaginal sex is permissible in Islam, because it is from this place children are produced. Allah says "so go to your tilth when or how you will" which means that all variations of intercourse are permitted, so long as it is in the place of tilth, i.e., the vagina, not the anus. So it is permissible for a man to have intercourse with his wife from behind or from in front or lying on their sides so long as it is in the place of tilth and not the anus. All Muslim jurists agree that anal sex is Haram, based on the Hadith of the Prophet, peace and blessings be upon him: "Do not have anal sex with women." (Reported by Ahmad, At-Tirmidhi, An-Nasaa'i, and Ibn Majah.) Khuzaymah Ibn Thaabit, also reports that the Messenger of Allah, said: "Allah is not too shy to tell you the truth: Do not have sex with your wives in the anus." (Reported by Ahmad, 5/213.) It was narrated from Abu Hurayrah that the Messenger of Allah said: "The one who has intercourse with his wife in her back passage has disavowed himself of that which was revealed to Muhammad." Narrated by Abu Dawood (3904)

Allah Almighty knows best.

ZAWAJ.COM

Islam Online Fatwa Committee

**7.14.ጎልማሳ ወንዶችን ጡት ማጥባት /Adult Suckling/፡-** በእስልምና እምነት ሙስሊም በሆኑት በሴቷና በወንዱ መካከል ፆታዊ ግንኙነት እንዳይኖር ከተፈለገ በማንኛውንም ዓይነት ሁኔታ በአንድ ላይ አብረው መቀመጥ የለባቸውም፡፡ ወንዱ ራሱን መቆጣጠር ስለማይችል ሴቷ በሂጃብ እንድትሸፈን ቢደረግም ይህም በቂ

ስላልሆነ አብራው እንዳትቀመጥ ነው የተወሰነው፡፡ ሴቷ ከወንዱ ጋር አብራው በአንድ ክፍል ከተቀመጠች ግን እስልምናው ያስቀመጠው አንድ መፍትሄ አለ፡፡ ሴቷ ለወንዱ ጡቷን ታጠባዋለች፡፡ ጡቷን ካጠባቸው ለእርሱ “ሃራም” (ፈጽሞ የተከለከለ) ስለምትሆንበት ከዛ በኋላ ከእርሷ ጋር ወሲብ መፈጸም አይችልም፡፡



በሳሂህ ሙስሊም ሐዲስ ላይ የተመዘገበን አንድ ታሪክ በምሳሌነት ማየት እንችላለን፡፡ ሱሃይል የተባለው ሰው ሴት ልጁ ለመሐመድ አንድ የነገረቻቸው ነገር አለ፡፡ አቡ ሁዳይፋ በሚባል ሰው በባርነት ተይዞ የነበረው ሳሊም በኋላ ነጻ ቢለቀቅም አብሯቸው ይኖር ነበር፡፡ ሴቷም ልጅ ሁኔውን ለመሐመድ ስትነግራቸው “ሳሊም አሁን እንደ ወንዶች የጉልምስና ዕድሜ ደረጃ ላይ ደርሷል፡፡ እነርሱ የሚረዱትን ነገር ሁሉ እርሱም ይረዳል፤ ወደቤታችንም በነፃነት ነው የሚገባው፡፡ ምንም ቢሆን ግን በአቡ ሁዳይፋ ልብ ያለውን ሃሳብና የሚያስጨንቀውን እኔ እገነዘባለሁ” ትላቸዋለች፡፡ ይህን ጊዜ መሐመድ የሰጧት ምላሽ ‹‹ለወጣቱ ጎልማሳ ጡትሽን አጥቢው›› የሚል ነበር፡፡ ‹‹ጡትሽን አጥቢው ከዛ በኋላ አንቺ ለእርሱ ሃራም (ክልክል) ትሆኚበታለሽ፣ አቡ ሁዳይፋም በልቡ የሚያስጨንቀው ነገር ይጠፋለታል›› ብለው ነው መሐመድ የመፍትሄውን ሃሳብ የሰጧት፡፡ እርሷም እንደታዘዘችው አደረገች፡፡ ቃል በቃል እንዲህ ነው ያለችው፡- “አጠባሁት፣ ያን ጊዜም አቡ ሁዳይፋን በልቡ የሚያስጨንቀው ነገር ጠፋለት፡፡” A'isha reported that Salim, the freed slave of Abu Hudhaifa, lived with him and his family in their house. She (i. e. the daughter of Suhail came to Allah's Apostle and said: Salim has attained (puberty) as men attain, and he understands

what they understand, and he enters our house freely, I, however, perceive that something (rankles) in the heart of Abu Hudhaifa, whereupon Allah's Apostle said to her: Suckle him and you would become unlawful for him, and (the rankling) which Abu Hudhaifa feels in his heart will disappear. She returned and said: So I suckled him, and what (was there) in the heart of Abu Hudhaifa disappeared. Sahih Muslim 8:3425

መሐመድ ሴቷ ጡቷን በማጥባት ሃራም (ፈጽሞ ክልክል) ልታደርግ የምትችልባቸውን ሌሎች ሕጎች ሠርተው ነበር፡፡ እንዲያውም አይሻ እንደተናገረችው ከሆነ መጀመሪያ መሐመድ ከሰማይ የመጣልኝ ሕግ ነው ብለው የደነገጓቸው አስር የጡት ማጥባት ሕጎች እንደነበሩ ነው፡፡ ከእነዚህም ውስጥ አምስቱ ተሻሩ፤ መሐመድ ሲሞቱ ደግሞ የቀሩትም ተሸረው አሁን ቁርአን ላይ ብቻ ያለው እንደቀረ ነው አይሻ የተናገረችው፡፡

“the wife of the Prophet said, ‘Amongst what was sent down of the Qur'an was 'ten known sucklings make haram'-then it was abrogated by 'five known sucklings'. When the Messenger of Allah died, it was what is now recited of the Qur'an.’” (Malik’s Muwatta: Book 30, Number 30.3.17)

በተጨማሪም የሸሪዓውን ሕግ ጨምሮ ቀጥሎ ባሉት ሐዲሶች ላይ ስለ ጡት ማጥባት በሰፊው ተጠቅሶ እናገኘዋለን፡፡ (Sahih Muslim: Book 008, Number 3426), Sha’ria book (ref. 8, pp.575-576), (Shahih Muslim: Book 008, Number 3391), (*Sunaan Abu Dawud: Book 34, Number 4210*), (Malik’s Muwatta: Book 30, Number 30.3.15), (Malik’s Muwatta: Book 30, Number 30.1.7), (Malik’s Muwatta :Book 30, Number 30.1.8), (*Malik’s Muwatta: Book 30, Number 30.1.11*)

7.15.ሚስት ባሏ ሌላ ሴት ጋር ሄዶ እንዳይወሰልትና እንዳይማግጥ ከፈለገች የእርሱን ውሽማ (ቅምጥ) ጡቷን ማጥባት አለባት፡- ይህን አነጋገር እስልምናው በሐዲሱ ላይ እንደ ሕግ ያስቀመጠው ነገር ነው እንጂ እኔ ከራሴ የተናገርኩት አይደለም፡፡ መጀመሪያ ሐዲሱ ላይ የተጻፈውን ነገር እንመልከት፡- በአል-ሙዋታ ሐዲስ ላይ አንድ ታሪክ ተጽፎ እናገኛለን፡፡ አንድ ሰው ኡማር ፍርድ ወደሚሰጥበት ቦታ ይመጣና ከሚስቱ በተጨማሪ ባሪያ ሴት እንዳለችውና ከእርሷም ጋር ዝሙት ይፈጽም እንደነበር ነገረው፡፡ ነገር ግን ሚስቱ ይህንን ስታውቅ ሄዳ ለባሪያይቱ ጡቷን ታጠባታለች፡፡ ባል ተብየው በሌላ ጊዜ ወደ ባሪያይቱ ልጅ ሲሄድ ሚስቱ ታየውና ‹‹ጡቴን አጥብቻታለሁና ላንተ ክልክል ሆናለች ተጠንቀቅ›› ትለዋለች፡፡ ፍርድ ሰጪው ኡማርም ይህን ሲሰማ ሚስቱን እንዲደበድባትና ወደ ባሪያይቱም እንዲሄድ ነው

ሰውየውን ያዘዘው፡፡ የሐዲሱን ማስረጃ ቀጥሎ ይመልከቱት፡፡ "A man came to Umar ibn al-Khattab and said, 'I have a slave-girl and I used to have intercourse with her. My wife went to her and suckled her. When I went to the girl, my wife told me to watch out, because she had suckled her!' Umar told him to beat his wife and to go to his slave-girl because kinship by suckling was only by the suckling of the young.'" Al-Muwatta 30 2.13, See also: Al-Muwatta 30 30.213b

በዚህ ሕግ መሠረት ሚስት ባሏ ሌላ ሴት ጋር ሄዶ እንዳይወሰልትና እንዳይማግጥ ከፈለገች የእርሱን ውሽማ (ቅምጥ) ጡቷን ማጥባት እንዳለባት ነው በሐዲሱ ላይ የተደነገገው፡፡ እንግዲህ ወንዱ አስር ሴት ጋር ቢማግጥ ሚስቱ ባሏን የግሏ ለማድረግና ውሽሞቹም ጋር እንዳይሄድ አስሩም ውሽሞቹ ጋር እየዞረች ማጥባት አለባት ማለት ነው፡፡ ይህንንም አድርጋ ራሱ ባሏ ሌላ ሴት ጋር እንዳይሄድ ማድረግ እንዳልቻለች ነው ከላይ ባየነው ሐዲስ ላይ ማረጋገጥ የቻልነው፡፡ ሴቷ ለባሪያይቱ ጡቷን ስላጠባቻትና ባሏም ከባሪያዋ ጋር ወሲብ መፈጸም ስላልቻለ ነውኮ ሴቷ እንደገና እንድትደበደብ የተፈረደባት! ወንዱ ሙስሊም ከገደብ አልባ ብዙ የጦር ምርኮኞች ጋር ወሲብ መፈጸም እንደሚችል መሐመድ የፈቀዱለት መሆኑን እናስታውስና እስቲ ከዚህ ሕግ ጋር እናገናኘው፡፡ ሚስት ተብዬዋ ስንቱን ቅምጥ አጥብታ ትዘልቀዋለች? ብታጠባቸውም እንኳ ባሏ እነርሱ ጋር እንዳይደርስ ስላደረገች ዱላ ነው የሚጠብቃት፡፡ ባል ተብየውም እርሷን ደብድቦ ውሽሞቹና ቅምጥ ባሪያዎቹ ጋር መሄድ ይችላል፡፡

**7.16.ከጦር ምርኮኞችና በባርነት ከተያዙ ሴቶች ጋር ወሲብ መፈጸም /Sex with war captives & slave girls/**፡- በዚህ ርዕስ ዙሪያ ሌሎች ቦታዎች ላይ በሰፊው ስለተጠቀሰ አሁን ምንም የማነሳው አዲስ ሀሳብ የለም፡፡ ነገር ግን አቢይ ርዕሳችን «ወሲብና ወሲባዊነት በእስልምና» /Sex and sexuality in Islam/ የሚል በጥቂቱም ቢሆን ሳይጠቀስ መታለፍ የለበትም፡፡ እስልምናው ሙስሊም ወንዶችን በቁጥር ደረጃ ገደብ ከሌላቸውና በጦርነት ከማረኳቸው ምርኮኛ ሴቶች ጋር በግዳጅ ወሲብ እንዲፈጽሙ ይፈቅድላቸዋል፡፡ ሕጉን መሐመድም ሆነ በወቅቱ የነበሩት ተከታዮቹ ተግባራዊ አድርገውታል፡፡ ይህም በቁርአኑና በሐዲሱ ለቁጥር በሚያሰለች ሁኔታ በሰፊው ተጠቅሶ ይገኛል፡፡ ሰፊና ዝርዝር መረጃዎችን በገጽ---፣----ላይ ይመልከቱ፡፡ ለአሁኑ ግን ለመሐመድና ተከታዮቻቸው ከሊፋዎች ገደብ ከሌላቸውና በጦርነት ከማረኳቸው ምርኮኛ ሴቶች ጋር ወሲብ እንዲፈጽሙ ቁርአኑ ትእዛዝ የሰጡበትን ክፍል ብቻ ጠቆም ማድረግ እፈልጋለሁ፡፡ እስቲ እነዚህን የቁርአን ጥቅሶች ልብ ብላችሁ ተመልከቱ፡-

«እነሱ ብልቶቻቸውን ጠባቂዎች የሆኑት አገኙ፡፡ በሚስቶቻቸው ወይም እጆቻቸው

በያዟቸው ባሪያዎች ላይ ሲቀር እነሱ በእነዚህ የማይወቀሱ ናቸው» (ሱረቱ አል-ሙእሚኑን 23:6 ተመሳሳይ አገላለጽ በሱረቱ አል-መዓሪጅ 70፡29 ላይ)፣ «እጆቻችሁ በምርኮ የያዟቸውን ሴቶች ተገናኙዋቸው» (ሱረቱ አል-ኒሳእ 4:24)፣ «አንተ ነቢዩ ሆይ! እነዚያን እጅህ የጨበጠቻቸውን ምርኮኞች ለአንተ ፈቅደንልሃል» (ሱረቱ አል-አሕዛብ 33፡50)፣ «ቀኝ እጆቻችሁ የራስ ያደረጉትን ንብረት ያዙ» "…and that which your right hand possesses" (አል-ኒሳእ 4፡3)

እነዚህን የቁርአን መመሪያዎች መሠረት በማድረግ መሐመድና ተከታዮቻቸው ሴቶችን በጦርነት ከማረኳቸው በኋላ አስገድደው ይደፍሯቸው ነበር፡፡ ለምሳሌ ራሳቸው መሐመድ የፈጸሙትንና በቡኻሪ ሐዲስ ላይ የተጠቀሰውን ማየት እንችላለ፡፡ እነ መሐመድ ሁሉንም የካይባር ወንዶች ከገደሉ በኋላ ሴት የጦር ምርኮዎቹን በባርነት ይዘውለዝሙት እንዲጠቀሙባቸው መሐመድ ፈቅደውላቸዋል፡፡ መሐመድም ሳፊያ ቢንት ሁያይ የተባለችውን ምርኮኛ ሴት ቆንጆ ስለነበረች ለራሳቸው ወስደዋታል፡፡ ነቢያቸው አባቷን፣ ባሏን፣ ወንድሞቿን ከገደሉ በኋላ ነው እርሷን የዚያኑ ዕለት በግዳጅ ዝሙት ሲፈጽሙባት ያደሩት፡፡ Sahih Bukhari 1:8:367. (ገጽ—ላይ በዝርዝር ይመልከቱ፡፡)

የመሐመድ ተከታዮችም ቢሆኑ እርሳቸው እንደፈቀዱላቸው ከጦር ምርኮዎቻቸውና በባርነት ከያዟቸው ሴቶች ጋር ዝሙት ሲፈጽሙ ለባርነት ንግድ እንዲያመቻቸው የዘር ፈሳሻቸውን ወደ ውጭ በማፍሰስ (coitus interruptus) በመፈጸም እንዳያረግዙ ያደርጉ ነበር፤ ይህንንም ቀደም ብለን «የዘር ፈሳሽን ወደ ውጭ እንዲፈስ ማድረግ» በሚለው ርዕስ ስር በደንብ አይተናል፡፡ ቀጥሎ ባሉት የሐዲስ ጥቅሶች ላይ በወቅቱ የነበሩት የመሐመድ ተከታዮች በጦርነት ከማረኳቸው ሴቶች ጋር በግዳጅ ወሲብ ይፈጽሙ እንደነበር በግልጽ ተጽፏል፡፡ Sahih Bukhari 5:59:459, Sahih Muslim 8:3432, Sahih Muslim 8:3433, Sahih Muslim 8:3433, Sahih Muslim 8:3371, Abu Dawud 2:2150, Abu Dawud 11:2153, See also: Sahih Bukhari 8:77:600, Sahih Bukhari 3:34:432, Abu Dawud 31:4006.

እንዲሁም በወቅቱ የነበሩት የመሐመድ ተከታዮች በባርነት ከያዟቸው ሴቶች ጋር ዝሙት ይፈጽሙ እንደነበር በገጽ--ላይ ‹‹መሐመድ ከባሪያዎችና ከጦር ምርኮኛ ሴቶች ጋር ግብረ ስጋ ግንኙነት መፈጸምን ፈቅዷል›› የሚለውን ንዑስ ርዕስ ይመልከቱ፡፡

በጦር ከተማረከች ሴት ጋር ወሲብ መፈጸም የማይቻለው በወርሃዊ ልማዷ ወቅት ብቻ ነው፡፡ ስትነፃ ጠብቆ መፈጸም ግን ይቻላል፡፡ "It is not lawful for a man who believes in Allah and the Last Day to have intercourse with a captive woman till she is free

from a menstrual course.” (Sunaan Abu Dawud: Book 11, Number 2153)

7.16.1.አንድ ሙስሊም በባርነት በያዛቸው ሁለት እኅትማማቶቾች ላይ በየተራ ወሲብ መፈጸም ይችላል፡- በጦር ተማርከው የተያዙ ሁለት እኅትማማቶቾችን አንድ ሙስሊም ከፈለገ በተራ ወሲብ ሊፈጽምባቸው ወይም ላይፈጽምባቸው ይላል፡፡ በጦርነት የተማረኩት እናትና ልጅ ከሆኑ ግን አንድ ወንድ ሁለቱም ላይ በተራ ወሲብ መፈጸም አይችልም፡፡ አንዷን መርጦ ግን ማድረግ ይችላል፡፡ የሐዲሶቹን ማስረጃ ይመልከቱ፡፡ “a man asked Uthman ibn Affan whether one could have intercourse with two sisters who one owned. Uthman said, "One ayat makes them halal, and one ayat makes them haram” (Malik’s Muwatta:Book 28, Number 28.14.34), “Umar ibn al-Khattab was asked about a woman and her daughter who were in the possession of the right hand, and whether one could have intercourse with one of them after the other Umar said, "I dislike both being permitted together." He then forbade that.” (*Malik’s Muwatta: Book 28, Number 28.14.33*)

5.ዘካ ያልተከፈለበት ገንዘብ በዕለተ ምፅዓት ቀን ገንዘቡ ራሱ ወደ መርዛማ እባብነት ይለወጥና ባለቤቱን ይውጠዋል:- የዘካ ክፍያ ያልከፈሉበት ገንዘብ ካለዎት በዕለተ ምፅዓት ቀን ገንዘቡ ራሱ ወደ ግዙፍ ራሰ-መላጣና ወንድ መርዛማ እባብነት ይለወጥና "እኔኮ ዘካ ያላወጡብኝ ገንዘብዎ ነኝ" እያለ ሊውጥዎ ያባርርዎታል፡፡ እርስዎም ሊያመልጡ ቢሞክሩም አይሳካልዎትም፣ እባቡ ተከታትሎ ይይዝዎትና ይውጥዎታል፡፡ እንዲሁም መሐመድ በወቅቱ የግመል ባለሀብቶች ለነበሩት ሰዎችም ይህንኑ መልእክት አስተላልፈዋል፡፡ የግመሎች ባለቤት የሆነ ሰው ዘካ ካላወጣ በዕለተ ምፅዓት ቀን ግመሎቹ ወደ እርሱ ይመጡና በኮቴዎቻቸው ፊቱን ይመቱታል፡፡ Allah's Apostle said, "On the Day of Resurrection the Kanz (Treasure or wealth of which, Zakat has not been paid) of anyone of you will appear in the shape of a huge bald-headed poisonous male snake and its owner will run away from it, but it will follow him and say, 'I am your Kanz.'" The Prophet added, "By Allah, that snake will keep on following him until he stretches out his hand and let the snake swallow it." Allah's Apostle added, "If the owner of camels does not pay their Zakat, then, on the Day of Resurrection those camels will come to him and will strike his face with their hooves." Sahih Bukhari 9:86:89

ዘካ ወይም ሰደቃ እነ መሐመድ በነበሩበት ወቅትና አሁን በዚህ ዘመን ባሉት ሙስሊሞች ዘንድ ያለው ትርጉምና ዓላማ እንዲሁም የአሠራሩ ሁኔታው የተለያየ ነው፡፡ በዚህ ዘመን ያሉት ሙስሊሞች ዘካን ወይም ሰደቃን የሚያወጡት ለነፍሳችን ዋጋ ያሰጠናል በማለት ሲሆን በመሐመድ ዘመን ግን ዓላማው ይህ አልነበረም፡፡ ምክንያቱም ዘካው ይከፈል የነበረው ለራሳቸው ለመሐመድ ነበር፡፡ እንኳን የዘካውን ብር ይቅርና ተከታዮቻቸው በጦርነት ዘርፈው ያመጡትን ንብረት አንድ አምስተኛውን ድርሻ "ለአላህና ለመልእክተኛው የተገባ ነው" (ቁርአን 8፡1) በማለት ይቀበሏቸው እንደነበር ቁርአኑ በግልጽ አስቀምጦታል፡፡

6.በአላህ መንገድ ተዋግቶ በጂሃድ ለተሳተፈ ጦረኛ አላህ ለፈረሱ ያወጣውን ወጪ በዕለተ ምፅዓት ይከፍለዋል:- አንድ ጂሃዲስት (ጦረኛ) በአላህ መንገድ ለመዋጋት በጂሃድ ለመሳተፍ ቃል ገብቶ ለዚህም እንዲያመቸው ፈረሱን በደንብ ተንከባክቦ ዝግጁ ከሆነ አላህ ለፈረሱ ያወጣውን ሙሉ ወጪ የቀለቡንም ዋጋ ጭምር በዕለተ ምፅዓት ይከፍለዋል፡፡ The Prophet said, "If somebody keeps a horse in Allah's Cause motivated by his faith in Allah and his belief in His Promise, then he will be rewarded on the Day of Resurrection for what the horse has eaten or drunk and for its dung and urine." Sahih Bukhari 4:52:105

7.መላኢኮች (መላእክት) አርብ አርብ መስጊድ ያልመጣውን ሰው በቀሪ ይመዘግባሉ፡- ሁልጊዜ አርብ አርብ በሶላት ሰዓት መላኢኮች ወደ መስጊድ እንደ አመጣጣቸው ቅደም ተከተል መሠረት የሚመጡትን ሰዎች ስም ለመመዝገብ በየመስጊዶቹ በር ላይ መመዝገቢያ ብራና ወረቀት ይዘው ይጠብቃሉ፡፡ አሰጋጁ ኢማም ቦታውን ሲይዝ ያን ጊዜ ወረቀታቸውን ይጠቀልላሉ፡፡ ወረቀቱም ከተጠቀለለ በኋላ የሚመጣ ሰው እርሱ ቀሪ ነው፡፡ The Prophet said, "On every Friday the angels take heir stand at every gate of the mosques to write the names of the people chronologically (i.e. according to the time of their arrival for the Friday prayer and when the Imam sits (on the pulpit) they fold up their scrolls and get ready to listen to the sermon." Sahih Bukhari 4:54:433

8.ነቢያቸው መሐመድ እስራኤላውያን ወደ አይጥነት ተለውጠዋል አሉ፡- ሁለት ሰዎች በመሐመድ ቁጥጥር ስር ስለነበሩና በኋላም ስለተሰወሩ እስራኤላውያን እየተነጋገሩ ነው፡፡ አንደኛው ስለ ሁኔታው ለኋደኛው በዝርዝር ይነግረዋል፡፡ በቁጥጥር ስር የዋሉ የእስራኤላውያን ሰዎች በአንድ ወቅት ከእነ መሐመድ እይታ መሰወራቸውን፣ ማንም ሰው ስለ እነርሱ ማወቅ አለመቻሉን፣ ይህን ጊዜም መሐመድ ሰዎቹ “ወደ አይጥነት ተለውጠው ነው የተሰወሩብን” በማለት ለተከታዮቻቸው መናገራቸውንና ቀጥሎም እነርሱንም ሊያገኙ የሚችሉበትን ዘዴ መሐመድ ሲናገሩ “የግመልን ወተት በአይጥ ፊት ብታስቀምጥ አትጠጣውም፤ የበግን ወተት ግን በአይጥ ፊት ብታስቀምጥ  አይጧ ትጠጣዋለች” ብለው መናገራቸውን ለኋደኛው ይተርክለታል፡፡ ኋደኛውም ይህንን ማመን ያቅተውና “ይህንን በእውነት ከነቢዩ ነው የሰማኸው?” ብሎ ሲጠይቀው “እመነኝ አዎ” ይለዋል፡፡ ካብ የተባለው ይኸው ማመን ያቃተው ሰው ነገሩን ደጋግሞ ይጠይቀዋል፡፡ ይህን ጊዜ በጥያቄው መደጋገም የተሰላቸው ተጠያቂ “እኔ ታዲያ የብሉይን መጽሐፍ አላነበብኩ ከነቢዩ የሰማሁትን ነገርኩህ እንጂ” በማለት ነው የመጨረሻውን ምላሽ የሰጠው፡፡ The Prophet said, "A group of Israelites were lost. Nobody knows what they did. But I do not see them except that they were cursed and changed into rats, for if you put the milk of a she-camel in front of a rat, it will not drink it, but if the milk of a sheep is put in front of it, it will drink it." I told this to Ka'b who asked me, "Did you hear it from the Prophet?" I said, "Yes." Ka'b asked me the same question several times.; I said to Ka'b. "Do I read the Torah? (I.e. I tell you this from the Prophet.)" Sahih Bukhari 4:54:524

9.ኃጢአት ያደረጉ ሰዎች ወደ ዝንጀሮነትና አሳማነት ይለወጣሉ፡- ከመሐመድ ተከታዮች ውስጥ ሕጋዊ ያልሆነ ግብረ ሥጋ ግንኙነት የሚያደርጉ፣ ከሐር የተሠራ ልብስ የሚለብሱ፣ የአልኮል መጠጥ የሚጠጡና ሙዚቃ መጫወትን ሕጋዊ እንደሆኑ አድርገው የሚጠቀሙ ሰዎች ይኖራሉ፡፡ የእነዚህ ሰዎች የመጨረሻ ዕጣ ፈንታቸው ወደ ዝንጀሮነትና አሳማነት መለወጥ ነው፡፡ ከፊላቸውን አላህ ያጠፋቸዋል፡፡ የተቀሩትን ደግሞ ወደ ዝንጀሮነትና አሳማነት ይለውጣቸዋል፡፡ ይህም ቅጣታቸው እስከ ዕለተ ምፅዓት ድረስ የፀና ነው፡፡ The Prophet said: "From among my followers there will be some people who will consider ille-

gal sexual intercourse, the wearing of silk, the drinking of alcoholic drinks and the use of musical instruments, as lawful. And there will be some people who will stay near the side of a mountain and in the evening their shepherd will come to them with their sheep and ask them for something, but they will say to him, 'Return to us tomorrow.' Allah will destroy them during the night and will let the mountain fall on them, and He will transform the rest of them into monkeys and pigs and they will remain so till the Day of Resurrection." Sahih Bukhari 7:69:494

10.የአይሁድና የክርስቲያኖች ተቃራኒ ለመሆን ከፈለጋችሁ ጸጉራችሁን ቀለም ተቀቡ፡ መሐመድ ተከታዮቻቸውን ሁሉንም ነገር ከአይሁድና ከክርስቲያኖች ተቃራኒ በሆነ መልኩ እንዲያደርጉ አዘዋቸዋል፡፡ ትእዛዝ ነውና ሙስሊሞችም አይሁድና ክርስቲያኖች የሚያደርጉትን ነገር በተቃራኒው ማድረግ ግዴታቸው ነው፡፡ እነ መሐመድ በወቅቱ ጸጉራቸውን እንኳን ቀለም ይቀቡ የነበረው አይሁድና ክርስቲያኖች ጸጉራቸውን ቀለም ስለማይቀቡ ነው፡፡ Dye your hair because Jews and Christians don't፡ “The Prophet said, ‘Jews and Christians do not dye their hair so you should do the opposite of what they do.’” Sahih Bukhari 7:72:786 እንግዲህ በወቅቱ እነ መሐመድ ስንቱን ነገር ከአይሁድና ከክርስቲያኖች ተቃራኒ በሆነ መልኩ አድርገው እንደዘለቁት እነርሱ ብቻ ናቸው የሚያውቁት፡፡







በሁለተኛ ደረጃ ሙስሊሞች ፂማቸውን የሚያሳድጉት አንድም የበላይነታቸውን ለማጉላትና በሌሎች ላይ የበላይነትን ለመውሰድ መሆኑን ሐዲሱ ይናገራል፡፡ ከእስልምና እምነት ውጭ ባሉ ሰዎች ላይ የበላይነትን ለመግለጽ ሲባል ፂምን ማሳደግ ተገቢ መሆኑን መሐመድ ለተከታዮቹ አስተምሯል፡፡ The Messenger of Allah said: Act against the polytheists,

trim closely the moustache and grow beard. Sahih Muslim 2:500, See also: Sahih Muslim 2:501

11.የአየር ንብረትን በተመለከተ የመሐመድ አስተምህሮ፡- ሳሂህ ሙስሊም ሐዲስ 1፡4፡1290 እና ቡኻሪ ሐዲስ 4፡54፡482 ላይ እንደተጠቀሰው የገሀነም እሳት በአላህ ፊት ታዛዥ ሆና ትቀርብና እንዲህ ትላለች፡- “ጌታዬ ሆይ! በውስጤ ያሉ ነፍሳት እርስ በእርሳቸው ተባላሉ” በማለት ለአላህ ቅሬታዋን ስታቀርብ የተሰጣት መልስ ሁለት ጊዜ እንድትተነፍስ ነው፡፡ አንድ ጊዜ በክረምት ሌላ ጊዜ ደግሞ በበጋ ተንፍሽ ተባለች፡፡ እንደተባለችውም ተነፈሰች፡፡ ይህን ጠቅሰው መሐመድ የአየር ንብረት ትምህርታቸውን ቀጠሉና እንዲህ አሉ፡- “በዚህ ምክንያት ነው በበጋ ከፍተኛ ሙቀት በክረምት ደግሞ ከፍተኛ ብርድ ተከስቶ የምታገኙት”

"The Messenger of Allah said: The Fire made a complaint before the Lord saying: ‘O Lord, some parts of mine have consumed others.’ So it was allowed to take two exhalations, one exhalation in winter and the other exhalation in summer. That is why you find extreme heat (in summer) and extreme cold (in winter). *Sahih Muslim* vol.1 book 4 no.1290 p.302.

Allah's Apostle said, "The (Hell) Fire complained to its Lord saying, 'O my Lord! My different parts eat up each other.' So, He allowed it to take two breaths, one in the winter and the other in summer, and this is the reason for the severe heat and the bitter cold you find (in weather)." Sahih Bukhari 4:54:482

ይህንና ይህንን መሰል አስተሳሰቦችን በውስጡ አጭቆ የያዘውን መጽሐፋቸውንና ሃይማኖታቸውን ነው እንግዲህ እስልምና ሃይማኖታችን “ከሳይንስ ጋር ይስማማል” የሚሉን፡፡ በመሠረቱ «ሰው ማለት በዝግመተ ለውጥ (evolution) ከጦጣ የተገኘ ፍጡር ነው» ብሎ የሚያምነውን ሳይንስን እንደ ትክክለኛ ሃይማኖት ማረጋገጫ አድርጎ ማቅረቡ በራሱ ከሃይማኖት የወጣና የዘቀጠ አስተሳሰብ ነው፡፡

12.የግመል ሽንት መድኃኒት ነው፡- መሐመድን ተከትለው ወደ እስልናው የመጡ ሰዎች የመዲና ከተማ የአየር ንብረቱ ሳይስማማቸው ቀርቶ ቢታመሙ የግመልን ወተትና ሽንት ለመድኃኒትነት እንዲጠቀሙ ነው የመከሯቸው፡፡ Bukhari, Volume 4 Number 261. The climate of Medina did not suit some people, so the Prophet ordered them to follow his shepherd, i.e. his camels, and drink their milk and urine (as a medicine). So they followed the shepherd that is the camels and drank their milk and urine till their bodies became healthy. Sahih Bukhari 7:71:590

13.ዝንብን እንደ መድኃኒት መጠቀም፡- መጠጥ እየጠጡ እያለ ድንገት ዝንብ መጠጥዎ ውስጥ ብትገባ አውጥተው መጣል የለብዎትም፡፡ እንደ መሐመድ ትምህርት ከሆነ ዝንብ በአንድ ክንፏ በሽታን የሚያመጡ ተሕዋሲያንን ብትይዝም በሌላኛው ክንፏ ደግሞ መድኃኒቱንም ጭምር ስለያዘች አውጥቶ ከመጣል ይልቅ ዝንቧ እዛው መጠጡ ውስጥ እያለች መጠጣት ነው የለብዎ፡፡ The Prophet said "If a house fly falls in the drink of anyone of you, he

should dip it (in the drink), for one of its wings has a disease and the other has the cure for the disease." Sahih Bukhari 4:54:537

14.የሰይጣን መኝታ ቤት፡- የሰይጣን መኝታ ቤት የት ይመስላችኋል? ጨለማ ውስጥ?ሲኦል? አመድ ምናምን ወይ የሆነ ቆሻሻ ነገር የተደፋበት ወንዝ ውስጥ? ወይስ የት የሚተኛ ይመስላችኋል? እስቲ ገምቱ! ገምቱና በኋላ እኔ የመሐመድን መልስና አስተምህሮ እነግራችኋለሁ። እንደ መሐመድ ትምህርት ከሆነ የእኛ የአፍንጫችን ቀዳዳ የሰይጣን መኝታ ቤት ነው፡፡ ከእንቅልፋችሁ ስትነቁ አሉ መሐመድ «ከእንቅልፋችሁ ስትነቁ ውዱ አድርጉ (በሃይማኖታዊ ስርዓት ታጠቡ) የአፍንጫችሁን ቀዳዳዎች በውኃ እጠቡና 3 ጊዜ በውኃው ተናፈጡ ምክንያቱም በላይኛው የአፍንጫችሁ ውስጣዊ ክፍል ውስጥ ሰይጣን ሌሊቱን ሙሉ ተኝቶበት አድሯልና» ቡኻሪ 4፡54፡516፤ ሳሂህ ሙስሊም 2፡462.



"Narrated Abu Huraira: The Prophet said, 'If anyone of you rouses from sleep and performs the ablution [ritual washing], he should wash his nose by putting water in it and then blowing it out thrice, because Satan has stayed in the upper part of his nose all night."(1)

The translator's Footnote (1) says, "We should believe that Satan actually stays in the upper part of one's nose, though we cannot perceive how, for this is related to the unseen world of which we know nothing except what Allah tells us through His Apostle." *Bukhari* vol.4 book 54 (The Beginning of Creation) ch.10 no.516 p.328.

"Abu Huraira reported: The Apostle of Allah said. When any one of you awakes up from sleep and performs ablution, he must clean his nose three times, for the devil spends the night in the interior of his nose." Sahih Muslim 2:462

15.ሰይጣን በሚያፋሽጉ ሰዎች ላይ ይስቅባቸዋል፡- እንደ መሐመደ ትምህርት ከሆነ ማፋሸግ ከሰይጣን፣ ማስነጠስ ደግሞ ከአላህ ነው፡፡ ስለዚህ አላህ ማፋሸግን ሲጠላ ማስነጠስን ግን ይወዳል፡፡ እናም የሚያፋሽጉ ከሆነ ሰይጣን ስለሚስቅብዎ ማፋሸግዎን ለማቆም የተቻለዎትም ሁሉ ማድረግ አለብዎ፡፡ ሲያስነጥሱ ግን አላህ ስለሚደሰትብዎ በሚያስነጥሱ ሰዓት አላህን ማመስገን ይጠበቅብዎታል፡፡ The Prophet said, "Allah likes sneezing and dislikes yawning, so if someone sneezes and then praises Allah, But as regards yawning, it is

from satan, so one must try one's best to stop it, if one says 'Ha' when yawning, satan will laugh at him." Sahih Bukhari 8:73:242. Narrated Abu Huraira: The Prophet said, "Yawning is from Satan and if anyone of you yawns, he should check his yawning as much as possible, for if anyone of you (during the act of yawning) should say: 'Ha', Satan will laugh at him." Sahih Bukhari 4:54:509

16.ሰይጣን በሰው ጆሮ ውስጥ ሽንቱን ሸንቶ አደረ፡- መሐመድ ሌሊቱን ሙሉ ተኝቶ ስላደረ አንድ ሰው ይሰማሉ፡፡ ሰውየው ሌሊት ለሶላትና ለጸሎት እንዳልተነሳ ይልቁንም እስከ ጠዋት ድረስ ተኝቶ እንዳደረ ለመሐመድ ይነገራቸዋል፡፡ ያን ጊዜ መሐመድ የሰጡት አስተያየት *"ሰይጣን በጆሮው ውስጥ ሸንቶበት ነው"* የሚል ነው፡፡ "A person was mentioned before the Prophet and he was told that he had kept on sleeping till morning and had not got up for the prayer. The Prophet said, "Satan urinated in his ears." Sahih Bukhari 2:21:245

17.ሰይጣን የሙስሊሞችን ጸሎት ለማስታጎል ሲል ፈሱን ይፈሳባቸዋል፡- ሙስሊሞች ለመስገድና ጸሎት ለማድረግ ጥሪ ሲደረግላቸው ጥሪውን እንዳይሰሙና ተረጋግተውም በሰከነ አእምሮ ሆነው ዱአ እንዳያደርጉ ሰይጣን ፈሱን ይፈሳባቸዋል፡፡ የእርሱን የፈስ ሽታ ተቋቁመው ተረጋግተው ጸሎታቸውን ቢያደርጉም እንኳን የጸለዩትን ነገር እንዳያስታውሱ ይልቁንም እንዲረሱት ያደርጋቸዋል፡፡ Allah's Apostle said, "When the Adhan is pronounced Satan takes to his heels and passes wind with noise during his flight in order not to hear the Adhan. When the Adhan is completed he comes back and again takes to his heels when the Iqama is pronounced and after its completion he returns again till he whispers into the heart of the person (to divert his attention from his prayer) and makes him remember things which he does not recall to his mind before the prayer and that causes him to forget how much he has prayed." Sahih Bukhari 1:11:582

18.ማንኛውም ሕጻን ገና ሲወለድ ሰይጣን ይዋሐደዋል፡- እንደ መሐመድ አስተሳሰብ ከሆነ ማንኛውም ሕጻን ገና ሲወለድ ሰይጣን በሁለት ጣቶቹ ሁለቱንም ጎኖቹን ይዳስሳቸዋል፡፡ በዚህም ከሕጻኑ ጋር ውሕደትና ቁርኝት ይፈጥራል፡፡ ይህ ነገር ያልተፈጸመው በመሪየምና በልጇ በዒሳ ላይ ብቻ ነው፡፡ ሰይጣን ሁልጊዜ እንደሚያደርገው ሁሉ ዒሳንም ሲወለድ ሊዳስሰው ቢሞክርም ሳይችል ቀርቷል፡፡ በእርሱም ምትክ የእንግዴ ልጇን ነው የነካው፡፡ The Prophet said, "When any human being is born, Satan touches him at both sides of the body with his two fingers, except Jesus, the son of Mary, whom Satan tried to touch but failed, for he touched the placenta-cover instead." Sahih Bukhari 4:54:506. ይህ የመሐመድ አስተሳሰብ ሁለት ነገሮችን በጣም ግልጽ ያደርግልናል፡፡ የመጀመሪያው ከላይ እንዳየነው ማንኛውም ሕጻን ገና ሲወለድ ሰይጣን ጎኖቹን በመዳሰስ የሚቆራኘው መሆኑን የሚያስረዳ ሲሆን በጣም የሚገርመውና ሁለተኛው ነገር መሐመድ ራሳቸውን ከእንደዚህ

ዓይነቱ የሰይጣን ቁርኝትና ፈተና ነፃ ለማድረግ አለመፈለጋቸው ነው። እርሳቸውም የችግሩ ገፈት ቀማሽ ነበሩ ማለት ነው። ለነገሩኮ በሌላ ቦታ መሐመድ ባልና ሚስት የግብረ ሥጋ ግንኙነት እያደረጉ እያለ *"በአላህ ስም! ኦ አላህ ሆይ! ከሰይጣን ጠብቀን፤ የምትሰጠንንም ልጅ ሰይጣን እንዳይደርስበት አንተ ጠብቅልን"* በማለት ጸሎት ካደረጉ ሰይጣን በልጃቸው ላይ እንደማይደርስባቸው ለአማኞቻቸው ማረጋገጫ የምትሆነውን ጸሎት አስተምረው ነበር። በግብረ ሥጋ ግንኙነታቸው ወቅት ይህቺን ጸሎት ካልጸለዩ ግን በዚያች ቅፅበት የሚፀነሰውን ልጃቸውን ሰይጣን ይቆራኘውና አብሮት ያድጋል። Sahih Bukhari 4:54:493

የመሐመድ አስተምህሮ ይህ ብቻ አይደለም። ሲወለድ ሰይጣን የማይነካውና የማይቆራኘው የአዳም ዘር ስለሌለ ማንኛውም ሕጻን ሲወለድ የዚህ ችግር ተጠቂ ነው። ሕጻናትም ልክ ከእናታቸው ማኅፀን ሲወጡ የሚያለቅሱት ሰይጣኑ በሁለት ጣቶቹ ጎኖቻቸውን ስለዳሰሳቸው ነው። Abu Huraira said, "I heard Allah's Apostle saying, 'There is none born among the off-spring of Adam, but Satan touches it. A child therefore, cries loudly at the time of birth because of the touch of Satan, except Mary and her child." Then Abu Huraira recited: "And I seek refuge with You for her and for her offspring from the outcast Satan." (3.36) Sahih Bukhari Book 55 No. 641 አሁንም ቢሆን ከዚህ ችግር ፍጹም ነፃ ሆነው የተወለዱት እመቤታችንና ልጇ ብቻ ናቸው። እመቤታችን ስትወለድና እርሷም ልጇን ስትወልድ ከዚህ ችግር የተጠበቁ ለመሆኑ ቁርአኑም በግልጽ ምስክርነቱን አስቀምጧል።

19.ሰይጣን የሚመገባቸው ምግቦች:- መሐመድ ዐይነ ምድር እየተፀዳዱ እያለ አንድ ሰው በአጠገባቸው ሲያልፍ ስላዩቸው ነቢያቸው «መጥረጊያ የሚሆን ድንጋይ አምጣልኝ» ይሉታል። መሐመድ በዚህ ብቻ አላቆሙም። ሰውየውን ድንጋይ ብቻ ነው የምታመጣልኝ አጥንት ወይም ከእንስሳት የሚወጡትን (በጠጥ፣ እበት ወይም ፋንድያ) እንዳታመጣ ይሉታል። ምክንያቱም እንደ መሐመድ አስተሰሳሰብ እነዚህ ነገሮች የሰይጣን ምግቦች ናቸው። እንዲያውም ሰይጣኖች መሐመድን የሚበሉትን ፍርፋሪ ምግብ እንዲሰጧቸው ጠይቀዋቸው ነበር። መሐመድም በዚህ አዝነው አላህን ንጹሕ ምግብ እንዲሰጣቸው ለምነውላቸዋል። That once he was in the, company of the Prophet carrying a water pot for his ablution and for cleaning his private parts. While he was following him carrying it(i.e. the pot), the Prophet said, "Who is this?" He said, "I am Abu Huraira." The Prophet said, "Bring me stones in order to clean my private parts, and do not bring any bones or animal dung." Abu Huraira went on narrating: So I brought some stones, carrying them in the corner of my robe till I put them by his side and went away. When he finished, I walked with him and asked, "What about the bone and the animal dung?" He said, "They are of the food of Jinns. The delegate of Jinns of (the city of) Nasibin came to me--and how nice those Jinns were--and asked me for the remains of the human food. I invoked Allah for them that they would never pass by a bone or

animal dung but find food on them." Sahih Bukhari 5:58:200

20.ሰይጣን በሦስት የተለያዩ ምሽቶች በሰው አምሳል እየተገለጠ የሰዎችን ምግብ ሰርቋል፡- Allah's Apostle said, "Verily, he told you a lie and he will return." I waited for him attentively for the third time, and when he (came and) started stealing handfuls of the foodstuff, I caught hold of him and said, "I will surely take you to Allah's Apostle as it is the third time you promise not to return, yet you break your promise and come." He said, "Forgive me"... The Prophet said, "He really spoke the truth, although he is an absolute liar. Do you know whom you were talking to, these three nights, O Abu Huraira?" Abu Huraira said, "No." He said, "It was Satan." Sahih Bukhari 3:38:505t

21.ሰይጣን መሐመድን ከጸሎት ሊያቋርጣቸው መከረ፡- መሐመድ ዱዓ አድርገው ሲጨርሱ ስለራሳቸው ሲናገሩ "ሰይጣን በፊት ለፊቴ መጥቶ ትኩረቴን ወደ ሌላ አቅጣጫ ሊቀይርብኝ በፅኑ ሞከረ ነገር ግን አላህ እንዳሸንፈው ጥንካውን ሰጠኝ" በማለት ተናግረዋል፡፡ The Prophet offered a prayer, and (after finishing) he said, "Satan came in front of me trying persistently to divert my attention from the prayer, but Allah gave me the strength to over-power him." Sahih Bukhari 4:54:504

22.የእምነትን ሕግ በጣሱ ሰዎች ላይ በዕለተ ምፅዓት ቀን በጀርባቸው በኩል ባንዲራ ይታሰርባቸዋል፡፡ It is narrated on the authority of Abu Sa'id that the Messenger of Allah said: On the Day of Judgment there will be a flag fixed behind the buttocks of every person guilty of the breach of faith. Sahih Muslim 19:4309

23.ሰይጣን ማታ ማታ በእያንዳንዱ ሰው ጀርባ ላይ ሦስት የድግምት ቋጠሮዎችን አስሮ ያድራል፡- በእያንዳንዱ ሰው ጀርባ ላይ ማታ በተኛበት ሰይጣን ሦስት ቋጠሮዎችን ከጀርባው ይቋጥርበታል፡፡ በሁሉም ቋጠሮዎች ላይ "ሌሊቱ ረጅም ነው ስለዚህ በደንብ ተኛ" የሚል ቃልን ይተነፍስባቸዋል፡፡ ሰውየው ልክ እንደነቃ አላህን የሚያመሰግን እንደሆነ አንደኛው ቋጠሮ ይጠፋለታል፡፡ ውዱ ሲያድርግ ሁለኛው፡፡ ጸሎት ሲያደርግ ደግሞ የመጨረሻው ቋጠሮ ይጠፋለታል፡፡ ይህን ካደረገ ጠዋት ሲነቃ ደስተኛ ይሆናል አለበለዚያ ግን ቀኑ አሰልቺና ድብርታም ይሆንበታል፡፡ Allah's Apostle said, "During your sleep, Satan knots three knots at the back of the head of each of you, and he breathes the following words at each knot, 'The night is, long, so keep on sleeping,' If that person wakes up and celebrates the praises of Allah, then one knot is undone, and when he performs ablution the second knot is undone, and when he prays, all the knots are undone, and he gets up in the morning lively and gay, otherwise he gets up dull and gloomy. " Sahih Bukhari 4:54:491

24.ሙሴ ከሰይጣን (ከመልአከ ሞት) ጋር ቦክስ ገጠመ፡- ሙሴ (በእነርሱ ሙሳ) ከሰይጣን (ከመልአከ ሞት) ጋር ቦክስ ገጥሞ የሰይጣንን ፊት በቦክስ ነርቶት ፊቱ እንዲበልዝ አድርጎታል፡፡

Moses and Boxing Angels፡"Abu Huraira reported that the Angel of Death was sent to Moses (peace be upon him) to inform of his Lord's summons. When he came, he (Moses) boxed him and his eye was knocked out. He (the Angel of Death) came back to the Lord and said: You sent me to a servant who did not want to die. Allah restored his [the angel's] eye,..." *Sahih Muslim* vol.4 book 29 no.5851 p.1264. Also*Sahih Muslim* vol.4 book 28 no.5852 p.1265. እንዲሁም ሙሴ ሰይጣንን በጥፊ ያጮለበት ሌላ ተመሳሳይ አጋጣሚም ነበር፡፡ The angel of death was sent to Moses and when he went to him, Moses slapped him severely, spoiling one of his eyes. The angel went back to his Lord, and said, "You sent me to a slave who does not want to die." Sahih Bukhari 2:23:423,

25.መሐመድና ሰይጣን ተደባደቡና መሐመድ አሸነፉ፡- ነቢያቸው መሐመድ ጸሎት እያደረጉ እያለ ሰይጣን በፊት ለፊታቸው መጣባቸውና ጸለታቸውን ሊያቋርጣቸው ሞከረ፡፡ መሐመድ ያን ጊዜ አንድ ነገር አደረጉ፡፡ አላህ ቀኝ እጅ ሆነላቸውና ሰይጣንን ጉሮሮውን ይዞ አነቁትው፡፡ እዛው በመስጊድ ውስጥ ባለው አንዱ ምሰሶ ላይም አሰሩት፡፡ The Prophet once offered the prayer and said, "Satan came in front of me and tried to interrupt my prayer, but Allah gave me an upper hand on him and I choked him. No doubt, I thought of tying him to one of the pillars of the mosque till you get up in the morning and see him. Sahih Bukhari 2:22:301

26.ሰይጣኖች በማታ ቁርአንን እንደሰሙ ዛፏ ለመሐመድ አሳወቀቻቸው፡- "I asked Masruq, 'Who informed the Prophet about the Jinns at the night when they heard the Qur'an?' He said, 'Your father 'Abdullah informed me that a tree informed the Prophet about them.'" Sahih Bukhari 5:58:199

27.ሰይጣን በሕልም መሐመድን ተመስሎ ሊታይ አይችልም፡- The Prophet said, "Whoever has seen me in a dream, then no doubt, he has seen me, for Satan cannot imitate my shape. Sahih Bukhari 9:87:123, See also Sahih Bukhari 9:87:124, Sahih Bukhari 9:87:125, and Sahih Bukhari 9:87:126

///////////////////////////////

28.መሐመድ ሕጋዊ ያልሆነ ወሲብ የፈጸሙትን ዝንጀሮ በድንጋይ ወግረው ገደሉ፡- "በቅድመ እስልምናው የአላዋቂነት ዘመን አንድ ሴት ዝንጀሮ በሌሎች ብዙ ዝንጀሮዎች ተከባ አየሁ፡፡ ሕገ ወጥ የሆነ የግብረ ስጋ ግንኙነት ፈጽማ ስለነበር በድንጋይ እየወገሯት ነበር፡፡ እኔም ከእነርሱ ጋር አብሬ ወገርኳት" illegal sexual intercourse of monkey: Narrated 'Amr bin Maimun: During the pre-Islamic period of ignorance I saw a she-monkey surrounded by a number of monkeys. They were all stoning it, because it had committed illegal sexual intercourse. I too, stoned it along with them. Sahih Bukhari 5:58:188

29.ሴት፣ ፈረስና ቤት መጥፎ ገዶች (ምልክቶ) ናቸው፡- "Bad omen is in the woman, the

horse and the home." Sahih Bukhari, Volume 5, Book 58, number 188: Sahih Al Bukhari 76/5

30.ዝንጀሮ፣ ጥቁር ውሻ፣ አህያና ሴት ጸሎትን ዋጋ ቢስ ያደርጋሉ፡- "ዝንጀሮ፣ ጥቁር ውሻና ሴት ጸሎት በሚያደርግ ሰው ፊት ለፊት አቋርጠውት ካለፉ ጸሎቱ ዋጋ ቢስ ነው ወይም ይሻርበታል" በማለት ነቢያቸው አስተምረዋል፡፡ "If a monkey, a black dog or a woman passes in front of a praying person, his prayer is nullified." (Sahih Bukhari 8/102 and Hanbel 4/86.) Narrated 'Aisha: The things which annul the prayers were mentioned before me. They said, "Prayer is annulled by a dog, a donkey and a woman (if they pass in front of the praying people)." I said, "You have made us (i.e. women) dogs... "Sahih Bukhari 1:9:490

31.ግርፋትና በድንጋይ ወግሮ መግደል፡- አንድ ያላገባ ወንድና ያላገባች ሴት ዝሙት ቢፈጽሙ መቶ ግርፋት መገረፍና ለአንድ ዓመት ከሀገር ወጥተው በግዞት መቀመጥ አለባቸው፡፡ ሁለቱም ዝሙት የፈጸሙት ያገቡ ከሆነ ደግሞ መቶ ግርፋት መገረፍና በድንጋይ ተወግረው መገደል አለባቸው፡፡ Sahih Muslim, Book 017, Number 4191

32.ሰይጣን መሬትን ተሸክሟታል፡- እንደ መሐመድ ትምህርት ከሆነ መሬትን ሰይጣን ተሸክሟታል፡፡ የመሬት መንቀጥቀጥም የሚከሰተው ሰይጣኑ ጭንቅላቱን ሲያወዛውዝ ወይም ሲያነቃንቅ ነው፡፡ the earth is carried on a giant bull; when it shakes its head, then an earthquake occurs. (Ibn Katheer 2/29; 50/1)

33.በመሐመድ ዘመን ጨረቃ ለሁለት ተሰኝጥቃለች፡- በመሐመድ ዘመን ጨረቃ ለሁለት ተሰኝጥቃ ወይም ተከፍላ ነበር፣ ስትሰነጠቅም መሐመድ በዓይናቸው አይተዋታል፡፡ እንዲያውም ለተከታዮቻቸው "እኔ ተአምረኛ ሰው ነኝ ጨረቃንኮ ለሁለት ሰንጥቄያታለሁ" ነው ያሏቸው፡፡ ቡኻሪ 4፡56፡830. "Narrated Ibn 'Abbas: The moon was split into two parts during the lifetime of the Prophet." *Bukhari* vol.4 book 56 (The Virtues and Merits of the Prophet and his Companions) ch.26 no.830 p.534.

34.የሙስሊሞቹ ነቢይ መሐመድና መጠጥ፡- መሐመድ በሕይወት በነበሩበት ወቅት መጠጥ ይጠጡ እንደነበር ሐዲሱ ላይ ተጠቅሷል፡፡ ለዚያውም ተከታዮቻቸውን «መጠጥ ፈልጋችሁ አምጡልኝ» ብለው እያዘዙ እነርሱም ወይን እያመጡላቸው ነው ሲጠጡ የነበረው፡፡ ጉዞም ሲሄዱ ወተትና ወይን እየያዙ ነበር፡፡ "We were with the messenger of Allah, PBUH and he asked for a drink. One of his men said: "Oh Messenger of Allah, Can we offer you wine to drink?" He said Yes. He (Gaber) went out looking for the drink and came back with a cup of wine. The messenger (Peace Be Upon him) asked:"Have you fermented it, even with one piece of ferment?" He (Gaber) said "yes" and he (Muhammad) drank. Sahih Muslim - Hadith #3753 Narrated Abu Huraira: Allah's Apostle was presented a bowl of milk and a bowl of wine on the night he was taken on a journey (Al-Mi'raj). Sahih Bukhari 7:69:508

35.መሐመድ ስለ ራሳቸው የሰጡት ግምት፡- ነቢያቸው መሐመድ ስለ ራሳቸው ሲናገሩ "በዕለተ ምፅዓት ቀን የሰው ዘር ሁሉ መሪ እሆናልሁ" ነው ያሉት፡፡ በዚያን ጊዜ ሁሉም የሰው ዘር በአላህ ፊት ይቆማል፡፡ አስታርቆ የሚያድናቸው ሰው ይፈልጋሉ፡፡ አዳም፣ ኖኅ፣ አብርሃም፣ ሙሴ፣ ኢሳ (ለስም አጠራሩ ክብርና ምስጋና ይግባውና ጌታ ኢየሱስም ጭምር) ሁሉም አማልደው ሰዎችን ከአላህ የቁጣ ፍርድ ማዳን አይችሉም፡፡ መሐመድ ብቻ ናቸው ለሁሉም የሰው ዘር መሪ ሆነው የመዳን ዋስትና የሚያስገኙላቸው፡፡ Mohammed Had High Self Esteem:"I shall be the leader of mankind on the Day of Resurrection." People would look for someone to intercede for them before Allah. Adam, Noah, Abraham, Moses, and Jesus would all decline, all but Jesus said because of their faults. Jesus would suggest they go to Mohammed, and then Mohammed will call out to God. *Sahih Muslim* vol.1 book 1 no.378 p.129-132. See also vol.1 book 1 no.381 p.133.

36.መንገድ ላይ ያገኛችሁትን ሰው ገፍትራችሁ እለፉ፡- መሐመድ ለተከታዮቻቸው አንድ የሰጧቸው ትእዛዝ አለ፡፡ አንድ ሙስሊም መንገድ ላይ እየሄደ ከፊት ለፊቱ አይሁዳዊ ወይም ክርስሪያን የሆነ ሰው ቢመጣ ያንን ሰው ገፍትሮ ከመንገዱ በማስወጣት በጠባቡ መንገድ በኩል እንዲያልፍ ማስገደድ አለበት፡፡ ቀድሞም ሰላምታ መስጠት የለበትም፡፡ ሙስሊሞችም በአጠቃላይ አይሁዶችንና ክርስቲያኖችን ቀድመው ሰላም ማለት የለባቸውም፡፡ *Sahih Muslim* vol.3 book 24 no.5389,5390 p.1185 says, "Abu Huraira reported Allah's Messenger (may peace be upon him) as saying: Do not greet the Jews and Christians before they greet you and when you meet any one of them on the roads force him to go to the narrowest part of it."

37.በረመዳን ወር ሰይጣን ጡረታ ይወጣል፡- የረመዳን ወቅት ሲመጣ የጀነት በሮች ክፍት ሲሆኑ የገሀነም በሮች ደግሞ ማንም ሙስሊም እንዳይገባባቸው ይዘጋሉ፡፡ ያን ጊዜ ሰይጣንም ጡረታ የሚወጣበት ወቅት ነውና በተከርቸም ይታሰራል፡፡ Allah's Apostle said, "When the month of Ramadan comes, the gates of Paradise are opened and the gates of the (Hell) Fire are closed, and the devils are chained." Sahih Bukhari 4:54:497

38.ከሞተ ውሻና ከቆሻሻ ጋር የተቀለቀለ ውኃ ንጹሕ ነው፡- ሴቶች በወርሃዊ ልማቸው ወቅት የተጠቀሙበት ጨርቅ፣ የሞተ ውሻና ሌሎችም ቆሻሻ ነገሮች የተጣሉበት የወንዝ ውኃ ንጹሕ ስለሆነ እርሱን መጠቀም ይቻላል፡፡ "The people asked the Messenger of Allah 'Can we perform ablution out of the well of Buda'ah, which is a well into which menstrual clothes, dead dogs and stinking things were thrown? He replied: Water is pure and is not defiled by anything." Abu Dawud 1:66 , See Also Abu Dawud 1:67

39.የበሽታዎች ሁሉ መነሻ፡-የሲኦል እሳት የሙቀት መጠኑ ሲጨመር ለበሽታዎች ሁሉ መነሻ ነው፡፡ The Prophet said, "Fever is from the heat of Hell, so abate fever with water." Sahih Bukhari 7:71:621, See Also Sahih Bukhari 7:71:619.

40.ሙስሊሞች መስመራቸውን ጠብቀው ካልሰገዱ አላህ ፊታቸውን ያጣምማቸዋል፡- ሙስሊሞች ሲሰግዱ መስመራቸውን በጥንቃቄ ጠብቀው ካልሰገዱ አላህ ፊታቸውን ይለውጠዋል፡- The Prophet said, "Straighten your rows or Allah will alter your faces." Sahih Bukhari 1:11:685

41.ሙስሊሞች አላህን ወደፊት ያለ ጫማ ባዶ እግሩን ሆኖ፣ እርቃኑን በእግሮቹ እየሄደ ያዩታል፡- በሳሂህ ሙስሊም ሐዲስ ላይ እንደተጻፈው አላህ የራሱ ባለሆነ በተለየ የአካል ቅርጽ ለሰዎች ይገለጽና "እኔኮ ጌታችሁ ነኝ" ይላቸዋል፡፡ *Sahih Muslim* vol.1 book 1 no.349 p.115 "...Allah would then come to them in a form other than His own Form, recognizable to them, and would say: I am your Lord. They would say: We take refuge with Allah from thee...." See also *Bukhari* vol.8 book 76 no.577 p.375; *Bukhari* vol.9 book 93 no.532 p.395-396. ሙስሊሞች ወገኖቻችን የወልደ እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው መሆንና አምላክነቱ ፈጽሞ አይዋጥላቸውም፡፡ የእምነትና የአመለካከት ጉዳይ እስከሆነ ድረስ እኛም ያ ለምን ሆነ አንልም፡፡ ግን ደግሞ ከዚህ የአምላክ ሰው መሆን ጋር በተገናኘ አንድ አስገራሚ ነገር በራሳቸው መጽሐፍ ላይ ተጽፎ እናገኛለን፡፡ ነቢያቸው መሐመድ ለተከታዮቻቸው ሲያስተምሩ እንዲህ ነው ያሉት፡- "አላህን ያለ ጫማ ባዶ እግሩን ሆኖ፣ ያለ ምንም ልብስ እርቃኑን ሆኖ፣ በእግሮቹ እየሄደና ያልተገረዘ ሆኖ ታገኙታላችሁ" The Prophet said, "You will meet Allah barefooted, naked, walking on feet, and uncircumcised." Sahih Bukhari 8:76:531, See also Sahih Bukhari 8:76:532, Sahih Bukhari 8:76:533. እንዲሁም ይህ አገላለጽ በሐዲሱ ውስጥ ብዙ ቦታ ተጽፎ ይገኛል፡፡ (Sahih Bukhari Volume 1, Book 4, Number 238) & (Sahih Bukhari Volume 8. Book 76. Number 532.)

በመሠረቱ በእነዚህ ጥቅሶች ላይ አጉልቶ ለማሳየት የተፈለገው አላህ ሰዎች ባልጠበቁት መንገድ ራሱን በሌላ አካል ገልጾ እንደሚያሳፍራቸው ለመግለጽ ነው፡፡ ለመሆኑ "በባዶ እግር፣ ያለ ምንም ልብስ እርቃንን መሆን ለዚያውም ያልተገረዘ አካልን ማሳየት" ምን ማለት ነው? በምስጢር ደረጃ ካየነው የቃሉ ትርጉም ምንድነው? አላህ የራሱን ማንነት ደብቆ በሌላ አካል ተመስሎ ለሰዎች ራሱን መገለጽ ከቻለና በአንድ በኩል ደግሞ ሙስሊሞቹ የእነርሱ አምላክ ፍጹም እርቃኑን ሆኖ ኃፍረተ ሥጋውን እንኳን ሳይሸፍን ያን ያህል ተጋላጭ ሆኖ ለዚያውም አለመገረዙን እንኳን እስኪያሳያቸው ድረስ የሚገለጽላቸው ከሆነ ምነው ታዲያ ኢየሱስ ክርስቶስ የሰውን ሥጋ ፍጹም ተዋሕዶ መገለጡ አልዋጥላቸው አለ? አሁን ማን ይሙት እስቲ "አምላክ ሰው ሆነ" ብሎ ከማመንና "አምላክ እርቃኑን ሆኖ ሳይገረዝ ሀፍረተ ሥጋውን እያሳየ በገሃድ ይታያል" ብሎ ከማመን የትኛው ይከብዳል? በባዶ እግር መሄድ፣ እርቃን ሆኖ መታየትና አለመገረዝ... እነዚህና የመሳሰሉት ነገሮች ፍጹም የሥጋ ባሕሪያቶች ናቸውና ለመለኮት አይስማሙትም፡፡ መለኮት በባሕርይው እነዚህ ነገሮች ፈጽሞ የሉበትም፡፡

42.ከብር በተሠራ ዕቃ መጠጣት ለገሀነም እሳት ይዳርጋል፡-ከብር በተሠራ ዕቃ መጠጣት ኃጢአት ነው፡፡ መሐመድ ይህንን በተመለከተ ያስተማሩት ትምህርት እንዲህ የሚል ነው፡- "ከብር በተሠራ ዕቃ የሚጠጣ ሰው ቢኖር እርሱ ሆዱን በገሀነም እሳት የሚሞላ ነው" Allah's

Apostle said, "He who drinks in silver utensils is only filling his abdomen with Hell Fire." Sahih Bukhari 7:69:538

43.የሙሴን ልብስ ይዛ የሮጠችው ድንጋይ፡- ሙሴ ሻወር ሊወስድ ብሎ ልብሱን አውልቆ ድንጋይ ላይ ያስቀምጣል፡፡ ድንጋይዋ እርሱ ራቁቱን መሆኑን አይታ በፍጥነት ልብሱን ይዛበት እሮጠች፡፡ ሙሴም «አንቺ ድንጋይ ልብሴን አምጪ እንጂ! ኧረ ልብሴን....» እያለ ተከተላት፡፡ Abu Huraira reported that Moses was a modest person. He was never seen naked and Banu Isra'il said: (He was afraid to expose his private part) because he had been suffering from scrotal hernia. He (one day) took bath in water and placed his garments upon a stone. The stone began to move on quickly. He followed that and struck it with the help of a stone (saying): O stone, my garment; O stone, my garments, O stone..... Sahih Muslim 30:5850, See also: Sahih Bukhari 4:55:616

44.የመሐመድ ምግብ አላህን አመሰገነች፡- We used to consider miracles as Allah's Blessings, but you people consider them to be a warning. Once we were with Allah's Apostle on a journey. I saw the water flowing from among the fingers of Allah's Apostle , and no doubt, we heard the meal glorifying Allah, when it was being eaten (by him). Sahih Bukhari 4:56:779

45.በመካ ያሉ ድንጋዮች ለመሐመድ ሰላምታ ይሰጡ ነበር፡- Jabir b. Samura reported Allah's Messenger as saying: I recognise the stone in Mecca which used to pay me salutations before my advent as a Prophet and I recognise that even now. Sahih Muslim 30:5654

46.ውዱ፣ ጸሎትና ፈስ መፍሳት፡- ውዱ ማለት ከሶላት በፊት የሚካሄድ ኃይማኖታዊ የመታጠብ ሥርዓት ነው፡፡ ሙስሊሞች ጸሎት እያደረጉ እያለ ድንገት ቢፈሱ ጸሎታቸውን አቋርጠው እንደገና ውዱ ማድረግና ያቋረጡትን ጸሎት እንደገና መጀመር አለባቸው፡፡ ይህ ካልሆነ አላህ ጸሎታቸውን አይሰማቸውም፡፡ በሚፈሳ ሰውም መሳቅ ክልክል ነው፡፡ The Apostle of Allah said: When any of you breaks wind during the prayer, he should turn away and perform ablution and repeat the prayer. Abu Dawud 1:205 & Sahih Bukhari 1:4:139 Narrated Abu Huraira: The Prophet said, "Allah does not accept prayer of anyone of you if he does Hadath (passes wind) till he performs the ablution (anew)." Sahih Bukhari 9:86:86 Narrated 'Abdullah bin Zam'a: The Prophet forbade laughing at a person who passes wind. Sahih Bukhari 8:73:68

47.በጀነት ውስጥ መቶ ዓመት ሙሉ ጋልበው የማያቋርጡት የዛፍ ጥላ አለ፡- በጀነት ውስጥ እጅግ ግዙፍ የሆነ አንድ ዛፍ አለ፡፡ እርስዎ ምንም እንኳን ኃይለኛ ጋላቢ ቢሆኑም የዚህን ዛፍ ጥላ ለመቶ ዓመት ያህል እንኳን ጋልበው ላያቋርጡት ይችላሉ፡፡ Allah's Apostle said, "In Paradise there is a tree so big that in its shade a rider may travel for one hundred years without being able to cross it." Sahih Bukhari 8:76:559t

48.ጠቢቡ ሰሎሞን በአላህ መንገድ የሚዋጋ ወታደር ለመውለድ ሲል በአንድ ሌሊት ከመቶ ሴቶች ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት አደረገ፡- እንደ መሐመድ አስተምህሮ ጠቢቡ ሰሎሞን እንዲህ ብሎ ተናገረ፡- «በአላህ ስም ዛሬ ማታ ከመቶ ወይም ከ99 ሴቶች ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት አደርጋለሁ፡፡ እያንዳንዳቸውም በአላህ መንገድ የሚዋጋ ወታደር ይወልዳሉ፡፡» Allah's Apostle said, "Once Solomon, son of David said, '(By Allah) Tonight I will have sexual intercourse with one hundred (or ninety-nine) women each of whom will give birth to a knight who will fight in Allah's Cause." Sahih Bukhari 4:52:74i

49.የአውራ ዶሮና የአህያ ጩኸት፡- አውራ ዶሮ ሲጮህ ከሰማችሁ ያን ጊዜ አላህን አመስግኑ ምክንያቱም የጮኸው ማላኢኮችን (መላእክትን) አይቶ ስለሆነ ነው፡፡ በተቃራኒው ግን አህያ ሲጮህ ከሰማችሁ አላህን አንተ ጠብቀን በሉት ምክንያቱም ሰይጣንን አይቶ ነውና የጮኸው፡፡ The Prophet said, "When you hear the crowing of cocks, ask for Allah's Blessings for (their crowing indicates that) they have seen an angel. And when you hear the braying of donkeys, seek Refuge with Allah from satan for (their braying indicates) that they have seen a satan." Sahih Bukhari 4:54:522

50.ላምና ተኩላ እረኛን በአንደበታቸው አናገሩት፡- እረኛው የሚነዳትን ላም ሲጋልባት ላሟ አፍ አውጥታ "እኛ ላሞች ለዚህ አልተፈጠርንም፣ እባክህ ውረድልኝ!" በማለት ስትናገረው ማንም ሰው በሌለበት መሐመድ ብቻ ሰምተዋታል፡፡ Once Allah's Apostle; offered the morning prayer and then faced the people and said, "While a man was driving a cow, he suddenly rode over it and beat it. The cow said, "We have not been created for this." The Prophet said, "I believe this, and Abu Bakr and 'Umar too, believe it, although neither of them was present there" እንደዚሁም በተመሳሳይ ሁኔታ በግ ጠባቂው እረኛ አንዷን በግ ነጥሎ የወሰደበትን ተኩላ አባሮ በጊቱን ያስጥለዋል፡፡ ያን ጊዜ ተኩላው እረኛውን በአንደበቱ "አንተ አስጣልከኝ አይደል!" ብሎ በቁጭት ተናግሮታል፡፡ ይህንን ያየውና የሰማው መሐመድ ብቻ ቢሆንም እነ አቡ በከርና ኦማርም አምነውታል፡፡ While a person was amongst his sheep, a wolf attacked and took one of the sheep. The man chased the wolf till he saved it from the wolf, where upon the wolf said, "You have saved it from me." The Prophet said, "But I believe this, and Abu Bakr and 'Umar too, believe this, although neither of them was present there." Sahih Bukhari 4:56:677

51.ሰዎች ልክ እንደ ግመሎች ናቸው፡- I heard Allah's Apostle saying, "People are just like camels. Sahih Bukhari 8:76:505

52.ውኃ ቆሞ መጠጣት ፈጽሞ የተከለከለ ነው፡- መሐመድ ውኃ ቆሞ መጠጣትን ከልክለዋል፡፡ ሙስሊሞች ከሆኑ ምናልባት እረስተው እንኳን ቆመው ከጠጡ ማድረግ ያለብዎ ነገር እንዲያስመልስዎ አድርገው ያስወጡት እንጂ ቆመው የጠጧት ውኃ ወደ ሆድዎ በፍጹም መግባት የለባትም፡፡ Abu Huraira reported Allah's Messenger as saying: None of you

should drink while standing; and if anyone forgets, he must vomit. Sahih Muslim 23:5022

53.ሙስሊሞች በሚሰግዱና በሚጸልዩ ጊዜ ዓይኖቻቸውን ወደ ሰማይ የሚያነሱ ከሆነ ከባድ ቅጣት አለባቸው:- ሙስሊሞች በሚጸልዩ ጊዜ ዓይኖቻቸውን ወደ ሰማይ የሚያነሱ ከሆነ ይህንን የሚያደርጉ ከሆነ ዓይኖቻቸው ተመንጭቀው መወሰድ ወይም መጥፋት አለባቸው፡፡ People should avoid lifting their eyes towards the sky while supplicating in prayer, otherwise their eyes would be snatched away. Sahih Muslim 4:863. Jabir b. Samura reported: The Messenger of Allah said: The people who lift their eyes towards the sky in Prayer should avoid it or they would lose their eyesight. Sahih Muslim 4:862

54.መሐመድ እጅግ አድርገው የሚፈቅሯቸው 3 ነገሮች ሴት፣ ሽቶና ምግብ ናቸው:- Aisha said "The Prophet of Allah liked three things of this world: Perfume, women, and food." Ibn Sa'd's Kitab Tabaqat Al-Kubra, Volume 1, Page 380

መሐመድ ይወዷቸው የነበሩትን ነገሮች ሕጻኗ ሚስታቸው አይሻ ነግራናለች፡፡ እርሳቸው በግል ይወዷቸውና ይጠሏቸው የነበሩ ነገሮች በዝርዝር ተቀምተዋል፡፡ የሚገርመው ነገር መሐመድ በግላቸው ይጠሏቸው የነበሩ ነገሮችን ሁሉ እንደሃይማኖታዊ ቀኖና ወይም ሥርዓት ተደርገው መወሰዳቸው ነው፡፡ ለምሳሌ መሐመድ በግል ባሕርያቸው ጥቁር ውሻ፣ አይጥና የቼዝ ጨዋታን አጥብቀው ይጠሉ ስለነበር እነዚህን ነገሮች ወደ ሃይማኖታዊ ቀኖናነት ለውጠዋቸው ሕግ ሠርተውበባቸዋል፡፡ ጥቁር ውሻና የቼዝ ጨዋታ "ሰይጣን ናቸው" ተብለው ሲፈረጁ አይጥ ቤትን በእሳት ስለምታጋይ "ቤት አቃጣይ" ተብላ በዋነኛ ጠላትነት ተመዝግባለች፡፡

Black dogs are devils፡ Abu Dharr reported: The Messenger of 'Allah said: When any one of you stands for prayer and there is a thing before him equal to the back of the saddle that covers him and in case there is not before him (a thing) equal to the back of the saddle, his prayer would be cut off by (passing of an) ass, woman, and black Dog. I said: O Abu Dharr, what feature is there in a black dog which distinguish it from the red dog and the yellow dog? He said: O, son of my brother, I asked the Messenger of Allah as you are asking me, and he said: The black dog is a devil. Sahih Muslim 4:1032

Playing chess is evil: Buraida reported on the authority of his father that Allah's Apostle said: He who played chess is like one who dyed his hand with the flesh and blood of swine. Sahih Muslim 28:5612

The Messenger of Allah, said, "Lock the door, tie the waterskin, turn the vessel over or cover it, and put out the lamp. Shaytan does not open a locked door or untie a tied knot, or uncover a vessel. A mouse may set fire to people's houses about them." Al-Muwatta 4910.21, "The mouse may set the house on fire over its

inhabitants." Sahih Muslim 23:4994

አሁንም መሐመድ የራሳቸውን ልማዶች ሃይማኖታዊ ሥርዓት ያደረጓቸውን ሌሎች እንግዳና ልማዳዊ ትእዛዞቻቸውን የተወሰኑትን እንይ፡- ውኃ ቆሞ መጠጣት ክልክል ነው፡፡ /ሳሂህ ሙስሊም 3፡21፡5014/፤ ሙስሊሞች ውኃ ሲጠጡ 3 ጊዜ እየተነፈሱ ከሆነ የበለጠ ጤናማና ብሩህ ይሆናሉ፡፡ /ሳሂህ ሙስሊም 3፡21፡5029/፤ ሙስሊሞች ጫማቸውን እንኳን ሲያድርጉና ሲያወልቁ ቅደም ተከተል መጠበቅ አለባቸው፡፡ ጫማ ሲያድርጉ መጀመሪያ ማድረግ ያለባቸው ቀኙን ነው፡፡ ሲያወልቁ ደግሞ ከግራ እግራቸው መጀመር አለባቸው፡፡ /*Sahih Muslim* vol.3 book 22 no.5231 p.1154,*Shamaa-il Tirmidhi* ch.19 no.9 (79) p.75./ አክታን ወይም ምራቅን ወደ ቀኝ ዞሮ መትፋት ክልክል ነው፡፡ ወደ ግራ ብቻ ዞሮ ነው መትፋት የሚቻለው፡፡ /ሳሂህ ሙስሊም 4፡41፡7149/፤ እንዲያውም ይህን ማድረጉ ትልቅ ጥቅም አለው፡፡ ከመጥፎ ሕልም ለመጠበቅ ይረዳል፡፡ ሁሉም መጥፎ ሕልም የሚመጣው ከሰይጣን ስለሆነ መጥፎ ሕልምን ያየ ሰው ባየው መጥፎ ሕልም ምክንያት ጉዳት እንዳይደርስበትና ከአላህ ጥበቃ እንዲያገኝ ወደ ግራ ዞሮ መትፋት አለበት፡፡ The Prophet said, "A good dream that comes true is from Allah, and a bad dream is from Satan, so if anyone of you sees a bad dream, he should seek refuge with Allah from Satan and should spit on the left, for the bad dream will not harm him." /Sahih Bukhari 9:87:115/፤

55.መሐመድ አሸናፊና ድል አድራጊ አይደለም ብለው ካሰቡ ራስዎን ይስቀሉ፡- አላህ መልእክተኛውን መሐመድን በዚህ ዓለምም ሆነ በመጨረሻይቱ ዓለም ድል ማድረግንና አሸናፊነትን አይሰጠውም ብሎ የሚያስብ ሰው ገመድን እስከ መኖሪያው ቤት ጣሪያ ድረስ ይዘርጋና በእርሱ ይታነቅበት፡፡ Whoso is wont to think (through envy) that Allah will not give him (Muhammad) victory in the world and the Hereafter (and is enraged at the thought of his victory), let him stretch a rope up to the roof (of his dwelling), and let him hang himself. Then let him see whether his strategy dispelleth that whereat he rageth!.Qur'an 22:15

56.ጂብሪል ለመሐመድ "አላህን ያመነና አንተን የተከተለ ዝሙተኛም ይሁን ቀማኛ ሌባ እርሱ ጀነት ይገባል" ብሎ ነገራቸው፡- መሐመድ ስለተሰጣቸው ቃልኪዳን ሲናገሩ እንዲህ አሉ፡- "መልአኩ ጂብሪል እንዲህ አለኝ፡- 'ከአላህ በቀር ሌላ ማንንም ያላመለከ የአንተ ተከታይ ማንም ቢኖር እርሱ ጀነት ይገባል፣ ሲኦልን አያይም' አለኝ፡፡ እኔም ጠየኩት፡- 'ሕጋዊ ያልሆነ ዝሙት የፈጸመ ወይም የሰረቀም እንኳ ቢሆን' ብዬ ጠየኩት፡፡ እርሱም 'አዎ ሕጋዊ ያልሆነ ዝሙት የፈጸመ ወይም የሰረቀም እንኳ ቢሆን እርሱ ጀነት ይገባል፣ ሲኦልን አያይም'" አለኝ፡፡ The Prophet said, "Gabriel said to me, 'Whoever amongst your followers die without having worshipped others besides Allah, will enter Paradise (or will not enter the (Hell) Fire)." i asked him, "Even if he has committed illegal sexual intercourse or theft?" He replied, "Even then." Sahih Bukhari 4:54:445

**የዐረቢያ ምድር- ከመሐመድ መወለድ በፊት፡-** የዐረቢያ ምድር ከጥንት ጀምሮ የሁሉም የቤዱይን ፓጋን ዐረቦች መሰባሰቢያ ነበረች፡፡ በተለይም ዋናዋ መካ ከተማ የብዙ ቤተ-ጣኦታት (House of god) መናኸሪያ ነበረች፡፡ በውስጧም ከ360 በላይ ጣኦታትን በጋራ የያዘ ካዕባ (ka'aba) እየተባለ የሚጠራ የማምለኪያ ቦታ ነበር፡፡ መካ ከተማ ለንግድ ወደ ብዙ ሀገራት ለሚመላለሱ የሲራራ ነጋዴዎች ማረፊያ ስትሆን ዋነኛ የንግድ ማዕከልም ነበረች፡፡ መካ ሲደርሱም በጣኦቶቻቸው ፊት አምልኮታቸውን ይፈጽማሉ፡፡ መካ የቀድሞ ስሟም «በካህ» ይባል ነበር፡፡ ቁርአኑ 3፡96 ላይ «ለሰዎች መጸለያ መጀመሪያ የተኖረው ቤት ቡሩክና ለዓለማት ሁሉ መምሪያ ሲሆን ያ በበካህ (በመካ) ያለው ነው» በማለት በግልጽ አስቀምጦታል፡፡

በዘላንነት ከሚኖሩት ከተለያዩ ፓጋን ዐረብ ጎሳዎች በተለየ ሁኔታ ቁራይሽ የሚባሉት ጎሳዎች ዋነኛ የንግድ መናኸሪያ በሆነችው በመካ ሰፍረው ይኖሩ ነበር፡፡ ቁራይሾቹ ነጋዴዎች ከሩቅ ሲመጡ በካዕባ አጠገብ ካለው ውሃ ጥማቸውን የሚቆርጡበት ዘምዘም የሚባል ውሃ ከመሸጥ ጀምሮ ከነጋዴዎች በተለያየ መንገድ ገንዘብ ያገኛሉ፡፡ መካን በዋናነት ሰፍረውባት የሚኖሩት ቁራይሾች ሦስት የተለያዩ ቡድኖች ወይም ግሩፖች ነበሩባት፡፡ የመጀመሪያዎቹ የ360 ጣኦታት መከማቻ የሆነውን የካዕባን ቤተ-ጣኦት ያስተዳድሩ የነበሩ የቀሳውስት አባላት ናቸው፡፡ ሁለተኛዎቹ በንግዱ የሚሳተፉ ትንሽ አባላት ያሉበት ሲሆን ሦስተኛዎቹ በኑሮ ደረጃቸው ዝቅተኛ የሆኑ ነገር ግን በርካታ አባላት ያሉበት ሲሆን ዋነኛ የገቢ ምንጫቸው በየዓመቱ ለአምልኮ ወደ መካ ለሚመጡ ለሌሎች ፓጋን ዐረቦች ውሃ በማቅረብ ይተዳደራሉ፡፡

ለአምልኮ የሚመጡት ሰዎች ወቅት ጠብቀው ስለሆነ እነዚህ ሦስተኛዎቹ ወገኖች ታዲያ በቂ ገቢ ስለማያገኙ በኑሮ የተጎዱ ነበሩ፡፡ አብደላህ (Abdullah) የተባለ የእነዚህ የሦስተኛዎቹ ወገን አባላት የሆነ የቁራይሽ ሰው ነበር፡፡ ሚስቱ አሚና ትባላለች፡፡ አብደላህ ቋሚና በቂ ገቢ ስላልነበረው ኑሮው አስቸጋሪ ስለነበር እራት ሳይበሉ የሚተኙበት ጊዜም ነበር፡፡ አሚና ይህ ሕይወታቸው በእጅጉ ያሳስባት ስለነበር ልጅ እንዳይወልዱ ለማድረግ የተለየ ዘዴን እንዲጠቀም ባሏን ታስገድደው ነበር፡፡ ይጠቀሙበት የነበረው ዘዴም የወንዱን የዘር ፈሳሽ ወደ ውጭ እንዲፈስ (ejaculate) በማድረግ ነው፡፡ አብደላህና አሚና ይህንን ዘዴ ለረጅም ጊዜ ተጠቅመውበታል፡፡ {*በነገራችን ላይ ይህን ዘዴ እነ መሐመድ የጀሃድ ጦርነት አድርገው ሴቶችንና ሕጻናትን በምርኮ (War captives) ከወሰዱ በኋላ ለባርነት ንግድ እንዲያመቻቸው በማለት ሴቶቹ እንዳያረግዙ ይህንን ዘዴ ይጠቀሙ እንደነበር በሐዲሱ ውስጥ ብዙ ቦታ*

*ተጠቅሷል፡፡ ቡኻሪ 3፡34፡436፡፡* እንዲያውም መሐመድ ተከታዮቻቸው ይህንን ዘዴ ተግባራዊ እንዲያደርጉ ትእዛዝ ሰጥተው ነበር፡፡ *"ወደ አላህ መልእክተኛ አንድ ሰው መጣና እንዲህ አለ፡- 'የምታገለግለን ባሪያ ሴት ልጃገረድ አለችን፡፡ ከእርሷ ጋር ዝሙት ፈጽሜያለሁ ነገር ግን እንድታረግዝ አልፈልግም' ነቢዩም እንዲህ ሲል መለሰለት፡- 'ከፈለግህ የዘር ፈሳሽህን ወደ ውጭ በማፍሰስ (coitus interruptus or ejaculate) በማድረግ እንዳታረግዝ ማድረግ ትችላለህ'" (Sahih Muslim 8:3383) "ከነቢዩ መሐመድ ጋር ሆነን የባኑ አልሙስጣሊቅ ጎሳዎችን በጦርነት ለመማረክ ሄድን፡፡ የጦር ምርኮዎቻችን የሆኑ ሴቶችንም ወሰድን፡፡ ለወሲብ ስለተመኘናቸውም የዘር ፈሳሻችንን ወደ ውጭ በማፍሰስ (coitus interruptus or ejaculate) በማድረግ እንዳያረግዙ አድርገን ከእነርሱ ጋር ግብረ ስጋ ግንኙነት መፈፀምን ፈለግን" (Sahih Bukhari 5:59:459)*}

ወደ አብደላህና አሚና እንመለስና ሁለቱ በቂ ገቢ ስላልነበራቸው ኑሮውም በጣም አስቸጋሪ ስለሆነባቸው አሚና ልጅ እንዳይወልዱ ለማድረግ ይህንን የወንዱን የዘር ፈሳሽ ወደ ውጭ እንዲፈስ (ejaculate) የማድረግ ዘዴን ለረጅም ጊዜ እንዲጠቀም ባሏን ስታስገድደው ኖራለች፡፡ ለረጅም ጊዜ ሲጠቀሙበትም ኖረዋል፡፡ ይህ ድርጊት ለብዙ ጊዜ ሳትወልድ እንድትቆይ ቢያደርጋትም እርሷ እንዳሰበችው ግን ዘላቂ አልሆነላትም፡፡ አንድ ቀን አብደላህ ራሱን መቆጣጠር ያቅተውና ዘሩን ወደ ውጭ ሳያፈስ ቀረ፡፡ አሚናም በዚያች ቀን አረገዘች፡፡ በዚህች ቅፅበት የሙስሊሞቹ ነቢይ መሐመድ ኢብን አብደላህ ተረገዙ፡፡

አሚና በማርገዟ በጣም ስለተናደደች ልታስወርደውም ብዙ ሞክራ አልሳካላት አለ፡፡ ባሏም ባራካት የተባለች ትውልዷ ኢትዮጵያዊ የሆነች ባሪያ ሴት ሠራተኛ ቢያመጣላትም አሚና ባረገዘች በ6 ወር ውስጥ አብደላህ ሞተ፡፡ "Because Abdullah did not have a consistent income, his household often suffered from deprivations. Many a times, the couple had to go to bed without food. Persistent poverty took its toll; the couple frequently fought and argued on their financial condition as well as on what was likely to happen to them in future. Recognizing the fact that she and her husband did not have the means to feed another mouth, Amina always forced her man to ejaculate his semen outside her vagina. This practice helped her to avoid pregnancy for some time, but one night Abdullah failed to control himself, and she ended up being a pregnant woman. Amina was angry. She tried her best to destroy the pregnancy, but failed. Unable to do anything else with her conception, she resigned to her fate and decided to carry her pregnancy to its full

term. Abdullah, her husband, felt for her discomforts and sought to help by providing her with the services of a slave-girl, named Barakat. But as misfortune would have it, Amina's husband died when she was six months into her pregnancy." (Muhammad and the Origins of Islam, p. 126 & Philip K. Hitti, History of the Arabs, p. 133)

2.የመሐመድ የልጅነት ሕይወት እጅግ አሰቃቂ ነበር፡- አብዱላህ ከሞተ ከሦስት ወር በኋላ ልጁ መሐመድ በ570 ዓ.ም ተወለዱ፡፡ አሚናም ስማቸውን ኮዛን (kothan) ብላ ጠራቻቸው፡፡ ነገር ግን በኋላ ላይ ወንድ አያታቸው መሐመድ ብሎ ሰይሟቸዋል፡፡ መሐመድ በተወለዱበት ዘመን መላው የዐረቢያን ምድር በአምልኮ ጣዖት፣ ልቅ በሆነ ዝሙትና በግብረ ሰዶማዊ ተግባርና በሌሎችም አጸያፊ ተግባራት የተጠመደ ሕዝብ ነበር የሚኖርባት፡፡ ይሁን እንጂ ከዚሁ ጋር ተያይዞ በዚህ ልቅና ቅጥ ባጣ ወሲባዊ ሕይወታቸው ምክንያት ሴቶቹ ዲቃላ ሲያረግዙ በጎብረተሰቡ ዘንድ በእጅጉ ይወገዙና ይጠሉ ነበር፡፡ አሚናም ዲቃላ ነው የወለደችው ተብላ ይህ መሰደብና መገለል ስለደረሰባት ልጁን አትይዘውም፣ ጡትም አታጠባውም ነበር፡፡ ይህንን ሁኔታ ተመልክታ የታዘበችው የመሐመድ አጎት የአቡ ላሀብ ሠራተኛ የሆነችው ዙዋይባህ ለጊዜውም ቢሆን በማለት መሐመድን እየተመላለሰች ትመግባቸው ነበር፡፡

ሀብታም የካራቫን ነጋዴዎች ወቅት ጠብቀው በካዕባ አምልኮአቸውን ሊሚፈጽሙ ወደ መካ ከተማ በሚመጡበት ጊዜ ድሀ የሆኑ የቤዱይን ዐረቦችም ወደ ቦታው እየመጡ ጥቃቅን ሥራዎችን ይሠሩና ይለምኑ ነበር፡፡ በዚህ ልማድ መሠረት ሀሊማ የተባለች ሴት ወደ መዲና መጥታ የአሚናን ቤት ታገኛለች፡፡ አሚናም ልጁን መሐመድን እንድትወስድላት ስትጠይቃት እንግዳዋ ሴትም ከፍ ሲል በእረኛነት አስቀጥሬው እጠቀምበታልሁ በማለት በአሚና ሀሳብ ተስማምታ መሐመድን ወሰደቻቸው፡፡ የሀሊማ ጎሳዎች ይኖሩ የነበረው በሰሜናዊ ዐረቢያ አካባቢ ለእርሻና ለእረኝነት አመቺ በሆነ ሸለቆያማ አካባቢ (pastoral valleys) ነበር፡፡ ሀሊማ በመሐመድ ዕድሜ የሚገኝ ማስሩድ የሚባል ልጅ ስለነበራት አብራ እያጠባች አሳደገቻቸው፡፡ ከአምስት ዓመት ዕድሜያቸው ጀምሮ መሐመድና ማስሩድ አንድ ላይ ሲጫወቱ የዋሉትን ጨዋታ ለሀሊማ ይነግሯት ነበር፡፡ አንድ ቀን ግን ማስሩድ ለእናቱ የተለየ ነገር ነገራት፡፡ «በዱር ስንጫወት መላዕክት የመሰሉ ሁለት ነጫጭ ሰዎች መጥተው መሐመድን ከበውት አየሁ» አላት፡፡ ንግግሩንም ቀጠለ፡- «እየተጫወትን እያለ ሁለቱ ሰዎች መጥተው መሐመድን መሬት ላይ ጣሉት፡፡ ከእነርሱ ውስጥ አንደኛው ጂብሪል የመሐመድን ልቡን ቀደደና ውስጡን አጠበለት፡፡ በዚህም በውስጡ ያለውን እንደ ጥቁር ያለ በዘር የሚተላለፈውን የአደምን በደል አጥቦ አውጥቶ ካነፃው በኋላ በእውቀትና በእምነት

ሞላው፡፡ የነቢይነትንም ብርሃን አሳየው፡፡ የነቢይነትንም ምልክት በትከሻና ትከሻዎቹ መሀከል የጠባሳ ምልክት አድርጎበታል» እያለ ሁኔታውን በዝርዝር ለእናቱ ከነገራት በኋላ ነገሩን ከመሐመድም አንደበት እውነት መሆኑን ካረጋገጠች በኋላ ሀሊማ ይህንን በአካባቢዋ ላሉ ሰዎች ሁሉ ነገረቻቸው፡፡ መሐመድንም አምጥታ በሰዎቹ ፊት ራቁታቸውን አቁማ በትከሻዎቻቸው መሀል ያለውን ጠባሳ አሳየቻቸው፡፡ በዚህም ፍርሃት ስላደረባት መሐመድን ወደ እናቱ መልሳ ወሰደቻቸው፡፡ ለእናታቸው ለአሚና የሆነውን ሁሉ ነገረቻትና ተመልሳ ወደ ሀገሯ ሄደች፡፡

አሚናም በመካ ያሉ ዘመዶቻቸውን ሁሉ እየወሰደች አሳየቻቸው፡፡ ከእናቷም ዘመዶች ጋር ልታገናኛቸው ወደ መዲና ከተማ ስትሄድ መንገድ ላይ ሳለች «አብዋ» በሚባል ቦታ ድንገት ሞተች፡፡ (አብዋ በመካና በመዲና መካከል የምትገኝ ትንሽ መንደር ነበረች፡፡) በዚህ ጊዜ መሐመድ 7 ዓመት እንኳን አልሞላቸውም ነበር፡፡ አብራ ተጉዛ የነበረችው ሠራተኛዋ ባራካት መሐመድን ለአያታቸው ለአብድ አል-ሙታሊብ ወስዳ ሰጠቻቸው፡፡ አብድ አል-ሙታሊብ የካዕባ ቤተ-ጣኦት ዋና ጠባቂ ነበር፡፡ ከዚህ ሥራው የተሻለ ገቢ የሚያገኝ ቢሆንም ቤተሰቡ ብዙ ስለሆነ የእርሱም የኑሮ ሁኔታ ሌላ ሰው ለመጨመር የሚያስችል አልነበረም፡፡ በዚህም ምክንያት ቤተሰቦቹ መሐመድን እንዲሄዱላቸው ሁልጊዜ የተለያየ በደል ያደርሱባቸውና ጥላቻቸውም ይገልጹላቸው ነበር፡፡ መሐመድም በዘመዶቻቸው ላይ ቂም እያያዙና ጥላቻ እያሳደሩ መጡ፡፡ ነገሩን አብድ አል-ሙታሊብ ሲሰማ መሐመድን ከ3 ዓመት ቆይታ በኋላ ለመጀመሪያ ልጁ ለአቡ ጣሊብ ሰጣቸው፡፡ አቡ ጣሊብም በኋላ ላይ አባቱ ሲሞት በምትኩ የካዕባ ቤተ-ጣኦት ዋና ጠባቂ ሆነ፡፡ መሐመድም በዚያ በቤተ ጣኦቱ ውስጥ የነበረውን ሁኔታ እያዩ እንዲያድጉ ምቹ ሁኔታዎች ተፈጠሩላቸው፡፡

የአቡ ጣሊብም ቤተሰብ በርካታ ስለነበር ገቢውን ለማሳደግ ከቤተ-ጣኦቱ ዋና ጠባቂነት በተጓዳኝ ከካራቫን ነጋዴዎች ጋር ለንግድ ወደ ሶሪያ፣ የመን፣ ግብፅና ሌሎችም ሀገራት እየሄደ መነገድ ጀመረ፡፡ መሐመድም አጎታቸውን አብሮ ይዟቸው እንዲሄድ ብዙ ከለመኑት በኋላ ይዟቸው መሄድ ጀመረ፡፡ መሐመድም በሄዱበት ሀገር ሁሉ ያለውን ሃይማኖታዊና ባሕላዊ ሥርዓት ይመለከቱና ይጠይቁ ነበር፡፡ ስለ እምነት ጉዳይ ከእነዚህ ሀገራት ያገኙትን ነገር እርሳቸው የሚፈልጉትን እየመረጡ ይወስዱና በመሠረቱት እስልምና ውስጥም ይጠቀሙበት ነበር፡፡ ይህንን ወደፊት ራሱን የቻለ ርዕስ ስላለው ያን ጊዜ በደንብ እናየዋለን፡፡ ለአሁን ግን አንድ ምሳሌ እንይ፡- አንድ ጊዜ ወደ ሶሪያ ሲሄዱ ቀይ ባሕር አካባቢ ኢይላ (eyla) በምትባል ትንሽ መንደር ያድራሉ፡፡ ነዋሪዎቿ ጣኦት አምላኪዎች ነበሩና ማታ ስለ ጣኦታቸው ሲያወሩ መሐመድ

ይሰማሉ፡፡ «አምላካችን ዓለምን ወደተሻለች ሌላ ዓለም ይለውጣታል» ብለው ያምኑ ነበር፡፡ በዚያን ጊዜም አምላካችን ኃጢአት የሠሩ ትላልቆቹን ሰዎች ወደ አሳማነት፣ ትናንሾቹን ሰዎች ደግሞ ወደ ዝንጀሮነት ይለውጣቸዋል ብለው እንደሚያምኑ ለእነ መሐመድ ነግረዋቸዋል፡፡ መሐመድም ይህንን በቀጥታ ወስደው በሐዲሱ ላይ ተጠቅመውበታል፡፡ ማለትም አላህ አይሁዶችን ወደ ዝንጀሮነት እንደሚለውጣቸው ተናግሯል፡፡ (ጥቅሱን አስቀምጥ-----)

ሌላም አንድ ምሳሌ እንይ፡- መሐመድ ከመካ ነዋሪዎች ጋር ጦርነት ውስጥ በገቡ ሰዓት ራሳቸውን ለጦርነት ለማዘጋጀትና ድጋፍም ለማግኘት ሲሉ ከመካ 70 ማይልስ ርቃ ወደምትገኘው ጣይፍ ወደምትባል ትንሽ መንደር ሄደው ነበር፡፡ በዚያም የሚኖሩ ታቂፍ የሚባሉ ፓጋን የዐረብ ጎሳዎች «አል-ላት» የተባለችውን አንዲን የአላህን ሴት ልጅ ያመልኩ ነበር፡፡ «ከሞት በኋላ ከአላህ ዘንድ እየለመነች ሥጋዊ ፍለጎታችንን የምታሟላልን አማልክታችን ናት» ብለው ያምናሉ፡፡ መሐመድም ጦራቸውን አዘጋጅተው እስኪመለሱ ድረስ ከአንድ ወር በላይ በዚህች መንደር ቆይተው ነበርና ይህንን የጣኦት እምነት እርሳቸውም «በጂሃድ ተሳትፎ በአላህ መንገድ ለሚጋደል ለአንድ ሙስሊም ከሞተ በኋላ በጀነት ውስጥ 72 ደናግላን ለዝሙት ተግባር በሽልማት ይሰጡታል» በማለት በቀጥታ ወስደው በቁርአኑና በሐዲሱ ውስጥ ተጠቅመውበታል፡፡ (በጀነት ውስጥ ከ72 ደናግላን ጋር ስለሚደረገው ዝሙት በገጽ----ላይ ይመልከቱ)

በሌላም ወቅት እንዲሁ አንድ የተፈጸመ ሌላ ታሪክ አለ፡፡ ሰልማን አል-ፓርሲ/ psalman al-parsi/ የተባለ የፐርሺያ ጦር መሪ ከሮማኖች ጋር ጦርነት ገጥመው ካሸነፉ በኋላ ወደ ሀገሩ ሳይመለስ ወደ መዲና በመሄድ መካን ለመውረር ይሰናዱ የነበሩትን መሐመድን ተቀላቅሏል፡፡ ሁለቱም ቀደም ብለው በንግዱ እያሉ በደንብ ይተዋወቁ ነበር፡፡ ሰልማን አል-ፓርሲ የዞራስትሪያን እምነት ተከታይ ሲሆን ለመሐመድ ይህንን እምነቱን በሚገባ ገልጾ አስተምሯቸዋል፡፡ ሰልማን ከነጭራሹም ወደ ሀገሩ ፐርሺያ ሳይመለስ በዚሁ በመዲና በቋሚነት ኖሮ ነው የሞተው፡፡ ዛሬም ድረስ በቁርአን ውስጥ የዞራስትሪያንን የእምነት አስተሳሰቦችን በሰፊው ተጽፈው የምናገኘው ለዚህ ነው፡፡

መሐመድ ለንግድ ወደ ሶሪያና ግብፅ በተጓዙበት ወቅት ከብዙ ክርስቲያኖች ጋር ተገናኝተው ስለ እምነታቸውም ብዙ ሰምተዋል፡፡ ባሂራ (bahira) የተባለ አንድን መነኩሴ እንዳገኙና ከእርሱም ጋር በተደጋጋሚ ተገናኝተው ስለ ክርስትናው፣ ስለ ጣኦታት ከንቱነት፣ መሠረታዊ የክርስትና ትምህርትን፣ ስለ መንግስተ ሰማያትና ስለ ሲኦል ብዙ እንዳስተማራቸው የመሐመድን የግል የሕይወት ታሪካቸውን በስፋት የዘገቡት የታሪክ መዛግብት ይገልጻሉ፡፡ መሐመድ ከዚህም ሌላ ከዐረብኛው በተጨማሪ

የዕብራይስጥኛን ቋንቋ የሚናገር አዳስ (Adas) ከተባለ መነኩሴም ጋር ብዙጊዜ አውርተዋል፡፡ ይህንን ቁርአኑ 16፡103 ላይ እንዲህ በማለት ጠቅሶታል፡፡ *‹‹ለመሐመድ ቁርአንን የሚያስተምረው ሰው ብቻ ነው ማለታቸውን በእርግጥ እናውቃለን፤ የዚያ ወደርሱ የሚያስጠጉበት ሰው ቋንቋ ዐጀም ነው፤ (1) ይሀ ቁርአን ግን ግልጽ ዐረብኛ ቋንቋ ነው››* ይላል ቁርአኑ፡፡

(1) የቁርአኑ የግርጌ ማስታወሻ ላይ ‹‹ዐጀም ከዐረብኛ ሌላ የሆነ ቋንቋ ነው›› ተብሎ ነው የተጻፈው፡፡

እንመለስና ምልከታችንን እንቀጥል፡- መሐመድ በንግዱ ሥራ ታታሪና ጎበዝ መሆናቸውን ተመልክተው የካራቫን ነጋዴዎች እንደ ወኪል (commericial agent) አድርገው ሊቀጥሩአቸው ብለው ነበር ነገር ግን ማንበብና መጻፍ የማይችሉ በመሆኑ ሀሳባቸው ሳይሳካና ሳይቀጥሩአቸው ቀሩ፡፡ መሐመድ ማንበብና መጻፍ የማይችሉ መሆኑን በቁርአኑ ላይ ጠቅሶታል፡፡ (ጥቅሱን አስቀምጥ---------)መሐመድ ለንግድ ኢየሩሳሌም ድረስ ሄሰው በዚያ በሞሪያም ከፍታ ላይ የተሠራውን የሰሎምንን ቤተ መቅደስም ተመልክተዋል፡፡ በኋላ ላይ እምነታቸውን ሲመሠርቱ ይህን የሰሎምንን ቤተ መቅደስ እንደ ግብዓት ተጠቅመውበታል፡፡ ማለትም መሐመድ ሲያስተምሩ አንድ ሴት ፈረስ ጋልበው ወደ ሰባቱ ሰማያት ሲሄዱ ፈረሷ በዚህ በሰሎሞን ቤተ መቅደስ ላይ አርፋ ነበር፡፡ ሴቷ ፈረስ ክንፍ ያላት ሲሆን ስሟ ‹‹ቡራቅ›› ይባላል፡፡ የፊቷ ቅርጽ የቆንጆ ሴት ፊት ሲሆን ጅራቷ ደግሞ የፒኮክ ጅራት ነው፡፡ መሐመድ ለተከታዮቻቸው እምነታቸውን ሲያስተምሩ በዚህች ‹‹ቡራቅ›› የምትባል ፈረስ ጋልበው በእኩለ ሌሊት እዚህ ቤተ መቅደስ ላይ ወጥተው በዚያውም ወደ ሰባቱ ሰማያት እንደሄዱ አስተምረዋቸዋል፡፡ ዛሬ ሙስሊሞቹ ይህንን ቦታ ከቤተ ጣኦቱ ከካዕባና መሐመድ መዲና ላይ ከሠሩት ከነቢ መስጂድ /masjidul nabi/ ቀጥሎ 3ኛው ቅዱስ ቦታችን ነው የሚሉት ለዚህ ነው፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ አንድ ነገር ማንሳት ፈለግሁ፡፡ ነቢያቸው መሐመድ መዲና ላይ በግመላቸው ጠቋሚነት መስጂዱን ከሠሩ በኋላ ተከታዮቻቸውን እንዴት አድርገው መጥራት እንዳለባቸው ግራ ተጋብተው ነበር፡፡ የጦር መሪ እያደረጉ ያሰማሯቸው የነበሩትን ሰዎችም ሰብስበው አማከሯቸው፡፡ ‹‹እናንተን ለስግደት ስጠራ ጥሪ ማድረግ ያለብኝ እንዴት ነው? እንደ አይሁዶች የትራምፔት ድምጽ በማሰማት ልጥራ? ወይስ የመስጂዱ ጫፍ ላይ በመሆን እሳት በማንደድ ልጥራ?›› እያሉ ሲጠይቋቸው መልስ ከሰጧቸው ሰዎች መሀል ‹‹ለምን አንድ ሰው ከመስጂዱ አናት ላይ ወጥቶ አይጮህም?›› የሚለው የዛይድ ልጅ የሆነው የአብዱላህ ሀሳብ ነው ተቀባይነትን ያገኘው፡፡ ‹‹ታዲያ ጮሆ የሚጣራው ሰው ማን ይሁን?›› ሲባል ድምጹ በጣም ያምር

የነበረውና በባርነት ተይዞ የነበረው በኋላ ለጂሃድ ውጊያ ሲባል ነጻ የተለቀቀው የአቢሲኒያው ተወላጅ ቢላል ሀበሺ ተመራጭ ሆኖ የመጀመሪያው ጥሪ አድራጊ ሆነ፡፡ መደበኛ ሥራውም ይህ ብቻ ሆኖ ቀረ፡፡ መሐመድ በሞቱ ጊዜ በዚያ ራሳቸው በሠሩት መስጂድ ውስጥ ነው የተቀበሩት፡፡ ሙስሊሞች ዛሬ መዲናን «የነቢዩ ከተማ» /the city of the prophet/ በማለት ነው የሚጠሯት፡፡ መዲና ከተማ ላይ ዛሬም ሆነ ወደፊት አውሮፕላን ፈጽሞ አያርፍባትም ምክንያቱም አውሮፕላኑ የመስቀል ቅርፅ ስላለው ነው፡፡

የመሐመድን የሕይወት ጉዞ ወደማየቱ እንመለስና በ25 ዓመታቸው የመጀመሪያ ሚስታቸውን የ40 ዓመቷንና ሀብታሟን ከድጃን ካገቡ በኋላ ሕይወታቸው በአንድ ጊዜ ነበር የተለወጠው፡፡ ከድጃ አባቷ ኩዋሊድ ከቁራይሾች ወገን ሲሆን ቀደም ብላ ሁለት ጊዜ አግብታ ሁለቱም የሞቱባት ቢሆንም ሁለተኛው ባሏ ሀብታም ስለነበር ሀብቱን አውርሷታል፡፡ ኩዛይማ የሚባል የወንድሟ ልጅ ነው ከመሐመድ ጋር ያስተዋወቃት፡፡ ኩዛይማና መሐመድ ለአምልኮ በየጊዜው ወደ ካዕባ ቤተ-ጣኦት ሲሄዱና ሲገናኙ በዚያው ወዳጅነት መሠረቱ፡፡ መሐመድም አንድ ቀን የተሻለ ሥራ ቢያገኙ ደስተኛ እንደሚሆኑ ሲነግሩት ወስዶ ከከድጃ ጋር አገናኛቸው፡፡ እርሷም ንግዷን የሚቆጣጠርላት ጠንካራ ሰው ትፈልግ ስለነበርና መሐመድን ገና እንዳየቻቸው ስለወደደቻቸው እሳቸውን ለማግባት ጊዜ አልፈጀችም፡፡ አግብታውም የንግዱን ኃላፊነት ሙሉ በሙሉ ሰጠቻቸው እርሳቸውም በብቃት ተወጡት፣ ትርፋማ መሆንም ጀመሩ፡፡ ለንግድ በሄዱባቸው ሀገራት ሁሉ ያዩአቸውን የሕዝቦች ባሕልና እምነት በመካ ካለው የዘቀጠና ሞራላዊ እሳቤ ከሌላቸው ወገኖቻቸው ጋር ሲያነፃፅሩት ሀዘን ይሰማቸው ነበርና ይህንንም ለመለወጥ ተመኙ፡፡ ይህንንም ለማድረግ ሲነሡ ብዙ ነገሮችን ማሰባሰብ ጀመሩ፡፡ በዝሙትና በባዕድ አምልኮ የተጠመዱ ወገኖቻቸውን ለመለወጥ ካላቸው ፅኑ ፍላጎትና ምኞት የተነሳ በቅድሚያ ስለ ሌሎቹ እምነቶች ማወቅና መረጃም ማሰባሰብ ጀመሩ፡፡ የክርስትናውን ትምህርት ማለትም ቀደም ብሎ ያ ባሂራ (bahira) የተባለው መነኩሴ ያስተማራቸውን ትምህርት፣ ስለ ብሉይ ኪዳንና ሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት (ሙስሊሞቹ ዛሬ ተውራትና ኢንጂል ይሏቸዋል) ጠየቁ፡፡ ከላይ እንዳልነው ወገኖቻቸውን ለመለወጥ ካላቸው ፅኑ ፍላጎትና ምኞት የተነሳ ከወገኖቻቸው ባዕድ እምነት የተሻለ ነው ብለው ያሰቡትን ትምህርት አሰባሰቡ፡፡ ለምሳሌ በወቅቱ ተነስተው የነበሩ የመናፍቃንንም ትምህርት እንኳን ሳይቀር የዞራስትሪያንን ትምህርት፣ የታልሙድን ሥርዓትና የጁዲይዝምን ትምህርት በአጠቃላይ በሄዱባቸው ሀገራት ሁሉ የተሻለ ነው ያሉትን ትምህርትና ሥርዓት ሰብስበው ነው ወደ

እምነት ምሥረታ የገቡት፡፡ (ወደፊት የቁርአን ምንጮች ምን ምን እንደሆኑና ከየት ከየት ተሰብስበው በአንድ እንደተጠቃለሉ ኮፒ ከተደረጉበት ጋር አንድ ላይ በማያያዝ በዝርዝር እናየዋለን) አሁን ግን የተነሳሁበትን ሀሳብ ልቀጥልና መሐመድ በዚህ ሁኔታ ላይ እያሉ ነው «መልአኩ ጂብሪል ተገለጠልኝ» እያሉ ብቻውን ስንቃቸውን እያየዙ ወደ ሂራ (hira) ተራራ መሄድ የጀመሩት፡፡ በዚያም በሚያጋጥማቸው ነገር ልክ በልጅነታቸው እንዳደረገው «ጂብሪል መጥቶ ልቤን ቀዶ ውስጤን አጥቦ የነቢይነትን መንፈስ በድጋሚ ሞላኝ» በማለት መሐመድ እንደተናገሩ በሐዲሱ ላይ ተመዝግቧል፡፡ በኋላ ላይ ሰይጣን ይዞኛል በማለት በዚህም ባጋጠማቸው ነገር እጅግ ስለፈሩ ራሳቸውን ለማጥፋት ሁሉ ሞክረው መልአኩ እንደከለከላቸውና እንዳዳናቸው ራሳቸው መሐመድ በሐዲሱ ላይ ተናግረዋል፡፡ (ዝርዝሩን በገጽ---ላይ ተመልከት)

መሐመድ በዚህ መልኩ «ጂብሪል ነቢይ መሆኔን አብስሮኛል» ካሉ በኋላ ነው እምነታቸውን ለመመስረት የተነሡት፡፡ በቁርአኑ ላይም እምነታቸውን ለመመስረት የመጀመሪያ ሰው ሆነው እንደተነሡ ብዙ ቦታ ላይ ተጠቅሷል፡፡ ለምሳሌ ሱረቱ አል-አንዓም 6፡163 ላይ "እኔም የሙስሊሞች መጀመሪያ ነኝ" ብለው ተናግረዋል፡፡ በሌላም ቦታ በሱረቱ አል-ዙመር 39፡12 ላይ "የሙስሊሞችም መጀመሪያ እንድሆን ታዘዝኩ" ነው ያሉት፡፡ እናም በዚህ መልኩ በ610 ዓ.ም እምነታቸውን ለመመስረት ሲነሡና የመጀመሪያውን መገለጥ ከጂብሪል ተቀበልኩ ሲሉ ዕድሜአቸው 40 ነበር፡፡ «ነቢይ ሆንኩ» ብለው ለመነሣት ለምን ይህንን ዕድሜ መረጡት? ካልን ፓጋን ዐረቦቹ በባሕላቸው መሠረት አንድ ሰው በ40 ዘመኑ የበቃ የነቃ ይሆንና ከሁሉም የበላይ ከሆነው አምላክ ጋር የጠበቀ ግንኙነት ይኖረዋል ተብሎ ስለሚታመን ነው፡፡

መሐመድ እንደተናገሩት በሂራ ተራራ ዋሻ ውስጥ ሆነው ጂብሪል አረፋ እስኪደፍቃቸው ድረስ ልባቸውን በኃይል ሦስት ጊዜ እየተጫነ ቃሉን በልባቸው ላይ እንዳኖረላቸው ነው የተናገሩት፡፡ በዋሻው ውስጥ ለብዙ ጊዜ እየቆዩ ወደቤታቸው የሚመለሱት ሰውነታቸው በላብ ተዘፍቆ እንደነበር ሚስታቸው ከዲጃ ተናግራለች፡፡ እቤት እንደገቡም «በብርድ ልብስ ሸፍኑኝ» ይሏትና ይተኙ ነበር፡፡ በተኙም ሰዓት ጂብሪል ተገልጦላቸው «እስካሁን ተኝተሃል እንዴ? ተነሣና ስበክ እንጂ!» እያለ ከተኙበት እንደቀሰቀሳቸው ራሳቸው መሐመድ ተናግረዋል፡፡

ነቢያቸው መሐመድ ስብከታቸውን በጀመሩ ሰዓት ለባሏ ዓላማ መሳካት የራሷን አስተዋፅኦ ለማድረግና ሂደቱንም ለማስጀመር ስትል የመጀመሪያ የእምነታቸው ተከታይ የሆነችው ሚስታቸው ከድጃ ናት፡፡ እርሷም በ619 ዓ.ም በ65 ዓመቷ ነው የሞተችው፡፡ ከእርሷ ቀጥሎ የአጎቷ ልጅ የሆነው ዋራቅ ኢብን ኖፋል መካ ውስጥ የነበረው አስከፊ

ገፅታ እንዲለወጥ ካለው ፍላጎት የተነሣ የቅርብ ሰዎችን በማስተዋወቅ ሁኔታዎችን ያመቻቸ ቢሆንም አላመነበትም ነበርና የመሐመድን እምነት ሳይቀበል ነበር የሞተው፡፡ አሳዳጊ አጎታቸው አቡ ጣሊብም እንዲሁ ለመሐመድ ሁኔታዎችን ያመቻቸላቸውና በከፍተኛ ሁኔታ የረዳቸው ሰው ቢሆንም እምነታቸውን ግን ሳይቀበል ነበር የሞተው፡፡ እንዲሁም አምሩ ኢብን ሂሺም የተባለውን የመሐመድን አጎት ቁራይሾች «የእውቀት አባት» 'father of wisdom' እያሉ ይጠሩት ነበር ምክንያቱም ሚዛናዊ ውሳኔዎችን በመስጠትና በብልህ ፈራጅነቱ ያደንቁት ስለመነበር ነው፡፡ ሆኖም በተቃራኒው ይኸኛውም ብልሁ አጎታቸው መሐመድን ስላልተቀበላቸው እንዳውም መሐመድን «ተው ልጄ ይህ ነገር ይቅርብህ» እያለ ይመክራቸው ነበር፡፡ መሐመድ ግን ምክሩን አልቀበል ከማለታቸውም በላይ ብልህ አጎታቸው እምነታቸውን አልቀበል ስላለ በንዴት «አቡ ጃህል» የሚል ስያሜ አውጥተውለታል፡፡ ትርጉሙም «የሞኝ አባት» 'father of fully' ማለት ነው፡፡ በቁራይሾች ዘንድ «የእውቀት አባት» ለተባለው ስሙ የአፀፌታ ምላሽ መሆኑ ነው፡፡

ከመሐመድ ሚስት ቀጥለው የሰለሙት የመጀመሪያዎቹ አምስት ሰዎችም የከድጃና የእርሳቸው የቅርብ ዘመዶች ናቸው፡፡ ከእነዚህ ሰዎች ጋር ሆነው ለተከታታይ ሦስት ዓመታት ያህል በምሥጢር ቤት ለቤት ነበር ይሰብኩ የነበረው፡፡ ተከታዮቻቸውም እስከ 40 ከደረሱላቸው በኋላ ነው በግልጽና በድፍረት መስበክ የጀመሩት፡፡ መሐመድ በገሀድ መስበክ እንደጀመሩ የመካ ሰዎች በእርሳቸው ላይ የተለያየ አስተሳሰብ ነበራቸው፡፡ አንዳንዶቹ «ትምህርቶችህ ቀድሞ የምናውቃቸው ተረቶች እንጂ ሌላ አይደሉም» ሲሏቸው ሌሎቹ ደግሞ የአእምሮ ችግር እንጋጠማቸው በማሰብ «የአብድ አል-ሙታሊብ የልጅ ልጅ የሆነው ይህ ሰው አብዷል» ይሏቸው ነበር፡፡ ሌሎች ሰዎች ደግሞ «በሰይጣን ተይዟል» እያሉ ሲያዝኑላቸው በሌላ በኩል ደግሞ «አንዳች የማጂክ ኃይል» እንዲኖረው የሚፈልግ መተተኛ ዓይነት ሰው እንደሆኑ አድርገው ያስቧቸው ነበር፡፡ የባሰባቸው ደግሞ እሰብካለሁ ሲሉ የግመል ፈርስና ቆሻሻ እያነሱ ፊታቸው ላይ እየጣሉባቸው ትተዋቸው ይሄዱ ነበር፡፡ ምክንያቱም መሐመድ ሰዎችን ብቻ ሳይሆን ጂኒዎችንም (ሰይጣኖችን) ጭምር ወደ እስልምና ለማምጣት እንደተላኩ ይሰብኩ ስለነበር ነው፡፡ ይህም በቁርአኑ 46ኛውና 72ኛው ሱራ ላይ ተጠቅሷል፡፡ መሐመድ ከዚህ በኋላ ሰላማያዊ በሆነ መልኩ ማስተማሩ እንዳላዋጣቸው ሲያውቁ ነው ሰይፍን እንደዋነኛ የእምነታቸው ማስፋፊያ መሳሪያ አድርገው የተጠቀሙበት፡፡ (የመሐመድን አጠቃላይ የሕይወት ጉዞአቸውን መመልከታችንን በኋላ ስለምመለስበት ለአሁኑ ትንሽ ገታ ላድርገውና ከእምነት ምስረታቸው ጋር ብቻ ተያያዥ የሆኑ ነጥቦችን ላንሳ፡፡ ስለዚህ

ቀጥሎ የማነሳቸውን ሦስት ተያያዥ ርዕሶችን ልብ ብላችሁ እንድትመለከቱልኝ እፈልጋለሁ)

**መሐመድ ያደጉት የፓጋን ዐረቦችን ሃይማኖታዊና ባህላዊ ሥርዓታቸውን እየፈጸሙ ነበር፡-** ከመሐመድ መነሳት በፊት የነበሩ ፓጋን ዐረቦች የተያዩ ሃይማኖታዊ ክብረ በዓሎች ነበሯቸው፡፡ ለምሳሌ ከወሩ ውስጥ አንዱን ቀን የመጾም ልማድ ነበራቸው፤ ሲጾሙም ምግብና መጠጥ ይበላሉ፣ ይጠጣሉ ነገር ግን ምንም አያወሩም ነበር፡፡ አማልእክቶቻችን እንዳይጠፉ እያሉ ስለ ፀሐይና ጨረቃ መግባትና መውጣት በጾማቸው ወቅት ሦስት ጊዜ ይጸልያሉ፡፡ ሌላው ክብረ በዓላቸው የነበረው ነገር ወቅት እየጠበቁ አንድ ላይ ተሰብስበው ወደ ቤተ-ጣኦቱ ካዕባ የሃጂ ጎዞ (pilgrimage) ያደርጋሉ፡፡ የቤተ-ጣኦቱንም የካዕባን ግንብ ሰባት ጊዜ ይዞራሉ፡፡ በዚያ ለሚገኙትም በርካታ ጣኦቶቻቸው በስማቸው እንስሳትን መሥዋዕት አድርገው ያቀርባሉ፡፡ ሌላው ሥርዓታቸው ደግሞ ማርዋ እና ሳፋ የተባሉ ሁለት ከፍታ ቦታዎች አሉ፡፡ በእያንዳንዳቸው ላይ ሴትና ወንድ ጣኦታት ያሉ ሲሆን ከአንደኛው ወደ ሌላኛው ሮጠው በመሄድ በዓል የማክበር ልማድ ነበራቸው፡፡ የሁሉንም ወንዶች ጸጉር መላጨት የበዓላቸው የፍጻሜ ፕሮግራም ነበር፡፡ የመሐመድም ጎሳ አባላት የሆኑት ቁራይሾች በካዕባ ይካሄዱ የነበሩ ባዕድ አምልኮዎችን ይፈጽሙ ነበር፡፡ መሐመድም ይህንኑ ያሳዳጊዮቻቸውን እምነት ይዘው ድርጊቶቹን ሁሉ ተግባራዊ እያደረጉ ነው ያደጉት፡፡ እንዲያውም ያሳደጉአቸው አያታቸውና አጎታቸው የቤተ-ጣኦቱ ጠባቂዎች መሆናቸውን ቀደም ብለን አይተናል፡፡ እናም መሐመድ ከእነዚህ የፓጋን ዐረቦች ሃይማኖታዊ ሥርዓት ውስጥ አንዳንዶቹን አሁንም ላለው እስልምና መሠረት አድርገዋቸዋል፡፡ ለምሳሌ በእስልምናው አሁን እንደ ሃይማኖታዊ ሥርዓት ከሚደረጉት ነገሮች ውስጥ አንዱ ወደ መካ ሄዶ በፊት የጣኦታት ቤት የነበረውን ካዕባን እንዲሳለሙና እርሱንም ሰባት ጊዜ እንዲዞሩ ማድረግ ነው፡፡ ጾማቸውንም ቢሆን ከፓጋን ዐረቦች የጾም ሥርዓት በተወሰነ ምልኩ ነው ማሻሻያ ያደረጉበት፡፡ ሌላው መሐመድ ከፓጋን ዐረቦቹ ባዕድ አምልኮ ውስጥ በዋናነት የወረሱት ነገር እነርሱ ከሁሉም የበላይ አድርገው የሚያመልኩትን «አላህ» የሚባለውን የጣኦት ስም ነው፡፡ ይህንን ቀጥሎ ባለው ርዕስ ላይ በደንብ እናየዋለን፡፡

**መሐመድ አምላካቸውን ፈጠሩ፡-** ከመሐመድም መነሳት በፊት በቅድመ እስልምና ዘመን በአረቢያ ምድር በካዕባ ውስጥ ጣኦታትን ያመልኩ የነበሩ ፓጋን አረቦችም «አላህ» የሚለውን ስም ለጣኦታቸው የግል መጠሪያ ስም አድርገው ይጠቀሙበት እንደነበር ብዙ ማስረጃዎች አሉ፡፡ ፓጋን ዐረቦቹ በካዕባ ካሉ አማልእክቶቻቸው መሀል

የበላይ አድርገው የሚያስቡትን አምላክቸውን «አል-ረሂም» ማለትም ሩህሩህ የሆነ ጌታ ብለው ይጠሩታል፡፡ እንዲሁም «አል-ረህማን-አን» ማለትም መህሪው ጌታ በሚባል ሌላ ስያሜም ይጠሩታል፡፡ «አላህ» በሚለው ስያሜ የሚታወቀው ጣኦት በእነዚህ ስሞቹም ይጠራ ነበር፡፡ በአሁኑም እስልምና «ለአላህ» 99 የተለያዩ ስሞች አሉት፡፡ ቁርአኑ በሱረቱ አል-ኢስራእ 17፡110 ላይ *"አላህን ጥሩ፤ ወይም አልረህማህንን ጥሩ፤ ከሁለቱ ማንኛውንም ብትጠሩ መልካም ነው፤ ለእርሱ መልካም ስሞች አሉትና በላቸው"* ተብሎ ነው የተጻፈው፡፡ ከመሐመድ መነሳት በፊት ፓጋኖቹ በወቅቱ በካዕባ ካሉ አማልእክቶቻቸው መሀል የበላይ አድርገው የሚያስቡትንና አል-ረሂም (ሩህሩህ)፣ አል-ረህማን (መህሪው)፣ አላህ... እያሉ በተለያየ ስም የሚጠሩትን አምላካቸውን የሰው ልጆች ሁሉ ባሕርያት እንዳሉት ያስቡ ነበር፡፡ እርሱ ሕይወት እንደሰጣቸውና በይቅርታም እንደሚያኖራቸው ያምናሉ፡፡ የሚታይና የሚዳሰስ አምላክ እንደሆነም ስለሚያስቡ ሀውልት አቁመውለት ነበር፡፡ ሦስት ልጆችም እንዳሉት ስለሚታሰብ በካዕባ ውስጥ ሀውልቱ ቆሞለት የነበረው ከሦስት ልጆቹ ጋር ነበር፡፡

መሐመድም በተነሡ ጊዜ ይህንን የካዕባ የ360 ጣኦታት አምልኮ ወደ አንድ አምልኮ ሥርዓት ነው የለወጡት፡፡ የእርሳቸው ጎሳ አባላት የሆኑት ቁራይሾች ከእነዚህ ጣኦታት ውስጥ የሚያመልኩትንና ከሁሉም የበላይ ተድርጎ የሚታሰበውን አላህን «የሁሉም የበላይ ስለሆነ እርሱን አምልኩ» በማለት ለሕዝቡ መስበክ ጀመሩ፡፡ ይህንንም ጥንታዊ የሆኑት የታሪክ መዛግብት ብቻም ሳይሆኑ ቁርአኑም ራሱ ያረጋግጥልናል፡፡ አራት ቁጥሮች ብቻ ያሉት 106ኛው ምዕራፍ እንዲህ ይላል፡፡ *«ቁረይሽን ለማላመድ ባለዝሆኖቹን አጠፋ፡፡ የብርድንና የበጋን ወራት ጉዞ ሊያላምዳቸው ይህንን ሠራ፡፡ ስለዚህ የዚህን ቤት የካዕባን ጌታ ይገዙ፡፡ ያንን ከረኃብ ያበላቸውን ከፍርሃትም ያረካቸውን ጌታ ይገዙ»* በማለት ቁርአኑ እንደመሰከረው መሐመድ እነዚያን 360 ጣኦታት አጥፍተው ነው በመጨረሻ አንዱንና የእርሳቸው ወገን ያመልኩት የነበረውን ብቻ አስቀርተው ነው ለአንድ አምላክ ተገዙ ያሏቸው፡፡ መሐመድ በተነሡና መካ ከተማን በኃይል በተቆጣጠረ ሰዓት የካዕባን 360 ጣኦታት ደምስሰው ሲያጠፉ ከሁሉም የበላይ ነው ተብሎ የሚታሰበውን «አላህ» የሚባለውን ጣኦት ግን ትተውታል፡፡ ይህም በሐዲሱ ላይ ተጠቅሷል፡፡ ቡኻሪ ሐዲስ ላይ እንዲህ ተብሎ ነው የተጻፈው፡- "ነቢዩ መካን በተቆጣጠራት ሰዓት ወደ መካ ሲገባ 360 ጣኦታት በካዕባ ዙሪያ ነበሩ፤ ነቢዩም በረጅም ዱላ ይመታቸው ጀመር፡፡" "When the Prophet entered Mecca on the day of the Conquest, there were 360 idols around the Ka'aba. The Prophet started striking them with a stick." (Sahih Bukhari: 5:59:583) ለመሆኑ

መሐመድ ሁሉንም 360 የካዕባ ጣኦታን በዱላ ጨፍጭፈው ሲያጠፉ ለምን «አላህ» የሚባለውንስ ጣኦት አላጠፉትም? ቢባል ስለ ሁለት ምክንያት ነው፡፡ አንድም የመሐመድ ነገድ የነበሩት የቁራይሽ ነገዶችና ቤተሰቦቻቸውና ራሳቸው መሐመድም ጭምር ያመልኩበት የነበረ የጣኦት ስም ስለሆነ ነው፡፡ 2ኛው ምክንያት ደግሞ ፓጋን ዐረቦች በካዕባ ውስጥ ያሉ ጣኦታትን ሁሉ ሲያመልኩ «አላህ» የሚባለውን ከሁሉም የበላይ አድርገው ያስቡ ስለነበር «የምታውቁትን፣ የምታመልኩትንና ከሁሉም የበላይ የሆነውን አምላክ አከበርኩላችሁ» ብለው ታማኝነትና ተቀባይነት ለማግኘት ነው፡፡
አሁን ደግሞ ሦስቱ የአላህ ልጆች የተባሉትን ጣኦታት በደንብ እንያቸው፡፡ በፓጋን ዐረቦቹ ዘንድ ሦስቱ የአላህ ልጆች የሚባሉት በስም አል-ላት፣ አል-ዑዛና መናት እንደሚባሉ በቁርአኑ ሱረቱ አል-ነጅም 53፡19 ላይ በግልጽ ተቀምጧል፡፡ *«አል-ላትንና አል-ዑዛን አያችሁን? ሦስተኛይቱንም አነስተኛዋን መናትን (1) አያችሁን? የምትገዟቸው ኃይል አላቸውን? ለእናንተ ወንድ ለእርሱም ሴት ልጅ ይኖራልን? ይህቺ ያን ጊዜ አድላዊ ክፍያ ናት፡፡ እነርሱ፣ እናንተና አባቶቻችሁ አማልክት ብላችሁ የጠራችኋቸው ስሞች ብቻ እንጂ ምንም አይደሉም፡፡ አላህ በእርሷ መገዛት ምንም ማስረጃ አላወረደም»* ይላል ቁርአኑ፡፡ እንዲሁም በቁርአኑ ላይ በሌላ ቦታ «ለአል-ረህማን ልጅ የለውም እንጂ ቢኖረው እኔ ለልጁ የተገዢዎቹ መጀመሪያ ነኝ በላቸው» ተብሎ ነው የተጻፈው፡፡ 43፡81
*(1)* ተብሎ በተቀመጠው የግርጌ ማስታወሻ ላይ "እነርዚህ ሦስቱ የጣዖታት ስሞች ናቸው" ተብሎ ተጽፏል፡፡
የመካ ሕዝቦች መሐመድን መጀመሪያ አካባቢ የጣኦቶቻቸውን ስም እየጠሩላቸው ስላስተማሩ በደስታ ይሰሟቸው ነበር፡፡ መጀመሪያ ላይ እንደተነሡ ስለ ጣኦቶቻቸውም ጥሩና መልካም ነገሮችን መናገር ቢጀምሩም ቆይተው ግን «እነርሱ አያስፈልጉም ዋናውንና አምሳያ የሌለውን አላህን ብቻ አምልኩ» እያሉ መስበክ ሲጀምሩ በተቃውሞ ተነሱባቸው፡፡እንዲያውም እንደነ አል-ዋሊድ ቢ.አል-ሙግሂራ ዓይነት ያሉ ሽማግሌዎች ቆሻሻና የግመል ፈርስ በመሐመድ ፊት ላይ ይደፉባቸው ጀመር፡፡ ከዚያ በኋላ የመካ ሕዝቦች በመሐመድ ላይ ያላቸውን ተቃውሞ አጠናከረውባቸዋል፡፡ ትምህርታቸውንም «እኛ ቀድሞ የምናውቃቸው ተረቶች ናቸው» ይሏቸው እንደነበር ቀደም ብለን በገጽ---- ላይ አይተናል፡፡ በቁርአኑ 109፡2 ላይ *«እናንተ ከሓዲዮች ሆይ ያንን የምትገዙትን ጣኦት አሁን አልገዛም፡፡ እናንተም እኔ የምገዛውን አምላክ አሁን ተገዢዎች አይደላችሁም፣ ወደፊትም ተገዢዎች አይደላችሁም»* በማለት ነው መሐመድ ይህንኑ ተቀባይነት ያጡበትን ክስተት የገለጹት፡፡ መሐመድም ወገኖቹ የመካ ነዋሪዎች እንዳልተቀበሏቸው

ሲያውቁ ወደ እናታቸው ትውልድ ሀገር መዲና በ622 ዓ.ም ተሰደዱና በዚያ ኃይል አሰባስበው በመምጣት ነው መካን የተቆጣጠሯት፡፡

የፓጋን ዐረቦቹ ከሁሉ በላይ የሆነውና የዋናው አምላካቸው የፅንሰ ሀሳቡ መነሻ ጨረቃና ፀሐይ ናቸው፡፡ ቁርአኑ 91፡1 ላይ ገና ሲጀምር «በፀሐይና በጨረቃ እምላለሁ» ይላል፡፡ በጣም አስገራሚ በሆነ መልኩ ብዙዎቹ የቁርአን ምዕራፎች የሚጀምሩት በዚህ «በፀሐይና በጨረቃ እምላለሁ» በሚለው ቃለ መሀላ ነው፡፡ እንደ ፓጋን አረቦቹ እምነት የፀሐይ አምላክ ሴት አምላክ ስትሆን የጨረቃ አምላክ ደግሞ የወንድ አምላክ ነው፡፡ «አላህ» የሚለው ስም ደግሞ የጨረቃው አምላክ የግል መጠሪያ ስሙ ነበር፡፡ ስለዚህ የፀሐይና የጨረቃ አምለክ ማለትም ሴቷና ወንዱ ተጋብተው ሦስት ሴት ልጆችን ማለትም አል-ላትን፣ አል-ዑዛንና መናትን ወለዱ፡፡ ይህ ግልጽ የሆነ የፓጋን ዐረቦች እምነት ነው፡፡ ለእያንዳንዳቸውም ቤተ መቅደስ ሰርተው ጣኦት አቁመውላቸው ነበር፡፡ ይህ ነው እንግዲህ መሐመድን በቁርአኑ ላይ “አላህ ሴት ልጅ የለውም” ብለው እንዲናገሩ ያደረጋቸው ነገር፡፡



The moon-god from all four sides. Note the cresent moon carved on his chest.

ከላይ ያለው ስዕል በአራቱም አቅጣጫ የሚያሳየው የወንዱን የጨረቃ አምላክ ሃውልት ነው፡፡ በደረቱ ላይ የጨረቃዋ ምስል መኖሩን አስተውሉ፡፡ ቀጥሎ ያለው ስዕል ደግሞ ከአላህ ሴት ልጆች ውስጥ አንደኛዋ የአል-ኡዛ /Al-Uzza/ እና የቤተ መቅደሷ ሃውልት ነው፡፡



አል-ኡዛ /Al-Uzza/ ማለት በቁራይሾች ዘንድ ከሌሎቹ የአላህ ልጆች በተለየ ሁኔታ ከዋናው አምላካችን ታስታርቀናለች ተብሎ የሚታመንባት ነበረች፡፡ ራሳቸው መሐመድ ከልጅነታቸው ጀምሮ ከጎሳቸው ጋር ሆነው በለየ ሁኔታ ያለምኩባትና መሥዋዕት ይሠውላት ነበር፡፡ እንዳውም ከመሐመድ አጎቶች ውስጥ አንደኛውና አሳዳጊው በእርሷ ስም የተሰየመ ነበር፡፡ ሙሉ ስሙ አብድ አል-ኡዛ (Abd al-uzza) ሲባል በኋላ ነው በቅጽል ስሙ አቡ ላሀብ እየተባለ መጠራት የጀመረው፡፡

«የፀሐይና የጨረቃ አምለክ (ሴቷና ወንዱ) ተጋብተው ሦስት ሴት ልጆችን ወለዱ» የሚለው ግልጽ የሆነ የፓጋን ዐረቦች እምነት በመሐመድ ላይ ምን ያህል ከፍተኛ ተፅዕኖ እንዳሳደረባቸው የሚታወቀው ይህንን አስከፊ የሆነ የፓጋኖችን እምነት ወደ ክርስትናውም ሊያመጣው መሞከሩ ነው፡፡ መሐመድም ሆነ ቁርአኑ ወይም አሁንም ያሉት ሙስሊም መምህራን በክርስትናው «ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ ነው» የሚለውን አስተምህሮ እጅግ አሳዛኝና አስቂኝ በሆነ መልኩ ነው የሚረዱትና የሚተረጉሙት፡፡ ማለትም «የእግዚአብሔር ልጅ አለው» ሲባል በሰው ሰውኛ ግብር እግዚአብሔር ሚስት አግብቶ ግብረ ሥጋ ግንኙነት አድርጎ የወለደው መስሎ ነው የሚታያቸው፡፡ “ለእርሱ (ለአላህ) ሚስት የሌለችው ሲሆን እንዴት ለእርሱ ልጅ ይኖረዋል” /ሱረቱ አል-አንዓም 6፡101/ በማለት ቁርአኑ ይሞግታል፡፡ በሌላም ቦታ ቁርአኑ “እነሆ የጌታችን ክብር ላቀ፤ ሚስትንም ልጅንም አልያዘም” /ሱረቱ አል-ጂን 71፡3/ በማለት የእግዚአብሔርን የልጅነት ምሥጢር በግብረ ሥጋ ግንኙነት እንደተገኘ አድርጎ ሲያቀርበው ትንሽ እንኳ ትዝብት ውስጥ እገባለሁ ብሎ አለማፈሩ እጅግ አስገራሚ ነው በእውነት፡፡ እንደ እውነቱ ከሆነ እንኳን ክርስቲያኖቹ ሰይጣንም እንደዚያ ብሎ አያምንም፡፡ መሐመድም ሆኑ አሁን ያሉት ተከታዮቻቸው ቢያንስ ክርስቲያኖቹ ምን ብለው ነው የሚያምኑት? የሚለውን ነገር እንኳን አጣርተው አለማወቃቸው ምን ያህል ትዝብት ውስጥ እንደጣላቸው ተመለከቱ!

**አላህ-የሚለው የቃሉ ትርጉም፡-** ከላይ እንዳየነው ቁርአኑ በሱረቱ አል-ኢስራእ 17፡110 ላይ "አላህን ጥሩ፤ ወይም አልረሕማህንን ጥሩ፤ ከሁለቱ ማንኛውንም ብትጠሩ መልካም ነው፤ *ለእርሱ መልካም ስሞች* አሉትና በላቸው" ተብሎ ነው የተጻፈው፡፡ "Say, Call Him Allah or call Him Ar-Rahman; whatever the name you call Him, all His names are beautiful." (Qur'an 17:110) በዚህ ጥቅስም ሆነ በሌሎች የቁርአን ጥቅሶች ላይ "አላህ" የሚለው ቃል በራሱ «የመጠሪያ ስም» ብቻ መሆኑን ነው የሚያለመክተው፡፡ ቁርአኑ በግልጽ «አላህን ወይም አልረሕማህንን ጥሩ... ለእርሱ መልካም ስሞች አሉት» ካለ "አላህ" የሚለው ቃል በራሱ «አላህ» በመባል የሚጠራ የአንድ አካል የመጠሪያ ስም ብቻ መሆኑን ነው እንጂ የአምላክነቱ ወይም የባሕርይው መገለጫ ስያሜ አይደለም፡፡

በእስልምናው አንድ ሰው መጀመሪያ ሙስሊም መሆኑ የሚታወቀው በዐረብኛ "አላሁ አከበር! ላ ኢላሃ ኢል አላህ መሐመድ ራሱል አላህ" ብሎ በሚያሰማው የምስክርነት ቃል ነው፡፡ በእነርሱ ሸሀዳ (ምስክርነት) ይሉታል፡፡ ትርጉሙም "አላህ ትልቅ ነው፤ ከአላህ በቀርም ሌላ አምላክ የለም፤ መሐመድም መልእክተኛው ነው" ማለት ነው፡፡ "ላ ኢላሃ ኢል አላህ" የምትለዋን ቃል በደንብ ማየት ስለፈለኩ ነው ይህን ያነሳሁት፡፡ "ላ ኢላሃ ኢል አላህ" /La ilaha illAllah/ የሚለው የአረብኛ ቃል ትርጓሜው "ከአላህ በቀር ሌላ አምላክ የለም" የሚል ትርጓሜን የሚሰጥ ይመስላል፡፡ ግን አይደለም፡፡ ይህንን ቀጥሎ ያለውን ትርጓሜ ልብ ብላችሁ ተመልከቱ፡- La [no] ilaha [god] ill [except] Allah [Allah]. ይህም "አላህ" የሚለው ቃል በራሱ የመጠሪያ ስም ብቻ መሆኑን ነው የሚያመለክተው እንጂ የአምላክነቱ ወይም የባሕርይው መገለጫ ስያሜ አለመሆኑን አይተናል፡፡ ይህንንም የእንግሊዝኛው ፊደል የበለጠ ግልጽ ያደርግልናል፡፡ በእንግሊዝኛ አምላክ የሚለውን ቃል ለመግለጽ በትልቁ ፊደል በ"G" ይጀምራል፡፡ በትንሹ ፊደል በ"g" ከጀመረ ግን የጣኦትን ስም ለመግለጽ ነው የሚያገለግለው፡፡ ስለዚህ የአረብኛው "ilaha" የሚለው ቃል የሚወክለው «God» የሚለውን ሳይሆን «god» የሚለውን ቃል ነው፡፡ ይህ "ilaha" የሚለው ቃል የተጠቀሰው ከመሐመድ መነሳት በፊት በካዕባ ይመለኩ የነበሩ ጣኦታን ለመግለጽ ነው፡፡ ስለዚህ "ላ ኢላሃ ኢል አላህ" /La ilaha illAllah/ ለሚለው የዐረብኛ ቃል "ከአላህ በቀር ሌላ አምላክ የለም" የሚለው ትርጉም ቀጥተኛና ተዛማጅ የሆነ ትርጓሜው አይደለም፡፡ የአረብኛው "ilaha" የሚለው ቃል ትርጓሜው ጣኦት /god/ ማለት ሲሆን «አላህ» የሚለው ቃል ደግሞ የግል መጠሪያ ስሙ ነው፡፡ ስለዚህ እንደ ዐረብኛው ቃል መነሻ ሀሳብና አገባብ ከሆነ "ላ ኢላሃ ኢል አላህ" La [no] ilaha [god] ill [except] Allah [Allah] የሚለው የዐረብኛ ቃል

ትክክለኛ አገባቡ “ካሉት ጣኦታት ውስጥ አላህ ብቻ እንጂ ሌሎች ጣኦታት ሊመለኩ አይገባም” የሚል ነው፡፡ የቃሉን አውዳዊ አገባቡ /contextual meaning/ በትክክል የሚያሳየን ይህንን ብቻ ነው፡፡

መሐመድ የካዕባን ባዕድ እምነት አጥፍተው «አላህን» ብቻ ለይተው ለሕዝቡ ያስተዋወቁበትን መንገድ እንዲህ ባለ መልኩ ካየን አሁን ደግሞ «የመሐመድን አጠቃላይ የሕይወት ጉዞውን መመልከታችንን ለጊዜው ትንሽ ገታ ላድርገውና በኋላ ስለምእመለስበታለሁ» ወዳልኩት ሀሳብ ልመለስ፡፡ መሐመድ በ5ኛ ዓመት ስብከታቸው ተከታዮቻቸው እስከ 70 በደረሱ ጊዜ ነው ፓጋን ዐረቦችን ፊት ለፊት በግልጽ መዋጋት የጀመሩት፡፡ ሰላማያዊ በሆነ መልኩ ማስተማሩ እንዳላዋጣቸው ሲያውቁ ሰይፍን እንደዋነኛ የእምነታቸው ማስፋፊያ መሳሪያ አድርገው ተጠቀሙበት፡፡ መጀመሪያ ያደረጉት ነገር የቅርብ ዘመዶቻቸውን ከመካ ከተማ አስወጥተው ጥገኝነት የሚያገኙበትን ሀገር ሲያስብ የአቢሲኒያው (የኢትዮጵያው) ንጉሥ ማንኛውንም እንግዳ የሚያከብር እንዲሁም ሃይማኖቱና ምግባሩ ነቅ የሌለበት ደግ ንጉሥ መሆኑን ቀደም ብለው ሰምተው ነበርና ዘመዶቻቸውን «እዚያ ሂዱ ሰላም ታገኛላችሁ» በማለት ወደ አቢሲኒያ ላኳቸው፡፡ ይህም የሆነው በ615 ዓ.ም ሲሆን የላኳቸውም ሴት ልጃቸውን ሩቂያን ጨምሮ ባሏን ኡትማን ኢብን አፋንን የሌሎች 10 ሰዎች መሪ አድርገው ነው፡፡ ኢትዮጵያ እንደደረሱም በመካ ያሉ ከመሐመድ ጋር ጦርነት ውስጥ የገቡት ቁራይሾች ተከታትለዋቸው የመጡ ቢሆንም ንጉሡ አሳልፎ ሳይሰጣቸው ቀርቷል፡፡

መሐመድ ከዚህ በኋላ እነዚህን 70 የመጀመሪያ ተከታዮቻቸውን በጥቅማ ጥቅም መያዝና ለተቃውሞም ብቁ ከማድረግ አኳያ እንደመፍትሄ የወሰዱት እርምጃ የመካ ካራቫን ነጋዴዎች ወደ ተለያዩ ሀገራት ለንግድ ሲሄዱ እነርሱን ጠብቆ መዝረፍን ነበር፡፡ እንዳሰቡትም ተግባራዊ አደረጉትና መሐመድ ራሳቸውንና ተከታዮቻቸውን በጦር መዝረፍንና ጂሃድ ማወጅን አስጀመሯቸው፡፡ በድርጊቱም የሚገኘውን ውጤት ለመጀመሪያ ጊዜ አጣጣሙ፡፡ ተከታዮቻቸውም በመጀመሪያዋ ዘረፋ ባገኙዋት ንብረት ተነሳሽነታቸውም ሆነ ቁጥራቸው በጣም እየጨመረ መጣ፡፡ (ከሃይማኖታቸው ማስፋፋት ጎን ለጎን የተለያዩ ዝርፊያዎችን እንዴት አድርገው ይፈጽሙ እንደነበር ዝርዝር ሁኔታዎችን በገጽ------ላይ «መሐመድ የፈጸሚቸው የሽብር ጥቃቶች» የሚለውን ርዕስ ይመልከቱ)

መሐመድ በ622 ዓ.ም ተከታዮቻቸውን ይዘው ከመካ ወደ መዲና ተሰደዱ፡፡ ሙስሊሞች ዘመናቸውን አንድ ብለው የሚቆጥሩት ከዚህ ዓመት ጀምሮ ነው፡፡ መዲና ከመካ ከተማ በስተሰሜን 250 ማይልስ ርቀት ላይ የምትገኝ ከተማ ስትሆን በወቅቱ

በዋናነት 5 የተላያዩ ጎሳዎች ይኖሩባት ነበር፡፡ እነዚህም ባኑ ቃይኑቃ፣ ባኑ ናድህር፣ ባኑ ቁራይዛ የተባሉት ሦስቱ የአይሁድ ጎሳ አባላት ናቸው፡፡ የተቀሩት ሁለቱ ጎሳዎች ካዝራጅና አውስ የተባሉ ፓጋኖች ሲሆኑ እነዚህ መሐመድን ወዲያው ነው የተቀላቀሏቸው፡፡ ምክንያቱም የአይሁዶቹ ጎሳዎች የተለያዩ የዕደ ጥበብ ሥራዎችን በመሥራትና ያትሪብ በሚባለው ቦታ ላይ የግብርና ውጤቶችን በከፍተኛ ሁኔታ በመጠቀም የተሻለ የኑሮ ደረጃ ስለነበራቸው፣ የእነርሱንም ልጆች ብቻ ለይተው የሚያስተምሩበትም ት/ቤት ስለነበራቸው እነርሱንም ለማጥቃት ሲሉ ፓጋኖቹ መሐመድን በፍጥነት ነበር የተቀበሏቸው፡፡ መሐመድም ጂሃድ አውጀውባቸው ያሰለሙትን አስልመው እምቢ ያላቸውን ሰይፈው ንብረት፣ ሴቶችና ሕጻናቶቻቸውን በምርኮ ወስደው ለራሳቸውና ለተከታዮቻቸው አከፋፍለዋቸዋል፡፡ ከሁሉም አስከፊ የነበረውና እኔም ብዙ ቦታ ላይ የጠቀስኩት 900 የሚሆኑ የባኑ ቁራይዛዎች ጅምላ ጭፍጨፋ ነው፡፡ አልሳካላቸው አለ እንጂ መሐመድ እነዚህን በመዲና የሚኖሩትን የአይሁድ ጎሳዎች መጀመሪያ አስተምረው ለማሳመን ብዙ ሞክረው ነበር፡፡ ለማሳመንም ሲሉ አንዳንድ የአይሁዶችን ሥርዓተ እምነቶች በመሠረቱት አዲሱ እምነታቸው ውስጥ እንዲካተቱ አድርገውላቸው ነበር፡፡ ለምሳሌ፡- ለአብርሃም ብቻ የተሰጠውን የግዝረትን ሥርዓትና ትእዛዝ ሙስሊሞችም እንዲተገብሩት አዘዙ፡፡ ሌላው እነ መሐመድ በመካ እያሉ የሚሰግዱት ወደ ቤተ-ጣኦቱ ወደ ካዕባ ዞረው ነበር፡፡ አሁን ግን መሐመድ ልክ እንደ አይሁዶቹ ወደ ኢየሩሳሌም ዞረው እንዲሰግዱ አዘዙ፡፡ እነዚህንና ሌሎችም ሥርዓተ እምነታቸውን ወደ እስልምናው በመውሰድ አንድ ሊያደርጓቸው ቢሞክሩም ከሁለቱ ፓጋን ዐረቦች በቀር አይሁዶቹ አልቀበል ስላሏቸው እነርሱ ላይ ጂሃድ አውጀው ድል ካደረጓቸው በኋላ የጸሎትና ስግደት አቅጣጫውንም መልሰው ወደነበረበት ወደ መካ እንዲሆን አድርገውታል፡፡ ቅዳሜ የነበረውን የአይሁድ የሰንበት በዓል መጀመሪያ የተቀበሉት ቢሆንም በጦርነት ካሸነፏቸው በኋላ ግን ‹‹ቅዳሜ ሳይሆን አርብ የሙስሊሞች ቅዱስ ቀን ይሁን›› ብለው ነቢያቸው አወጁ፡፡ ይህም ‹‹መሲሁ ኢየሱስን በዚህ ዕለት አይሁድ ሰቀሉት›› ብለው መከራውን እያሰቡ የሚውሉትን ሌሎች ክርስቲያኖችን ለመቃወም ሲሉ ያደረጉት ነገር ነው እንጂ መሐመድ ዕለተ አርብን ‹‹ልዩና ቅዱስ ቀን›› አድርገው እንዲከበሩ የሚያዙበት ሌላ ምንም ምክንያት አልነበራቸውም፡፡ በሐዲሱም ላይ በግልጽ ተጽፎ እንደምናገኘው ከአይሁድና ከክርስቲያኖች ተቃራኒ የሆኑ ነገሮችን ማድረግ እንዳለባቸው መሐመድ ለተከታዮቻቸው አስተምረዋቸዋል፡፡ ለምሳሌ፡- አይሁድና ክርስቲያኖች ጸጉራቸውን ቀለም ስለማይቀቡ በመሐመድ ትእዛዝ መሠረት ሙስሊሞች ከክርስቲያኖቹ

በተቃራኒው ጸጉራቸውን ቀለም መቀባት እንዳለባቸው ተነግሯቸዋል፡፡ ይህንንም ቀደም ብለን በገጽ ----ላይ አይተነዋል፡፡ “The Prophet said, "Jews and Christians do not dye their hair so you should do the opposite of what they do.” Sahih Bukhari 7:72:786. አሁን ደግሞ እስቲ መሐመድ «ከሰማይ ወረደልኝ» ስላሉት ቁርአን አንዳንድ ነጥቦችን ላንሳላችሁ፡፡ ከዚህ ርዕስ ልጀምር፡-

<u>አብደላህ ኢብን ሳድ ኢብን አቢ ሳርህ ማን ነው</u>? (Abd Allah Ibn Sa`d Ibn Abi Sarh and verse 6:93)

በአማኞቹ እንደሚታሰበው ከሆነ ቁርአኑ በቀጥታ ከሰማይ በአላህ ዘንድ ካለው መዝገብ ተቀድቶ በጂብሪል በኩል ለመሐመድ የመጣላቸው መገለጥ ነው፡፡ ይህም በ23 ዓመታት ውስጥ በየጊዜው ነው ለመሐመድ ሲገለጥላቸው የነበረው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ራሱ ቁርአኑ እንደሚያረጋግጠው መሐመድ ምንም ስላልተማሩ ማንበብና መጻፍ እንኳን አይችሉም ነበር፡፡ (ምንጭ------) እነዚህንና ሌሎችንም ነገሮች ታሳቢ በማድረግ ሙስሊሞች ሊሰሟቸውና ሊጠየቁ የማይፈልጓቸውን እጅግ በርካታ ጥያቄዎችን ማንሳት እንችላለን፡፡

መሐመድም ማንበብና መጻፍ ካልቻሉ ታዲያ እንዴት በየጊዜው የመጡ እነዚያን የ23 ዓመታት መገለጦች ዛሬ በአንድ ላይ ተጠርዘው በቁርአን መልክ ልናገኛቸው ቻልን? መሐመድ ከሞቱ በኋላ ነውና የተሰበሰቡት በአንድ ላይ ጠርዞ ያዘጋጃቸውስ ማን ነው? ያሰባሰቡ ሂደትስ እንዴትና ምን ይመስል ነበር? መሐመድ ራሳቸው «ተገለጠልኝ» ያሉበት መንገድስ አግባብ ነው? ማለትም የሆነ አንድ አካል (መሐመድ መልአኩ ጂብሪል ነው ያሉት) እርሳቸውን ወደ ሂራ ተራራ ጫፍ ላይ ወስዶ በአፍ በአፍጫቸው አረፋ እስኪደፍቁ ድረስ መሬት ላይ ጥሎ እያሰቃየ መገለጦቹን እንደሰጣቸው ሐዲሱ ይናገራል፡፡ (ዝርዝሩን በገጽ-----ላይ በስፋት ስላየነው ከዚያ ላይ ይመልከቱ) ታዲያ ከእውነተኛ አምላክ የሚመጣ መገለጥ በእንደዚህ ዓይነት መልኩ መሆን ነበረበት? ይህንን ተከትሎ በተፈጠረባቸው ስሜት መሐመድ ብዙ ጊዜ ራሳቸውን ሊያጠፉ ሞክረው እንደነበር አሁንም ሐዲሱ ይመሰክራልና መሐመድ ለምን ብዙ ጊዜ ራሳቸውን ሊያጠፉ ሞከሩ? እስልምና በመላእክትና በነቢያት ያምናል፡፡ ለመሆኑ ለየትኛው ነቢይ ነው መላእክት በእንደዚያ ዓይነት ሁኔታ የተገለጡለት? የአምላክስ ቅዱስ መንፈስ ለነቢይ በእንደዚያ ዓይነት መንገድ መምጣት ነበረበት? የቁርአኑንስ ይዘት ልብ ብላችሁ ካያችሁት በውኑ ከሰማይ የመጣ ይመስላል? ማለትም በውስጡ ያሉት የታሪክ መፋለሶች፣ የጀመረውን ያለመጨረስ ችግርና የቋንቋ ሰዋሰዋዊ ሕግን አለመጠበቁ (grammatical errors) እነዚህና ሌሎቹም ስሕተቶቹ የእውነት ከሰማይ የመጣ

ያስመስሉታል? ታሪኩን ጠለቅ ብላችሁ የምታውቁት ሙስሊሞችስ የመሐመድ የግል ጸሐፊው ስለነበረው ሰው ስለ አብደላህ ኢብን ሳድ ኢብን አቢ ሳርህ ምን የምትሉት ነገር አለ?

ቀጥሎ የምንመለከተው የእነዚህንና የሌሎችንም ጥያቄዎች መልስ ነው፡፡ ከዚያ በፊት ግን አንድ ነገር ማስገንዘብ እፈልጋለሁ፡፡ ይህን ጽሑፍ ስታነቡ ቢቻልና የምታገኙት ከሆነ ቁርአኑን አብራችሁ በእጃችሁ ይዛችሁ ቢሆን በእጅጉ ይመረጣል፡፡ በዚህም እኔ ያነሳሁት ሀሳብ ምን ያህል እውነት መሆኑን ማረጋገጥ ትችላላችሁ፡፡ ወይም ደግሞ ሙሉውንም ሆነ ተፈላጊውን ምዕራፍና ቁጥር ከየትኛውንም ኢስላማዊ መካነ ድር (Web site) ላይ ማውረድ (download) ማድረግና ማረጋገጥ እንደሚቻል መጠቆም እፈልጋለሁ፡፡ ወደ ርዕሱ እንመለስና በመጀመሪያ አብደላህ ኢብን ሳድ ኢብን አቢ ሳርህ ማን ነው? የሚለውን እንይ፡-

አብደላህ ኢብን ሳድ ኢብን አቢ ሳርህ ማለት የመሐመድ የግል ጸሐፊው የነበረ ሰው ነው፡፡ በቀርአኑ ሱረቱ አል-አንዓም 6፡93 ላይ እንዲህ በማለት ተጽፏል፡- "በአላህም ላይ እብለትን ከቀጣጠፈ ወይም ወደርሱ ምንም ያልወረደለት ሲሆን ወደኔ ተወረደልኝ ካለና አላህም ያወረደውን ብጤ በእርግጥ አወርዳለሁ ካለ ሰው ይበልጥ በዳይ ማን ነው?" ይላል ቁርአኑ፡፡ ይህ አነጋገር ከመሐመድ ሌላ ቁርአንን ወረደልኝ የሚል ሰው ሊኖር ስለመቻሉ ነው በግልጽ የሚናገረው፡፡ ይህ ሰው ደግሞ መሐመድ ቁርአንን እንዲጽፉላቸው ካደረጓቸው በርካታ ሰዎች ውስጥ አንዱ የሆነው አብድ አላህ ኢብን ሳድ ኢብን አቢ ሳርህ የሚባለው ሰው ነው፡፡ በኋላ ላይ መሐመድንም ሆነ እምነታቸውን ትቶ ከመዲና ወደ መካ ተመልሶ ሄዶ ነበር፡፡ መሐመድም ጸሐፊያቸው ተፈልጎ እንዲገደል ትእዛዝ አስተላልፈውበት ነበር፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይ አብደላህ አብድ አል-ፋዲ ተባለው ጸሐፊ "Is the Qur'an Infallible?" ማለትም "ቁርአን እንከን የለሽ ነውን?" በሚል ርእስ በጻፈው ጽሑፍ ላይ የሚከተለውን አስፍሯል፡-

"የመሐመድ ጸሐፊዎች በቁጥር 42 ነበሩ፡፡ አብደላህ ኢብን ሳርህ አል-አሚሪ ከእነርሱ ውስጥ አንዱ ነበር፡፡ እስልምናን ትቶ ከመሄዱ በፊት መካ ውስጥ ከጻፉት መካከል እርሱ የመጀመሪያው ቁራይሽ ነው፡፡ እንዲህም ይል ነበር፡- 'መሐመድን እኔ ወደፈለኩበት እመራው ነበር፡፡ 'በጣም የላቀ'፣ 'ሁሉን አዋቂ' እያለ ቢቃል ያጽፈኛል፤ እኔም 'በጣም የላቀ' የሚለውን እተውና 'ሁሉን አዋቂ' የሚለውን ብቻ እጽፍ ነበር፡፡ እርሱም 'አዎ ተመሳሳይና አንድ ዓይነት ነው፤ ይህንና ይህን የመሳሰለውን ጻፍ' ይለኛል፡፡ ነገር ግን እኔ 'ጻፍ' የሚለውን ቃል ብቻ ነበር እጽፍ የነበረው፡፡ 'የፈለከውንም ጻፍ' ይለኝ ነበር'" በማለት አብደላህ ኢብን ሳርህ ተናግሯል፡፡ በዚህም ሁኔታ

መሐመድን ሲያጋልጠው መሐመድ ቁርአን ላይ “ወደርሱ ምንም ያልወረደለት ሲሆን ወደኔ ተወረደልኝ ካለና አላህም ያወረደውን ብጤ በእርግጥ አወርዳለሁ ካለ ሰው ይበልጥ በዳይ ማን ነው?” የሚል ጥቅስ አጻፈ፡፡ “ስለዚህም መሐመድ መካን በተቆጣጠረ ጊዜ ጸሐፊው የነበረውን አብደላህ ኢብን ሳርህን እንዲገደል ትእዛዝ ሰጥቶበታል” በማለት አብደላህ አብድ አል-ፋዲ ተባለው ጸሐፊ በሰፊው አብራርቷል፡፡ “The scribes of Muhammad were 42 in number. `Abdallah Ibn Sarh al-`Amiri was one of them, and he was the first Quraishite among those who wrote in Mecca before he turned away from Islam. He started saying, "I used to direct Muhammad wherever I willed. He would dictate to me 'Most High, All-Wise', and I would write down 'All-Wise' only. Then he would say, 'Yes it is all the same'. On a certain occasion he said, 'Write such and such', but I wrote 'Write' only, and he said, 'Write whatever you like.'" So when this scribe exposed Muhammad, he wrote in the Qur'an (6:93), "And who does greater evil than he who forges against God a lie, or says, 'To me it has been revealed', when naught has been revealed to him." So on the day Muhammad conquered Mecca, he commanded his scribe to be killed. But the scribe fled to `Uthman Ibn `Affan, because `Uthman was his foster brother (his mother suckled `Uthman). `Uthman, therefore, kept him away from Muhammad. After the people calmed down, `Uthman brought the scribe to Muhammad and sought protection for him. Muhammad kept silent for a long time, after which he said yes. When `Uthman had left, Muhammad said "I only kept silent so that you (the people) should kill him." (Is the Qur'an Infallible? by `Abdallah `Abd al-Fadi, & Al-Sira by al-'Iraqi)

አብድ አላህ ኢብን ሳድ ኢብን አቢ ሳርህ በእርግጥ መሐመድ መካን በተቆጣጠሩ ሰዓት ባሳደገው ወንድሙ ኦትማን ኢብን አፋን አስታራቂነት ከመሐመድ ጋር ታርቆ ወደ እስልምናም ተመልሷል፡፡ የጦር መሪና አዛዥም ሆኖ ተሹሞ በብዙ ጂሃዶች ላይ ተሳተፏል፡፡ ነገር ግን መጀመሪያ ላይ ማለትም መሐመድ መካን በተቆጣጠሩ ሰዓት መሐመድ እንዲገሉ ትእዛዝ ከሰጠባቸው ሰዎች ውስጥ አንዱ ኢብን አቢ ሳርህ ነበር፡፡ ይህንንም የአቡ ዳውድ ሀዲስ ዘግቦት ይገኛል፡፡ በሐዲሱ ዘገባ መሠረት መካ በቁጥጥር ስር በዋለችበት ዕለት መሐመድ ሊገድሏቸው ከሚፈልጓቸውና በስም ከጠቀሷቸው ከ4 ወንዶችና 2 ሴቶች በስተቀር ነዋሪዎቿ ጥበቃ እንዲደረግላቸው ትእዛዝ ሰጥተዋል፡፡ ኢብን አቢ ሳርህም ከሚገደሉት ሰዎች ውስጥ አንዱ ነበር፡፡ “On the day when Mecca was conquered, the Apostle of Allah gave protection to the People except four men and two women and he named them. Ibn AbuSarh was one of them.” Abu Dawud

14:2677
ልብ በሉ የዚህን ጸሐፊ ታሪክ ቀደም ብለን ካየነው ከመሐመድ ታሪክ ጋር ብናገናኘው አንድ ነገር እንደ ማጠቃለያ መናገር እንችላለን፡፡ መሐመድ ለንግድ በሄዱባቸው ሀገራት ስለ ተለያዩ እምነቶች ሲተረክላቸው የሰሟቸውን ታሪኮች ሰብስበው ነው ለሰዎች በድጋሚ በሚፈልጉት መልኩ ሲያጽፉ የነበረው ማለት ነው፡፡ የቁርአኑን ይዘት በደንብ ስናስተውለው ይህ ምን ያህል እውነት መሆኑን እናረጋግጣለን፡፡ ወደፊት በደንብ እናየዋለን ለአሁኑ ግን የጀመርነውን እንቀጥል፡፡ አብድ አላህ ኢብን ሳድ ኢብን አቢ ሳርህ የመሐመድን ሁኔታ ካየ በኋላ ከመዲና ወደ መካ ትቷቸው ሄዷል፡፡ ማለትም መሐመድ ሲፈልጉ «የፈለከውንና ደስ ያለህን ጨምረህ ጻፍ» ሲሉት በአንድ በኩል ደግሞ «ከሰማይ ወደረልኝ» እያሉ ለተከታዮቻቸው ሲያስተምሩ ሲያያቸው እየተደረገ ያለውን የሐሰት ሥራ ስለታዘበ መሐመድን «እንደዚህማ ከሆነ እኔም ነቢይ መሆንና ማስተማር እችላለሁ» ብሎ ጥሏቸው ጠፋ፡፡ መሐመድም ምስጢሬን ያወጣብኛል ብለው ስለፈሩ *"በአላህም ላይ እብለትን ከቀጣጠፈ ወይም ወደርሱ ምንም ያልወረደለት ሲሆን ወደኔ ተወረደልኝ ካለና አላህም ያወረደውን ብጤ በእርግጥ አወርዳለሁ ካለ ሰው ይበልጥ በዳይ ማን ነው?"* (ሱረቱ አል-አንዓም 6፡93) የሚለውን ጥቅስ በቁርአኑ ውስጥ በማካተት «የቁርአን መገለጦች የመጡልኝ ብቸኛው ሰው እኔ ነኝ» የሚል አንድምታ ያለው አዋጅ አወጁ፡፡

ኢብን አቢ ሳርህን ከመሐመድ ዘንድ በድብቅ ጠፍቶ እንዲሄድ ያስገደደው የመጨረሻው ክስተት የቁርአኑ 23ኛ ምዕራፍ ላይ ስለ ሰው አፈጣጠር የሚናገረው ነው፡፡ ሱረቱ አል-ሙእሚን 23፡14 ላይ ከቁ.12 ጀምሮ ስለ ሰው አፈጣጠር መሐመድ ኢብን አቢ ሳርህን ያጽፉታል፡፡ «በእርግጥም ሰውን ከነጠረ ጭቃ ፈጠርነው» ብሎ ይጀምርና «በተጠበቀ መርጊያ ካደረግነው በኋላ የስፐርም ሴል (የፍቶት ጠብታ) አደረግነው» ይላል፡፡ ከዚያም ስፐርም ሴሉ ወደ ረጋ ደምነት፣ የረጋው ደም ወደ ቁራጭ ሥጋነት፣ ቁራጩ ሥጋ ወደ አጥንትነት ከተለወጠ በኋላ አጥንቱን ሥጋ በማልበስ ሌላ ፍጥረት እንደተፈጠረ ቁርአኑ ይናገራል፡፡ ያ ሌላ ፍጥረት ደግሞ ሰው ሆነ፡፡ በዚህም አላህ ከሰዓሊዎች ሁሉ የበላይ እንደሆነ በመናገር ሰው የተፈጠረበትን መንገድ መሐመድ ከምድራዊ ሰዓሊ ጋር አነፃፅረውታል፡፡ ቀጥሎ ስካን (scan) የተደረገውን የቁርአኑን ጥቅስ ይመልከቱ፡፡



12 በእርግጥም ፡ ሰውን ፡ ከነጠረ ፡ ጭቃ ፡ ፈጠርነው ።
13 ከዚያም ፡ በተጠበቀ ፡ መርጊያ ፡ ውስጥ ፡ የፍቶት ፡ ጠብታ ፡ አደረ ግነው ።
14 ከዚያም ፡ ጠብታዋን ፡ (በአርባ ፡ ቀን) ፡ የረጋ ፡ ደም ፡ አድርገን ፡ ፈጠርን ፤ የረጋውንም ፡ ደም ፡ ቁራጭ ፡ ሥጋ ፡ አድርገን ፡ ፈጠ ርን ፤ ቁራጭዋንም ፡ ሥጋ ፡ አጥን ቶች ፡ አድርገን ፡ ፈጠርን ፤ አጥን ቶቹንም ፡ ሥጋን ፡ አለበስናቸው ፤ ከዚያም ፡ (ነፍስን ፡ በመዝራት) ፡ ሌላ ፡ ፍጥረትን ፡ አድርገን ፡ አስገ ኘነው ፤ ከሰዓሊዎችም ፡ ሁሉ ፡ በላጭ ፡ የኾነው ፡ አላህ ፡ ላቀ ።

በቅንፍ ውስጥ ያሉት (በአርባ ቀን፣ ነፍስን በመዝራት) የሚሉት ቃላት ትርጉም እንዲሰጡ በማሰብ ዘመናዊ ሙስሊም ምሁራን (Muslim scholars) በቅርብ ጊዜ የጨመሯቸው ቃላት ናቸው፡፡

የእውነት ሰው በእንደዚህ ዓይነት መንገድ ተፈጥሯል ወይ? የሚልና ሌሎችም በርካታ ጥያቄዎች ቢኖሩም አሁን ግን ጉዳዩ መሐመድን ከጸሐፊያቸው ጋር እንዴት ሊያጣላቸው እንደቻለ ማየቱ የተሻለ ነው፡፡ መጨረሻ ላይ ያለውን ሀሳብ ማለትም ‹ከዚያ ሁሉ ሂደት በኋላ ሌላ ፍጥረት በመፈጠሩ አላህ ከሰዓሊዎች ሁሉ የበላይ ሆነ› የሚለውን የፅንሰ ሀሳቡን መቋጫ ጸሐፊው ኢብን አቢ ሳርህ ያልተነገረውን ነገር ከራሱ ሀሳብ አመንጭቶ ነበር የጨመረበት፡፡ በወቅቱም መሐመድ ሀሳባቸውን ስለጠቀለለላቸው በሆነው ነገር ደስተኛ ነበሩ፡፡ ይህቺ ክስተት ናት ለመጨረሻ ጊዜ ኢብን አቢ ሳርህን ከመሐመድ ተለይቶ እንዲጠፋና የግደሉት ትእዛዝ እንዲተላለፍበት ያደረገችው፡፡

እስካሁን ይህን ስለ ኢብን አቢ ሳርህ ያየነውን በሙሉ ራሳቸው የዐረብ ጸሐፊዎች ሳይቀሩ በጻፏቸው መጻሕፍቶቻቸው ላይ በደንብ መስክረዋል፡፡ ለምሳሌ ኢብኑ ሂሻምና ዛኪ አሚን የተባሉ ጸሐፊዎች በዐረብኛ በተከታታይ «አል-ሲራ አል-ናባዊያ» እና «አል-ሲራ አል-ሀላቢያ» በተባሉ መጽሐፎቻቸው ላይ ታሪኩን በደንብ ጽፈውታል፡፡ ለማሳያ ያህል ከኢብኑ ሂሻም «አል-ሲራ አል-ናባዊያ» መጽሐፍ ከገጽ 57 ላይ ስካን (scan) ተደርጎ ከዐረብኛው ጎን ለጎን የእንግሊዝኛውም ትርጉም የያለበትን ጽሑፍ ቀጥሎ ይመልከቱ፡፡


6

*Al Sira Al Nabawiya, by Ibnu Hisham, Ch. IV, p. 57*

ذكر الأسباب الموجبة المسير إلى مكة وذكر فتح مكة ٥٧

يقطعنَ كل ساعد وجُمجُمة ضَرْباً فلا يُسْمَع إلاّ غمغمة(١)

لهمْ نَهيتُ خلفَنَا وهَمهَمَة لم تنطقِي في اللوم أدنى كلمة(٢)

...ض أهل العلم بالشعر قوله «كالموتمه»، وتروى



الطائف

وكان شِعار أصحاب رسول الله ﷺ يوم فتح مكة وحُنينٍ والطائف، شعارُ المهاجرين: يا بني عبد الرحمن، وشعار الخزرج ... بني عُبيدِالله.



عهد الرسول إلى أمرائه وأمره بقتل نفر سماهم

قال ابن إسحاق:

وكان رسول الله ﷺ قد عَهِدَ إلى أمرائه من المسلمين، حين أمرهم أن يدخلوا مكة، أن لا يقاتلوا إلا من قاتلهم، إلا أنه قد عَهِد في نفر سمّاهم أمر بقتلهم وإن وُجدوا تحت أستار الكعبة، منهم عبدالله بن سعد، أخو بني عامر بن لؤي.

[٥٢/٤] / سبب أمر الرسول بقتل سعد وشفاعة عثمان فيه

وإنما أمر رسولُ الله ﷺ بقتله لأنه قد كان أسلم، وكان يكتب لرسول الله ﷺ الوحي، فارتد مشركاً راجعاً إلى قريش، ففرّ إلى عثمان بن عفان، وكان أخاه

= خطيب قريش. والموتمة والموتم بلا همز، وتجمع على مياتم، وهي المرأة مات زوجها وترك لها أيتاما. وقال ابن إسحاق في غير هذه الرواية: «المؤتمة» الأسطوانة، وهو تفسير غريب، وهو أصح من التفسير الأول، لأنه تفسير راوي الحديث. وعلى قوله هذا يكون لفظ المؤتمة من قولهم: وتم، وأتم: إذا ثبت، لأن الأسطوانة تثبت ما عليها. ويقال فيها على هذا: مؤتمة بالهمز، وتجمع على مآتم، وموتمة بلا همز، وتجمع على: مواتم. (انظر «الروض الأنف»).

(١) الغمغمة: أصوات غير مفهومة لاختلاطها.

(٢) النهيت: صوت الصدر، وأكثر ما يوصف به الأسد. والهمهمة: صوت في الصدر أيضا.

(٣) كذا في أكثر الأصول. وفي ا: «الرعاس» قال أبو ذر: «الرعاش: يروى ههنا بالسين والشين، وصوابه بالشين المعجمة لا غير».

ቦታና ጊዜ ከመቆጠብ አንጻር በአንዱ ገጽ ላይ ብቻ ተወሰንን እንጂ ይህ የኢብኑ ሂሻም መጽሐፍ የኢብን አቢ ሳርህን ታሪክ በስፋትና በጥልቀት ነው የሚተርከው፡፡ ሌሎች የምናያቸው በጣም ብዙ ነገሮች ስላሉ ነገሩንም እየጠቀለልነው ለማለፍ እንዲመቸን ወደ መጀመሪያው ሀሳብ እንመለስ፡፡ መሐመድ ለንግድ በሄዱባቸው ሀገራት ሁሉ ስለተለያዩ እምነቶች ሲተረክላቸው የሰሚቸውን ታሪኮች ሰብስበው ለግል ጸሐፊዎቻቸው በድጋሚ በሚፈልጉት መልኩ አጽፈው ነው ለተከታዮቻቸው ከሰማይ ወረደልኝ ያሉት፡፡ ይህንንና ተያያዥ ጉዳዮችን ማለትም ቁርአኑ ምን ያልህ በሰው የተቀናበረ እንደሆነ ቀጥሎ በስፋት እናየዋለን፡፡ አሁን አንድ ነገር በግልጽ እንድታዩልኝ እፈልጋለሁ፡፡ ከላይ እንዳየነው ቁርአን ማለት መሐመድ በ3ኛ ወገን በኩል በጸሐፊ ያጻፉትና የሰዎች ቅንብር መሆኑን ለማረጋገጥ ብዙ መንገዶች አሉ፡፡ የመጀመሪያው

ማረጋገጫ መንገድ ይዞቱን በደንብ መመርመር ነው፡፡ ቁርአን በብዙ የቋንቋ ሰዋሰዋዊ ስሕተቶች /grammatical errors/ የተሞላ ነው፡፡ የጀመረውን ሳይጨርስ ነው ስለ ሌላ የሚያወራው፡፡ ለእነዚህ ሁለት ነጥቦች ማሳያ እንዲሆን ከቁርአኑ ላይ ቀጥታ ስካን (scan) አድርጌ ያስገባኋቸውን ቀጥሎ ያሉትን አንቀጾች በደንብ ተመልከቷቸው እስቲ!!!

A) 13 በአላህና ፡ በመልክተኛው ፡ ያላመነም ፡ ሰው ፣ እኛ ፡ ለከሓዲዎች ፡ እሳትን ፡ አዘጋጅተናል ።

B) 82 ፡-በሞትንና ፡ ዐፈርና ፡ አጥንቶች ፡ በኾን ፡ ጊዜ ፣ እኛ ፡ ተቀስቃሾች ፡ ነን ? አሉ ።

83 ይህንን ፡ እኛም ፣ ከእኛ ፡ በፊትም፡ የነበሩት ፡ አባቶቻችን ፣ በእርግጥ፡ ተቀጥረናል ፤ ይህ ፡ የመጀመሪያዎቹ ፡ ሰዎች ፡ ተረቶች ፣ እንጂ ፡ ሌላ ፡ አይደለም ፡ (አሉ) ።

C) 69 እነዚያ ፡ ያመኑና ፣ እነዚያም ፡ ይሁዳውያን ፡ የኾኑ ፣ ሳቢያኖችም ፣ ክርስቲያኖችም ፣ (ከነርሱ)፡ በአላህና ፣ በመጨረሻው ፡ ቀን ፡ ያመነና ፡ መልካምን ፡ ሥራ ፡ የሠራ ፣ ሰው ፣ በነርሱ ፡ ላይ ፡ ፍርሃት ፡ የለባቸውም ፤ እነርሱም ፡ አያዝኑም ።

ከላይ ያሉትን ጥቅሶች በደንብ ስትመለከቷቸው ምን ስሕተት አገኛችሁባቸው? እኔ በጥቅሶቹ ላይ የገኘሁባቸውን ስሕተቶች ሁሉንም አንድ በአንድ ለማሳየት እሞክራለሁ፡፡ A) ሱረቱ አል-ፈትሕ 48፡13 ላይ ያለው ጥቅስ *«በአላህና በመልክተኛው ያላመነም ሰው እኛ ለከሓዲዎች እሳትን አዘጋጅተናል»* ይላል፡፡ የጥቅሱ የመጀመሪያ ስሕተት የቋንቋ ሰዋሰዋዊ ሕግን ያለመጠበቅ ችግር ነው፡፡ የሰዋሰዋዊ ስሕተቱ (grammatical error) ያለው «ያላመነም ሰው» የሚለው ላይ ነው፡፡ «ላላመነም ሰው» ተብሎ ቢነገር ግልጽና የተሻለ ይሆን ነበር፡፡ ፊደል «ያ» ያለቦታዋ ነው የገባችው፡፡ እስቲ እነዚህን ሁለት ቃላት አቀያይራችሁ እያስገባችሁ ጥቅሱን በደንብ አንብቡትና ልዩነቱን እዩት፡፡ ምናልባት ወደ አማርኛ ሲተረጎም የፊደል ግድፈት ተከስቶ ነው እንዳይባል ኦሪጂናሉ የዐረብኛው ቁርአን ላይም በተመሳሳይ የፊደል አገባብ ነው የተቀመጠው፡፡ ይህንን ይበልጥ የሚረዱት የዐረብኛውን ፊደልና የአገባብቡን ሁኔታ በደንብ የሚያውቁት ናቸው፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ ምንም እንኳን እንደ ስሕተት ባይታይም «እኛ» ብሎ ራሱን በብዙ ቁጥር የገለጸው አካል ግልጽ አይደለም፡፡ ቁርአኑ ከመጀመሪያው ጀምሮ እስከ መጨረሻው ምዕራፍ ድረስ “ፈጠርን፣ ሠራን፣ አደረግን…” በሚሉ ቃላት የታጨቀ ነው፡፡ ሙስሊሞች «አላህ አንድ ብቻ ነው» እያሉ ምሥጢረ ሥላሴን በፅኑ

ይቃወማሉ፡፡ ግን ደግሞ ሙሉ ቁርአናቸው “ፈጠርን” እያለ ነው አላሃቸው ፈጣሪ መሆን የሚያወራው፡፡ ይህ ለምን እንደሆነ ወደፊት በሰፊው እናየዋለን፡፡ በምናያቸው የቁርአን ጥቅሶች ላይ አላህ ራሱን በብዙ ቁጥር የገለጸ መሆኑን እግረ መንገዳችንን ልብ እንድንለው ለማለት ያህል ነው፡፡ 2ኛው ስሕተት ደግሞ «እርሱ» ተብሎ ስለሚጠራ አንድ ሰው ማለትም ስለ ሦስተኛ መደብ ነጠላ ቁጥር እየተናገረ እያለ ይህን የጀመረውን ሳይጨርስ ስለ አንደኛ መደብ ብዙ ቁጥር መናገር ጀመረ፡፡

ስለዚህ በአጭሩ «በአላህና በመልክተኛው ያላመነም ሰው እኛ ለከሓዲዎች እሳትን አዘጋጅተናል» ተብሎ የተነገረው ነገር የቋንቋ ሰዋሰዋዊ ሕግን እንዲጠብቅና ትርጉም በሚሰጥ መልኩ እንዲነገር ከተፈለገ በነጠላው ቁጥር «በአላህና በመልክተኛው ላላመነም ሰው እኛ ለከሓዲ እሳትን አዘጋጅተናል» ወይም ደግሞ በብዙው ቁጥር «በአላህና በመልክተኛው ላላመኑም ሰዎች እኛ ለከሓዲዎች እሳትን አዘጋጅተናል» ተብሎ ቢነገር ግልጽና የተሻለ ይሆን ነበር የሚል የግል አስተያየት አለኝ፡፡

B) 2ኛው ጥቅስ ቁርአኑ 23፡83 ላይ ያለው ነው፡፡ «ይህንን እኛም ከእኛ በፊትም የነበሩት አባቶቻችን በእርግጥ ተቀጥረናል፤ ይህ የመጀመሪያዎቹ ሰዎች ተረቶች እንጂ ሌላ አይደለም (አሉ)» ተብሎ ነው የተጻፈው፡፡ ጥቅሱ በማን መደብ እንደጀመረና እንደጨረሰ አስተውሉ፡፡ «እኛም ከእኛ በፊትም የነበሩት አባቶቻችን በእርግጥ ተቀጥረናል» የሚለው አገላለጽ ላይ «እኛ» ብሎ ስለ አንደኛ መደብ የጀመረውን ሀሳብ ሳይጨርሰው «አባቶቻችን» በማለት ስለ ሦስተኛ መደብ በመሀል ላይ መናገር ጀመረ፡፡ ስለዚህ አገላለጹ አንድም «ይህንን እኛም ከእኛ በፊትም የነበሩት አባቶቻችን በእርግጥ ተቀጥረዋል…» አሊያም «ይህንን እኛም ከእኛ በፊት_ እንደነበሩት አባቶቻችን በእርግጥ ተቀጥረናል…» ተብሎ ቢነገር ግልጽና የተሻለ ይሆን ነበር የሚል የግል አስተያየት አለኝ፡፡

C) በ3ኛ ደረጃ ያየነው ጥቅስ አል-ማኢዳህ 5፡69 ላይ «እነዚያ ያመኑና እነዚያም ይሁዳውያን የሆኑ ሳቢያኖችም፣ ክርስቲያኖችም (ከነርሱ) በአላህና በመጨረሻው ቀን ያመነና መልካምን ሥራ የሠራ ሰው በነርሱ ላይ ፍርሃት የለባቸውም፤ እነርሱም አያዝኑም» ተብሎ የተጻፈውን ነው፡፡ ሲጀመር መሐመድ ስለ ሳቢያኖችና ክርስቲያኖች መናገር ሲጀምሩ «እነዚያ ያመኑና…» በማለት መጀመሪያውኑ ቀድመው ያመኑ መሆናቸውን በግልጽ መስክረውላቸዋል፡፡ ነገር ግን ቀድመው «ያመኑ» ቢሆኑም መልሰው እንደገና በአላህ ማመን እንዳለባቸው ነው የተናገሩት፡፡ ወደ ሰዋሰዋዊ ስሕተቱ ስንመጣ ስሕተቱ ከሁለተኛው ጥቅስ ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡ «እርሱ» ተብሎ በሁለተኛ መደብ የተጠቀሰው መሀል ላይ የገባው ያለቦታው ነው፡፡ «እነዚያ» ብሎ ስለ ሦስተኛ መደብ እየተናገረ እያለ በመሀል ስለ ሁለተኛ መደብ መናገረ ጀመረና ይህንን ሳይጨርስ

እንደገና «እነዚያ» ብሎ ጨረሰው፡፡ ሲጀመር «እነዚያ ያመኑና እነዚያም ይሁዳውያን የሆኑ...» እያለ ቃላት መደጋገም አልነበረበትም፡፡ ሙሉ ሀሳቡ «እነዚያ ያመኑና ይሁዳውያን የሆኑ...» ተብሎ መገለጽ ይችል ነበር፡፡ ሙሉ ጥቅሱ በአጠቃላይ ቀጥሎ ካሉት ሁለት አማራጮች ውስጥ በአንደኛው መንገድ መነገር መቻል ነበረበት፡፡ አንድም «እነዚያ ያመኑ_ ይሁዳውያን የሆኑ ሳቢያኖችም፣ ክርስቲያኖችም (ከነርሱም ውስጥ) በአላህና በመጨረሻው ቀን ያመኑና መልካምን ሥራ የሠሩ ሰዎች በነርሱ ላይ ፍርሃት የለባቸውም፤ እነርሱም አያዝኑም» ተብሎ ቢነገር መልካም በሆነ ነበር አሊያም ስለ አንድ ሰው መናገር ከተፈለገ ደግሞ «ከእነዚያ ይሁዳውያን ከሆኑ ሳቢያኖችና፣ ክርስቲያኖች (መካከል) በአላህና በመጨረሻው ቀን ያመነና መልካምን ሥራ የሠራ ሰው በርሱ ላይ ፍርሃት የለበትም፤ እርሱም አያዝንም» ተብሎ መነገር ነበረበት የሚል አስተያየት አለኝ፡፡ እንዲሁም በተመሳሳይ ሁኔታ 4፡69 ላይ ያለውን ተመልከቱ፡፡ እንዲህ ይላል፡- «አላህንና መልክተኛውንም የሚታዘዝ ሰው እነዚህ ከነዚያ አላህ በነርሱ ላይ ከለገሰላቸው ከነቢያት፣ ከጻድቃንም፣ ከሰማዕታትም፣ ከመልካሞቹ ጋር ይሆናሉ፡፡ የነዚያም ጓደኝነት አማረ!» ተብሎ በተጻፈውም ላይ አላህንና መሐመድን ስለሚታዘዝ ስለ አንድ ሰው የጀመረውን ሳይጨርስ ከጻድቃንና ከሰማዕታት ጋር ስለሚሆኑት ስለ ብዙ ሰዎች ተናግሮ ነው የጨረሰው፡፡ አብዛኛዎቹ የቁርአን አንቀጾች በዚህ መልኩ ተጽፈው የተቀመጡ ስለሆነ እንዲህ ነው... እንዲህ ነው እያልኩ ከዚህ በላይ ቦታና ጊዜ መፍጀት አልፈልግም፡፡ ለማሳያ ያህል ነው እነዚህን ሦስት ምሳሌዎች ያነሳሁት እንጂ ወደፊት የምናያቸው በርካታ ተያያዥ ጉዳዮች ስላሉ እነሱን ማየቱ የተሻለ ነው፡፡ በቁርአኑ ውስጥ ሌላው ቢቀር ቃላቶቹን እርስ በእርስ የሚያያይዙት መስተዋድዶች (prepositions) እንኳን ያለ ቦታቸው የገቡበት ሁኔታ አለ፡፡ አንድ ምሳሌ ብቻ ላሳያችሁ፡፡ በአማርኛው ቁርአን 4፡3 ላይ «ከሴቶች ለናንተ የተዋበላችሁን ሁለት ሁለት፣ ሦስት ሦስትም፣ አራት አራትም አግቡ» ይላል፡፡ የዐረብኛውንና ሻኪር የተባለው ሙስሊም ተርጓሚ ወደ እንግሊዝኛ የተረጎመውን ቁርአን ደግሞ ቀጥሎ እንመልከት፡፡

በዐረብኛው "fainkihoo ma taba lakum mina alnnisa-i mathna wathulatha warubaAAa" ይላል፡፡ ይህንን የተረጎመው ሻኪር ደግሞ (Shakir: “... marry such women as seem good to you, two and three and four.”) በማለት ጽፏል፡፡ የሻኪርን ትርጓሜ ወደ አማርኛ ስንመልሰው «... ሁለት እና ሦስት እና አራት አግቡ» ነው የሚለው፡፡ የአማርኛውም ቁርአን «... ሦስት ሦስትም፣ አራት አራትም አግቡ» ስለሚል ከሻኪር ትርጓሜ ጋር ተመሳሳይ የሆነ ይመስላል፡፡ ብቸኛና ዋና ማመሳከሪያ ሊሆን የሚችለው የዐረብኛውን ቁርአን ስለሆነ እርሱን ማየቱ የተሻለ ነው፡፡ ዋ (wa)

የምትለው የዐረብኛ ቃል ትርጓሜዋ «እና/and » የሚል ነው፡፡ ስለዚህ ሻኪር የዐረብኛውን ቁርአን መሠረት በማድረግ «...ሁለት እና ሦስት እና አራት አግቡ» በማለት ያስቀመጠው ትርጓሜ ትክክል ነው ማለት ነው፡፡ ነገር ግን በዐረብኛውና በእንግሊዝኛው ቁርአን ላይ «እና/and» የሚለው መስተዋድድ (preposition) ያለ ቦታው ነው የገባው፡፡ እስቲ አገላለጹን ልብ ብለን እንየው!!! «...ሁለት እና ሦስት እና አራት አግቡ» ማለትኮ 2+3+4 ማለት ነው፡፡ ነገር ግን ቃሉ በትክክል መነገር የነበረበት «... ሁለት ወይም ሦስት ወይም አራት አግቡ» ተብሎ ነበር፡፡ ችግሩን ያመጣው ደግሞ «እና/and » የሚለው መስተዋድድ ነው፡፡ የዐረብኛውም ቁርአን መጠቀም ያለበት «እና» የሚል ትርጉም ያለውን ቃል «wa=and» ሳይሆን «ወይም» የሚል ትርጉም ያለውን «aw=or» የሚለውን ቃል መጠቀም ነበረበት፡፡ ችግሩን ስላዩት ነው የአማርኛው ቁርአን ተርጓሚዎች አገላለጹን ከዐረብኛው ትንሽ ለወጥ ያደረጉት፡፡ ትርጉሙ ግን ያው ነው፡፡ አንዳንድ የውጭዎቹ ትርጓሚዎች ግን ችግሩን በደንብ ስላዩት ሙሉ በሙሉ በዐረብኛው ቁርአን ላይ በትክክል የተጻፈውን ትተው ሌላ የራሳቸውን ማያያዣ መርጠዋል፡፡ ዩሱፍ ዓሊና ፒክታል የተባሉት ጸሐፊዎቻቸውም በቅርብ ጊዜ ዐረብኛውን ወደ እንግሊዝኛ ሲተረጉሙ «aw=or» የሚለውን መጠቀም መርጠዋል፡፡ “... marry women of your choice, two or three or four.” ይላል ከዐረብኛው የተለየው የዩሱፍ ዓሊ ትርጓሜ፡፡ ሰላምንና ጥሩ ነገርን ከመፍጠር አንጻር አሁን ያሉት ሙስሊም መምህራን ሌሎችንም ጥቅሶች (ለምሳሌ እነዚያን ዘግናኝ የግድያ ጥቅሶች...) እንዲህ አሁን እነ ዩሱፍ ዓሊ እንዳደረጉት ቀየር እያደረጉ ለሕዝባቸው ቢያቀርቡ ጥሩ ይሆን ነበር፡፡ ዓለምም የተሻለ የሰላም አየር ትተፍስ ነበር!!!

እንደ እውነቱ ከሆነ «አብድ አላህ ኢብን ሳድ ኢብን አቢ ሳርህ» የተባለው የመሐመድ ጸሐፊ ሁኔታውን ካየ በኋላ ማለትም መሐመድ ሲፈልጉ «ጨምረህ ጻፍ» ሲሉት በአንድ በኩል ደግሞ «ከሰማይ ወደረልኝ» እያሉ ለተከታዮቻቸው ሲያስተምሩ ካያቸው በኋላ እየተደረገ ያለውን የሐሰት ሥራ ስለታዘበ መሐመድን «እንደዚህማ ከሆነ እኔም ነቢይ መሆንና ማስተማር እችላለሁ» በማለት ጥሎ መጥፋቱ በጣም ትክክል ነበር፡፡ እኔ እርግጠኛ ሆኜ አንድ ነገር እነግራችኋለሁ፡፡ ይህንን እኔ የምነግራችሁን ነገር እናንተ ቁርአኑን ገልጸችሁ አይታችሁ ፈራጆች ሁኑ፡፡ በየትኛውም ዘመን የነበረ አንድ ተራ ምድራዊ ደራሲ ከቁርአን የበለጠ ጥሩ ድርሰት መጻፍ ይችላል፡፡ ይህንን ለማረጋገጥ የቁርአኑን ይዘት መመርመር ነው፡፡

ቁርአን ማለት በአጠቃላይ እነዚህን ከላይ ያየናቸውን በመሰሉ ግድፈቶች የተሞላ ነው፡፡ የቋንቋ ሰዋሰዋዊ ሕግን አይጠብቅም፤ በውስጡ ያሉት ታሪኮች በትክክል ከሌሎች

እምነቶች የተኮረጁ ናቸው፤ እንደዛም ሆኖ የጀመረውን ታሪክ አይጨርስም፤ ቁርአኑ ራሱ መጽሐፍ ቅዱስን አረጋግጣለሁ ይላል፤ ከመሐመድ ሞት በኋላ ሆን ተብሎ በከሊፋዎቹ አማካኝነት የተወሰኑ የቁርአን አንቀጾች እንዲቃጠሉ ተደርጎ ተፈላጊና ጠቃሚ ናቸው ተብለው የታሰቡት አንቀጾች ብቻ ተሰብስበው በአንድ የተጠቃለሉበት መንገድ በእጅጉ አነጋጋሪ ነው፤ ከምንም በላይ ደግሞ እጅግ አሳዛኙ ነገር ምን መሰላችሁ? ቁርአኑ አጠቃላይ ይዘቱ እጅግ አሰልቺ ነው፡፡ የቃላት መደጋገም ከማብዛቱም በላይ ያዘነውን ከማፅናናትና ያጠፋውን መክሮ ወደ ንስሓ ከመመለስ ይልቅ በዛቻና ማስፈራሪያ ቃላቶች የተሞላ ነው፡፡ ከነፍስ ይልቅ ለሥጋ ቅድሚያ ይሰጣል፡፡ ሌላው ቢቀር ነፍስ ከሞት በኋላ ወደ አላህ የምትሄደው የሥጋን ፍላጎት ልትፈጽም ነው፡፡ ከላይ ጀምሮ ለምን እነዚህን የጠቀስኳቸውን ነገሮች እንዳነሳሁ ይህን ስለ ቁርአን እየተነጋገርንበት ያለውን ርዕስ አንብባችሁ ስትጨርሱ በደንብ ትረዱታላችሁ፡፡ ምክንያቱም እያንዳንዷን ነገር ከላይ ባየነው መልኩ በዝርዝር እያየነው ስለምንሄድ ነው፡፡ ስለዚህ እይታችንን ከዚህ ርዕስ ነው የምንጀምረው፡-

<u>በቁርአን ላይ የደረሱ ብክለቶችና እንዳይታመን ያደረጉት ነገሮች (Corruption of the Qur'an)</u>

እኔ በበኩሌ በቁርአን እንዳላምን ያደረጉኝ እጅግ በርካታ ነገሮች ቢሆኑም ዋና ዋናዎቹን ቀጥሎ በዘረዘርኳቸው ነጥቦች ላይ እንዲካተቱ አድርጌያለሁ፡፡ ከቁርአኑና ከሐዲሱ ማስረጃዎችን በማጣቀስ ሁሉንም ነጥቦች በዝርዝር ስናያቸው ቀጥሎ የጠቀስኳቸው ነጥቦች ምን ያህል እውነት መሆናቸውን ይህን ጽሑፍ የሚያነብ አንባቢ ራሱ ፍርዱን ይሰጣል፡፡ ቁርአንን እንዳይታመን ካደረጉት ዋና ዋና ነጥቦች ውስጥ የሚከተሉት ይገኙበታል፡-

1ኛ. ከላይ እንዳየነው መሐመድ በ3ኛ ወገን በኩል በጸሐፊ ያጻፋት ስለሆነና ጸሐፊውም የራሱን ሀሳብ ስለጨመረበት ቁርአን ሊታመን አይችልም፡፡

2ኛ. ቁርአኑ በየጊዜው ተለዋዋጭ እንደሆነ ራሱ ቁርአኑ ስለሚናገር ታማኝ አይደለም፡፡

3ኛ. የቁርአኑ የተለያዩ አንቀጾች ተሰብስበው በአንድ የተጠቃለሉበት መንገድ አሳማኝና አግባብነት የሌለው በመሆኑ ሊታመን አይችልም፡፡

4ኛ. ቁርአኑ በብዙ የቋንቋ ሰዋሰዋዊ ስሕተቶች /grammatical errors/ የተሞላ ስለሆነ ሊታመን አይችልም፡፡

5ኛ. በቁርአኑ ውስጥ ያሉት ታሪኮች ከሌሎች እምነቶች የተኮረጁ ስለሆኑ ታማኝ አይደለም፡፡

6ኛ. ቁርአን የመጽሐፍ ቅዱስ አረጋጋጭ መሆኑን ስለሚናገር ሊታመን አይችልም፡፡

7ኛ. ቁርአኑ ለመሐመድ ሰይጣናዊ በሆነ መንገድ የተገለጠ በመሆኑ ታማኝ አይደለም፡፡

8ኛ. ቁርአኑ አጠቃላይ ይዘቱ እጅግ አሰልቺ በመሆኑ ታማኝ አይደለም፡፡

9ኛ. የጀመረውን ሀሳብም ሆነ ታሪክ የማይጨርስ ስለሆነ ሊታመን አይችልም፡፡

10ኛ.ቁርአኑ ከሰማይ የወረደ ሳይሆን የራሱ የሆኑ ምንጮች ስላሉት ሊታመን አይችልም፡፡

11ኛ.ቁርአን ከዐረብኛ ውጭ የሆኑና ከሌሎች ቋንቋዎች የወረሳቸው ባዕድ ቃላትን ስለሚጠቀም ታማኝ ሊሆን አይችልም፡፡

12ኛ. የመሐመድ ትምህርቱና የሕይወት ተሞክሮአቸው በጣም ብዙ አስከፊ ገጽታዎች ያሉት በመሆኑ ከእርሳቸው የተገኘው ቁርአንም ፈጽሞ ሊታመን አይችልም፡፡

13ኛ. ከቁርአኑ ውስጥ የተሰረዙና እንዲጠፉ የተደረጉ ጥቅሶች በመኖራቸው ሊታመን አይችልም፡፡

14ኛ. ቁርአን ወደፊት ስለሚሆነው የዓለም ክስተት ምንም ነገር አለማወቁ እንዳይታመን አድርጎታል፡፡

አሁን እያንዳንዱን ነጥብ ከቁርአኑና ከሐዲሱ ውስጥ ማስረጃዎችን በማጣቀስ ሁሉንም በዝርዝር ማየት እንችላለን፡፡ የመጀመሪያውን «ቁርአኑ በመሐመድ የግል ጸሐፊ በኩል የተጻፈ ስለሆነና የጸሐፊውም የግል ሀሳብም ስለተጨመረበት ቁርአኑ ሊታመን አይችልም» የሚለውን ቀደም ብለን ስላየነው ተራ ቁጥር ሁለት ላይ ካለው እንጀምራለን፡-

2ኛ.ቁርአኑ በየጊዜው ተለዋዋጭ እንደሆነ ራሱ ቁርአኑ ይናገራል፡- ቀጥሎ ያለውን የቁርአን ጥቅስ ተመልከቱ፡፡ "ከአንቀጽ ብንለውጥ ወይም እርሷን ብናስረሳህ ከእርሷ የሚበልጥን ወይም ብጤዋን እናመጣለን፤ አላህ በነገሩ ሁሉ ላይ ከሃሊ መኾኑን አታውቅምን?" ሱረቱ አል-በቀራህ 2፡106፡፡ ምን ማለት ነው? ሲጀመር የአምላክ ቃል እንዴት በየጊዜው ሊለዋወጥ ይችላል? ነቢይስ እንዴት ከአምላክ የተቀበለውን ይረሳል? አምላክስ ነቢይ ላደረገው ሰው ለምን አንቀጽን ማስረሳት አስፈለገው? ደግሞ ቢረሳስ እንዴት ከበፊት የበለጠ አንቀጽ ይሰጠዋል? የአምላክ ቃል መበላለጥ አለበት እንዴ?.... እያልን ሌሎችም በጣም ብዙ ጥያቄዎችን ማንሳት እንችላለን፡፡ ዓላማዬ ጥያቄ መጠየቅ ስላልሆነ ነገሩን በመንፈሳዊ ዓይን ወደማየቱ ብመለስ ነው የሚሻለው፡፡ ነገሩን በሰው ሰውኛ አስተሳሰብ እንኳን ብናየው ብዙ ነገሮችን ማንሳት እንችላለን፡፡ የአምላክ ቃል በየጊዜው የሚለዋወጥ መሆን የለበትም፡፡ የአምልክ ቃል ዘላለማዊ፣ ሕያው ነውና አንድ ጊዜ የተናገረው ፈጽሞ ሊለወጥ አይችልም፡፡ ተገቢም አይደለምም፡፡ አላህ ግን ይህን ባሕርይ ለራሱ ማድረግ አልፈለገም፡፡ "ብጤ" ወይም "የምትበልጥ" የተባለችው አንቀጽ መምጣት አለመምጣቷ በራሱ ጥያቄ ቢሆንም መሐመድም ቢሆኑ ራሳቸውም ይርሱ

ወይም አምላካቸው ያስረሳቸው ብቻ እርሳቸው የረሷቸው አንቀጾ ስለመኖራቸው ጥቅሱ በራሱ በቂ ፍንጭ ይሰጣል፡፡

መሐመድም የቁርአኑን ጥቅስ በፈለጉት መንገድ ይለውጡና ያስተካክሉ እንደነበር ከሐዲሱ ላይ አንድ ማሳያ ልጥቀስላችሁ፡፡ መሐመድ የተለያዩ አጋጣሚዎችንና የተሻሉ ሁኔታዎችን ሲያገኙ ቁርአኑን ያሻሽሉት እንደነበር ሐዲሱ ይናገራል፡፡ ለምሳሌ ቁርአን 4፡95 ላይ "እቤታቸው የተቀመጡ አማኞችና በጂሃድ ታግለው የተዋጉ አማኞች በጀነት እኩል አይደሉም" የሚለውን ጥቅስ መሐመድ ሲናገሩ አሚር ቢን ኡም ማክቱም የተባለ አንድ ዓይነ ስውር ሰው ይሰማቸዋል፡፡ ወደ መሐመድም ጠጋ ይልና "ኦ የአላህ ሐዋርያ ሆይ! እኔ ዓይነ ስውር ሰው ነኝና ከላይ የጠቀስከውን ጥቅስ በተመለከተ ለእኔ ያለህ ትእዛዝ ምንድን ነው?" ብሎ ጠየቃቸው፡፡ መሐመድም ይህን ጊዜ "የአካል ጉዳት ያለባቸው ወይም ዓይነ ስውር ካልሆኑ በቀር እቤታቸው የተቀመጡ አማኞችና በአላህ መንገድ ታግለው የተዋጉ አማኞች እኩል አይደሉም" በማለት በቁርአኑ ጥቅስ ላይ ማሻሻያ እንዳደረጉበት ሐዲሱ ይመሰክራል፡፡ "Narrated Al-Bara: There was revealed: 'Not equal are those believers who sit (at home) and those who strive and fight in the Cause of Allah.' (4.95) The Prophet said", "Call Zaid for me and let him bring the board, the inkpot and the scapula bone (or the scapula bone and the ink pot).'" Then he said, "Write: 'Not equal are those Believers who sit.", and at that time 'Amr bin Um Maktum, the blind man was sitting behind the Prophet. He said, "O Allah's Apostle! What is your order for me (as regards the above Verse) as I am a blind man?" So, instead of the above Verse, the following Verse was revealed: 'Not equal are those believers who sit (at home) except those who are disabled (by injury or are blind or lame etc.) and those who strive and fight in the cause of Allah.' (4.95) Sahih Bukhari 6:61:512

በመጨረሻም ከዚህች «ከአንቀጽ ብንለውጥ ወይም እርሷን ብናስረሳህ ከእርሷ የሚበልጥን ወይም ብጤዋን እናመጣለን» (2፡106) ከምትለዋ አገላለጽ ጋር በተገናኘ አንድ ነጥብ ላንሳ፡፡ ያም "ብንለውጥ... እናመጣለን" እያለ ራሱን በብዙ ቁጥር የሚገልጸው ማን ነው? በጣም በሚገርም ሁኔታ ቁርአኑ ከመጀመሪያው ምዕራፍ እስከ መጨረሻው ምዕራፍ ድረስ "ሠራን፣ አደረግን፣ ፈጠርን..." በሚሉ ቃላት ሙሉ በሙሉ የታጨቀ ነው፡፡ ሙስሊሞች አላህ አንድና አንድ ብቻ ነው እያሉ በሌላ በኩል ደግሞ አላህ እንዴት ራሱን በብዙ ቁጥር ሊገልጽ ቻለ? አላህ ረዳቶቹና አገልጋዮቹ ስለሆኑት መላኢኮች (መላእክት) መናገሩ ነው እንዳይባል እነርሱ በመፍጠር ውስጥ ምንም ሚና የላቸውም፡፡ ሊኖራቸውም አይችልም፡፡ ያገለግላሉ፣ ይራዳሉ እንጂ አይፈጥሩም፡፡

የአክብሮት አነጋገር ነው እንዳይባል አክብሮት በብዙ ቁጥር አይደለም የሚገለጠው፡፡ ደግሞ አምላክ የፈጠራቸው ፍጥረታት ፈጣሪያቸውን በአክብሮት ስም ይጠሩታል እንጂ አምላክ ራሱን በአክብሮት ስም አይጠራም፡፡ "ሥራን፣ አደረግን፣ ፈጠርን…" የሚሉት ቃላትም በራሳቸው የአክብሮት ቃላት አይደሉም፡፡ በቁርአኑ ውስጥ አላህ ስለራሱ ሲናገር "ፈጠርን" እያለ እጅግ ብዙ ጊዜ ተናሯል፡፡ ታዲያ አላህ ራሱን በዚህ መልኩ በብዙ ቁጥርና በአንድነት የሚገልጸው ለምን ይሆን? በቁርአኑ ላይ እንደተጻፈው "ፈጠርን" ብሎ ጀምሮ ሲያበቃ የጥቅሱ መጨረሻ ላይ ደግሞ "አላህ ሁሉን ቻይ ነው፤ ሁሉን አዋቂ ነው፤ የሚሳነው የለም…" እያለ ራሱን ከሚገልጽ ይልቅ "አድራጊም ፈጣሪም እኔ ብቻ ነኝ፤ ሰማያትን ለብቻዬ የዘረጋሁ፣ ምድርንም ያፀናሁ…" እያለ ራሱን ቢገልጽ ከራሳቸው ከሙስሊሞቹ አስተምህሮ አንጻር የተሻለ አይሆንም ነበር ወይ? "ፈጠርን" ብሎ ጀምሮ "አላህ ሁሉን ቻይ ነው" ብሎ ከመጨረስና "ፈጠርኩ" ብሎ ጀምሮ "አላህ ሁሉን ቻይ ነው" ብሎ ከመናገር የቋንቋ ሰዋሰዋዊ ሕግንስ ከመጠበቅም አንጻር የትኛው ነው የሚሻለው? እግረ መንገዳችንን ለማንሳት ያህል ነው እንጂ በዚህ ጉዳይ ላይ ራሱን የቻለ ርዕስ ስላለው ወደፊት በስፋት እናየዋለን፡፡

**3ኛ.የቁርአኑ የተለያዩ አንቀፆች ተሰብስበው በአንድ የተጠቃለሉበት መንገድ አስቸጋሪነት ነበር (Difficulty in Collecting the Qur'anic Verses)፡-** የቁርአኑ የተለያዩ አንቀጾችን የአሰባሰቡ ሂደት አስቸጋሪ መሆኑ ብቻ ሳይሆን የተሰበሰቡበት መንገድና ሁኔታው በአጠቃላይ አሳማኝና አግባብነት የሌለው ነበር፡፡ ሐዲሱ ላይ በግለጽ እንደተመዘገበው በወቅቱ የቁርአኑን የተለያዩ አንቀጾች በቃላቸው የያዙ ሰዎች በጦርነት ተጎድተው ከመሞታቸው በፊት አንቀጾቹን እንዲሰበስብ ኃላፊነት የተሰጠው ዛይድ ነው ይህንን ያለው፡፡ የሐዲሱን ማስረጃ ቀጥሎ እናየዋለን፡፡ በ23 ዓመታት ውስጥ በመሐመድ ተቀነባብሮ የተዘጋጀው ቁርአን እንዴት አንድ ስብስብ ሊሆን ቻለ? ቁርአኑ ተሰብስቦ በአንድ ጥራዝ የተዘጋጀው መሐመድ ከሞቱ በኋላ ተከታዮቻቸው በነበሩት ከሊፋዎች አማካኝነት ነው፡፡ እነርሱ እንዴት ሊሰበስቡት እንደቻሉ የቡኻሪ ሐዲስ የሚከተለውን ታሪክ ይናገራል፡-

በያማማ ጦርነት ወቅት ቁርአንን በቃላቸው የያዙት በርካታ ሙስሊሞች መጎዳታቸውን ተከትሎ እነርሱ ከመሞታቸው በፊት አቡ በከርና ኦማር በጋራ ሆነው የቁርአን አንቀጾችን የመሰብበሰብ ኃላፊነትን ለዛይድ ጥለውበት ነበር፡፡ ዛይድም አቡ በከር «ሰዎቹ በያማማ ጦርነት በእጅጉ ተጎድተውብናል፡፡ በሌላኛውም የጦር ሜዳ ቢሆን ቁርዓኑን በቃላቸው ያጠኑት ሰዎቻችን ይሞቱብናል የሚል ፍርሃት አለኝ፡፡ ያ ከሆነ ደግሞ አንተ ካልሰበሰብክ በቀር የቁርዓኑ ብዙው ክፍል ሊጠፉብን ይችላል፡፡ ማሰባሰብ

አለብህ» በማለት የጣለበትን ኃላፊነትን ተናግሯል፡፡ ዛይድም የቆሰሉ ሰዎች በቃላቸው የያዟቸውን የቁርአን አንቀጾችን እንዴት አድርጎ እንደሚሰበሰብ ግራ ስለገባው «እስካሁን ድረስ ነቢዩ ያላደረገውን ነገር እኔ እንዴት አሁን ማድረግ እችላለሁ?» ብሎ ቢጠይቅም ከኡማር ዘንድ የተሰጠው ምላሽ «በአላህ መንገድ ይህ ጥሩ ነገር ነው» የሚል ነበር፡፡ ዛይድም ንግግሩን በመቀጠል እንዲህ አለ፡- «ኡማር ያቀረበልኝን ዕቅዱን እንድቀበለው ለማሳመን በተደጋጋሚ ጫና አደረገብኝ፡፡ አቡ በከርም ከኡማር ጋር ተቀምጦ ሳለ 'አንተ ወጣትና ብልህ ሰው ነህ፤ አንጠረጥርህም፤ አንተ ለነቢዩ የመለኮትን መገለጥ የመጻፍ ልማድ ነበረህ፡፡ ስለዚህም ቁርአኑን ፈልግና በአንድ ረቂቅ ጽሑፍ/ manuscript/ መልክ አዘጋጀው' አለኝ፡፡ የቁርአንን አሰባሰብ በተመለከተ አቡ በከር ቁርአንን እንድሰበስብ ከሚያዘኝ ይልቅ አንድን ተራራ ወደ ሌላ ቦታ እንዳንቀሳቅስ አዞኝ ቢሆን ኖሮ ለእኔ ከባድ አይሆንም ነበር፡፡ ሁለቱንም 'ነቢዩ ራሱ ያልሠራውን ነገር እንዴት ሥራ ትሉኛላችሁ?' አልኳቸው፡፡ አቡ በከርም 'በአላህ መንገድ ይህ ጥሩ ነገር ነው' አለኝ፡፡ እናም አላህ ለእነርሱ በልባቸው ግልጽ እስካደረገላቸውና የእኔንም ልብ ግልጽ እስካደረገው ድረስ በሀሳቡ ተስማማሁና የቁርአን ልዩ ልዩ ማስረጃዎችን ማስቀመጥ ጀመርኩ፡፡ ከብራና ወረቀቶች፣ ከፓልም ቅጠልና ከሰዎች ልብ ውስጥም ሰበሰብኩ፡፡ በማንም ዘንድ የትም ቦታ ያላገኘሁትን የኩዛይማህን ሁለት የሱራት አል-ተውባህ ግጥሞችን አገኘሁ፡፡» በማለት ዛይድ ስለ ሁኔታው በዝርዝር አስረድቷል፡፡ Sahih Bukhari 6:60:201 እንዲሁም ይህንኑ ታሪክ በተመሳሳይ ሁኔታ በብዙ ሐዲሶች ውስጥ ማግኘት ይቻላል፡- Sahih Bukhari 9:89:301, Sahih Bukhari 6:61:509

"Narrated Zaid bin Thabit Al-Ansari: who was one of those who used to write the Divine Revelation: Abu Bakr sent for me after the (heavy) casualties among the warriors (of the battle) of Yamama (where a great number of Qurra' were killed). 'Umar was present with Abu Bakr who said, 'Umar has come to me and said, The people have suffered heavy casualties on the day of (the battle of) Yamama, and I am afraid that there will be more casualties among the Qurra' (those who know the Qur'an by heart) at other battle-fields, whereby a large part of the Qur'an may be lost, unless you collect it. And I am of the opinion that you should collect the Qur'an." Abu Bakr added, "I said to 'Umar, 'How can I do something which Allah's Apostle has not done?' 'Umar said (to me), 'By Allah, it is (really) a good thing.' So 'Umar kept on pressing, trying to persuade me to accept his proposal, till Allah opened my bosom for it and I had the same opinion as 'Umar." (Zaid bin Thabit added:) Umar was sitting with him (Abu Bakr) and was not speaking. me). "You are a wise young man and we do not suspect you (of telling lies or of forgetful-

ness): and you used to write the Divine Inspiration for Allah's Apostle. Therefore, look for the Qur'an and collect it (in one manuscript). "By Allah, if he (Abu Bakr) had ordered me to shift one of the mountains (from its place) it would not have been harder for me than what he had ordered me concerning the collection of the Qur'an. I said to both of them, "How dare you do a thing which the Prophet has not done?" Abu Bakr said, "By Allah, it is (really) a good thing. So I kept on arguing with him about it till Allah opened my bosom for that which He had opened the bosoms of Abu Bakr and Umar. So I started locating Quranic material and collecting it from parchments, scapula, leaf-stalks of date palms and from the memories of men (who knew it by heart). I found with Khuzaima two Verses of Surat-al-Tauba which I had not found with anybody else."Sahih Bukhari 6:60:201, See Also Sahih Bukhari 9:89:301, Sahih Bukhari 6:61:509

4ኛ.ቁርአኑ በብዙ የቋንቋ ሰዋሰዋዊ ስሕተቶች /grammatical errors/ የተሞላ ስለሆነ ሊታመን አይችልም፡- ይህንን ርዕስ ከላይ በደንብ ስላየነው በዚያ ዓይነት አካሄድ አልመለስበትም፡፡ ይልቁንም የዐረብኛውን ፊደልና ንባብ ከነትርጉሙ የሚያውቁት ሙስሊሞች ቁርአኑን አይተው ፍርዱን ለመስጠት እንዲያመቻቸው በማለት የዐረብኛውን ቁርአን በእንግሊዝኛ ጽሑፍ በማድረግ ቀጥሎ በዝርዝር አስቀምጫአዋለሁ፡፡ ይህም ቁርአኑ ምን ያህል ሰዋሰዋዊ ስሕተቶች /grammatical errors/ እንዳሉት ለሙስሊሞቹ ለማሳየት በትክክል ይረዳል ብዬ ስላሰብኩ ነው፡፡

የጽሑፉ ምንጮች በውጭው ዓለም ያሉ ቀደም ብለው በእስልምናው የነበሩ ነገር ግን አሁን እስልምናውን ትተው ወደ ክርስትናው የገቡ በፊት እስልምናን ያስተምሩ የነበሩ ሰዎች ናቸው፡፡ እነዚህ የቀድሞ ሙስሊም መምህራኖች ዓለም ላይ ባሉ ኢስላም ሀገራት ላይ እየዞሩ ቁርአኑን፣ ሙዓዚንንና ሂድሰን ተፍሲርን ለበርካታ ዓመታት ሲያስተምሩ የነበሩ ናቸው፡፡ አድራሻቸውንና ማንነታቸውን መጥቀሱ ለደህንነት ሲባል አስፈላጊ ስላልሆነ ትቼዋለሁ፡፡ ለዚህ መጽሐፍ ዝግጅትም የእነዚህ ሰዎች አስተዋፅኦ እጅግ ከፍተኛ ነው፡፡ ለዚህም ነው በመጽሐፉ መግቢያ ላይ መጽሐፉን ቀድሞ ሙስሊም የነበሩ ብዙ ሰዎች በጋራ ያዘጋጁት ሥራ መሆኑን የጠቀስኩት፡፡ እነርሱ ቁርአኑንና ሐዲሱን ከእኔ ይበልጥ በደንብ ጠንቅቀው ያውቁታል፡፡ እኔ ዐረብኛ ቋንቋ አልችልም ለእነርሱ ግን የአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ነው፡፡ ስለዚህ አሁን ቀጥሎ የማቀርብላችሁን የቁርአን ሰዋሰዋዊ ስሕተቶችን የሚያሳየውን ጽሑፍ እነርሱ የዐረብኛውን ቁርአን በእንግሊዝኛ ጽሑፍ ቀይረው ያዘጋጁትን ነው፡፡ ይህንንም ማድረግ ያስፈለገው የዐረብኛውን ፊደል፣ ንባብና ትርጉም የሚያውቁት ሙስሊሞች ነገሩን እንዲመለከቱት

በማሰብ ነው፡፡ (የተሰመረበትና ወፍራም (bold) እንዲሆን የተደረገው ቃል ሰዋሰዋዊ ስሕተቱ ያለበት ሲሆን በትክክል መጻፍ የነበረበትንና ትክክለኛውን ቃል ደግሞ የጥቅሱ ማብቂያ ላይ በቅንፍ ውስጥ መግለጫ ተሰጥቶበታል)

Error 1) 5:69: "Innal-laziina 'aamanuu wal-laziina haaduu was-Saabi'uuna wan-Nasaaraa man 'aamana bilaahi wal-Yawmil-'Aakhiri wa 'amila saali-hanfalaa khaw-fun 'alay-him wa laa hum yah-zanuun." (The word Saabi'uu-na should be Saabi'iina.)

Error 2) 4:162: "Laakinir-Raasi-khuuna fil-'ilmi minhum wal-Mu'-minuuna yu'-minuuna bi-maaa 'unzila 'ilayka wa maaa 'unzila min-qablika wal-muqiimiin as-Salaata wal mu'-tuunaz-Zakaata wal-Mu'-mi-nuuna billaahi wal-Yawmil-'Aakhir: 'ulaaa 'ika sanu'-tii-him 'ajran 'aziimaa." (The word muqiimiin should be muqiimuun.)

Error 3) 20:63 "Qaaluuu inna haazaani la-saahiraani ..." (The word haazaani should be haazayn.)

Error 4) 2:177 "Laysal-birra 'an-tuwalluu wujuuhakum qibalal-Mashriqi wal-Maghrib wa laakinnal-birra man 'aamana billaahi wal-Yawmil-'Akhiri wal-malaaa-'ikati wal-Kitaabi wan-nabiyyiin: wa 'aatal-maala 'alaa hubbihii zawilqurbaa wal-yataamaa wal-masaakiina wabnas-sabiili was-saaa-'iliina wa fir-riqaab: wa'aqaamas-Salaata wa 'aataz-Zakaata; wal-muufuuna bi'ahdihim 'izaa 'aahaduu was-Saabiriina fil-ba'-saaa'i wazzarraaa-'i ..." (In the above verse there are five gramatical errors. In four of them the wrong tense was used, as the sentence begins in the present tense with the verb tuwalluu, while the other four verbs were written in the past tense: 'aamana should be tu'minuu; 'aata shoud be tu'tuu; 'aqaama should be tuqimuu; 'aata shoud be tu'tuu.)

Error 5) 3:59: "Inna massala 'Isaa 'indal-laahi ka-masali 'Adam; khalaqahuu min-turaabin-sum-ma qaala lahuu kun fa-yakuun." (The word yakuun ("is" in English) should be kana ("was") to be consistent with the past tense of the previous verb "said")

Error 6) 21:3: "Laahiyatan - quluubuhum. Wa 'asarrun-najwallaziin zal-amuu..." ( *'asarru* should be *'asarra.*)

Error 7) 22:19: "haazaani Khismani 'ikhtasamuu fi rabbihim ..." (The word 'ikhtasamuu should be 'ikhtasamaa.)

Error 8) 49:9: "wa 'in-taaa-'ifataani mi-nal-Mu'-miniinaq-tatalu fa-'aslihuu baynahumaa." (The verb 'eq-tatalu should be 'eqtatalata.)

Error 9) 63:10: "... Rabbi law laaa 'akhartaniii 'ilaaa 'ajalin-qariibin-fa-'assaddaqa wa 'akum-minas-salihiin." (The verb 'akum was incorrectly conjugated. It should be 'akuuna)

Error 10) 91:5: "was-samaaa-'i wa maa ba-naahaa." (The word maa should have been man (meaning "who"))

Error 11) 41:11: "... faqal laha wa lel-Arad 'iteya taw'aan aw karha qalata atayna ta'e'een." (ta'e'een which is used for plural should be ta'e'atain)

Error 12) 7:56: "... inna rahmata Allahi qaribun min al-mohseneen." (The word qaribun (which is masculine) should instead be qaribah (its feminine form))

Error 13) 7:160: "wa qata'nahom 'ethnata 'ashrata asbatan." (Instead of asbatan it should read sebtan. In the Arabic it literally says "twelve tribes". That is correct in English but not correct in Arabic. In Arabic it should say twelve tribe because the noun that is counted by a number above ten should be singular. This rule is observed correctly for example in 7:142, 2:60, 5:12, 9:36, 12:4.)

Error 14)......እንዲህ እየተባለ በቁርአኑ ውስጥ ያሉ በርካታ ሰዋሰዋዊ ስሕተቶችን የዐረብኛውን ጽሑፍ ለሚያውቁት ሙስሊሞች ማሳየት ይቻላል፡፡ ነገር ግን ቦታና ጊዜ ከመቆጠብ አንጻር ይህ የእስካሁኑ ከበቂም በላይ ነው፡፡ ይበልጥ ደግሞ እነርሱ ቁርአናቸውን በደንብ ቢያዩትና ቢመረምሩት የተሻለ ይሆናል፡፡ በንጹሕ ልቡና ሆነው ቁርአኑን ቢመረምሩት ያን ጊዜ መጽሐፋቸው ምን ያህል የሰዎች ቅንብር መሆኑን በትክክል ይረዱታል፡፡ በውጭው ዓለም ያሉ ሙስሊም መምህራኖች ቁርአኑን ከእንደዚህ ዓይነት ስሕተቶች ነፃ ለማድረግ ብለው ብዙጊዜ ማስተካከያዎችን ቢያደርጉበም አፅድተው ማስተካከል ግን አልቻሉም፡፡ በቁርአኑ ውስጥ አንድ ቃል ትርጉም እንዲሰጥ ለማድረግ ሲባል ብቻ በቅንፍ ( ) እየተደረጉ የተጨመሩ ቃላት እጅግ በርካታ ናቸው፡፡ እንግዲህ ከብዙ ማስተካከያዎች በኋላ እኛችን ላይ የገባው ቁርአን ይህን ያህል ስሕተቶችን ከያዘ የመጀሪያው ቁርአንማ ምን ዓይነት ይዘት ኖሮት

ይሆን? ብዙ ማሻሻያዎችን የተደረገበት የአሁኑ ቁርአን ብዙ እርስ በርሳቸው የሚጋጩ ሀሳቦችን ከያዘ የያን ጊዜው ቁርአንማ ምን መልክ ኖሮት ይሆን? (ቁርአኑ ውስጥ ያሉትን እርስ በርሳቸው የሚጋጩ ሀሳቦች ወደፊት እናያቸዋለን) ከዚህ አንጻር እነ አቡ በከር ገና ሲጀመር ቁርአን ናቸው ተብለው ከተለያዩ ቦታዎች የተሰበሰቡትን የቁርአን አንቀጾች ሰብስበው ማቃጠላቸውና እነርሱ የሚፈልጉትን ብቻ ማስቀረታቸው በጣም ትክክል ነበሩ ማለት ነው፡፡ (ይህንንም ወደፊት በደንብ እናየዋለን) ቀጥሎ ደግሞ በቁርአኑ ውስጥ ያሉት ታሪኮች ከሌሎች እምነቶች የተኮረጁ መሆናቸውንና ቁርአን መጽሐፍ ቅዱስን የሚያረጋግጥ መጽሐፍ እንደሆነ ራሱ ቁርአኑ መናገሩን በዝርዝር እናያለን፡፡

5ኛ.ሌላው ቁርአኑ ሊታመን ያልቻለበት ምክንያት በውስጡ ያሉት ታሪኮች ከሌሎች እምነቶች የተኮረጁ በመሆናቸው ነው፡- ክርስትናና እስልምና ሁለቱም ፍጹም ተቃራኒ የሆኑ ሃይማኖቶች ናቸው፡፡ ሁለት ተቃራኒ የሆኑ ነገሮች ደግሞ ስለ አንድ ነገር አንድ ዓይነት አቋምና አመለካከት ሊኖራቸው አይችልም፡፡ መኖርም የለበትም፡፡ የሁለቱም አማኞች ተዋደውና ተከባብረው መኖር ይችላሉ ነገር ግን ሃይማኖቶቹ በመሠረተ እምነታቸው ፈጽመው እስከተለያዩ ድረስ በመጽሐፎቻቸው ውስጥ ያለውም ታሪክ ፈጽሞ የተለያየ ነው መሆን ያለበት፡፡ በውስጣቸው በአንድ ርዕሰ ጉዳይ ላይ አንድ ዓይነትና ተመሳሳይ ታሪክ መኖር የለበትም፡፡ የሆነው ግን ይህ አይደለም፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስና በቁርአን በሁለቱም ላይ የአንድ ሰው ታሪክ በአንድ ዓይነት አቀራረብ ተመዝግቦ ይገኛል፡፡ ይህን ጊዜ ነው «ለምን?» ብሎ መመርመር የሚያስፈልገው፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ብሉይ ኪዳን ላይ ያሉ ታሪኮች ቁርአንም ውስጥ አሉ፡፡ ይህ እንዴት ሊሆን ቻለ?

መልሱ ቀላል ነው፡፡ ለጊዜው የብሉይ ኪዳኑን ዘመን እንተወውና በክርስቶስ የተመሠረተው የሐዲስ ኪዳን ክርስትናና በመሐመድ የተመሠረተው እስልምና በትንሹ የ600 ዓመት ልዩነት አላቸው፡፡ ክርስቶስ ካረገ በኋላ በ570 ዓ.ም ተወልደው ከ622 ዓ.ም በኋላ ነው መሐመድ እስልምናን የመሠረቱት፡፡ መቼም ካልነበረና ገና ወደፊት ከሚኖር ነገር ላይ ተገልብጦ አይወሰድምና ታሪኮቹን መጽሐፍ ቅዱስ ከቁርአን ገልብጦ ወስዷል ብሎ ማሰብ አይቻልም፡፡ ስለዚህ እርግጠኞች ሆነን መናገር የምንችለው ነገር ታሪኮቹን ቁርአን በትንሹ 600 ዓመት ከሚቀድመው ከመጽሐፍ ቅዱስ ገልብጦ ወስዷል፡፡ ጠብቁኝ ይህንን በደንብ አረጋግጥላችኋለሁ! በጣም የሚገርመው ሌላው ቢቀር በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉትን ቅዱሳን ቁርአኑ ታሪካቸውን ገልብጦ ሲወስድ ለየት ያለ የስም ለውጥ እንኳን አላደረገባቸውም፡፡ የመጽሐፍ ቅዱሱን ሙሴን ቁርአኑ ሙሳ ብሎ ነው የቀየረው፡፡ ሌሎቹንም እንዴት እንደቀየራቸው ቀጥሎ ተመልከቱ፡-

አዳምን አደም፣ ሔዋንን ሐዋ፣ አብርሃምን ኢብራሂም፣ ኖኅን ኑኅ፣ ዳዊትን ዳውድ፣ ሰለሞንን ሱለይማን፣ ሎጥን ሉጥ፣ ዮናስን ዩኑስ፣ ይስሐቅን ኢስሐቅ፣ ኤልያስን ኢልያስ፣ እስማኤልን ኢስማዒል፣ ያዕቆብን ያዕቁብ፣ ዮሴፍን ዩሱፍ፣ አሮንን ሀሩን...... የሐዲስ ኪዳኖቹንም መጥምቁ ዮሐንስን የሕያ ሲለው አባቱን ዘካርያስን ደግሞ ዘከሪያ፣ ገብርኤልን ጂብሪል፣ ሚካኤልን ሚካል፣ ድንግል ማርያምን መሪየም፣ ኢየሱስን ዒሳ በማለት ቁርአኑ ያን ያህል የተለየ የስም ለውጥ እንኳን አላደረገም። ታሪካቸው በቁርአኑ ውስጥ የተቀመጠው የታሪክ ፍሰቱን ባልጠበቀ መልኩ ከመሆኑም በላይ ሐሰተኛና ትርጉም አልባ በሆኑ ክስተቶች ነው ታሪኮቹ የተቋጩት።

ለዚህም ማሳያ ይሆን ዘንድ አንድ ምሳሌ አንስተን ማየት እንችላለን። ሙሴ ከግብፅ በስደት በሄደባት በምድያም ምድር የአማቱን የካህኑ ዮቶርን በጎች እረኛ ሆኖ እየጠበቀ ሳለ ነበር ሕዝበ እስራኤልን ከፈርኦን እጅ አላቆ ከግብፅ ሀገር መርቶ እንዲያወጣ በእግዚአብሔር የተጠራው። ካህኑ ዮቶር ሌላ ስሙ ራጉኤል ይባላል። ሊቀ ነቢያት ሙሴ በፈርኦን ቤት ልጅ ሆኖ ቢያድግም በኋላ በባርነት ስለተያዙት ሕዝቦቹ ቅናት አደረበትና አንዱን ግፍ ሲፈጽም የነበረን ግብፃዊ ገድሎ በስደት የሄደባት የምድያም ምድር የዛሬዋ ኢትዮጵያ ናት። ይህ እንዴት ይታወቃል ቢሉ መጽሐፍ ቅዱሱ ይመሰክራልና ነው። አንድም በዘኊ 12፡1 ላይ «ሙሴም ኢትዮጵያይቱን አግብቷልና ባገባት በኢትዮጵያይቱ ምክንያት ማርያምና አሮን በእርሱ ላይ ተነጋገሩ» ተብሎ እንደተጻፈ ሁለትም በዘጸ 2፡21 ላይ «ለምድያምም ካህን ሰባት ሴቶች ልጆች ነበሩት... ሙሴም ከዚያ ሰው ጋር ሊቀመጥ ወደደ፤ ልጁንም ሲፓራን ለሙሴ ሚስት ትሆነው ዘንድ ሰጠው። ወንድ ልጅም ወለደች» ተብሎ ስለተጻፈ ሙሴ ከፈርኦን ሸሽቶ በስደት የሄደባት የምድያም ምድር የዛሬዋ ኢትዮጵያ ናት መባሉን መጽሐፍ ቅዱሱ በዚህ መልኩ አስረግጦ ስለነገረን ከዚህ ሌላ ምንም ማስረጃ አያስፈልገንም። ይበልጥ ደግሞ መጽሐፍ ቅዱስን ግለጹትና ዘጸ 2፡11-25 እና ዘኊ 12፡1-12 ላይ ያለውን በደንብ አንብቡት።

ይልቅስ እግረ መንገዴን እኔን በጣም ያስገረመኝን አንድ ነገር ማንሳት ፈለግሁ። ሙሴ ማለት ከክርስቶስ ልደት ከ1300 ዓመት በፊት የነበረ ነቢይ ነው። በሙሴ ጊዜም ሆነ ከዚያ በፊት ኢትዮጵያ ውስጥ እግዚአብሔርን የሚያገለግል ካህን ነበረ። ይህ ደግሞ ኢትዮጵያ ከክርስትናው ጋር ምን ያህል ጥልቅና የተሳሰረ ታሪክ እንዳላት ያሳያል። በዘጸ 18፡13-27 ላይ ያለውን ታሪክ በደንብ ብታዩት ሙሴ ሕዝበ እስራኤልን ከግብፅ ሲያወጣ ሕዝቡን እንዴት አድርጎ መምራት እንዳለበት ምክርና መመሪያ የሰጠው ኢትዮጵያዊው ካህኑ አማቱ ዮቶር ነው። ያን ጊዜ ካህኑ ለሙሴ የሰጠው ምክርና

መመሪያ ዛሬ በዘመናዊው ትምህርት «የሕዝብ አስተዳደር» "public administration" የምንለው ነው፡፡ ዘጸ 18፡13-27 ሙሉውን ስታነቡት ይህን ታረጋግጣላችሁ፡፡ ታዲያ ይህ ታሪክ ቁርአኑ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚገኙ ታሪኮችን ቀድቶ (copy አድርጎ) ወስዷል ካልከው ጋር በምን ይገናኛል? እንዳትሉኝ፤ ልመጣበት ነው፡፡ በዚያውም ኢትዮጵያና አምልኮተ እግዚአብሔር ይህን ያህል የተቆራኘ ታሪክ እንዳላቸው እንድናውቀው ብዬ ነው፡፡ አሁን በዋናነት ለማሳየት ወደፈለኩት ነጥብ ልምጣ፡፡ ወደ ቁርአኑ ከመግባታችን በፊት ከቁርአኑ ጋር ለማስተያየት እንዲያመቸን ስለሚረዳን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በኦሪት ዘጸአት ላይ ከምዕራፍ 2 ቁ.11 ጀምሮ እስከ ምዕራፍ 3 ቁ.12 ድረስ ያለውን ታሪክ ቀጥሎ በደንብ ተመልከቱት፡፡

«በዚያም ወራት እንዲህ ሆነ፤ ሙሴ ጎበዝ በሆነ ጊዜ ወደ ወንድሞቹ ወጣ፥ የሥራቸውንም መከራ ተመለከተ፤ የግብፅም ሰው የወንድሞቹን የዕብራውያንን ሰው ሲመታ አየ። ወዲህና ወዲያም ተመለከተ፥ ማንንም አላየም፥ ግብፃዊውንም ገደለ፥ በአሸዋም ውስጥ ሸሸገው። በሁለተኛውም ቀን ወጣ፥ ሁለቱም የዕብራውያን ሰዎች ሲጣሉ አየ፤ በዳዩንም ለምን ባልንጀራህን ትመታዋለህ? አለው። ያም በእኛ ላይ አንተን አለቃ ወይስ ዳኛ ማን አደረገህ? ወይስ ግብፃዊውን እንደ ገደልኸው ልትገድለኝ ትሻለህን? አለው። ሙሴም በእውነት ይህ ነገር ታውቆአል ብሎ ፈራ። ፈርዖንም ይህን ነገር በሰማ ጊዜ ሙሴን ሊገድለው ፈለገ። ሙሴ ግን ከፈርዖን ፊት ኰበለለ፥ በምድያምም ምድር ተቀመጠ፤ በውኃም ጉድጓድ አጠገብ ዐረፈ። ለምድያምም ካህን ሰባት ሴቶች ልጆች ነበሩት፤ እነርሱም መጥተው ውኃ ቀዱ፥ የአባታቸውንም በጎች ሊያጠጡ የውኃውን ገንዳ ሞሉ። እረኞችም መጥተው ገፉአቸው፤ ሙሴ ግን ተነሥቶ ረዳቸው፥ በጎቻቸውንም አጠጣላቸው። ወደ አባታቸው ወደ ራጉኤልም በመጡ ጊዜ ስለ ምን ዛሬ ፈጥናችሁ መጣችሁ? አላቸው። እነርሱም አንድ የግብፅ ሰው ከእረኞች እጅ አዳነን፥ ደግሞም ቀዳልን፥ በጎቻችንንም አጠጣ አሉ። ልጆቹንም እርሱ ወዴት ነው? ለምንስ ያንን ሰው ተዋችሁት? ጥሩት እንጀራም ይብላ አላቸው። ሙሴም ከዚያ ሰው ጋር ሊቀመጥ ወደደ፤ ልጁንምሲፓራን ለሙሴ ሚስት ትሆነው ዘንድ ሰጠው። ወንድ ልጅም ወለደች። በሌላ ምድር መጻተኛ ነኝ ሲል ስሙን ጌርሳም ብሎ ጠራው። ከዚያም ከብዙ ቀን በኋላ እንዲህ ሆነ፤ የግብፅ ንጉሥ ሞተ፤ የእስራኤልም ልጆች ከባርነት የተነሣ አለቀሱ፥ ጮኹም፥ ስለ ባርነታቸውም ጩኸታቸው ወደ እግዚአብሔር ወጣ። እግዚአብሔርም የለቅሶአቸውን ድምፅ ሰማ፥ እግዚአብሔርም ከአብርሃምና ከይስሐቅ ከያዕቆብም ጋር ያደረገውን ቃል ኪዳን አሰበ። እግዚአብሔርም የእስራኤልን ልጆች አየ፥ እግዚአብሔርም በእነርሱ ያለውን ነገር አወቀ። ሙሴም የዮቶርን የአማቱን

የምድያምን ካህን በጎች ይጠብቅ ነበር፤ ወደ ምድረ በዳ ዳርቻም በጎቹን ነዳ፥ ወደ እግዚአብሔርም ተራራ ወደ ኮሬብ መጣ። የእግዚአብሔርም መልአክ በእሳት ነበልባል በእሾህ ቍጥቋጦ መካከል ታየው፤ እነሆም ቍጥቋጦው በእሳት ሲነድድ ቍጥቋጦውም ሳይቃጠል አየ። ሙሴም ልሂድና ቍጥቋጦው ስለ ምን አልተቃጠለም ይህን ታላቅ ራእይ ልይ አለ። እግዚአብሔር እርሱ ይመለከት ዘንድ እንደ መጣ ባየ ጊዜ እግዚአብሔር ከቍጥቋጦው ውስጥ እርሱን ጠርቶ። ሙሴ፥ ሙሴ ሆይ አለ። እርሱም እነሆኝ አለ። ወደዚህ አትቅረብ፤ አንተ የቆምህባት ስፍራ የተቀደሰች መሬት ናትና ጫማህን ከእግርህ አውጣ አለው። ደግሞም እኔ የአባትህ አምላክ፥ የአብርሃም አምላክ የይስሐቅም አምላክ የያዕቆብም አምላክ ነኝ አለው። ሙሴም ወደ እግዚአብሔር ያይ ዘንድ ፈርቶአልና ፊቱን ሸፈነ። እግዚአብሔርም አለ፥ በግብፅ ያለውን የሕዝቤን መከራ በእውነት አየሁ፥ ከአስገባሪዎቻቸውም የተነሣ ጩኸታቸውን ሰማሁ፤ ግብፃውያንም የሚያደርጉባቸውን ግፍ ደግሞ አየሁ። አሁንም ና፥ ሕዝቤን የእስራኤልን ልጆች ከግብፅ ታወጣ ዘንድ ወደ ፈርዖን እልክሃለሁ። ሙሴም እግዚአብሔርን ወደ ፈርዖን የምሄድ የእስራኤልንም ልጆች ከግብፅ የማወጣ እኔ ማን ነኝ? አለው። እርሱም በእውነት እኔ ከአንተ ጋር እሆናለሁ፤ እኔም እንደ ላክሁህ ምልክትህ ይህ ነው፤ ሕዝቡን ከግብፅ ባወጣህ ጊዜ...›› እያለ መጽሐፍ ቅዱስ ታሪኩን በዝርዝር ይነግረናል፡፡

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያለውን ይህንን የሙሴን ታሪክ ቁርአኑ እንዴት አድርጎ መስመሩን በሳተና በተበላሸ ሁኔታ እንደገለበጠው (copy እንዳደረገው) ቀጥሎ እናያለን፡፡

በቁርአኑ 28፡22 ጀምሮ እንዲህ ተብሎ ነው የተጻፈው፡- ‹‹ሙሳም ወደ ምድየን አቅጣጫ ፊቱን ባዞረ ጊዜም ጌታዬ ቀጥተኛውን መንገድ ሊመራኝ እከጅላለሁ አለ፡፡ ወደ ምድየንም ውሃ በመጣ ጊዜ በርሱ ላይ ከሰዎች ጭፍሮችን የሚያጠጡ ሆነው አገኘ፤ ከነሱ በታችም ሁለት ሴቶችን አገኘ፡፡ ከሁለቱ አንደኛይቱም አባቴ ሆይ ቅጠረው ከቀጠርከው ሰው ሁሉ በላጩ ብርቱው ታማኙ ነውና አለችው፡፡ ሙሳም ጊዜውን በጨረሰና ከቤተሰቦቹ ጋር በሄደ ጊዜ ከጡር ተራራ ጎን እሳትን አየ፤ ለቤተሰቡ እዚሁ ቆዩ፤ እኔ እሳትን አየሁ፤ ከርሷ ወሬን ወይም ትሞቁ ዘንድ የተለኮሰ ችቦን አመጣላችኋለሁ አለ፡፡ በመጣትም ጊዜ ከሸለቆው ቀኝ ዳርቻ ከዛፊቱ በኩል በተባረከችው ስፍራ ውስጥ ሙሳ ሆይ! እኔ የዓለማት ጌታ አላህ ነኝ በማለት ተጠራ›› እያለ ይቀጥላል ቁርአኑ፡፡ ታሪኩ በተመሳሳይ ሁኔታ በድጋሚ 27፡8-15 እና 20፡9-20 ላይም ተጽፎ ይገኛል፡፡

በእስልምናው እምነት ይህ የሙሴ ታሪክ ትርጉሙ ምንድው? እንዲያው ዝም ብሎ ይህን አደረገ ብሎ ትረካ ተርኮ ከማለፍ ውጭ ምን ምሥጢር አለው? በታሪኩ ውስጥ ማሳየትና ማስተላለፍ የተፈለገው መልእክትስ ምንድው? እስልምናው ለእነዚህና ሌሎችም ተያያዥ ጥያቄዎች መልስ የለውም፡፡ ታሪኩን ዝም ብሎ በታሪክነቱ ብቻ ነው ያስቀመጠው፡፡

በክርስትናው ግን እያንዳንዱ ክስተት የጠለቀ ምሥጢርና ትርጉም አለው፡፡ ብሉይ ኪዳን ለሐዲስ ኪዳን ምሳሌ ስለሆነ በዘመነ ብሉይ የተፈጸሙ ነገሮች ሁሉ በሐዲስ ኪዳን ለተገለጠው ክርስቶስ ምሳሌና ትንቢት ናቸው፡፡ ክርስቶስ ወደዚህች ምድር የመጣው ድንገት እንደ እንግዳ ደራሽ፣ እንደ ውሃ ፈሳሽ ሳይሆን ቀድሞ ነቢያትን ትንቢት አናግሮ፣ ሱባኤ አስቆጥሮና በብዙ ምሳሌዎች ራሱን ገልጦ ነው፡፡ ስለዚህ ሙሴ የክርስቶስ ምሳሌ ሲሆን ግብፅ የሲኦል ምሳሌ ናት፡፡ ሙሴ በግብፅ ሳለ ለወገኖቹ አግዞ የገደለው ግብፃዊው ሰው የዲያብሎስ ምሳሌ ነው፡፡ «በአሸዋም ውስጥ ሸሸገው» ያለው የመስቀሉ ምሳሌ ነው፡፡ የአዳም ልጆች ምሳሌ በሆኑት በእስራኤላውያን ላይ መከራ ያፀኑባቸው የነበሩ ግብፆች የኢጋንንት ምሳሌ ናቸው፡፡ ሕዝበ እስራኤልን ግብፆች መከራ ሲያፀኑባቸው ሙሴ የሕዝቦቹን መከራ አይቶ በማዘን ግብፃዊው ገድሎ በአሸዋ መቅበሩና በኋላም ከግብፅ ምድር ተሰዶ ሕዝቦቹን ከግብፅ ባርነትና አሽከርነት ነፃ ማውጣቱ መድኃኔዓለም ክርስቶስ በከፉ ኢጋንንት የአዳምን ልጆች የደረሰባቸውን ስቃይና በደል ተመልክቶ አዝኖላቸው ከዙፋኑ ወርዶ ሞቶ ሰይጣንን በመስቀሉ ገድሎ የአዳምን ልጆች ሁሉ ከሲኦል እስራት ነፃ የማውጣቱ ምሳሌ ነው፡፡ ውስጡ ሌሎች ብዙ ምሥጢራት አሉት፡፡ ስለዚህ ቁርአኑ ውስጥ ዝም ብለው እንደልጆች ተረት በታሪክነታቸው ብቻ ተጽፈው የተቀመጡት ታሪኮች በክርስትናው ውስጥ ግን እጅግ የጠለቀ ምሥጢርና ትርጉም ነው ያላቸው፡፡

ሙሴ «እነሆም ቍጥቋጦው በእሳት ሲነድድ ቍጥቋጦውም ሳይቃጠል አየ» ተብሎ የተነገረውም እንዲሁ ታላቅ ምስጢር አለው፡፡ ቁርአኑ እንደሚለው ሙሴ ወደ እሳቱ ሄዶ ወሬን ወይም ቤተሰቡ የሚሞቀው የችቦ እሳት አላመጣም ሊያመጣም አይችልም፡፡ ይልቁንም ያቺ ነደ እሳት ሰፍሮባት፣ በነደ እሳት ተከባ ሳለ ነገር ግን ቈጥቋጧ ምንም ሳይቃጠሉ ሙሴ ያያት ያቺ ዕፅ የድንግል ማርያም ምሳሌ ናት፡፡ ሙሴ በግልጽ ያየው ነበልባል ከሐመልማል፣ ሐመልማል ከነበልባል ጋር ተዋሕዶ፣ ነበልባሉ ሐመልማሉን ሳያቃጥለው፤ ሐመልማሉ ነበልባሉን ሳያጠፋው ነው፡፡ ይህንንም ምስጢር በደንብ ለመረዳት ወደዚያ ሲጠጋ እግዚአብሔር ከቁጥቋጦው ውስጥ ሆኖ በመጣራት ጫማውን ከእግሩ እንዲያወልቅ ነግሮታል፡፡ የዚህ ምሳሌው ለጊዜው ሐመልማል

የተባለ የሕዝበ እስራኤል የመከራቸው ምሳሌ ነው፡፡ ሐመልማሉ ነበልባሉን ያለማጥፋቱ እስራኤልም መከራውን ንስሐ ገብተን ቀኖና ይዘን እናርቀው አለማለታቸውን ሲያጠይቅ፤ ነበልባሉ ሐመልማሉን ሳያቃጥል መታየቱ የግብፅ መከራ እስራኤልን ጨርሶ አለጠፋቸውምና ይህን ሲያጠይቅ ነው፡፡ ፍጻሜው ግን ነበልባሉ የክርስቶስ፣ ሐመልማሉ ደግሞ የድንግል ማርያም ምሳሌ ነው፡፡ ነበልባሉ ሐመልማሉን እንዳላቃጠለው ሁሉ እሳተ መለኮት ክርስቶስም 9 ወር ከ5 ቀን በማሕፀኗ ባደረ ጊዜ ድንግል ማርያምን ባሕርየ መለኮቱ አላቃጠላትም፤ ሐመልማሉ ነበልባሉን እንዳላጠፋው ሁሉ ክርስቶስም ከቅድስት ድንግል ማርያም ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍሷ ነፍስ ነስቶ ሰው ቢሆንም መለኮትነቱ አልተለወጠም፡፡ አንድም ሙሴ ያየው የነበልባል የሐመልማል ተዋሕዶ የመለኮትና የሥጋ ተዋሕዶ ምሳሌ ነው፡፡ ነበልባሉ ሐመልማሉን እንዳላቃጠለው ሐመልማሉ ነበልባሉን እንዳላጠፋው ሁሉ ምልአቱን፣ ስፋቱን፣ ርቀቱን ሳይተው ሥጋም ግዙፍነቱን ሳይተው የመዋሐዳቸው አንድ አካል አንድ ባሕርይ የመሆናቸው ምሳሌ ነው፡፡

ይህንን በእርግጥ እውነተኞቹ ክርስቲያኖች ጠንቅቀው ያውቁታል፡፡ ነገር ግን ይህን የመሰለ ጥልቅ ምስጢርና ትርጉም ያለውን የሙሴን ታሪክ መሐመድ በቁርአናቸው ላይ ገልብጠው ወስደው በእንዴት ዓይነት አስከፊ ሁኔታ እንደተጠቀሙበት ማሳየት ስለፈለኩ ነው ይህን ያነሳሁት፡፡ በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ብሉይ ኪዳን ላይ ያሉ የቅዱሳን ታሪኮች ሁሉ በቁርአኑ ውስጥ የተቀመጡት የታሪክ ፍሰታቸውን ባልጠበቀ መልኩ ከመሆኑም በላይ ሐሰተኛና ትርጉም አልባ በሆኑ ክስተቶች ነው ታሪኮቹ የተቋጩት፡፡ የራስ ያልሆነ ገንዘብ አንድ ቀን እንደተሰረቀ መታወቁ አይቀርም፡፡ እውነት ስትመረመር ሐሰት በራሷ ጊዜ ይፋ መውጣቷ አይቀርም፡፡ ነቢያቸው መሐመድም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያለውን ነገር ንባቡን እንጂ ምሥጢሩን መስረቅ ስላልቻሉ ሐሰተኛነታቸው በገሃድ ሊታወቅባቸው ችሏል፡፡ ቁርአናቸው የአንዳንዶቹን ታሪክ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንደተጻፈው አድርጎ ይጀምረውና የሆነ ቦታ ላይ አካሄዱንና ይዘቱን ይለውጠዋል፡፡ ከላይ ያየነው የሙሴ ታሪክ የዚህ አንድ ማሳያ ነው፡፡ ከዚህ በተለየ ሁኔታ ግን ቁርአኑ ጆሮን ጭው የሚያደርጉ ውሸቶችንም ከክርስትናው ጋር እያገናኘ ይናገራል፡፡ ለምሳሌ ከዚህ በፊት እንዳየነው ክርስቲያኖቹ ምን ብለው ነው የሚያምኑት የሚለውን ነገር እንኳን በቅጡ አያውቀውም፡፡ ድንግል ማርያምን ከሦስቱ ሥላሴ አንዷ ናት ብሎ ማቅረቡ ፈጽሞ በክርስትናው የሌለ ነው፡፡ «ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ ነው» የሚለውን መሠረታዊና ዋነኛ የክርስትና ትምህርት ቁርአኑ የሚረዳው ባልና ሚስት አንሶላ

ተጋፊው በግብረ ሥጋ ግንኙነት እንደወለዱት አድርጎ ነው፡፡ በክርስትናው ግን ፈጽሞ እንዲህ አይደለም፡፡ (ዝርዝሩን በገጽ---ላይ ይመልከቱ፣ ወደፊት የእውነተኛውን ክርስትና ትምህርትም በደንብ እናየዋለን) አሁን ግን ለማሳየት የፈለኩት ቁርአኑ የአንዳንዶቹን ታሪክ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንዳለው አድርጎ ይጀምርና የሆነ ቦታ ላይ አካሄዱንና ይዘቱን ሲለውጥ በሌላ በኩል ደግሞ ጆሮን ጭው የሚያደርጉ ውሸቶችን ከክርስትናው ጋር እያገናኘ መናገሩን ነው፡፡ የተወሰኑትን ለማየት ያህል፡-

እንደ ቁርአኑ አገላለጽ ሰይጣን ከገነት የተባረረው ለአዳም አልሰግድም ብሎ ነው (18፡50)፤ አዳምና ሔዋን ከገነት ከተባረሩ በኋላ ምህረትን ስለለመኑ በሕይወት ኑሩ ተብለው በመሬት ኖሩ እንጂ ወደ ገነት ተመልሰው እንደገቡ ቁርአኑ አይናገርም (7፡11-27፣ 20፡115-122፣ 38፡71-85፣ 2፡30-37)፤ አብርሃም ካዕባ የተባለውን ቤተ ጣኦት በመካ እንደገነባ እና የዐረብ ነቢይ ከመገለጥ ጋር እንዲመጣ እንደጸለየ ቀርአኑ ይናገራል (3፡96፣ 2፡125-131፣ 22፡26)፤ ከዚህም ሌላ ቁርአኑ የሙሴ እኅት ማርያምንና የጌታን እናት ድንግል ማርያምን አንድ እንደሆኑ መናገሩ፣ ኢዮብ ሚስቱን እንደበደባት መናገሩ፣ በሙሴ ጊዜ ሰማርያ የሚባል ስምና ቦታ ባልነበረበት ወቅት ቁርአኑ ግን የወርቁን ጥጃ የሠሩት ሰማርያውያን እንደሆኑ መናገሩ፣ ንጉሡ ሰለሞን ከወፎች ጋር ቃል በቃል እንደተነጋገረ፣ ሰይጣን ከገነት ውስጥ የተባረረው ለአዳም አልሰገደም ብሎ መሆኑን ቁርአኑ መናገሩ፣ ኢየሱስ ስለ መሐመድ መምጣት ትንቢትን እንደተናገረ አድርጎ ቁርአኑ ይናገራል፡፡ ኢየሱስም አልተሰቀለም በእርሱ ተመሳስሎባቸው ሌላ ሰው ነው የሰቀሉት በማለት ይናገራል፡፡ 4፡157፡፡ በሱረቱ መሪየም 19፡16-35 ላይም ስለ ድንግል ማርያም ሲናገር ልጇን ለመፀነስ እርሷ ወደ ሩቅ ስፍራ እንደሄደች፣ ምጥም በጀመራት ጊዜ ከዘንባባ ዛፍ ስር እንደተኛች፣ በምጡ ሕመም ምክንያት ይህ ከመሆኑ በፊት በሞትኩ ኖሮ የተረሳም ነገር በሆንኩ ኖሮ በማለት እንደተናገረች፣ የማታውቀውም ድምፅ እርሷን በመልካም ዜና እንዳፅናናትና እንድትጠጣውም ተብሎ ወንዝ በአጠገቧ እንዲያልፍ እንደተደረገላት እንዲሁም የዘንባባውን ዛፍ ብትወዘውዘው ቴምር እንደሚረግፍላትና እንደምትበላ ተነግሯታል በማለት ይናገራል፡፡ ቁርአኑ እነዚህንና ሌሎችንም ብዙ አዳዲስ አስቂኝና አሳዛኝ ፈጠራዎችን ይዟል፡፡ ነገር ግን እነዚህ ነገሮች በክርስትናው ፈጽሞ የሌሉ ነገሮች ከመሆናቸውም በላይ አሳዛኝ የፈጠራ ተረቶች ናቸው፡፡

በመሐመድ በተነሡበት ዘመን እነዚህንና መሰል ትምህርቶቻቸውን ለክርስትያኖችና ለአይሁዶች ይዘው በመምጣት ለማስተማር ሞክረው ነበር ነገር ግን እነርሱ ፈጽሞ ሊቀበሏቸው አልቻሉም፡፡ መሐመድ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉ ታሪኮችን ሲፈልጉ

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ካለው ጋር አመሳስለው፣ ሲፈልጉ ይዘቱን በተወሰነ መልኩ ብቻ ቀየር አድርገው፣ ሲፈልጉ በወቅቱ የነበሩ የመናፍቃንን ትምህርትና የራሳቸውን ምኞትና ፈጠራዎች ጨምረው ነበር ሲያስተምሩ የነበረው፡፡ አሁን በቁርአኑ ውስጥ ተጽፎ ያለውም ይኸው ነው፡፡ መሐመድ እነዚያን ዝብርቅርቅና ትርጉም አልባ ታሪኮችን ከክርስቲያኖቹ መጽሐፍ በተሳሳተ መንገድ ቀድተውና ኮርጀው መስመራቸውን በሳተ መልኩ ማስተማራቸው በክርስትያኖችና በአይሁዶች ዘንድ ቀተባይትን ስላሳጣቸው ጂሃድን የመፍትሄ አካል አድርገው በወቅቱ በመዲናና አካባቢዋ ያሉ አይሁዶችንና በሌላም ቦታ ያሉ ክርስቲያኖችን ሊያጠፉ ችሏል፡፡ በእነርሱ ዘንድ ተቀባይነትን እንዳላገኙ ሲያውቁ በ2ኛ ደረጃ ምን አደረጉ መሰላችሁ? መሐመድ ከሌሎች እምነቶች በኮረጁት ትምህርት ምክንያት ከተፈጠረባቸው አለመረጋጋትና ከዚህም አስቸጋሪ መምታታት ውስጥ ለመውጣት ሲሉ ከጂሃድ ቀጥሎ የነበራቸው ብቸኛ አማራጭ «ክርስትያኖችንና አይሁዶችን መጽሐፍ ቅዱስን ለውጠውታል» የሚል ወቀሳና ክስ ማቅረብ ነበር፡፡ ይህን ወቀሳና ክስ አሁንም ያሉት ሙስሊሞች ያቀርቡታል፡፡ እነዚያን ቁርአን ግልብጥብጣቸውን ያወጣቸውና ትርጉም አልባ ያደረጋቸው ታሪኮች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተጻፉትኮ መሐመድ ከመወለዳቸው ቢያንስ ከ600 ዓመት በፊት ነው፡፡ ለዚያውም የሐዲስ ኪዳኑን ብቻ ወስደን ነው፡፡ ታዲያ እንዴት በፊት የነበረው ነገር ገና ወደፊት ከስንት መቶ ዓመት በኋላ ከሚመጣ ነገር ላይ ለውጥ ሊያደርግ ይችላል? እንዲህስ ብሎ የሚያስብ ምን ዓይነት አእምሮ ነው? ደግሞ ለውጠውታል ከተባለ ለምንድን ነው ቁርአኑ መሐመድንም ሆነ ሙስሊሞችን ስለ እስልምናው በመጠራጠር ውስጥ ቢሆኑ የመጽሐፉን ሰዎች ማለትም ክርስትያኖችንና አይሁዶችን እንዲጠይቁ ያዘዛቸው? (ቁርአኑ ሙስሊሞች ክርስቲያኖችን ጠይቀው እውነቱን እንዲረዱ ያዘዘ መሆኑን በቀጣዩ ርዕስ ላይ በደንብ እናየዋልን፡፡) ታዲያ እውነትን ለማወቅ እንዴት ከተለወጠ ነገር አረጋግጡ ይባላል? ምንም ይባል ምን የቱንም ያህል ከንቱ ምክንያት ይቅረብ ካልነበረና ገና ወደፊት ከሚኖር ነገር ላይ ገልብጦ ወስዶ ለውጥ ማድረግ አይቻልም፡፡ ፈጽሞ ሊሆንና ሊታሰብ የማይችል ነገር ነው፡፡ ሙስሊም ወገኖቻችን «መጽሐፍ ቅዱስ ተለውጧል» እያሉ በነፍሳቸው ለዘላለም ከሚሞቱ ይልቅ የራሳቸውን አእምሮ ለውጠው ወደ ሕይወት እንዲመጡ ከልብ ልንጸልይላቸው ይገባል በእውነት!!!

6ኛ.ቁርአኑ ታማኝ ካልሆነባቸው ምክንያቶች ውስጥ አንዱ መጽሐፍ ቅዱስን አረጋግጣለሁ ማለቱ ነው፡- እስካሁን እንዳየነው ቁርአን መቼም ቢሆን መጽሐፍ ቅዱስን ሊያረጋግጥ አይችልም፡፡ ግን ደግሞ ምንም እንኳን ሊያረጋግጠው ባይችልም ቁርአኑ በራሱ መጽሐፍ ቅዱስን አረጋግጣለሁ ብሎ ተቃራኒው ነኝ ለሚለው የክርስቲያኖች መጽሐፍ ዕውቅና መስጠቱ ነገሩን አስገራሚም አስቂኝም ያደርገዋል፡፡ ቁርአኑ ይህንን በግልጽና በድፍረት ነው የሚናገረው፡፡ «ወደ አንተም መጽሐፉን ከበፊቱ ያለውን መጽሐፍ አረጋጋጭና በርሱ ላይ ተጠባባቂ ሲሆን (ቁርአንን) በእውነት አወረድን» ይላል፡፡ ሱረቱ አል-ማኢዳህ 5፡48፡፡ ተመሳሳይ የሆኑ አገላለጾችን ቁርአኑ ላይ ብዙ ቦታ ተጽፈው እናገኛለን፡፡ ለምሳሌ፡-

«ቁርአን የሚቀጣጠፍ ወሬ አይደለም፤ ግን ያንን በስተፊቱ ያለውን አረጋጋጭ፣ ለነገርም ሁሉ ገላጭ ነው» (12፡111) ፤ «አላህ አወረደው በላቸው፡፡ ያንንም በፊቱ የነበረውን መጽሐፍ አረጋጋጭ መጽሐፍ ነው» (6፡92)፤ «እናንተ መጽሐፉ የተሰጣችሁ ሆይ! ከናንተ ጋር ያለውን የሚያረጋግጥ ሆኖ ባወረድነው ቁርአን እመኑ» (4፡47)፤ «ከእነርሱም ጋር ያለውን መጽሐፍ አረጋጋጭ የሆነ መጽሐፍ ከአላህ ዘንድ በመጣላቸው ጊዜ…» (2፡89)፣ «ቁርአን ከእነርሱ ጋር ላለው መጽሐፍ አረጋጋጭ እውነተኛ ሲሆን ይክዳሉ» (2፡91)፤ «ቁርአኑን ከበፊቱ ለነበሩት መጻሕፍት አረጋጋጭ ለምእመናን መሪና ብስራት ሲሆን በአላህ ፈቃድ በልብህ ላይ አውርዶታል» (2፡97)፤ «እነርሱ ጋር ላለው መጽሐፍ አረጋጋጭ የሆነ መልክተኛ ከአላህ ዘንድ በመጣ ጊዜ…» (2፡101)፣ «ከርሱ በፊት ያሉትን መጻሕፍት የሚያረጋግጥ ሲሆን ቁርአንን ባንተ ላይ ከፋፍሎ በእውነት አወረደ» (3፡3)፤ «ያም ከመጽሐፉ ወዳንተ ያወረድንልህ ከበፊቱ ላለው አረጋጋጭ ሲሆን እርሱ እውነት ነው» (35፡31) እንዲሁም 10፡37፣ 46፡12፣ 46፡30፣ 5፡43፣ 3፡81፣ 37፡37 ይመልከቱ፡፡

አሁን ደግሞ ወጣ ያለ አንድ አስቂኝ የቁርአን ጥቅስ ላሳያችሁ ነው፡፡ በሱረቱ አል-ኒሳእ 4፡157 ላይ «የመሪየምን ልጅ አልመሲህ ዒሳን ገደልን በማለታቸውም ረገምናቸው፤ አልገደሉትም፤ አልሰቀሉትምም፤ ግን ለነሱ የተገደለው ሰው በዒሳ ተመሰለ፤ በእርግጥም አልገደሉትም» ተብሎ እንደተጻፈ ክርስቶስ አልተሰቀለም በማለት ይልቁንም ሌላ ሰው በእርሱ ተመስሎ እንደተሰቀለ ቁርአኑ ይናገራል፡፡ እጅግ የሚያስቀው ነገር ቁርአኑ የክርስቶስን መሰቀል እንዲህ ሽምጥጥ አድርጎ እየካደ እንደገና መልሶ መጽሐፍ ቅዱስን አረጋግጣለሁ ማለቱ ነው፡፡ ይህ እብደትም ጭምር ነው በእውነት! መጽሐፍ ቅዱስ ማለትኮ ከመጀመሪያው ገጽ (ከዘፍጥረት) ጀምሮ እስከ መጨረሻው ገጽ (ዮሐንስ ራእይ) ድረስ የክርስቶስን ሰው መሆንና ዓለሙን ሁሉ ለማዳን ሲል ተሰቅሎ መሞቱን

ነው የሚናገረው፡፡ ይህን ደግሞ ቅዱሳት መጻሕፍት ብቻ ሳይሆኑ የዓለም ታሪክም በብዙ ማስረጃዎች የሚያረጋግጠው እውነት ነው፡፡ ታዲያ ቁርአን ይህንን ሀቅ እየካደና እየተቃወመ እንደገና መልሶ መጽሐፍ ቅዱስን አረጋግጣለሁ ማለት ምን ዓይነት ቅጥፈት ነው? ለመሆኑ መጽሐፍ ቅዱስና ቁርአን በአጠቃላይ ይዘታቸውም ቢሆን የሰማይና የምድር ያህል ተራርቀው ሳለ፣ የብርሃንና የጨለማ ያህል ተለያይተው ሳለ፣ ቁርአኑ እንዴት የክርስቲያኖቹን መጽሐፍ አረጋግጣለሁ ይላል? ማረጋገጥ አልቻለም እንጂ ቢችል ኖሮስ እንዴት በሌሎች እምነት ላይ ይደገፋል? ለምንስ ለክርስቲያኖቹ መጽሐፍ ታኮ መሆን ፈለገ? ለምን ራሱን ችሎ አልቆመም? አረጋጋጭ ስለመሆኑስ ለምን ይህን ያህል አሰልቺ በሆነ መልኩ ትኩረት ሰጥቶ ሊናገር ቻለ? ይህም ሁሉ ነገር በአጠቀላይ ቁርአኑን ትዝብት ውስጥ እንዲገባና በአማኞቹም ዘንድ ታማኝነት እንዳይኖረው አድርጎታል፡፡ ብዙዎቹም አማኞቹ አፍረውበታል፡፡ እኔን ጨምሮ ብዙዎች በጣም ሙስሊሞች ቁርአኑን በደንብ ከመረመሩት በኋላ እስልማውን እርግፍ አድርገው በመተው ወደ ክርስትናው የመጡትም ለዚህ ነው፡፡

መሐመድ ስለ ክርስቲያኖችና አይሁዶች ጥሩም መጥፎም አመለካከቶች ነበሯቸው፡፡ ጥሩ አመለካከታቸውን ስናየው የማባበል ሥራ ይሠሩበት የነበረውን አካሄድ እናገኛለን፡፡ ይህም እስልምናን ገና መስበክ እንጀመሩ ለሚመሠርቱት እምነት ክርስቲያኖቹ መነሻቸው እንደሆኑ፣ መጻሕፍቶቻቸውም ትክክል እንደሆኑ፣ በነቢያቶቻቸውም እንደሚያምኑ፣ መንግሥተ ሰማያትም እንደሚገቡ ሆኖም ግን በአላህና በእርሳቸውም ነቢይነት ማመን እንዳለባቸው ያስተምሩ ነበር፡፡ (እነዚህ ነገሮች በቁርአኑ ስለተካተቱ በኋላ በደንብ እናያቸዋለን፡፡)

ሁለተኛው አቋማቸው ግን ከዚህ የተለየ ነበር፡፡ መሐምድ ክርስቲያኖችንና አይሁዶችን ዕውቅና እየሰጧቸው ለእስልምናውም እነርሱ ምንጭ መሆናቸውን፤ ቁርአንም የእነርሱን መጽሐፍ እንደሚያረጋግጥ ይነግሯቸው ነበር፡፡ ለማመሳሰል ሲሉ ይህን ሁሉ እየተናገሩ ቢያስተምሯቸውም እምነታቸውን ፈጽሞ እንዳልተቀበሏቸው ሲያውቁ ያን ጊዜ ፊታቸውን አዞሩባቸውና ሁለተኛ አቋማቸውን በተግባር ማሳየት ጀመሩ፡፡ «የተረገሙና ከፉዎች ናቸው፣ የማያምኑ ናቸው፣ ደንቆሮዎች ናቸው፣ ሲኦል ነው የሚገቡት፣ መጽሐፋቸውን ለውጠዋል…» የሚሉ ትችቶችን አቀረቡባቸው፡፡ «እናንተ መጽሐፉን የተሰጣችሁ ሆይ! ፊቶችን ሳናብስና በጀርባዎች ላይ ሳንመልሳቸው ወይም የሰንበትን ባለቤቶች እንደረገምን ሳንረግማቸው በፊት ከእናንተ ጋር ያለውን የሚያረጋግጥ ሆኖ ባወረድነው (ቁርአን) እመኑ፤ የአላህም ትእዛዝ ተፈጻሚ ነው» (4፡47)፤ «የእስራኤል ልጆች ቃልኪዳናቸውንም በማፍረሳቸው ረገምናቸው፤ ልቦቻቸውንም ደረቆች አደረግን፤ ቃላትን ከቦታዎቻቸው ይለውጣሉ» (5፡12)፤ «አይሁዶችና ክርስቲያኖችም ሃይማኖታቸውን እስከምትከለተል ድረስ ካንተ ፈጽሞ

አይወዱም» (2፡120) እንዳለ ቁርአኑ፡፡ ስለዚህ መሐመድ በትችትና በነቀፌታ ብቻ አላቆሙም በመጨረሻ በአካባቢው በሚኖሩት ላይ ጂሃድ አውጀውባቸው ለሰይፍ ዳረጓቸው፡፡ እንዲሁም «አላህ ወደ ዝንጀሮነትና ከርከሮነት ለውጧቸዋል» በማለትም ተናግረዋል፡፡ 5፡60፡፡
ወደ መነሻው ሀሳብ ልመለስና መሐመድ «ነቢይነቴን ብቻ ተቀበሉኝ አላህም አምላክ እንደሆነ እመኑ እንጂ የእናንተን መጻሕፍት እቀበላለሁ» ብለው በተነሡበት ሰዓት ክርስትያኖችንና አይሁዶችን «የመጽሐፉ ሰዎች» (people of the book) አንዳንድ ቦታ ደግሞ «የመጽሐፉ ባለቤቶች» እያሉ ብዙጊዜ ጠቅሰዋቸዋል፡፡ (3፡110፣ 4፡115፣ 5፡59፣ 5፡65፣ 5፡68፣ 5፡77፣ 17፡4፣ 98፡6) የዕውቀት ባለቤቶች መሆናቸውን ተናግረውላቸዋል፡፡ የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍቶቻቸውም ብርሃን እንደሆኑና ቀጥተኛ መመሪያዎች እንደሆኑ ቁርአኑም ይህን ሊያረጋግጥ እንደመጣ ተናግረዋል፡፡ በቁርአኑ ላይ በግልጽ እንደተጻፈው መጽሐፋቸው የክርስቲያኖቹን መጽሐፍ አረጋጋጭ ከመሆኑም በላይ መሐመድም ሆኑ ተከታዮቻቸው ሙስሊሞች በክርስቲያኖቹ መጽሐፍ እንዲያምኑና የማውቁትም ነገር ቢያጋጥማቸው እንኳን ክርስቲያኖቹን እንዲጠይቁና እንዲረዱ አዘዋቸዋል፡፡ ቀጥሎ ያሉትን ጥቅሶች ተመለከቱ፡-
1ኛ. «ቁርአን ከአላህ ሌላ ከሆነ ፍጡር የተቀጠፈ ሊሆን አይገባውም፤ ግን ያንን ከርሱ በፊት ያለውን መጽሐፍ የሚያረጋግጥና በመጽሐፉ ውስጥ ያለውን የሚዘረዝር፣ በርሱ ጥርጣሬ የሌለበት ሲሆን ከዓለማነት ጌታ የተወረደ ነው፡፡» (10፡37)
2ኛ. «እኛ ተውራትን (ኦሪትን) በውስጧ መምሪያና ብርሃን ያለባት ስትሆን አወረድን፤ እነዚያ ትእዛዝን የተቀበሉት ነቢያት በነዚያ ይሁዳውያን በሆኑት ላይ በርሷ ይፈርዳሉ፤ ሊቃውንቱና ዐዋቂዎቹም ከአላህ መጽሐፍ እንዲጠብቁ በተደረጉትና በእርሱም ላይ መስካሪዎች በሆኑት ይፈርዳሉ፤… በፈለጎቻቸውም በነቢያቶቹ ፈለግ ላይ የመሪየምን ልጅ ዒሳን ከተውራት (ከኦሪት) በስተፊቱ ያለውን አረጋጋጭ ሲሆን አስከተልን፤ ኢንጂልንም (ወንጌልንም) በውስጡ ቀጥታና ብርሃን ያለበት በስተፊቱ ያለችውን ተውራትንም የሚያረጋግጥ ለጥንቁቆችም መሪና ገሳጭ ሲሆን ሰጠነው» (5፡44-46)
3ኛ. «ወደ አንተም ካወረድነው (ቁርአንን) በመጠራጠር ውስጥ ብትሆን እነዚያን ከአንተ በፊት መጽሐፉን የሚያነቡትን ጠይቅ» (10፡94)
4ኛ. «ከአንተም በፊት ወደነሱ የምናወርድላቸው የሆኑ ሰዎችን እንጂ ሌላ አልላክንም፤ የማታውቁ ብትሆኑ የመጽሐፉን ባለቤቶች ጠይቁ» (21፡7)
5ኛ. «አላህ በመልክተኛው ላይ ባወረደው መጽሐፍ በዚያም ከበፊቱ ባወረደው መጽሐፍ እመኑ» (4፡136)

6ኛ. «በጣም የተብራራውንም መጽሐፍ ሰጠናቸው» (37፡117)

7ኛ. «እነዚያ መጽሐፉን የሰጠናቸው ተገቢ ንባቡን ያነቡታል፤ እነዚያ በእርሱ ያምናሉ» (2፡121)

8ኛ. «በአላህና ወደኛ በተወረደው ወደ ኢብራሂምም፣ ወደ ኢስማዒልና ወደ ኢስሐቅ ወደ ያዕቁብና ወደ ነገዶቹም በተወረደው፣ በዚያም ሙሳና ዒሳ በተሰጡት በዚያም ነቢያት ሁሉ ከጌታቸው በተሰጡት ከነርሱ በአንድም መካከል የማንለያይ ስንሆን አመንን፤ እኛም ለእርሱ ለአላህ ታዛዦች ነን በሉ» (2፡136)

9ኛ. «እናንተ የመጽሐፉ ባለቤቶች ሆይ! ተውራትንና ኢንጂልን (ኦሪትንና ወንጌልን) ከጌታችሁም ወደናንተ የተወረደውን እስከምታቆሙ ድረስ በምንም ላይ አይደላችሁም» (5፡68)

ቁርአኑ በእንደዚህ ዓይነት መልኩ ለመጽሐፍ ቅዱስ ታኮ መሆን ለምን ፈለገ? ለሚለው ጥያቄ መልሱ አንድና አንድ ነው- ቁርአኑ በራሱ ሙሉ ስላልሆነ ነው፡፡ መሐመድ ታሪኮቹን ከክርስትናው ገልብጠው ወስደው ራሳቸው በሚፈልጉት መልኩ በጸሐፊዎቻቸው አማካኝነት ካጻፈፉና ካዘጋጁ በኋላ ነው «ቁርአን ከሰማይ ወረደልኝ» ያሉት፡፡ ለዚያውም ቁርአኑ በ23 ዓመታት ውስጥ በተለያየ ጊዜ እንደወረደላቸው ነው የተናገሩት፡፡ ሙሉው ቁርአን ማለትም 114ቱም ሱራዎች (ምዕራፎች) ለምን በአንድ ጊዜ አልወረዱላቸውም? በየጊዜው የሚያጽፉትን ነገር ነበር «ከሰማይ ወረደልኝ» ይሉ የነበረው፡፡

ነቢያቸው በወቅቱ ለንግድ በሄዱባቸው ሀገራት ያገኙዋቸው መናፍቃን ስለ ክርስትናው በተሳሳተ መንገድ የተረኩላቸው ተረቶችና የምንፍቅና መጻሕፍቶቻቸው መሐመድን ለከፋ ስሕተት አጋልጠዋቸዋል፡፡ ቁርአኑም በግልጽ «በእርግጥ ካለፉት ወሬዎች ባንተ ላይ እንተርካለን፤ ከእኛም ዘንድ በእርግጥ ቁርአንን ሰጠንህ» (20፡99) ተብሎ እንደተነገረ ሌሎች የተረኩላቸውን ወሬዎች ስለተቀበሉ በክህደት ላይ የነበሩ ሰዎች ለበለጠ ክህደት ዳርገዋቸዋታል፡፡ ምናልባት በመርዝ ሊሞቱ ሲሉ ንስሓ ሊገቡ ፈልገው ይሆን እንዴ መሐመድ ኃጢአተኛ መሆናቸውንና ስሕተተት መሥራታቸውን በቁርአናቸው ላይ ያሰፈሩት ??? ለማንኛውም እሳቸው ለፈጠሩት እጅግ ከባድ ስሕተት ዋና አቀናባሪው የሰው ልጆች ሁሉ በእውነተኛው አምላክ አምነው፣ እውነተኛዋን ሃይማኖት ይዘው እንዳይድኑ የሚፈልገውና «ሐሰተኛ የሐሰት አባት» (ዮሐንስ ወንጌል 8፡44) የተባለው እርሱ ዲያብሎስ ነው፡፡ ቢቃ ይሄ ነው እውነቱ፡፡ በእምነት ጉዳይ ላይ በአጠቃላይ የተፈጠረው ልዩነትኮ በክርስቶስና በዲያብሎስ መካከል ያለ ልዩነት ነው እንጂ የክርስትናና የእስልምና ጉዳይ አይደለም!!!

7ኛ.ቁርአኑ ለመሐመድ ሰይጣናዊ በሆነ መንገድ የተገለጠ በመሆኑ ታማኝ አይደለም

ይህንን ጉዳይ በገጽ—- ላይ «ሰይጣናዊ መገለጦች» በሚል ርዕስ እንዲሁም በገጽ—ላይ «መሐመድ ባደረባቸው መንፈስ ምክንያት ራሳቸውን ሊያጠፉ ይሞክሩ ነበር» በሚል ርዕስ በሰፋት ስላየነው አሁን በድጋሚ ማንሳቱ ተገቢ ስላልሆነ አልመለስበትም፡፡ ስለዚህ ወደኋላ ሄደው በጠቀስኳቸው ገጾች ላይ ዝርዝር መረጃዎችን ማለትም በትክክል ለመሐመድ በመልአኩ ጂብሪል ተመስሎ የተገለጠላቸው ሰይጣን እንደነበር የሚገልጸውን የሐዲስ መረጃ በገጾቹ ላይ ይመልከቱ፡፡

8ኛ.ቁርአኑ አጠቃላይ ይዘቱ እጅግ አሰልቺ በመሆኑ ታማኝ አይደለም፡- አንድ የከፋው ወይም ያዘነ ሰው ቁርአንን ገልጾ ቢያነብ የግድያ፣ የዛቻና የማስፈራሪያ ቃላት በብዛት ተደርድረው ያገኛል እንጂ ከሀዘኑ ሊያፅናኑት፣ መከፋቱን ሊያርቁለት የሚችሉ አፅናኝ ቃላትን አያገኝም፡፡ በእርግጥ በጀነት ስላለው ወሲባዊ ሕይወት ቁርአኑ በደንብ ይተርካል፡፡ ከዚህ ውጭ ግን ቁርአኑ የአላህን ሕልውና ከመግለጽ ይልቅ ስለ ተቃራኒው የክርስትና ሃይማኖት ነው በብዛት የሚያወራው፡፡ ተጀምረው ያልተቋጩ ሀሳቦች ይበዙበታል፡፡ መልእክቶቹ ግልጽ አይደሉም፡፡ አንድን ሀሳብ አድካሚ በሆነ ሁኔታ በጣም በተደጋጋሚ ይጠቅሳል፡፡ እነዚህና ሌሎቹም አግባብነት የሌላቸው ባሕርያቶቹ ቁርአኑን በጣም አሰልቺ አድርገውታል፡፡ እነዚህ ነገሮች ደግሞ እንኳን አምላክ ነው ከሚባል አካል ሊገኙ ይቅርና ከአንድ ተራ ምድራዊ ደራሲ ራሱ የሚጠበቁ አይደሉም፡፡ ቁርአንን ፈጽሞ ማመን አይቻልም፡፡ እኔ ይህንን የምናገረው ለመተቸት አይደለም፡፡ የቁርአኑን የተወሰኑ ገጾችን ብቻ በማየት ይህንን እኔ ያልኩትን ነገር ማረጋገጥ ይቻላል፡፡ እደግመዋለሁ ሙሉውን አይደለም ያልኩት የተወሰኑ የቁርአኑን ገጾችን ብቻ በማየት እኔ የተናገርኳቸውን ነገሮች ማረጋገጥ ይቻላል፡፡

9ኛ.የጀመረውን ሀሳብም ሆነ ታሪክ የማይጨርስ ስለሆነ ሊታመን አይችልም

ቁርአን ውስጥ ያሉ ታሪኮች በሙሉ በእንጥልጥል የቀሩ ናቸው፡፡ ምንም እንኳን ታሪኮቹ ከሌሎች እምነቶች የተኮረጁ ቢሆኑም ቁርአኑ በሚፈልገው መንገድ ራሱ የታሪኮቹን ፍጻሜ ማሳየት አልቻለም፡፡ ራሱ አንኳር የሆነውን የአዳምንና የሔዋንን ታሪክ ብናየው ቁርአኑ አዳምና ሔዋን አትብሉ የተባሉትን ፍሬ ስለበሉ ከገነት ስለመውጣታቸው ይናገራል ነገር ግን በምን ዓይነት ሁኔታ፣ መቼ፣ እንዴት ወደ ገነት ተመልሰው እንደገቡ አይናገርም፡፡ 7፡11-27፣ 20፡115-122፡፡ በቁርአን ውስጥ ተጀምረው ፍጻሜ ያላገኙ ታሪኮች በጣም ብዙ ናቸው፡፡ የሚጠቅሳቸው እያንዳንዳቸው ታሪኮች ጥርት ባለ አገላለጽ ያልተነገሩ ከመሆናቸውም በላይ በእንጥልጥል የቀሩ ናቸው፡፡ ለዚህ ማሳያ የሚሆን አንድ ምሳሌ ላሳያችሁ፡፡ የብዙዎቹ ታሪክ ረጅም ስለሆነ እነርሱን ለማሳየት

አሙቺ አይደለም፡፡ አጠርና ቀለል ባለ መልኩ ስለተጻፈች ችግሩን ያን ያህል አጉልታ ባታሳይም ለአቀማመጥ አሙቺ ስለሆነች የቁርአኑን 111ኛ ምዕራፍ ለማሳያነት ይሆናል ብዬ ስላሰብኩ ከነሙሉ ቁጥሩ ስካን (scan) አድርጌ ያስገባሁት ስለሆነ ቀጥሎ ይመልከቱት፡፡

ምዕራፍ ፡ 111 ፡ አል-ለሀብ ። ክፍል ፡ 30 ።

111ኛ ፡ ሱረቱ ፡ አል-ለሀብ ፤ (የመንቀልቀል ፡ ምዕራፍ) ። በ መካ ፡ የወረደች ፡ ናት ፤ አያትዋ ፡ (አንቀጾችዋ) ፡ 5 ፡ ናቸው ።

በአላህ ፡ ስም ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡ ርኅሩኅ ፡ በጣም ፡ አዛኝ ፡ በሆነው ።

1 የአቡ ፡ ለሀብ ፡ ሁለት ፡ እጆች ፡ ከሰሩ ፡ (ጠፉ ፤ እርሱ) ፡ ከሰረም ።

2 ከርሱ ፡ ገንዘቡና ፡ ያም ፡ ያፈራው ፡ ሁሉ ፡ ምንም ፡ አልጠቀመውም ።

3 የመንቀልቀል ፡ ባለቤት ፡ የኾነችን ፡ እሳት ፡ በእርግጥ ፡ ይገባል ።

4 ሚስቱም ፡ (ትገባለች) ፤ እንጨት ፡ ተሸካሚ ፡ ስትኾን ፤

5 በአንገትዋ ፡ ላይ ፡ ከጭረት ፡ የኾነ ፡ ገመድ ፡ ያለባት ፡ ስትኾን ።

በቃ 111ኛው ምዕራፍ እንደዚህ ብሎ የሚያልቀው፡፡ ከዚህ በኋላ 112ኛው ምዕራፍ ነው የሚቀጥለው፡፡ ሲጀመር አቡ ለሀብ ማለት መሐመድ ገና እምነታቸውን ሊመሠርቱ ሲነሡ «ተው ይቅርብህ ይሄ ነገር ጥሩ አካሄድ አይደለም» እያለ ይመከራቸው የነበረ አሳዳጊው አጎታቸው ነው፡፡ በኋላም አቡ ለሀብ እምነታቸውን ሳይቀበል ስለሞተ መሐመድ በጠላትነት ሊፈርጁት ችሏል፡፡ ከአሁን በፊት እንዳየነው መሐመድን አጎቶቻቸው እምነታቸውን አልተቀበሉአቸውም ነበር፡፡ እናም ይህ 111ኛ ምዕራፍ የተጻፈው ስለ አቡ ለሀብ ነው፡፡ ቁ4 እና ቁ5 ላይ ስለ አቡ ለሀብ ሚስት የተገለጸበትን መንገድ ልብ ብላችሁ ተመልከቱት እስቲ! ትርጉም እንዲሰጡ በማለት በቅንፍ ውስጥ ( ) እየተደረጉ የተጨመሩ ቃላት መኖራቸውንም ተመልከቱ፡፡ እነዚህ በቅንፍ ውስጥ እየተደረጉ የተጨመሩ ቃላት ግን በዋናው ዐረብኛና እንግሊዝኛ ቁርአን ላይ የሉም፡፡

ቁ5 ላይ «በአንገትዋ ላይ ከጭረት የሆነ ገመድ ያለባት ስትኾን፡፡» ብሎ ነው ሙሉ 111ኛ ምዕራፉን በአራት ነጥብ የዘጋው፡፡ ከመጀመሪያውም ከቁ.1 ጋር አያይዘን ብናየው አገላለጹ ትርጉም አልባ ከመሆኑም በላይ ሀሳቡ በእንጥልጥል ነው የቀረው፡፡ ሀሳቡ ቀጣይ ነው እንዳይባል ከቁ5 በኋላ 112ኛው ምዕራፍ ነው የሚቀጥለው፤ እርሱም ስለ ሌላ ነገር ነው የሚናገረው፡፡ ቁ4 እና ቁ5 ላይ ባለው በእንደዚህ ዓይነት አገላለጽ መጨረስ አልነበረበትም፡፡ ይሄ የአገላለጽ ጉዳይ ቢሆንም ቁርአኑ በውስጡ ያሉ ታሪኮችንም በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታ ነው ያስቀመጣቸው፡፡ በዚያ ላይ አቡ ለሀብም

ሆነ ቤተሰቡ ለምን እንደሚቀጡ ምንም የተጠቀሰ ነገር የለም፡፡ እስልምናን ስላልተቀበለ ነው ብዬ የጠቀስኩት ከመሐመድ ከግል ሕይወት ታሪካቸው (biography) የተገኘ ነው፡፡

10ኛ.ቁርአኑ ከሰማይ የወረደ ሳይሆን የራሱ የሆኑ የተለያዩ ምንጮች ስላሉት ሊታመን አይችልም፡- መሐመድ የቁርአንን አንቀጾች በትረካ ሲናገሩ በጽሑፍ ይገለብጥላቸው የነበረ ‹‹አብድ አላህ ኢብን ሳድ ኢብን አቢ ሳርህ›› የተባለ ጸሐፊ እንደነበራቸው፣ እሳቸውም ምንም ያልተማሩ በመሆኑ ማንበብና መጻፍም ስለማይችሉ ጸሐፊያቸው የግሉን ሀሰብ በቁርአኑ ላይ ይጨምር እንደነበር ከዚህ በፊት በገጽ------ ላይ አይተናል፡፡ ውስጡ ያለው ይዘትና አጠቃላይ ባሕርያቶቹ በትክክል እንደሚያሳዩት ቁርአን ፈጽሞ ከሰማይ የመጣ ሊሆን አይችልም፡፡ እንደዚያ ዓይነት ይዘት ያለውን መጽሐፍ ቁርአንን ‹ከሰማይ መጣ› ብሎ ማስብ በራሱ አምላክን እንደመሳደብ ነው በእውነት! ቁርአንን የመሐመድ የግል ሥራ ብቻም አይደለም፡፡ በአንድ አካል ወይም በአንድ ሰው ብቻ ተቀናብሮ የተዘጋጀ ነገር አይደለም፡፡ የቁርአን ቅንብር ላይ የብዙ ሰው እጅ አለበት፡፡ ድርሰቱን በማዋቀር፣ የቁም ጽሕፈቱን በመጻፍ፣ አንቀጾቹን በማሻሻል/በማስተካከል፣ ከአንቀጾቹ ውስጥ የተወሰኑትን በማጥፋትና በማቃጠል አሊያም የሚፈልጉትን ሀሳብ በማስገባት በርካቶች ተሳትፈውበታል፡፡ ታሪካቸውን ወደፊት በደንብ የምናያቸው እነ ኢምሩል ቃይስ፣ ዛይድ ቢን አምር፣ ሀሰን ቢን ጣቢት፣ ሰልማን፣ ባሂራ፣ ኢብን ቁምታ፣ ዋራቃና ዑባይ ቢን ካብ በተባሉ ግለሰቦች እጅ ነው አሁን ያለውን ቁርአን የተቀናበረው፡፡ “The Qur'an is not the creation of a single entity or a single person. There were several parties involved in the composition, scribing, amending, inserting and deleting the Qur'anic verses. The most important personalities involved in the creation of the Qur'an were: Imrul Qays, Zayd b. Amr, Hasan b. Thabit, Salman, Bahira, ibn Qumta, Waraqa and Ubayy b. Ka'b. Qur'an is definitely not the word of Allah-it is a human-made scripture which Muhammad simply passed up as Allah's final words to mankind. Qur'an, thus, is a compilation of various religious books that existed during Muhammad's time. Muhammad, not Allah, simply adopted, picked and chose from various sources and created the Qur'an.” (Hughe's Dictionary of Islam, p.425)

የመሐመድ እምነት መነሻው የፓጋን ዐረቦች እምነት ነው፡- የመሐመድ የዘር ሀረግ የሆኑት ቁራይሾች በእምነታቸው ፓጋን ነበሩ፡፡ እርሳቸውም ይህንን እምነት ይዘው ነው ያደጉት፡፡ ፓጋን ዐረቦች 360 ጣኦታት የነበሯቸው ሲሆን እያንዳንዱን ቀን ለአንድ ጣኦት የመታሰቢያና የክብረ በዓሉ ቀን አድርገው ያከብሩት ነበር፡፡ መሐመድ እምነታቸውን ሲመሠርቱ ከፓጋን ዐረቦቹ ያልወረሱት አንድ ብቸኛ ነገር ቢኖር ይህን

የብዙ አማልክቶቻቸውን እምነት ብቻ ነው፡፡ ከዚህ በፊት በገጽ—ላይ ስለ ሦስቱ የአላህ ልጆች በስፋት አይተናል፡፡ መሐመድ በወቅቱ «አላህ አንድ ብቻ ነው፣ ልጆች የሉትም፣ መደምደሚያ መልእክተኛውም እኔ ብቻ ነኝ» ብለው ከማስተማር በቀር ሌላውን የፓጋን ዐረቦቹን የእምነት ስርዓት እንዳለ ነው በእስልምናውም የተጠቀሙበት፡፡ ስለዚህ ቁርአኑ በውስጡ የያዘው ሀሳብ የፓጋን ዐረቦቹን የእምነት ሥርዓት መሠረት ያደረገ ሲሆን ከሌሎች እምነቶች ጋር በተለይም ከክርስትናው ጋር ቀላቅሎ የያዘ ስለሆነ የተምታቱ ሀሳቦች ይበዙበታል፡፡ ይህም መሐመድ የክርስትናውን ትምህርት ያገኙት በወቅቱ ክርስትናውን ይቃወሙ ከነበሩት መናፍቃን መሆኑ አካሄዱን በሙሉ እጅግ አስከፊ አድርጎባቸዋል፡፡ በዚያ ላይ መሐመድ እያንዳንዷን የቁርአን አንቀጽ በሌላ ሰው በ3ኛ ወገን እንዲጻፍ ማድረጋቸውና ጸሐፊዎቹም የራሳቸውን ሀሳብ እየጨመሩ መጻፋቸው ሌላኛው አስከፊ ገጽታው ነው፡፡ እርሳቸውም ከሞቱ በኋላ ተከታዮቻቸው ከሊፋዎች የቁርአኑን ድርሰት በማዋቀር፣ የቁም ጽሕፈቱን በመጻፍ፣ አንቀጾቹን በማሻሻልና በማስተካከል፣ ከአንቀጾቹ ውስጥ የተወሰኑትን በማጥፋት ወይም የሚፈልጉትን ሀሳብ በማስገባት ነበር ቁርአኑን ያዋቀሩት፡፡

መሐመድ በሕይወት እያሉም ቁርአኑን በሰዎች ሲያጽፉ የተለያዩ ምንጮችን በግብአትነት ተጠቅመዋል፡፡ በሥራው ላይ ማለትም በቁርአኑ ውስጥ ስለሚጻፈው ነገር ሀሳብ በማመንጨት፣ በመጻፍና በማቀናበር ቀጥተኛ ተሳትፎ ከነበራቸው ግለሰቦች ውስጥ የተወሰኑትን 16 ግለሰቦች ቀጥሎ በዝርዝር እናያቸዋለን፡-

10.1. ኢምሩል ቃይስ፡- በጥንት ዐረቢያ ምድር የነበረ ገጣሚ ሲሆን ግጥሞቹም በኅብረተሰቡ ዘንድ በከፍተኛ ሁኔታ ተቀባይነት ነበራቸው፡፡ በወቅቱ የነበሩ ጸሐፊዎችም ግጥሞቻቸውን በካዕባ ግድግዳ ላይ በመሰቀል የከተማው ሰዎች እንዲያነቡላቸው ያደርጉ የነበረ ሲሆን ኢምሩል ቃይስ ከሁሉም ዝነኛና ታዋቂ ነበር፡፡ (Hughe's Dictionary of Islam, p.460) በወቅቱ በአካባቢው በተነሳ ኢምሩል ቃይስ ጦርነት ወደ ኮንስታንቲኖፐል ተሰዶ ሄዶ በዚያ ሲኖር በግጥሞቹ ምክንያት የኮንስታንቲኖፐልን ልዕልት ልብ መማረክ ስለቻለ ባሏ የሮማኑ ገዥ በ540 ዓ.ም አስገድሎታል፡፡ ይህም መሐመድ በ570 ዓ.ም ከመወለዳቸው ከ30 ዓመታት በፊት ማለት ነው፡፡ ኢምሩል ቃይስ ከሞተም በኋላ ግጥሞቹ በዐረቢያ ምድር በስፋት ይነገሩ ነበር፡፡ ግጥሞቹም በካዕባ ግድግዳ ላይ ተጽፈው እየተሰቀሉ የአካባቢው ሰዎች በቃላቸው ያነበንቧቸው ነበር፡፡ በወቅቱ 7 ጸሐፊዎች ግጥሞቻቸውን በቋሚነት የሚሰቅሉበት የየራሳቸው ቦታ ነበራቸው፡፡ የተሰቀሉት ግጥሞቻቸውም «ሙአላቃት» ተብለው ይጠሩ ነበር፡፡

ሙስሊሞች ለመጀመሪያ ጊዜ ለመሐመድ የወረደችላቸው የመጀመሪያዋ ቁርአን ሱራ (ምዕራፍ) 96 ናት ብለው ያምናሉ፡፡ ከ611-615 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ በመካ ከተማ ለመሐመድ ወርደውላቸዋል ተብለው የሚታመኑት የመጀመሪያዎቹ ሱራዎች/ምዕራፎች (1, 51-53, 55-56, 68-70, 73-75, 77-97, 99-104, 111-114) ናቸው፡፡ (አሁን ባለው ቁርአን ላይ የተቀመጡት በአወራረዳቸው ቅደም ተከተል መሠረት ስላልሆነ የምዕራፎቹ አጻጻፍ ግር እንዳያሰኘን፡፡) እናም ከእነዚያ የመጀመሪያ ናቸው ከተባሉት ምዕራፎች ውስጥ 99ኛው፣ 100ኛውና 103ኛው የቁርአን ምዕራፎችና ሌሎችም ስንኞች በቀጥታ ከኢምሩል ቃይስ ግጥሞች ተቀድተው በተወሰዱ ስንኞች የተሞሉ መሆናቸውን በዘርፉ ሰፊ ጥናት ያካሄዱት አጥኚዎች ይገልጻሉ፡፡ (W.St. Calir-Tisdall, The Origins of the Koran, p.235-236 & Hughe's Dictionary of Islam, p.485) ለምሳሌ ያህል በቁርአኑ 54፡1 መጀመሪያ ላይ መሐመድ የተጠቀሙበት «ሰዓቲቱ ተቃረበች፤ ጨረቃም ተገመሰች» የሚለው ቃል በቀጥታ ተቀድቶ የመጣ የኢምሩል ቃይስ ግጥም አንዱ ስንኝ ነበር፡፡ እንዲያውም በወቅቱ የመሐመድ ሴት ልጅ ፋጢማ አንድን ግጥም «የአባቴ ግጥም ነው» እያለች ለጓደኞቿ በቃሏ ስትገጥምላቸው የኢምሩል ቃይስ ልጅ ሰምታ «የሞተው አባቴን ግጥም ነው የወሰድሽው» ብላ እንዳለቀሰች ታሪክ ጸሐፊዎች መዝግበውታል፡፡ (W. St. Calir-Tisdall, The Origins of the Koran, p.236.)

10.2 ዛይድ ቢን አምር ቢን ነውፋል፡- መሐመድ ከመነሣታቸው በፊት የፓጋኖችን እምነት ፈጽሞ በመተው ወደ ሌላ እምነት የሄዱ ሰዎች ነበሩ፡፡ ለምሳሌ ኡቤይዱላህ ቢን ጃህሽ ወደ አቢሲኒያ (ኢትዮጵያ) ሄዶ ክርስቲያን ሆነ፤ ኡትማን ቢን አል-ሁዋይሪዝ ወደ ቢይዛንታይን ግዛት ሄዶ ክርስቲያን ሆነ፤ ዋራቃ ቢን ነውፋልም እንዲሁ ክርስቲያን ሆኖ መሞቱ ታውቋል፡፡ ዛይድ ቢን አምር ቢን ነውፋል ደግሞ ፓጋኒዝምን የተወው የአብርሃምን እምነት እከተላለሁ ብሎ ነበር፡፡ መካ በሚገኘው በቤተ ጣቱ በካዕባ ውስጥ ለጣኦታቱ እንስሳት መሰዋታቸውንና ሕጻን ሴት ልጅ ስትወለድ በሕይወት እያለች ትቀበርበት የነበረውን የፓጋን ዐረቦችን ድርጊት ይቃወም ነበር፡፡ በፓጋን ዐረቦች እምነት መሠረት ሴት ልጅን መውለድ እንደ ውርደት ይቆጠር ስለነበር ሴቷን ልጅ በሕይወት እያለች ይቀብሯት ነበር፡፡ ዛይድ ቢን አምርም በድፍረት ይህንንና ባዕድ አምልኮአቸውን ስለተቃወማቸው የመካ ነዋሪዎች እርሱን እንዳይደርስባቸው ከከተማው አስወጥተውት ስለነበር ሂራ ተራራ ላይ ወዳለው ዋሻ እየሄደ ሃይማኖታዊ ሥርዓቱን ይፈጽም ነበር፡፡ በዚህም የአብርሃምን ዓይነት ሥራ እንደሠራ ያምን ነበር፡፡ (Ibn Ishaq p.99-103) መሐመድም «ጂብሪል በዚህ ተራራ ነው የሚገለጥልኝ» እያሉ ወደዚህ ቦታ በሄዱ ጊዜ ነው ከዛይድ ቢን አምር ጋር በዚህ ተራራ ላይ የተገናኙት፡፡

ይህም ታሪክ በሐዲሱ ላይ ተጽፎ ይገኛል፡፡ መሐመድ ከያዙት ስንቅ ሲሰጡት ዛይድ ቢን አምር «ለጣኦት የተሰዋ አልበላም» በማለት እምቢ ብሏቸዋል፡፡ በዚያውም ለፓጋን ዐረብ ጣኦታት የተሰዋን ሙብላት ተገቢ አለመሆኑንና ሎሎችንም የባዕድ አምልኮ ሥርዓቶችን እንዳይከተሉ ለመሐመድ አስተምሯቸዋል፡፡ “Allah's Apostle said that he met Zaid bin 'Amr b. Nufal at a place near Baldah and this had happened before Allah's Apostle received the Divine Inspiration. Allah's Apostle presented a dish of meat (that had been offered to him by the pagans) to Zaid bin 'Amr, but Zaid refused to eat of it and then said (to the pagans), "I do not eat of what you slaughter on your stone altars (Ansabs) nor do I eat except that on which Allah's Name has been mentioned on slaughtering.” (*Sahih Bukhari, Volume 7, Book 67, Number 407) See also Volume 5, Book 58, Number 169)*

በሂራ ተራራ ቆይታቸው ወቅት ዛይድ ቢን አምር መሐመድን ማንበብና መጻፍ ሊያስተምራቸው ሞክሮ ነበር፡፡ ዛይድ የራሱንም ግጥሞች ጨምሮ እነዚያን «ሙአላቃት» ተብለው ይጠሩ የነበሩና የተሰቀሉ ግጥሞችን ያነብላቸውና ይተርክላቸው ነበር፡፡ በወቅቱ ዛይድም የአብርሃምን ሃይማኖት እፈልጋለሁ ብሎ እስከ ሶሪያ ድረስ ሄዶ ከክርስቲያኖችና ከአይሁዶች ጋር ለመወያየት ችሎ ነበር፡፡ ነገር ግን በኋላ ተመልሶ ወደ መካ በመጣ ጊዜ በደረሰበት ተቃውሞ ምክንያት ሊገደል ችሏል፡፡ “Zaid bin 'Amr bin Nufal went to Sham, inquiring about a true religion to follow. He met a Jewish religious scholar and asked him about their religion. He said, "I intend to embrace your religion, so tell me some thing about it." The Jew said, "You will not embrace our religion unless you receive your share of Allah's Anger." Zaid said, "'I do not run except from Allah's Anger, and I will never bear a bit of it if I have the power to avoid it. Can you tell me of some other religion?" He said, "I do not know any other religion except the Hanif." Zaid enquired, "What is Hanif?" He said, "Hanif is the religion of (the prophet) Abraham who was neither a Jew nor a Christian, and he used to worship none but Allah (Alone)" Then Zaid went out and met a Christian religious scholar and told him the same as before. The Christian said, "You will not embrace our religion unless you get a share of Allah's Curse." Zaid replied, "I do not run except from Allah's Curse, and I will never bear any of Allah's Curse and His Anger if I have the power to avoid them. Will you tell me of some other religion?" He replied, "I do not know any other religion except Hanif." Sahih Bukhari 5:58:169 see also (Ibn Ishaq p. 102)

ዛይድ ቢሞትም መሐመድ የእርሱን አስተሳሰቦችና ፍልስፍናዎች ካነበበላቸው ታሪኮች ጋር በማገናኘት ለእምነታቸው መስረታ ተጠቅመውባቸዋል፡፡ «አብርሃም አይሁዳዊም ክርስቲያንም አልነበረም፣ በከተማችን በሚገኘው ካዕባ ውስጥ አላህን ያመልክ ነበር» ለሚለው የእስልምና ትምህርት መሐመድ ፅንሰ ሀሳቡን የወሰዱት በቀጥታ ዛይድ ከነገራቸው ነገር በመነሳት ነው፡፡ (Ibn Sa'd, vol.i, p.185)

በአሁኑ ቁርአን ውስጥ ያሉትን ስለክርስቲያኖችና ስለአይሁድ የተነገሩ ከ31 በላይ ጥቅሶችን የጻፋቸው ዛይድ እንደሆነ የመሐመድን ግለ ታሪክ (biography) የጻፉት ሰዎች በመጽሐፍቶቻቸው ላይ አስፍረውታል፡፡ እንደሁም ዛይድ ቢን አምር ፓጋን ዐረቦች ሴት ልጅን በሕይወት ይቀብሩ የነበረበትን ሁኔታ የተቃወመበትን ጥቅስ መሐመድ በቀጥታ እንዳለ ወስደው ነው በቁርአኑ ውስጥ የተጠቀሙበት፡፡ ለምሳሌ «ልጆቻችሁንም ድኽነትን ለመፍራት አትግደሉ፤ እኛ እንመግባቸዋለን፤ እነሱን መግደል ታላቅ ኃጢአት ነውና» (17፡31)፣ «በሕይወቷ የተቀበረችውም ሴት ልጅ በተጠየቀች ጊዜ በምን ወንጀል እንደተገደለች...» (81፡8) የሚሉት አነጋገሮች ይገኙበታል፡፡ እነዚህን ጥቅሶች ራሱ ዛይድ ቢን አምር በግጥም መልክ አድርጎ የጻፋቸው ቢሆንም መሐመድ ግን ወስደው በቁርአኑ ውስጥ ተጠቅመባቸዋል፡፡ ይህ ሀሳብ የመሐመድ አለመሆኑን ለማረጋገጥ ከተፈለገ ራሳቸው መሐመድም ያመልኩበት በነበረው በፓጋኖቹ የባዕድ እምነት ሥርዓት መሠረት ሴት ልጅን በሕይወት እያለች እንደቀበሩ የሚያስረዱ የተለያዩ ጽሑፎች አሉ፡፡ መሐመድ እንኳን የሴትን ልጅ በሕይወት መቀበር ተቃውመው በቁርአናቸው ሊጽፉ ይቅርና ራሳቸውም ሴትን ልጅ በሕይወት እያለች ይቀብሩ ነበር፡፡

**10.3 ላቢድ፡-** በዐረቢያ ምድር ከነበሩት ሰባት ታዋቂ ገጣሚያን ውስጥ አንዱ ነበር፡፡ ግጥሞቹም እንደ ኢምሩል ቃይስ ግጥሞች በኅብረተሰቡ ዘንድ በከፍተኛ ሁኔታ ተቀባይነት ነበራቸው፡፡ ሙስሊም መምህራኑ ላቢድ 2ኛውን የቁርአን ምዕራፍ በካዕባ ላይ ተገልጦ በማየቱ ግጥሞቹን ጥሎ እስልምናን እንደተቀበለ ያስተምራሉ፡፡ በሐዲሱ ላይ እንደተጻፈው መሐመድ የላቢድ ግጥሞችን «በጣም እውነተኛና ታማኝ ግጥሞች ናቸው» በማለት አሞካሽተዋቸዋል፡፡ ታዲያ መሐመድ የላቢድን ግጥሞች በማድነቅ ብቻ ያለልፏቸው ይሆን? ሐዲሱ ምን እንደሚል ተመልከቱ፡- "The Prophet said, "The most true words said by a poet was the words of Labid." He said, Verily, Everything except Allah is perishable and Umaiya bin As-Salt was about to be a Muslim (but he did not embrace Islam)" (Sahih Bukhari: Volume 5, Book 58, Number 181)

"The Prophet said, "The truest poetic verse ever said by a poet, is: Indeed! Everything except Allah, is perishable." (Sahih Bukhari Volume 8, Book 76, Number 496)

"Abu Huraira reported Allah's Messenger as saying: The truest word spoken by an Arab (pre-Islamic) in poetry is this verse of Labid:" Behold! Apart from Allah everything is vain." (Sahih Muslim Book 028, Number 5604)
መሐመድ የላቢድ ግጥሞችን ያሞካሹበት ምክንያት ላድናቆት ብቻ አይደለም፡፡ አብዘኞቹ የቁርአን አንቀጾች ግጥማዊ ዓይነት ይዘት አላቸው፡፡ መሐመድ የላቢድን ግጥሞች በቁርኑ አንቀጾች ውስጥ በሚፈልጉት መልኩ እንዲገቡ በማድረግ ግጥሞቹ የማቀናበሩን ሥራ በቀላሉ ስላቀላጠፉላቸው ነው አድናቆታቸውን ለግጥሞቹ የለገሷቸው፡፡ «በገጣሚ ከተነገሩ ቃላት ውስጥ በጣም እውተኛ የሆኑት የላቢድ ቃላት ናቸው» በማለት ነውኮ ያደነቋቸው!!! "The Prophet said, "The most true words said by a poet was the words of Labid."

**10.4 ሀሰን ቢን ጣቢት፡-** ይህ ሰው በይፋ የሚታወቅ የመሐመድ ጸሐፊ ነበር፡፡ ሀሰን ቢን ጣቢት ከመጀመሪያውም ቢሆን በዐረቢያ ምድር የስነ ሕግ ጉዳዮችን በግጥም ይጽፍ የነበረ ሰው ነው፡፡ መሐመድ ከመካ ወደ መዲና በተሰደዱበት ወቅት ጸሐፊያቸው አድርገው አብረው ይዘውት ሄደዋል፡፡ ለመሐመድ ማንኛውንም የግል ጉዳዮች ይጽፍላቸው የነበረ ቢሆንም ሙስሊሞችን ግን አይወዳቸውም ነበር፡፡ በሐዲሱ ላይ በግልጽ እንደተቀመጠው ሀሰን ቢን ጣቢት መሐመድ በመስጂድ የሚተርካቸውን ግጥሞች ያዘጋጅላቸው ነበር፡፡ ለፓጋን ዐረቦችና ለሌሎችም ተቃዋሚዎቻቸው የሚሆኑ የነቀፋ ጽሑፎችንም እንዲጽፍላቸው ያዙት ነበር፡፡

*From Sahih Bukhari: Muhammad approved Hassan b. Thabit to recite poetry in a mosque.* Volume 4, Book 54, Number 434: "Umar came to the Mosque while Hassan was reciting a poem. ('Umar disapproved of that). On that Hassan said, "I used to recite poetry in this very Mosque in the presence of one (i.e. the Prophet) who was better than you." Then he turned towards Abu Huraira and said (to him), "I ask you by Allah, did you hear Allah's Apostle saying (to me), "Retort on my behalf. O Allah! Support him (i.e. Hassan) with the Holy Spirit?" Abu Huraira said, "Yes."
Muhammad instructed Hassan, the poet to lampoon the pagans....4.54.435 "The Prophet said to Hassan, "Lampoon them (i.e. the pagans) and Gabriel is with you." (Sahih Bukhari Volume 4, Book 54, Number 435), The Prophet said to Hassan, "Abuse them (with your poems), and Gabriel is with you (i.e, supports you)." (Sahih Bukhari Volume 5, Book 59, Number 449) These Hadiths demonstrate that Hasan b. Thabit used to compose poems as per Muhammad's likes and dislikes.
Muhammad asked his poet Hassan to abuse the B. Qurayzah Jews through his

poetry. Sahih Bukhari: 5:59:449.

See also Sahih Bukhari: 4:56:731, Sahih Muslim Book 005, Number 2186, Book 031, Number 6077, Book 031, Number 6081.

መሐመድ ከመጀመሪያውም ቢሆን በመካ እንደነበሩት ገጣሚዎች ታዋቂና ተቀባይነት ያለው ታላቅ ሰው የመሆን ትልቅ ህልምና ፍላጎት የነበራቸው ቢሆንም ምንም ፊደል አለመቁጠራቸውና አለመማራቸው ታዋቂ የመሆን ህልማቸውን አከሽፎባቸው ቆይቶ ነበር፡፡ ቆይቶ ግን የእነ ዛይድ ቢን አምርንና የእነ ላቢድን ታዋቂነት እንደ ሽፋን በመጠቀም በእነርሱም ጥላ በመጠለል ወደ እውቅናው መምጣት ችለዋል፡፡ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ የታዋቂ ገጣሚዎቹን ግጥሞች በስፋት መጠቀም መጀመራቸው ታዋቂነትን እያተረፈላቸው መጥቶ ነበር፡፡ እንዲያውም ፊደል አለመቁጠራቸውን ያላወቁ አንዳንድ ሰዎች «ገጣሚ» እንደሆኑ አድርገው ያስቡቸአቸው እንደነበር ቁርአኑ ይናገራል፡፡ (21፡5፣ 52፡30) መሐመድም «ገጣሚ ነው» መባላቸው ቢያስደስታቸውም ገጣሚ ሳይሆኑ በሰማይ ካለው አምላክ የተላኩ መልእክተኛ መሆናቸውን መናገር ጀመሩ፡፡ 36፡69፡፡ በኋላ ላይ መሐመድ «ቁርአኑ ከሰማይ ወረደልኝ» ብለው መስበክ በጀመሩ ጊዜ ተቀባይነት ካጡባቸው ምክንያቶች ውስጥ አንዱ አብዛኛዎቹ አንቀጾቹ የመካ ሰዎች ቀድመው ከሚያውቋቸው ግጥሞች ጋር ተመሳስለው መገኘታቸው ነበር፡፡ ሰዎቹ በግልጽ «ይሄ የገጣሚዎቻችን ሥራ ነው» እያሉ የቃወሟቸው ነበር፡፡ አንድም ደግሞ መገለጦቹን ተቀብዬ መጣሁ ለማለት ወደ ሂራ ተራራ ላይ ወጥተው ሲመለሱ ፊታቸው ተለዋውጦ፣ ሰውነታቸው በላብ ተዘፍቆና አረፋ ደፍቀው ነበር፡፡ እቤትም ሲገቡ «ብርድ ብርድ አለኝ ደራርባችሁ አልብሱኝ» እያሉ ይናገሩ እንደሁም ሰይጣን ይዞኛል ብለው ስላሰቡ ራሳቸውንም ሊያጠፉ ይሞክሩ ስለነበር «ነቢይ ነኝ» ባሏቸው ሰዓት የመካ ሰዎች ፈጽሞ ሊቀበሏቸው አልቻሉም ነበር፡፡ እንዲያውም «ሰይጣን ይዞት ነው? ወይስ በጠንቋይ መተት ተደርጎበት?» እያሉ እርስ በእርሳቸው ይጠቋቆሙባቸው ነበር፡፡ በተለይም አብዛኛዎቹ የቁርአኑ አንቀጾች ቀድመው ከሚያውቋቸው የገጣሚያን ሥራዎች ጋር ተመሳሳይ መሆናቸው መሐመድ በሀሰት እያስተማሩ ለመሆኑ እርግጠኞች ነበሩ፡፡ ይህም በቁርአኑ ውስጥ ብዙ ቦታዎች ላይ ተጠቅሷል፡፡ «**እርሱ ቁርአን የተከበረ መልክተኛ ቃል ነው**፡፡ እርሱም የባለቅኔ ቃል (ግጥም) አይደለም፡፡ ጥቂትን ብቻ ታምናላችሁ፡፡ የጠንቋይም ቃል አይደለም፤ ጥቂትን ብቻ ታስታውሳላችሁ፡፡ ከዓለማት ጌታ የተወረደ ነው» ይላል ቁርአኑ፡፡ 69፡40-42፡፡ እንዲሁም 37፡36፣ 21፡5 ይመልከቱ፡፡

እዚሁ ላይ እንዳለን አንድ ነገር ላይ ማተኮር ፈለግኩ፡፡ «እርሱ ቁርአን የተከበረ መልክተኛ ቃል ነው» የሚለውን የመሐመድን አነጋገር በደንብ ተመልክታችሁታል? ምን ማለት ነው? መሐመድ በወቅቱ «ቁርአንን ገጣሚዎች ወይም ጠንቋዮች አልጻፉትም»

በማለት ተቃዋሚዎቻቸውን ለማሳመን ብለው እንደቀልድ ይናገሩት እንጂ ሳያስቡትኮ ትልቁን ምስጢር ነው ያወጡት፡፡ ቁርአን ማለት ሙስሊሞች እንደሚሉት የአላህ ቃል ሳይሆን የራሱ የመሐመድ ቃል ነው፡፡ በማያሻማ መልኩና ጥርት ባለ አገላለጽ «እርሱ ቁርአን የተከበረ መልክተኛ ቃል ነው» በማለት በቁርአኑ ላይ የተናገሩትኮ ባለጉዳዩ ራሳቸው መሐመድ ናቸው፡፡

10.5 ፐርሺያዊው ሰልማን፡- ሰልማን የዞራስትሪያንን እምነት ይከተል የነበረ ፐርሺያዊ ሰው ሲሆን መዲና ከተማ ውስጥ ይኖር የነበረና የባኑ ቁራይዛ የአይሁድ ጎሳ አባል የሆነ ሰው ጋር ተቀጥሮ እየሠራ ይኖር ነበር፡፡ መሐመድም በስደት ወደ መዲና በመጡ ሰዓት ተገኝተው ነበር፡፡ የቅርብ ጓደኛሞችም መሆን ችለዋል፡፡ መሐመድ ሊመሠርቱት ስላሉት እስልምናና ወደፊት ብዙዎችን በጦርነት የመማረክ ሀሳብ እንዳላቸው በሰፊው ሲነግሩት ሰልማንም በተራው ስለ ዞራስትሪያን እምነቱ በሰፊው ነግሮሯቸዋል፡፡ አይሻም እንደተናገረችው ቤተሰባዊ ግንኙነት በመፍጠር ሁለቱም ማታ ማታ አብረው እያመሹ ስለ ሃይማኖታዊ ጉዳዮች ያወሩ ስለነበር ሰልማንም የመሐመድን እምነት ተቀብሎ ተከታያቸው ከሆነ በኋላ ብዙ ነገሮችን እንደ አማካሪአቸው ሆኖ ይነግራቸው ነበር፡፡ ለምሳሌ መሐመድን በትሬንች ጦርነት ወቅት ትልቅና ሰፊ ጉድጓድ በመቆፈር ጠላቶችን ማጥቃት እንደሚቻል የመከራቸው ሰልማን ነው፡፡ ሰልማን ስለ ዞራስትሪያን ብቻም ሳይሆን ስለ አይሁድና ግሪኮች እምነት በደንብ ያውቅ ስለነበር ስለ እነርሱም በስፋት ለመሐመድ ነግሮሯቸዋል፡፡ መሐመድም ከዞራስትሪያን እምነት ቀጥታ የወሰዷቸው ሀሳቦች አሉ፡፡ ለምሳሌ በቁርአኑ ውስጥ በጀነት ሙብል፣ መጠጥ፣ ዝሙት... ያለበት የተንደላቀቀ ሕይወት መኖሩንና በሲኦል ስላለው መከራ የሚናገሩት አንቀጾች ከዞራስትሪያን እምነትና አስተምህሮ ጋር ተመሳሳይና አንድ ናቸው፡፡ መሐመድ ስለ ሲኦልና ጀነት ከሰልማን የሰሟቸውን ነገሮች በቀጥታ ወስደው ነው በቁርአኑና በሐዲሱ ውስጥ የተጠቀሙባቸው፡፡ (የሙስሊሞች ጀነት ምን እንምትመስል ዝርዝር መረጃውን በገጽ---ላይ በሰፊው እንዳየነው አስታውሱ)

10.6 መነኩሴው ባሂራ፡- ባሂራ ሶሪያ ውስጥ ይኖር የነበረ ክርስቲያን መነኩሴ ሲሆን ጊዮርጊስ የሚል የክርስትና ስም ነበረው፡፡ ሕግ ጥሶ ይሁን አሊያም የሃይማኖት ሕፀፅ ተገኝቶበት ብቻ ምክንያቱ በውል ባይታወቅም ከነበረበት የሶሪያ ገዳም ተወግዞና ተባሮ ሊወጣ ችሏል፡፡ ከዚያም ወደ ዐረቢያ ምድር ሄዶ በዚያ መኖር እንደጀመረ ከመሐመድ ጋር ተገናኝቷል፡፡ "Bahira was a Nestorian Christian monk who lived in Sham (Syria). His Christian name was Georgius. It is believed that he was expelled from the monastery for certain offences. To expiate it, he set out on a mission to Arabia.

In Mecca, he met Muhammad, became intimate with him and stayed with him. He had confidential conversation with Muhammad, in which he surely told Muhammad many facets of Christianity. It is not clear why Bahira was expelled from the Syrian church. Could it be that he held views on Christianity that was blasphemous to the Nestorian church? Or could it be that he did some criminal act? No one knows. Anyway, Muhammad had a wealth of information on Christianity (apocryphal or main-stream) from this monk. The verses in the Qur'an dealing with Christianity must have emanated from Bahira, the monk. Muhammad simply re-wrote them with the help of his Qur'an collectors or scribes." (Hughe's Dictionary of Islam)

መሐመድም በወቅቱ በእምነት ጉዳይ ላይ በአስከፊ ሁኔታ ያሉትን የመካ ሕዝቦች ለመለወጥ ከፍተኛ ጉጉት ስለነበራቸው ብዙ ነገሮችን ለማወቅ ይጥሩ ነበር፡፡ ለዚህም እንዲረዳቸው ከዐረቢያ ምድር ውጭ ያገኙዋቸውን ሰዎች ሁሉ ስለ እምነታቸው አጥብቆ ይጠይቁ ነበር፡፡ ለንግድ በሄዱባቸው ሀገራት ሁሉ ይህንን ሲያድርጉ ቆይቷል፡፡ አሁን ደግሞ ይህንን ከፍቶት የተሰደደ መነኩሴ ሲያገኙት በደስታ ነበር የተቀበሉት፡፡ መቼም ሲያገጣጥም አይጣል ነውና መነኩሴው ባሂራም ከመሐመድ ጋር ተቀምጦ ክርስትናውን ከመነሻው እስከ መድረሻው ድረስ በደንብ አስተምሯቸዋል፡፡ መጽሐፎፉንም ሰጥቷቸዋል፡፡ ነገር ግን መሐመድ ሌላ እምነት ይመሠርታሉ ብሎ አላሰበም ነበር፡፡ ቁርአኑ ውስጥ ከክርስትናው ጋር በተገናኘ የተጻፉት ነገሮች በሙሉ ምንጫቸው ይህ መነኩሴና መጻሕፍቶቹ ናቸው፡፡ ከዚህ በኋላ መሐመድ ሁኔታዎችን በሚፈልጉት መልኩ እየለወጡ ነው ቁርአኑን ያዘጋጁት፡፡

‹‹መጽሐፍ ቅዱስና ቁርአን ሁለት ፍጹም የተለያዩ መጽሐፎች እስከሆኑ ድረስ እንዴት አንድ ዓይነት ታሪኮችን በጋራ ሊይዙ ቻሉ?›› እያልኩ ስንጠይቅ ለነበረው ጥያቄ መልሱ ይሄ ብቻ ነው፡፡ አኩራፊው መነኩሴ ያመጣው ጣጣ ነው፡፡ የነገሮች አቀናባሪ ደግሞ የእውነት ተቃዋሚ የሆነው ሐሰተኛው አጅሬ ጥንተ ጠላት ዲያብሎስ ነው፡፡ መሐመድን መጀመሪያ ለወገኖቹ ቀናኢ የሆኑ አስመስሎ በማስነሳት ከዚያም ‹‹ወዳንተ ተልኬ የመጣሁት መልአኩ ጂብሪል ነኝ››፣ ‹‹አንተ የነቢያት ሁሉ የበላይና መደምደሚያ ነህ›› እያለ ሲጫወትባቸው ከቆየ በኋላ በመጨረሻ ነገሮችን አልጋ በአልጋ አደረገላቸው፡፡ በዓለማዊ አስተሳሰብ ከታየ ነገሩ እውነት ላይመስል ይችላል፡፡ ነገር ግን የሰይጣንን ጥበበብና እጅግ ረቂቃዊ አሠራር የተገነዘበ ሰው አንድ ነገር በቀላሉ መረዳት ይችላል፡፡ አጅሬ ሰይጣን በፈተና ብዛት መነኩሴውን እንዲወድቅ በማድረግ ከገዳም ካስወጣው በኋላ እውነተኛውን እምነት ለማጥፋት ሲል ነው መነኩሴውን ከመሐመድ

ጋር ያገናኘው፡፡ መሐመድንም ለጽድቅ የቆሙ በማስመሰል ሰይፍ አስጨብጦ በክርስቲያኖች ላይ አዘመታቸው፡፡ የግብር ልጆቹንና ተከታዮቹንም መጠቀሚያ በማድረግ ይኸው እስከዛሬም ድረስ የሚሊዮኖችን ሕይወት እየቀጠፈና ደም እያፈሰሰ ይኖራል፡፡ ወደፊትም ቢሆን እንደዚያው፡፡ የሰው ልጆች ሁሉ ጠላት ክፉ ዲያብሎስ!

10.7 ኢብን ቁምታ፡- ኢብን ቁምታ መካ ከተማ ውስጥ በባርነት ይኖር የነበረ ክርስቲያን ነበር፡፡ መሐመድ የቁርአኑን 19ኛ ምዕራፍ «ሱረቱ መሪየም» የሚለውን ስለ ኢየሱስና እናቱ ድንግል ማርያም የሚናገረውን ክፍል እንዲጽፍላቸው አድርገውታል፡፡ ይህንንም ሐዲሱ በግልጽ ይመሰክራል፡፡ በቡኻሪ ሐዲስ 4፡56፡814 ላይ ክርስቲያን የነበረ አንድ ሰው ቁርአንን ለመሐመድ ይጽፍላቸው እንደነበር በግልጽ ተጽፏል፡፡ ኢብን ቁምታ ወደ እስልምናው ተቀይሮ የነበረ ቢሆንም ተመልሶ እንደገና ክርስቲያን እንደሆነና እንደተገደለም ተጽፏል፡፡ መጀመሪያ ላይ ወደ እስልመናው እንደተቀየረ ስለ ኢየሱስና እናቱ ድንግል ማርያም የሚያውቀውን ሁሉ ለመሐመድ እየነገራቸው እንደገና እርሳቸው በሚፈልጉት መንገድ እያደረገ ይጽፍላቸው ነበር፡፡ ኢብብን ቁምታ በመጨረሻም «መሐመድ ምንም አያውቅም፣ እኔ ነኝ የጻፍኩለት» በማለት እውነቱን ስለተናገረ ሊገደል ችሏል፡፡ "Narrated Anas: There was a Christian who embraced Islam and read Surat-al-Baqara and Al-Imran, and he used to write (the revelations) for the Prophet. Later on he returned to Christianity again and he used to say: "Muhammad knows nothing but what I have written for him." Then Allah caused him to die." (Sahih Bukhari: Volume 4, Book 56, Number 814)

A Christian who converted to Islam wrote Muhammad's revelations; then he reverted back to Christianity and claimed that Muhammad knew nothing and he wrote the Quran for Muhammad. (The Origins of The Koran, p.102)

ካሁን በፊት አብድ አላህ ኢብን ሳድ ኢብን አቢ ሳርህ ስለተባለው የመሐመድ የግል ጸሐፊ በሰፊው አይተናል፡፡ ኢብን አቢ ሳርህ ስለ ኢብን ቁምታ ምስክርነቱን ሰጥቷል፡፡ አቢ ሳርህ መሐመድን ጥሎ ጠፍቶ ከመዲና ወደ መካ በተመለሰ ሰዓት በመዲና ስለነበረው ሁኔታ ለቁራይሾቹ እንዲህ በማለት ነግሮአቸዋል፡- «መሐመድን ያስተምረው የነበረው ክርስቲያኑ ባሪያ ብቻ ነበር፡፡ እኔም ለመሐመድ እጽፍለት ነበር፣ የፈለኩትንም ነገር እቀይር ነበር፡፡» በማለት ተናግሯል፡፡ "A more ancient historian, Wakidi, has the following sentence in which it is suggested that 'Abdallah b. Sa'd b. Abi Sarh, and a Christian slave, ibn Qumta, had something to do with the Koran. And ibn Abi Sarh came back and said to Quraish: "It was only a Christian slave who was teaching him (Muhammad); I used to write to him and change whatever I wanted." (Alphonso Mingana, *The Transmission of the Koran*, The Origins of The Koran, p.103)

10.8 ጃብር፡- አሪትንና ወንጌልን በደንብ የሚያውቅ ሰው የነበረ ሲሆን መሐመድም እቤቱ ድረስ እየሄዱ ስለ ክርስትናው ይጠይቁት ነበር፡፡ ስለ ቅዱስ ዳዊትና ልጁ ሰሎሞን በሰፊው አስረድቷቸዋል፡፡ በቁርአን ውስጥ የተካቱ የመዝሙረ ዳዊት ጥቅሶች ከጃቢር የተገኙ ናቸው፡፡

10.9 ሳቢያኖች፡- በሶሪያ ይኖሩ የነበሩ ሕዝቦች ሲሆኑ በክርስትናው እንዳሉ ተደርጎ ይታሰብ እንጂ በከዋክብትና በልዩ ልዩ አማልክት ያምኑ ነበር፡፡ መሐመድ እነርሱን እውነተኛ ክርስቲያኖች ናቸው ብለው ያስቡ ስለነበር ከእነዚህ ሰዎች የወሰዷቸው ብዙ ልማዶች አሉ፡፡ ለምሳሌ ሳቢያኖች በሞተ ሰው ላይ ያደርጉት የነበረውን ጸሎት መሐመድም በጸሎታቸው ውስጥ የአላህንና የራሳቸውን ስም በማስገባት እንዳለ ወስደው ተጠቅመውበታል፡፡ (W.St. Clair Tisdal, *The Sources of Islam*, The Orgins of the Koran, pp.236-237) ሳቢያኖች ፀሐይ ስትገባ ጀምረው እስክትወጣ ድረስ የመጾም ልማድ ነበራቸው፡፡ መሐመድም ወቅቱን በማዞር ጾማቸውን ከማለዳ ጀምረው ፀሐይዋ እስከምትጠልቅበት ድረስ አደረጉት፡፡ በቁርአኑም ላይ «እናንተ ያመናችሁ ሆይ! ጾም በነዚያ ከናንተ በፊት በነበሩት ሕዝቦች ላይ እንደተጻፈ በናንተም ላይ ተጻፈ» ብለው ያሉት ለዚህ ነው፡፡ ሱረቱ አል-በቀራህ 2፡183፡፡

መሐመድ ሳቢያኖችን እውነተኛ ክርስቲያኖች ናቸው ብለው ስላሰቡ ይበልጥ ደግሞ በአላህና በእርሳቸው ቢያምኑ በፍርድ ቀን ምንም ዓይነት ፍርሃት እንደማያጋጥማቸው በቁርአኑ ላይ ተናግረውላቸዋል፡፡ «እነዚያ ያመኑና እነዚያም ይሁዳውያን የሆኑ፣ ሳቢያኖችም፣ ክርስቲያኖችም ከእነርሱ በአላህና በመጨረሻው ቀን ያመና መልካምን ሥራ የሠራ ሰው በእነሱ ላይ ፍርሃት የለባቸውም፤ እነርሱም አያዝኑም» ይላል ቁርአኑ፡፡ 2፡62፡፡ እንዲሁም ይህንኑ አገላለጽ በ5፡69 ላይ በድጋሚ ይጠቅሰዋል፡፡ 22፡17 ላይ ደግሞ «መጁሶችም» በማለት ሶራስትሪያንን አካተዋቸዋል፡፡ መሐመድ ስለ ሳቢያኖችና ክርስቲያኖች መናገር ሲጀምሩ «እነዚያ ያመኑና...» ብለው በመናገር ሳያስቡት በቂ ምስክርነት ነውኮ የሰጡት! ምክንያቱም ቀድመው ያመኑ መሆናቸውን በግልጽ መስክረውላቸዋል፡፡ ነገር ግን ቀድመው «ያመኑ» ቢሆኑም መልሰው እንደገና በአላህ በእሳቸውም ማመን እንዳለባቸው ነው የተናገሩት፡፡

10.10 ከድጃ፣ ዋራቃና ኡቤይዱላህ፡- ዋራቃ የመሐመድ የመጀመሪያ ሚስት የሆነችው የከድጃ የአጎቷ ልጅ ነው፡፡ ዋራቃ ከፓጋን ዐረቦቹ ተለይቶ ወደ ክርስቲያንነት ተቀይሮ ስለነበር የወንጌል መጽሐፎችን ወደ ዐረብኛ ቋንቋ እየተረጎመና እየጻፈ ያነብ ነበር፡፡ ይህም በሐዲሱ ላይ ተጠቅሷል፡፡ ዋራቃ መጽሐፍ ቅዱስን ያነብና ይጽፍ የነበረው በዐረብኛ ቋንቋ ብቻ ሳይሆን መጽሐፍ ቅዱስ ለመጀመሪያ ጊዜ በተጻፈበት

በእብራይስጥኛ ቋንቋም ጭምር ያነብና ይጽፍ እንደነበር ሐዲሱ ይናገራል፡፡ ከድጃም መሐመድን ወደ ዋራቃ ዘንድ በተደጋጋሚ ትወስዳቸደው ነበር፡፡ ከድጃ መሐመድ ለሃይማኖት መስረታ በተነሡበት ወቅት እርሷ የመጀመሪያዋ ሙስሊም እንደሆነችና ለመሐመድም የተለያዩ እገዛዎችን ታደርግላቸው እንደነበር ከዚህ በፊት በደንብ አይተናል፡፡ አሁንም መሐመድን ክርስቲያን ወደሆነው ዘመዷ ቤት ለምን ይዛቸው እንደምትሄድ መገመት ይቻላል፡፡ መሐመድም ወደ ዋራቃ ቤት በተደጋጋሚ እስከሄዱ ድረስ ዋራቃ የተረጎማቸውን የወንጌል ክፍሎች ለማግኘታቸው በጣም እርግጠኞች መሆን እንችላለን፡፡ የሐዲሱን ማስረጃዎች እንያቸው፡-

*"The Prophet returned to Khadija while his heart was beating rapidly. She took him to Waraqa bin Naufal who was a Christian convert and used to read the Gospels in Arabic Waraqa asked (the Prophet), "What do you see?" When he told him, Waraqa said, "That is the same angel whom Allah sent to the Prophet) Moses. Should I live till you receive the Divine Message, I will support you strongly."* (Sahih Bukhari Volume 4, Book 55, Number 605)

We learn from Sahih Bukhari that Waraqa used to read the Gospel in Arabic. This confirms that the Arabic translation of the Gospel was available during Muhammad's time. Not only that Waraqa read the Gospel in Arabic, he also translated Gospel in his own version in Arabic. Sahih Bukhari confirms this: *"Khadija then took him to Waraqa bin Naufil, the son of Khadija's paternal uncle. Waraqa had been converted to Christianity in the Pre-Islamic Period and used to write Arabic and write of the Gospel in Arabic as much as Allah wished him to write"* (Sahih Bukhari Volume 6, Book 60, Number 478)

Waraqa even knew how to read and write in Hebrew! Sahih Bukhari confirms this: *"Khadija then accompanied him to her cousin Waraqa bin Naufal bin Asad bin 'Abdul 'Uzza, who, during the PreIslamic Period became a Christian and used to write the writing with Hebrew letters. He would write from the Gospel in Hebrew as much as Allah wished him to write"* (Sahih Bukhari Volume 1, Book 1, Number 3)

The above information, especially those quotes from the Sahih Bukhari will leave one without any doubt that Waraqa, as well as Khadijah were big-time contributors to the compilation of the Qur'an- especially those verses dealing with Christianity and Judaism.

ከዚሁ ጋር በተያያዘ የኡቤይዱላህንም ጉዳይ አብረን ማየት እንችላለን፡፡ ኡቤይዱላህ ማለት የአብድ አል-ሙጣሊብ የልጅ ልጅ ሲሆን ለመሐመድ ደግሞ የአጎታቸው ልጅ

ነው፡፡ መካ ውስጥ የፓጋን ዐረቦችን እምነት ትቶ እስልምናን በመቀበል መሐመድን ተከተላቸው፡፡ መሐመድ በጦርነት እንዳይጎዱ በማለት ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ ኢትዮጵያ ከላኳቸው ሰዎች ውስጥ አንዱ ኡቤይዱላህ ነበር፡፡ ነገር ግን በኋላ ላይ እስልምናውንም ትቶ ክርስቲያን ሆኖ በዚያው ኖሮ ነው የሞተው፡፡ ወደ ክርስትና ከመለወጡ በፊት ግን ለመሐመድ ስለ ክርስትና የተጻፉ ብዙ ጽሑፎችን ወደ ዐረብኛ ቋንቋ ተርጉሞ እየጻፈ ይልክላቸው ነበር፡፡ በቁርአኑ ውስጥ ከክርስትናው ጋር በተገናኘ በተጠቀሱት ነገሮች ላይ የኡቤይዱላህም አስተዋፅኦ ከፍተኛ ነበር፡፡

10.11 አብዱላህ ቢን ሰላምና ሙካያሪቅ፡- ሌላው ለቁርአን ክርስቲያናዊ ምንጭ በመሆን ለመሐመድ ከፍተኛ እገዛ ያደረጉላቸው ሁለት የአይሁድ ተወላጆች አሉ፡፡ መሐመድ በስደት መዲና እንደደረሱ የባኑ ቃይኑቃ የአይሁድ ጎሳ አባል የነበረና እስልምናን ተቀብሎ መሐመድን የተከተለ አንድ ሰው ነበር፡፡ መሐመድ «አብዱላህ ቢን ሰላም ቢን አል-ሀሪዝ» ብሎ በሰየሙት ስሙ ነው የሚታወቀው፡፡ (Ibn Ishaq, p.239) ሌላው መሐመድን የተከተላቸው የአይሁድ ተወላጅ የሆነው ሙካያሪቅ ይባላል፡፡ እነዚህ ሁለት የአይሁድ ተወላጆች ስለ ኦሪት ሕግ ለመሐመድ በቂ መረጃዎችን እንደሰጧቸው የመሐመድን ግለ ታሪክ (biography) የጻፉ ሰዎች ዘግበዋል፡፡

10.12 አን-ናድር ቢን አል-ሀሪዝ፡- መካ ውስጥ አን-ናድር ቢን አል-ሀሪዝ የሚባል ብዙ የጥንት ታሪኮችንና ተረቶችን የሚያውቅ ሽማግሌ ሰው ነበር፡፡ ይህ ታሪክና ተረት አዋቂ ሽማግሌ የመሐመድ ጎረቤት ነበር፡፡ ገና እንደጀመሩ አካባቢ መሐመድ ሰዎችን ሰብስበው ታሪኮችን ሲነግሯቸው «የአን-ናድር ተረቶች የተሻሉ ናቸው» በማለት ጥለዋቸው ይሄዱ ነበር፡፡ «የምትናገራቸው ነገሮች ሁሉ ቀድሞ የምናውቃቸው ተረቶች ናቸው» እያሉም ያሾፉባቸው ነበር፡፡ ይህም ቁርአኑ ላይ ብዙ ቦታ ተጠቅሷል፡፡ «ይህ የመጀመሪያዎቹ ሰዎች ጽሑፍ ተረቶች እንጂ ሌላ አይደሉም ይላሉ» (8፡31)፤ «ጌታችሁ በመሐመድ ላይ ምንን አወረደ በተባሉ ጊዜ እርሱ የመጀመሪያዎቹ ሕዝቦች ተረቶች ነው ይላሉ» (16፡24)፤ «ይህንን እኛም ከእኛ በፊትም የነበሩት አባቶቻችን በእርግጥ ተቀጥረናል፤ ይህ የመጀመሪያዎቹ ሰዎች ተረቶች እንጂ ሌላ አይደለም አሉ» (23፡83) እንሁም በተመሳሳይ አገላለጽ 25፡5፣ 27፡68፣ 46፡17፣ 68፡15 ላይ ተጠቅሷል፡፡ ሰዎች በዚህ መልኩ ተቃውሞ ሲያበዙባቸው መሐመድ የተሻሉ ታሪኮችንና ተረቶችን ያውቃል የተባለውን አን-ናድርን ቀርበው ብዙ ታሪኮችን እንዲነግሯቸው ስለጠየቁት እርሱም ነግሯቸዋል፡፡ ነገር ግን መሐመድ በሽማግሌው የተነገሩአቸው ታሪኮች ከአምላክ እንደመጡላቸው አድርገው ማውራት ሲጀምሩ አን-ናድር ድርጊቱን እንዲያቆሙ ቢመክሯቸውም እምቢ ስላሉ ምሥስጢራቸውን ይናገሩባቸው ጀመር፡፡ መሐመድም

ከስደት በኋላ መካን ሲቆጣጠሩ በመጀመሪያ አን-ናድርን ነው እንዲገደል ያደረጉት፡፡

10.13 ኡቤይ ቢን ካብ፡- የመሐመድ የግል ጸሐፊው የነበረ ሲሆን ቁርአንን ከሰበሰቡት 6 ሰዎች ውስጥ አንዱ ነው፡፡ ቁርአንን የሰበሰቡት የተቀሩት 5 ሰዎች ዛይድ ኢብን ጣቢት፣ ሙአድህ ኢብን ጃበል፣ አቡ አል-ዳርዳ፣ ሳድ ኢብን ኡቤይድና አቡ ዛይድ ናቸው፡፡ (ibn sa'd, vol.i, p.457) ኡቤይ ቢን ካብ በሌላ ስም «አቡ ሙንድሂር» ተብሎም ይጠራል፡፡ መሐመድ ከመካ ወደ መዲና እንደተሰደዱ መዲና ውስጥ መጀመሪያ ላይ ሰልመው ከተከተሏቸው ሰዎች ውስጥ አንዱና ዋነኛው ኡቤይ ቢን ካብ ነው፡፡ መሐመድም አማካሪአቸውና ጸሐፊአቸው አድርገው ይጠቀሙበት ነበር፡፡ ከመካ ከተማ ውጭ መዲና ውስጥ ለመሐመድ ወርደውላቸዋል የሚባሉትን የቁርአን አንቀጾች ብዙዎቹን የጻፋቸው ኡቤይ ቢን ካብ ነው፡፡ እነዚህ የመዲና አንቀጾች መካ ውስጥ እንደተጻፉት የግጥም ይዘት የላቸውም፡፡ ምክንያቱም ኡቤይ ቢን ካብ ግጥም ስለማይችልና ስለማይወድ በደብዳቤ መልክ ነበር የጻፋቸው፡፡ ብዙ ገጣሚዎችም ይኖሩ የነበረው በመካ ነበር፡፡

The following quoted Hadith tells us that some verses of the Qur'an were written by people other than Muhammad's official Qur'an scribes. Please note that Khuzaima b. Thabit al-Ansari, mentioned in this Hadith was not one of the official Qur'an writers of Muhammad.

*Narrated Zaid bin Thabit: "When we wrote the Holy Quran, I missed one of the Verses of Surat-al-Ahzab which I used to hear Allah's Apostle reciting. Then we searched for it and found it with Khuzaima bin Thabit Al-Ansari. The Verse was:- 'Among the Believers are men Who have been true to Their Covenant with Allah, Of them, some have fulfilled Their obligations to Allah (i.e. they have been Killed in Allah's Cause), And some of them are (still) waiting" (33.23) So we wrote this in its place in the Quran."* (Sahih Bukhari Volume 5, Book 59, Number 379)

10.14 አይሻ፡- መሐመድ አይሻን አያቷ በሚሆኑበት ዕድሜአቸው በ53 ዓመታቸው እርሷ ደግሞ የ9 ዓመት ሕጻን ልጅ ሳለች ነው አግብተው ወሲብ የፈጸሙባት፡፡ (ይህንን በተመለከተ የሐዲሱን ማስረጃና ዝርዝር መረጃውን ከገጽ----ጀምሮ ይመልከቱ፡፡) በዚህ ዕድሜዋ አይሻ መሐመድ የነገሯትን ማንኛውንም ነገር አምና እንደምትቀበላቸው ምንም ጥርጥር የለውም፡፡ ስለዚህ ከሌሎቹ ሚስቶቻቸው በተለየ ሁኔታ አይሻ ጋር ብቻ ሲተኙ መገለጦች ይመጡላቸው እንደነበር ራሳቸው መሐመድ በሐዲሱ ላይ ተናግረዋል፡፡ ሌሎቹ ሚስቶቻቸውን «ከሰማይ ወረደልኝ» ሲሏቸው እንኳ በቀላሉ አምነው ላይቀበሏቸውና ብዙ ጥያቄዎችንም ሊጠይቋቸው ይችሉ ነበር፡፡ ስለዚህ የ9

ዓመቷ አይሻ መሐመድ ከእርሷ ጋር ሲተኙ መገለጦቹ የሚመጡላቸው ብቸኛዋ ሚስታቸው ልትሆን ችላለች፡፡ ይህንንም ሐዲሱ ያረጋግጥልናል፡፡ ከእርሷ ጋር ብቻ ሲሆኑ በሌላ ጊዜ ሲነገራቸው የሰሙትን በቃላቸው ያነቡና ይተርኩ እንደነበር አይሻ መስከራለች፡፡ መሐመድም «መገለጦቹን ጂብሪል ሰጠኝ» እያሉ ይነግሯት ነበር እንጂ እርሷ ምንም የምታየው ነገር አልነበረም፡፡ እንዲያውም «አንቺ ባታይውም ጂብሪል ሰላም ብሎሻል» ይሏት ነበር፡፡ መሐመድ መገለጦችን እንደተቀበሉ ለማስመስከር የአይሻን የሕጻንነት አእምሮ ተጠቅመውበታል፡፡ ራሳቸውም በሐዲሱ ላይ በግልጽ እንደተናገሩት «አይሻ ጋር ብቻ ስተኛ ነው መገለጦቹ የሚመጡልኝ» ነው ያሉት፡፡ ስለዚህ አይሻ በቀጥታም ባይሆን በተዘዋዋሪና ባላወቀችው መንገድ መሐመድ ላዘጋጁቸው ቁርአን የጭምብል ሽፋናቸው ሆና አገልግላቸዋለች፡፡ እንዲያውም መሐመድ ከሞቱ በኋላ አይሻ አንድ ጸሐፊ የቁርአንን ጥቅስ በምትፈልግበት መንገድ እንዳጻፈች ሐዲሱ በግልጽ ይናገራል፡፡ Divine inspiration came to Muhammad only when he slept with Aisha (5:57:119): “The people used to send presents to the Prophet on the day of 'Aisha's turn. 'Aisha said, "My companions (i.e. the other wives of the Prophet) gathered in the house of Um Salama and said, "0 Um Salama! By Allah, the people choose to send presents on the day of 'Aisha's turn and we too, love the good (i.e. presents etc.) as 'Aisha does. You should tell Allah's Apostle to tell the people to send their presents to him wherever he may be, or wherever his turn may be." Um Salama said that to the Prophet and he turned away from her, and when the Prophet returned to her (i.e. Um Salama), she repeated the same, and the Prophet again turned away, and when she told him the same for the third time, the Prophet said, "O Um Salama! Don't trouble me by harming 'Aisha, for by Allah, the Divine Inspiration never came to me while I was under the blanket of any woman amongst you except her.” (*Sahih Bukhari Volume 5, Book 57, Number 119*) see also Sahih Bukhari Volume 3, Book 47, Number 755.

Muhammad told Aisha that Gabriel greeted her (8:74:270):

“Narrated 'Aisha: that the Prophet said to her, "Gabriel sends Salam (greetings) to you." She replied, "Wa 'alaihi-s-Salam Wa Rahmatu-l-lah.” (meaning:Peace and Allah's Mercy be on him) (*Sahih Bukhari Volume 8, Book 74, Number 270*)

Muhammad used to recite Qur’an while reclining on the lap of a menstruating Aisha (3:591)

“A'isha reported: The Messenger of Allah would recline in my lap when I was menstruating, and recite the Qur'an.” (Sahih Bukhari Book 003, Number 0591)

The following Hadith informs us that after Muhammad's death a Qur'an was compiled exclusively for Aisha. Then Aisha dictated to her scribe a verse of the Qur'an.

"Abu Yunus, the freed slave of 'A'isha said: 'A'isha ordered me to transcribe a copy of the Qur'an for her and said: When you reach this verse:" Guard the prayers and the middle prayer" (2:238), inform me; so when I reached it, I informed her and she gave me dictation (like this): Guard the prayers and the middle prayer and the afternoon prayer, and stand up truly obedient to Allah. 'A'isha said: This is how I have heard from the Messenger of Allah." (Sahih Muslim Book 004, Number 1316)

10.15 ዓይነ ስውሩ ኢብን ኡም ማክቱም፡- ኢብን ኡም ማክቱም ዓይነ ስውር ቢሆንም የቁርአንን ይዘት በማስለወጥ ረገድ የራሱን አስተዋፅኦ ያደረገ ሰው ነው፡፡ ቀድመው ከሰለሙ የመሐመድ ተከታዮች ውስጥ አንዱ ስለሆነ ሁለቱም የቀረበ ግንኙነት ነበራቸው፡፡ ኢብን ኡም ማክቱም መሐመድ ተከታዮቻቸውን ለጂሃድ ሲያነሳሱ በጂሃድ የተሳተፉና እቤታቸው የተቀመጡ ሙስሊሞች በጀነት እኩል ዋጋ እንደማያገኙ ሲናገሩ ይሰማል፡፡ ይህን ጊዜ ኢብን ኡም ማክቱም በጂሃድ መሳተፍና መጋደል ስለማይችል ወደ መሐመድ ጠጋ ይልና «የእኔስ ጉዳይ…?» ብሎ ይጠይቃቸዋል፡፡ መሐመድም ቀድሞ ያጽፉት የነበረውን ዛይድን ፈጥነው ይጠሩትና «ከምእመናን የጉዳት ባለቤት ከሆኑት በቀር…» የሚል ቃል መጀመሪያው ጥቅስ ላይ እንዲጨምር ይነግሩታል፡፡ ከዚያም ይህ የተጨመረው አዲስ ጥቅስም በድጋሚ የወረደልኝ ነው አሉ፡፡ ጥቅሱም በቁርአኑ 4፡95 ላይ ይገኛል፡፡ ሙሉ ታሪኩንም ሐዲሱ ብዙ ቦታ ላይ ዘግቦታል፡፡

Narrated Al-Bara: "When the Verse 'Not equal are those of the believers who sit (at home)' (Quran 4:95) was revealed, Allah Apostle called for Zaid who wrote it. In the meantime Ibn Um Maktum came and complained of his blindness, so Allah revealed: 'Except those who are disabled (by injury or are blind or lame…'" etc.) (Sahih Bukhari Volume 6, Book 60, Number 117) _"There was revealed: 'Not equal are those believers who sit (at home) and those who strive and fight in the Cause of Allah.' (4:95). The Prophet said, "Call Zaid for me and let him bring the board, the inkpot and the scapula bone (or the scapula bone and the ink pot).'" Then he said, "Write: 'Not equal are those Believers who sit…", and at that time 'Amr bin Um Maktum, the blind man was sitting behind the Prophet . He said, "O Allah's Apostle! What is your order For me (as regards the above Verse) as I am a blind man?" So, instead of the above Verse, the following Verse was revealed: 'Not equal are those believers who sit (at home) except those who are disabled (by injury or are blind or lame etc.) and those who strive and fight in the cause of Allah.'" (Sahih

Bukhari Volume 6, Book 61, Number 512) see also (Sahih Muslim Book 020, Number 4676)

**10.16 ራሳቸው መሐመድ በፈጠራ ያዘጋጁዋቸው ጥቅሶች፡-** ቁርአኑ በግልጽ እንደሚናገረው መሐመድ ምንም ማንበብና መጻፍ የማይችሉ ሰው (illiterate) ስለነበሩ የቁርአን ጥቅሶችን ራሳቸው ያዘጋጁሉ ብሎ ማሰብ አጠራጣሪ ሊሆን ይላል፡፡ ነገር ግን መሐመድ ከራሳቸው ሕሊና ያፈለቋቸው አንዳንድ ጥቅሶች በቁርአኑ ውስጥ ይገኛሉ፡፡ በቁርአኑም 69፡40 ላይ በግልጽ *‹‹እርሱ ቁርአን የተከበረ መልክተኛ ቃል ነው››* ተብሎ ነው የተጻፈው፡፡ ከቁርአኑ ላይ ሌሎች ምሳሌዎችንም ማየት እንችላለን፡- ‹‹ከአላህ ሌላ ዳኛን እፈልጋለሁን? ከተጠራጣሪዎቹም አትሁን›› (6፡114)፤ ‹‹…እኔ በናንተ ላይ ጠባቂ አይደለሁም›› (6፡104) የሚሉት አነጋገሮች ከሌላ የተወሰዱ ሳይሆኑ ራሳቸው መሐመድ ፈጥረው የተናገሯቸው ናቸው፡፡ The words, 'I am not a keeper over you' (6:104), 'Shall I seek for judge other than Allah?'(6:114) are undoubtedly Muhammad's own words.

እንዲሁም በተመሳሳይ ሁኔታ ቀጥሎ ባሉት የቁርአን ጥቅሶች ላይ ያሉት አገላለጾች በትክክል የመሐመድ የፈጠራ ንግግሮች መሆናቸውን ዐረብኛውን ቁርአን በደንብ የሚያውቁት ሰዎች ያስረዳሉ፡፡ 1:1-7, 19:9, 19:64, 37:164, 51:50, 70:40-41, 86:17, 53:2፡፡ ትርጉሙን ለማስቀየር ሲባል በአንዳንዶቹ ጥቅሶች ላይ በቅንፍ ውስጥ እየተደረገ ‹‹በላቸው›› የሚል ቃል በአማርኛው ቁርአን የተጨመረ ቢሆንም በዐረብኛው ቁርአን ላይ ግን ተመሳሳይ ትርጉም ያለውን ‹‹ኩል/kul›› የሚለውን ቃል ተጽፎ አናገኘውም፡፡ በእንግሊዝኛውም ቢሆን የዩሱፍ አሊ ትርጉም ‹‹say›› የሚለውን ቃል በቅንፍ አድርጎ የተጠቀመ ቢሆንም ሌሎቹ እነ ፒክታልና ሻኪር ግን በትርጉማቸው ላይ ‹‹በላቸው/say›› የሚለውን ቃል ፈጽሞ አልተጠቀሙም፡፡

ርዕሳችንን ‹‹ቁርአኑ ከሰማይ የወረደ ሳይሆን የራሱ የሆኑ የተለያዩ ምንጮች ስላሉት ሊታመን አይችልም›› የሚል መሆኑን እናስታውስና ርዕሱን እናጠቃለው፡፡ ቁርአኑ በአጠቃላይ የተለያዩ ምንጮች አሉት፡፡ እስካሁን በሰፊት እንዳየነው ቁርአኑ በአጠቃላይ የብዙ ሰዎች እጅ አለበት፡፡ ቅንብሩ ላይ ብዙዎች ናቸው የተሳተፉበት፡፡ እንደነ ኢብን አቢ ሳርህ ያሉት ደግሞ የግል ሀሳባቸውንና ምኞታቸውንም ጨምረው ጽፈውታል፡፡ እንዲህ እስከሁን ባየነው መንገድ በመሐመድ ጊዜ በሰዎች ቅንብር የተጻፈው ቁርአን በከሊፋዎቹ በነ አቡ በከር አማካኝነት መጨረሻ ላይ መሐመድ ከሞቱ ከብዙ ዘመን በኋላ ነው በአንድ ጥራዝ ተደርጎ የተዘጋጀው፡፡ እነርሱም በወቅቱ ከየቦታው ከግለሰቦች እጅ ከተሰበሰበው የቁርአን አንቀጽ ውስጥ ያልመሰላቸውን አቃጥለው፣ የተሸለ ነው ያሉትን ደግሞ በአንድ ላይ ጠርዘው የዛሬውን ቁርአን

አውርሰውናል፡፡ ቁርአን በአጠቃላይ የሰዎች የፈጠራ ውጤት መሆኑ ውስጡ ባለው ይዘት በደንብ ማረጋገጥ ይቻላል፡፡

11.ቁርአን ከዐረብኛ ውጭ የሆኑና ከሌሎች ቋንቋዎች የወረሳቸው ባዕድ ቃላትን ስለሚጠቀም ታማኝ ሊሆን አይችልም፡- ቁርአን የብዙ ሰዎች አሻራ ያረፈበት ቅንብር ስለሆነ የሌሎች ሃይማኖታዊ ጽሑፎችንም በምንጭነት ስለተጠቀመ ሌላው ቢቀር ከዐረብኛ ውጭ የሆኑ ባዕድ ቃላትን ሲጠቀም እናየዋለን፡፡ ቁርአኑ ከሌሎች ቋንቋዎች ከግብፅ፣ ከአረማይክ፣ ከግእዝ፣ ከሳባውያን... የተውጣጡ ብዙ ባዕድ ቃላትን በውስጡ አጭቆ ይዟል፡፡ ለምሳሌ፡-

1ኛ.ቁርአኑ በዐረብኛ «ጀነት» ማለት ሲችል «ኤደን» የሚለውን የዕራይስጥ ቃል ይጠቀማል፡፡

2ኛ.ቁርአኑ በዐረብኛ «ባስራ» ማለት ሲችል «ኢንጂል» የሚለውን የግሪክ ቃል ይጠቀማል፡፡

3ኛ.ቁርአኑ በዐረብኛ «የሹዋ» ማለት ሲችል «ኢሳ» የሚለውን የሶሪያ ቃል ይጠቀማል፡፡ በቁርአኑ 26፡195 ላይ «ግልጽ በሆነ ዐረብኛ ቋንቋ የተወረደ ነው» ተብሎ ነው የተጻፈው፡፡ ሌሎችም ቁርአን ዐረብኛ ቋንቋ ብቻ የተጻፈ እንደሆነ የሚናገሩ ብዙ ጥቅሶች አሉ፡፡ ታዲያ ለምንድን ነው የተለያዩ ሀገራትን ባዕድ ቃላት የተጠቀመው? የራሱን ዐረብኛ ቋንቋ ብቻ መጠቀም ሲችል መቀላወጥ ለምን አስፈለገው? እንዲህ ከላይ ባየነው ዓይነት መንገድ ቁርአኑ ከሌሎች ቋንቋዎች እየኮረጀ የተጠቀመባቸው ብዙ ቃላት አሉ፡፡ ለምሳሌ፡-

1ኛ. ቁርአን (4፡43) ላይ «ታያሙም» የሚለው ቃል ከአይሁድ ታልሙድ ጽሑፍ ላይ የተወሰደ ነው፡፡

2ኛ. ቁርአን (2:260, 3:49, 5:110) ላይ ወፎች ላይ ነፍስ ስለመዝራት የተነገረው ቃል ከግብፆች መጽሐፍ የተወሰደ ነው፡፡

3ኛ. ቁርአን (2:102) ላይ «ሐሩትና ማሩት» የሚሉት ቃላት ከአርመኖች መጽሐፍ ላይ የተወሰደ ነው፡፡

4ኛ. ቁርአን (19:23) ላይ «መሪየም በዘንባባ ዛፍ ስር ወለደች፣ ምጡም ፀንቶባት ምነው በሞትኩ አለች» የሚለው አነጋገር በወቅቱ ከነበሩ ከመናፍቃን የወንጌል መጽሐፍ ላይ የተወሰደ ነው፡፡

5ኛ. በቁርአን ውስጥ እጅግ በጣም ብዙ ቦታ ላይ ከሞት በኋላ ዝሙትን ጨምሮ በጀነት ስላለው የተንደላቀቀ ሕይወት የሚናገሩት ጥቅሶች ዞራስትሪያን ከሚባሉ መናፍቃን መጽሐፍ ላይ የተወሰዱ ናቸው፡፡ (7፡43፣ 9፡72፣ 18፡31፣ 19፡62፣ 32፡17፣ 35፡53፣ 57፡21፣ 76፡12...)

6ኛ. ቁርአን (43:4, 85:21-22) ላይ አሪጂናሉ የቁርአን ቅጂ በሰማይ ነው ያለው ተብሎ

የተነገረው ቃል ከታልሙድ የሥርዓት መጽሐፍ የተወሰደ ነው፡፡ እነርሱም እንደዚያ ብለው ያምኑ ነበርና፡፡

7ኛ. ቁርአን (6:61, 7:37, 32:11) ላይ ስለ መላእክተ ሞት የተነገረው ቃል ከዞራስትሪያን መጽሐፍ ላይ የተወሰደ ነው፡፡

8ኛ. ቁርአን (12፡1-64) ላይ ስለ ዮሴፍ የተነገረው ታሪክ «ሚድራሽ» ከሚባለው ከአይሁድ መጽሐፍ ላይ የተወሰደ ነው፡፡

9ኛ. ቁርአን (21:78-82, 27:17-19, 27:22-23) ላይ ስለ ንጉሥ ሰሎሞንና ንግሥት ሳባ የተነገረው ታሪክ «ሀጋዳ» ከሚባለው ከአይሁድ መጽሐፍ ላይ የተወሰደ ነው፡፡

10ኛ. ቁርአን (11፡7) ላይ የአላህ ዙፋን በውኃ ላይ እንደሆነ የተነገረው ነገር ከአይሁድ የታልሙድ መጽሐፍ ላይ የተወሰደ ነው፡፡

11ኛ. ቁርአን (2:29, 41:12) ላይ ስለ ሰባቱ ሰማያት የተጻፈው ነገር ከሂንዱ የእምነት መጽሐፍ ላይ የተወሰደ ነው፡፡

12ኛ. ቁርአን (3:55, 4:157-158) ላይ «ክርስቶስ አልሞተም አልተሰቀለም» የሚለውን ሀሳብ የወሰደው «የበርናባስ ወንጌል» በሚል ርዕስ አንድ ጣሊያናዊ የካቶሊክ መናፍቅ ቄስ ከጻፈው ሐሰተኛ መጽሐፍ ላይ ነው፡፡

«የበርናባስን ወንጌል» በተመለከተ ነገሩ ወዲህ ነው፡- በ1500 ዓ.ም አካባቢ ሙሉ አውሮፓን ለማስለም ሰፊ እንቅስቃሴ ተደርጎ ነበር፡፡ ከሮሙ ጳጳስ ጋር ተጣልቶ የነበረው አንድ የካቶሊክ ቄስ ጳጳሱን ለማብሸቅ ብሎ ወደ እስልምና ሃይማኖት ይገባና የወንጌላትን መልእክት ወደ ቁርአን ለማዞር ከፍተኛ ሙከራ አድርጎ ነበር፡፡ በዚህ ጊዜ ነበር ይህ ጣሊያናዊ የካቶሊክ መናፍቅ ቄስ በጣሊያንኛ ቋንቋ «የበርናባስ ወንጌል» የሚል መጽሐፍ ጽፎ ያዘጋጀው፡፡ የአራቱንም ወንጌላውያንን መጽሐፍ በአንድ ላይ በማዘጋጀት ኢስላማዊ ይዘት እንዲኖረው አድርጎታል፡፡ ለማስመሰል ሲል ከ12ቱ ሐዋርያት ውስጥ የቶማስን ስም በመሰረዝ በበርናባስ ተክቶታል፡፡ ነገር ግን በወንጌል ላይ የተጠቀሰው እውነተኛው በርናባስ የቅዱስ ጳውሎስ አገልጋይ የነበረ ሰው ነው፡፡ ሐዋ 14፡11-15፤ 13፡2፤ 16፡36፡፡

ይህ የካቶሊክ መናፍቅ ቄስ በወንጌል ስም ጽፎ ባዘጋጀው ሐሰተኛ መጽሐፍ ውስጥ የወንጌላቶቹን መልእክት የተለየ ይዘት እንዲኖራቸው በማሰብ ክርስቶስ እንዳልተሰቀለ ይልቁንም ሌላ ሰው በእርሱ እንደተመሰለ አድርጎ ነው የጻፈው፡፡ መሐመድም ይህንን ሀሳብ ነው በቀጥታ ወስደው በቁርአናቸው ውስጥ የተጠቀሙበት፡፡ አሁን አሁን አንዳንድ ሙስሊም መምህራኖችም መሐመድን ከክርስትናው ጋር ለማቀራረብ ሲፈልጉ ይህንን መጽሐፍ መጥቀስ ጀምረዋል፡፡ መጽሐፉንም በቅርቡ ፓኪስታን ውስጥ በብዛት

አሳትመውት እየተጠቀሙበት ይገኛሉ፡፡ ወንጌል ግን እንዲህ ትላለች፡-

«የሚያናውጡአችሁ የክርስቶስንም ወንጌል ሊያጣምሙ የሚወዱ አንዳንዶች አሉ። ነገር ግን እኛ ብንሆን ወይም ከሰማይ መልአክ፥ ከሰበክንላችሁ ወንጌል የሚለይ ወንጌልን ቢሰብክላችሁ፥ የተረገመ ይሁን። አስቀድመን እንዳልን እንዲሁ አሁን ሁለተኛ እላለሁ፥ ከተቀበላችሁት የተለየውን ማንም ቢሰብክላችሁ የተረገመ ይሁን» ገላቲያ 1፥6፡፡

12ኛ.የመሐመድ ትምህርቱና የሕይወት ተሞክሮው በጣም ብዙ አስከፊ ገጽታዎች ያሉት በመሆኑ ቁርአን ሊታመን አይችልም፡- ቁርአንን እንዳይታመን ካደረጉት ነገሮች ውስጥ አንደኛው የመሐመድ ሕይወታቸው ብዙ አስከፊ ገጽታዎች ያሉት መሆኑ ብሎም ኃጢአተኛ ሆነው መገኘታቸው ነው፡፡ መሐመድ «ሱናዬን ያልፈጸመ ማለትም እኔ ያደረኩትን ነገር ያላደረገ ከእኔ ጋር ግንኙነት የለውም» በማለት ተናግረዋል፡፡ "And he who turns away from my Sunnah, he has no relation with me" Sahih Muslim 8፡3236. መሐመድ የተናገሯት ንግግር ወይም ያደረጓት አንዷ ድርጊት ናት ሱና (Sunnah) የምትባለው፡፡ ቁርአኑና ሐዲሱ መሐመድን የሰው ዘር በሙሉ ምሳሌ ሊያደርጋቸው እንደሚገባና ሁሉም ከእርሳቸው የሕይወት ተሞክሮ መማርና እርሳቸውንም መከተል እንዳለበት በስፋት ይናገራሉ፡፡ የመሐመድ ትእዛዛት ማለት የአላህ ትእዛዛት እንደሆኑም ነው የተነገረው፡፡ "I heard Allah's Apostle saying, 'He who obeys me, obeys Allah, and he who disobeys me, disobeys Allah.'" Bukhari 4፡52፡203. በቁርአኑም 4፡80 ላይ «መልክተኛውን የሚታዘዝ ሰው በእርግጥ አላህን ታዘዘ» ተብሎ ነው የተጻፈው፡፡ «ለናንተ አላህንና የመጨረሻውን ቀን የሚከጅል በአላህ መልካም መከተል አላችሁ (33፡21) /3፡132፣ 4፡59፣5፡92፣ 8፡24፣ 8፡46፣ 47፡33፣ 64፡12/ ተብለው የተጻፉትን ነገሮች ስናይ የመሐመድ ትእዛዛት የአላህ ትእዛዛት እንደሆኑ ተደርጎ ነው የተነገረው፡፡

እንዲያው የእውነት እንነጋገር እስቲ! ከመሐመድ ሕይወት ምንድን ነው የምንማረው? በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ስለ መሐመድ ግላዊ ሕይወት በዝርዝር ያየናቸውን ነጥቦች በድጋሚ እንድናስታውሳቸው እፈልጋለሁ፡፡ እነዚያ ነጥቦች ከመሐመድ ሕይወት ምን ልንማር እንደምንችል በትክክል ጠቋሚዎች ናቸው፡፡ እስካሁን ድረስ ቁርአኑንና ሐዲሱን መሠረት አድርገን ከመሐመድ የግል ሕይወታቸውና ካስተማሩት ትምህርታቸው ጋር የተገናኙ ብዙ ነጥቦችን እንዳየነው ከሆነ ከመሐመድ ሕይወት ምንድን ነው የምንማረው? በዝርፊያ ምድራዊ ሀብት ማከማቸትን?፣ የሰዎችን አካል እየቆራረጡ ማሰቃየትን?፣ ለሴቶች ክብር አለመስጠትን?፣ ጥላቻ መስበከን?፣ ጦርነትና ጂሃድ ማወጅን?፣ አሸባሪነትን?፣ ግድያን?፣ ጅምላ ጭፍጨፋን?፣ ባርነትን?፣ ዘረኝነትን?

፣የዝሙት ሱሰኛነትን?፣ ራስን ማስመለክን?፣ ውሸትን?፣ ግብዝነትን?፣ ጣዖት ማምለክን?፣ አታላይነትን?፣ ሙሰኝነትን?… ወይስ ምንድን ነው ከመሐመድ ሕይወት የምንማረው?

13ኛ.ከቁርአን ውስጥ የተሰረዙና እንዲጠፉ የተደረጉ ጥቅሶች መኖራቸው ቁርአኑን እንዳይታመን አድርጎታል፡- ሁለቱንም ርዕሶች ማለትም ከቁርአን ውስጥ የተሰረዙና እንዲጠፉ የተደረጉ ጥቅሶች ስለመኖራቸው ለየብቻ በዝርዝር እናያቸዋለን፡-

የተሰረዙ የቁርአን ጥቅሶች /Cancelled Verses/ ፡- በሐዲሱ ላይ አንድ የተጻፈ ታሪክ አለ፡፡ ከመሐመድ ጋር ቅራኔ ውስጥ የገቡ ራል፣ ዳክዋን፣ ባኒ ሊህያን እና ባም ኡሳይያ የተባሉ ጎሳዎች ወደ መሐመድ ይመጡና እስልምናን መቀበላቸውን ይናገራሉ፡፡ በኋላም መሐመድን «ጦርነት አለብን ተዋጊ ሰዎች ስጠን» ብለው ይጠይቋቸዋል፡፡ እርሳቸውም 70 ተዋጊዎችን ሰጧቸውና ይዘው ተመለሱ፡፡ ነገር ግን ቢር-ማዓና በተባለው ቦታ ሲደርሱ 70ውንም የመሐመድ ሰዎች በበቀል ገደሏቸው፡፡ መሐመድም ወታደሮቻቸውን አታለው ወስደው የገደሉባቸውን ሰዎች አላህ እንዲያጠፋላቸው ለ40 ቀን ለመኑ፡፡ ይህ ታሪክ በሳሂህ ቡኻሪ 4፡52፡299 ላይ ተመዝግቦ ይገኛል፡፡

እነዚያ የተገደሉት 70 የመሐመድ ወታደሮችም «ጌታችንን እንዳገኘንና እርሱም ከእኛ ጋር እንደተደሰተ እኛንም እንዳስደሰተን ለሕዝቦቻችን ነገርልን» ብለው ለመሐመድ መናገራቸውን የሚገልጽ ቁርአን ወርዶ እንደነበር ሐዲሱ ይናገራል፡፡ ነገር ግን ይህ እነርሱ የተናገሩት ነገር ከቁርአን ውስጥ ተሰርዞ ጠፍቷል በማለት አሁንም ሐዲሱ ይናገራል፡፡ "ቢር-ሙዓና በተባለው ቦታ ስለተገደሉት ሰዎች የወረደ የቁርአን ይቅስ ነበር፡፡ እኛ በቃላችን እንገጥመው የነበረው ጥቅስ በኋላ ሊሰረዝ ችሏል፡፡ ጥቅሱም 'ጌታችንን እንዳገኘንና እርሱም ከእኛ ጋር እንደተደሰተ እኛንም እንዳስደሰተን ለሕዝቦቻችን ነገርልን' የሚል ነበር፡፡" "There was reveled about those who were killed at Bir-Mauna a Quranic Verse we used to recite, but it was cancelled later on. The Verse was: 'Inform our people that we have met our Lord. He is pleased with us and He has made us pleased'" Sahih Bukhari 4:52:69 "Gabriel informed the Prophet that they (i.e the martyrs) met their Lord, and He was pleased with them and made them pleased. We used to recite, 'Inform our people that we have met our Lord, He is pleased with us and He has made us pleased' Later on this Quranic Verse was cancelled. The Prophet invoked Allah for forty days to curse the murderers from the tribe of Ral, Dhakwan, Bani Lihyan and Bam Usaiya who disobeyed Allah and his Apostle." Sahih Bukhari 4:52:57

ድርጊቱ ምንም ይሁን ምን ከላይ ያየናቸው ሁለት የሐዲስ ጥቅሶች አንድ የሚያረጋግጡልን ነገር ቢኖር የተሰረዘ የቁርአን ጥቅስ መኖሩን ነው፡፡ ሙስሊሞቹ

እንደሚሉት አይደለም እንጂ ቁርአኑ የአምላክ ቃል እንኳን ቢሆን የአምላክ ቃል እንዴት ሊሰረዝ ቻለ? መሰረዝስ ነበረበት ወይ? ታዲያ በዚህ ዓይነት ሌሎች የተሰረዙ የቁርአን ጥቅሶችስ ላለመኖራቸው ምን ማረጋገጫ አለ? ቁርአን ከብዙ ነገሮቹ አንጻር ሲታይ ታማኝነት የሌለው መጽሐፍ ነው ያስባለውም አንዱ ይህ ነው፡፡ ከመጀመሪያው ከአሰባሰቡ ጀምሮ በዘመናት አልፎበት የመጣበት ሂደት ውስጡ ካለው ይዘት ጋር ሲታይ ፍጹም ታማኝነቱን ያጎለዋል፡፡ እንዲህ የተሰረዙ ጥቅሶች መኖራቸውን የማያውቁ አማኞቹ ግን «ቁርአናችን የሰው እጅ ያላረፈበት ንጹሕ መጽሐፍ ነው» ይሉታል፡፡

<u>የጠፉ የቁርአን ጥቅሶች /Lost Verses/</u>፡- አሁን ባለው ቁርአን ውስጥ እንዳይካተት የተደረገ ቢሆንም ነገር ግን ቁርአን በድንጋይ ወግሮ ስለ መግደል የሚናገር የቅጣት ሕግ ነበረው፡፡ ሁለተኛው ከሊፋ ኡማር እንደተናገረው አላህ ለመሐመድ ካወረደላቸው ሕግ ውስጥ ዝሙት የፈጸሙ ሰዎችን በድንጋይ ወግሮ ስለመግደል ይገኝበታል፡፡ እነርሱም ይህንን በአእምሮአቸው ይዘውትና ተረድተውት እንደቆዩም ተናግሯል፡፡ «በድንጋይ ወግሮ መግደል በአላህ መጽሐፍ የወረደ ግዴታ ነው» በማለትም አስተምሯል፡፡ ይህም ወንዱ ወይም ሴቷ ከጋብቻ ውጭ ስታመነዝር ከተያዘችና ከተመሰከረባት ወይም ካረገዘች ተወግራ እንድትገደል መሐመድ አዘዋል፡፡ ነገር ግን ይህ የመሐመድ ትእዛዝ በአሁኑ ቁርአን ውስጥ የለም፡፡ ቀድሞ በቁርአኑ ላይ ተጽፎ የነበረ ሕግ ቢሆንም አሁን ባሉት የቁርአን እትሞች ላይ እንዳይካተት ተደርጓል፡፡

<u>Verse of Rajam (Stoning)</u>፡ "Umar b. Khattab sat on the pulpit of Allah's Messenger and said: Verily Allah sent Muhammad with truth and He sent down the Book upon him, and the verse of stoning was included in what was sent down to him. We recited it, retained it in our memory and understood it. Allah's Messenger awarded the punishment of stoning to death and, after him, we also awarded the punishment of stoning, I am afraid that with the lapse of time, the people may forget it and may say: We do not find the punishment of stoning in the Book of Allah, and thus go astray by abandoning this duty prescribed by Allah. Stoning is a duty laid down in Allah's Book for married men and women who commit adultery when proof is established, or it there is pregnancy, or a confession." Sahih Muslim 17:4194

ይህን «በድንጋይ ወግሮ ስለ መግደል» የሚናገረውን የመሐመድን ሕግ በቀጣዩ ርዕስ በደንብ በዝርዝር ስናየው የበለጠ ግልጽ ይሆንልናል፡፡

## በድንጋይ ወግሮ መግደልና የክብር ግድያ /honor killing & Stoning/

ለመሆኑ ይህ በድንጋይ ወግሮ የመግደል ሕግ አሁን ባለው ቁርአን ውስጥ ለምን አልተካተተም? መኖር አለመኖሩ አሳስቦኝ አይደለም የጠየኩት፡፡ ይልቁንም ቁርአኑ በፊት የነበረውን ነገር አሁን ለምን እንዳይኖረው ተደረገ? ነው ጥያቄዬ፡፡ ሕጉ ምንም ይሁን ምን ሊጠፋ ወይም ተቆርጦ ሊወጣ አይገባውም ነበር፡፡ ይህ ከሆነ ሌሎችስ የቁርአን ሕጎች ጠፍተው ወይ ደግሞ ስንቶች አዳዲስ ሕጎች ተጨምረው እንሆነ የሚታወቅ ነገር የለም፡፡ ለነገሩ ይህ በድንጋይ ወግሮ የመግደል ሕግ የጠፋበትን ምክንያት አይሻ ስትናገር «ፍየል በልታው ነው የጠፋው» ነው ያለችው፡፡

ፍየል በልታው የጠፋው የቁርአን ክፍል፡- እንደ መሐመድ ትምህርት ሙስሊሟ ሴት (ባለትዳርም ትሁን ጎረዳ) ከወጣት ወንድ ጋር በአንድ ክፍል ውስጥ አብረው ቢሆኑ ወንዱ በዝሙት እንዳያስባት ለማድረግ ሴቷ ጡቷን ለወንዱ ታጠባዋለች፡፡ ይህንንም ገጽ----ላይ «ጎልማሳ ወንዶችን ጡት ማጥባት/Adult Suckling» በሚለው ርዕስ ስር በደንብ አይተነዋል፡፡ በዚህ ‹የጡት ማጥባት› ሕግ መሠረት ሴቷ ወንዱን ጡቷን ካጠባችው በኋላ ለእርሱ ሀራም (ክልክል) ስለምትሆንበት ከእርሷ ጋር ግብረ ሥጋ ግንኙነት ማድረግ በፍጹም አይችልም፡፡ ይህም ግልጽ የሆነ የነቢያቸው የመሐመድ ሕግ ነው፡፡ ይህንን ሕግና በድንጋይ ወግሮ ስለመግደል የሚናገረውን ሕግ ፍየል ስለበላችው ዛሬ ባለው ቁርአን ውስጥ ሳይካተት እንደቀረ የተናገረችው የመሐመድ ሚስት አይሻ ናት፡፡ እንዲህ ነው ያለቸው፡- “በድንጋይ ወግሮ ስለመግደልና ወጣት ጎረምሳን 10 ጊዜ ስለማጥባት የሚናገሩ ጥቅሶች ለነቢዩ ተገልጸውለት ነበር፣ በወረቀት ላይ ተጽፈውም በአልጋዬ ስር ተቀምጠው ነበር፡፡ ከነቢዩ ሞት በኋላ በእርሱ ሞት ምክንያት በሀሳብ ተውጠን ስለነበር እኛ ሳናይ ፍየሏ በሩን አልፋ ገብታ ወረቀቱን በልታዋለች” Narrated Aisha: "The verse of the stoning and of suckling an adult ten times were revealed, and they were (written) on a paper and kept under my bed. When the messenger of Allah expired and we were preoccupied with his death, a goat entered and ate away the paper." (Musnad Ahmad bin Hanbal. vol. 6, p. 269; Sunan Ibn Majah, p. 626; & Ibn Qutbah, Tawil Mukhtalafi 'l-Hadith (Cairo: Maktaba al-Kulliyat al-Azhariyya. 1966) p. 310 see also: As-Suyuti, ad-Durru 'l-Manthur, vol. 2, p. 13)

ይህ ሕግና በድንጋይ ወግሮ ስለመግደል የሚናገረው ሕግ ፍየል ስለበላችው ዛሬ ባለው ቁርአን ውስጥ ሳይካተት ከቀረ ሌሎችም የቁርአን ክፍሎች በዚህ ዓይነት መንገድ የጠፉ ይኖራሉ ማለት ነው፡፡ የድንጋይ ወገራዋ ሕግ ግን ሆን ተብላ እንድትጠፋ ነው የተደረገችው፡፡ ምክንያቱም በወቅቱ መሐመድ ትልቅ ትኩረት ሰጥተውት ሕግ

እንደሠፍለት ሐዲሱ በተደጋጋሚ ይናገራል፡፡ በሐዲሱ ላይ በግልጽ እንደተመዘገበው መሐመድ በሕይወት እያሉ ዝሙት የፈጸሙ ብዙ ሰዎች በድንጋይ ተወግረው እንዲገደሉ ትእዛዝ ሰጥተው ነበር፡፡ በትእዛዛቸውም መሠረት ሰዎቹ በድንጋይ ተወግረው ተገድለዋል፡፡

“A bedouin came and said, "O Allah's Apostle! Judge between us according to Allah's Laws." His opponent got up and said, "He is right. Judge between us according to Allah's Laws." The bedouin said, "My son was a laborer working for this man, and he committed illegal sexual intercourse with his wife. The people told me that my son should be stoned to death; so, in lieu of that, I paid a ransom of one hundred sheep and a slave girl to save my son. Then I asked the learned scholars who said, "Your son has to be lashed one-hundred lashes and has to be exiled for one year." The Prophet said, "No doubt I will judge between you according to Allah's Laws. The slave-girl and the sheep are to go back to you, and your son will get a hundred lashes and one year exile." He then addressed somebody, "O Unais! go to the wife of this (man) and stone her to death" So, Unais went and stoned her to death.” Sahih Bukhari 3:49:860.

“The Jews came to Allah's Apostle and told him that a man and a woman from amongst them had committed illegal sexual intercourse. Allah's Apostle said to them, "What do you find in the Torah (old Testament) about the legal punishment of Ar-Rajm (stoning)?" They replied, (But) we announce their crime and lash them." Abdullah bin Salam said, "You are telling a lie; Torah contains the order of Rajm." They brought and opened the Torah and one of them solaced his hand on the Verse of Rajm and read the verses preceding and following it. Abdullah bin Salam said to him, "Lift your hand." When he lifted his hand, the Verse of Rajm was written there. They said, "Muhammad has told the truth; the Torah has the Verse of Rajm. The Prophet then gave the order that both of them should be stoned to death. ('Abdullah bin 'Umar said, "I saw the man leaning over the woman to shelter her from the stones." Sahih Bukhari 4:56:829.

በዚህ መልኩ በሐዲሱ ውስጥ እንደተመዘገበው መሐመድ ዝሙት የፈጸሙ ሰዎችን ያለምንም ርህራሄ በድንጋይ ተወግረው እንዲገደሉ አድርገዋል፡፡ ቦታ ከመቆጠብ አንጻር ተውኳቸው እንጂ በእንደዚህ ዓይነት መንገድ የተፈጸሙ የድንጋይ ወገራ ግድያዎች በጣም ብዙ ናቸው፡፡ የተለያዩ አሳዛኝ ታሪኮች የሚገኙባቸውን ጥቅሶች ግን በአጭሩ ላስቀምጥ፡- ቡኻሪ ሐዲስ (2:23:413, 3:34:421, 3:50:885, 3:49:860, 6:60:79, 8:78:629, 8:82:803, 8:82:805, 8:82:809, 8:82:813, 8:82:842, 9:89:303, 9:93:633, 4:56:829,

7:63:195, 7:63:196, 7:63:230, 8:82:806, 8:82:810, 8:82:816, 9:92:432)
ሳሂህ ሙስሊም ሐዲስ (17:4191, 17:4194, 17:4196, 17:4198, 17:4199, 17:4202, 17:4206, 17:4207, 17:4209, 17:4211, 17:4216, 20:4483, 17.4201:1,17:4205,17:4212)
አቡ ዳውድ ሐዲስ (38:4421 , 38:4424 , 38:4426 , 38:4429 , 38:4433)
አል-ሙዋታ ሐዲስ (28 28.1126, 36 36.2120, 41 41.11, 41 41.14, 41 41.15, 41 41.16, 41 41.18, 41 41.110, 41 41.620)

መሐመድን አርአያ በማድረግ ተከታዮቻቸውም ዛሬ ምንም እንኳን ሕጉ ከቁርአኑ ውስጥ ተቆርጦ እንዲወጣ ቢደረግም እነርሱ ግን ይህንን በድንጋይ ወግሮ የመግደልን ሕግ ተግባራዊ ያደርጉታል፡፡ "The Prophet had a woman stoned and a pit was dug up to her breasts." Abu Dawud 38:4429, "when the latter stoned a lady to death on a Friday, 'Ali said, 'I have stoned her according to the tradition of Allah's Apostle.'" Sahih Bukhari 8:82:803.

እንዲያውም በዘመናችን ያሉት ሙስሊሞች መምህራኖቻቸው እንደሚሉት «መሐመድ ወስኖ ያስቀመጠውን በድንጋይ ወግሮ የመግደልን ሕግ በጥይት ወይም በሰይፍ እንኳን መለወጥ ፈጽሞ አይቻልም» ይላሉ፡፡ Islam Q&A, Fatwa No. 14312.



ይህ ኢራን ውስጥ በቅርቡ የተፈጸመ ድርጊት ሲሆን ሰዎቹ የሚቿን ሴት ጭንቅላት በድንጋይ ለመውገር እንዲያመቻቸው እስከደረቷ ድረስ ብቻ መሬት ውስጥ ሲቀብሯት ነው ፎቶው የሚያሳየው፡፡ Woman Stoning is a fine Islamic Tradition. It all started from Mohammed's era until the present time. Woman Stoning is a public event often held with

much excitement for the whole family to participate and watch. It is kind of like a Sports Game held in stadiums of the West! Woman Stoning is happening right now all around the Islamic world, but when it comes to the International public opinion and media, it is all hush hush! Look at this poor woman pleading for her life while the Iranian Female Police with machine gun on her back (on the right) tries to comfort her by convincing her that now she will be free of her sins! Two revolutionary guards are anxiously burying her and getting her ready for the main event while the public is getting impatient holding the stones! The stones must not be too large to kill in one shot and not too small to be ineffective. They must be just the right size to inflict a lengthy, torturous painful death carried on for hours of fun and joy!

The following photo also shows a dead woman which is killed by stoning



ፎቶ አፍጋኒስታን ውስጥ ሴቷ ተወግራ ከተገደለች በኋላ በጉድጓድ ውስጥ እንደተጣለች ያሳያል




ሶማሊያ ውስጥ የሂዝቡል ኢስላሞች ሟችን በሕይወት እስከትከሻ ድረስ ከቀበሩ በኋላ ነው ግድያውን የፈጸሙት፡፡ የግድያውም መንስኤ ወሲብ መፈጸም ነው፡፡

ከዚሁ በድንጋይ ወግሮ ከመግደል ጋር በተያያዘ አንዳንድ ተያያዥ ነገሮችን ማንሳት ፈለኩ፡፡ ፍጹም የሆነችው የወንጌል ብርሃን ባልበራችበት ዘመን በዚያ በጨለማው ዘመን በኦሪቱ ጊዜ ሙሴ ሕዝቦቹ ከእርኩሰታቸው እንዲጠበቁ በማለት ይህን ሕግ ሠርቶላቸው ነበር፡፡ የገደለ ይገደል፣ ዓይን ያጠፋ ዓይኑ ይጥፋ፣ ጥርስ ያወለቀ ጥርሱ ይውለቅ… የምትለው ደካማዋ የኦሪት ሥርዓት ከአምላካቸው ተለይተው በአምልኮ ጣዖት፣ በዝሙት…በኃጢአት ባሕር እየዋኙ ለሚኖሩ የኦሪት ሕዝቦች የተሰጠ መቀጣጫ ነው-ድንጋይ ወገራ ማለት፡፡ ይህም የቆየው በክርስቶስ ፍጹም የሆነችው የወንጌል ሕግ እስከመጣችበት ጊዜ ድረስ ብቻ ነበር፡፡ ነገር ግን የሙሴ ዘመን ሰዎች በኃጢአታቸው ምክንያት በሙሴ የተሠራላቸው ያ የኃጢአት መቅጫ ሕግ ከክርስቶስ በኋላ ፈጽሞ የለም፡፡ እርሱ ክርስቶስ በጽድቅ ፈራጅ፣ ኃጢአትን ይቅር ባይ ነውና ጨለማውን አጥፍቶ የወንጌልን ብርሃን ካበራልን ይኸው ሁለት ሺህ ዘመናት አልፈዋል፡፡ ሕጉን ከሙሴ የኮረጁት የሙስሊሞቹ ነቢይ መሐመድ ግን በዘመናቸው ተግባራዊ

አድርገውታል፤ ለተከታዮቻቸውም እንዲተገብሩት በትእዛዝ አስተላልፈውላቸዋል፡፡ እነርሱም ይኸው እስከ አሁን ድረስ እየተገበሩት ነው፤ ወደፊትም ይተገብሩታል፡፡ ማስተዋል የማይችል ኅሊና ምንኛ ክፉ ነው በእውነት!

“There came to the Prophet a woman from Ghamid and said: Allah's Messenger, I have committed adultery, so purify me. The Prophet turned her away. On the following day she said: Allah's Messenger, Why do you turn me away? Perhaps, you turn me away as you turned away Ma'iz. ...she came to him with her child who was holding a piece of bread in his hand. She said: Allah's Apostle, here is he as I have weaned him and he eats food. The Prophet entrusted the child to one of the Muslims and then pronounced punishment. And she was put in a ditch up to her chest and he commanded people and they stoned her.” Sahih Muslim 17:4206.

«አንድ ሴት ወደ መሐመድ መጣች፣ ዝሙት ፈጽሜያለሁና አንፃኝ አለችው፡፡ ዞር እንድትልለት አደረጋት፡፡ በቀጣዩም ቀን ‹ለምን ዞር እንድል ታደርገኛለህ?› አለችው፡፡ በእጆቹ ትንሽ ዳቦ የጨበጠ ልጇን እንደያዘች መጣችና ‹የአላህ ሐዋሪያ ሆይ! ምግብ ያስጀመርኩትና አሁን መብላት የጀመረው ልጄ እርሱ ነው› አለችው፡፡ ነቢዩም ኃላፊነቱን ከሙስሊሞቹ ለአንዱ ሰጠውና ቅጣቱን አወጀ/ወሰነ፡፡ እርሷም እስከ ደረቷ ድረስ በጉድጓድ ውስጥ እንድትገባ ተደረገ፡፡ መሐመድም ሰዎቹን እንዲወግሯት አዘዛቸው፤ እነርሱም ወገሯት» ይላል ሐዲሱ የመሐመድን ውሳኔ ሲገልጽ፡፡ ይህም ውሳኔ የተላለፈባት ሴት ልጇን የወለደችው ካላገባችው ሰው ስለሆነ ነው፡፡ ሰውየውም እንዲሁ በተመሳሳይ ሁኔታ ተወግሮ ተገድሏል፡፡

+++ «ኢየሱስ ግን ወደ ደብረ ዘይት ሄደ። ማለዳም ደግሞ ወደ መቅደስ ደረሰ፤ ሕዝቡም ሁሉ ወደ እርሱ መጡ። ተቀምጦም ያስተምራቸው ነበር። ጻፎችና ፈሪሳውያንም በምንዝር የተያዘችን ሴት ወደ እርሱ አመጡ፤ በመካከልም እርሱዋን አቁመው መምህር ሆይ፥ ይህች ሴት ስታመነዝር ተገኝታ ተያዘች፤ ሙሴም እንደነዚህ ያሉት እንዲወገሩ በሕግ አዘዘን፤ አንተስ ስለ እርስዋ ምን ትላለህ? አሉት። የሚከሱበትንም እንዲያገኙ ሊፈትኑት ይህን አሉ። ኢየሱስ ግን ጐንበስ ብሎ በጣቱ በምድር ላይ ጻፈ፡፡ መላልሰው በጠየቁት ጊዜ ግን ቀና ብሎ፣ ከእናንተ ኃጢአት የሌለበት አስቀድሞ በድንጋይ ይውገራት አላቸው። ደግሞም ጐንበስ ብሎ በጣቱ በምድር ላይ ጻፈ። እነርሱም ይህን ሲሰሙ ሕሊናቸው ወቀሳቸውና ከሽማግሌዎች ጀምረው እስከ ኋለኞች አንድ አንድ እያሉ ወጡ፤ ኢየሱስም ብቻውን ቀረ፤ ሴቲቱም በመካከል ቆማ ነበረች። ኢየሱስም ቀና ብሎ ከሴቲቱ በቀር ማንንም ባላየ ጊዜ አንቺ ሴት፥ እነዚያ ከሳሾችሽ ወዴት አሉ? የፈረደብሽ የለምን? አላት። እርስዋም ጌታ ሆይ፥

አንድ ስንኳ አለች። ኢየሱስም እኔም አልፈርድብሽም፤ ሂጂ ከአሁንም ጀምሮ ደግመሽ ኃጢአት አትሥሪ አላት። ደግሞም ኢየሱስ እኔ የዓለም ብርሃን ነኝ፤ የሚከተለኝ የሕይወት ብርሃን ይሆንለታል እንጂ በጨለማ አይመላለስም ብሎ ተናገራቸው። ፈሪሳውያንም አንተ ስለ ራስህ ትመሰክራለህ፤ ምስክርነትህ እውነት አይደለም አሉት። ኢየሱስ መለሰ አላቸውም እኔ ስለ ራሴ ምንም እንኳ ብመሰክር ከወዴት እንደመጣሁ ወዴትም እንድሄድ አውቃለሁና ምስክርነቴ እውነት ነው፤ እናንተ ግን ከወዴት እንደ መጣሁ ወዴትም እንድሄድ አታውቁም። እናንተ ሥጋዊ ፍርድን ትፈርዳላችሁ፤ እኔ በአንድ ሰው ስንኳ አልፈርድም» ዮሐንስ ወንጌል 8፡1-14፡፡ +++

መድኃኔዓለም ክርስቶስ «እኔ በአንድ ሰው ስንኳ አልፈርድም» ማለቱ አንድም ሥጋን ተዋሕጄ ወደዚህች ምድር የመጣሁት ለአዳም ካሳ ልከፍል፣ የበደለኞችን በደል ልሽር፣ ኃጢአተኞችን ከኃጢአታቸው ላነፃ ነው እንጂ በሕይወት ልፈርድባቸው አልመጣሁም ማለቱ ነው፡፡ ሁለትም በዳግም ምፅዓት የሚፈርድባችሁ እኔ ያስተማርኩት ትምህርትና የሰማችሁት የወንጌል ቃል ነው ሲለን ነው፡፡

ከዚሁ በድንጋይ ወግሮ ከመግደል ጋር በተያያዘ አንድ ሌላ ሳልጠቅሰው ማለፍ የሌለብኝን ነገር ልንሳ፡፡ በእስልምናው ውስጥ «የክብር ግድያ» (honor killing) የሚባል የግድያ ዓይነት አለ፡፡ በፊትም ሆነ አሁን በሸሪዓው ሕግ መሠረት በዓለም ላይ ባሉ ኢስላም ሀገራት በብዛት እየተፈጸመ ስለሆነ በደንብ እንየው፡፡ በአብዛኛው ዘጠና አምስት በመቶ በሴቷ ላይ ስለሚፈጸም በሴት ጾታ ብገልጸው ይቀላል፡፡ አንዲት ሴት ሳታገባ አርግዛ ብትገኝ፣ እናትና አባቷ ሳይድሯት እጮኛ ብትይዝ፣ ሙስሊም ሆና ሳለች ከክርስቲያን ጋር በፍቅር ብትወዳጅ... ወይም ከትዳሯ ውጭ ብታመነዝር «የቤተሰቧን ክብር አጉድፋለች» በሚል ክስ አንድ ቅጣት እንትቀጣ እስልምናው ደንግጓል፡፡ ይህም የራሷ ቤተሰብ እንዲገድላት ይደረጋል፡፡ ከላይ በዘረዘርኳቸው ድርጊቶች ምክንያት «የቤተሰቤን ክብር አጉድፋለች» ብሎ ካመነ አባት ልጁን መግደል ይችላል፡፡ ጅል እናቱን መግደል ይችላል፡፡ ወንድም እኅቱን፣ ባልም ሚስቱን መግደል ይችላል፡፡ የክብር ግድያ!!!

ግድያው የሚፈጸመው በስቅላት፣ በድንጋይ በመውገር፣ በሽጉጥ፣ በመርዝ ወይም በኤልትሪክ... በምንም ሊፈጸም ይችላል፡፡ እስቲ አንድ እውነተኛ ታሪክ በምሳሌ እንይ፡- የሶራያ ማኑቼሪ እጅግ አሳዛኝ የግድያ ታሪክ ኢስላም ሀገራት በሴቶች ላይ እያደረሱ ያለውን የስቅላትና የድንጋይ ወገራ ግፍ ቁልጭ አድርጎ ለመላው ዓለም አሳይቷል፡፡ ሶራያ በ13 ዓመቷ አግብታ 9 ልጆችን የወለደችለትና ለ35 ዓመታት በትዳር አብራው የኖረችው ባሏ «ለትዳሬ አልተመቸችኝም» በማለት ባላደረገችው ነገር ብዙ ሴራዎችን

ይጠነስስባት ጀመር፡፡ ሁለቱ የመጀመሪያ ልጆቿን በእርሷ ላይ እንዲነሳሱባት አደረገ፡፡ በቤት ውስጥ ይደበድባት ጀመር፡፡ በመጨረሻም «በትዳሬ ላይ ማግጣለች» በማለት የሐሰት ክስ አቅርቦ በድንጋይ ተወግራ እንድትገደል አደረጋት፡፡ ባሏ ይህንን ያደረገው ሊያገባት የፈለገው የ14 ዓመት ኮረዳ ስላገኘ ነበር፡፡ በአያቶላህ ካኦሚኒ የኢራን ሕግ መሠረት ወንዶች ብዙ ሚስቶችን ማግባት እንደሚችሉ ቢፈቅድም የሶራያ ባል ግን እርሷን ማስወገድ ነበር የፈለገው፡፡ ፍሬይዱን ሳሂብጃም የተባለው የፈረንሳይ ጋዜጠኛ የትውልድ መንደሩ ወደሆነችውና ኢራን ውስጥ ወደምትገኘው አንዲት ትንሽ ተራራማ መንደር ሲመጣ በሶራያ ላይ የተፈጸመውን ይህንን አሳዛኝ ታሪክ በዝርዝር ይሰማል፡፡ የሶራያ አክስት ዛህራ ካኑም «ዓለም ይወቅልን» በማለት ሙሉውን የሶራያ ታሪክ በዝርዝር አስረዳችው፡፡ ፈረንሳዩ ጋዜጠኛ በዚያ ያሉ ሌሎች ሴቶችን በማነጋገርና ከዓይን እማኞችም መረጃዎችን ሰብስቦ ወደ ፈንሳይ ሲመለስ ዜናውን ለዓለም አዳረሰ፡፡ ሶራያም ዛሬ "*The Stoning of Soraya M.*" በሚል ርዕስ ፊልም ተሰርቶላትና መጽሐፍ ተጽፎላት የሚሊዮኖችን ዓይን በእንባ አርጥባለች፡፡ ዓለም ስለ እርሷና መሰሎቿ አዘነ፡፡ የሶራያን እውነተኛ ታሪክ መሠረት ተደርጎ የተሰራውን ፊልም------ከሚለው የፌስቡክ አድራሻዬ ላይ እንዲመለከቱ ልጋብዝና ታሪኩን ልቋጨው፡፡

ይህን ታሪክ እዚህ ጋ ያመጣሁበት ዋነኛ ምክንያት ታሪኩን ለመተረክ ብቻ አይደለም፡፡ ሶራያ ተወግራ ስትገደል ድንጋይ ከወረወሩባት ገዳዮቿ መካከል ባሏ አንዱ ነበርና ድርጊቱን የፈጸመው (ድንጋይ ወርውሮ የገደላት) በልጆቿ ፊት ነበር፡፡ ይህ ዓይነቱ ግድያ ነው በእስልምና «የክብር ግድያ» (honor killing) የሚባለው፡፡

ከላይ እንደጠቀስኩት ሴቷ ሳታገባ አርግዛ ብትገኝ፣ እናትና አባቷ ሳይድሯት እጮኛ ብትይዝ፣ ሙስሊም ሆና ሳለች ከክርስቲያን ጋር በፍቅር ብትወዳጅ ወይም ከትዳሯ ውጭ ብታመነዝር... ብቻ በአጠቃላይ «የቤተሰቧን ክብር አጉድፋለች» ተብሎ ከታመነ አባት ልጁን፣ ጆል እናቱን፣ ወንድም እኅቱን፣ ባልም ሚስቱን መግደል ይችላል ያልኩት ነገር በአሁኑ ሰዓት በዓለም ኢስላም ሀገራት ላይ በብዛት እየተፈጸመ መሆኑን ለማሳየት በቅርቡ የተፈጸሙትን ብቻ የተወሰኑ ምሳሌዎችን በአጭሩ ቀጥሎ እናያለን፡፡

ከዛ በፊት ግን ማስታወስ የምፈልገው ነገር ቢኖር ሰዎቹ ወንጀል ሲሠሩ ከተገኙ በኃጢአታቸው ወይም በሠሩት ወንጀል ከነጭራሹ መቀጣት የለባቸውም የሚል አቋም ባይኖረኝም (ለምሳሌ ሴቷ ከትዳሯ ውጭ ስታመነዝር ብትገኝ መቀጣት አለባት) ነገር ግን ገና ከመነሻው የፈለገችውን መርጣ ስላገባች «ቤተሰብ የመረጠልሽን ብቻ ካላገባሽ» ተብላ ተወግራና ተሰቅላ መገደል በፍጹም የለባትም፡፡ እየሆነ ያለው ግን ይሄ ነው፡፡ ቀጥሎ የምናያቸው አሰቃቂ ግድያዎች የተፈጸሙት «ለምን የመረጥሽውን አገባሽ? ለምን

ሙስሊም ካልሆነ ወንድ ጋር አወራሽ? ለምን ተገደሽ ተደፈርሽ?...» በሚሉ ተልካሻ ምክንያቶች ነው እንጂ ለግድያም ሆነ ለቅጣት የሚያደርስ ምንም ነገር አልነበረም፡፡ በጣም የሚገርመው ነገር ገዳዮቹ በቤተሰባቸው ላይ ግድያውን የፈጸሙት «ክብራችን ተነካ፣ ስማችን ጠፋ» ብለው ነው እንጂ ኃጢትን ወይም ወንጀልን ተፀይፈው አለመሆኑ ነው፡፡ ግድያዎቹን እንያቸው፡- (በቅንፍ ውስጥ በእንግሊዝኛ በተጻፈው ርዕስ አማካኝነት ሙሉ ታሪኩን ከኢንተርኔት ላይ ማንበብ ይቻላል፡፡ ወይም ሙሉውን ታሪካቸውን በግል አድራሻ ማግኘት እንደሚቻል ሳልጠቁም አላልፍም)

1ኛ. ሳሚና ራጅፑት የተባለች የ18 ዓመት ወጣት ራሷ ከመረጠችው ሰው ጋር ጋብቻ ስለመሠረተች ፓኪስታን ውስጥ ታህሳስ 3 ቀን 2011 ዓ.ም ወንድሟ በጥይት ገድሏታል፡፡ (ምንጭ፡- Girl killed over karo-kari)

2ኛ. ሊቢያ ውስጥ በጋዳፊ ወታደሮች የአስገድዶ መድፈር ወንጀል የተፈጸመባቸውን ሦስት ሴቶች ልጆች በ15፣ 17 እና 18 ዓመት ዕድሜያቸው ነሐሴ 2011 ዓ.ም የገዛ አባታቸው ጉሮሮአቸውን ወግቶ ገድሎአቸዋል፡፡ (Father slit throats of three daughters in 'honour killing' after they were raped by Gaddafi's troops)

3ኛ. ፓኪስታን ውስጥ ሐምሌ 26 ቀን 2011 ዓ.ም ራዚያና ሳሚና የተባሉ ሁለት ሴት ልጆች ጾታዊ ግንኙነት ጀምረዋል በማለት አባታቸው የእነርሱን 4 ታናናሽ እኅቶቻቸውን ጨምሮ 6 ሴቶች ልጆቹን በጥይት ገድሏቸዋል፡፡ (Honour killings: Man guns down six daughters)

4ኛ. ፓኪስታን ውስጥ በማታ «ለምን ከቤት ወጣሽ?» በማለት አንዱ ልጅ ሀሊማ ባሸር የተባለች የ40 ዓመቷን እናቱን በጥይት ገድሏታል፡፡ (Woman gunned down by son over 'honour')

5ኛ. ፓኪስታን ውስጥ የ17 ዓመቷ ሳኒያ ካንን «አንቺ የፈለግሽውን ማግባት አትችይም» በማለት አጎቷ ጭንቅላቷን በጥይት ብሎ ገድሏታል፡፡ (One month's bride killed for 'honour')

6ኛ. ኢራቅ ውስጥ 2 ልጃገረዶችን አባታቸው ድንግልናቸውን አጥፍተዋል በሚል ጥረጣሬ የፈላ ውኃ ደፍቶባቸው አሰቃይቶ ከገደላቸው በኋላ አስከሬናቸው ሲመረመር ግን ድንግል ሆነው ተገኝተዋል፡፡ ('Honor killings' require tougher laws, say Iraqi women)

7ኛ. ዮርዳኖስ ውስጥ አሊያ አህመድ የተባለችውን ወጣት «ባሏን ትታው ሄዳለች» በማለት ወንድሞቿ 28 ጊዜ ሰውነቷን በስለት ወግተው ገድለዋታል፡፡ (Jordan aims to deter 'honour crime')

8ኛ. ሳውዲ ዐረቢያ ውስጥ ከክርስቲያን ጋር ተነጋግራለች በማለት ራኒያ የተባለችውን

ልጅ አባቷ ምላሷን ቆርጦ በማውጣትና በእሳት አቃጥሎ በማሰቃየት ገድሏታል፡፡ (Christian Convert Burned Alive in Saudi Arabia)

9ኛ. ኢራን ውስጥ ሳሚያህ የተባለች የ14 ዓመቷን ልጅ አባቷ ጾታዊ ግንኙነት ጀምራለች ብሎ ስላሰበ በድንጋይ ተወግራ እንድትገደል አድርጓታል፡፡ (Father Stones 14 Year Old Daughter to Death)

10ኛ. ኢራን ውስጥ ፋርዛናህ የተባለች የ17 ዓመት ልጃገረድ የባሏ ወንድም አፍኖ በመውሰድ አስገድዶ ስለደፈራት አባቷም ክብሬ ተነካ ብለው አፍና አፍንጫዋን በማፈን አየር አሳጥቶ ገድሏታል፡፡ (Iran - Honor killing claims life of 17-year-old girl)

11ኛ. ፓኪስታን ውስጥ ዛሁር አህመድና ናሲም የተባሉ ማልና ሚስት ከ10 ዓመት በፊት የተጋባችሁት ሕጋዊ ባልሆነ መንገድ በጠለፋ ነው ተብለው ከተከሰሱ በኋላ ሁለቱም በሕይወት እያሉ በእሳት እንዲቃጠሉ ተፈርዶባቸው በእሳት ተቃጥለዋል፡፡ (In the name of honour: Pak couple burnt alive)

12ኛ. ፓኪስታን ውስጥ ዛኪያ የተባለችው ሴት ባሏን «ሌላ ተጨማሪ ሚስት አግብተህ አቤት አታመጣም» ብላ ስለተከራከረችው ሰውነቷን በመቆራረጥ አሰቃይቶ ገድሏታል፡፡ ቱርክ ውስጥም እንዲሁ ተመሳሳይ ድርጊት ተፈጽሟል፡፡ (Woman ‘tortured to death’)

13ኛ. ቱርክ ውስጥ ኔይል ኤርዳስ የተባለች የ16 ዓመት ወጣት በደረሰባት አስገድዶ መደፈር ምክንያት ስላረገዘች አባቷ፣ ወንድሞቿና አጎቶቿ ደብድበው ገድለዋታል፡፡ (Pregnant As a Result of Rape, She Was Killed By Her Family)

14ኛ. ኩዌይት ውስጥ አስማ የተባለችውን የ13 ዓመት ልጅ አባቷ ድንግልናሽን አጥተሻል በሚል ጥርጣሬ አንገቷን በስለት ወግቶ ገድሏታል፡፡ (Father slit his daughter's throat)

15ኛ. ግብፅ ውስጥ ኖራ ማርዙክ አህመድ የተባለችውን የ25 ዓመት ወጣት ትወደው የነበረውን ፍቅረኛዋን በድብቅ በማግባቷ አባቷ አንገቷን ሰይፎታል፡፡ (A matter of honour: Egyptian style)

16ኛ. ሳውዲ ዐረቢያ ውስጥ ከወንድ ጋር በፌስቡክ አውርታለች የተባለች አንዲትን ወጣት አባቷ ነው ደብድቦ የገደላት፡፡ (Saudi woman killed for chatting on Facebook)

17ኛ. አሜሪካ ውስጥ ባሏን ፍቺ የጠየቀችው አሲያ ሀሰን እርሷን ሳይሆን የፈታት አንገቷን ነው በሰይፍ የቆረጠው፡፡ (The "Honor Killing" of Aasiya Hassan)

18ኛ. ዩናይትድ ኪንግደም ውስጥ ሁለት ልጆች ሻህዛድ የተባለች እናታቸውን እጆቿን ቆራርጠው ሰውነቷን በስለት ወግተው ገድለዋታል፡፡ ምክንያታቸው ደግሞ «ከባሏ

ተለየች፣ ከሌላም ሰው ጋር መገናኘት ጀምራለች» የሚል ነበር፡፡ እናታቸው በዚህ ጊዜ ዕድሜዋ 40 ነበር፡፡ (Son severs mum's hands in fatal 'honour' stabbing)

19ኛ. በጀርመን ሀገር ባሏ ነፃ ሆና በራሷ ሀሳብ ለመመራት ፈልጋለች በማለት የወነጀላትን ሙጅድ የተባለችውን ሙስሊም ወጣቷን ሚስቱን 46 ጊዜ ሰውነቷን በስለት ወግቶ ካሰቃያት በኋላ በላይዋ ላይ መኪና በመንዳት ገድሏታል፡፡ (Muslim man sentenced to life in jail after killing his German-born wife because she was 'too independent')

20ኛ. የ20 ዓመቷ ሂና ሳሊም ጣሊያን ውስጥ «ሂጃብ ለምን አለበስሽም? ፒዜሪያ ውስጥ ለምን ትሰሪያለሽ? እኛ የመረጥንልሽን ትተሽ ለምን የራስሽን እጮኛ ያዝሽ?» በማለት ቤተሰቦቿ አንገቷን በስለት ወግተው ገድለዋታል፡፡ (Pakistanis in Italy murder trial)

በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታ የተፈጸሙ በሙቶዎች የሚቆጠሩ «የክብር ግድያዎችን» መዘርዘር ይቻላል፡፡ ለማሳያ ያህል ግን ይህ በቂ ነው፡፡ «የክብር ግድያ» ሕግ በአሁኑ ጊዜ በዓለም ላይ ባሉ በሁሉም ኢስላም ሀገራት በተግባራዊ ላይ እየዋለ ነው፡፡ የዜጎች መብት ሙሉ በሙሉ ይከበርበታል በሚባለው በምዕራቡ ዓለም እንደ ፈረንሳይ ፣ጀርመንና እንግሊዝ ባሉ ሀገራትም ጭምር የሚኖሩ ሙስሊሞች ሕጉን ሲተገብሩት እየታየ ነው፡፡ ይህም የሚያሳየን ችግሩ በኢስላም ሀገራት ላይ ብቻ የሚፈጸም እንዳልሆነ ነው፡፡ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት /United Nations/ በ2008 ዓ.ም ባወጣው መረጃ መሠረት በዓለም ላይ ያሉ ሙስሊሞች በሚፈጽሙት «የክብር ግድያ» ምክንያት በየዓመቱ 5 ሺህ ሴቶችና ሕጻናት በቤተሰቦቻቸው ይገደላሉ፡፡ The United Nations reports that family members kill more than 5,000 women and girls around the world each year via Islamic honor killings.

http://barenakedislam.com/2008/12/28/honor-killings-murder-in-the-name-of-pride/

በነገራችን ላይ ከእስልምናው እምነት ውጭ ያሉ ሰዎችም ቤተሰቦቻቸውን የገደሉ ሊኖሩ ይችላሉ ነገር ግን እንደነዚህ ያሉት አንድም ጠጥተው ሰክረውና በተለያዩ ሱሶች ደንዝዘው አሊያም የጤናና የአእምሮ መታወክ አጋጥሟቸው ወንጀሉን ይፈጽሙ ይሆናል እንጂ «ለክብር ግድያ» ብለው በማንም ላይ ጉዳት አያደርሱም፡፡ በእስልምናው እንዳለው የሸሪዓ ሕግ ግን «ለክብሬ ስል ልገደላት» ብሎ ሚስቱን፣ እኅቱን ወይም እናቱን የሚገድል ማንም የለም፡፡ ማንም ጤነኛ የሆነ ሰው ይህንን አያደርግም፡፡ ይህንን የሚያደርገው እርሱ ነፍሰ በላው ጥንተ ጠላት ዲያብሎስ ብቻ ነው፡፡

+++ «...እናንተ ከአባታችሁ ከዲያብሎስ ናችሁ የአባታችሁንም ምኞት ልታደርጉ ትወዳላችሁ። እርሱ ከመጀመሪያ ነፍሰ ገዳይ ነበረ፤ እውነትም በእርሱ ስለ ሌለ በእውነት አልቆመም። ሐሰትን ሲናገር ከራሱ ይናገራል፥ ሐሰተኛ የሐሰትም አባት ነውና» ዮሐ 8፡43፡፡ +++

14ኛ. ቁርአን ወደፊት ስለሚሆነው የዓለም ክስተት ምንም ነገር አለማወቁ እንዳይታመን አድርጎታል፡- ቁርአንን በተመለከተ ይህ የመጨረሻ ርዕሳችን ነው፡፡ ቁርአን በጥቅሉ ሙስሊሞች ጀነት እንደሚገቡና በዚያም ዝሙትን ጨምሮ የተንደላቀቀ ሕይወት እንደሚኖሩ በአንጻሩ ደግሞ ክርስቲያኖች ሲኦል ገብተው መራራ ምግብ እንደሚመገቡና እሳት እንደሚበላቸው ከመናገር ውጭ ስለ ወደፊቱ ነባራዊ ሁኔታ ምንም ዓይነት ትንቢት አይገኝበትም፡፡ የአምላክ ቃል በትክክልና በእርግጠኝነት ወደፊት የሚሆነውን ነገር በትንቢት መናገር መቻል አለበት፡፡ ቁርአን ግን አንዲት የዓለምን ሁኔታ እንኳን በትንቢት መልክ ለመናገር ድፍረት አላገኘም፡፡

በአንጻሩ ደግሞ መጽሐፍ ቅዱስ ሙሉ በሙሉ የትንቢት መጽሐፍ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ ብሉይ ኪዳን እንዳለ የሐዲስ ኪዳን ትንቢትና ምሳሌ ነው፡፡ ስለ መሲሁ ክርስቶስ ብሉይ ኪዳን ላይ የተነገሩ ትንቢቶች በሙሉ በሐዲስ ኪዳን ተፈጽመዋል፡፡ በሐዲስ ኪዳን ስለ ወደፊቱ (መጻዒው ዓለም) የተነገሩ ትንቢቶች ደግሞ እስካሁን የተፈጸሙ አሉ፣ አሁንም እየተፈጸሙ ነው፣ ወደፊትም ይፈጸማሉ፡፡ ለምሳሌ ክርስቶስ የዓለም ፍጻሜ ከመድረሱ በፊት በምድር ላይ ምን ምን እንደሚከሰት በማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 24 ላይ በዝርዝር ተናግሯል፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ የመጨረሻው የዓለም ጦርነት በትክክል የት ቦታ እንደሚሆንም በዮሐንስ ራእይ 16 ላይ ተናግሯል፡፡ የሚነሳውን ሐሰተኛ ነቢይ ማንነት በራእይ 13 ላይ በግልጽ አስቀምጦታል፡፡ በቁርአን ውስጥ ግን እንደዚህ ዓይነት ግልጽና ቁርጥ ያሉ ትንቢቶች በፍጹም አይገኙም፡፡

ከላይ «ብሉይ ኪዳን እንዳለ ሙሉው ክፍል የሐዲስ ኪዳን ትንቢትና ምሳሌ ነው» ያልኩትን ነገር በምሳሌ ማየት እንችላለን፡፡ እውነተኛው አምላክ መድኃኔዓለም ኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋን ተዋሕዶ ወደዚህች ምድር የመጣው በነቢያት ትንቢት አስነግሮ ሱባኤ አስቆጥሮ ነው፡፡ እንዲሁ እንደ እንግዳ ደራሽ እንደ ውኃ ፈሳሽ በድንገት አልመጣም። እርሱ በወንጌል የፈጸማት እያንዳንዷ ነገር ከ1000 እና ከ700 ዓመታት በፊት ቀድማ በነቢያት ትንቢት የተነገረች ናት። (1000 እና 700 ዓመታት የተባለው ከክርስቶስ ልደት በፊት ዳዊትና ኢሳይያስ የነበሩበትን ዘመን ነው) ክርስቶስ በነቢያት ስለ እርሱ የተነገሩትን ትንቢቶች በሙሉ ፈጽሟቸዋል። ለዚህም ነው በወንጌል ላይ በጣም ብዙ ቦታ «በነቢይ...ተብሎ የተነገረው ይፈጸም ዘንድ ክርስቶስ እንዲህ... አደረገ» እየተባለ

የተጻፈው፡፡ የተወሰኑ ምሳሌዎችን እንይ፡-
ከክርስቶስ መወለድ ከ700 ዓመት በፊት የነበረው ነቢዩ ኢሳይያስ *«ጌታ ራሱ ምልክት ይሰጣችኋል፤ እነሆ ድንግል ትፀንሳለች፥ ወንድ ልጅም ትወልዳለች፥ ስሙንም አማኑኤል ብላ ትጠራዋለች»* በማለት የተናገረው ትንቢት በክርስቶስ የተፈጸመ መሆኑን ማቴዎስ ወንጌል ላይ እንዲህ ተጽፎ እናነባለን፡- «የኢየሱስ ክርስቶስም ልደት እንዲህ ነበረ፡- እናቱ ማርያም ለዮሴፍ በታጨች ጊዜ ሳይገናኙ ከመንፈስ ቅዱስ ፀንሳ ተገኘች። እጮኛዋ ዮሴፍም ጻድቅ ሆኖ ሊገልጣት ስላልወደደ በስውር ሊተዋት አሰበ። እርሱ ግን ይህን ሲያስብ፥ እነሆ የጌታ መልአክ በሕልም ታየው፥ እንዲህም አለው፡- የዳዊት ልጅ ዮሴፍ ሆይ፥ ከእርስዋ የተፀነሰው ከመንፈስ ቅዱስ ነውና እጮኛህን ማርያምን ለመውሰድ አትፍራ። ልጅም ትወልዳለች፤ እርሱ ሕዝቡን ከኃጢአታቸው ያድናቸዋልና ስሙን ኢየሱስ ትለዋለህ። *በነቢይ ከጌታ ዘንድ እነሆ፥ ድንግል ትፀንሳለች ልጅም ትወልዳለች፥ ስሙንም አማኑኤል ይሉታል* የተባለው ይፈጸም ዘንድ ይህ ሁሉ ሆኖአል፣ ትርጓሜውም እግዚአብሔር ከእኛ ጋር የሚል ነው» ማቴ 1፡18-23፡፡
ነቢዩ ኢሳይያስ ከ700 ዓመት በኋላ ሊፈጸም ስለሚችለው ነገር ምን ያህል እርግጠኛ ሆኖ እንደተናገረ እናስተውል! «ድንግል የሆነች ሴት ወደፊት ልትፀንስና ልትወልድ ትችል ይሆናል» አላለም፡፡ አሊያም «ድንግል የሆነች ሴት ወደፊት ልትፀንስና ልትወልድ ትችላለች» አይደለም ያለው፡፡ *«እነሆ ድንግል ትፀንሳለች፥ ወንድ ልጅም ትወልዳለች»* (ኢሳ 7፡14) በማለት እርግጠኛ ሆኖ ነው ከ700 ዓመት በኋላ የሚሆነውን ነገር የተናገረው፡፡
መጽሐፍ ቅዱስ ሙሉ በሙሉ የትንቢት መጽሐፍ ነው የሚባለው ለዚህ ነው፡፡ መድኃኔዓለም ክርስቶስ ዓለሙን ሁሉ ለማዳን ሲል መፀነሱ፣ መወለዱ፣ መጠመቁ፣ ሞቶ መቀበሩ፣ ከሙታን መካከል ተለይቶ መነሳቱና ማረጉ አስቀድሞ በነቢያት ትንቢት የተነገረ ነው፡፡ ክርስቶስ በወንጌል ላይ ያደረጋት እያንዳንዷ ድርጊት ቀድማ በትንቢት የተነገረች ናት፡፡ ለምሳሌ፡- በአህያ ውርንጭላ ላይ ሆኖ ወደ ቤተመቅደስ መግባቱ እንኳን ቀድማ የተነገረች ትንቢት ናት፡፡ ነቢዩ ዘካርያስ «የኢየሩሳሌም ልጅ ሆይ እልል በዪ፣ እነሆ ንጉሥሽ ጻድቅና አዳኝ ነው፤ ትሑትም ሆኖ በአህያይቱ ግልገል በውርንጭላ ላይ ተቀምጦ ወደ አንቺ ይመጣል» (ዘካ 9፡9) በማለት የተናገረው ትንቢት ክርስቶስ በተግባር እንደፈጸመው አራቱም ወንጌላዊያን ጽፈውታል፡፡ (ማቴ 21፡1-11፣ ማር 11፡1-11 ፣ ሉቃ 19:28-40፣ ዮሐ 12:13) ማቴዎስ ወንጌል ላይ ያለውን እንይ፡- «ወደ ኢየሩሳሌምም ቀርበው ወደ ደብረ ዘይት ወደ ቤተ ፋጌ ሲደርሱ፥ ያንጊዜ ኢየሱስ ከደቀ መዛሙርቱ ሁለት ላከ፥ እንዲህም አላቸው፡- በፊታችሁ ወዳለችው መንደር ሂዱ፥ በዚያን ጊዜም

የታሰረችን አህያ ውርንጫም ከእርስዋ ጋር ታገኛላችሁ፤ ፈትታችሁ አምጡልኝ፡፡ ማንም አንዳች ቢላችሁ ለጌታ ያስፈልጉታል በሉ፤ ወዲያውም ይሰዳቸዋል። ለጽዮን ልጅ ‹እነሆ፥ ንጉሥሽ የዋህ ሆኖ በአህያ ላይና በአህያይቱ ግልገል በውርንጫይቱ ላይ ተቀምጦ ወደ አንቺ ይመጣል በሉአት› *ተብሎ በነቢይ የተነገረው ይፈጸም ዘንድ ይህ ሆኑ*› ይላል የማቴዎስ ወንጌል፡፡ በእንደዚህ ዓይነት መንገድ ክርስቶስ በወንጌል ላይ ያደረጋት እያንዳንዷ ድርጊት ቀድማ በትንቢት ተነግራለች፡፡ በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታ የብሉይ ኪዳን ትንቢቶች በሙሉ በክርስቶስ መፈጸማቸውን በዝርዝር ገጽ---ላይ ይመልከቱ፡፡

በቁርአን ውስጥ ግን እንደዚህ ዓይነት ግልጽና ቁርጥ ያሉ ትንቢቶች በፍጹም የሉም፡፡ ሊኖሩም አይችሉም፡፡ ሙስሊሞች ‹‹መሐመድ የነቢያት ሁሉ መደምደሚያ ነው›› ይላሉ፤ በቁርአኑም ላይ ይህ ተደጋግሞ ተጽፏል፡፡ ነገር ግን በቁርአኑ ላይ አንድ እንኳን ትንቢት ስለ መሐመድ አልተነገረም፡፡ ነቢያት በእግዚአብሔር መንፈስ ተነድተው የጻፏቸው የብሉይ ኪዳን መጻሕፍትኮ ሙስሊሞቹም ጋር ‹‹ተውራት›› የሚል ስያሜ ተሰጥቷቸው በቁርአናቸው ውስጥ አሉ፡፡ የትንቢት መጻሕፍቶቹ እነርሱም ጋር ካሉ ታዲያ ለምን ወደፊት ‹‹የነቢያት ሁሉ መደምደሚያ›› ሆኖ ስለሚመጣው መሐመድ አንድ እንኳን ትንቢት አልተናገሩም? ስለማንኛውም ነገር ቢሆንኮ በቁርአን ውስጥ ግልጽና ቁርጥ ያሉ ትንቢቶች የሉም፡፡ የዘመኑ ሙስሊም መምህራኖች የዚህ ማጣፊያው ሲያጥራቸው ሐዲስ ኪዳን ላይ ‹‹ኢየሱስ ስለ መሐመድ ትንቢት ተናግሯል›› በማለት ጆሮን ጭው የሚያደርግ የሐሰት ፈጠራቸውን ማራገብ ጀምረው ነበር፡፡ ካፈርኩ አይመልሰኝ ዓይነት ነው ነገሩ፡፡ በወንጌሉ ላይ ስለ መንፈስ ቅዱስ የተነገረውን ጥቅስ ጠምዝዘው ለመሐመድ ሊሰጡት ሞክረዋል፡፡ ወደ እውነታው ስንመጣ ግን መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ግብፅ ጠንቋዮች እንኳን ይናገራል፡፡ ሆኖም ግን መሐመድንም ሆነ እምነታቸውን ፈጽሞ አያውቃቸውም፡፡ እርግጥ ነው መድኃኔዓለም ክርስቶስ ወደፊት በዓለም ስለሚሆነው ነባራዊ ሁኔታ ሲናገር ‹‹ኢየሱስም በደብረ ዘይት ተቀምጦ ሳለ ደቀ መዛሙርቱ ለብቻቸው ወደ እርሱ ቀርበው ንገረን፥ ይህ መቼ ይሆናል? የመምጣትህና የዓለም መጨረሻ ምልክቱስ ምንድር ነው? አሉት። ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አላቸው፡- *ማንም እንዳያስታችሁ ተጠንቀቁ፤... ብዙ ሐሰተኞች ነቢያትም ይነሣሉ፣ ብዙዎችንም ያስታሉ*›› ብሏል፡፡ ማቴ 24፡1-11፡፡ ይህ ትንቢት ደግሞ በትክክል መሐመድንም ያካትታል፡፡ ‹‹ብዙ ሐሰተኞች ነቢያትም ይነሣሉ›› ነው የተባለው፡፡ ሐሰተኛ ነቢይ!!!

## እናወዳድር እንዴ!?

ማንን ከማን ጋር እናወዳድር? መሐመድን ከሌሎች ነቢያት ጋር? ከእርሳቸው በፊት ካሉት ነቢያት ጋር ነው ወይስ በኋላ ካሉት? ወይስ በእርሳቸው ዘመን ከነበሩት ሌሎች ቅዱሳን ሰዎች ጋር እናነጻጽራቸው? አሊያም ከሐዋርያት ጋር እናወዳድራቸው ይሆን? ነው ወይስ ሙስሊሞቹ እንደሚያደርጉት መሐመድን ከዒሳ ጋር እናወዳድር? ፈጽሞ ከሁሉም ጋር ሊወዳደሩም አይችሉም፡፡ መሐመድን ከነቢያትና ከአባቶች ጋር ብሎም ከክርስቶስ ጋር ለማወዳደር መሞከሩ በራሱ ትልቅ ድፍረት ነው፡፡ ይህን ርዕስ የመረጥኩት ለማወዳድርም ፈልጌ አይደለም፡፡ ሆኖም ግን ሙስሊም ወገኖቻችን በተለይ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ «ነቢያችን መሐመድ የነቢያት ሁሉ መደምደሚያ ነው» እያሉ እርሳቸው ከሁሉም ነቢያትና ቅዱሳን ጋር እያወዳደሩ ፈጽሞ ነቢያቸውን የማይመለከቱ ጥቅሶችን ወስደው ለእርሳቸው በመለጠፍ የበላይነትን ማዕረግ ሊሰጧቸው ይሞክራሉ፡፡ ስለዚህ እኔም «ማወዳደር» የሚለውን ርዕስ ዝም ብሎ ማለፉ አልታየኝምና እንደ እነርሱ አካሄድ መሐመድን ላነጻጽራቸው ነው፡፡ ነገር ግን ንጽጽሩ ከላይ ከጠቀስኳቸው ነቢያት ጋር አይደለም፡፡ ክርስቶስን ከመሐመድ ጋር ማነጻጸርም ፈጽሞ የማይታሰብ ነው፡፡ ፈጣሪን ከተራ ኃጢአተኛ ፍጡር ጋር ለማነጻጸር መሞከሩ በራሱ ትልቅ ድፍረትና ኃጢአት ነው፡፡ (የክርስቶስን ፈጣሪነት ወደፊት ሄደው ገጽ---- ላይ ይመልከቱ፡፡) የክርስቶስን ፈጣሪነት መጽሐፍ ቅዱስና ሌሎችም ቅዱሳት መጻሕፍት ብቻ ሳይሆኑ ቁርአኑም ይመሰክርለታል፡፡ በመሠረቱ ቁርአን ክርስቶስን ፈጽሞ አያውቀውም፡፡ ስለ ክርስቶስ የባሕርይ አምላክነት ለማስረዳት የቁርአን ምስክርነት አያስፈልገንም፡፡ ከእርሱ የሚገኝን ጥቅስን ማስረጃ አድርጎ ማቅረብም ፍጹም ተገቢ አይደለም፡፡ ምንም እንኳን ቁርአን ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ማንነት ለመመስከር እውቀቱም ሆነ ብቃቱ ፈጽሞ ባይኖረውም አሁንም እንደ ሙስሊሞቹ አካሄድ ለመሄድ ሲባል ብቻ ከቁርአኑ አንድ ጥቅስ አሳያችኋለሁ፡፡

አብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ በፈቃድ ፍጹም አንድ ናቸውና ጌታ በወንጌል ላይ «በአባቴ ፈቃድ...» ብሎ የገለጸውን ቁርአኑ በመጠምዘዝ «በአላህ ፈቃድ» እያለ ይጠቀምበታል፡፡ እንዴትም አድርጎ ቢጠቀምበት ግን የሚመሰክረው ነገር አለ፡፡ ቁርአኑ ክርስቶስ እፍ ብሎ በእስትንፋሱ ነፍስ መፍጠሩን፣ በደረቅ ግንባር ላይ ዓይን መፍጠሩንና ሙታንን ማስነሳቱን እንዲህ በማለት ይናገራል፡- «ዒሳ ይላልም፡- እኔ ከጌታዩ ዘንድ በተአምር መጣሁላችሁ፡፡ እኔ ለእናንተ ከጭቃ እንደ ወፍ ቅርጽ እፈጥራለሁ፤ በእርሱም እተነፍስበታለሁ፤ በአላህም ፈቃድ ወፍ ይሆናል፡፡ በአላህም

ፈቃድ ዕውር ሆኖ የተወለደን፣ ለምጻምንም አድናለሁ፤ ሙታንንም አስነሳለሁ» እያለ ይቀጥላል ቁርአኑ:: 3፡49::

«በአባቴ ፈቃድ...» የምትለዋን የወንጌል ቃል ቁርአኑ ጠምዘዝ አድርጎ «በአላህ ፈቃድ» ከማለቱ በቀር ክርስቶስ የሕይወት ፈጣሪና የድንቅ ድንቅ ተአምራት ባለቤት መሆኑን ነው እየተናገረ ያለው:: መሐመድን ከክርስቶስ ጋር ማነጻጸር በራሱ ትልቅ ኃጢአት ነው ያልኩት ለዚህ ነው:: ተራ ፍጡር ከፈጣሪው ጋር ፈጽሞ ሊነጻጸር አይችልም:: ለዚያውምኮ መሐመድ ተራ ፍጡር የሆኑ ሰው ብቻ አይደሉም:: የስንቱን ንጹሐን ደም ያፈሰሱ፣ በኃጢአት ባሕር ውስጥ ሲዋኙ የነበረ፣ በእርኩስ መንፈስ የተያዙና በእርኩስ መንፈሱም ይመሩ የነበሩ ጨካኝ አረመኔ ሰው ነበሩ:: ይህንን ደግሞ ሌላ ማስረጃ ሳያስፈልገን ራሳቸው ቁርአኑና ሐዲሱ የሚያረጋግጡት መሆኑን ነው እስካሁን ድረስ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ያየነው:: እነርሱ የሚሉትን ነው መልሼ በግልጽ ያወራሁት እንጂ እኔ ከራሴ አልተናገርኩትም:: ስለዚህ ታዲያ መሐመድን ከማን ጋር እናነጻጽራቸው?

ኢ.ኤ.አ ከታህሳስ 23 ቀን 1805 ዓ.ም እስከ ሰኔ 27 ቀን 1844 ዓ.ም ድረስ የኖረው አሜሪካዊው የሞርሞኒዝም ሃይማኖት መሪ የነበረው ጆሴፍ ስሚዝ /joseph smith/ ነቢይ ነኝ ብሎ በተነሳበት ወቅት በሺዎች የሚቆጠሩ በርካታ ተከታዮችን ማፍራት ችሎ ነበር:: «የኋለኛው/የፍጻሜው ዘመን ቅዱስ እንቅስቃሴ» /Latter day saint movement/ የሚል መርህ ይዞ የነበረው ይህ ግለሰብ በዘመኑ «የመርሞን መጽሐፍ» የሚል የእምነቱ መመሪያ መጽሐፍም አሳትሞ ነበር:: ነገር ግን መጽሐፉን እኔ ጻፍኩት አልነበረም ያለው ይልቁንም «ሞሮኒ የሚባል መልአክ ነው ከሰማይ ያወረደልኝ» በማለት ሲያስተምር ያለጥርጣሬ የተከተሉት በሺዎች የሚቆጠሩ ነበሩ:: እንደ እርሱ ትምህርት ሞሮኒ የሚባል መልአክ መገለጦችን በየጊዜው ያመጣለት ነበር:: የጆሴፍ ስሚዝ ተከታዮችም በመጨረሻው ዘመን የተገኘ የነቢያት ሁሉ መደምደሚያ እንደሆነ ይመሰክሩለት ነበር:: በካርቴጅ ኢሊኖይስ እስር ቤት ከመታሰሩና ከመሞቱ በፊት የአሜሪካ ፕሬዝዳንት የመሆን ትልቅ ሕልም ነበረው:: ታዲያ ይህን ግለሰብ ከመሐመድ ጋር እንዴትና በምን እናነጻጽረው? ከተባለ ራሱ ጆሴፍ ስሚዝ በአንድ ወቅት ሲናገር «እኔ ለዚህ ተውልድ ሁለተኛው መሐመድ እሆንለታለሁ» ብሎ የተናገረው ሕዝብ በተሰበሰበበ አደባባይ ነበር:: "I will be to this generation a second Mohammed, whose motto in treating for peace was 'the Alcoran [Koran] or the Sword.' So shall it eventually be with us—'Joseph Smith or the Sword!'" (Fawn M. Brodie, No Man Knows My History, second edition, (New York: Alfred A. Knopf, 1971), p. 230–231) See also "History of the [Mormon] Church, Vol. III, p.167" (Joseph Smith made this

statement at the conclusion of a speech in the public square at Far West, Missouri on October 14, 1838.)

በእርግጥ ጆሴፍ ስሚዝ እንዳለው ለነበረበት ትውልድ ሁለተኛ መሐመድ ሆኗል ወይስ አልሆነም? የሚለው በራሱ ብዙ ጥናት ማድረግ የሚፈልግ ቢሆንም እኔ ግን አሁን የፈለኩት ሁለቱን ሰዎች ብዙ የሚያመሳስሏቸው ነገሮች መኖራቸውን ማሳየት ነው፡፡ ስለዚህ መሐመድንና ጆሴፍ ስሚዝን በጣም የሚያመሳስላቸውንና አንድ የሚያደርጓቸውን 18 ነጥቦችን ቀጥለን እናያለን፡፡

1ኛ. ሁለቱም ገና ሲጀምሩ «በመልአክ ተጎበኘቻለሁ» ብለው ነው የተነሱት፡፡ መሐመድ በጂብሪል፣ ጆሴፍ ስሚዝ ደግሞ ሞሮኒ የሚባል መልአክ፡፡

2ኛ. ሁለቱም «ራእይ አይቻለሁ» ብለው አስተምረዋል፡፡

3ኛ. ሁለቱም «መገለጦችን መልአክ ከሰማይ አምጥቶልኛል» ብለው ነው የተነሱት፡፡

4ኛ. ሁለቱም አምላክ በሰማይ ያዘጋጀውን መጽሐፍ ቅጂውን ለእነርሱ በምድር ላይ እንደሰጣቸው አስተምረዋል፡፡

5ኛ. መሐመድ ከነጭራሹ ፊደል ያልቆጠሩ ሲሆን፤ ጆሴፍ ስሚዝም እስከ 2ኛ ክፍል ድረስ ብቻ ነበርና የተማረው ሁለቱም ማንበብና መጻፍ አይችሉም ነበር፡፡ ሁለቱም አለመማራቸውን «መጽሐፍ ከአምላክ ነው የተሰጠኝ» ለሚለው ትምህርታቸው እንደምክንያት አድርገው ተጠቅመውበታል፡፡

6ኛ. ሁለቱም «ከእኔ በፊት በምድር ላይ እውነተኛ ሃይማኖት አልነበረም፤ ለሕዝቡ እውነተኛውን መንገድ ላሳየው ተልኬያለሁ» ብለው የተነሱት፡፡

7ኛ. ሁለቱም የቀድሞዎቹን አባቶች የእነርሱ እንደነበሩ አስተምረዋል፡፡ መሐመድ እነ አዳምንና አብርሃምን ሙስሊም ነበሩ ሲሉ ጆሴፍ ስሚዝ ደግሞ እርሱ እስከተነሳበት ጊዜ ድረስ ያሉትን ቅዱሳን በሙሉ የሞርሞኒዝም እምነት ተከታዮች እንደነበሩ አስተምሯል፡፡

8ኛ. ሁለቱም መጽሐፍ ቅዱስ እንደተበረዘ፣ ቅጂዎቹም እንደጠፉና አስተማማኝነት እንደሌለው አስተምረዋል፡፡

9ኛ. መሐመድ ቁርአኑን ፍጹም እንደሆነ፣ በሰው እጅም እንዳልተነካ ሲናገሩ ጆሴፍ ስሚዝም እንዲሁ የሞርሞን መጽሐፉን በሰው እጅም እንዳልተነካና ፍጹም እንደሆነ አስተምሯል፡፡

10ኛ. ሁለቱም «አምላክ የላከኝ የመጨረሻው ነቢይ እኔ ብቻ ነኝ» እያሉ በሰፊው አስተምረዋል፡፡ተከታዮቻቸውም የመጨረሻው ነቢይ መሆናቸውን አተምረውላቸዋል፡፡

11ኛ. ሁለቱም «አምላክ ለሰው ልጆች ሁሉ የመጨረሻ መልእክቱን ያስተላለፈው በእኔ መጽሐፍ ብቻ ነው፣ እውነተኛውም መመሪያ የእኔ መጽሐፍ ብቻ ነው» በማለት

አስተምረዋል፡፡ ተከታዮቻቸውም ይህንኑ በገሃድ አተምረውላቸዋል፡፡

12ኛ. ሁለቱም ራሳቸውን ከክርስቶስ ጋር እያነጻጸሩ እነርሱ እንደሚበልጡ ተናግረዋል፡፡

13ኛ. ሁለቱም የዓለም ሕዝብ በሙሉ የእነርሱን ሃይማኖት ካልተከተለ እንደማይድን በስፋት አስተምረዋል፡፡

14ኛ. ሁለቱም በእውነተኛው እምነታቸው ምክንያት በብዙ ሰዎች ዘንድ ተቀባይነት እንዳላገኙና እንደተከሰሱ አስተምረዋል፡፡

15ኛ. ሁለቱም /polygamist/ ብዙ ሚስቶችን ለራሳቸው ይሰበስቡ ነበር፡፡ መሐመድ በቅምጥነት ወይም በዕቁባትነት የያዟቸውን ሳይጨምር ያገቧቸው ሴቶች 31 ነበሩ፡፡ ይህንንም በገጽ----ላይ በዝርዝር ይመልከቱ፡፡ ጆሴፍ ስሚዝም በተመሳሳይ ሁኔታ በግልጽ የታወቁ 30 ሚስቶች ነበሩት፡፡

16ኛ. ሁለቱም የእምነቶቻቸውን መሠረተ ሀሳብ የወሰዱት ከእምነት የለሾች፣ ከከሀዲዎችና ከመናፍቃን መጻሕፍት ሲሆን ከተለያዩ ምንጮች ያገኙትን ሀሳብ ከክርስትናው ጋር ቀላቅለው ነበር ያስተማሩት፡፡

17ኛ. ሁለቱም ከእነርሱ በኋላ ተከታዮቻቸው እንዴትና በማን መመራት እንዳለባቸው በግልጽ አልተናገሩም ነበር፡፡ መሐመድ ከሞቱ በኋላ «የሱኒ ሙስሊሞች» አዲስ መሪ እንምረጥ ሲሉ «የሺዓ ሙስሊሞች ደግሞ ልጃቸው ወይም የቅርብ ዘመዳቸው ነው መሪ መሆን ያለበት» ብለው በወቅቱ ስለተለያዩ ይኸው ዛሬም ድረስ እንደ ተለያዩ ቀርተዋል፡፡ የጆሴፍ ስሚዝ ተከታዮችም ቢሆኑ እንዲሁ በተመሳሳይ ሁኔታ ከእርሱ ሞተ በኋላ «ልጁ ይምራን ወይስ ሌላ ሰው?» በሚለው ሀሳብ እስከመጣላት ደርሰው ተለያይተዋል፡፡

18ኛ. የጆሴፍ ስሚዝ ተከታዮች በ1857 ዓ.ም መስከረም 11 ቀን 140 ሰዎችን የገደሉ ሲሆን የመሐመድም ተከታዮች በተመሳሳይ ወርና ቀን መስከረም 11, 2001 ዓ.ም በአሜሪካው የንግድ ማዕከል ላይ የሽብር ጥቃት ፈጽመው 3 ሺህ ሰዎችን ገድለዋል፡፡ ይህ በርግጥ የአጋጣሚ ጉዳይ ቢሆንም ጊዜው ስለተመሳሰለ ነው የጠቀስኩት፡፡

ጆሴፍ ስሚዝ የተነሳው መሐመድ ከነበሩበት ጊዜ 1212 ዓመታት በኋላ ቆይቶ ነው፡፡ ለመሆኑ በሁለቱ መካከል የዚህን ያህል የጊዜ ርቀት እያለ እንዴት እንዲህ ሊመሳሰሉ ቻሉ? ከተባለ መልሱ ቀላል ነው፡፡ ጆሴፍ ስሚዝ በትክክል አርአያ (role model) አድርጎ የተነሳው መሐመድን ስለሆነ የእርሳቸውን መንገድ ሊከተል ችሏል፡፡ ይህ ምንም የማያሻማ ግልጽ የሆነ ነገር ነው፡፡ ራሱ ጆሴፍ ስሚዝ ሲናገር «እኔ ለዚህ ተውልድ ሁለተኛው መሐመድ እሆንለታለሁ» ብሎ መናገሩን ቀደም ብለን አይተናል፡፡

ከጆሴፍ ስሚዝ በተሻለ ሁኔታ መሐመድን አርአያ አድርጎ የተነሳ አንድ ሌላ ሰው ማየት እንችላለን-አዶልፍ ሂትለርን፡፡ መሐመድ በ627 ዓ.ም ቁጥራቸው 900 የሚሆኑ የባኑ ቁራይዛ የአይሁድ ጎሳዎችን በአንድ ቀን የጂምላ ጭፍጨፋ እንዳካሄዱባቸው ከዚህ በፊት በገጽ-----ላይ በዝርዝር አይተናል፡፡ ይህም ታሪክ በሐዲሱና በቁርአኑ ላይ በጣም ብዙ ቦታ ተመዝግቦ ይገኛል፡፡ የጀርመኑ አዶልፍ ሂትለርም ከ6 ሚሊዮን በላይ አይሁዳውያንን በግፍ ሲጨፈጭፍ ሃይማኖትን መሠረታዊ ጉዳይ አድርጎ ነበር የተነሳው፡፡ ሂትለር ይህን ዘግናኝና አረመኔያዊ ድርጊቱን ሲፈጽም "ይህን የማደርገው ፈጣሪዬን ለማገልገል ስል ነው" ብሎ ነበር፡፡ መሐመድም በአላህ መንገድ ለመዋጋትና ለክብሩም ሲሉ ነው 900 አይሁዳውንን እንዲሰየፉ ያደረጉት፡፡ ልዩነቱ መሐመድ ድርጊቱን የፈጸሙት በአንድ ቀን ሲሆን ሂትለር ደግሞ በተለያየ ጊዜ መሆኑ ብቻ ነው፡፡ አዶልፍ ሂትለር መሐመድን እንዴት አድርጎ በአርአያነት እንደተጠቀመባቸው ቀጥለን በዝርዝር እናያለን፡፡

ሂትለር በዘመኑ «ሜይን ካምፍ/Mein Kampf» የተባለ አንድ ትልቅ መጽሐፍ ጽፏል፡፡ በጣም በሚገርም ሁኔታ የዚህ የሂትለር መጽሐፍ ይዘቱ ከቁርአኑ ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡ መሐመድና ሂትለር ሁለቱም ለተከታዮቻቸው ያስተማሯቸው ትምህርቶችና የፈጸሟቸው ድርጊቶች አንድ ናቸው፡፡ ለዚህም ማሳያ ይሆን ዘንድ ከሁለቱም መጽሐፎች የተወሰዱ ጥቅሶችን ቀጥለን በዝርዝር እንይ፡-

1ኛ. መሐመድና ሂትለር ሁለቱም በወቅቱ አይሁዶችን ከምድረ ገጽ ማጥፋት እንዳለባቸው ለተከታዮቻቸው ትእዛዝ ሰጥተዋል፡፡ "Jews are vampires who must die sooner or later. They must be destroyed" (Mein Kampf. P.450) "The Prophet then killed their men and distributed their women, children and property among the Muslims." (Sahih Bukhari 5:59:362), "Just issue orders to kill every Jew in the country." (Bukhari:1:1:6)

2ኛ. ሁለቱም አይሁዶችን የጨፈጨፉት በአምላካቸው ትእዛዝና ፈቃድ እንደሆነ ተናግረዋል፡፡ ቁርአኑ «አላህ ነው እንጂ እናንተ አልገደላችኋቸውም» ይላል፡፡ 8:17፡፡ ሂትለርም የአምላኩን ፈቃድ በእርሱ እንደተገለጸጠና ድርጊቱን ተግባራዊ እንዳደረገው ነው የተናገረው፡፡ "It is not ye who slew them; it is God; when thou threwest a handful of dust, it was not thy act, but God's....." (The killing of surrendered men of Qurayza tribe was done by the wish of Allah). (Qur'an, 8:17), "I believe today that I am acting in the sense of the Almighty Creator. By warding off the Jews I am fighting for the Lord's work." (Hitler's speech: 1936, Reichstag), "... We have the right to murder 400,000 to 500,000 people in the Nazi Revolution!" (Hitler's

speech: January 30, 1937 Berlin, Reichstag)

3ኛ. ሁለቱም ለተከታዮቻቸው ሽብር በመፍጠር ማጥቃት እንዳለባቸው ትእዛዝ መስጠታቸውንና ማስተማራቸውን በየመጽሐፎቻቸው ላይ በሰፊው ጽፈዋል፡፡ እነርሱም ራሳቸው አሸናፊ የሆኑት በሽብር መሆኑን ተናግረዋል፡፡ “Allah shall cast terror into the hearts of the unbelievers. Strike them above the necks, smite their fingertips”. (Qur’an 8:12), “Allah made the Jews leave their homes by terrorizing them so that you killed some and made many captive. And He made you inherit their lands, their homes, and their wealth. He gave you a country you had not traversed before.” (Qur'an 33.26), “Therefore, when you meet the unbelievers smite their necks...” (Qur’an, 47:4), “Allah’s Apostle said, ‘I have been sent with the shortest expressions bearing the widest meanings, and I have been made victorious with terror.’” (Bukhari: 4:52:220), "Spiritual terror...men must threaten and dominate men by compulsion. Compulsion is only broken by compulsion and terror by terror." (Mein Kampf:676), “The importance of physical terror against the individual and the masses also became clear to me.” (Mein Kampf.P. 58)

4ኛ. ሁለቱም ለተከታዮቻቸው ጥላቻን ይሰብኩ ነበር፡፡ ከሌሎች ጋር ተከባብሮ በወዳጅነት ከመኖር ይልቅ በጥላቻ ስሜት መራራቅን አስተምረዋል፡፡ መሐመድ ሙስሊሞች ክርስቲያኖችን ፈጽሞ ጓደኛ አድርገው እንዳይዙ በቁርአኑ ላይ አስጠንቅቀዋል፡፡ እነርሱን ጓደኛ አድርገው ከያዙም አላህ ይቀጣቸዋል፡፡ ሂትለርም ይህንን የጥላቻ ትምህርት በድጋሚ አስተምሮበታል፡፡ “O ye who believe! take not the Jews and the Christians for your friends and protectors” (Qur’an, 5:51), “Let not the believers take unbelievers for friends or helpers rather than believers: if any do that, in nothing will there be help from Allah.” (Qur’an: 3:28), “If a people are to become free it needs pride and will-power, defiance, hate, hate, and once again hate...” (Hitler’s speech: April 10, 1923. Munich)

5ኛ. ሁለቱም ማለቂያ የሌለው ውጊያንና ጦርነትን እንዲሁም በጅምላ ወረራ አድርጎ መማረክን አስተምረዋል፤ ራሳቸውም ተግባራዊ አድርገውታል፡፡ "Since our view of life will never share power with another, it cannot co-operate with the existing doctrines it condemns. It is obliged to fight by all available means until the entire world of hostile ideas collapses." (Mein Kampf:677),

"Our Prophet, the Messenger of our Lord, ordered us to fight you till you worship Allah Alone." (Bukhari:4:53:386)

6ኛ. እንደ መሐመድ አስተምህሮ ከሆነ በመጨረሻው ቀን የሰው ዘር ሁሉ ለፍርድ በአላህ ፊት ይቆማል፡፡ አስታርቆ የሚያድናቸው ሰው ይፈልጋሉ፡፡ አዳም፣ ኖኅ፣ አብርሃም፣ ሙሴ፣ ኢሳ ሁሉም አማልደው ሰዎችን ከአላህ የቁጣ ፍርድ ማዳን አይችሉም፡፡ መሐመድ ብቻ ናቸው ለሁሉም የሰው ዘር መሪ ሆነው የመዳን ዋስትና የሚያስገኙላቸው፡፡ "I shall be the leader of mankind on the Day of Resurrection." People would look for someone to intercede for them before Allah. Adam, Noah, Abraham, Moses, and Jesus would all decline, all but Jesus said because of their faults. Jesus would suggest they go to Mohammed, and then Mohammed will call out to God. (Sahih Muslim 1:1:378 & 1:1:381) ሂትለርም እንዲሁ ስለ ራሱ ሲናገር ጀርመንንና ቀሪውን ዓለም የሚያድነው እርሱ ብቻ መሆኑን ተናግሯል፡፡ Hitler addressed to his fellowship, "Workers, you must look upon me as your guarantor." (Hitler's speech: December 10, 1940. Berlin)

7ኛ. ሁለቱም የተሳካ ንግግር ማድረግ (አፈ ቀላጤ መሆን) ለስኬት እንደሚያበቃ ያስተምሩ ነበር፡፡ ሁለቱም ጥሩ ተናጋሪዎች መሆናቸውን በጊዜያቸው በተግባር ለማሳየት ሞክረዋል፡፡ "The emphasis was put on the spoken word because only it is in a position to bring about great changes for general psychological reasons. Enormous world revolutionary events have not been brought about by the written word, but by the spoken word. The agitatory activity of speech is bound to have mass influence." (Mein Kampf:704), "Allah's Apostle said, 'Some eloquent speech is as effective as magic.'" (Bukhari:6:60:662), "The Prophet said, 'I have been given the keys of eloquent speech and given victory with terror so the treasures of the earth were given to me.'" (Bukhari:9:87:127)

8ኛ. ሁለቱም በሌሎች ላይ የእምነት ጥሰት በማድረግ ሰዎች እነርሱ የሚያምኑበትን ብቻ እንዲያምኑ በኃይል ያስገድዱ ነበር፡፡ የእነርሱን እምነትና አስተሳሰብ ያልተከተለውንም ሰው እንዲገደል አዘዋል፡፡ "The greatness of a movement is exclusively guaranteed by the unrestricted development of its inner strength to achieve final victory over all competitors. The justification...for fighting to achieve complete victory...is caused by absolute intolerance." (Mein Kampf:486), "I have been commanded to fight against people till they testify to the fact that there is no god but Allah, and believe in me (that) I am the messenger and in all that I have brought. (Muslim:9:1:31), "Fight the unbelievers around you, and let them find harshness in you." (Qur'an 9.123), "Allah's Apostle said, 'I have been ordered to fight the people till they say, "None has the right to be worshipped but Al-

lah."' (Bukhari:4፡52፡196)

9ኛ. ሁለቱም አይሁዶችን እነርሱ በምድር ላይ እንደቀጧቸው አምላካቸው ደግሞ በሲኦል እንደሚቀጣቸው ያስተምሩ ነበር፡፡ "They are God's chastisement. The Jews have only received a thousandth the reward they deserve for the sins they have committed. They sold themselves to the Devil and landed in his domain. They are monsters who torture the beloved people to the point of despair. The Jew will be punished by Heaven." (Mein Kampf:428), "The Jews are devoid of sense. There is a grievous punishment awaiting them. Satan tells them not to believe so they will end up in Hell." (Qur'an 59፡14)

በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታ መሐመድንና ሂትለርን ተመሳሳይ የሚያደርጓቸው የጋራ የሆኑ በጣም ብዙ ነጥቦችን መጥቀስ ይቻላል፡፡ ሁለቱም ያስተማሯቸውን ትምህርቶችና ያዘዟቸውን አንድ ዓይነትና ተመሳሳይ የሆኑ ትእዛዛት ከመጽሐፎቻቸው ውስጥ በመቶዎች የሚቆጠሩ ብዙ ጥቅሶችን ለቅሞ ማውጣት ይቻላል፡፡ ቦታ ከመቆጠብ አንጻር ግን እስካሁን ያየነው በቂ ነው የሚል ግምት አለኝ፡፡ ስለዚህ ምንም እንኳን አዶልፍ ሂትለር እንደ ጆሴፍ ስሚዝ ‹‹እኔ ለዚህ ተውልድ ሁለተኛው መሐመድ እሆንለታለሁ›› ብሎ በግልጽ ባይናገርም ድርጊቶቹ ግን መሐመድን አርአያ (role model) አድርጎ እንደተነሳ በቂ ምስክር ናቸው፡፡ ሂትለር ምንም እንኳን ‹‹ነቢይ ነኝ›› ባይልም በትክክል የመሐመድን አካሄድና ስታይል ነው የተከተለው፡፡ በአይሁዶች ላይ ያን ያህል አንድ ዓይነትና ተመሳሳይ አቋም መያዛቸው እንዲሁም በቁርአኑና ሐዲሱ ውስጥ ያሉ ሀሳቦች በሂትለር ‹‹ሜይን ካምፍ/Mein Kampf›› መጽሐፍ ውስጥም መንጸባረቃቸው የአጋጣሚ ጉዳይ ነው ሊባል አይችልም፡፡

ደግሞ ከምንም በላይ ማወቅ ያለብን ነገር ሂትለር በትክክል የመሐመድን አካሄድና ስታይል እንደተከተለ ራሱ ሂትለር የተናገረ መሆኑን ነው፡፡ ሂትለር የክርስትናውን ሃይማኖት እንደመጥፎ አጋጣሚ የቆጠረው ሲሆን የመሐመድን ሃይማኖት ግን ከናዚዎች ጋር በተሻለ ሁኔታ ተስማምቶ አንድ ላይ የሚሄድ መሆኑን በግልጽ ተናግሯል፡፡ "You see, it's been our misfortune to have the wrong religion...The Mohammedan religion too would have been more compatible to us than Christianity. Why did it have to be Christianity with its meekness and flabbiness?" (Adolf Hitler, August 28, 1942) እንዲያውም ሂትለር አክሎ ሲናገር አይሁዶች ዓለምን እንዳይቆጣጠሩ ለማድረግ ሲባል ናዚዎች ወደ እስልምናው እምነት ተቀይረው እንደ እነርሱም በመሆን የጀግንነት ሥራ መሥራት እንዳለባቸው ለወታደሮቹ መልእክቱን አስተላልፏል፡፡ ጀርመንም ዓለምን መቆጣጠር የምትችለው በዚህ በእነ መሐመድ ጂሃዳዊ መንገድ መሆኑን አበክሮ ነው ሂትለር ያስገነዘበው፡፡ "The world had already fallen into the hands of the Jews, so gutless a thing Christianity! -then we should in all probability have been converted to Mohammedanism (Islam), that cult which glorifies the heroism and which opens up the seventh Heaven to the bold warrior

alone. Then the Germanic races would have conquered the world." (Adolf Hitler, August 28, 1942)

አንድ ነገር እርግጠኛ ሆኜ ልንገራችሁ፡፡ ሙስሊሞች ሂትለርን ይወዱታል፡፡ ለምን ይመስልዎታል? መልሱ በጣም ቀላል ነው፡፡ ከ6 ሚሊዮን በላይ አይሁዳውያንን በግፍ ስለጨፈጨፈላቸው ነው የሚወዱት፡፡ ነገሩ «የጠላቴ ጠላት ወዳጄ ነው» እንደሚባለው ሆኖ ነው እንጂ ሂትለር በራሱ በእስልምና እንዲወደድ የሚያደርገው ምንም ነገር የለም፡፡ በቃ በዚህች ድርጊቱ ብቻ ለእነርሱ ተወዳጅ ሰው ነው፡፡ እንዲያውም ሲያወድሱትና ሲያንቆለፓፕሱት «ሂትለርን እግዚአብሔር ይባርከው/God Bless Hitler» እያሉ በሰላማዊ ሰልፋቸው ላይ መርቀውታል፡፡







አሁን በዚህ ዘመን ያሉት የአንዳንድ ኢስላማዊ ሀገራት ወታደራዊ መመሪያቸውና ስልጠናቸው የሂትለርን መንገድ የተከተለ ነው፡፡ ከጥንቱም ቢሆን አንዳንድ ኢስላማዊ መሪዎች ከራሱ ከሂትለር ጋር ቀጥተኛና የጠበቀ ግንኙነት ነበራቸው፡፡





በቀኝ በኩል «Arabic Grand Mufti» ማለትም ኢስላማዊ ሕግጋትን የማስረዳት ሕጋዊ መብት ያለው ግለሰብ አሚን አል-ሁሴን ከሂትለር ጋር ሲነጋገር ያሳያል፡፡ በግራ በኩል ያለውም ራሱ አሚን አል-ሁሴን በ2ኛው የዓለም ጦርነት ወቅት ከሂትለር ናዚ ፓርቲ ጋር በርሊን ከተማ በስብሰባ ላይ እንዳለ ያሳያል፡፡



የናዚ ሙስሊም ወታደሮች ኢስላማዊ የስግደት ሥርዓት ሲፈጽሙ (1943 ዓ.ም)











አሁን ባሉ ኢስላማዊ ሀገራት ውስጥ ሂትለራዊ የስልጠና ስታይልን ተከትለው ይሰለጥናሉ (በፎቶው ላይ ሙስሊሞቹ የሚሰለጥኑበት መንገድ ከግራ በኩል ከሚታየው ሂትለር ጋር ተመሳሳይ መሆኑን አስተውሉ)

ወደ ማወዳደሩ እንመለስና እንዲያውም አጠቃላይ ነገሮችን ከስር መሠረቱ አይተን መሐመድንና ሂትለርን በእውነተኛው ማንነታቸው ላይ ተመርኩዘን ካነጻጸርናቸው ሂትለርን በአንዳንድ ነገሮች ከመሐመድ የተሻለ ሰው ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ ቢያንስ መሐመድ በገሀድ የፈጸሟቸውን ወንጀሎችና የሠሯቸውን ኃጢአቶች ሂትለር ሲያደርግ አልታየም፣ አድርጓልም አልተባለም፡፡ እስቲ በሁለቱ መካከል ቀጥሎ ያሉትን የማነጻጸሪያ ነጥቦች ይመልከቷቸው፡፡




Adolph Hitler and Hitler's Mein Kampf    Islamic Allah's Koran and Mohammed

**The things that Hitler and Mohammed had in common are in red.**

| Hitler | | Mohammed | |
|---|---|---|---|
| Married 6-year old girl when 51: | No | Married 6-year old girl when 51: | Yes |
| Raped 9-year old girl when 54: | No | Raped 9-year old girl when 54: | Yes |
| Child Molester and Child Rapist: | No | Child Molester and Child Rapist: | Yes |
| Had Dozens of Sex Slaves: | No | Had Dozens of Sex Slaves: | Yes |
| Number of Wives: | 1 | Number of Wives: | > 10 |
| Hated Jews: | Yes | Hated Jews: | Yes |
| Personally beheaded hundreds of Jews in one day: | No | Personally beheaded hundreds of Jews in one day: | Yes |
| Loved by Muslims: | Yes | Loved by Muslims: | Yes |
| Considered ideal man by Muslims: | No | Considered ideal man by Muslims: | Yes |
| Considered a prophet by Muslims: | No | Considered a prophet by Muslims: | Yes |
| Vegetarian: | Yes | Vegetarian: | No |
| Loved Dogs: | Yes | Loved Dogs: | No, killed dogs. |
| Loved Art: | Yes | Loved Art: | No, killed art. |
| Loved Music: | Yes | Loved Music: | No, killed music. |
| Reign of Terror Lasted: | 12 years | Reign of Terror Lasted: | Over 1,400 years. |
| Current Followers: | Unknown | Current Followers: | 1/5 of world. |
| Stoned Women to Death: | No | Stoned Women to Death: | Yes |
| Had Others Drink His Urine: | No | Had Others Drink His Urine: | Yes |
| Violence Against Wife: | No | Violence Against Wife: | Yes |
| Violence Against Sex Slaves: | N/A | Violence Against Sex Slaves: | Yes |
| Rode to heaven on Buraq: | No | Rode to heaven on Buraq: | Yes |

## በእስልምናውም አላህ ወደፊት የሰውን ሥጋ ለብሶ ይገልጣል

ከዚህ በፊት በገጽ---ላይ ሙስሊሞች ወደፊት አላህን ያለ ጫማ ባዶ እግሩን ሆኖ፣ እርቃኑን በእግሮቹ እየሄደ እንደሚያዩት ሐዲሱ ላይ የተጻፈውን በመግጽ አይተን ነበር፡፡ አሁንም ሰፋ ባለ ምልኩ እናየዋለን፡፡ በሐዲሱ ሳሂህ ሙስሊም 1፡1፡349 ላይ እንደተጻፈው አላህ የራሱ ባለሆነ በተለየ የአካል ቅርጽ ለሰዎች ይገለጽና “እኔኮ ጌታችሁ ነኝ” ይላቸዋል፡፡ *Sahih Muslim* vol.1 book 1 no.349 p.115 "...Allah would then come to them in a form other than His own Form, recognizable to them, and would say: I am your Lord. They would say: We take refuge with Allah from thee...." See also *Bukhari* vol.8 book 76 no.577 p.375; *Bukhari* vol.9 book 93 no.532 p.395-396.

ሙስሊም ወገኖቻችን ስለ ወልደ እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው መሆንና አምላክነቱም ፈጽሞ ስለማይዋጥላቸው በጉዳዩ ላይ ሲቀልዱና ሲያንጓጥጡ ብሎም ከክርስቲያኖቹም ጋር አላስፈላጊ ጉልጭ አላፋ ክርክሮችን ሲያደርጉ ይስተዋላሉ፡፡ ግን ደግሞ ከዚህ የአምላክ ሰው መሆን ጋር በተገናኘ አስቂኝና አስገራሚ ነገር በራሳቸው መጽሐፍ ላይ ተጽፎ መገኘቱን እንኳን አለማወቃቸው በራሱ አሳዛኝ ነገር ነው፡፡ መሐመድ ለተከታዮቻቸው ሲያስተምሯቸው እንዲህ ነው ያሉት፡- "አላህን ያለ ጫማ ባዶ እግሩን ሆኖ፣ ያለ ምንም ልብስ እርቃኑን ሆኖ፣ በእግሮቹ እየሄደና ያልተገረዘ ሆኖ ታገኙታላችሁ" The Prophet said, "You will meet Allah barefooted, naked, walking on feet, and uncircumcised." Sahih Bukhari 8:76:531, See also Sahih Bukhari 8:76:532, Sahih Bukhari 8:76:533. እንዲሁም ይህ አገላለጽ በሐዲሱ ውስጥ ብዙ ቦታ ተጽፎ ይገኛል፡፡ "Narrated Abu Huraira: The Prophet said, 'You will meet Allah barefooted, naked, walking on feet, and uncircumcised.'" (Sahih Bukhari Volume 1, Book 4, Number 238), "I heard Allah's Apostle while he was delivering a sermon on a pulpit, saying, 'You will meet Allah barefooted, naked, and uncircumcised.'" (Sahih Bukhari Volume 8. Book 76. Number 532.)

የሙስሊሞቹ ነቢይ መሐመድ ሲያስተምሩ "አላህን ያለ ጫማ ባዶ እግሩን ሆኖ፣ ያለ ምንም ልብስ እርቃኑን ሆኖ፣ በእግሮቹ እየሄደና ያልተገረዘ ሆኖ ታገኙታላችሁ" ያሉት ነገር ምን ማለት ነው? በምስጢር ደረጃ ካየነው የቃሉ ትርጉም ምንድነው? አላህ የራሱን ማንነት ደብቆ በሌላ አካል ተመስሎ ለሰዎች ራሱን መገለጽ ከቻለና በአንድ በኩል ደግሞ ሙስሊሞቹ የእነርሱ አምላክ ፍጹም እርቃኑን ሆኖ ኃፍረተ ሥጋውን እንኳን ሳይሸፍን ያን ያህል ተጋላጭ ሆኖ ለዚያውም አለመገረዙን እንኳን እስኪያሳያቸው ድረስ የሚገለጽላቸው ከሆነ ምነው ታዲያ አየሱስ ክርስቶስ የሰውን ሥጋ ፍጹም ተዋሕዶ መገለጡ አልዋጥላቸው አለ? "አምላክ ሰው ሆነ" ብሎ ከማመንና "አምላክ እርቃኑን ሆኖ ሳይገረዝ ከነሀፍረተ ሥጋው በገሃድ ይታያል" ብሎ ከማመን የትኛው ነው ለኅሊና የሚከብደው? በባዶ እግር መሄድ፣ እርቃን ሆኖ መታየትና አለመገረዝ... እነዚህና የመሳሰሉት አነጋገሮች ፍጹም የሥጋ ባሕሪያቶች ናቸውና ለመለኮት አይስማሙትም፡፡ መለኮት በባሕርይው እነዚህ ነገሮች ፈጽሞ የሉበትም፡፡ እንግዲህ ስለ ራሳቸው አምላክ ይህ ሁሉ በግልጽ ተጽፎ እያለ ነው ሙስሊሞች "ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ ነው" ወይም ደግሞ "ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው የሆነ አምላክ ነው" የሚለውን የክርስቲያኖች መሠረታዊ ትምህርት በፅኑ የሚቃወሙት፡፡ ግን የራሳቸውን እምነት እስልምናውን በትክክል ቢያውቁት ኖሮ ይህንን እውነተኛ ሕይወት የሚገኝበትን መሠረታዊ ትምህርት ባልተቃወሙ ነበር፡፡ ምክንያቱም ዓለም ሁሉ

የዳነው በአምላክ ሰው መሆን ስለሆነ ነው፡፡ አንድም የእነርሱም አምላክ “አላህ” ፈጽም የሰው ባሕርያቶችን ገንዘብ ያደረገ መሆኑን ቁርአኑና ሐዲሱ በግልጽ የሚናገሩ መሆኑን ቢያውቁ ኖሮ መሠረታዊውን የክርስትናውን ትምህርት ባልተቃወሙ ነበር፡፡ አላህ የሰው ባሕርያቶችን ይዞ እንደሚገለጥ እስካሁን ባየናቸው የሐዲስ ጥቅሶች ላይ በዝርዝር አይተናል፡፡ አሁንም ቢሆን በቁርአኑ ላይ ለአላህ ፍጹም ሰዋዊ ባሕርያት የተሰጡት መሆኑን ቀጥለን እናያለን፡-

## ለአላህ የተሰጡ ሰዋዊ ባሕርያት

ሙስሊሞች ለአምላክ ሰዋዊ ባሕርይ መስጠት የአምላካቱን ክብር እንደመቀነስ ወይም እንደመሳደብ አድርገው ስለሚቆጥሩት ለአምላክ አካላዊ ገለጣ መስጠት ተገቢ አይደለም ብለው ክርስቲያኖችን በፅኑ ይቃወማሉ፡፡ ነገር ግን እስካሁንም እንዳየነው በራሳቸውም ቁርአንና ሐዲስ ላይ ለአላህ ሰዋዊ ባሕርያትን ተሰጥተውታል፡፡ በቁርአኑ ውስጥ ብቻ ከ30 በላይ ጥቅሶች ለአላህ ሰዋዊ ባሕርይ መገለጫ ሆነው ተነግረዋል፡፡ እንደ ቁርአኑ አገላለጽ አላህ ስምንት መላእክት ተሸክመውት በዙፋኑ ላይ ተቀምጧል፤ በፊቱ የቆሙ ሰዎችን መቁጠርን፣ መፍረድን፣ መፈተንንና የመሳሰሉትን ነገሮች ለማከናወን የስሜት ሕዋሳቶቹን ይጠቀማል፤ እጆቹ የተዘረጉ ናቸው፤ እስትንፋሱን እፍ ብሎ መንፈሱን በሰዎች ላይ ያሳድራል፤ በፀሐይና በጨረቃ መሀላን ይምላል፤ በፍርድ ቀን ሰዎችን በግራውና በቀኙ ያቆማል፤ ሙስሊሞቹ በፍርድ ቀን የእግሮቹን ባቶች ተገልጠው እየዩ ነው የሚሰግዱለት፤ በተጨማሪም አላህ ፊቱ በሀዘን ይጠቁራል፤ ሙስሊም ያልሆኑትን እስከሚፀየፍ ወይም እስከሚጠላ ድረስ ስሜት እንዳለው ተደርጎ በቁርአኑ ተገልጧል፡፡ ጥቅሶቹን እንያቸው፡-

«አንዳቸውም ለአል-ረሕማን ምሳሌ ባደረገው ነገር በሴት ልጅ በተበሰረ ጊዜ እርሱ በቁጭት የተመላ ሆኖ ፊቱ የጠቆረ ይሆናል» (43፡17)፤ «እርሱ የተቆጨ ሆኖ ፊቱ ጠቁሮ ይውላል» 16፡58፡፡

የአላህን ዐርሽ (ዙፋን)በትንሣኤ ቀን እርሱ በዙፋኑ ላይ ተቀምጦ ስምንት መላእክት ከበላያቸው ይሸከሚሉ፡፡ 69፡17

የአላህን ዙፋን የተሸከሙ መላእክት ያለማቋረጥ ዙሪያውን ከበውና ዙሪያውን እየዞሩ ይቅርታ የሚገባቸው ሙስሊሞች ይቅር እንዲባሉ ልመናን ያቀርባሉ፡፡ 40፡7

እያንዳንዱ በምድር ላይ ሕይወት ያለው ፍጡር ሁሉ ጠፊ ነው ነገር ግን የአላህ ፊቱ ለዘላለሙ አይጠፋም፡፡ 55፡27

አላህ ከፈራጆች ሁሉ የበለጠ ፈራጅ ነው፡፡ 95፡8፣ 10፡109

አላህ መሐላን ይምላል፡፡ በፀሐይና በጨረቃ ይምላል፣ በቀንና በሌሊት ይምላል፡፡ 91፡1፡፡ አላህ በጨለማና በቀኑ፣ በጎዶሎና በሙሉ ምሽት ሁሉ ይምላል፡፡ 92፡2፡፡
አላህ እስልምናን የማይቀበሉትን ሁሉ ይጠላል 40፡10፣ 30፡45
በመጨረሻው ፍርድ ሰዓት ሙስሊሞች በአላህ ቀኝ እጁ በኩል ይቆማሉ እነዚያ የቁርዓንን ትምህርት የካዱት ደግሞ በግራ እጁ በኩል ይቆማሉ፡፡ 90፡17
አላህ በትንሣኤ ቀን ብቻቸውን በፊቱ እንዲቆሙ ሰዎችን ሁሉ በጥንቃቄ ይቆጥራል፡፡ 19፡94
አላህ ከአማኞቹ መካከል ማን እንደሚፀና ለማወቅ ፈተና ይፈትናቸዋል፡፡ 47፡31
አላህ በምድር ላይም የተገለጠበት ወቅት ነበር፡፡ ሙሴ ከሚቃጠለው ቁጥቋጦ ውስጥ የሰማው ድምፅ "...ሙሴ! እኔ የዓለማት ጌታ አላህ ነኝ" የሚል ነው፡፡ 28፡30፣ አላህ በእሳቱ ውስጥና በዙሪያው ሁሉ ነበረ፡፡ 27፡8
አላህ እያንዳንዱን የተሠራውን ነገር ሁሉ ለማወቅ የእያንዳንዱን ነፍስ አጠገቡ ቆሞ ይጠብቃል፡፡ 13፡33፡፡ ሦስት ሰዎች በምስጢር ቢነጋገሩ አራተኛው አላህ ነው፡፡ አራት ሆነው ቢነጋገሩ አምስተኛው አላህ ነው፡፡ አምስት ሆነው ቢነጋገሩ ስድስተኛው አላህ ነው፡፡ 58፡7
በመጨረሻው ቀን የአላህ ባቶች ተገልጠው እየታዩ ነው አማኞቹ የሚሰግዱለት፡፡ 68፡42
አላህ ሁሉን ነገር ይሰማል፣ ያያል፣ ይመለከታልም፡፡ 4፡134፡፡ አላህ ባሏን በፈታቸው ሴትና በመሐመድ መካከል የተደረገውን ውይይት ሰምቷል፣ ተመልክቷል፡፡ 58፡1
የአላህ እጆቹ የተዘረጉ ናቸው፡፡ 5፡64፡፡ ሙስሊሞች እጆቻቸውን በአንድ ላይ አድርገው ቃል በሚገቡበት ጊዜ የአላህም እጅ ከእነርሱ እጆች በላይ ነው፡፡ 48፡10
አላህ በባሕር ላይ የሚሄድን ሰው ዐይኖቹ አይተዋል፡፡ 20፡39
አላህ እስትንፋስ አለው፣ መንፈሱንም እፍ ብሎ በሰዎች ላይ ያሳድራል፡፡ 38፡72
አላህ ፍጥረቱን በሁለት እጆቹ ነው የፈጠረው፡፡ 38፡75

በመጨረሻው ቀን ፍጥረት ሁሉ ሲያልፍ አላፊ ሆኖ የማይቀረው "የአላህ ፊት" ብቻ ነው፡፡ «በምድር ላይ ያለው ሁሉ ጠፊ ነው፡፡ የልቅናና የልግስና ባለቤት የሆነው የጌታህ ፊትም ይቀራል፤ አይጠፋም» ይላል ቁርአኑ፡፡ አል-ረሕማን 55፡27፡፡
እነዚህ ከላይ ያየናቸው ጥቅሶች የሚያስረዱን ነገር ቢኖር አላህ ራሱን በሰዋዊ ባሕርያት እንደገለጠ ነው፡፡ ነገር ግን ብዙ ሙስሊሞች እንዲህ ዓይነት ነገር በቁርአናቸው ውስጥ መኖሩን አያውቁትም፡፡ ትልቁ ችግር ብዙ ሙስሊሞች ለመስገድ እንዲያስችላቸው ብቻ የተወሰኑ ዐረብኛ ቃላትን በቃላቸው ሸምድደው ከመያዝ ውጭ በቁርአናቸውና

በሐዲሳቸው ላይ በትክክል ምን እንደተጻፈ አለማወቃቸው ነው፡፡ እውነት ነው በቁርአናቸውና በሐዲሳቸው ላይ በትክክል ምን እንደተጻፈ አውቀውት ቢሆን ኖሮ ክርስትናውን ከመተቸትና ከመንቀፍ ይልቅ ወደ እውነተኛው ሕይወት በሚወስደው መንገድ በተጓዙ ነበር፡፡ በጣም አሳዛኙ ነገር በእስልምና ሃይማኖት ውስጥ ከእምነትና ከመንፈሳዊነት እይታ አንጻር ሊነገሩ የማይገባቸው አንዳንድ አፀያፊና ዘግናኝ ሀሳቦች ሲሰሙ እንኳን "ይህ ለምን ሆነ?" ብሎ ራሳቸውን ከመመርመር ይልቅ ለነገሩ አስቂኝና አሳዛኝ ምክንያቶችን መደርደሩ ይቀላቸዋል፡፡ ይህ ዓይነቱ አካሄድ እውነቱን ለማወቅ ካለመፈለግ የመነጨ ብቻ ሳይሆን ስለክርስትናው ካላቸው ፍጹምና ጭፍን ጥላቻ በመነሳት ነው፡፡ ሁሉን መርምሮ እውነትን ለማወቅ ከመጣር ይልቅ የማይመስሉና የማይጠቅሙ ምክንያቶችን በመደርደርና ትክክል ባልሆነ መንገድ የሌላውን ሃይማኖት በመተቸት ብቻ የራስን ሃይማኖት ለመጠበቅ መሞከሩ በራሱ አንድ ትልቅ ውድቀት ነው፡፡ ነገሩ የራሷ ሲያርባት የሰው እንደምታማስለው ሴት ሆኖ ነው እንጂ እውነታውን የዘመኑ ሙስሊም ምሁራኖቻቸውስ መቼ አጡትና! እነርሱ «ይህ ነገር እውነት ነው እንዴ?» ብለው ነገሮችን ከማመዛዘን ይልቅ ምንም ይሁን ምን በእምነታቸው ጉዳይ ላይ ለሚነሳው ማንኛውም ጉዳይ አሳዛኝና አስቂኝ የሆኑ ትንታኔዎችን ለመስጠት ነው የሚሞክሩት፡፡ "የሰውን አንገት በሰይፍ ቀንጥሰህ ጣልና ጀነት ግባ" ለሚለው መሐመዳዊ የጂሃድ ትእዛዝ ምክንያት ለመስጠት ይሞክራሉ፤ "በጀነት 72 ደናግላን ሴቶች ለሙስሊም ወንድ ለዝሙት ተግባር በሽልማት መልክ ይሰጡታል" ለሚለው መመሪያቸው ምክንያት ለመስጠት ይሞክራሉ፡፡ ሌላው ቢቀር "የግመልን ሽንትና የሞቶችን ዝንብ ለመድኃኒትነት መጠቀም ይቻላል" ብለው መሐመድ ለተከታዮቻቸው ላስተማሩት ትምህርትም ምክንያት ለመስጠት ይሞክራሉ፡፡ በእርግጥ እውነቱ የቱ ጋር እንዳለ ለይተው ካወቁ በኋላ "እስልምና ማለት ይህ ከሆነማ..." እያሉ ወደ እውነተኛው ክርስትና በመምጣት የእውነትን መንገድ የተከተሉ እኔም በአካልም ጭምር የማገኛቸው ሙስሊሞች በርካታ ናቸው፡፡ ብዙዎቹ ግን እንደነዚህ አይደሉም፡፡ ጭፍን በሆነ አስተሳሰብ የማይረባና አሳዛኝ ምክንያቶችን ነው የሚደረድሩት፡፡ መሐመድ ራሳቸው ኃጢአት መሥራታቸውን በግልጽ በቁርአኑ ላይ ተናግረው እያለ የዘመኑ ሙስሊም ምሁራኖች ግን ይህንንም ሊያስተባብሉ ይሞክራሉ፡፡ ነቢያቸውም ለሠራቸው ከባድ ኃጢአቶች እነርሱ ምክንያት ሊሰጡላቸው ይሞክራሉ፡፡

ስለዚህ እነዚህን ከላይ ያየናቸውን ከ20 በላይ የሚሆኑ የአላህን ሰዋዊ ባሕርያትንም «ምሳሌዎች ናቸው» በሚል ምክንያት ደብቀው ሊያልፉት ይሞክራሉ፡፡ ግን ቁርአኑ ውስጥ የተነገሩት በምሳሌነት አይደለም፡፡ እስትንፋስን እፍ ማለት ምሳሌ አይደለም፤

በሁለት እጆች መፍጠር ምሳሌ አይደለም፤ ሌሎቹን በእስልምና የማያምኑትን ሰዎች መጥላት፣ በዙፋን ተቀምጦ መፍረድ፣ እጅን መዘርጋት፣ ፊትን ማጥቆር… እነዚህ ሁሉ ምሳሌ ሊሆኑ አይችሉም፡፡ ለሙሴ ከሚቃጠለው ቁጥቋጦ ውስጥ ሆኖ “ሙሴ! እኔ የዓለማት ጌታ አላህ ነኝ” የሚል ድምጽ ማሰማት በፍጹም ምሳሌ ሊሆን አይችልም፡፡ ይልቁንም መገለጥን ነው በገሃድ የሚያሳየው፡፡ ከዚህም ሌላ ቁርአኑ አላህ ከሰዎች ጋር ቃል በቃል እንደተነጋገረ በግልጽ ከትቦ አስቀምጦልናል፡፡ ይህንንም ቀጥሎ እናየዋለን፡፡ በቁርአኑ ላይ በግልጽ ተጽፎ እንደምናገኘው አላህ ከሰዎች ጋር በቀጥታ ቃል በቃል ተነጋግሯል፡፡ ይህም፡-

1ኛ.ከአዳም ጋር፡- «ከእርሷም ሰይጣን አንዳለጣቸው፤ በውስጡም ከነበሩበት ድሎት አወጣቸው፡፡ ከፊላችሁም ለከፊሉ ጠላት ሲሆን ውረዱ፤ ለእናንተም በምድር ላይ እስከ ጊዜ ሞታችሁ ድረስ መርጊያና መጣቀሚያ አላችሁ አልናቸው» (አል-በቀራህ 2፡36) በማለት አላህ አዳምን ቃል በቃል ካናገረው በኋላ ወደ ምድር እንዳወረደው ተጽፏል፡፡ በፍርድ ቀንም አላህ ሰዎችን እንዲህ ይላቸዋል፡፡ «ወራዶች ሆናችሁ በውስጧ/በሲዖል እርጉ፣ አታናግሩኝም ይላቸዋል» 23፡108፡፡

2ኛ.ከሙሴ ጋር፡- «አላህም ሙሳን ማነጋገርን አነጋገረው» አል-ኒሳእ 4፡164፡፡ እንደ ቁርአኑ አገላለጽ ሙሴ ከሚቃጠለው ቁጥቋጦ ውስጥ የአላህን ድምጽ ሰምቷል፡፡ «ሙሴ ሆይ! እኔ የዓለማት ጌታ አላህ ነኝ በማለት ተጣራ» ይላል ቁርአኑ፡፡ 28፡30፡፡

3ኛ.ከአንድ ተጠራጣሪ ሰው ጋር፡- «አላህም ገደለው፤ መቶ ዓመትን አቆየውም፤ ከዚያም አነሳው፡፡ ምን ያህል ቆየህ? አለው፡፡ አንድ ቀን ወይም የቀንን ከፊል ቆየሁ አለ፡፡ ለእርሱም በማየት በተገለጠለት ጊዜ አላህ በነገሩ ሁሉ ላይ ቻይ መሆኑን አውቃለሁ አለ፡፡» አል-በቀራህ 2፡259፡፡

4ኛ.ከመሐመድ ጋር፡- «ነቢያችሁ መሐመድ አልተሳሳተም፤ አልጠመመምም፡፡ ከልብ ወለድም አይናገርም፡፡ እርሱ ንግግሩ የሚወረድ ራእይ እንጂ ሌላ አይደለም፡፡ ኃይሎቹ ብርቱው አስተማረው፡፡ የእውቀት ባለቤት የሆነው አስተማረው፤ በተፈጥሮው ቅርጹ ሆኖ በአየር ላይ ተደላደለም፡፡ እርሱ በላይኛው አድማስ ሆኖ ከዚያም ቀረበ፣ ወረደም፡፡ የሁለት ደጋኖች ጫፍ ያህል ወይም ከዚህ ይበልጥ የቀረበ ሆነም፡፡ ወደ ባሪያውም ያወረደውን አወረደ፡፡ ነቢዩም በዐይኑ ያየውን ልቡ አልዋሸም፡፡ ታዲያ በሚያየው ላይ ትከራከሩታላችሁን? በሌላይቱም መውረድ ጊዜ በእርግጥ አይቶታል፡፡ በመጨረሻይቱ ቁርቁራ አጠገብ፤ እርሷ ዘንድ መኖሪያይቱ ጀነት ያለች ስትሆን፤ ቁርቁራይቱን የሚሸፍን ነገር በሚሸፍናት ጊዜ አየው፡፡» አል-ነጅም 53፡11-16፡፡

በዚህ በ4ኛው ጥቅስ ጉዳይ ላይ ራሳቸው ሙስሊም መምህራኖቹ በሁለት ጎራ

ተከፍለው ይከራከሩበታል፡፡ አንደኛው ወገን «መልአክ ነው እንጂ አላህ አይደለም» ብሎ ሲከራከር ሌላኛው ወገን ደግሞ «አይደለም ስለ ራሱ ስለ አላህ ነው የተነገረው» ይላሉ፡፡ የእኔን ሀሳብ ለመስጠት የምፈልገው እንደሚከተለው ነው፡-

ከዚህ በፊት ስናይ እንደነበረው ነቢያቸው መሐመድ አንድም ቦታ መልአኩ ጂብሪል በእንደዚህ ዓይነት መንገድ ተገለጠልኝ አላሉም፡፡ ምንም እንኳን የተገለጠላቸው እውነተኛ መልአክ ባይሆንም ማለት ነው፡፡ እንዲያውም ራሳቸው መሐመድ ጂብሪል በሂራ ተራራ ተገለጠልኝ ያሉት መሬት ላይ ጥሏቸው ልባቸውን እረግጦት አረፋ እስኪደፍቃቸው ድረስ እያስጨነቃቸው ነበር፡፡ ራሳቸውንም ለማጥፋት እስኪያስቡ ድረስ ሁኔታው ለእርሳቸው እጅግ አስጨናቂ ነበር፡፡ ዝርዝሩን በገጽ---ላይ ይመልከቱ፡፡ እንዲሁም በሌላ ቦታ ነቢያቸው መሐመድ ሲናገሩ እርሳቸው በጂሃድ በተሳተፉበት ጦርነት ሁሉ ጂብሪልም ጸጉሩ በአቧራ እስኪሸፈን ድረስ አብሯቸው ይዋጋ ነበር፡፡ መሐመድ መልአክ እነዚህንና እነዚህን በመሰሉ መንገዶች ነው ተገለጠልኝ ያሉት፡፡ ከዚህ አንጻር ከላይ በቁጥር 4 ላይ የተነገረው ለመልአክ ነው ለማለት አያስደፍርም፡፡ ደግሞ የተገለጠው አላህም ይሁን መልአክ ይህ አሁን እኔ የፈለኩት ጉዳይ አይደለም፡፡ ምክንያቱም ርዕሳችን «መገለጥ» እስከሆነ ድረስ ማንም ይገለጥ ማን ብቻ በእስልምናው ሃይማኖት መሐመድ እንዲህ ዓይነት መገለጥን አይቻለሁ ብለው ነግረውናል፡፡

ከምንም በላይ ማወቅ ያለብን ነገር መሐመድ አላህን በሦስት ዓይነት መንገድ ተገልጦልኛል ማለታቸውን ነው፡፡ ይህም በራእይ፣ በበግርዶ ጀርባ ሆኖ እና መልአክን በመላክ እንደሆነ ተናግረዋል፡፡ *«ለሰውም አላህ በራእይ ወይም በግርዶ ወዲያ ወይም መልእክተኛን (መልአክን) የሚልክና በፈቃዱ የሚሻውን ነገር የሚያወርድለት ነው፡፡»* ተብሎ ነው የተጻፈው፡፡ ሱረቱ አል-ሹራ 42፡51፡፡ «በግርዶ ወዲያ» ሆኖ የምትለዋ ቃል ምን ዓይነት ምልእክት እንዳላትና እንዴት ሆና በተግባር እንደምትገለጽ ማሰብ መቻል አለብን፡፡

ከላይ እንዳየነው የተገለጠው ማንም ይሁን ማን ቁርአኑ ስለ መገለጥ ግልጽ በሆነ አነጋገር ነው ያስቀመጠው፡፡ «በተፈጥሮው ቅርጹ ሆኖ… በመጨረሻይቱ ቁርቁራ አጠገብ አየው» በማለት ለመሐመድ የታየውን መገለጥ በግልጽ አስቀምጦታል፡፡ አላህ ሙሴን ከሚቃጠለው ቁጥቋጦ ውስጥ ሆኖ አነጋግሮታል፡፡ ይህም ግልጽ የሆነ «መገለጥ» ነው፡፡ ስለዚህ በእስልምናውም «መገለጥ» አዲስ የሆነ ክስተት አይደለም ማለት ነው፡፡ እንግዲህ በእስልምናው የአላህ መገለጥ በቁርአኑ ውስጥ በዚህ መልኩ ከተነገረ የአሁኖቹ ዘመናዊ ሙስሊሞች ለምን ሀቁን መካድ አስፈለጋቸው? ሌሎች እጅግ ብዙ የሆኑ ነገሮችን እንተዋቸውና ቢያንስ ቁርአኑ ውስጥ የተጠቀሰውን ነገር ማመን

ለምን አቃታቸው? አላህ እንዲህ ከላይ ባየነው መልኩ ራሱን ለሰዎች መግለጡን ቁርአኑ በግልጽ አውጆ ሳለ እነርሱ ለምን የክርስቲያኖችን አምላክ መገለጥ ይቃወማሉ? በመሠረቱ መሐመድም ሆኑ ቁርአኑ ወይም አሁንም በዚህ ዘመን እንኳን ያሉት ሙስሊም መምህራኖቻቸው የአምላክን ልጅነት በተመለከተ ወይም «ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ ነው» መባልን በተመለከተ እጅግ አሳዛኝና አስቂኝ በሆነ መልኩ ነው የሚረዱትና የሚተረጉሙት፡፡ «እግዚአብሔር ልጅ» አለው ሲባል በሰው ሰውኛ ግብር እግዚአብሔር ሚስት አግብቶ ከእርሷም ጋር ግብረ ሥጋ ግንኙነት አድርጎ የወለደው ነው የሚመስላቸው፡፡ ለማሳያ ያህል ከቁርአኑ የተወሰኑ ጥቅሶችን እንመልከት፡-

"ለአላህ ሚስት የሌለችው ሲሆን እንዴት ለእርሱ ልጅ ይኖረዋል" ሱረቱ አል-አንዓም 6፡101

"እነሆ የጌታችን ክብር ላቀ፤ ሚስትንም ልጅንም አልያዘም" ሱረቱ አል-ጂን 71፡3

"ለአላህ ልጅን መያዝ አይገባውም፤ ከጉድለት ሁሉ ሁሉ ጠራ" ሱረቱ መርየም 19፡35

"አላህ አንድ አምላክ ብቻ ነው፡፡ ለእርሱ ልጅ ያለው ከመሆን የጠራ ነው" ሱረቱ አል-ኒሳእ 4፡171

በጣም የሚያሳዝነው ነገር አሁን በዚህ ዘመን ያሉ ሙስሊሞችም ቢሆኑ "ክርስቲያኖች ምን ብለው ነው የሚያመኑት?" የሚለውን እንኳ ግንዛቤ ውስጥ አለማስገባታቸው ነው፡፡ ይህንን በተመለከተ አንድ ምሳሌ ልጨምር፡- እኛ ክርስቲያኖች «ቅድስት ድንግል ማርያም እግዚአብሔር ወልድን ስለወለደች ከአምላክ እንደተሰጣት ክብር መጠን እናከብራታለን፣ እንወዳታለን፣ ፍጹም አማላጃችን ናትና በምልጃዋ ፍጹም ድኅነት እናገኝባታለን» ብለን እናምናለን እንጂ እርሷ አምላካችን ናት ብለን በፍጹም አናምንም፡፡ ይልቁንም «ወላዲተ አምላክ/አምላክን የወለደች» በማለት ነው ክብሯን የምንገልጸው፡፡ ቁርአኑ ግን ከሥላሴ አንዷ እንደሆነች አድርጎ ነው የሚናገረው፡፡ *"አላህም፡- የመርየም ልጅ ኢሳ ሆይ! አንተ ለሰዎቹ እኔንና እናቴን ከአላህ ሌላ ሁለት አምላኮች አድርጋችሁ ያዙ ብለሃልን? በሚለው ጊዜ አስታውስ፤ ጥራት ይግባህ፤ ለእኔ ተገቢዬ ያልሆነን ነገር ለእኔ አይገባኝም"* ተብሎ ነው የተጻፈው፡፡ ሱረቱ አል-ማኢዳህ 5፡116፡፡ በዚህ የቁርአን ጥቅስ መሠረት ክርስቲያኖች ሥላሴ ብለው የሚያምኑት አብን፣ ድንግል ማርያምንና ኢየሱስን ነው፡፡

እንዲሁም ቁርአኑ ስለ ሥላሴ የሚናገረው "የሦስት ሦስተኛ ክፍልፋይ" እንደሆኑ አድርጎ ነው፡፡ ይህ ማለት ደግሞ ዘጠኝ አካል አላቸው እያለን ነው፡፡ ቁርአኑ እንዲህ ነው የሚለው፡- *"እነዚያ አላህ የሦስት ሦስተኛ ነው ያሉ በእርግጥ ካዱ፤ ከአምላክም አንድ አምላክ እንጂ ሌላ የለም"* ሱረቱ አል-ማኢዳህ 5፡73፡፡ እውነተኞቹ ክርስቲያኖች

ደግሞ በፍጹም እንደዛ ብለው አያምኑም፡፡ ቁርአኑ ክርስቲያኖች እንዲህ ብለው ያምናሉ እያለ የተናገራቸው ነገሮች ሁሉ በእውነተኛው ክርስትና ውስጥ ፍጹም የሌሉ ነገሮች ናቸው፡፡

ክርስቲያኖች አምላካችን በስም (አብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ)፣ በአካል፣ በግብር ሦስት ሲሆን በሥልጣን፣ በአገዛዝ፣ በአኗኗር፣ ዓለምን በመፍጠርና በማሳለፍ... አንድ አምላክ ነው» ብለው ያምናሉ እንጂ ቁርአኑ እንደሚለው ከሦስቱ አካል አንዷ ማርያም አይደለችም፡፡ ወይም ክርስቲያኖች ሥላሴን "የሦስት ሦስተኛ ክፍልፋይ" ናቸው ብለው በፍጹም አያምኑም፡፡ እንኳን አማኞቹ ክርስቲያኖች ቀርቶ ሰይጣንም ይህን አይልም በእውነት፡፡ ስለዚህ መሐመድና አሁንም ያሉት ተከታዮቻቸው ቢያንስ "ክርስቲያኖቹ ምን ብለው ነው የሚያምኑት?" የሚለውን ነገር እንኳ በቅጡ ለይተው አለማወቃቸው በእጅጉ ትዝብት ውስጥ እንዲወድቁ አድርጓቸዋል፡፡ አንድን ነገርኮ ለመቃወም ቢያንስ ስለዚያ ነገር በበቂ ሁኔታ ማወቅ ያስፈልጋል፡፡

ወደመነሻው ሀሳብ እንመለስና ሙስሊሞች የራሳቸው አምላክ እስካሁን ባየነው መልኩ በሰው ተመስሎ እንደሚገለጥ ተነግሮ ሳለ እንዲሁ በጭፍን አስተሳሰብ ብቻ "እግዚአብሔር እንዴት ልጅ ይኖረዋል?" በማለት ልጅነቱም በግብረ ሥጋ ግንኙነት እንደተገኘ አድርገው ማሰባቸው በራሱ አስገራሚ ነው በእውነት፡፡ ሌላ አንድ አስገራሚ ጥቅስ ከቁርአኑ ላውጣላችሁ፡፡ ሱረቱ አል-ዙመር 39፡4 ላይ እንዲህ ተብሎ ነው የተጻፈው፡- "አላህ ልጅን መያዝ በፈለገ ኖሮ ከሚፈጥረው ውስጥ የሚሻውን ይመርጥ ነበር፤ ጥራት ተገባው" ይላል፡፡ እስቲ ጥቅሱን በደንብ እንመልከተው!!! ስላልፈለገ ነው እንጂ ፍለጎቱ ቢኖረው ኖሮ አላህ ልጅ ይኖረው ነበር ነው ቁርአኑ እያለን ያለው፡፡ ነገሩ የፍላጎት ጉዳይ ብቻ ነው፡፡ አላህ ስላልፈለገ ብቻ ነው ልጅ የሌለው እንጂ እንዲኖረው ቢፈልግ ኖሮ ልጅ ይኖረው ነበር፡፡

<u>ለመሆኑ በትክክለኛው የክርስትና ትምህርት መሠረት «የአምላክ መገለጥ» ሲባል እንዴት ነው?</u>፡- በእውነተኛው የክርስትና ትምህርት መሠረት የአምላክ መገለጥ ሲባል ምን ማለት ነው? አምላክ ለምን መገለጥ አስፈለገው? መቼና እንዴት ነው የሚገለጠው? የተገለጠውና የሚገለጠውስ ለእነማን ነው? መገለጡስ የግድ አስፈላጊ ነውን? ሙስሊም እኅቶቻችንና ወንድሞቻችን እነዚህንና መሰል ጥያቄዎችን ይዘው ቀጣዩን ጽሑፍ በደንብ ቢያነቡት ስለ እውነተኛው አምላክና ስለመገለጡ ትክክለኛ ግንዛቤ ይኖራቸዋል፡፡ መዳን የሚገኝበትንም እውነተኛ የሕይወት ትምህርት ያገኛሉ፡፡

## ‹‹የመገለጥ ሃይማኖት››